# አዲሱ የምሳሌያዊ አነጋገሮች መጽሐፍ

## ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ከሚስጥራዊ ፍቺዎቻቸው ጋር የቀረበ ልዩ ዝግጅት

- በልዩ አቀራረብ የተዘጋጀ የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች መጽሐፍ
- ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ከሚስጥራዊ ፍቺዎቻቸው ጋር በፊደል ተራ ቅደም ተከተል የቀረበበት
- ለተማሪዎችና ለመምህራን እንዲያመች በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ ጥያቄዎች ከነመልሶቻቸው የተካተቱበት
- በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ በተለይ ከአንድ በላይ ፍቺ ላላቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ልዩ ትኩረት የተሰጠበት ዝግጅት
- የራሱ የሆነ ልዩ የሙዳየ ቃላት መፍቻን ያካተተ መጽሐፍ

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ እንግዳ

Zion
Books

# አዲሱ የምሳሌያዊ አነጋገሮች

## መጽሐፍ

ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና
ከምሥጢራዊው ፍቺዎቻቸው ጋር

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ

Publisher
Aster Nega Publishing Enterprise

የመጀመሪያ እትም 1999 ዓ.ም

ሁለተኛ እትም 2000 ዓ.ም

ሦስተኛ እትም 2002 ዓ.ም

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ

© Publisher
Aster Publishing Enterprise

## ምሥጋና

በጽሕፈት ሥራ ሳይሰለች ሌት ተቀን በመሥራት ለረዳኝ ለልጄ ለአሰናቀ ደበበ ምሥጋናዬ ይድረሰው፡፡

በመጨረሻም ይህን መጽሐፍ በዚህ መልኩ ለማዘጋጀት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለረዱኝ ጸሐፍትና ደራሲያን የላቀ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አዘጋጅ- ደበበ ኃይለጊዮርጊስ እንግዳ

## ማውጫ

1. ምሥጋና ........................................................... I
2. መግቢያ ........................................................... II
3. የምሳሌያዊ አነጋገር አገልግሎትና መልዕክት........ 1
4. ሀ-ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 12
5. ለ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 17
6. ሐ-ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 38
7. መልመጃ 1 ........................................................... 41
8. መ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 47
9. ሠ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 69
10. መልመጃ 2........................................................... 72
11. ረ-ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 78
12. ሰ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች............................ 80
13. መልመጃ 3........................................................... 104
14. ሸ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 111
15. ቀ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋግሮች............................ 114
16. መልመጃ 4 ........................................................... 122
17. በ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 128
18. መልመጃ 5 ........................................................... 156
19. ተ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 163
20. ቸ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 173
21. ኀ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች............................ 174
22. መልመጃ 6 ........................................................... 174
23. ነ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች............................ 178
24. መልመጃ 7 ........................................................... 188
25. አ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 190
26. መልመጃ 8 ........................................................... 218
27. እ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 225
28. መልመጃ 9 ........................................................... 243
29. ከ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 249
30. መልመጃ 10 ........................................................... 277
31. ወ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 283
32. ዐ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 295
33. መልመጃ 11 ........................................................... 302
34. ዘ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ............................ 308
35. መልመጃ 12 ........................................................... 313

36. የ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 317
37. መልመጃ 13 .......................... 383
38. ደ-ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 389
39. መልመጃ 14 .......................... 399
40. ጀ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 405
41. ገ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 407
42. መልመጃ 15 .......................... 419
43. ጠ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 426
44. ጨ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 433
45. ጰ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 435
46. መልመጃ 16 .......................... 436
47. ፀ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 441
48. ጸ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 441
49. ፈ- ቤት ምሳሌያዊ አነጋገሮች .......................... 442
50. መልመጃ 17 .......................... 447
51. አንድና ከአንድ በላይ አቻ ምሳሌያዊ አነጋገር ያላቸው 453
52. የቃላት መፍቻ .......................... 463
53. የመልመጃዎች መልሶች .......................... 470



## መግቢያ

ምሳሌያዊ አነጋገር የሥነ-ቃል አንዱ ክፍል ነው:: በዚህም ማኅበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር በሚደረግ መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞችም ማንጸባረቂያ ነው::

በሥነ-ቃል ሕዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል፣ ስለአካባቢያቸው በአጠቃላይ ስለሚኖሩባት ዓለም ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርጹበታል:: ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋነኛ መሣሪያቸውም ነው:: ኃዘን ደስታቸውን፣ ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ ድል ሽንፈታቸውን፣ ድጋፍ ተቃውሞአቸውን በአጠቃላይ የሕይወታቸውን መልኮች ያንጸባርቁበታል::

የሥነ ቃል ዓይነቶች ብዙ ናቸው:: በየአገሩና በየባሕሉ የተለያዩ የሥነ ቃል ዓይነቶች ቢኖሩም አብዛኞዎቹ በሁለት ዐበይት ቅርጾች ይከሰታሉ:: የመጀመሪያዎቹ በዝርውና በትረካ የሚነገሩ ሲሆን፤ ሁለተኞዎቹ ደግሞ በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡና የሚዜሙ ናቸው:: በዝርው ከሚቀርቡት መሃል ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ አፈ ታሪኮች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዳ ቀልዶች ... ወዘተ ሌሎችም ይገኙበታል::

ምሳሌያዊ አነጋገሮችን የደረሳቸው እገሌ ነው አይባልም:: ምክንያቱም እጅግ ከረዥም ዘመናት በፊት ከሕዝቦች አንደበት፣ ለሕዝቦች፣ በሕዝቦች በጋራ ሀብትነት ሲጠቀሙባቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል፣ ዛሬ ደግሞ በጽሑፍ መልክ ሲተላለፉ በመኖራቸው ነው:: በዚህም ምክንያት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሕዝብ ሀብት ናቸው::

በእኔ በኩል ያደረግሁት ነገር ቢኖር እነዚህን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማሰባሰብ፣ መልክ በመስጠት ለእያንዳንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር አቻ ናቸው ከምላቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወይም ከምስጢራዊው ፍቺያቸው ጋር አቀናጅቼ ማቅረቤ ብቻ ነው:: ይህንንም ሥራ ለመሥራት ረዥም ጊዜና ብዙ ጥረት የጠየቀ ነበር::

በአጠቃላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከ8000 በላይ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወይም ከምሥጢራዊው ፍቺዎቻቸው ጋር እንዲሁም ከ2000 በላይ መልመጃዎች ከነመልሶቻቸው የቀረቡበት ዝግጅት ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገሮቹንም በተመለከተ ከዚህ ቀደም ተዘጋጅተው ከቀረቡት ዝግጅቶች ሁሉ ይህኛው በዓይነትም በብዛትም የመጀመሪያው የተዋጣለት ሥራ በመሆኑ ኅብረተሰቡ በተለይም መምህራንና ተማሪዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮቹን ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወይም ከምሥጢራዊው ፍቺዎቻቸው ጋር እንዲህ በሥርዓት ተዘጋጅተው ሲያገኙ በእጅጉ አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ተስፋ አደርጋለሁ።

አዘጋጁ



## ምሳሌያዊ አነጋገር

የሰው ልጅ በሕይወት ገጠመኙ በኑሮውና በሥራው የተለያዩ ልማዶችንና ወጐችን ያዳብራል። በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ይጠቀምባቸዋል። እንዲያውም ኑሮውን፣ሕይወቱን እንዲያጣፍጥለት በየጊዜው ይበልጥ ያበለጽጋቸዋል። ከነዚህ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ አቻና ወደር የሌለው የትውፊት አካል ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ምሳሌያዊ አነጋገር የቀረበበት ምክንያትና ሰበብ በቃል እየተጠና በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ትልቅ ትንሽ ሳይባል ባህላችንን ደንባችንን ሥነ-ምግባራችንን አጢቃሎ በያዘው በምሳሌያዊ አነጋገር እየተጠቀምን ስሜታችንን በማያሻማ ሁኔታ እንገልጻለን።

ምሳሌያዊ አነጋገሮችን የደረሳቸው እከሌ ነው አይባልም። ምክንያቱም እጅግ ከረዥምም ዘመን በፊት ጀምሮ ሕዝቡ እንደጋራ ሀብት በጋራ ሲጠቀምባቸው በመኖሩ ነው። በዚህም ምክንያት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሕዝብ ሀብት ናቸው።

እያንዳንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር ለተባለለት ጉዳይ ሲውል ግቡን ይመታል። ነገር ግን አወቅሁ ተብሎ በማያገለግልበት ቦታ ቢደነቅሩት ጠቀሜታ የለውም። ለምሳሌ የፋከራ ምሳሌ የሚነገረው የጀግንነት ተግባር ሲገለጽ ነው። ምሳሌያዊ አነጋገር አስፈላጊ በሆነበት ቦታ በትክክል ሳያንዛዙ ቢጠቀሙበት ነገርን በቀላሉ ለማስረዳትና ለማብራራት ብዙም ሳይጨነቁ በቀላሉ ግብን የሚያስመታ ትውፊት ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገር የያዘው ቁም ነገርና የሚያስተላልፈው ሰፊና ጥልቅ ሐሳብ በረጅሙ የአዝጋሚ ለውጥ ሒደት ውስጥ የተፈተነ ነው። የሰው ልጅ ያለፈውን አሁን ያለበትንና መጪውን ሕይወቱን በሚመለከት ምሳሌያዊ አነጋገር ታላቅ የገለጻና የማስረዳት ጥንካሬ አለው። መልእክትን ባጭሩና በተዋበ አባባል አስከዛሬ ሲገለጽበት እንደቆየ ሁሉ ወደፊትም ሊያቋርጠው የሚችል ነገር ሳይኖር ሰው እስካለ ድረስ ሥራ ላይ መዋሉ አይቀሬ ነው።

## የምሳሌያዊ አነጋገር አገልግሎት

እያንዳንዱ ምሳሌያዊ አነጋገር የሰውን ልጅ እንቅስቃሴና ሕይወትን በተለያየ ገጽታዎች የሚመለከት ስለሆነ ይህንኑ ለመግለጽ ያስችለን ዘንድ በትንንሽ ርዕሶች ከፋፍለን ለመናገር ቢያስቸግረንም በመጠኑ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ፖለቲካዊና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳዮችን አስመልክተው የማያገለግሉንን ለአብነት ያህል እንመለከታለን። የአማርኛ ባህሉ፣ ደንቡና ቋንቋው ከነአገባቡ ተጠቃሎ የሚገኘው ከምሳሌውና ከተረቱ ላይ ስለሆነ ሰፊና ጠንካራም ነው።

የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በብዛት ባለሁለት ሐረጎች ናቸው:: እነዚህም እንደ ሥነ - ቃል ቅርስነታቸው ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየተገናዘቡ ለመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት፤ ለድርሰትና ሥነ-ጽሑፍ ዕድገትና ብልጽግና ለቲያትርና ሲኒማ መነሻ ጭብጥ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ምክንያቱም በረዥሙ የአዝጋሚ ለውጥ ሒደት ውስጥ ሕብረተሰቡ የሕይወት ገጠመኙን ያካበተበት በመሆኑ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ግንኙነቱንና አስተሳሰቡን በጉልህ ያንጸባረቀበት ስለሆነ ነው::

"ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ " የሚባለው ምሳሌያዊ ንግግር በአማርኛ ከተራ የዕለት ንግግር እስከ ሸንጐ ክርክር ሲያገለግል መኖሩን ይጠቁማል:: የተጣላ አስታራቂ ፣ሸንጐ መሪ የሆኑ "ንግግር ዐዋቂ" ለሚባሉ ለምችም የንግግር ማጣፈጫቸው አሁንም ወትሮም ምሳሌያዊ አነጋገር ነው::

## የምሳሌያዊ አነጋገር አጠቃቀም በጥንት ሸንጐ ላይ

ምሳሌያዊ እነጋገሮች በአገር ባህል የፍርድ አሰጣጥ ሥነ - ሥርዓት ወይም ሙግት ጊዜም ያገለግሉ እንደነበር የታወቀ ነው:: የባህላዊው ሙግት እሰጥ አገባ ስለሆነ ተሟጋቾች:-

<u>ምሳሌ 1</u>

በላ !ልበልሃ!
የእጤ ሥረዓቱን
የአብርሃም እራቱን
አልናገርም ሐሰቱን
ስርከ እውነቱ እውነቱን

በሚሉ ሐረጐች ይጀምሩና አጫጭር ግጥሞችን በምሳሌያዊ ንግግር አስደግፌው የሙግታቸውን ውርድ /ከላይ ወደታች/ ይደረድራሉ::

በአንድ ሙግት አቤቱታ ላይ ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ አባቱ ልጅነቱን እንዲቀበለው አቤት ይላል:: አባቱ ልጁን መቀበል ስላልፈለገ መልስ ይሰጣል::
እንዲህ ብሎ:-

<u>ምሳሌ 2</u>

ታገር ክፉ ወጨፌ
ተንጨት ክፉ ጥፌ
ተህል ክፉ ባቄላ
ተልጅ ክፉ ዲቃላ
ተልብስ ክፉ ነጠላ
ከቤት ክፉ ሰቀላ

በማለት ከሳሹ አልሞት የነበረውን የመከራከሪያ ነጥብ ከዚህ በላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ዲቃላ ክፉ ነውና አልቀበለውም ለማለት ይሞክራል::



ከሳሹ ፈጣንና ብልህ ከሆነ የቀረበውን መልስ በተመሳሳይና ዘልቆ በሚገባ መልስ ይናገራል::

እንዲህ ብሎ:-

<u>ምሳሌ 3</u>

ካወቁበትስ ታገር ጥሩ ወጨፌ
ተንጨት ጥሩ ጥፌ
ችግር ይገፋል ባቄላ
ጥቃት ያወጣል ዲቃላ
ቀን ያሳልፋል ነጠላ
ከደህና ያደርሳል ሰቀላ
ካወቁበት ሁሉም አይጠላ

በማለት በምሳሌያዊ ንግግር መልስ ሰጥቶ እባት አሳዋቂ በመሆን ልጁን እለመቀበሉ ስሕተት እንደሆነ እንኳ ሳይቀር ይመክራል፣ ያስተምራል ፣ ሙግቱንም ይረታል::

## የምሳሌያዊ አነጋገር አገልግሎትና መልዕክት

ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩ ማኅበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ-ልቦናዊ መልዕክቶችን የያዙ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንመለከታለን::

ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚታዩትን አስነዋሪ ባህርያትን ለመዋጋትና መልካም ሥነ-ምግባር እንዲዳብር፣ፍቅር፣ታማኝነት፣ደግነት፣ትህትና፣እውነት፣ሰላም እንዲሰፍኑና ትእግስት እንዲኖር የሚያሳስቡና የሚያስተምሩ ናቸው::

<u>ምሳሌ 4</u>

- ሰው ለወዳጁ ጫጩት ያርዳል
- እንኳን ለቤቱ ይተርፋል ለጐረቤቱ
- የተናገሩት ከሚጠፋ ፣ የወለዱት ይጥፋ
- ሁለት ሆነው የተናገሩት፣ በመሬት የቀበሩት
- ትእግስተኛ ከፈለገበት ይደርሳል

ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣በሕብረተሰቡ መካከል መፈቃቀርና መተዛዘን እንዲኖር ማጭበርበር፣ ስለትና ንፍገት እንዲጠፋ ያስገነዝባሉ::

<u>ምሳሌ 5</u>

- ከሰስታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው
- አታላይ ለጊዜው ያመልጣል፣በኋላ ይሰምጣል
- ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል
- ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ

- ንፋግ ለግሶ ቢሰጥ፣እጁ ይንቀጥቀጥ
- አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
- ይሉኝታና ጥቅም ጉን ለጉን አይሄዱም
- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሕፃናት በሥርዓት ተኰትኩተው ማደግ እንደሚያስፈልጋቸው ወላጆችና አሳዳጊዎችን ይመክራሉ፣ያስጠነቅቃሉ::

ምሳሌ 6

- ለልጅ ከሣቁለት ለውሻ ክሮጡለት
- ልጅን በጡት፣ እህልን በጥቅምት
- ልጅህንና አትክልትህን ፣ ተጠባበቅ ጉረቤትህን
- ልጅ ሲያባብሉት ያለቅሳል

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሕብረተሰቡን አንድነትና ሰላም ጠብቀው ያኖሩት አረጋውያንና አረጋውያት ታላላቆች ክብርና እንክብካቤ እንዳይነፈጋቸው ይመክራሉ:: "ነግ በኔ" እንዲሉ::

ምሳሌ 7

- የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ፣ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ
- ሽማግሌ ይገላግላል፣የታጠቀ አቤት ይላል
- ሽማግሌ በምክሩ ፣ አርበኛ በሰናድሩ
- አባት ያበጀው፣ ለልጅ ይበጀው
- የሰው አባት የሚሰድብ፣ አባቱን ያሰድብ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጉብዝናን፣ጀግንነትን ያደፋፍራሉ:: ፍርኃትን ያንኳስሳሉ::

ምሳሌ 8

- ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
- ፎክሮ መሸሽ ታሪክ ያበላሽ
- ጦር እንደወረወሩት ጉራጌ እንደለነዘሩት
- ጉልማሳ ካለበት ከብት አይሰረቅም ሽማግሌ ካለበት ነገር አይነጠቅም

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሕዝቡ ከበሽታ እንዲጠነቀቅ ፣በበሽታ ከተያዘም በጊዜው አስፈላጊውን የሕክምና ወይም የወጌሻ ዕርዳታ እንዲጠይቅ ምክር ይለግሳሉ፣ ያስተምራሉ::

ምሳሌ 9

- ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ
- በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም



- ሐኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል
- ጉመን በጤና
- በበሽታው የተጎዳ በጥንስሱ የተቀዳ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ሥራ መሥራት የሚያስከብር፣የሚያኮራ ከችግርና ከሐሳብ ነፃ የሚያወጣ መሆኑን ይመክራሉ፣ ያስተምራሉ::

ምሳሌ 10

- ሳይሠሩ ማግኘት ሳይጸድቁ ገነት
- በሰኔ ካልዘሩ በጥቅምት ካለቀሙ፣እህል አይገኝም ከድንበር ቢቆሙ
- ካልሠሩ አይገኝ መከሩ
- ነገር አለኝ ከማለት ሥራ አለኝ ማለት
- ነጋዴ ወረቱን ዘላን ከብቱን፣ ገበሬ ምርቱን መሥራት ያስከብራል

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የጊዜን ክቡርነት በመግለጽ ሕብረተሰቡ ለነገ ሳይል ሥራውን በወቅቱ መፈጸም እንዳለበት፣ይህ ካልሆነ ግን በሥራ ፈትነት መታወቅ፣ መከበርና መሞገስ እንደማይገኝ ያስጠነቅቃሉ::

ምሳሌ 11

- ሰነፍ ገበሬ በመስከረም ያርማል
- በድህነት ላይ ስንፍና፣ በቂጥኝ ላይ ቁምጥና
- ሰነፍ ከመውለድ ይሻላል ማስወረድ
- ሰሞኝ ሰኔ በጋው፣መስከረም ክረምቱ
- ጊዜ ወርቅ ነው፣ግን ኃላፊ ነው

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የአፈ ሙሌዎች ዕውቀትና ችሎታው ሳይኖራቸው የሚመጻደቁትን ለማስጠንቀቅ ይጠቅማል::

ምሳሌ 12

- ሁሳይሉ ጥፋት ውል ሳይዙ ሙግት
- አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ
- አፍና ቅብቅብ ሁልጊዜ አያበላም
- ዐወቅሽ ዐወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የመማርን ጥቅምና አስፈላጊነት አበክረው ያስረዳሉ::

ምሳሌ 13

- ሁባሉ ተዝካር በሉ
- ትምህርት የማያልቅ ምርት

– ለምሽት መብራት ፣ለመከራ ጊዜ ብልሃት

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የመምረጥ ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ይተቻሉ፡፡

ምሳሌ 14

– ሁሉቱን የተመኘ አንዱንም አላገኘ
– ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት
– አንዱን ሳይዘው ደረሰ ጊዜው

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሰዎች ተዘጋጅተው፣ተሰናድተውና ተጠንቅቀው ካልተቀመጡ አስቸኳይ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ቢደርስ እንደሚቸገሩ ያስገነዝባሉ፡፡

ምሳሌ 15

– ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
– የማታ እሩጫ እንቅፋት ትርፉ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴብነትን ዘረፋን ሕገወጥ ወንጀሎችን በትዝብት ከማየት ይልቅ ሕዝባዊ ቅጣት እንዲኖርም የሚጠይቅ መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡

ምሳሌ 16

– ሌባ ተይዞ ዱላ አይጠየቅም
– የሚዘንን አባይ ለእሳት፣ የዳኛን አባይ ለሰንሰለት

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሰዎች ባልፈጸሙት ጥፋት ወንጀለኞች ተብለው ሲያዙ የመቃወሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

ምሳሌ 17

– እህያውን ፈርቶ ዳውላውን
– አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ
– አሞራ በበላ ጥፍጥሬን በዱላ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ርኅራኄን የሚጠይቁ፣ ለጥፋተኞች ይቅርታን የሚለምኑ፣ ቂም በቀል እንዲቀር የሚመክሩ ናቸው፡፡

ምሳሌ 18

– መተው ነገሬን ከተተው
– ሰው ሆኖ የማይበደል፣ ዕንጨት ሆኖ የማይጨስ
– ሲታጠቡ እስከ ክንድ፣ ሲታረቁ ከሆድ



– ይቅር ለእግዜር ወድቆ አይሰበር፣ሞቶ አይቀር

ምሳሌያዊ አነጋገሮች አጉል ችኩልነትን መታዘቢያ ናቸው፡፡

ምሳሌ 19

– መች መጣሽ ሙሽራ፣ መች ቀረጠምሽ ሽንብራ
– ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
– ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
– የቸኮለች አፍሳ ለቀመች
– የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ዓላማው ከክንውኑ ጋር አለጣጣም ሲል አለመገናኘቱን ይጠቁማሉ፡፡

ምሳሌ 20

– ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ
– ማርና ወተት ምን አገናኝቶት

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የወዳጅ ጠላትን መውቀሻም ናቸው፡፡

ምሳሌ 21

– የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ
– የሆድ ምቀኛ አፍ ነው
– የሚከድ ሰው አደራ ሲያስቀምጡበት እጅ ይነሳል

ወጣቱ ትውልድ ለወገኑና ለሀገሩ ተቆርቋሪ እንዲሆን ትምህርት ከሚሰጡት ውስጥ

ምሳሌ 22

– ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ፣ ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ
– አገር የሌለው ሰጌታ አዳሪ፣ማጭድ የሌለው መስክ ሰፋሪ

በቀድሞው ዘመን የነገሥት መደብ አባላት ምሳሌያዊ ንግግሮችን የግል ጥቅማቸውን ማስጠበቂያ የመበዝበዣና የመጨቆኛ መሣሪያ አድርገው ተጠቅመውባቸዋል፡፡ የራሳቸውን ክብርና ዝና ለማስጠበቅ ሲሉ የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነውን ንጉሥ ኃያልነት ገናናነት ሊጋስነትና መሀሪነትን ለማረጋገጥ በርከት ያሉ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመፍጠርና በሕዝቡ አእምሮ ሰርጸው እንዲገቡ ያደርጉ ነበር፡፡

ምሳሌ 23

- ንጉሥ መንቀፍ ነብር ማቀፍ
- ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ
- ንጉሥን ያገለገለ ከትልቅ ሀብት የታደለ
- ንጉሥ የቆረጠው እጅ ካሰ ይቆጠራል
- ንጉሥ የገደለው ቀባሪ የሌለው

ከንጉሥ በታች አዛዥ ገዥ አስቃ ወዘተ የሚባሉ የፊውዳሉ ሥርዓት አራማጆች ስለነበሩ እነሱም እንደ ሥልጣን ተዋረዳቸው እንዲያስገብሩ እንዲበዘብዙ ሥርዓቱ ሙሉ ሥልጣን ስላስጨበጣቸው እምባገነንነታቸውን የሚዘክሩ ምሳሌዎችን በመፍጠር ሲጠቀሙ ቆይተዋል።

ምሳሌ 24

- ድሀና ሹም ተሟግቶ፣ድንጋይና ቅል ተማትቶ የማይሆን ነው ከቶ
- ከሹም አይጣሉም ከግንብ አይታገሉም
- ተልባ ቢንጫጫ በንድ ሙቀጫ

ድርብ ጭቆናን የሚያንጸባርቁ ሴቶች በማጀት ብቻ ተከልለው እንዲኖሩ ተጽእኖ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮችንም ፈጥረዋል።

ምሳሌ 25

- ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ ቤታቸውን ይከዱ
- ሴት በማጀት ወንድ በችሎት
- ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ
- አህያና ሴት ሲረግጧት አይከፋት
- ወንድ ባለ በለት፣ ሴት ባለች ባመት

ለዕደ ጥበብ ሙያ እንቅፋት የሚሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮች

ምሳሌ 26

- ለፋቂ ግማት፣ለአይጥ ሞት፣ብርጉድ አይገኝለት
- ከመሆን ፋቂ ይሻላል ነጣቂ
  ከሚሉት ለመረዳት ይቻላል።

የቀድሞው ዘመን የገዥው መደብ አባላት በተሰጣቸው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት ብዝበዛና ጉቦን ሕጋዊ ለማድረግ ጥረዋል። በዚህም ለሹም ለአስቃ እጅ መንሻ ጉቦ መስጠት ከመጉላላት እንደሚያድንና ትክክለኛ ነገር እንደሆነ ሕዝቡ አምኖ እንዲቀበል አድርገዋል።

ምሳሌ 27

- ተሹሞ የማይበላ ተጥዶ የማይፈላ
- ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል
- ያማከሩት ዳኛ ያግዛል፣የመተሩበት እጅ ይወዛል

ሰፊው ሕዝብም በሚያገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የራሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በመጠቀም ቅሬታውን ብሶቱን ይገልጽ ነበር።

ምሳሌ 28

- አገር ቢያብር ለንጉሥ ያስቸግር
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

እንስሳቱን እንደሰው በማናገር በገዥው መደብ ላይ የነበረውን ምሬት ይገልጽ ነበር።

ምሳሌ 29

- ትላንትና ልጄን ዛሬ እናቴን ምን ይበጃል ዘንድሮ አለ አውራ ዶሮ
- በካብ ላይ ብሠራ እባቡ መከራ፣ በዛፍ ላይ ብሠራ አሞራው መከራ፣ የት ውዬ የት ልደር አለች ወፍ።

ሕብረተሰቡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ግልጽና ቀጥታ በሆነ አነጋገር አይጠቀምም ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያላብሳቸዋል። ይህም የታመቀ የውስጥ ስሜቱንና አይታውን በሚስጥር ለመግለጽ እንዲያመቸው ነው ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ተነጻጻሪ

ሁለት ተቃራኒ ሐረጎችን በማነጻጸር ወይም በማወዳደር ይገልጻል።

- የጨዋ ልጅ ሲፋታ ይጋባ ይመስላል
- የጠፋ ከለማ እኩል ነው

ለ. ግነት

ጉዳዩን ከሚገባው በላይ በማጋነን የማገለጽ

- ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ
- ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት እብቁ ዓይኔ ገባ አለ

ሐ. ሰውኛ

እንስሳት እንደሚሰሙና እንደሚናገሩ በመቁጠር ቅሬታን መግለጽ

- ሺ ቢታሰብ ያው በገሌ አለች ድመት

- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

መ. ምጸት

በአሽሙር መልክ የሚተላለፍበትና የታሰበው መልእክት ሰወር ባለ መንገድ የሚነገርበት

- ሲሉ ሰምታ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ
- ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች መልክት ለማስተላለፍ የሚከተሉትን ስልቶች ይጠቀማሉ::

ሀ. ጥያቄና መልስ

ራሳቸው ጠይቀው ለራሳቸው መልስ የሚሰጡ ናቸው

- በቅሎ አባትሽ ማነው? ቢሏት ፈረስ አጐቴ ነው አለች
- ወጥ ማን ያውቃል? ቀላዋጭ

ለ. ሳቢያና ውጤት

ጥሩም ሆነ መጥፎ ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት የሚጠቁሙ ናቸው::

- ካላረፉ መከራ ነው ትርፉ
- ዕውር ዕውርን ቢከተል ተያይዞ ገደል

ሐ. አማራጭ

ሁለት ተጻራሪ ነገሮችን በማወዳደር የሚነገር

- ከመልካም ጠላ ክፉ ጠጅ
- ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ

መ. ማወዳደር

ሁለት የማይገናኙ ነገሮችን በማወዳደር እኩል ውጤት እንዳላቸው ተደርጎ የሚቀርብበት ነው::

- ንብ ባውራው ገበሬ ባዝመራው
- መሬት ላራሹ ጥይት ለተኳሹ

ባጠቃላይ ተረትና ምሳሌ ማለት ባጭር አገላለጽ፣ጠባይን፣ወግን፣ልምድን፣ጠቅላላ ባህልንና ምክርን የምንገልጽበት የአነጋገር ፍልፍልና ነው::

ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንድናጠና ከሚያስገድዱን ምክንያቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ባህል ደንብ ቋንቋ ከነአገባቡ ተጠቃልሎ የሚገኘው በምሳሌያዊ አነጋገሩ ውስጥ በመሆኑ ነው:: ስለሆነም የምሳሌያዊ አነጋገር ዋጋ በግልጽ የሚታየው መሰል ነገር ሲያጋጥም ብቻ ስንጠቀምበት አንጂ ዐወቅን በማለት ካለቦታው ደርሰን ብንመሰለው ከጣዕሙና ከፍልፍልናው ማጨናገፍ ይሆናል::



በዚህ መጽሐፍ የማቀርባቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ካሁን በፊት በልዩ ልዩ መልክ ከቀረቡት በብዛትም በጥራትም ከአቻ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ከፍቺያቸው ጋር በመቅረባቸው በዓይነቱ የመጀመሪያው ይሆናል:: በተለይም ተማሪዎቻችን የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ስልትንና የሚያስከትሉትንም ትርጉም ጭምር ዐውቀው እንዲጠቀሙባቸው እንጂ ተረቱንም ሆነ ምሳሌያዊ አነጋገሩን እንዲሁ እንዳለ በቃል ቢያጠኑት የምሳሌያዊ አነጋገር ትምህርት ዓላማ ተሟልቷል ለማለት ስለማያስችል ነው:: ተማሪዎች የምሳሌያዊ አነጋገርን የአፈታትና የሚስጥሩን አጠቃቀም በመጽሐፉ ውስጥ በቀረበላቸው ምሳሌዎች መሠረት ካጠኑ በኋላ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ተከትለው አቻ ምሳሌያዊ አነጋገር ወይም ፍቺ ወይም ትርጓሜ የሚሰጡባቸው በርካታ መልመጃዎች በልዩ ልዩ የአጠያየቅ መልክ ቀርበዋል::

እንደቀረቡት መልመጃዎች መመሪያዎችና አካሄድ መሠረት መምህራንና ተማሪዎች መልመጃዎቹን በጥንቃቄ አያስተዋሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አሳስባለሁ::

# ሀ

ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ነው ለሃምሳ ግን ጌጡ ነው።
- በጣም የሚከብድን ሥራ ከተረዳዱበት በጣም ይቀላል።

ሀ ሳይሉ ጥፈት ውል ሳይዙ ሙግት
- ምንም መረጃ ሳይኖር አሸንፋለሁ ማለት ዘበት ነው።

ሀ ባሉ ተዝካር በሉ
- ትንሽ በሠሩ ብዙ እንደሠሩ ተቆጥሮላቸው ተጠቀሙ።

ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ድሀ ለድሃ ይለቃቀሱ
- ቢጤ ለቢጤ

ሀብታም ሲለፕ የድሃ ሙርጥ አበጠ
- አንዱ ሲለጥ ሌላው ተመቀኘ

ሀብታም ቢወድቅ ከለገነት ድሃ ቢወድቅ ከመሬት
- ሀብትም ሲከስር በአንዴ የሚደርስበት የሞራል ውድቀት ከፍተኛ መሆኑ ሲሆን ድሃ ግን ብዙም አይሰማውም

ሀብታም በምጽዋቱ፣ ድሀ በጸሎቱ
- ሁሉም በየችሎታው እምላኩን ያስታውሰዋል

ሀብታም በከብቱ ድሃ በጉልበቱ
- ሁሉም የእኔ ነው የሚለው ነገር አለው

ሀብታም በወርቁ ድሃ በጨርቁ
- ሁሉም ባለውና በእሱነቱ ይጠቀማል

ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ድሃ በጥበቡ ይከብራል
- ሁሉም ሰው የሚኮራበት የየራሱ ተሰጥኦ አለው

ሀብታም በገንዘቡ ድሃ በጥበቡ እርስ በእርስ ይቃረቡ
- ሀብታም በገንዘቡ ድሃ በጉልበቱ

ሀብታም ቢሰጥ አበደረ እንጅ አልሰጠም
- ሀብታም ገንዘብ ቢሰጥ በምትኩ የድሃን ጉልበት ይሻል

ሀብታም ነው መባል ያኮራል ድሃ ነው መባል ያሳፍራል
- ሕብረተሰብ ያከበረው ሲከበር ያንቋሸሸው ይንኳሰሳል

ሀብታም እንደሚበላለት፣ ድሃ እንደሚከናወንለት
- ሁሉም በየችግሩ ላይ ያተኩራል

ሀብታም ያለ ድሃ አይኮራም፣ ድሃ ያለ ሀብታም አይበላም
- ሀብታም ከሌለ ድሃ የለም፣ ድሃ ከሌለ ሀበታም የለም

ሀብታም ገንዘቡን ያሰባል፣ ድሃ ቀኑን ይቆጥራል
- ሀብታም የሀብቱን መጨመር ሲያሰብ ድሃ ግን ገንዘብ የሚያገኝበትን ቀን ይቆጥራል

ሀብትና ዕውቀት አይገኝ እንድነት
- ሁሉን አሟልቶ አይሰጥ

12 ሀብታም - ድሃ



ሀብት የጠዋት ጤዛ ነው
- ሀብት ጠፊ ነው መልክም ረጋፊ ነው

ሁለተኛ ግፌ፣ ጫንቃዬን ተገርፌ፣ልብሴን መገፈፌ
- የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
- የግፍ ግፍ በደል ተፈጸመብኝ

ሁለተኛ ግፍ ልብሴን ይገፍ ጀርባዬን ይገረፍ
- የግፍ ግፍ ሥራ ነው የተፈጸመብኝ

ሁለተኛ ጥፋት፤ቆሞ ማንቀላፋት
- ከመጀመሪያው ጥፋት ሁለተኛው ይባስ

ሁለተኛ ጥፋት፤ከገበያ ማንቀላፋት
- ከመጀመሪያ ጥፋት ሁለተኛው የባሰ ሆነ

ሁለቱን ወንበዴ፤በአንድ ዘዴ፤
- ሥራን ቶሎ ለመጨረስ በዘዴ መጠቀም ይገባል

ሁለቱን የተመኘ፤ አንዱንም አላገኘ
- ከሁለት የወደቀ ዛፍ

ሁለት ሆነው የተናገሩት በመሬት የቀበሩት
- ከራስ ያለፈ ሚስጥር ተደብቆ ሊቆይ አይችልም

ሁለት ሞት መጣ ቢለው፤ አንዱን ግባ በለው አለ
- የማይቀርን ነገር አምኖ መቀበል ይገባል

ሁለት ቁና ስጥቼ፤ አንድ ጥንቅል
- ባጕረስኩ እጄን ተነከስኩ

ሁለት ባላ ትክል አንዱ ቢሰበር ባንዱ ተንጠልጠል
- አንቺ ምንቸገረሽ ሁለት አባት አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
- ሁለት አማራጭ ይኑርህ

ሁለት ብልጥ፤ ኑግ አያደቅ
- የፉከከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

ሁለት ነዶ ይዞ ወደ ክምር ጠጋ
- ትንሽ ቆሎ ያደርሳል ከአሻሮ

ሁለት አይወዱ፤ ከመነኮሉ አይወልዱ
- ሁለት ነገሮችን በአንድ ጊዜ አትመኝ

ሁለት አገር አራሽ ለባልንጀራ አውራሽ
- ሩቅ ለፍቶ ደከሞ ለለው

ሁለት እፎች ባይናከሉ፤ ይናቀሉ
- ባይጕዳዱም በጥቂቱ መሞካከራቸው የማይቀር ይሆናል

ሁለት እግር አለኝ ብሎ፤ ከሁለት ዛፍ አይወጡም
- ሁለት ነገሮችን በአንድ ጊዜ ማከናወን አይቻልም

ሁለት የተመኘ፤ አንድም አላገኘ
- አሥር ያባረረ አንድ አይዝም
- ይሀንንም ያንንም መመኘት ውጤቱ አያምርም

ሁለት የወደደ፤ አንዱን ሳያገኝ ሄደ
- ሁሉን የተመኘ አንድም አላገኘ

ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም
- ሁለት አማራጭ ያለው ችግር ላይ አይወድቅም

ሁለት ጊዜ ተናግረሀ ክፋህ፤ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ
- የምከርከው ሁሉ አልሆነልህም

ሁለት ጊዜ ነው የዶሮ ልደት፤ አንዱ በእንቁላል አንዱ በጫጩት
- የተፈጥሮ ሂደት ይሟላል ወደፊት

ሁለት ጊዜ ይፍረዱ፤ ጉድ ይውሰዱ
- የሠሩት በደል አይለቅም በቀላል

ሁለት ጥፉ፤ ካገር ይጥፉ
- ሁለት ጥፉዎች ስለሆኑ አስወግዷቸው

ሁሉ ሄዶ፤ ተበተነ ፤እሀሀና እኔ ቀረነ ፤አለ አያዘነ
- ለችግሬ ያገኘሁት መፍትሔ የለም አሁንም ኃዘንተኛ ነኝ እሀሀ እያልኩ እንደተቆጨሁ ቀረሁ

ሁሉ ሆነ ቃልቻ፤ ማን ይሸከም ስልቻ
- ሁሉ አለቃ ከሆነ ሥራውን ማን ይሥራ

ሁሉም ሰው መምሰሉ፤ ባይታይ ዓመሉ
- ሲያዩት ጨዋ የሚመስለው ሁሉ ውሎ አድሮ ሲታይ ግን መጥፎ ባህርያቸው መገለጡ አይቀርም

ሁሉም ሽክሙን፤ፍቅርም ያዥውን
- የነብር ዐይን ክፍየል፤የፍየል ዓይን ከቅጠል

ሁሉም በየዘመድህ ቢሉት፤ አክንባሎ ጋጥ ገባ
- በየወገንህ ቢሉት የመቶ ዓመት ቆዳ ከበረት ገባ

ሁሉም አካል ነው፤ግን እንደ ዐይን አይሆንም
- ከሁሉም አብልጨ የምወደው እርሱን ነው

ሁሉም ከኋላው፤ ያገኘዋል እንደሥራው
- ሁሉም ወንፊሉን ፈታይም ድውሩን

ሁሉም ወንፊሉን፤ ፈታይም ድውሩን
- ሁሉም እንደየሥራው ያገኘዋል

ሁሉም ያልፋል፤ እስኪያልፍ ያለፋል
- ዳገቱን ካልወጡ ሜዳው አይታይም

ሁሉም ያልፋል እውነት ብቻ ይተርፋል
- እውነት ቆይታ ቆይታ ትወጣለች

ሁሉ በጀ፤ሁሉ በደጀ
- ምንም የሚጐድለኝ ነገር የለም

ሁሉን ቢናገሩት ማን ይሰማል
- የደንቆሮ ለቅሶ፤ መልሶ መላልሶ



**ሁ**ሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል
- መታገስ ይገባል

**ሁ**ሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት
- ዐይን አዋጅ

**ሁ**ሉ አረሰ፤ ማን ይሸምት
- ሁሉ ሆነ ቃልቻ፤ ምን ይሸከም ስልቻ

**ሁ**ሉ የሚገኝ ከርሱ፤የሚገኝ የለም ያለርሱ
- ሁሉን የሚሰጥ የሚነሳም አንድ ዓምላክ ብቻ ነው

**ሆ**ደ ሰፊ፤ ነገር አሳላፊ
- ታጋሽ ሰው

**ሆ**ደ ሰፊ ይሻላል ከአኩራፊ
- ቅሬታን በኩርፊያ ከማድረግ ያልተቀየሙ በመምሰል ማሳለፍ

**ሆ**ዱ ናረት፤ ሙያው ከጅረት
- ሆዱን ይወዳል መጠጥ ያዘወትራል

**ሆ**ዱን ወዶ፤ አፉን ከዶ፤ከፉ ለምዶ
- መጥፎ ልምድ ለማስወገድ ያስቸግራል

**ሆ**ዱን ያለ፤ ሆዱን ተወጋ
- ስግብግብ ሰው ችግር ላይ መውደቁ አይቀርም

**ሆ**ዱ ፈሪ ፤ እግሩ ዳተኛ፤ አዳም ሲዋጋ እርሱ ይተኛ
- በቁም ነገር ላይ የማይገኝ፤ ከሰው በታች የዋለ

**ሆ**ዳም ሰው፤ እምብርት የለውም
- ሆዳም ሰው ቶሎ አይጠግብም

**ሆ**ዳም ቢሽከም፤የበላ ይመስለዋል
- አጉል በተግባር የማይገለጽ ምኞት

**ሆ**ዳም ቢፈተፍት፤የጠገበ ይመስለዋል
- ይሄ ሌላ ያ ሌላ
- አጉል በተግባር የማይገለጽ ምኞት

**ሆ**ዳም ሰው፤ፍቅር አያውቅም
- ሆዳም ሰው ለሌላው አያስብም እራሱን ብቻ ነው የሚወደው

**ሆ**ዴ ሆዴ የሚለውን ጌታ ያየዋል፤ ዐይኔ ዐይኔ የሚለውን ሰው ያየዋል
- ጌታ የድብቁን ሰው የፊት ለፊቱን ይመለከታል

**ሆ**ዴ በጀርባዬ ቢሆን ገፍቶ በጣለኝ
- ክፉ ባላጋራዬ ሆዴ ነው

**ሆ**ዴ ኑር በዘዴ
- ተስማምተህ ኑር

**ሆ**ዴ አታጣላኝ ከዘመዴ
- ሁሉንም ቻል አድርገው

**ሆ**ድህን ጎመን ሙላው፤ ጀርባህን ለጠላት አታሳየው
- ለጠላትህ እጅህን አትስጥ

ሆድ ሆዱን የምትል ወፍ አለች ምን አለች?
- ያለሆዱ የሚያሳስበው ጉዳይ የለውም

ሆድ ለማታ በልቶ ለጧት
- ምን ዛሬ ብንበላ ነገ ሆድ አዲስ ነው

ሆድ ለባለው ማጭድ አታውሰው
- እንኳንስ እናቱ ሞታ እንዲሁም አልቅስ አልቅስ ይለኛል

ሆድ ሲሞላ ራስ ባዶ ይቀራል
- ለሆድ ብቻ ሳይሆን ለዕውቀትም እንጣር

ሆድ ሲሞላ ፍቅሩ ሌላ፤ ሆድ ሲጎድል ሰው ያጋድል
- የሰው ልጅ ዋልታው ምግብ ነው
- ሰው ካልበላ ቆሞ መራመድ አይችልም

ሆድ ሲያር ጥርስ ይስቃል
- ውስጡን ለቁስ

ሆድ ሲያውቅ፤ዶሮ ማታ
- ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት

ሆድ ባዶ ይጠላል
- በተለመደው ሰዓት ምንም ይሁን ምን መመገብ አለብህ

ሆድና ልጅ አይጣላህ
- ልጅንና የሚሞትን ሽማግሌ አታስቀይም

ሆድና ግንባር አይሸሸግም
- ስመብላት እየፈለክ አትግደርደር

ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይስግማል
- እራት የሌለው ቁስ እንደልቡ አይቀድስ

ሆድ እንዳሳዩት ነው
- ሆድ እንዳስለመዱት ነው

ሆድ ክሁዳድ ይሰፋል
- ቻለው፤ ታጋሽ ሁን

ሆድ ወዶ፤ እፍ ከዶ፤ ክፉ ለምዶ
- የተለመደ ልማድ መታወቁ መገለጡ አይቀርም

ሆድ የኔ ነው ሲሉት፤ ቁርጠት ሆኖ ይገላል
- የተማመኑበት ዘመድ መልሶ ጠላት ይሆናል

ሆድ ያበላውን ያመሰግናል
- ውሻ በበላበት ይጮኻል

ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል
- ስካር ቅሬታን ስመናገር ይገፋፋል

ሆድ ዘመድ ሳይወድ፤አፍ እህል ሳይለምድ
- የተመኘኸውን ፈጥነህ አከናውን

ሆድ ድንጋይ ልበላ ነው ቢል፤ጉሮሮ በየት አሳልፈህ? አለው
- የማይደረግን ነገር ለተቀባይ ሰው ማስፈራራት እማይኮን የማይደረግ ነገር ነው



# ለ

ለሀምሳ ጋን አንድ አሎሎ
- ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ

ለሀብት መትጋት ሰውነትን ያከሳል፤ገንዘብ ማሰብ እንቅልፍ ይነሣል
- ለሀብትና ለገንዘብ የሚደረግ ሩጫ ሰላም መንሳቱ አይቀርም

ለሁሉም ጊዜ አለው
- ወቅቱን ጠብቆ የሚሆነው ይሆናል

ለሂያጅ የለውም ወዳጅ
- የተሾመን ይሟገቱለታል፤ የተሻረን ይመሰክሩበታል
- ለባለጌ ጥሩ የሚመኝለት የለም

ለሆዳም ሰው ማብላት ውቅያኖስን ለመደልደል መቃጣት
- የማይሆንን ነገር እንዲሆን መሞከር ትርፉ ድካም ብቻ ነው

ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል
- ለአንዳንዱ በሰሰ ይቀናዋል

ለሆዴ ጠግቤ ፤በልብሴ አንግቤ
- ሁሉ ሞልቶ ተርፎ ምን ጐድሎ

ለሆድ ቁርጠት ብላበት፤ለራስ ምታት ጨህበት
- ያልሆነ ምክር መምከር

ለላሙ መንጃ፤ ለሽማው መቅደጃ
- መሣሪያ ጠቃሚ ነው
- ለማንኛውም ነገር መሣሪያና መጠቀሚያ ያመቻችለታል እግዚአብሔር

ለላሙ መንጃ፤ ለሽማው መከንጃ
- ሥራን ለመከወን መሣሪያ ጠቃሚ ነው
- ሥራን ለማከናወን ቸሩ እግዚአብሔር ያመቻችለታል

ለላም ቀንዷ አይከብዳትም
- የእኔ ነው የተባለ በሙሉ አያስጨንቅም

ለላም ከጥጃዋና፤ ከእላቢዋ ማን ይቀርባታል
- ሁሉቱም የእሷ ጥገኞች ናቸው

ለላም የሣር ሰምለም
- የሚጠቅምን ነገር መጠበቅ አለበት

ለላም ጥጃዋ፤ለአህያ ውርንጭላዋ
- ሁሉም ለራሱ

ለሌለው ምን ትሰው
- ያጣን ሰው ምን አድርግ ትለዋለህ

ለሌባ ቅሌቱ ልብሱ ነው
- ሌባ ሁሌም እንደተዋረደ ነው

ለልጅ ሲሉ ይበሉ፤ ለወዳጅ ሲሉ ይጣሉ
- ለምትወደው ነገር ተጠቃ

ለልጅ አይሥቁለትም፣ለውሻ አይሮጡለትም
- ለልጅ ፊት ካሳየኸው ያዋርድሃል

ለልጅ ጥርስህን ለዝንብ ቁስልህን አታሳይ
- ለልጅ ፊት ካሳየህ ያዋርድሃል

ለልጅ ጨዋታ ለባለጌ ቧልት
- ልጅ ጨዋታ እንደሚወድ ሁሉ ባለጌም ቁም ነገር የለውም

ለሎሌው ምን ትለው?
- ለተከታይ ምን የምትለው ይኖርሃል?

ለሕልም ምሳሌ የለውም
- ለአንዳንዱ ጉዳይ ማስረጃ አይገኝም

ለመሄድና ለመመለስ፤ አዛዥ ራስ
- ሁሉም የሚወሰነው በራስ አዛዥነት ነው

ለመሆኑ ሳይሆን እንዴት ይሆናል ቢሆን
- የሆነበት ስልትና ዘዴ ምን ይሆን
- መጥፎም ደግም ነገር ሳይሆን ደግ ቢሆን መልካም መጥፎ ቢሆን ወይም ቢያጋጥም ምን ይሆናል

ለመሥራት ያፈረ፤ መብላት ደፈረ
- ሥራ አይወድም ግን ሆዳም ነው

ለመሪህ ዓሣ ምሰል
- ከአለቃህ ጋር ሽርጉድ እያልክ ኑር

ለመስማት የፈጠንህ ለመናገር የዘገየህ ሁን
- የቸኮለ አፍሶ ለቀመ ነውና ብዙ ከመናገር ጥቂት ማዳመጥ የበለጠ ነው

ለመስጠት አለመቸኮል፣ከሰጡም ወዲህ አለመጸጸት
- ለመስጠት አጥንቶ መስጠት ከተሳሳትክ በኋላ ግን አትጸጸት
- ፈጥኖ መስጠት ኋላ ለመጸጸት

ለመታማት መፍራት
- ይሉኝ ማለት ተገቢ ነው

ለመነኩሴ መልካም ሎሌ
- ለነፍሱ ያደረ ጨዋ ረዳት አያጣም

ለመከራ የጣፈው፣ቢነግድ አይተርፈው
- የአርባ ቀን ዕድሉ የሆነ ምንም ቢለፋ አያልፍለትም

ለመከራ ያለው መነኩሴ ፤ዳዊት ሽጦ አህያ ይገዛል
- ያለሙያው የተሠማራ ትርፉ ችግር ብቻ ነው

ለመኾን እማዬ፣ለአገልጋይ እትዬ ብርቋ ነው
- እይቶ ለማያውቅ ሁሉ ቁልምጫ ብርቁ ነው

ለሙት የለው መብት
- ላለፈ ለማይመለስ መሟገት ፋይዳ የለውም



**ለሚ**መለከት ለሚያየው፤ሞት ቅርብ ነው
- ሰው ሟች መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው

**ለሚ**ስት ያጉርሷል፣ለተመታ ይክሷል
- ለሚስት እንክብካቤ እንደሚደረግ ሁሉ ለተበደለም ካሳ ያስፈልገዋል

**ለማ**ረም ማን ብሎት፣ሲሠራው ግን ግድፈት
- ሰው የሠራውን ያጥላላ፤ እራሱ ግን ሥራ አይችልም

**ለማ**ን አለው ፈጣሪ አለው፣ጠጅ ለሌለው ውኃ አለው
- ምርጡ ባይገኝ እንኳ ተራው ነገር መገኘቱ አይቀርም

**ለማ**ን ይፍረዱ? ለወደዱ፤ አይደለም ለወደዱ፤ ለወለዱ።
- ለሚወዱት ሰው ጥሩ ቢያደርጉም ከአብራክ ለወጣ ልጅ ደግሞ የበለጠ ያደላሉ

**ለማ**ኝ ቢያብድ ስልቻውን አይጥልም
- ዓላማ ካለህ ዓላማህን መሳት የለብህም

**ለማ**ኝ አያማርጥም፤ ማር አያኮመጥጥም
- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

**ለማ**የት የፈለገ ዐይኑን ይገልጣል
- ለሁሉም ነገር መሠረቱ ፍላጐት ነው

**ለማ**ያውቀው፣ፎገራ ዱሩ ነው
- የማያውቁትን ነገር ለማድረግ መሞከር በጣም አስቸጋሪ ነው

**ለማ**ያውቅሽ ታጠኝ
- ስለማውቅሽ አታታልይኝም

**ለማ**ይሞት መድኃኒት አለው
- ችግር የሌለበት ስለችግር አያወራም

**ለማ**ይሰጥ ሰው ፤ስጡኝ ማለት ማን አስተማረው
- ላም ያልዋበት ኩበት ለቀማ

**ለማ**ዕበል ወደብ ለነፋስ ገደብ የለውም
- ከአቅም በላይ የሆነን ነገር ለማቆም መሞከር ትርፉ ድካም ነው

**ለም**ላጭ የሰጡት ገላ አያምም
- ተስማምተው ያደረጉት ነገር አይከብድም

**ለም**ሽት መብራት፤ ለመከራ ጊዜ ብልሃት
- ችግር ከመድረሱ በፊት ለችግርህ መፍትሔ መፍጠር አለብህ

**ለም**ሽት መብራት፤ ለሥራ ብልሃት
- ሥራን ለማከናወን ዘዴና ብልሃት ያስፈልጋል

**ለም**ን ተክገፎ፤ አምላክን ይገፎ
- አምላክ እስካለ ያሰብኩትን ሁሉ ይፈጽምልኛል

**ለም**ን ያለው ስልቻውን፤ ጫን ያለው ኮርቻውን አያጣም
- የአምላክ ስጦታ የተጓደለ አይደለም

**ለም**ን ጊዜው ነቀዝሽ
- ምነው እንዲህ ፈጥነሽ መጥፎ ልትሆኝ ቻልሽ?

ለምኖ ለማኝ፣ ቆቤን ቀማኝ

- ከሌላ ለምኜ ያገኘሁትን ሌላው ለምኖ ወሰደብኝ

ለሞኝ ሰኔ በጋው፣ መስከረም ክረምቱ

- ሞኝ ማድረግ የሚገባውን ነገር በትክክል በወቅቱ አይሠራም

ለሞኝ ንገረው ምን ይሰማ ብዬ፣ ለብልህ ንገረው፣ ምን ይሳተው ብዬ?

- ሞኝ የሚነግሩትን አይሰማም፣ ብልህ ግን ነገሮች በሙሉ በቀላል ይገባዋል

ለሞኝ ከሣቁለት፣ለቅዘን ከሮጡለት

- ለሞኝ ፊት ካሳዩት ይዘረጥጥሃል

ለሞኝ ከሣቁለት፣ለውሻ ከሮጡለት

- ለሞኝ ፊት ካሳዩት ይዘረጥጥሃል

ለሞኝ ጉድጓድ አያሳዩትም፣ ቤት ነው ብሎ ይገባበታል

- ሞኝ ጠቃሚና ጎጂውን አያገናዝብም

ለሞፈር ቆራጭ፣እርፍ አይታየውም በግላጭ

- ባለማስተዋል በቅርብ ያለውን ነገር ሳይጠቀምበት ይቀራል

ለረዥም መንገድ አትሩጥበት፣ ለረዥም ነገር አትቸኩልበት

- በእርጋታ የሚሠሩት ሥራ ውጤታማ ይሆናል

ለራሱ አብዶ ይሮጣል፣ አትርሳኝ ብሎ ተከትሎታል

- ምንም የማይፈጽምልህን ሰው አታስቸግር

ለራሱ አያውቅ፣ሰው አይጠይቅ

- አጉል መኮፈስ

ለራሱ አያውቅ ነዳይ ፤ ቅቤ ለመነ ላዋይ

- ለራሱ አያውቅ ጠንቋይ መድኃኒቱን ሳዋይ

ለራሱ የማይረባ ፤ለሰውም አይረባ

- ወይ አይበላ ወይ ሰው አያስበላ

ለራሱ ጥላ፣ ለእግሩ ከለላ

- አለኝታ መከታ፣ ጋሻ

ለራስ ምታት ጨህበት፣ ለሆድ ቁርጠት ብላበት

- ተቃራኒ ምክር

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

- ራስ ወዳድ መሆንን ያመለክታል

ለራስ ከበጁ፣ አይታጡ ክደጁ

- ራስን መንከባከብ ከመጥፎ ሁኔታዎች ይጠብቃል

ለራበው ሰው ቆሎ፣ ለቁልቁለት በቅሎ

- ተስማሚ የሚሆን ነገር መምረጥ ትክክል ነው

ለራት የማይተርፍ ዳረጎት

- ብዙ የማይጠቅም ለሰውም የማይሆን ለራስም የማይሆን

ለርስት ሴቶች ሰንኳ ይሞቱበታል

- ለጥቅም ሲል የማይታገል አይኖርም



**ለ**ሰለባ የመጣ ልብስ ቢጥሉለት አይመለስ

- ሰውን ለመጉዳት ሆን ብሎ የተነሳን ሰው መመለስ ያስቸግራል

**ለ**ሰማይ ምሰሶ የለው፣ ለባዕድ ሥር የለው

- ባዕድ ምንም ቢያቀርቡት ዞሮ ያው ነው ያው ዘመድ ይሻላል

**ለ**ሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት

- ለቦና ጥጃ ውስ አያንሰውም

**ለ**ሰባቂ ጆሮህን አትስጠው

- ወሬኛን ማዳመጥ የለብህም

**ለ**ሰው ልጅ ከሚያበሉ፣ ለውሻ ልጅ ያብሉ

- በችግር ጊዜ ሰውን ለማይከዳ ውሻ ማብላት ይሻላል

**ለ**ሰው ልጅ ከማብላት ለውሻ ማብላት

- በችግር ጊዜ ሰውን ለማይከዳ ውሻ ማብላት ይሻላል

**ለ**ሰው ሞት አነሰው

- ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

**ለ**ሰው ሰው ነው ልብሱ

- የሰውን ችግር የሚያቃልል ሰው ነው

**ለ**ሰው ቢነግሩት መልሶ ለሰው፣ ጫር ጫር አድርጌ ዐፈር ሳልብሰው

- ምስጢር የብቻ የግል ነው

**ለ**ሰው ብሎ መሞት አምላክነት ያሻል

- ከራስ በላይ ነፋስ

**ለ**ሰው ብሎ ሲያማ፣ለእኔ ብለህ ስማ

- ነግ በኔ

**ለ**ሰው ብትል ትጠፋለህ፣ ለእግዜር ብትል ትለማለህ

- እግዚአብሔር የሚወደውን ነገር መፈጸም ጽድቅ ነው

**ለ**ሰው ከበሬታው ሰው፣ ለወጥ ማጣፈጫው ጨው

- ለሰው ሰው ነው ልብሱ

**ለ**ሰው የማይል ሰው፣ ሞት ሲያንሰው

- ለተቸገረ የማያዝን ሰው አያስፈልግም

**ለ**ሰው ጠላቱ፣ይወጣል ከቤቱ

- አንዳንዴ የተማመኑበት ዘመድ ጠላት ይሆንብሃል

**ለ**ሰይጣን አትስጠው ሥልጣን

- ጨካኝን ሰው አትሹመው

**ለ**ሰጭም አያንሰው፣ ለበይም አይደርሰው

- በስጦታው ያልረካ ሰው

**ለ**ሴት ልጅ እስከ አርባ ቀን ሞቷን ፤ ከዚያ ወዲያ ሀብቷን

- ክፉን ቀን እንደምንም ካለፉት መልካም ቀን ያጋጥማል

**ለ**ሴት ምክር አይገባትም

- ቢመክሯት የማትለወጥ ፍጥረት ነች

ለሴት ጠላ፤ ለፈረስ ቆላ
- ለሁለቱም አይስማማቸውም

ለሴትና ለጉም አይዘገኑም
- ሴትን ማመን አይገባም

ለስሟ መጠሪያ ቁና ለፋች
- የምትታወስበትን ተግባር አከናወነች

ለስሱ ፍትፍት እሳይቶ እበት ማጉረሱ
- ለገብጋባ መልካሙን ሳይሆን የማይሆነውን መስጠት

ለሸማኔ ማገጃ፤ ለሰት ማረጃ
- ተስማሚ የሆነ መሣሪያ ያስፈልጋል

ለሹመት ካልመከሩለት፤ ለጥርስ ካልከደኑለት
- ለመሾም ቅድሚያ ሰውየውን ማጥናት ያስፈልጋል

ለሹመት ያደለው፤ የለማኝ አለቃ ይሆናል
- ምንም ክብርና ዝና ለሌለው ቦታ መታጨት

ለሺ ፍልጥ ማለሪያው ልጥ
- ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

ለበሬ ወለባ፤ ለውሻ ገለባ
- ያልሆነ ሥራ መሥራት ምንም አይጠቅምም

ለበግ ደጋ፤ ለምቾት አልጋ
- በተገቢው ቦታ ተስማሚ ነገር

ለቡናሽ ቁርስ የለሽ ፤ ለነገርሽ ለዛ የለሽ
- ምንሽም ምንሽም አያምርም

ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ
- ባለጌ ውርደታም ስለሆነ ጥሩ እንደሠራ ሁሉ ይኩራራል

ለባብ እግር የለው፤ ለሞኝ መላ የለው
- መፍትሔ ለሌለው ነገር ብዙ አትጨነቅ

ለባዕድ የሰጡት ኮሶ፤ ይወጣል ደም ጎርሶ
- ከማይሆን ሰው ጋር የተዋዋሉት ውሎ አድሮ ችግር ማስከተሉ አይቀርም

ለቤት ሳማ፤ ለውጭ ቁጤማ
- ለቤቷ ጨቅጫቃ ለውጪ ሰው መሬት ነች

ለቤት ማገር፤ ለሰው አለቃ፤ ለነገር ጠበቃ ያስፈልገዋል
- አስፈላጊው ሁሉ በቦታው ላይ ቢገኝ ሕይወት የተሟላች ትሆናለች

ለቤት ባላ፤ ለችግር ነጠላ ያስፈልገዋል
- በችግር ጊዜ ብዙ ባይገኝም በተገኘችው በትንሿ ማዝገም የግድ ነው

ለቀላል ምስጢር መንገር፤ በቀዳዳ ጤፍ መቋጠር
- ምስጢር ለማይደብቅ ሰው አትናገር

ለቀማኛ የለውም እጅ፤ ለበቅሎ የለውም ልጅ
- እባቡን ሆዱን ፀይቶ እግር ነሳው



ለቀባሪው አረዱት
- ለሚያውቀው ሰውዬ ያላወቀ መስሏቸው ነገሩት

ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው፤ ቀንዱ ይከላከለዋል
- የራሱ ባህርይ ይወቀሰው

ለቀንጫ ሰምድ ያወጣል
- የማይጠበቅ ነገር

ለቂጠ ጨርቅ የለው፤ ቆንጆ ያባብላል
- እሱነቱን የማያውቅ

ለቅልብልብ እማት፤ ሲሶ በትር እላት
- መቅለብለቧ ስለማይቀር መመታቷ አይቀርም

ለቅሶ ሳለ ከቤት፤ ይሄዳል ከጐረቤት
- የቤተሰብህን ችግር ሳታቃልል የሌላን ሰው ችግር ለማቃለል አትሞክር

ለቅናት የለውም ጥናት
- ስሜታዊ ነገሮች ከስሜት የሚመነጩ እንጂ ከልምድ አይገኙም

ለቅዘን እግር እንስተውለት፤ ለውሻ ሽሽተውለት
- ለሞኝ ፊት ካሳየኸው ይዘረጥጥሃል

ለብልህ አይነግሩ፤ ለአንበሳ አይመትሩ
- ብልህ ፈጥኖ ስለሚረዳ የተንዛዛ ምክር ሊሰጠው አይገባም

ለብልህ አይነግሩ፤ ለድመት እያበሩ
- ብልህ ፈጥኖ ስለሚረዳ የተንዛዛ ምክር ሊሰጠው አይገባም

ለብዙ ጸሎት፤ማሠሪያው አቡነ ዘበሰማያት
- ማንኛውም ነገር ፍጻሜ ሊኖረው ይገባል

ለቦና ጥጃ ውስ አያንሰውም
- ጉዳት ያጋጠመው ሰው ለአደጋ የተጋለጠ ነው

ለተማሪ ቆሎ፤ ለወታደር በቅሎ
- አስፈላጊ ነገሮች ናቸው

ለተሚጋች መዘዘኛ፤ የዳኛ ትዕግሥተኛ
- ከነገረኛ ሰው ጋር ሲኖሩ ትዕግሥት ያሻል

ለተረታ ያበደረ፤ እሳት ጨመረ
- በማይሆን ቦታ ገንዘብንና ጉልበትን ማዋል ፋይዳ የለውም

ለተራብ በግብር፤ ለተበደለ በነገር
- ሰውን እንደየችግሩ እያዩ መደገፍ ተገቢ ነው

ለተሸሸገ ምግብ፤ የተሸሸገ ሆድ አይጠፋለትም
- የሰለቱት ነገር መጥፋቱ አይቀርም

ለተሾመ ይሟገቱለታል፤ ለተሻረ ይመሰክሩበታል
- ጥቅም ፍለጋ

ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው
- ሰውን ይተቻል ነገር ግን የሥራ ችሎታ የለውም

ለተባባሰው ማጭድ አታውሰው
- የተከፋን ሰው አታበሳጨው

ለተቸገረ የማያዝን እምብርት የለውም
- ለችግረኛ የማያዝን አረመኔ ነው

ለተንኮለኛ ሲሉ ይለበለባሉ፤ ለቅን ይፈርዳሉ
- ሁሉም እንደሥራው

ለትኋን ልጓም ማጉረስ፤ ላፈኛ ሰው መመለስ አይቻልም
- ከተንኮለኛ ሰው አትጨቃጨቅ

ለቸኮለ ዋንጫ አስጨብጠው
- ችኩል ባህሪውን እንዲተው በዘዴ አስተምረው

ለኃጥአን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል
- የጠንቀኛ ፈስ ዓይን ያፈስ
- የመጥፎ ሰው ጦስ ለሌላው ይተርፋል

ለነገረኛ ሰው ፤ጀርባህን ስጠው
- መልስ አትስጠው

ለነገረኛ ነገር ተውለት ፤ ለሆዳም እህል አቅርብለት
- መተው ነገሬን ከተተው

ለኔ ነግ በኔ
- በሌላ የደረሰው ነገም በኔ ይደርሳል ብለህ አስብ

ለንጉሥ ያልረዳ ፤ከባህር ያልቀዳ
- የምትጠቀምበትን ስልትና ዘዴ ፀውቀህ ተገኝ

ለንፉግ ሰው፤ የገበያ መንገድ ይጠበዋል
- ሌላ ሰው እንዲጠቀም አይፈልግም

ለአምላክ ልንገረው፤ለማያስቀረው
- ችግርን በደልን ዐይቶ ተመልክቶ መፍትሔ የሚሰጥ አምላክ ብቻ ነው

ለአበባ የለው ገለባ
- መልካም ለሆነ ነገር እንከን የለውም

ለአቤቱታ ፤ የለው ይሉኝታ
- የተበደለ ሰው በደሉን አቤት ከማለት አይመለስም

ለአንበሳ አታበድር፤ካበደርክ አትጠይቅ
- እኩያህ ካልሆነ ሰው ጋር አትዋዋል

ለአንዱ የዘነበለት ፤ለሌላው ሳያካፋ አይቀርም
- ሁሉም እንደሥራውና እንደልፋቱ መጠን ማግኘቱ አይቀርም

ለአንድ ያሉት፤ ለሁለት ይተርፋል
- በረከት አለው

ለአኩራፊ ምሳው እራት ይሆነዋል
- አኩራፊ እራሱን ነው የሚጎዳው

ለአዋጅ ነጋሪት፤ ለጥጥ ልቃቂት
- ሥራን ለማከናወን መሣሪያ ያስፈልጋል



ለእፊ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል
- ላያስችል አይሰጥም

ለእፍታ፤ የለውም ፋታ
- ምንም ጊዜ የለውም

ለእፍ ዳገት የለውም
- ምንም ችሎት ሳይኖረው አስተያየት የሚሰጥ

ለእሳት ዕንጨት፤ ካልነፈጉት አይጠፋም
- ለተገቢው ነገር ተገቢ ነገር መደረግ አለበት

ለእሳት ውኃ፤ ለጠጉር ቡሃ
- ለጥሩ ነገር ጥሩ ነገር አለው ለመጥፎም መጥፎ አለው

ለእሳት ፍላት፤ ለጮማ ስባት
- ነገርን ካልተውት እየተባባሰ ይሄዳል

ለእበጥ ፍላት፤ ለዕንጨት እሳት
- ለሁሉም የበላይ አለው

ለእባብ እግር የለው፤ለሞኝ መላ የለው
- ሞኝ የሚሠራው ነገር ሁሉ በግምት ነው ብልሃትን አይጠቀምም

ለእብለት ሥር የለው ፤ለባብ እግር የለው
- ሥር የሌለው መነሻ የሌለው ነገር ማውራት ትርፉ ውርደት ነው

ለእውነት ማማ ፤ ለውሸት ጨለማ
- የማታመንን ነገር በይፋ ማድረግ አያሳማም

ለእጅ ርቆ፤ ለዓይን ርቆ
- ካሉበት ቦታ በጣም ርቆ የሚገኝ

ለእግሩ የተጠየፈ፤ ለቂጡ አተረፈ
- ቀላሉን ነገር ሲጸየፍ የባሰ ነገር ደረሰበት

ለእግሩ የተጠየፈ፤ ለእራሱ አተረፈ
- ቀላሉን ነገር ሲጸየፍ የባሰ ነገር ደረሰበት

ለእግር የፈሩት ለቂጥ ይተርፋል
- ለቀላል ነገር ሲጸየፍ የባሰ ነገር ገጠመው

ለእግዚአብሔር የቀነቀነ ለጽድቅ፤ ለጌታ ለንጉሥ የቀነቀነ ለወርቅ
- እግዚአብሔር የሚወደውን ተግባር የሚፈጽም ይጸድቃል
- አለቃው የሚወደውን ተግባር የሚፈጽም ይሾማል ይሸለማል

ለከሳ ጥላ፤ ቢርብህ ብላ
- የሚጠቅምህን አስበህ አድርግ

ለከሳሽ የለው ምላሽ
- አንዱ ማንሳት የፈለገውን ጉዳይ ለምን አነሳህ አይባልም

ለካህን ጥምቀት፤ ለገበሬ ግንቦት
- ሁሉም የሚወደውን ነገር ሲያገኝ ደስ ይለዋል

ለኮ መሳቢያ፤ ወፍጮ ማለሚያ
- ማንኛውም መሣሪያ የሚያከናውነው ተግባር ይኖረዋል

ለወሬ ወዳጁ ወሬ፤ ለመነኩሴ ጥሬ
- ሁሉም የሚወደውን ነገር ሲያገኝ ደስ ይለዋል

ለወሬ፤የለው ፍሬ
- ከወሬ የሚገኝ ጥቅም የለም

ለወሬ የለው ፍሬ፤ ለአበባ የለው ገለባ
- ከወሬ የሚገኝ ጥቅም የለም

ለወሬ የቸኮለ እናቱን በመንገድ ላይ ያረዳል
- ችኩል ሰው መጥፎ ነገር ሲገጥመው ይችላል

ለወርቅ ያሉት አንገት ለአሽከት
- ጥሩ ደረጃ ይደርሳል የተባለ ያልታሰበበት ቦታ ላይ ወድቆ ቀረ

ለወታደር ሰፊ መንደር፤ ለወንዲላ መልካም ዱላ
- ለሥራ አመቺ ቦታ፤ለአስቸጋሪ ደግሞ ቅጣት

ለወዳጁ ማር ወለላ፤ ለጠላቱ አመኬላ
- የሚወዱትን ይወዳሉ፣ይጠቅማሉ፤ የሚጠሉትን ይጠላሉ፣ይጐዳሉ

ለወዳጅና ለዐይን ትንሽ ይበቃዋል
- ወዳጅ በቀላሉ ስለሚቀየም በጥንቃቄ መያዝ ይገባል

ለወጡም አዘኑለት ፤ አንዳንድ ጊዜ ደረቅ ጉረሱለት
- ቁጠባ መልካም ነው

ለወጡም አዘኑለት፤ ከደረቁም ብሉለት
- ቁጠባ ጥሩ ነው

ለወጥ የሚሻል ቅልውጥ
- መልካም ወጥ ለመብላት በየቤቱ መቀላወጥ

ለዋሶ አፍ የለው፤ ለጉንዳን ደም የለው
- አንዴ ከሆነ ወዲያ ዝም ብሎ መቻል ነው

ለዋንጫ ቡሽ፤ ለውኃ ጉሽ የለውም
- አንድን ነገር አልሆነ ቦታ ላይ መፈለግ

ለውሻ ምሳ የለው ራት ብቻ
- ተመጽዋች የሰጡትን ብቻ ይቀበላል

ለውሻ ሞት፤ ፊት አይነጩለትም
- ብዙም ማዘን አይገባም

ለውሻዬ ያልሁትን ልጄ ቢበላብኝ አልወድም
- አንዴ ለአንዱ ያሰብኩትን ነገር ለማንም ቢሆን አልሰጥም

ለውሽማ ሞት ፊት አይነጩለት
- ውስጥ ውስጡን አሚያብከነክን ይፋ የማይወጣ ኃዘን

ለውጡኝ ባይ የሚሻለውን ዐውቆ
- ጠቃሚውን ለይቶ መወሰን /አጉል ብልጠት/

ለዓይነ ሥውር መስታወት
- የማይጠቅም ነገር



ለዓይን የሚከፋ፤ ለአፍንጫ ይከረፋ
- ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል

ለዕውር ዝማሜ፤ ለመላጣ ጋሜ
- የማይቻል ነገር ይሆናል ብሎ ማሰብ

ለዘመዴ ያዝናል ሆዴ
- ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

ለዚህ ሆዴ ጠላኝ ዘመዴ
- ዛሬ ቢበሉ ሆድ ነገ አየሁ አይልም

ለዝናቡ ጌታ ፤ ውኃ ነሱት
- የገዛ ንብረቱን ከለከሉት
- የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው

ለይቶት አባ ንጉሧ
- ትንሿን ነገር አግዝፎ የሚመለከት ሌላውን ዓይቶ የማያውቅ ሰው

ለይቶ እንደፈፋ፤ አንጓሎ እንዳረፋ
- የጠሉትን ከአጠገብ ማራቅ

ለደህና ሰው ዋጋ አነሰው
- መልካም ሰው ቁጥሩ በርከት ቢል ምን አለ

ለደህና ሰው ውሸት ፤ ለጅብ እሾት
- የማይሆን ነገር

ለደብተራ፤ መቋሚያና ጭራ
- ሁሉም የሚወደውን ነገር ሲያገኝ ደስ ይለዋል

ለደደብ ማስረዳት፤ ድንጋይ ቅቤ መቀባት
- ለማይገባው ሰው ማስረዳት ትርፉ ድካም ነው

ለደግ ንጉሥ ዕለት ዕለት ማልቀስ
- በጾም በጸሎት ዕድሜ እንዲሰጠው ወይም ነፍሱን እንዲምራት ማዘን

ለዳርቻው ሲሳሱ፤ መካከሉን ተነሱ
- የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

ለዳባ ለባሽ ፤ ነገርክን አታበላሽ
- መፍትሔ ለማይሰጥህ ሰው ችግርህን አትግለጽ

ለዳኛ አመልክት፤ እንዲሆን መሠረት
- ፍርድ ለሚሰጥ ዳኛ አመልክት እንጂ በሌላ መንገድ አትሞክር

ለዳኛ የነገሩ በርጥብ ያቃጠሉት
- ነገሩ ሳይባባስ ቶሎ መፍትሔ መፈለግ ይገባል

ለዳኛ ዳኛ አለው፤ለአንበሳ ተኩላ አለው
- ሁሉም የበላይ አለው

ለድሃ ማን ሰጠው ውኃ
- ለድሃ ትኩረት የሚሰጥ ሰው የለም

ለድህነት የፈጠረው ቢነግድ አያተርፈው
- ለድካም የጣፈው ቢነግድ አያተርፈው

ለድሪ ያሉት አንገት ስአሸንክታብ

- እንደተመኙት አይገኝም

ለድካም የጣፈኝ፤ ብነግድ አያተርፈኝ

- ለድህነት የፈጠረው፤ ቢነግድ አያተርፈው

ለዶሮ ሲነግሩ ምጥማጥ ይሰማል

- ለወዳጅ የሚነግሩት ሚስጥር ጠላት ሊሰማው ይችላል

ለጆሮ ጥርስ፤ ለሆዳም ስስ

- አያጋጥም

ለገላጋይ ደም የለውም

- መልካም አሠራ ብሶ አደጋ ላይ ይወድቃል

ለገበሬ መልካም በሬ

- ለሠራተኛ ሰው ጥሩ መሣሪያ ያስፈልገዋል

ለገቢህ ተንገብገብ

- ለምታገኝበት ጉዳይ ትኩረት ስጥ

ለገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ

- የበላይና የበታች በዚያ ቦታ የለም

ለገደለ ጉፈሬ፤ ላረጋገጠ ወሬ

- ሁሉ በትክክል ሥራ ላይ ሲውል

ለገዳም የረዳ፤ አይጐዳ

- ገንዘቡን ለመልካም ጉዳይ ያዋለ አይጐዳም

ለጉንዳን ደም የለው፤ ለዝንብ ቤት የለው

- ማንኛውም ሰው ተግቶ ከሠራ ገንዘብ ማግኘት ይችላል

ለጉንዳን ደም የለው፤ለገንዘብ ቤት የለው

- ማንኛውም ሰው ተግቶ ከሠራ ገንዘብ ማግኘት ይችላል

ለጋስ ቢሰግስ፤አበደረ እንጂ አልሰጠም

- ነገ እሱም የእጁን ያገኘዋልና

ለጠላትህ እንደ ዳቦ፤ እስኪገምጥህ አትመቸው

- ጠላት ሲደጠቃህ በሚችልበት ቦታ፣ እራስህን አታመቻችለት

ለጠቢብ አንድ ቃል ይበቃል

- ጠቢብ ቶሎ ይገነዘባል

ለጠጪ ሰው የመጠጥ ወሬ አውራው

- በሚወደው በሚያፈቅረው መንገድ ሄድለት

ለጥልና ለዳኛ ያለው ገንዘብ አፋፍ ይቆደል

- ውጣ ያለው ገንዘብ ግድግዳ ሲፎክት ያድራል

ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

- ለታቀደው ነገር ማዋል እርካታ ይሰጣል

ለጥርጣሬ፤ ምንጣሬ

- ያልጠረጠረ ተመነጠረ



**ለጥቅም** ሲታጠቁ፤ ከጎኑ ይጠንቀቁ

- ተቀናቃኝ ስለሚያጋጥምህ ጥንቃቄ አድርግ

**ለጨለማ** ጊዜ መብራት፤ ለመከራ ጊዜ ብልሃት

- ችግርን ለመቅረፍ ዘዴ እና ብልሃት መፍጠር ያስፈልጋል

**ለጨቅጫቃ** ስው ከማበደር፤ ይሻላል በእጅ ማሳደር

- በሰዓቱ ለማይመልስ ሰው ገንዘብ ማበደር አያስፈልግም

**ለጭ**ሰኛ መሬት፤ ለሣር ቤት ክብሪት

- አብረው የማይሄዱ ነገሮችን አታቀራርብ

**ለጾም** ግድፌት፤ ለበዓል ሽረት

- ጾምንና በዓልን ማክበር ይገባል

**ለፈ**ረስህ አንገት፤ ለጋሻህ እንብርት

- የሚያመችህን አስቀድመህ አስብበት

**ለፈሪ** ሜዳ አይነሱም

- ፈሪ የሚያደርስብህ አደጋ ስለሌለ ተወው እንደፈለገ ይሁን

**ለፈሪ** ይበቃል ፍርፋሪ

- ፈሪን በፍርፋሪ ታታልለዋለህ

**ለፍቅር** ብተኛ ለጠብ አረገዘች

- መልካም ባስብላት ተንኮል ሸረበችብኝ

**ለፍየል** ሕመም በሬ ማረድ

- ትንሽ ነገር አድናለሁ ብለህ ትልቁን ማጥፋት

**ለፍየ**ል ስም አውጣ ቢለው፤ ሞት አያድርስ አለው

- ትንሽ ነገር ለሚያስገኝ ጉዳይ ብዙ መጨነቅ

**ለፍየል** ቆላ፤ ለሙክት ባቄላ

- ተስማሚውን ፈልጐ ማገናኘት

**ሊሸ**ገር ቢያምረው ይዋኛል፤ ሲሚገት ቢያምረው ይዳኛል

- የሚያስፈልገውን ሁሉ በስልትና በዘዴ ይጠቀማል

**ሊበ**ሉት የፈስጉትን እሞራ፤ ይሉታል ጅግራ

- ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት

**ሊወጋ** የመጣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም

- የሚያጋጥምህን እንደሁኔታው ተጋፈጠው እንጂ አትሽሽው

**ሊያ**ልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ

- አትቸኩል ትዕግሥት ይኑርህ

**ሊያ**ሰቡት አይገድም

- የሚያስጨንቅ የሚያሳስብ ነገር አይጠፋም

**ሊ**ጣላ የመጣ ሰበብ አያጣም

- ጠብ ያሻ መኮንን የዶሮ ሻኛ አምጡልኝ ይላል

**ላህያ** ማር አይጥማትም

- ጥሩ ነገር ቢቀርብስትም አይፈልገውም

ላህያ ያልከበደው፤ ለመጫኛ ከበደው
- የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ

ላህያ ፈስ፣ አፍንጫ አይዙለትም
- ለውሻ ሞት ፊት አይነጩለትም

ላላው ቅንጭብ ያረግዳል
- ላለው ሰው ሁሉም ያሽረግዳል

ላለፈ አይጸጸቱ፤ ለሚመጣው አይበለጡ
- ካለፈው ስሕተት ተምረህ ለአሁኑ መጠንቀቅ

ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራለትም
- ላለፈው ነገር መቆጨት አይገባም

ላለፈው ጸሎት ከንቱ ጩኸት
- ላለፈው ነገር መቆጨት አይገባም

ላሊበላ ሄደሽ ከሕንፃው ብትሰፍሪ አይገኝም ጽድቅ አለባህሪ
- መልካም ሥራ ካልሠራሽ በቤተክርስቲያን በመገኘት ብቻ ጽድቅ አይገኝም

ላሊበላ አደራውን አይበላ
- ወደኋላ አይልም ታማኝ ነው

ላሊበላ የቃሉን አይበላ
- ወደኋላ አይልም ታማኝ ነው

ላሊበላን ካላጠገቡት ይጮኻል፤ ሎሌም ካልሰጡት ይከዳል
- ሁሉንም እንደየባህርይው መያዝና መንከባከብ ተገቢ ነው

ላላወቀው ፎገራ ዱሩ ነው
- ባላወቁት ነገር አጥብቆ መከራከር ተገቢ አይሆንም

ላላየው የሚያስገርም ለሰማው የሚያስደንቅ
- አዲስ ነገር መገኘቱ

ላላዩ ልጅ ፤ ዳቦ ፍሪዳው
- ለመሃን እማዩ ለአገልጋይ እትዬ ብርቋ ነው

ላመት ልብስ፤ ለአለት ጉርስ
- ሕይወቱን ለማቆየት ያህል

ላሜ ቦራ የልጆቼን ነገር አደራ
- ልጆቼን አሳድጊልኝ

ላሜ ወለደች
- የተመኘሁትን አገኘሁ

ላም ሲበዘብዝ ፤ ጭራዋን ያዝ
- የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም አብረህ ዝረፍ

ላም በረቱን የሰው ልጅ አባቱን አይረሳም
- ሁሉም የራሱ የሆነውን አይዘነጋም

ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ
- ምንም የማይገኝ ነገር ፍለጋ የተገባቢጦሽ ሥራ መሥራት



ላሆ ነጂዋን እንጂ ጌታዋን አታውቅም
- በሩቁ ካለ ነገር ይልቅ በቅርብ ስላለ ነገር የተሻለ ዕውቅና ይኖራል

ላሆ አሰች በደረጣ ወተቷ ምን ይነጣ
- እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ እህል የሚደርሰው በፍልሰታ

ላሆ አሰኝ በሰማይ ወተቷንም አሳይ
- እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ እህል የሚደርሰው በፍልሰታ

ላሆ አሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት
- አስቸጋሪና አስጨናቂ ነገር

ላሆ ከወንዙ ልጅ ከቦዝ (የተናቀ ቦታ)
- ላምን መንከባከብ ይገባናል ልጅን ብትንከባከበውም ከመጥፎ ቦታ ከመድረስ ወደኋላ አይልም

ላሆ የዋለችበትን ትመስላለች
- ሰው ኑሮውን ይመስላል

ላሳር የጣፈው ፤ቢነግድ አይተርፈው
- ይታደሷል እንጂ አይታገሉም

ላታመልጠኝ አታሩጠኝ
- ምን ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ

ላታመልጥ አትሩጥ
- ምን ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ

ላታገኝ አትመኝ፤ ላታጣ አትቆጣ
- በምኑም በምኑም እራስህን አታስጨንቅ

ላትከፍል አትዋስ፤ላትደርስ አትገሥግሥ
- የማይሳካልህን ነገር አትሞክር

ላንበሳ አይመትሩ ለዐዋቂ አይናገሩ
- ለዐዋቂ ምክር አያስፈልገውም

ላንደ ብርቱ ፤ሁለት መድኀኒቱ
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

ላንደ አልሚ፤ዘጠኝ ቋሚ
- ሴት ሲበዛ ጎመን ጠነዛ

ላንድ አራሚ፤ ዘጠኝ ቋሚ
- ሴት ሲበዛ ጉመን ጠነዛ

ላንደ ጭቃ አገር ዘጠኝ ምሰሶ
- ሴት ሲበዛ ጉመን ጠነዛ

ላዋቂ ምክር ፤ላላዋቂ በትር
- ሁሉን እንደባህርይውና እንዳስፈላጊነቱ

ላዋቂ ቦትወቅበት፤ለረኛም አትከንዳበት
- ከዐዋቂ በላይ አውቃለሁ ብለህ አትሞክር

ላያሸንፉት መታገል፤ ትርፉ ገደል
- ዕያወቁ አለቁ ነውና የማይረቱበትን ነገር ችላ ማለት ይገባል

ላያቱ ዕዳ ፤ላማቱ ፍሪዳ
- አስመሳይ ይዩልኝ ባይ

ላያጠግቡ መጋበዝ ላይገድሉ ካራ መምዘዝ
- የማያደርጉትን አደርጋለሁ ማለት ያዋርዳል

ላያጥብ አይሰብስ ፤ላያርም አያርስ
- የኋላውን ችግር ተረድቶ ራስን መቆጠብ

ላይሆን ቤት፤ በበዓል ስፌት
- ጠብ ላይል ከንቱ ልፋት

ላይሆን ዘመድ ፤ገንዘቤንም አልስድ
- ላይጠቅመኝ ነገር ገንዘቤን አላባክንም

ላይሉኝ ቸር፤ በየቦታው ስፈነቸር
- ማንም ላያመሰግነኝ ስለፋ ከረምኩ

ላይሉኝ ወሶ ደርሼ ነበር ከረጋ ለቅሶ
- ማንም ላያመሰግነኝ በከንቱ ለፋሁ

ላይምረው እማስነው፤ ላይበላው አበላሸው
- ላይድን በከንቱ ልፋት

ላይሞት ይፈራል፤ላይድን ይሸሻል
- መሞቱ ላይቀር ብዙ ተንገላታ

ላይቀር ሞቱ፤ መንጠራወቱ
- መሞቱ ላይቀር ብዙ ተንገላታ

ላይቀር ሣቁ ፤ ችኩ
- ሥራው ላይቀርልሽ ጊዜ አታባክኚ

ላይቀር ጣጿው አታብርጂው
- ሥራው ላይቀርልሽ ጊዜ አታባክኚ

ላይበላው ፤አበላሸው
- ላይሆንለት ከንቱ ሙከራ

ላይታች አይፈርድ፤ ላያተርፍ አይነግድ
- ሁሉን ፈርቶ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ

ላይችል አይሰጥም፤ ላይጠግን አይሰብርም
- ሁሉን ነገር አሟልቶ አስማምቶ ይሰጣል ቸሩ እግዚአብሔር

ላይንና ለወዳጅ ጥቂት ይበቃል
- የሚዋደዱ ሰዎች በጥቂት ነገር ስለሚጣሉ መከባበር አለባቸው

ላይን የሚከፋ ለአፍንጫ የሚከረፋ
- የማይፈልጉት የማይመኙት ነገር

ላይኛው ከንፈር ለከርከር ታችኛው ከንፈር ለምስክር
- ሁሉም እንዳመቺነቱ

ላይዘሩ አያርሱ፤ ካላረሱ አይጉርሱ
- ለዓላማው ተግቶ የሠራ በውጤቱ ይደሰታል



ላይፈሩ ቁጣ፤ከዕብደት አንድ ነው
- ከንቱ ልፋት

ላነልጋይ ትዕግስት፤ለባለቤት መጠቃት
- ለገቢህ ተንገብገብ /ለሠራተኛ ትዕግሥትን፣የቅርብ ሰውን መጠቃት ማንም አይወድም

ላነሩ እንግዳ፤ ለሰው ባዳ
- በአካባቢው ታይቶ የማይታወቅ

ላነሩ ፈደል እንግዳ፤ ላባቱ ቋንቋ ባዳ
- ያልታየ፣ያልታወቀና ያልተለመደ

ላነሬ ሰው እንኳን ነጋሪት አታሞ አይሰጠው
- ላያውቅበት ፣ላይጠቀምበት ምን ይፈይድለታል

ላጠፋ ምህረት፤ ላጣ ቸርነት
- በዓምላክ ዘንድ የተወደደ ተግባር

ላፈኛ ሰው መመለስ ፤ ለትኋን ልጓም ማጉረስ
- ጠቀሜታ የሌለው ትርፍ ድካም ብቻ

ላፏላ ያለወጉ ፈላ
- ያለጊዜው እለሁ እሉሁ ማለት

ሌሊት የምክር እናት
- ተኝተው ያሰቡበት ነገር ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው

ሌላው ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ
- ነግ በኔ

ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል
- ልማደኛ ልማዱ አይለቀውም

ሌባ ቢያዩኝ እሥቅ፤ ባያዩኝ እሰርቅ
- ራስን ሳያጋልጡ ለመጠቀም መሞከር

ሌባ ባይሰርቅ፤ ዳኛም ባይገድ
- የሌባ መኖር ዳኛ እንዲኖር አስገደደ

ሌባ ተይዞ ዱላ ጥየቃ
- በትር ከእጅህ አባብ ከእግርህ

ሌባ እና ሌባ ተጣሉ በሰው ገለባ
- በሰው ገንዘብ መጣላት

ሌባ እናት ልጅዋን አታምንም
- ተንኮለኛ ሰው እራሱን አያምንም

ሌባ ውሻ ባፉ ሊጥ ፤በወገቡ ፍልጥ
- አዋራጅ ተግባር

ሌት ለአራዊት ቀን ለሠራዊት
- ሁሉም በየተወሰነለት ጊዜ መጠቀም

ሌት ከጅብ፤ቀን ከሕዝብ
- በሁሉም ቦታና ጊዜ የሚገኝ

ልሒድ ልሒድ ባይ፤ ስንቅ አጉዳይ
- ማድረግ የሚገባውን ማድረግ እንጂ ማዘግየት ቀውስ ይፈጥራል

ልማ በሥልሱ፤ ጥፋ በሥልሱ
- ምስክርነት በሦስት ሰው ይጸናል

ልማድ ሲቀር ፤ ምለህ ቅበር
- ያስወገድከውን ዓመል እንደገና ልትመለስበት አይገባም

ልማድ ከሰይጣን ይከፋል
- መጥፎ ልማድ ለመተው አስቸጋሪ ነው

ልማድ ይከብዳል ከግንድ
- መጥፎ ልማድ ለመተው አስቸጋሪ ነው

ልበ ሰፊ፤ ነገር አሳላፊ
- ትዕግስተኛ መሆን አስፈላጊ ነው

ልበ ሳምባ ዶሮዬ /በደረቱ አካባቢ ቀይ የሆነ/
- የማይሆነውን በመተው

ልቡ ለታመመ በመረቅ አትስጠው
- መፍትሔ የማሆን ነገር እንጂ አደጋ የሚጋብዝ ነገር አትፈጽም

ልቡ ነጭ ያቦካል
- ምኞቱ ሰፊ ነው

ልቡ ከቂም ከበቀል ፤ ቃሉ ከመበደል ፤ እጁ ከመግደል
- ጨካኝ ሰው ነው

ልባልማ ታጥቆ አዛባ፤ ሉሪ አውልቆ ፈረስ ጋለባ
- ተገቢ ያልሆነ ነገር መፈጸም አይገባም

ልባብ መሳቢያ፤ ልጓም ማቆሚያ
- እያንዳንዱ የራሱ ተግባር አለው

ልብ ሲያውቅ ፤ ገንፎ ያንቅ
- ዕያወቁ አለቁ

ልብ ሲያውቅ ጥርስ ከደመኛው ጋር ይሥቃል
- ለመኖር ሲባል ከአባት ገዳይ ጋር ተግባብቶ ይኖራል

ልብ ሲፈቅድ መግደርደር፤ እራስን መግደል
- ስትግደረደሪ ጾምሽን እደሪ

ልብ ሳይገዙ ነገር አያብዙ
- ድፍረቱ ሳይኖርህ አደርጋለሁ አትበል

ልብስ በውኃ፤ ገንዘብ በድሃ
- ለማትፈልገው ነገር ማስወገጃ ዘዴ ፈልግ

ልብስ በየፈርጁ ይለበሳል
- ሁሉንም እንደየጸባዩ

ልብስ ይፈጃል ሌት መልበስ፤ወጥ ይፈጃል መጎራረስ
- በቁጠባ አለመጠቀም ለችግር ይዳርጋል



ልብና ነፋስ ከሁሉ ያደርሳል
- አንድ ነገር ለማከናወን ቆራጥ መሆን ያስፈልጋል

ልብ እንቅርት ይመኛል
- አንካሳ ልቡ እየሩሳሌም አሳቡ

ልብ ከጉንጅ ፤ትምህርት ከደጅ
- በቅርብ እያለ በሩቁ ማሰብ

ልብ ካዘነ እንባ አይገድም
- ከልብ ከሆነ ማድረግ አያቅትም

ልብ ካጥባቂ፤ ፈረስ ይስባል
- ልብ ከማንኛውም በላይ ድፍረትና ፍላጐት አለው

ልብ የሌላት ውሻ ፤ ማር ትቀላውጣለች
- ሲሆን የማይችለውን ነገር መመኘት

ልብ የሚገኝ በስልሳ፤ ገንዘብ የሚገኝ በሰላሳ
- በወጣትነት ገንዘብ ይገኛል ግን በአግባቡ አይጠቀሙበትም

ልብ ያለው፤ አገሩ ሰማይ ነው
- ቆራጥ የፈለገውን ማድረግ ይችላል

ልብ ያሰበውን አፍ ይናገረዋል፤ ዐይን ያየውን እጅ ይሠራዋል
- እርስ በርስ በመደጋገፍ መሥራት መልካም ነው

ልብ ደስ ሲለው ፊት ያበራል፤ ልብ ሲያዝን ፊት ይጠቁራል
- መከፋቱንና መደሰቱ በፊቱ ይታወቃል

ልብ ዳኛ ዐይን እረኛ
- ያዩትን ለመፈጸም የሕሊና ፈቃድ ያሻል

ልባን እሞራ በልቶታል
- የነገሯትን ትረሳለች

ልታስቸግር አታበድር፤ ላትከፍል አትበደር
- የማይሆንልህን ከወዲሁ በመገመት ወስን

ልታይ ልታይ ማለት፤ ሽሽጉኝ ሽሽጉኝ ያመጣል
- እኔ ነኝ እኔ ነኝ ማለት ኋላ መዋረድን ያመጣል

ልትደርቅ የደረሰች ምንጭ ጭል ጭል ትላለች
- ልታልፍ የደረሰች ሕይወት በትንሹ እሰሁ እሰሁ ትላለች

ልክን ማወቅ ፤ ከራስ ጋር መታረቅ
- አቅምን ማወቅ ጥሩ ነው ታላቅ ችሎታ ነው

ልዩ ሥጋ ፤ በመንጋጋ
- ሁሉን እንዳመቺነቱ

ልደት ሲከበር ሞት አያፍር
- ደስታና ኃዘን ጎን ለጎን ናቸው

ልጁን በራብ፤ የእንጀራ ልጁን በጥጋብ
- የማይታመን የተገላቢጦሽ ሥራ

ልጄ መዝሩጥ፤ አባቴ እንደበላህ ሩጥ
- እንደውለታህ ፤ ለእኔ እንዳደረክልኝ መጠን

ልጅህንም አባትህንም ስታጎርስ፤ ለአንዱ ታበድራለህ ላንዱ ታካፍላለህ
- ውለታህን መመለስ አለብህ የተቸገረውን መርዳት አለብህ

ልጅህንና አትክልትህን ተጠባበቅ ጐረቤትክን
- ሁሉንም እንደሁኔታውና እንደችሎታው ተንከባከባቸው

ልጅ ለሣቀለት፤ ውሻ ለሮጠለት
- እንደፍላጐቱ ማሟላት

ልጅ ለእናቷ ምጥን አስተማረች
- የተገላቢጦሽ ሆነ

ልጅ ለወለደው፤ ሙቅ ላሞቀው
- ሁሉም ያገለገለውን ይጠራል

ልጅ ሲያረጅ አባት ይጠራል
- ውለታውን ይመልሳል

ልጅ ሲያባብሉት ያለቅሳል
- ሥነ ሥርዓት የሌለው ባለጌ

ልጅ ቢያስብ ምሳውን ፤አዝማሪ ቢያስብ ጠላውን
- ሁሉም እንደየልማዱና ፍላጐቱ

ልጅ ተውር፤እህል ተጉራንጉር
- የሚጠቅም ነገር የሚገኝበትን አካባቢ ተመልከት

ልጅቱ ለቤተሰቦቿ እንደንብ ናት
- ታታሪ ሠራተኛ ናት

ልጅ ታርጣጣ፤ እህል ከዘባጣ
- መልካምና የተሻለ ነገር የሚገኝበትን ቦታ መርምር

ልጅና ቁስ በሰው ገንዘብ ያለቅስ
- ሁለቱም የሚኖሩት ሰው በሚሰጣቸው በመሆኑ

ልጅና እህል እያደር ይበስላል
- እያደገ ሲመጣ አስተሳሰቡ እየሰፋ ይመጣል

ልጅና ወረቀት የያዘውን አይለቅም
- ያኖሩት ነገር መልካም

ልጅና ጉንዳን ሁልጊዜ እንደተጠቃ ነው
- የሚሠሩት ሥራ ቀላል አየመሰላቸው ከሥር ስለሆኑ መመከት አይችሉም

ልጅና ጦጣ ፤ውኃ ይጠጣ
- ለልጅ እትጨነቁለት እንደዕድሉ ያድጋል

ልጅና ጥሬ አይተጣጡም
- የሚዋደዱ እይተጣጡም

ልጅና ፊት አይበርደውም
- መቋቋም ስለሚችል ባይለብስም ምንም አይደለም



ልጅን መርገምና ራስን መሸናት ተመልሶ ጉዳት
- ተንጋለው ቢተፉት ተመልሶ በፉ

ልጅን በጡት ፤እህልን በጥቅምት
- ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በእርጥቡ

ልጅ አባቱን ፤ እይብ እንቱን ይመስላል
- ለሁሉም መሠረቱ ምንጩ መነሻው ነው

ልጅ አባቱን ገደለ ቢለው ፤ የኔ ልጅ እንዳይሰማ አለው
- ጤፍ እጎደለ ቢለው ገብስ እንዳይሰማ አለው

ልጅ አይወልድ አንድ አይፈርድም
- የአንድ ሰው ፍርድ ፍርድ አይባልም

ልጅ አንደአባቱ ፤ ሰው እንደቤቱ
- ሰው አንደቤቱ እንጂ እንደጐረቤቱ አይኖርም

ልጅ ከደረሰ ቤት ፈረሰ
- ኃላፊነት ስለማይሰማው ጥፋት ያስከትላል

ልጅ ከዋለበት ሽማግሌ አይውልም
- የእንዱ ለአንዱ ሲሆን አይችልም

ልጅ ከጠረው፤ ጥርስ የጠረው
- የአካል ጥንካሬ በስተርጅና ያስፈልጋል

ልጅ ካበጀው አባት ያበላሸው
- የሕይወት ልምድ ከሁሉም ይልቃል

ልጅ ካባቱ ፤ሾተል ካፎቱ
- መልካም እስተዳደግ

ልጅየው አባት ሆነ፤ ለሰውየው
- ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች

ልጅ የጫረው እሳት ለጐረቤት ይተርፋል
- በልጅ የመጣ ጠብ ቶሎ አይበርድም

ልጅ ያለ ልጅን አከለ
- ለልጅ ብሎ መብለክለክ ኋላ ጉዳት ያመጣል

ልጅ ያለ እናት፤ ቤት ያለ ጉልላት
- በእናት እጅ ያላደገ ልጅ ይጎሳቆላል

ልጅ ያባቱን፤ወቄራ ያፎቱን
- ማንኛውም ነገር ቅርብ የሚያገኘውን ያስቸግራል

ልጅ ያቦካው ለእራት እይበቃም
- የልጅ ሥራ እያሟላም

ልጅ ይሮጣል እንጂ አባቱን አይቀድምም
- የልጅ ሥራ ዳር አይደርስም

ልጅ ይወለዳል ከርጉዝ ፤ ላም ይገዛል ከወንዝ
- ልጅ ይወለዳል ከቦዝ ላም ይገዛል ከወንዝ

ልጅ ደረሰ፤ ቤት ፈረሰ
- ሁሉን ለእኔ፤ ሁሉ በእኔ

ልግመኛን መምከር፤ ውኃን በወንፊት ማኖር
- ላይሰማህ ጊዜህንህ ጉልበትህን አታጥፋ

ልግምን እግዜርም አይወድም
- ሥራን የማይወድ ሰው በማንም ሰው የተጠላ ነው

ልጓም ለቆ ቼቼ
- ስዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ

ልጡ የተራሰ ፤ መቃብሩ የተማሰ
- ሲሞት የተቃረበ

ልፋ ያለው ቆዳ ለመጫኛ ይሆናል
- አትረፊ ያላት ነፍስ እንዲሁ እንደባከነች ትኖራለች

ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል
- ድከም ያለው ጉልበቱን በማይጠቅም ነገር ላይ ያውላል

ልፋ ያለው እንድ ዕንጨት ያስራል
- የማይሆን ሙከራ ማድረግ

ሎሌ ለስሕተት፤ ጌታ ለምህረት
- እየሠራ ለሚሳሳት ምህረት ይቅርታ ይገባዋል

ሎሌ ሲከበር ጌታው ይከሳል፤ ሙክት ሲሰባ ሾተል ይልሳል
- ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል

ሎሌና አሞሌ ካዘዙት ይውላል
- በተፈለገበት ቦታ ተገኝቶ ትዕዛዝ ይፈጽማል

ሎሚና ትርንጎ ሞልቶልህ ባገር፤ እንቧይ ታሽታለህ የድሃ ነገር
- በማይረባ ነገር ላይ አታተኩር

ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ፤ ዳቦ ካልገመጡት ድንጋይ
- የሚፈለገውን ነገር በተገቢው ጊዜ ካልተደረገ ጥቅም የለውም

## ሐ

ሐሜተኛ ነው ከዳተኛ
- ሐሜተኛ ሰው ሥራው ስለሚደረሰበት እምነት ሊጣልበት አይገባም

ሐሜት አይቀር ከደሃም ቤት
- ሐሜተኛ መታማት የማይገባውን ሁሉ ነው የሚያማው

ሐሜተኛ ያፍራል እውነተኛ ይረታል
- ሐሜተኛ ሰው ሥራው ስለሚደረስበት ያፍራል እውነተኛ ሰው ግን ዞሮ ዞሮ ይረታል

ሐሜትና ጅራት ከበስተኋላ ነው
- የሚታማ ሰው መታማቱ በማይታወቅበት ሁኔታ ነው

ሐምሌ ቢያባራ በጋ ይመስላል
- ነገሮች የተለመደውን ተግባር ሲያቋርጡ እንደገና የሚቀጥሉ አይመስሉም



ሐምሌና ሙሽራ ሳይገለጡ ነው
- ከተሸፋፈኑ ለክፉ ነገር አይጋለጡም

ሐምሌን በብጣሪ ነሐሴን በእንጥርጣሪ
- ክፉን ቀን ማሳለፍ በምኑም በምኑም ነው

ሐረጉን ሳብ ዛፍ እንዲሳሳብ
- የጥቅም፣የሌብነት፣ የዝምድና፣ግንኙነት ካለ የአንዱ መነካት ሌላውን ያጋልጣል

ሐረግ ለመጸፍ ፤ አልጋ ለምንጣፍ
- እያንዳንዱ ነገር በተገቢው ቦታ ቢውል ጥሩ ነው

ሐሰተኛ ምስክር ጉልበት ይሰብር
- በሐሰት የሚመሰክር ሰው በተባዳዩ ላይ ከበድ ያለ ጉዳት ያደርሳል

ሐሰተኛ በቃሉ ፤ሰደተኛ በቅሉ ይታወቃሉ
- ሐሰት ተናጋሪ ገና ከአፉ ከአነጋገሩ ይታወቅበታል

ሐሰተኛ ብርቱ ወንጀለኛ
- ሐሰት መናገር ብርቱ ወንጀል ከመፈጸም ይቆጠራል

ሐሰተኛ ሲናገር ይታወቃል ፤ሰሉ ሲበላ ይታነቃል
- ሐሰት ተናጋሪ ገና ከአፉ ይታወቅበታል

ሐሰተኛ ያወራውን ፈረሰኛ አይመልሰውም
- ሐሰት አንዴ ከተሰራጨ ማስተካከያ የለውም

ሐሰተኛን ሲረቱ በወንድሙ በእህቱ
- ሐሰተኛን ለማጋለጥ በቅርብ ዘመዶቹ መጠቀም ያስፈልጋል

ሐሰቱ ስለበዛ እውነቱ ሆነ ዋዛ
- ሐሰተኛ በበዛበት እውነቱ አንደቀላል ተቆጥሮ ይሆናል ሐሰት

ሐሰት ቢናገሩ ውቃቢ ይርቃል
- ሐሰት መናገር ያዋርዳል

ሐሰት ነገር ክፉ፤ ገኃነም እሳት ትርፉ
- ሐሰት መናገር በምድርም በሰማይም ያስጠይቃል

ሐሰት አያቀላ እውነት አያደላ
- ሐሰት መናገር አያድንም ከችግር እውነት ደግሞ ጠፍቶ አይቀር

ሐሰት አያድንም መራቆት መልክ አያሳምርም
- ሐሰት መናገር ከችግር አያላቅቅም

ሐሰት አያደር ይቀላል፤ እውነትና ውኃ እያደር ይጠራል
- በሐሰት የተፈጸመ ነገር ዞሮ ዞሮ መጋለጡና እውነቱ መውጣቱ አይቀርም

ሐሰትና ስንቅ እያደር ያልቅ
- እውነት እየገነነ በመጣ ጊዜ ሐሰት እየመነመነ ይሔዳል

ሐሳቡ ጥልቅ ነገሩ ጥብቅ
- መሠረት ያለው ነገር

ሐሳብ ከውሲታ አይቆጠርም
- መረዳዳቱ ነው እንጂ በሐሳብ በቃል እንዲህ ነው ማለት ምንም አይጠቅምም

ሐሳብ ከፊት አይፈታ ሙት አይምታ
- ሐሳብ ማለቂያ የለውም ይህን ጨረስኩ ሲባል ሌላ ሐሳብ ደግሞ ይተካል

ሐሳብህን ጨርቅ ያድርገው
- ለተቸገርከው ጉዳይ መፍትሔ አግኝ

ሐሳብና መንገድ ማለቂያ የለውም
- ሰው ሆኖ ማሰብ አይቀርምና አንደኛው ሐሳብ ሲያልቅ በአንደኛው ይተካል

ሐሳብ ያገናኛል ፍርሃት ያሸኛኛል
- ልብ ለልብ መገናኘት አብሮ ያኖራል

ሐኪም ሲባዛ በሽተኛ ይሞታል
- የሐኪም መንዛዛት መፍትሔ አያመጣም

ሐኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል
- ማምሻም ዕድሜ ነው

ሐኪሞች እስኪመካከሩ በሽተኛ ይሞታል
- ለችግር ፈጥነው መፍትሔ ካላገኙለት ሥር ይሰዳል

ሒዳ ጉበት ቢነሷት፤ ታላቅ ታናሽ ለደዱልኝ አለች
- ራሷ ያልተሳካላት በመልክተኛ እንዲሳካላት አሰበች

ሒድ እትበለው እንዲሔድ አድርገው
- የማይወደውን ነገር ፈጽምበት

ሒድ እንዳልልህ ቀኑ ገና፤ ግባ እንዳልልህ ሚስቴ ገናና
- ሚስቴ ኃይለኛ በመሆኗ ላስተናግድህ አልችልም

ሒድ ካገር ኑር ካገር
- እንደ ንጉሡ፤ አጐንብሡ

ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም
- ስሕተት እፈጥር ይሆናል ተብሎ ሰው ሥራ ሳይሠራ አይውልም

ሕመሙ ቀርቶ ሞትን በሰጠኝ
- ከችግር የሚገላግለኝ ነገር ባጋጠመኝ

ሕመሙን የማይናገር በሽተኛ ፈውሱ መጋኛ
- ገና ለገና አይሆንም ብሎ ሥጋት መስጋት ተገቢ አይደለም

ሕመሙን የሸሸገ መድኃኒት የለውም
- ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም

ሕመሙን የደበቀ መድኃኒቱም አልታወቀ
- ሕመሙን የሸሸገ መድኃኒቱ አይገኝለትም

ሕያዋን ለነገሥታት፤ ሙታን ለካህናት ይገብራሉ
- ሁሉም ይረዳኛል የሚለውን ይማጠናል

ሕግ ይኖራል ተተክሎ ፤ ሥርዓት ይኖራል ተዛውሮ
- የአፈጻጸም ሥርዓት ቢሻሻል እንጂ ሕጉ ጸንቶ ይቆያል





## <u>መልመጃ አንድ /ሀ፤ለ፤ሐ/</u>

### ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ለሰበበኛ ------ መረቅ አታብዛበት
   ሀ. ቂጥ ለ. አንጀት ሐ ጉበት መ. ሳንባ
2. ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ደሀ ለደሀ --------
   ሀ. ይጠቃቀሙ ለ. ይታገሱ ሐ. ይለማመኑ መ. ይሰቃቀሱ
3. ሁለት እግር አለኝ ብለህ -------- አትወጣም
   ሀ. አንድ ዛፍ ላይ ሐ. ግንድ ላይ
   ለ. ሁለት ዛፍ ላይ መ. መኪና ላይ
4. ሐሳብና መንገድ ---------::
   ሀ. መልካም ነው ሐ. ረጅም ነው
   ለ. ማለቂያ የለውም መ. ያበሳጫል
5. ለሆዳም በሬ ---------::
   ሀ. ጭድ ያዝለታል ሐ. ጉመን ያዝለታል
   ለ. መልካም ገበሬ መ. ሀ እና ሐ
6. ሀብታም በሃብቱ -------- በጉልበቱ
   ሀ. ጉረምሳ ለ. ደሃ ሐ. ሽማግሌ መ. ሰነፍ
7. ለመከራ ያለው መነኩሴ --------
   ሀ. ሁልጊዜ ያለቅሳል ሐ. ገዳም ይገባል
   ለ. በክረምት ይሞታል መ. ዳዊቱን ሽጦ አህያ ይገዛል
8. ለወጡም እዘኑለት -----------
   ሀ. አስፈራሩለት ሐ. ቀስ ብላችሁ ብሉለት
   ለ. ከደረቁም ጉረሱለት መ. ሁሉም መልስ ነው
9. ሐምሌና ሙሽራ ----------
   ሀ. ይመሳሰላሉ ሐ. ሳይገለጡ ነው
   ለ. አብረው አይሄዱም መ. ተገልጠው ነው
10. ---------- ለአሸንክታብ
    ሀ. ለድሪ ያሉት አንገት ሐ. ለነሐስ ያሉት አንገት
    ለ. ለብር ያሉት አንገት መ. ሁሉም
11. ሁለት ጊዜ ነው -------- አንዱ በእንቁላል አንዱ በጫጩት
    ሀ. የዶሮ ሞት ሐ. የዶሮ ጩኸት
    ለ. የዶሮ ልደት መ. የዶሮ ምጥ
12. ሐረግ ለመጸፍ
    ሀ. ጉልበት ይሰብር ሐ. አልጋ ለምንጣፍ
    ለ. አንድ ለመንገድ መ. ሰወሬ የለው ፍሬ
13. ሆደ ሰፊ ---------
    ሀ. ታጋሽ ነው ሐ. ረጅም ነው
    ለ. ነገር አሳላፊ መ. አድርባይ ነው

14. ለመሥራት ያፈረ -------- ደፈረ
   ሀ. ለመብላት ደፈር    ሐ. እንዲያበሉት
   ለ. እንዲበላ    መ. ለማንሳት

15. ለሞኝ ሰኔ በጋው ---------
   ሀ. በጋ ክረምቱ    ሐ. መስከረም ክረምቱ
   ለ. ምን ይሆን ዋጋው    መ. ግንቦት በልጉ

16. ሀብታም ቢሰጥ -------- እንጂ አልሰጠም
   ሀ. አካፈለ    ለ. አበደረ    ሐ. አከፋፈለ    መ. ሀ እና ሐ

17. ሐረጉን ሳብ ---------
   ሀ. እንዲያጉነብስ    ሐ. እንዲደመሰስ
   ለ. እንዲበጠስ    መ. ዛፍ እንዲሳሳብ

18. ለመከራ የጣፈው ----------
   ሀ. ጨነቀው    ሐ. ቢነግድ አይተርፈው
   ለ. ቁስል ቆሰለበት    መ. መልሱ የለም

19. ሐኪም ሲበዛ ---------
   ሀ. በሽተኛ ይድናል    ሐ. ነጋሪ በዛ
   ለ. በሽተኛ ይሞታል    መ. ሰው ያልቃል

20. ሕልም ተፈርቶ ________
   ሀ. ሐኪም ቤት አይኬድም    ሐ. ሳይተኛ አይታደርም
   ለ. ወጌሻ ቤት አይኬድም    መ. ሀ እና ሐ

21. ለቅዘን እግር አንሰተውለት ---------- ሸሽተውለት
   ሀ. ለሕፃን    ለ. ለውሻ    ሐ. ለፈሪ    መ. ሀ እና ሐ

22. ሁለት አፎች ------- ይናቀሉ
   ሀ. ባይሳሳሙ    ለ. ባይሳደቡ    ሐ. ባይናከሱ    መ. ባይናገሩ

23. ሐሜት አይቀር ----------
   ሀ. ከደሃም ቤት    ሐ. ከጠንቋይ ቤት
   ለ. ከሐኪም ቤት    መ. ሁሉም መልስ ነው

24. ሁለት ቁና ሰጥቼ ----------
   ሀ. አራት እፈልጋለሁ    ሐ. ሦስት ይክፈሉኝ
   ለ. አንድ ጥንቅል    መ. ሦስት ጥንቅል

25. ሐሜተኛ ነው --------
   ሀ. ሐሰተኛ    ለ. ፍርሃተኛ    ሐ. ከዳተኛ    መ. ዋሾ ነው

26. ለቡናሽ ቁርስ የለሽ -------- ለዛ የለሽ
   ሀ. ለጭፈራሽ    ሐ. ላካሄድሽ
   ለ. ላረማመድሽ    መ. ለአነጋገርሽ

27. ለልጅ ጥርስህን ----------
   ሀ. ለጉበዝ ሱሪህን    ሐ. ለዝንብ ቁስልህን
   ለ. ለፈሪ ቤትህን    መ. ለ እና ሐ



28. ሀ ባሉ -------- በሉ
   ሀ. እንጀራ    ለ. ፓስታ    ሐ. መኮረኒ    መ. ተዝካር

29. ለእግሩ የተጠየፈ ---------
   ሀ. ለቂጡ አተረፈ    ሐ. ለእራሱ ተረፈ
   ለ. ለጀርባው ተረፈ    መ. ሁሉም

30. ለሞኝ ከሣቁለት -----------
   ሀ. የኮመኮ ይመስለዋል    ሐ. ለውሻ ከሮጡለት
   ለ. ለቅዘን ከሮጡለት    መ. ጭንቅላት ላይ ይወጣል

31. ለባለጌ ገድሉ ----------
   ሀ. ውርደቱ    ለ. መመታቱ    ሐ. ፉከራው    መ. መጮኹ

32. ሁሉ ሄዶ ተበተነ ----------- አለ እያዘነ
   ሀ. እኔ ብቻ ቀረሁ    ሐ. እኔና አበበ ቀረን
   ለ. እህህና እኔ ቀረና    መ. መልሱ የለም

33. --------- ፊት አይነጭለትም
   ሀ. ለውሽማ ሞት    ሐ. ለውሻ ሞት
   ለ. ለባል ሞት    መ. ሀ እና ሐ

34. ሆዴ ---------- በዘዴ
   ሀ. ሳልጠግብ    ለ. ጠግቤ    ሐ. ኑር    መ. መልሱ የለም

35. ሆድ ሲያውቅ --------
   ሀ. ሆዴ ተረበሸ    ሐ. ልቤ ተረበሸ
   ለ. ዶሮ ማታ    መ. ሀ እና ሐ

36. ለወዳጁ ማረ ወለላ ለጠላቱ -----------
   ሀ. አሜኬላ    ለ. ሰንካላ    ሐ. ሽቁጥቁጥ    መ. ወልጋዳ

37. ለሃምሳ ጋን ---------
   ሀ. ሦስት ገመድ    ሐ. አንድ አሎሎ
   ለ. ሀምሳ ገመድ    መ. አንድ ጠጠር

38. ለቀንዳም በሬ አትከልክለው ---------
   ሀ. ቀንዱ ይከለክለዋል    ሐ. ሻኛው ይከለክለዋል
   ለ. እልሁ ይከለክለዋል    መ. መልሱ የለም

39. ---------- እንደዳቦ እስኪገምጥህ አትመቸው
   ሀ. ለውሾች ለ. ለጅቦችሐ. ለጠላትህ    መ. ሀ እና ለ

40. ሐሰተኛ ያወራውን -------- አይመልሰውም
   ሀ. ጉበዝ    ለ. ጀግና    ሐ. አንበሳ    መ. ፈረስ

41. ለተቸገረ የማያዝን --------- የለውም
   ሀ. ርኅራኄ    ለ. እንብርት    ሐ. ጉበዝ    መ. ስስታም

42. ለፍቅር ብተኛት --------
   ሀ. አረገዘች    ሐ. ለጠብ አረገዘች
   ለ. ሙጥኝ አለችኝ    መ. ጥላኝ ፈረጠጠች

43. ላም ባልዋለበት --------- ለቀማ
   ሀ. ኩበት ለ. በጠጥ ሐ. እበት መ. ሁሉም መልስ ነው

44. ሁለት ጊዜ በልተህ ተፋህ ሁለት ጊዜ ተናግረህ ----------::
   ሀ. አላመንክ ለ. ከፋህ ሐ. ተለፋደድክ መ. ለ እና ሐ

45. ልብ ካዘነ --------- አይገድም
   ሀ. ኑሮ ለ. ገንዘብ ሐ. ለቅሶ መ. እንባ

46. ልጅና ጦጣ --------::
   ሀ. ኬክ ይብላ
   ለ. ውኃ ይጠጣ
   ሐ. ሻይ ይጠጣ
   መ. ሁሉም መልስ ነው

47. ለማያውቀው --------- ዱሩ ነው
   ሀ. ፎገራ ለ. ጓሮ ሐ. ከተማ መ. ለ እና ሐ

## ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሊያዊ አነጋገር ፍቺውን ምረጥ</u>

1. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል
   ሀ. ሌባ ያስመስላል
   ለ. ልማደኛ ልማዱን አይተውም
   ሐ. ሌባ ዘዴኛ ነው
   መ. ሀ እና ሐ
2. ላም እሳት ወለደች ልጅዋ ነበርና ላሰች
   ሀ. ጣት ገማ ተብሎ ቆርጦ አይጥሉት
   ለ. እሳት ቢፈጃት ወደ ልጅዋ ጣለች
   ሐ. እሳትና ጭድ አንድ ቤት አያድርም
   መ. እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ
3. ሆድ ድንጋይ ልበላ ነው ቢል
   ሀ. ዐይን « ይህን አላይም» ብሎ ተጨፈነ
   ለ. ጉሮሮ «በየት አላልፈህ? » አለው
   ሐ. ምላስ «ማን ሊገፋልህ ነው?» አለው
   መ. ጥርስ «ከማን ጋር ተማክረህ?» አለው
4. ለተቀማጭ ለማይ ቅርቡ ነው
   ሀ. ነገር ፈጣሪውን እሾህ አጣሪውን
   ለ. ራሴን መትቶ እግሬን ቢያከኝ አይገባኝ
   ሐ. ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር
   መ. ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ሰባት ዓመት ይደናቆሩ
5. ልብ ሲፈቅድ መግደርደር ራስን መግደል
   ሀ. ሆድን በጕመን ቢደልሉት በዳገት ይለግማል
   ለ. ተግደርዳሪ ጾም አዳሪ
   ሐ. የሆድ ምቀኛ አፍ ነው
   መ. ሁሉም መልስ ነው
6. ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች
   ሀ. የተገላቢጦሽ ተግባር ተፈጸመ
   ለ. ጉብዝ ልጅ ናት
   ሐ. መካሪው ብዙ
   መ. ያላወቁ አለቁ
7. ለራሉ ጥላ ለእግሩ ከለላ
   ሀ. ለራስም ለእግሩም አለው ከለላ
   ለ. መጠለያ አስፈላጊ ነው
   ሐ. አለኝታ የሚሆን ነገር አስፈላጊ ነው
   መ. ዣንጥላ አስፈላጊ ነው



8. አይጸጸቱ ለሚመጣው አይበለጡ
   ሀ. ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም
   ለ. ላለፈው ጸሎት ከንቱ ጩኸት
   ሐ. ከሆነ ወዲያ ንዴት ለሽበት
   መ. ሁሉም መልስ ነው

9. ለኃጥእን የወረደ ለጻድቅ ይተርፋል
   ሀ. የመጥፎ ሰው ጦስ ለሌላው ይተርፋል
   ለ. ጻድቃን ከኃጥአን ጋር ከዋለ ይበላሻል
   ሐ. ለኃጥአን መንገዱ ክፍት ነው
   መ. መልሱ የለም

10. ሀብትና ዕውቀት አይገኝ አንድነት
   ሀ. ጤናና ሀብት አንድ ላይ አይገኝ
   ለ. ሁሉን አሟልቶ አይሰጥ
   ሐ. ሀብታም አይማርም
   መ. ዕውቀት ያለው ሀብት የለውም

ሐ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | ሀ | | ለ |
|---|---|---|---|
| 1. | ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ | ሀ. | አንቺ ምን ቸገረሽ ሁለት አባ አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ |
| 2. | ሁለት የተመኘ አንዱንም አላገኘ | ለ. | የነብር ዐይን ከፍየል የፍየል ዐይን ከቅጠል |
| 3. | ሁለት ብልጥ ኑግ አያደቅ | ሐ. | ባጕረስኩ እጄን ተነከስኩ |
| 4. | ሴባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል | መ. | እንደንጉሡ አጐንብሱ |
| 5. | ሁለት ባላ ትከል አንዱ ቢሰበር ባንዱ ተንጠልጠል | ሠ. | ሁሉ ሆነ ቃልቻ ማን ይሸከም ሰልቻ |
| 6. | ሂድ ካገር ኑር ካገር | ረ. | ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀ |
| 7. | ሆድ ሲያር ጥርስ ይሥቃል | ሰ. | ከሁለት የወደቀ ዛፍ |
| 8. | ሁሉም ሽከሙን ፍቅርም ያኾርውን | ሸ. | ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ |
| 9. | ሁሉ አረሰ ማን ይሸምት | ቀ. | ውስጡን ለቄስ |
| 10. | ሁለት ቁና ሰጥቼ አንድ ጥንቅል | በ. | የፉከከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል |
| 11. | ለማኝ አያማርጥም ማር አይከመጥጥም | ተ. | የቸገረው እርጉዝ ያገባል |
| 12. | ለማይሰጥ ሰው ስጡኝ ማለት ማን አስተማረው | ቸ. | ላም ያልዋለበት ኩበት ለቀማ |
| 13. | ለራሱ የማይረባ ለሰውም አይረባ | ኀ. | ለቦና ጥጃ ውስ አያንሰውም |
| 14. | ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት | ነ. | ወያ አይበላ ወይ አያስበላ |
| 15. | ለሰው ሞት አነሰው | ኘ. | ከራስ በላይ ነፋስ |
| 16. | ለሰው ብሎ መሞት አምላክነት ያሻል | አ. | ለውን ማመን ቀብሮ ነው |
| 17. | ለቀማኛ የለውም እጅ ለበቅሎ የለውም ልጅ | ከ. | ለአባብ የልቡን አይቶ አግር ነሳው |
| 18. | ሆድ በጕመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል | ወ. | ሰውን ማመን ቀብሮ ነው |
| 19. | ለሰው ሞት አነሰው | ዘ. | መተው ነገሬን ከተተው |
| 20. | ለነገረኛ ነገር ተውለት ለሆዳም እህል አቅርብለት | ዠ. | እራት የሌለው ቄስ እንደልቡ አይቀድስ |
| 21. | ለዐይን የሚከፋ ለአፍንጫ ይከረፋ | የ. | ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ |
| 22. | ለዘመዴ ያዝናል ሆዴ | ደ. | ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል |
| 23. | ለዳርቻው ሲሳሉ መካከሉን ተነሉ | ጀ. | ውጣ ያለው ገንዘብ ሲፎክተ ያድራል |
| 24. | ለጥልና ለዳኛ ያለው ገንዘብ አፋፍ ያቆያል | ገ. | የቆውን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች |



## መ

ሙሄድ፡ መሄድን እያደራጀሁ፤እንደጉሬዛ አረጀሁ

- በሐሳብ ብቻ ቀረሁ ምንም ነገር ሳላደርግ

ሙሄድ፡ መመላለስ፤ ካሰቡት መድረስ

- ካሰብከበት ግብ ለመድረስ መሯሯጥ

ሙሄድ፡ መነሣት፤መከተል መሸኘት

- ለዓላማህ ፈጥነህ በመነሳት ጥረት አድርግ

ሙሄድ፡ በጋ ነው ፤መቀመጥ ክረምት ነው

- ከመቀመጥ የሚገኝ ምንም የለም

ሙሄድና መምጣት፤ማግኘትና ማጣት

- አግኝቶ ማጣት ያለ ነው

ሙሄድ፡ ያለዛቻ ብቻ፤ መሥራት የለ ሐሳብ ብቻ

- መሄድ መሄድን እያደራጀሁ እንደጉሬዛ አረጀሁ

ሙሄድ፡ ያማረው እራቱን በጨረቃ ይበላል

- ፈጥኖ ለመድረስ ማልዶ መነሳት

ሙሆን በሆነ ዳሩ ግን ምን ይሆናል አገርህ ሩቅ ሆነ

- ቢሳካማ ጥሩ ነበር

ሙሰመን የሰመደ ምላስ፤በሕልሙ አቁማዳ ይዋስ

- ልማደኛ ልማዱን አይተውም

ሙላ እንደ ሴት ግርማ እንደሴሊት

- ሴቶች መላ መፍጠር ይችሉበታል

ሙላከተኛ ከአጤ ቤት ይገባል

- አደራ ከባድ ነው

ሙልክ ጥፉ፤ በስም ይደግፉ

- በአንዱ ቢያጡ በአንዱ ይጠቀሉ

ሙልከኛ ከአጤ ቤት ይገባል

- ጎጃም በዘነበ ሳይንት እህል ሞላ

ሙልኩ የኔ ግብሩ ያረመኔ

- የቀይ ሰይጣነ ሆነ

ሙልካም ላባ፤ከመልካም ወፍ ይገኛል

- የጨዋ ልጅ ጨዋ ነው

ሙልካም ልብ አይነካም

- ሁነኛ ነገር ለሰውነት ተስማሚ ነው

ሙልካም ሚስት ለባልዋ ዘውድ ናት

- ጥሩ ሥነምግባር ያላት ሴት አክሊ ናት

ሙልካም ሠሪ በልጆቹ፤ የጨረቃ ንጋት በወፎቹ ይታወቃል

- መልካም ሰው ልጆቹ የተባረኩ ይሆኑለታል

መልካም ሱሪ ክተማሪ
- የሞራል ድጋፍ ማድረግ

መልካም ቆንጆ፤ የላት መቀናጆ
- ተወዳጅ ናት

መልካም በሬ ለእርሻ ዶማም አያሻ
- ጥሩ መሣሪያ አጋዥ አያስፈልገውም

መልካም ባል፤ መጥፎ ሴት ይገራል
- መጥፎ ከጥሩ ጋር ከዋለ ባህርይውን ይለውጣል

መልካም ተመኝ፤ መልካም እንድታገኝ
- ጥሩ ላደረገ ጥሩ ያጋጥመዋል

መልካም ንግግር ቁጣን ያበርዳል፤ መጥፎ ንግግር ልብን ያናድዳል
- መልካም ሁልጊዜም መልካም ሲሆን መጥፎ ነገር ሁሉ ህውከትን ይፈጥራል

መልካም አባት አጁን በልጁ ኪስ ይከታል
- ለልጁ ያስባል ይጨነቃል

መልካም አድራጊ እበዳሪ ፤ ክፉ አድራጊ ተግደርዳሪ
- ሁሉም የእጁን ብድሩን ያገኛል

መልካም ወሬ አጥንትን ያለመልማል፤ መጥፎ ወሬ ልብን ያደክማል
- መልካም ነገር ለሕይወት ጠቃሚ ሲሆን ክፉ ነገር ለሕይወት ጠንቅ ነው

መልካም ወገን ፤ የፀሐይ ውጋጋን
- አስተማማኝ ስለሆነ ለችግር ጊዜ ይደርሳል

መልካም ወጥ፤ እጅ ያስመጥጥ
- ተወዳጅነት ይኖረዋል

መልካም ጭራ ለደብተራ
- የሞራል ድጋፍ ጥሩ ለሚሠራ ሰው ነው

መልካም ፈረስ ለሩጫ፤ ሊጋር በቅሎ ለኮርቻ
- መልካም በሬ ለእርሻ፤ በሬም አይሻ

መልክ በግምት ይገኛል ልብ ትልቅ ይመኛል
- በማየት የእገሌ ልጅ ነው ማለት ይቻላል

መልክ ታጥቦ አይጠጣም
- ሴት ልጅ ሙያና ፀባይ ከሌላት ዋጋ የላትም

መልኳ ባያምር ዓመሏ ያምር
- መልክ ባይኖራትም ጸባይ ካላት ማንም ይወዳታል

መመራመር ያደርሳል ክቁም ነገር
- መመራመር ዕውቀትን ያሰጨብጣል

መመሳሰል የጋራ ነው
- በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ባሉ ነገሮች ላይ የሚታይ

መመከት ጋሻ አንግቦ ፤ መጸለይ ዳዊት አቅርቦ
- እንደቦታውና እንደሁኔታው ከአስፈላጊው መሣሪያ ጋር መገኘት



መመጽወት ያድናል ከድህነት
- መርዳት መልካም ተግባር ነው

መመጽወት ያድናል ከጸጸት
- በምድር የሰጡትን በላይኛው ቤት ያገኙታል

መምህራን ካሉ ፤ ዐዋቂዎች ይበዛሉ
- መምህራን የዓለም ብርሃን ናቸው

መምሬ አይበሉም ጥሬ
- ለአበ ነፍስ ጥሬ አይቀርብም

መምከርማ ድሃ ይመክራል፤ሰሚ አጥቶ ይቀራል
- ጥሩ ምክር የድሃ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ፤ ጥሩ ውኃ የጥቅምት ነበርሽ ማን ቢጠጣሽ

መሠረት ነዋሪ፤ መሪና አስተማሪ
- የመጀመሪያው ለኋለኛው ጊዜ መነሻ ነው

መሣሪያ ይዞ ጸሎት ካባ ለብሶ ማድቤት
- ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ይገባል
- ልበልባ ታጥቆ አዛባ፤ሱሪ አውልቆ ፈረስ ጋለባ

መሥራት እንጂ ማፍረስ አያቅትም
- መገንባት ጊዜ ፤ ጉልበት ሲፈጅ ማፍረስ በቀላሉ ይከናወናል

መሪና ንፉግ እያደር ይቆጨዋል
- ሁኔታዎች ካለፉ በኋላ ጸጸት አርባና የለውም

መሪ የሌለው ጨንባሳ፤ ምርኩዝ የሌለው አንካሳ
- ያለረዳት ያለአጋዥ የትም አይደረስም

መራጭ ይወድቃል ከምራጭ
- የዓይን አዋጅ ከሆነብህ ምራጭ ላይ ትወድቃለህ

መሬት ላራሽ ፤ነፍጥ ለተኳሽ
- ሥራ መሥራት የሚቻለው በአግባቡ በቦታው ነው

መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል
- ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ

መሬት በድንበር ፤ውበት በከንፈር
- መሬት በወንዙ እባብ በመርዙ

መሬት ባቅጣጫ ፤መልክ ባፍንጫ
- መሬት በድንበር ውበት በከንፈር

መሬት እናት፤ ዘር አባት
- መሬት ዘርን ተቀብላ እንድምታለመልም ሁሉ አባትና እናትም እንዲሁ

መሬት ከሰባ፤ ግዳይ ከሰለባ
- መሬት በፍግ ካመረ ውጤቱ ከፍተኛ ይሆናል

መሬት የወደቀ ሥጋ ፤ ዐፈር ሳይዝ አይነሳም
- አንድ የሆነ ግጭት ከተፈጠረ ከዚህም ከዚያም ጉዳት መድረሱ አይቀርም

መሬት ይገዟል ፤ዋጋ ያበዟል
- የመሬት ዋጋ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ስለማይሄድ የሚወሰን አይደለም

መርጦ ይገዟል፤ ዋጋ ያበዟል
- ሰወደድከው ነገር ከፍ ያሰ ዋጋ ትከፍልበታለህ

መርፌ መግቢያዋን እንጂ፤መውጫዋን አታይም
- አርቆ ማሰብ ያስፈልጋል

መርፌ ሰርቆ ማረሻ ቢተኩ ልብ አይሞላም
- በውል ከሄደች በቅሎዬ ያለውል የተበላች ቆሎዬ

መርፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም
- ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም

መርፌ ቢሰበሰብ ማረሻ አይሆንም
- ያሰወጉ ያለማዕረጉ አይሆንም

መርፌ ውጦ፤ ማረሻ መትፋት
- የማይሆን የማይታመን ድርጊት

መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ ለብዙ ሰው ትጠቅማለች
- ሰራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ሳዋይ

መሮጥ ሲበዛ፤ ልብ ያፈርሳል
- ያለእረፍት መሥራት ያደክማል

መሰሰ ሲል ምን ደሰ ይል
- የተመኘኸው ጉዳይ በጊዜው ሲፈጸም ምንኛ ያሰደስታል

መሳሳሚያ ከንፈር፤ መገናኛ ድንበር
- ለሁሉም የሚያስፈልገውን በቦታው ፤ በጊዜው ማዘጋጀት

መስሎ ከመታየት ሆኖ መገኘት
- ሳይሆኑ ከመምሰል የተፈለገውን ለመሆን ጥረት ማድረግ

መሥራት እንጂ፤ ማፍረስ አያቅትም
- ማፍረስ ቀላል ነው መሥራት እንጂ

መሰታወት ፊት ያሳያል፤ መሰንበት ሁሉን ያሳያል
- ዕድሜ መስታወት ነው

መሰታወት ፊት ያሳያል፤ መሰንበት ይበጃል
- ዕድሜ መስታወት ነው

መሰከረም ባበባው ፤ሠርግ በጭብጨባው
- ሁሉም ነገር በቦታው ሲሟላ ደስ ይላል

መስከረም የሚወልደው ፤ንጉሥ የሚፈርደው አይታወቅም
- ምን እንደሚፈጸም ግልጽ አይደለም

መሰጠት ቤት አይፈታም
- መርዳት ችግር አያመጣም

መሰጠት አያውቅ እራት፤ መምታት አያውቅ እናት
- የሚፈጽመውን ጉዳይ አያውቀውም



መስጠት የማያውቅ ፤የቁና እኩል
- ሰጦታው ሰው አያረካም

መሶብ ለፍቼ፤ ለአጤ አበርክቼ
- እየለፋሁ የሚጠቀመው ሌላ ነው

መሸሽማ አንባሳም ይሸሻል ፤መሰሰ ያለ እንደሆነ ሰውን ያበላሻል
- እያስተዋሉ መፈጸም ያስፈልጋል

መሸጥ የለመደ፤ እናቱን ያስማማል
- የለመደ እጅ አያርፍም

መቀመጥ፤ መቆመጥ
- መቀመጥ ያደኸያል

መቀመጥ በና ነው፤ መሔድ በልግ ነው
- መቀመጥ መቆመጥ

መቀመጫዬ ይብሳል አለ ዝንጀሮ
- ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ስጥ

መቀናጆ የሌለው በሬ፤ ደበሎ የሌለው ገበሬ
- ረዳት የሌለው ሰው ውጤቱ ጥሩ አይደለም

መቃን ከመግጨት ዝቅ ብሎ መግባት
- ራስን ከሁኔታዎች ጋር ማስተካከል

መቃ እንዲያ ሲያምር እያፈራ፤ ወርቅ ቢሞላ አይዘራ
- የፈለጉትን ያህል ሰማግኘት ጥረት ያስፈልጋል

መቃኘትና መሰከር፤ ላይመልሱ መበደር
- በቅኝትና በሰካር ጊዜ ሁሉ በእጅ ሁሉ በደጅ ይመስላል

መበለት በቁስ፤ ገበሬ በንጉሥ
- ሁሉም በየፊናው ይታዘዛል

መብሉ እኩል፤ ሥራው ስንኩል
- ታጥበህ እርዳኝ

መብላት ከሁሉቱ ፤ መፍረድ በውነቱ
- ከሳሽም ተከሳሽም ቢያበላኝ እኔ የምፈርደው እውነቱን ነው

መብላት ከባዕድ፤ ምክርን ከዘመድ
- መብልን ከሰው ቤት መኝታን ከቤት

መብሌ ሥንቆ፤ ምርኩዜ ሽንበቆ
- እሳዛኝ ሰው ነኝ

መብሌን ይገፎ ፤ ቅልውጤን ረሳሁት
- የበላችው ያሰገሳታል በሳይ በሳዩ ያጕርሳታል

መብልን ከሰው ቤት፤ መኝታን ከቤት
- መብላት ከባዕድ ምክርን ከዘመድ

መብልን ከባዕድ ፤ኃዘንን ከዘመድ
- የባዕዳን ገንዘብ ብላ የዘመድህን ኃዘን ችላ አትበል

መብል ያለመጠጥ፤ እንጀራ ያለወጥ
- ካልተሟላ በስተቀር አስቸጋሪ ነው

መብረቅ የመታውን ወዘት እስተኛው
- በጉዳት ላይ ጉዳት ደረሰበት

መብራት ለጨለማ እፍንጫ መያዝ እንዳይገማ
- ለሁሉም እንደሁኔታው የሚበጀውን ማድረግ

መተው ነገሬን ከተተው
- ትዕግስት ጥሩ ነው

መታለል ገደል መንከባለል
- አታላይ ያለሀን ሁሉ ይወስድብሃል

መታፈር በከንፈር
- መልካም ንግግር ያስከብራል

መታዘዝን ሳያውቁ ማዘዝ ፤ ታላቅ መዘዝ
- መታዘዝን ሳታውቅ ማዘዝን አትመኝ

መታጠቂያዬን አጥብቀልኝ
- ድጋፍ ስጡኝ

መቸር እጅ ሲያጥር
- በሌለበት ጊዜ ለመቸር መሞከር የማይሆን ሙከራ ነው

መቼ ገባህ ፊት፤ ምን በላህ ፍትፍት
- ቀድሞ መገኘት ጥቅም ለሚያስገኝ ነገር

መች መጣሽ ሙሽራ፤ መች ቀረጠምሽ ሽንብራ
- ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

መነኩሴ በቆብ፤ ወንበር በክታብ
- በዕድሜና በችሎታ መጠን ሁሉም ይስተናገዳል

መነኩሴ ቤት ሲሠራ ሐረግ ትሸሽጋለች
- ለሥራ አደናቃፊ ሰው ያጋጥምሃል

መነኩሴ ከደብሩ፤ አንበሳ ከዱሩ፤ ወጥተው ካደሩ
- ጥሩ ሰው ክተበላሸ መመለሻ የለውም

መነኩሴ ካልሞተ፤ ሥንዴ ካልሸተተ አይታወቅም
- አንድን ነገር ይሄ ነው ለማለት መነሻ ነገሮችን ማወቅ ይጠይቃል

መነዛነዝ ፤ያመጣል መዘዝ
- ንዝንዝ ችግር ያመጣል

መነገድ ለማትረፍ፤ መማር ለመጻፍ
- ሁሉም ነገር ለጥቅም ነው

መናኝ ለነፍሱ፤ አዳኝ ለጥርሱ ይገለግሉ
- ሁሉም ለጥቅሙ ይሯሯጣል

መናገር መልካም ነው፤ ማዳመጥ ይበልጣል
- መናገር ብር ነው ዝምታ ወርቅ ነው



መናገር ሳያስቡ፤ ምላጭ መሳብ ሳያልሙ
- ከመናገርህ በፊት አስብ

መናገር ብር ነው ዝምታ ወርቅ ነው
- መናገር መልካም ነው - ማዳመጥ ይበልጣል

መናፍቅ ለትርጓሜ፤ ትምባሆ ለልምላሜ
- ምንጊዜም የማይፈለግ ነገር እሰሁ እሰሁ ማለቱ አይቀርም

መንቀጥቀጥ፤ እንደወላድ ምጥ
- ፍርኃት ለጊዜው በጣም ያስጨንቃል

መንቻካ ሴት አትሆንም ባለቤት
- ጨቀጫቃ ሴት ለትዳር አትሆንም

መንካት ያደርሳል ከመንካት
- አላርፍ ያለች ጣት እር ጠንቁላ ትወጣለች

መንዜ እንደሚለው እስኪ ከቁርበቴ ልምከር
- አድረን አስበንበት ብንነጋገር ይሻላል

መንደር በልጆች፤ አገር በገበሬዎች
- ለአንድ አገር ወጣትና አራሽ አምራች አስፈላጊዎች ናቸው

መንደር ከዋለ ንብ፤ አደባባይ የዋለ ዝንብ
- ተኝቶ ከዋለ ብርቱ የተንቀሣቀሰ ገልቱ

መንገደኛ ከስንቁ፤ ነጋዴ ከወርቁ
- የሁለቱም ልብ ያለው በያዙት ላይ ነው

መንገዱ የተልባ፤ ወጥ ይሁንልህ
- መንገዱ ሳያደክምህ ቶሎ ድረስ

መንገድ ለቀደመ፤ ውኃ ለገደበ
- መቼ ገባህ ፊት ምን በላህ ፍትፍት

መንገድ ሳለ በዱር፤ በቅሎ ሳለ በእግር
- ቀላል ዘዴ እያለ ለምን ትደክማለህ

መንገድ በወሬ፤ ጠላ በአቦሬ
- በጉዞ ላይ ወግ እያወጉ መሔድ ሳይታወቅ ይደረሳል

መንገድ ባሳብ አይደረስም
- ቢያስቡትም ጥቅም የለውም

መንገድ ከመንገድ ያደርሳል
- የሆነ ሐሳብ ሌላ ጠቃሚ የሆነ ሐሳብ ያፈልቃል

መንገድ ከሽንት ይቀራል
- ለሽንት ቆም ሲሉ ጓደኛ አብሮ ተጓዥ የትናየት ይደርሳል

መንገድ ካገር ልጅ ፤ ምክር ከጨዋ ልጅ
- ጉዞንና ምክርን ከሚበጅህ ከሚስማማህ ጋር አድርገው

መንገድ ካገር ልጅ ፤ ለደት ከሹም ልጅ
- ከሹም ልጅ ጋር ብትለደድ በምግብም በሌላም አትጐዳም

መኖሪያዋን ትታ፤ መዘሪያዋን
- ጠቃሚ የሆነ ነገር ትታ የማይጠቀመው ላይ ማተከር

መኖሪያውን ትተው ፤ መናገሪያውን
- ጠቃሚ የሆነ ነገር ትተው የማይጠቅመው ላይ ማተከር

መኖር ማለት፤ ብርሃን መስንበት
- በሕይወት መኖር መልካም ነው

መኖር ማለት፤ ብርሃን መስታወት
- በሕይወት መኖር ሁሉን ያሳያል

መኖር በከንቱ ፤ ሰው አለቤቱ
- መኖር በከንቱ ያለባለቤቱ

መከራና ፍዳ፤ እንግዳና ሞት በድንገት
- በድንገት የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው

መከራና ጉም፤ እያደረ ይቀላል
- ለጊዜው ያስቃያል እንጂ ማለፉ አይቀርም

መከራን መሸፈን ፤ እግዜርን ማመን
- በዓምላክ እርዳታ መከራና ስቃይ ይቃለላሉ

መከራን የቻለ ፤ አሸናፊ ነው
- ትዕግሥት ካለ ክፉውን ጊዜ በአሸናፊነት ይወጡታል

መከራው ያላቀለለት በሬ፤ ከሞተ በኋላ ቆዳው ለነጋሪት ይጠፈራል
- ለመከራ የተፈጠረ ሰው ዕድሜ ልኩን እየተሰቃየ ይኖራል

መከፈንና መሸፈን ፤ እግዜርን ማመን
- ሁሉ በእሱና በእሱ የሚሆን ነው

መካር የሌለው ንጉሥ ፤ ያለ አንድ ዓመት አይነግሥ
- አገር ያለምክር ቤት ያለ ማገር

መከሮ ልብ አይደል፤ አፏጭቶ ጥርስ አይደል
- አስፈላጊው በቦታው ከሌለ አይሳካም

መከዳትና መከብለል ፤ ወድቆ መንከባለል
- መከዳት መጥፎ ተግባር ነው

መከፈልት ሲሹ መቅለፍት
- የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

መከርከሚያ ያላገኘ፤ መዘርጊያን ተመኘ
- ጥቂት ሳያገኝ ብዙ ነገር ተመኘ

መወለድ ቋንቋ ነው
- ከመወለድ መዛመድ፤ ከመዛመድ መላመድ

መወለድ ካለ ማዘን አይገድም
- ለሥጋህ መቆርቆር ማዘን ያለ ነው

መዋዕል ለፍስሐ ፤ ዕድሜ ለንስሐ
- በጊዜህ ተደሰተህ በመጨረሻ ደግሞ ንስሐ መግባት ይጠበቅብሃል



መዋጋት ከድርጅት፤ መብል ከጠቦት
- የጠቦት ከብት ለምግብነት አመቺ ነው

መውጫህን ሳታይ አትግባ
- አንድ ነገር ከማድረግህ በፊት አስብበት

መውደዱንስ እንተን እወዳለሁ ኋላ ወዴት እገባለሁ
- መውደቂያህን ካሁኑ አዘጋጅ

መዘዙን ሳታይ መልኩን ዐይታ
- በሬ ሆይ ሣሩን እየህና ገደሉን ሳታይ

መዝሙር በሐሌ ፤ ነገር በምሳሌ
- በምሳሌ መናገር ያረካል

መዝነብ ቢጠፋ ቢጠፋ ባገር፤ ቤት ቢላላ በማገር
- ሕዝብ የማያውቀው ምስጢር የለም

መድረሻ ያጣ ዱቄት ፣ከነፋስ ይጠጋል
- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

መጀመሪያ ስሕተት የኋለኛው ዕብደት
- ተደጋግሞ የሚፈጸም ስሕተት

መጋኛና ዘበኛ እርፎ አይተኛ
- ኃላፊነቱን ለመወጣት ጥረት ማድረግ

መግረፉን ግረፉ ፤ ግን ከባት አትለፉ
- ሁሉን የምታደርገውን በልክ አድረገው

መሻት ያከሳል
- የማይገኘን ነገር መከጀል ትርፉ ድካም፣ሰቀቀን ነው

መጠንቀቅ፣ ከመለጠቅ
- አብሮ ከማይሔዱት ከማይመስሉት ጋር ላለመሆን መጠንቀቅ

መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ
- ጆሮ ከአያት ያረጃል

መጠጥ ለጨዋታ ወንድም ለግርግርታ
- ወንድም መከታ ነው ፤አለኝታ ነው

መጠጥ ከጨዋ ልጅ፤ ምክር ከድሃ ልጅ
- የጨዋ ልጅ ክወደ ውኃው ነው

መጠጥ ከጨዋ ልጅ፤ ምክር ካገር ልጅ
- ምክር ሁልጊዜም ከራስ ፣ከወገን ቢሆን ይመረጣል

መጠጊያ ያጣ ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል
- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

መጣ ዝም ብሎ፤ ሔደ ተናግሮ
- ውኃን ምን ያናግረዋል ድንጋይ ይባላል

መጣደፍ መቸኮል፤ መረዋና ደወል
- መጣደፍ ስሕተት ላይ ይጥላል

መጣፍ ከመከረው፤ መከራ የመከረው
- ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው

መጥረቢያው የተውሶ ፤ ጠፋ ተመልሶ
- የራስ ያልሆነ ነገር አያኮራም

መጥፊያው መልሚያው፤ መስሎ ይታየዋል ለሰው
- ጥሩ መስሎ የሚታይ አንዳንዴ ለአደጋ ያጋልጣል

መጥፎ ሣር ይለመልማል እንጂ አይጠፋም
- የማይፈልጉት ነገር ይበረክታል

መጥፎ ወሬ ይበራል፤ መልካሙ ይተኛል
- ሰው በሰው ላይ ያለውን ክፉ ነገር እንጂ መልካሙን አያወራም

መጨነቅ የመጠበብ እናት
- ችግር ብልሃትን ትወልዳለች

መጫር ያበዛች ዶሮ ፤ የመታረጃዋን ካራ ታወጣለች
- አላርፍ ያለች ጣት እር ጠንቁላ ትወጣለች

መጭ ብሎ ቢመጣ፤ ብር ብሎ ቀደመው
- ጉቦ ወይም ገጸበረከት በማቅረብ የእሱ እንዲደመጥ አደረገ

መጭ መጭ፤ ከሚሉት በቅሎ መጫሚያ
- ከእጉል በቅሎ በእግር መሔዱ የተሻለ የሚሆንበት ጊዜ አለ

መጻፍና ተማሪ ፤ ቀለበትና ድሪ
- የተያያዙ ፤የማይለያዩ ናቸው

መፍረሱ ላይቀረኝ ለምን ፈጠረኝ
- መሞቴ ላይቀር ለምን ተፈጠርሁ

መፍራት ለመታማት
- ሰው ምን ይለኛል ማለት ጥሩ ነው

መፍታት ላለ መሞት
- መፍትሔው ቀላል እየሆነ መጨነቅ አያስፈልግም

ሙልጭ እንደ ሰበቆ፤እንጣጥ እንደፈቆ
- የፈለጉትን ለማግኘት የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም

ሙሽራ በሚዜ፤ ንስሐ በኑዛዜ
- ሙሽራ በሚዜ እንደሚታይ ሁሉ ኑዛዜ ሳያደርጉ ንስሐ ዋጋ የለውም

ሙሽራዋስ እኔ፤ ዶሮዋን ማን በላት ካለኔ
- እኔ በሌለሁበት ሁኔታው እንዴት ሊፈጸም ቻለ

ሙቅ ውኃና፤ የሰው ገንዘብ እይጠቅምም
- የሰው ገንዘብ ቢወለዱት፤ቢወሰዱት አይጠገብም

ሙታንን ከማመስገን ፤ ሕያዋንን ማስተንተን
- ጠቃሚ ባልሆነ ነገር ላይ ከማተኮር ጥቅም ያለው ላይ አተኩር

ሙት ለሙት ያለቅሳል
- ድሃ ለድሃ ይተዛዘናል



ሙት መውቀስ ፤ ድንጋይ መንከስ
- ላለፈ ነገር መቆጨት አያስፈልግም

ሙት ይዞ፤ ይሞታል
- ሰነፍ ሰነፍን ያሳንፋል

ሙቶ የተነሣ እግዚእብሔርን ረሳ
- አጥቶ ያገኘ እንደገና የሚያጣ አይመስለውም

ሙክት ሲሰባ ከካራ ይታከካል፤ ባለጌ ሲከበር ይፎከፋካል
- እሞሌ ሲወፍር እወንዝ እውርዳችሁ እጠቡኝ ይላል

ሙዙን ላጥ ዋጥ
- የተመቸ ነገር ሲያጋጥምህ ጊዜ አትስጥ

ሙዙን ላላይ መዘዙን
- በሬ ሆይ ሣሩን እየህና ገደሉን ሳታይ

ሙያ በልብ
- ማድረግ የፈለጉትን ሳይናገሩ ማድረግ

ሙግት ላፈኛ እብቹ ለጌኛ
- ዘዴ የሚያውቅ ሙግት ያሸንፋል

ሙግት ያውቃል፤ ይለቃል
- እንዳንዴ አይቶ እንዳላየ ይሆናል

ሚስቱን ጠልቶ፤ካማቱ ቤት ተሸሸገ
- ወንጀል ሠርቶ ፊት ለፊት ሔደ

ሚስቱ ከፉ ባቁላ እራቱ፤ ብሳና ዕንጨቱ ኃዘን ነው ቤቱን
- የተመቸው ሰው እይደለም

ሚስቱ ደግ፤ ሥንዴ እራቱ፤ ወይራ ዕንጨቱ፤ ደስታ ነው ቤቱ
- ቤቱ የተሟላ የተመቸው ሰው ነው

ሚስትህ አመዳም፤ ጉራዴህ ጎመዳም
- የምትኮራበት አንድም ነገር የለም

ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢለው ፤ ማንን ወንድ ብላ አለው
- የተናቅሁ ነኝ

ሚስትህን ስደድ ፤ በሬህን አረድ ይላል የባለጌ ዘመድ
- የመጥፎ ሰው ምክር

ሚስት ባታብል ባልዋን ትወልዳለች
- ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ይቀዳሉ

ሚስትና ዳዊት ከብብት
- የምትወደውን ነገር አጥብቀህ ያዝ

ሚስት ከፈቷት ባዳ፤ ማሽላ ከተቆረጠ አገዳ
- እንዴ ከሆነ ወዲያ ዋጋ የለውም
- ከሞተች ሚስቴ ምናለኝ ካማቴ

ሚስት ፈትቶ ካማት መቀለብ ፤በእንፉቅቅ መሔድ
- የማይወዱት ቦታ መገኘት

ሚዜ ቢከተል አሽከር ይመስላል
- ለጊዜው እንጂ የዘለቄታ አይሆንም

ሚያ ባልኩ፤ ፍየል ከፈልኩ
- አርፌ አለመቀመጤ ተጐዳሁ

ሚዳቋ ቀስ ብላ ስትሔድ የተያዘች ትመስላለች
- ሚዜ ቢከተል አሽከር ይመስላል

ሚዳቋ እንደ አንበሳ እጮሁ ብላ ተሰንጥቃ ሞተች
- ከአቅም በላይ መንጠራራት

ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር
- ከማይጋፋት ባላጋራ መጋፋት ከንቱ ልፋት

ማሰዳ የምትለቅምን ዶሮ ጭልፊት አትጠልፋትም
- በወቅቱ የሚያከናወኑት ተግባር ይጠቅማል ለአደጋ አይሰጥም

ማልደው ቢነሱ እኩለ ቀን አይደርሱ
- ዘግይተው የሚያከናውኑት ነገር አይጠቅምም ለአደጋ ያጋልጣል

ማሕሌት በግርግታ ዳዊት በቀስታ
- እንደ ባህሉ እንደልማዱ ይፈጸማል

ማማት የለመደ አፍ ሲዶልት ያድራል
- አፍ ሲያርፍ ወዳጁን ያማል

ማማው ምረት፤ ማሽላው ቅንብቢት
- አራንባና ቆቦ

ማማው ከጉልበት፤ ማሽላው ከእንብርት
- አይመጣጠኑም

ማምሻም ዕድሜ ነው
- ባለችው መጠቀም ነው

ማረገ ቢስ እራቱ ገሚስ
- ሁሉም እንደየጠባዩና እንደየማዕረጉ ይደረግለታል

ማረፍና መራገፍ ፤ እየበሉ መንገፍገፍ
- የማይሆን ሁኔታ ማሳየት

ማሩን አምሮ፤ ወተቱን አጥቁሮ
- የሌለ ውሸት ተናገረ

ማር ሊሰፍሩ ማር ይናገሩ
- መልካም ተመኝ መልካም እንድታገኝ

ማር ሲበዛ ይመራል
- ከልክ በላይ የሆነ ነገር ያሰጠላል

ማር ሸጦ ሙን ይበሏል ፤ ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል
- ልጅን ከማንም አስበልጦ ነው የሚወደደው

ማር ነክቶታል ብለህ እጅህን አትላስ
- አማይጠቅም ነገር የሚጠቅም መስሎህ እንዳትታመም



ማርና ቅቤ ይጣፍጣሉ፤ ከየት ይገናኛሉ
- በሥራና በድካም እንጂ በምኞት የሚገኝ ነገር የለም

ማርና ንብ፤ ጽህፈትና ንባብ
- አብረው የሚሔዱ ናቸው

ማርና ወተት፤ ምን አገናኝቶት
- የማይመስሳሉ ናቸው

ማር አገባ አገባ ፤ ገደል ገባ
- ችግር ላይ ወደቀ

ማስጠንቀቂያም አትንሳኝ፤ መጠንቀቂያም አታድርገኝ
- ምክር ለግሰኝ በስሕተቴ አታዋርደኝ

ማሽላ ለማሽላ፤ ተያይዞ ቆላ
- ዓላማቸው አንድ የሆነ ይግባባሉ

ማሽላ ሲያር ይሥቃል፤ ትዕቢተኛ ሲንደላቀቅ ይወድቃል
- ልብ ሲያውቅ ሆድ ከደመኛው ይሥቃል

ማሽላና ነገር፤ ካንገት ካንገቱ
- ነገርን በአጭሩ መቅጨት

ማሽላና ዘንጋዳ፤ መከታና ጓዳ
- የሚቀራረቡ

ማቅ ይሞቃል፤ሻሽ ይደምቃል፤ ገቢውን ባለቤት ያውቃል
- ያለባለቤቱ አይነድም አሳቱ

ማባበል፤ መቅለል
- መለማመጥ ለመዋረድ

ማባበልና፤ ማንቆሻበል
- ማሞኘትና መደለል

ማተብና አንገት፤ ክታብና ደረት
- የምትደርስበትን አስቀድመህ ግምት ውስጥ አስገባ

ማኅበር ቀረ፤ ሴረኛ ተሻረ
- ጉዳይህ መፍትሔ አገኘ

ማነህን መዋኛ፤ቤተመቅደስ መገኛ
- በአምነትህ ከሎሎች ጋር የምትቀላቀልበት ቦታ አለ

ማን ሊሰምሽ፤ ታምጠሙጫለሽ
- ምንም ፈላጊ የለሽም

ማን ቢያሮጠኝ ፤ሉፋጭ ቀረጠኝ
- እንዲያው ዕዳ ከሜዳ

ማንነትህን እንዳውቅ ጓደኛህን ንገረኝ
- እናትየውን አይተህ ልጅቱን አግባ

ማን አለ መርማሪ አለ ፈጣሪ
- የሁሉ የበላይ አንድዩ ብቻ ነው

ማን ያልነበረ፤ ማን ያልተቀበረ

- ሁሉም ጊዜው ሲደርስ ጽዋው ይሞላል

ማን ያርዳ የቀበረ፤ ማን ይናገር የነበረ

- የሚያውቅ ሰው ብቻ ይናገር

ማን ያውቃል ባላገር፤ ማን ያጠብቃል ማገር

- ሕዝብ የሚያውቀውን አትደብቅ

ማን ያውቅ አገር፤ ማን ያጥብቅ ማገር

- ሕዝብ የሚያውቀውን አትደብቅ

ማን ይሙት ጠላት፤ ማን ይኑር አባት

- ለገቢህ ተንገብገብ

ማንን ታሸንፋለህ፤ ሚስቴን

- ሁሉም እንደአቅሙ

ማወቅ መላቅ፤ አለማወቅ መናቅ

- አለማወቅ ያስንቃል

ማወቅ እናውቃለን ፤ ብንናገር እናልቃለን

- ማወቅ እናውቃለን ብንናገር አደጋ ይደርስብናል

ማውራት ነው ሴትነት፤መሥራት ነው ወንድነት

- ወሬኛ መሆን ያዋርዳል

ማውራት ነው ድህነት፤ መሥራት ነው ጌትነት

- ሥራ እንጂ ወሬ ምንም አይሠራም

ማዕረግ ቢሉ፤ አራቱ ገሚስ

- ሲያከብሩት የማይከበር ሰው የሚያገኘውን ሙሉ በሙሉ አያገኝም

ማየት ከመልአክ፤ መቀበል ከአምላክ

- ለሁሉ የሚቸር ዓምላክ ብቻ ነው

ማጀት በጎረሰ፤ ደጃፍ በመለሰ

- በጠቅላላው ሁሉም ሰው

ማጀት ያጠለቀው፤ ጉልቻ የላቀው

- ፍጹም ድሃ ነው

ማግኘት ማውጣትን ያስለምዳል

- ያለው ሲያወጣ ሲመዝ አይጨነቅም

ማግኘት ማውጣትን ይመልሳል

- ገንዘብ የሚያከብራትን ታከብራለች

ማጣትና ማግኘት ጆሮ ለጆሮ

- አንድ ጊዜ ቢያገኝ ሌላ ጊዜ ሊያጣ ይችላል

ማጣት ከሰማይ ይርቃል

- ድህነት አስከፊ ነው

ማጥፋት፤ በትንሽዋ ጣት

- ገንዘብህን ጨርሰህ እንዳታጠፋ በትንሽ በትንሽ አውጣ



ማሟዱም ገመዱም ከሣሩ ውስጥ ነው

- መፍትሔው አብሮ አለ

ማፈር ከሌለ፤ ክብር የለም

- አጸያፊ ተግባር ማከናወን ያስንቃል

ማፈር ከብዙ ነገር ይጠበቃል፤ አለማፈር በብዙ ነገር ያስጠይቃል

- አጸያፊ ተግባር ካላከናወንክ ያስከብርሃል፤ አጸያፊ ተግባር ካከናወንክ ያስንቅሃል

ሚዳ መራመድ ሳታውቅ ፤ተመሳሳል መውጣት ማን አስተማራት

- በሳል ልጅ ነች

ምለህ በክርስቶስ ተገዝተህ በቁስ

- በጌታ ስም የገባኸው ቃል አክብር

ምላሱ አይታጠፍም

- ቃሉን ያከብራል

ምላስ ቢጥም ቀዶ ይጠቅም

- ምላስ ክፉም ደግም ይናገራል፤ያስከፋልም፤ ያስደስታልም

ምላስ ይቀባል፤ ጥርስ ይወጋል

- በፍላጐት የፈለጉትን ማድረግ ይቻላል

ምላጭ ለምላጭ ፤ጠፍር ለመለመጫ

- አንዱን በአንዱ ወደሚፈልጉት ማምራት

ምላጭ ምላጭን አይቆርጠው፤ ሰው ሰውን አይበልጠው

- ብልጥን ብልጥ አያታልለውም

ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡ

- መፍትሔ የሚያስገኘው ከተበላሸ መፍትሔ ለማግኘት ያስቸግራል

ምላጭ አይበጥ፤ ያበጠውን ያፈርጥ

- ብልጥ ሰው አያታለልም ጎበዝ አይደፈርም

ምስጢር ከቤት ፤ምክር ከጎረቤት

- ምስጢርህን አደባባይ አታውጣ

ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም

- ምስጢር በአደባባይ የሚነገር አይደለም

ምስጢር ይደበቃል፤ ወፍጮ አይደለም

- ምስጢር በምስጢርነቱ ይያዛል

ምርት ከገለባ፤ ግዳይ ከሰለባ

- የሚጠቅመውን ከማይጠቅመው ለይቶ ማወቅ

ምርትና፣ ፍትፍት

- ክፉና ደግ

ምሳሌህ ሁሉ አንካሳ ነው

- ነገርህ ሁሉ አይጥምም

ምስለኔ ሁሉ እንደኔ

- የእኔ ነው ያልኩት ሁሉ ከእኔ አይሻልም

ምስር መዝራት ሙያ ማጣት፤ አተር መዝራት ወይ ብልሃት እለች ጦጣ
- የማይወዱትን ማጣጣል የሚወዱትን ነገር ከፍ ከፍ ማድረግ

ምስርሽን በጥጥሽ
- እዚያው ወደእኔ አታምጪው

ምስር ብልት ይቀሰር
- የወሲብ ስሜትን ይቀሰቅሳል

ምሰር እራቱ ፤ምስር ቢያጣ ሞቱ
- ሰው የፈለገውን ቢያጣ ቅር ይለዋል

ምሰር ይሰብራል፤ ጓያ ያማርራል
- ጓያ የሰበረው ሰው እንደተማረረ ኑሮውን ይገፋል

ምሰክር ለበሰጠ አውድማ ለመሰጠ
- እመቺ ሁኔታን ለፈጠረ ድጋፍ ይሰጠዋል

ምስክር ቢያድር ይሰጠጣል ሽንፍላ ቢያድር ይመሰጣል
- ማንኛውም ነገር በጊዜው መከወን ይገባል

ምስክር ከበሰጠ ባቄላ ከፈጠጠ
- በበቂ ምስክር ማሸነፍ ይቻላል

ምስክር ከተጠራ መስዋዕት ከተሠራ
- አንድ ነገር ቆርጠው ካደረጉት በኋላ ለመቀየር ያስቸግራል

ምሰክር ያለው ሙግት እያዳግትም ለመርታት
- ምስክር ከበለጠ ባቄላ ካፈጠጠ

ምሰጋና አዋቂን ያበራታል ቂልን ያሳብዳል
- ምስጋና ያበረታታል

ምሰጥ ከምድር ውስጥ
- ውስጥ ውስጡን ተንኮል የሚፈጽም ሰው

ምቀኛ እታሳጣኝ
- ምቀኛ ያለው ሰው ሳለመውደቅ ተግቶ ይሠራል

ምቀኛ የኑሮ መጋኛ
- ምቀኛ ጠላት ነው

ምቀኛ ጠሳቱን ይተካል ወዳጁን ይንቃል
- ወዳጁን ለመጉዳት ለጠላቱ ቀዳዳ ይከፍታል

ምነው ቢገዙ መድን ካበዙ
- ዋስትና ካለው ብዙ አይጨነቅም

ምናልባት ቢሰበር እናት ቅቤ ሺ ለመተኮሻ
- የክረምት መሽጋገሪያህን በበጋ ተመልከተው

ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ
- ወንድ የበላይ ነው

ምንም በሙቱ እራድማ ሽምቱ
- ምንም ቢሆን ያው ይሻላል



ምንም ቢሆን ሥር ነው እንጂ እጢ አይደማም
- የማይሆን ሁሉ አይሆንም የሚሆነውን ከማይሆነው አታዛንቅ

ምንም ቢሆን ጉፋያ ሥጋ ሥጋ ነው
- ባያስደስትም ያው ተመሳሳይ ነው

ምንም ቢታረስ በዘጠና ቤቱ አይለቅም ቀጠና
- ከድህነት መላቀቅ አልተቻለም

ምንም ቢቸገሩ ተበድሮ ጋሬዳ
- ያልሆነ ብድር ውሎ አድሮ የከፋ ነገር ያስከትላል

ምንም ቢያጠምዱ በዘጠና ቤቱን አይተው ቀጠና
- ከድህነት መላቀቅ አልተቻለም

ምንም ቢጠም መንገድ ምንም ቢከፋ ዘመድ
- ምንም ዘመድ ቢቀየምም ለችግርህ ጊዜ ደራሽ ነው

ምንም ቢፋቀሩ አብረው አይቀበሩ
- ምንም ቢዋደዱ ለእየቅል ነው መንገዱ

ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ ምንም ብደኸይ ጨዋ ነኝ
- ማንነቴን ሳታውቅ አትናቀኝ

ምንም ብታውቅ ከዳኛ ጋር አትሟገት
- ችግር ውስጥ እንዳትወድቅ

ምንም ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ
- የትም አትደርሺ እንዲያው ደከምሽ

ምንም ብትሞቺ እንዴት እደርሽ አንቺ
- አልረሳሽም ሳስታውሽ እኖራለሁ

ምንም ብወድህ በወንድሜ ግንባር ደም አልይብህ
- ክፉ ነገር እንዲገጥመው አልመኝም

ምንም ብጠላው በወንድሜ ግንባር ደም አልይብህ
- ክፉ ነገር እንዲገጥመው አልመኝም

ምንሽም ምንሽም እያምረኝ ከመሄድሽ በቀር
- የሚያስደስት ባሕርይ የላትም

ምን በእግሩ ቢመጣ በእጁ እንዳይመጣ አለ ዳኛ
- የሚያቀብለውን ጉቦ እየተመኘ

ምን ቢለፈልፉ ድካም ነው ትርፉ
- በጭቅጭቅ ምንም አይገኝም

ምን ቢነግሡ በጅ አይካሉ
- ከግብርና ሥራ ውጤት ብዙ አያገኙም

ምን ቢኖሩ ከሞት አይቀሩ
- ሞት የማይቀር ዕዳ ነው

ምን ቢከፉ አሳብ ነው ትርፉ
- ሐሳብ ምንጊዜም ከሰው ራስ አይወርድም

ምን ቢወቅሱ በእጅ አይካሱ
- ከእርሻ ምርት ብዙ አያገኙም

ምን ቢወዱ ባዕድን አይረዱ
- ዞሮ ዞሮ ዘመድ ከዘመዱ፣ አህያ ካመዱ

ምን ቢዋደዱ ለየቅል ነው መንገዱ
- ምን ቢፋቀሩ አብረው አይቀበሩ

ምን ቢያርሱ እንደጕመን አይጕርሱ
- የተናቀ ነገር ችግር ያቃልላል

ምን ቢያርሱ ድንበር አያፋርሱ
- ሁሉም ነገር ወሰን ወይም ልክ አለው

ምን ቢያውቁ ዳኛ አይሆኑ ምን ቢያምሩ ሙሽራ አይሆኑ
- በምኞች ብቻ የሚሆን ነገር የለም

ምን ቢጠም መንገድ ምን ቢከፋ ዘመድ
- ቢቀየምም ለችግር ጊዜ ዘመድ ደራሽ ነው

ምን ቢፈሩ ከሞት አይቀሩ
- ሞት የማይቀር ዕዳ ነው

ምን እበላ ሲሉ እንግዳ ምን እለብስ ቢሉ ዕዳ
- ችግር በችግር ላይ ይደራረባል

ምን ያህል የተባለው ዝናብ በሰማይ ደረቀ
- በአጭሩ ተቀጨ

ምን ያመጣል ለኔ ምን ይሠራል በዘኔ
- የሚታወቅ ነገር የለም

ምን ያመጣ ድሃ ምን ያገሳ ውኃ
- ከድሃ ምንም የሚገኝ የለ

ምን ይሰማ ጆሮ ምን ይውጥ ጉሮሮ
- ጆሮ የማይሰማው የለም

ምን ይበላል ነጭ ምን ይጠጣል ጠጅ
- ሁሉ ሞልቶ ሁሉ ተርፎ

ምን ይዞ ጉዞ
- ተጨባጭ ነገር የለም

ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ሽንኩራ ሆኖ እብቁ ዓይኔ ገባ አለ
- የተጋነነ ውሸት አወራ

ምኞትና ጉም አይጨበጥም
- ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ

ምከረው ፃ ከረው ባይሰማ ንከረው
- ችግር ያስተምረዋልና ተወው

ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው
- ችግር ያስተምረዋልና ተወው



ምክር ለሚሰማ፤ ውኃ ለቁጠማ
- ውጤት ለምታገኝበት ሥራ በርትተህ ጣር

ምክር ተቀባይ ሲያጣ ተመልሶ ወደባለቤቱ ይመጣ
- እንዲያው ከንቱ ልፋት መሆኑ ነው

ምክር ከሽማግሌ ነው ወንዝ መሻገር ከጉበዝ ነው
- የሽማግሌን ምክር መቀበል አለብህ

ምክር ከድሃ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ
- የድሀን ምክር የሚሰማው የለም

ምክር ዝክር በምድር ልጅ ተመክር
- ምክርን የሰማ በሕይወቱ ይጠቀማል

ምክር የብልህ ሀብት የግልህ
- ሁሉም ሰው እኩል አይደለም

ምክንያት እንደሴት ግርማ እንደሴት
- ሴቶች ዘዴኞች ናቸው

ምድር ሲደላደል ማላ ሲታደል ተወለድኩኝ አለ ጦጣ
- የተጋነነ ውሸ

ምድር በአለቃ ሰማይ በጨረቃ
- ሠራዊት በአለቃ ሲመራ ይደምቃል

ምድር በወለደች ነደደች
- እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች

ምድር በዛፍ ሕግ በመጽሐፍ
- ለሕዝብ የሚበጀው በሕግ መመራት ነው

ምድር በዶሮ ያውስ ማን ገብሮ
- የማይሆን ነገር መመኘቱ ዋጋ የለውም

ምጡን እርሺው ልጁን አንሺው
- በልጅሽ ተካሰሻል

ምጥ ለእናትየዋ አስተማረች
- የተገላቢጦሽ ነገር

ሞተ በለኝ ከፈኔን አለ በለኝ ቀለቤን
- ለሕይወቴና ለሞቴ ጊዜ የሚሆነኝን እድርግልኝ

ሞቴን ሞት ወሰደው
- ተፈወስኩ ዳንኩ

ሞትህ እንደሕይወትህ ሕይወትህ እንደሞትህ
- ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች

ሞት ካልቀረለት ምክንያቱ በይሁዳ ሆነበት
- የሚሆነው ሲሆን በእንተ ምክንያት እንዳይሆን ተጠንቀቅ

ሞት ሳይቀርለት ምክንያት ባልሆነበት
- አንተ በምክንያት ከመጠቀስ ዳን

ሞት ሳይቀር ፍርኃት ዓመል ሳይቀር ቅጣት
- ሳይቀር ፍርኃት አያስፈልግም

ሞትም ሞት ነው ያህያ ጉበት ነው
- የአህያ ጉበት እንደማይፈለግ ሁሉ ሞትም አይፈለግም

ሞት ርስት ነው መፍራቱ ለምንድነው
- ሳይቀር ፍርኃት አያስፈልግም

ሞት ሲደርስ ቄስ ጦር ሲደርስ ፈረስ
- ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

ሞት ሲገድል መቃብር ሲቀበል በቃኝ ጠገብኩ አይል
- መጨረሻ የሌለው ነገር

ሞት በአቤት ተዝካር በሮቤል
- ሁሉም ነገር መነሻ አለው

ሞት በአንቅልፍ ይሰመዳል
- ተመሳሳይነት አላቸው

ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር
- የማይመስል ነገር

ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስል
- አይመጣም ብሎ መዘናጋት የለም

ሞትና ዕድሜ ቢፈሩት አይቀርም
- መሆኑ ሳይቀር መጨነቅ አያስፈልግም

ሞትን ማስብ ከሁሉ መሰብሰብ
- ሞት ሳይቀር መቀያየም አያስፈልግም

ሞትን የሰጠ ቀባሪ አይነሳም
- ሳይደግስ አይጣላም

ሞትን ያህል ዕዳ መቃብርን ያህል አንግዳ
- ሞት ምንጊዜም አስደንጋጭና አዲስ ነው

ሞት አይለመድ ጉሽ አይጠመድ
- ሁልጊዜ አንግዳ ነው

ሞኝ ሁለት ጊዜ ይሥቃል
- መጀመሪያ ሳይገባው ሰይምሰል ይሥቃል ሲገባው ደግሞ ይሥቃል

ሞኝ ሰራሱ ያውቃል
- ራሱን አይጥልም

ሞኝ ለጠበቃው ምስጢር ይሸሽጋል
- ራስን በራስ መጉዳት

ሞኝ መካሪውን ባለጌ አክባሪውን እይወድም
- ሲመትሩለት የሚነጭ

ሞኝ ሰው ሁለት ጊዜ ያለቅሳል
- የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ



ሞኝ ሲናገር ብልህ ያዳምጣል
- ዕውቀት ይቀስማል

ሞኝ ሲቃበጡት የመቱት ይመስለዋል
- ሳያስተውሉ መቻኮል

ሞኝ ሲያከብሩት የፈሩት ይመስሰዋል
- ያሳዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል

ሞኝ በብልህ ይሥቃል
- አለማወቅ ያስተቻል

ሞኝ ቢስቱት የወጉት አይመስለውም
- የተስነዘረበትን አደጋ ባያደርስበትም አንደቀላል ይቆጥረዋል

ሞኝ ቢቆጡት የመቱት ይመስለዋል
- ሞኝ ሲቃጡበት የመቱት ይመስለዋል

ሞኝ ቢፈርዱስት አያውቅ ቢፈርዱበት አያውቅ
- ሞኝ ቢጠቅሙትም ቢጐዱትም አያውቅም

ሞኝ ቢፈርዱ ሞኝ ይወልዱ
- የእጅህን አታጣውም

ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር
- ዘመዶቹ ያፍሩበታል

ሞኝ ቤት ቢሠራ በልጥ ይመራ
- ዘላቂነት የሌለው ውሽልሽል ሥራ

ሞኝ ተላላ አበላል የት ያውቃል ፈትፈትው ሲያጉርሱት መዋጥ ያቅተዋል
- ሲመትሩለት የሚነጭ

ሞኝ ተናጋሪ ከፋውን በፊት ደጉን በኋላ
- ካስቀየመ በኋላ ለማስተካከል መሞከር ትርፉ ልፋት ብቻ ነው

ሞኝ ነጋዴ በራሱ መቀማት ሳያዝን ጓደኛው በማምለጡ ይቆጫል
- ሞኝ ሰው በማያስቆጨው ነገር ይቆጫል

ሞኝና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም
- ሞኝ የያዘው ፈሊጥ ውሻ የደፋው ሊጥ

ሞኝና ወፍራም ራሱን አያውቅም
- ሞኝ አስተዋይነት ይጐድለዋል

ሞኝና ውኃ እንደወሰዱት ይሔዳል
- በሰው ይመራል እንደቦይ ውኃ ይመራል

ሞኝና ጉታ እንዳይንገላታ
- የእህል ማስቀመጫው አንዳይበላሽ ሞኝም በሞኝነቱ እንዳይንገላታ መተው

ሞኝን ለሣቅ ሰልቻን ለስንቅ
- ሰሌሳ ለጠቃሚ ነገር አይበቁም

ሞኝ አሞራ ያባቱን ዋሻ ይጠየፋል
- እደጅ ያለ ጸበል ልጥ ይነከርበታል

ሞኝ አሳላፊ ወንድሙን ይጎዳል
- ያስማወቅ ያለመረዳት

ሞኝ አንዳጅ ግንዱን በውስጥ ጭራሮውን በላይ
- ሞኝ ሥራውን በሥረዓት ማከናወን አይችልም

ሞኝ አያውቁብኝም ባይ
- በሉቤት አለሉ ብልጥ የለም

ሞኝ እንደነገሩት በቅሎ እንዳለገሩት
- በነዱት የሚነዳ

ሞኝ ከመካሩ ቤት እሳት አይሞቅም
- ሲመከሩት የጐዱት ይመስለዋል

ሞኝ ከመካሪው ዕውር ከመሪው ይጣላል
- አቅምን አለማወቅ የነገን አለማለብ

ሞኝ ከመውለድ ማስወረድ
- ቢኖርም ብዙ ጠቀሜታ የለውም

ሞኝ ከጠገበበት አይወጣም
- የፋሲካ ዕለት የተገዛች ባሪያ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል

ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ
- ሞኝ ካገደደ ልጅ ከሰመደ

ሞኝ ካገደደ ልጅ ከለመደ
- ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ መመለሻ የለውም

ሞኝ ወርውሮ ቢስት የወጋ አይመስለውም
- ሞኝ ቢስቱት የወጉት አይመስለውም

ሞኝ ወታደር ሚስቱን ጥሎ መንደር
- አላልፎ ለሌላ ለው ይለጣል

ሞኝ ውኃ ሲወስደው ይሥቃል
- የኋላውን አለመገንዘብ

ሞኝ ዝም ሲል ዐዋቂ ይመስላል
- ዝምታ ሞኝና ብልጡን ሰመለየት ያስቸግራል

ሞኝ የለቱን ብልህ ያመቱን
- ሞኝ የሚያስበው ለዛሬ እንጂ ለነገ አያውቅም

ሞኝ የመከሩት ዕለት ቁንጫ የጠረገ ዕለት ይብሳል
- ሞኝ ሲመክሩት ፈሪ ሲሸሹለት አይወድም

ሞኝ የተከሰውን ልባም አይነቅለውም
- ሞኝ ያበላሸውን ለማስተካከል ከፍተኛ ድካም ይጠይቃል

ሞኝ የያዘው ብር ለብልህ ስንቁ ነው
- ብልህ ከሞኝ ስለሚጠቀም እንደራሱ ይጠቀምበታል

ሞኝ የያዘው ፈሊጥ ውሻ የደፋው ሊጥ
- ሞኝና እና ወረቀት የያዘውን አይለቅም

ሞያ ያለ መልክ ብቻ ዓመል ያለ ነገር ብቻ አስቸጋሪ ሰጋብቻ
- መልክ ብቻ ለትዳር አይሆንም ሙያና ዓመል ከሌላት ለትዳር አትፈለግም

ሞፈር ቆራጭ አርፍ አይታየውም በግላጭ
- በደንብ የምትፈልገው ነገር አጠገብህ እያለ ይሰወራል



## ሠ

ሠመረ ካሉ፣ ግብሩን ያሳያሉ።
- ከሠመረ በተግባር መታየት አለበት

ሠምና ወርቅ፣ እንጀራና መረቅ።
- ፍቅር ናቸው።

ሠምና ፈትል ካልተዋሃዱ ብረሃን የላቸውም።
- አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ።

ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ።
- ጦር መጣ ሲባል ሶማያ ቆረጣ።

ሠርገኛ ሳይመጣ፣ ሙሽሪት ትምጣ።
- ትክክል ያልሆነ ነገር ተፈጸመ።

ሠርገኞች መጡ፣ ብቅል አስጡ።
- ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ።

ሠርጉን ተዝካር ትለዋለህ።
- የሚያስደስተውን ነገር የሚያስከፋ አደረገው ።

ሣር ማጨድ በማጭድ ቤት መምረግ በጭቃ በጭድ።
- ተስማሚ መሣሪያ ማግኘት ጥሩ ነው።

ሣር ሲበቅል፣ ፈረስ ይሞታል።
- የምትፈልገውን ነገር ሲገኝ ፈላጊው ይጠፋል።

ሣር ያልለጧት ላም፣ ወተት እምጪ ቢሏት።
- ያልተንከባከቧትን ላም እምጪ ቢሏት ጥቅም አታስገኝም።

ሣር ይሸከሟል ለበሬ፣ ቆንጆ ያገባል ለወሬ
- ለገዘና ሳይሆን ለዘለቄታው ማለቡ ይጠቅማል።

ሣቅ ሲበዛ ለቅሶ ይሆናል።
- ማር ሲበዛ ይመራል።

ሣቅ ያበዛ ይቀላል፣ ዝምታ ያበዛ ይከብዳል።
- ቀልድና ጨዋታ ያዋርዳል ዝምታ ደግሞ ይከብዳል።

ሥልጡን እንግዳ፣ ይውላል እንዳ።
- እንግድነቱ ወደአገልጋይነት ተለወጠ።

ሥሩን የጠላ፣ እራሱን የጠላ።
- ወገንን መጥላት እራስን መጥላት ማለት ነው።

ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ላጣሪው።
- መጥፎ ሰው በራሱ ተንኮል ይጠፋል።

ሥራ ለሠሪው፣ ወሬ ላውሪው።
- ባወሩት ወሬ ጉዳቱ በራሳቸው ላይ ደረሰ።

ሥራ ከመፍታት፣ ልጄን ላፉታት።
- ያማይረባ ሰው ጊዜውን በከንቱ ያሳልፋል።

ሥራ ከሚፈቱ፣ አፍዎን ያፉቱ።
- የማይጠቅም ጉዳይ ላይ! መነጋገር ፋይዳ የለውም።

ሥራ ካልሠራችሁ፣ የት ይገኝ ምሣችሁ።
- በሐምሌና በነሐሴ ተግተው ካላረሙ እህል የት ይገኛል ከድንበር ቢቆሙ።

ሥራ ያጣ ለማኝ፣ አፍሶ ይለቅማል።
- ሥራ ፈት ሰው በከንቱ ጊዜውን ያባክናል።

ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ የሰፋል።
- ሥራ ያጣ ለማኝ፣ አፍሶ ይለቅማል።

ሥራ ያጣ፣ ሙቅ ያኝካል።
- ሥራ ፈት ሰው ምንም ውጤት የማይገኝበትን ሥራ ይሠራል።

ሥራ ያጣ፣ ሚስት ያወጣ።
- ሥራ ፈት ነገ መቸገሩን ሳያውቅ አጉል ሥራ ይሠራል።

ሥራ ያጣች፣ እፍ ሞት ትጠራለች።
- አጉል ንግግር ችግር ላይ ይጥላል።

ሥራ ያጣ፣ ገበሬ፣ በሰኔ ይሞታል።
- በሥራው ጊዜ እሱ ይታጣል።

ሥራ ያጣ ገበሬ፣ ጨው የሌለው በርበሬ
- ካልሠሩ ትዳር፣ ሕይወት አይሟላም

ሥራ ያጣ ገንፎ ያላምጣል።
- ሥራ ፈት ሰው የማይረባ ተግባር ያከናውናል።

ሥራ ያጣ፣ ጢስ ይሞቃል።
- ሥራ የጣ ገንፎ ያላምጣል።

ሥርዓት ያናግራል፣ ዕርቅ ያፋቅራል።
- ሁሉ ነገር በአግባቡ ሲሆን ያስደስታል።

ሥንዴ ለመቁረብ፣ ዋስ ለማቅረብ።
- እያንዳንዱ በሚፈለግበት ቦታ ሲገኝ።

ሥንዴ ምን አልኩ ዘመዴ፣ ምስር እስኪቀስር፣ አተር እስኪተረተር፣ ባቄላ አንተም እንደሌላ።
- እንተም እንደሌሎቹ ክፉ ሆንህ።

ሥንዴ ራቱ፣ ወይራ እሳቱ፣ ማለፊያ ሚስቱ፣ ለምን ሠርግ ይሄዳል፣ ሠርግ አለ በቤቱ።
- ጥሩ ትዳር ሁልጊዜ እንዳስደሰተ ነው።

ሥንዴ በማዶ፣ ይመስላል በረዶ።
- የሰው ባህርይ የሚታወቀው ከተግባቡ በኋላ ነው።

ሥንዴ በጭንቅ፣ ባለጌ በጥብቅ።
- ባለጌን በቅርብ መቆጣጠር ያስፈልጋል።

ሥንዴ ካለ፣ ፈታጊ አይጠፋም።
- ሥራ ካለ የሚሠራው ሰው እይጠፋም።

ሥጋ ለሥጋ ነው።
- ዘመድ ለዘመዱ እህያ ካመዱ።

ሥጋ ለጥጋብ፣ አጥንት ለትካዜ።
- አጥንት ላይ ያለን ሥጋ ሲበሉ በትዕግሥት ነው።



ሥጋም እጅግ ፍረጋቱን አበዛው፣ በመንቀጥቀጥ።
- እጅግም መርበድበድ ከሆነ ወዲያ ዋጋ የለውም።

ሥጋ ሰጥተው፣ ቢለዋ ቢነሱት።
- ሱሪ ሰጥተው አትቀመጥበት።

ሥጋ ሲያመልጥህ፣ በቆዳው ታጠቅ።
- ያገኘኸውን ሳትንቅ ተጠቀምበት።

ሥጋ ቀረ ዕዳ ቀረ ቀለለ።
- ሥጋ ቀረ ሰላም ሰፈነ።

ሥጋ ቀርቦለት ዐይኑ ወደፈርሰ።
- ጥሩ ነገር ቀርቦለት የማይረባ ነገር ላይ ማተኮር።

ሥጋ ቁጠር ቢሉት፣ ጣፊያ አንድ አለ።
- የሚጠቀመውን ምረጥ ቢሉት የማይጠቀመውን መረጠ።

ሥጋ በገበታ፣ ሹመት በተርታ።
- ሁሉም ነገር በሥርዓት ይከናወናል።

ሥጋ ቢወድቅ፣ ዐፈር ይዞ ይነሳል።
- ችግሩ ሌላ አስከትሎ ይመጣል።

ሥጋን ከጥሬው ነገርን ከወሬው።
- የሚበጀውንና ጠቃሚውን መለየት መቻል።

ሥጋ ያማረው መረቅ የሸተተው፣ ከበጎች መሃል ገብቶ ይተኛል።
- ሆዳም ቢፈተፍት የጠገበ ይመስለዋል።

ሥጋ ያማረውን፣ ልኳንዳ አትውሰደው።
- በጣም አታስጨንቀው።

ሥጋው ያሳማ፣ ከበላው የሰማው ገባ።
- የሆነው ቀርቶ ያልሆነው።

ሥጋ ያንገፈገፈው ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል።
- እባብ ያየ በልጥ በረየ።

ሥጋዬን ላራዊት፣ ነፍሴን ለገነት።
- መሥዋዕት ለመሆን ተዘጋጅቻለሁ።

ሦስቱን ቢጠጣቸው፣ ሁለቱን ጣላቸው።
- ሥራ ላይ የሚውለው በከፊል

ሦስት ጉልቻ ይሰጥህ።
- ትዳር ያዝ።

ሦስት ጊዜ ለካ፣ አንድ ጊዜ ቅደድ።
- ከመሥራትህ በፊት ደጋግመህ አስብ።

ሦስት ጊዜ ሰላምታ፣ አንዱ ለነገር ነው።
- ደጋግሞ ነገር ማንሳት ጥል እንደመፈለግ ነው።

## መልመጃ 2 /መገው/

## ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. ማን ይናገር የነበረ ________
ሀ. ማን ያርዳ የነበረ ሐ. ማን ያልቅስ የዘፈነ
ለ. ማን ያስተምር ያነበበ መ. ማን ይብላ የተራበ

2. መልክ ጥፉ ________
ሀ. በልብስ ይደግፉ ሐ. በጌጥ ይደግፉ
ለ. በስም ይደግፉ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

3. ________ ሰባሏ ዘውድ ናት
ሀ. መልካም ሴት ሐ. መልካም ሚስት
ለ. ኩሩ ሴት መ. እመቤት ሚስት

4. ሥራ ሰሠሪው ________ ላጣሪው
ሀ. ወሬ ለ. እጥር ሐ. እሾህ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

5. ማጥፋት ________
ሀ. በውኃ ለ. በትንሽዋ ጣት ሐ. በእውራ ጣት መ. ለእናሐ

6. ማጣትና፣ ማግኘት ________
ሀ. ጆሮ ለጆሮ ሐ. እኩል ናቸው
ለ. አይነጣጠሉም መ. መልሱ የለም

7. ሠርገኞች መጡ ________
ሀ. እጩብጭቡ ሐ. ሆይሎጋ በሉ
ለ. ተቀበሏቸው መ. ብቅል አስጡ

8. መሸጥ የለመደ ________
ሀ. ሥራ የለመደ ሐ. እናቱን ያስማማል
ለ. ገበያ ይወጣል መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

9. ሚያ ባልኩ ________
ሀ. ፍየል ተባልኩ ሐ. ድመት ተባልኩ
ለ. ፍየል ከፈልኩ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

10. ማሩን እምሮ ________
ሀ. ሬቱን አጣፍጦ ሐ. ሻይውን አጥቁሮ
ለ. ወተቱን አጥቁሮ መ. ቡናውን አጥቁሮ

11. ሞፈር ቆራጭ ________
ሀ. እርፍ አይታየውም ሐ. ገበሬ ነው
ለ. የሚቆርጠው አይታየውም መ. መልሱ የለም



12. ሥራ ከመፍታት ________
ሀ. ልጅን ላሠራት ሐ. ልጅን ላፋታት
ለ. አፌን ላፍታታ መ. ሚስቴን ላጋባት

13. ሥጋ ቁጠር ቢሉት ________
ሀ. ከጭንቅላት ጀመረ ሐ. እሺ አለ
ለ. አልቆጥርም አለ መ. ጣፊያ አንድ አለ

14. ምስር ________ ይቀስር
ሀ. ጣት ለ. ብልት ሐ. እግር መ. መልሱ የለም

15. መቀመጥ ________
ሀ. እረፍት መውሰድ ሐ. መቆመጥ
ለ. መሯሯጥ መ. መልሱ የለም

16. ሣቅ ሲበዛ ________ ይሆናል።
ሀ. ማር ለ. ቁጣ ሐ. ጨዋታ መ. ለቅሶ

17. ሥራ ያጣ ________ ያኘካል።
ሀ. ሥጋ ለ. ድንች ሐ. ሙቅ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

18. ሥንዴ በጭንቅ ________ በጥብቅ።
ሀ. ባለጌ ለ. ጨዋ ሐ. ጎበዝ መ. ሰነፍ

19. ሥንዴ በማዶ ይመስላል ________ ።
ሀ. ስንደዶ ለ. በረዶ ሐ. ሀረም መ. ገብስ

20. ሥራ ያጣ ገበሬ ________ ይሞታል።
ሀ. በመስከረም ለ. በግንቦት ሐ. በሰኔ መ. በሐምሌ

21. ሦስቱን ቢጠጣቸው ________ ጣላቸው።
ሀ. አንዱን ለ. አራቱን ሐ. በጠረባ መ. ሁለቱን

22. መልኩ የኔ ________
ሀ. ግብሩ ያረመኔ ሐ. ጉብዝናውም እንደኔ
ለ. ጸባዩም እንደኔ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

23. መልካም ሚስት ለባልዋ ________ ናት።
ሀ. ኃላፊ ለ. ተቆጣጣሪ ሐ. ዘውድ መ. ሁሉም መልስ ነው

24. መልካም በሬ ለእርሻ ________ አያሻ።
ሀ. ገበሬም ለ. ጢስኛም ሐ. ዘርም መ. ዶማም

25. ሣር ይሸከሚል ለበሬ ________ ለወሬ።
ሀ. ቀንጆ ያገቧል ሐ. ጋዜጠኛ ያገቧል
ለ. አዝማሪ ያገቧል መ. ሁሉም መልስ ነው

26. ሥርዓት ያናግራል ________ ያፋቅራል።
ሀ. ገንዘብ ለ. ሀብት ሐ. ዕርቅ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

27. ሥንዴ ካለ ________ አይጠፋም።
ሀ. ተመጋቢ ለ. መጋቢ ሐ. ፊታጊ መ. አስፈጪ

28. ሥጋ ከጥሬው ________ ከወሬው።
ሀ. ጋዜጠኛ ለ. አስተማሪ ሐ. ነገርን መ. ሁሉም መልስ ነ

29. ሥጋ ቢወድቅ ________
ሀ. አንሽው ብዙ ሐ. የከሳህ ትመስላለህ
ለ. ለውሻ ሠርጉ ነው መ. ዐፈር ይዞ ይነሳል

30. ማባበል ________።
ሀ. መለማመጥ ሐ. ማስላሰል
ለ. መቅለል መ. መፎገር

31. ምቀኛ ________ መጋኛ
ሀ. የሐሳብ ለ. የመንገድ ሐ. የኑሮ መ. የሰው

32. ማር ሲሰፍሩ ________ ይናገሩ።
ሀ. ውሸት ሐ. ሬት
ለ. እውነት መ. ማር

33. መናኛ ለነፍሱ ________ ይገስግሱ።
ሀ. ጅብ ሊጎርስ ሐ. ውሻ አጥንት ይዞ
ለ. አዳኝ ለጥርሱ መ. ሁሉም መልስ ነው

34. መናገር ________ ነው። ዝምታ ወርቅ ነው።
ሀ. ብር ለ. ወርቅ ሐ. ነሐስ መ. አልማዝ

35. መርፌ ውጦ ________ መትፋት
ሀ. ሐኪም ቤት ለ. በሠገራ ሐ. ማረሻ መ. አፍ

36. መንደር ከዋለ ንብ ________
ሀ. ጫካ የዋለ ውሻ ሐ. ያለሥራ የተቀመጠ ይሻላል
ለ. ሥራ የዋለ ሰው መ. አደባባይ የዋለ ዝንብ

37. ማምሻም ________
ሀ. ዕድሜ ነው ሐ. መማቻም
ለ. አይከፋም መ ሁሉም መልስ ነው

38. ሥጋ ሰጥተው ________
ሀ. ሱሪ ከለከሉት ሐ. ማረሻ ከለከሉት
ለ. ቢለዋ ከለከሉት መ. ሁሉም መልስ ነው

39. ሥጋ ቀርቦለት ________
ሀ. ቢለዋ ከለከሉት ሐ. ዐይኑ ወደፈርስ
ለ. ዐይኑ ወደ ድስት መ. ጎመጀ

40. ማወቅ እናውቃለን ________
ሀ. አላስተማርንም እንጂ ሐ. አልተጠቀምንበትም
ለ. ብንናገር እናልቃለን መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው



41. ምን ቢያርሱ ________
ሀ. ከድህነታቸው አልተላቀቁ ሐ. እንደጎመን አይጎርሱ
ለ. ለገበያ አያቀርቡ መ. መልሱ የለም

42. መመራመር ________
ሀ. ያራቅቃል ሐ. ያገባል ወስዋስ
ለ. አጉል መራቀቅ መ. ያደርሳል ቁም ነገር

43. ምጡን እርሺው ________
ሀ. የተኛውን ቀስቅሺው ሐ. ላለፈ ነገር አትጨነቂ
ለ. አታስታውሺው መ. ልጁን አንሺው

44. ሙት መውቀስ ________
ሀ. ያወቃቅስ ሐ. ድንጋይ መውቀስ
ለ. ደግ አይደለም መ. ውኃ ማፍሰስ

45. መጫር ያበዛች ዶሮ
ሀ. የመታረጃዋን ካራ ታወጣለች
ለ. ሰው ትረብሻለች
ሐ. ለጭልፊት ትዳረጋለች
መ. ሁሉም መልስ ነው

46. ማጀት ያጠለቀው ________
ሀ. ደጃፍ ያላጸዳው ሐ. ጉልቻ የላቀው
ለ. ውኃ የበላው መ. መልሱ የለም

47. ሣር ሲበቅል ________
ሀ. ሙጃ ይበዛል ሐ. አንበሳ ይሞታል
ለ. ጥጋብ ይሆናል መ. ፈረስ ይሞታል

48. ሠምና ወርቅ ________
ሀ. አይስማሙም ሐ. እንጀራና መረቅ
ለ. ብርና ነሐስ መ. እንጀራና ቂጣ

49. ሥሩን የጠላ ________
ሀ. ጓደኛውን የጠላ ሐ. እህቱን የጠላ
ለ. ዘመዱን የጠላ መ. እራሱን የጠላ

50. ሥጋ በገበታ ________
ሀ. ሹም በተርታ ሐ. ተማሪ በተርታ
ለ. ሠራተኛ በተርታ መ. ሁሉም መልስ ነው

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺውን ምረጥ</u>

1. ሦስት ጉልቻ ይስጥህ
ሀ. ትዳር ያዝ ሐ. ጧሪ አግኝ
ለ. ቤት ሥራ መ. ሁሉም መልስ ነው

2. ሦስት ጊዜ ለካ፣ አንድ ጊዜ ቅደድ
   ሀ. ለሰነፍ ሠራተኛ ሐ. ከመሥራትህ በፊት ደጋግመህ አሰብ
   ለ. ላልተማረ ሰው መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

3. መርፌ ሰርቆ ማረሻ ቢተኩ ልብ አይሞላም
   ሀ. ተይዞ ከመለማመጥ አርፎ መቀመጥ
   ለ. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቅንቁ
   ሐ. በውል ከሔደች በቅሎዬ ያለውል የተበላች ቆሎዬ
   መ. ሳል ይዞ ሰርቆት ቂም ይዞ ጸሎት

4. መቼ መጣሽ ሙሽራ መቼ ቆረጠምሽ ሽንብራ
   ሀ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
   ለ. ከምንጊዜው ነገር ጀመርሽ
   ሐ. ባፍ ይጠፉ ይለፈልፉ
   መ. መልሱ የለም

5. መጥፎ ሣር ይለመልማል እንጂ አይጠፋም
   ሀ. የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል
   ለ. ልማደኛ ልማዱን አይተውም
   ሐ. ቀን እስኪወጣ ታገስ
   መ. ሰነፍ ለሰነፍ ተያይዘው ይወድቃሉ

6. ሞኝ የተከለውን ልባም አይነቅለውም
   ሀ. ሞኝ ያቆመው ያወጀ የተማረ ሊለውጠው ያዳግተዋል
   ለ. መተባበር ኃይል ነው
   ሐ. ያባይን ልጅ ውኃ ጠማት
   መ. መልሱ የለም

7. መታፈር በከንፈር
   ሀ. በምላስህ ተናገርበት
   ለ. ሰው በምላሱ ይከበራል ወይም ይዋረዳል
   ሐ. የተገላቢጦሽ ሆነ
   መ. መልሱ የለም

8. መጽሐፍን የማይወድ ተማሪ በጁ አስተምረው
   ሀ. እየገረፍክ አስረደው
   ለ. በግድ ት/ቤት ውሰደው
   ሐ. የእጅ ሥራ የሙያ ትምህርት አስተምረው
   መ. የቀለም ት/ቤት አስገባው

9. ምላጭን ምላጭ አይቆርጠውም
   ሀ. ደነዝ ለደነዝ አብረህ አዝግም
   ለ. ብልጥ ለብልጥ ዐይን ብልጥጥ
   ሐ. ሞኝን ሞኝ አይሰርቀውም
   መ. አትርፍ ባይ አጉዳይ



10. ማሽላና ነገር፣ ካንገት ካንገቱ
   ሀ. ነገርን ቶሎ ሜር
   ለ. ነገርን ባጭሩ መቅጨት
   ሐ. ነገረኛን በካራ በለው
   መ. መልሱ የለም

ሐ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ሥራ ከመፍታት ልጂ ላፋታት | ሀ. | ለነገር ተዘጋጀ |
| 2. | መላ ቅጡ | ለ. | ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሰበሩ |
| 3. | መቃን ከመግጨት ዝቅ ብሎ መግባት | ሐ. | ተለማመጠ |
| 4 | ማን ያውቃል አገር ምን ያጠብቃል ማገር | መ. | መፈቃቀርን መስማማትን የሚገልጽ |
| 5. | ምላሱን አሾለ | ሠ. | ዝብርቅርቁ |
| 6. | ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር | ረ. | ዝም አይነቅዝም |
| 7. | መሬት ላሰ | ሰ. | ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል |
| 8. | መርፌ የምትሾልክበትን እንጂ የሚከተላትን ክር አታይም | ሽ. | ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት |
| 9. | መንፈራገጥ ለመላላጥ | ቀ. | የምትከነንን ነፍስ ጎረቤት ያውቃታል |
| 10. | መናገር ብር ነው፣ ዝምታ ወርቅ ነው | በ. | በስሕተት ጥፋተኛ ያልሆነውን መጉዳት እንደማይገባ |
| 11. | መስከረም በአበባው ሠርግ በጭብጨባው | ተ. | እሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ |
| 12. | ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ | ቸ. | የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው |
| 13. | ምጥ ስናትዋ አስተማረች | ኀ. | ለቀባሪው አረዱት |
| 14. | መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ ብዙ ጨርቅ ትጠቅማለች | ነ. | ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ |
| 15. | ሥጋ ያማረው ከበጎች መሀል ገብቶ ይተኛል | ኘ. | ሆዳም ቢፈተፍት የጠገበ ይመበለዋል |
| 16. | መንካት ያደርባል ከመነካት | አ. | ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ |
| 17. | መርፌ ሲለግም ቅቤ አይወጋም | ከ. | ዕዳ ከሜዳ |
| 18. | ማቅ ይሞቃል፣ ሻሽ ይደምቃል፣ ገቢውን ባለቤቱ ያውቃል | ወ. | መቼ ገባህ ፊት፣ ምን በላህ ፍትፍት |
| 19 | ሞኝ ሰው ሁለት ጊዜ ያለቅሳል | ዘ. | በሬ ሆይ ሣሩን ዐየህና ገደሉን ሳታይ |
| 20. | ማማው ሞረት ማሽላው ቅንብቢት | ገ. | የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ |
| 21. | ማን ባሮጠኝ፣ ሱሩጭ ቆረጠኝ | የ. | ሞኝ ካገደደ ልጅ ከለመደ |
| 22 | መዘዙን ሳታይ፣ መልኩን አይታ | ደ. | አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትወጣለች |
| 23. | መንገድ ለቀደመ ውኃ ለገደበ | ጀ. | ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማማ |
| 24. | ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ | ገ. | አራንባና ቆቦ |
| 25 | ማማት የለመደ አፍ ሲዶልት ያድራል | ጠ. | አፍ ሲያርፍ ወዳጁን ያማል |

## ረ

ረባዳ ቤቱ፣ ገራም ሚስቱ
- ምቾትንና የሚስት ሁኔታ

ረኸሮሙን ባላማ፣ አጭሩን በጫማ
- ጠላትን እንደየአስፈላጊነቱ ማጥቃት ይገባል

ረኸርም ባይፈራ፣ አጭር ባይኮራ
- ሁሉም የየራሱ ችግር ይኖረዋል

ረኸርምና ቀፉፉ፣ ገደልና ፈፋ
- ረኸርም ሰው ንትርክ አይወድም

ረኸርም ጦር፣ ባይወጉበት ያስፈራሩበት
- ወንድም ስግርግርታ ጋሻ ለመከታ

ሩቅ አሳቢ፣ ቅርብ አዳሪ
- እንዳሰቡት ላይሳካ ይችላል

ሩቅ አገር፣ ለውሸት ይመቻል
- ስደት መሔድ ለወሬ ይመቻል

ሩዋጭና በራሪ፣ ንፋግና ፈሪ
- ብዙ ባይመሳሰሉም ይቀራረባሉ

ራሱን ለተላጨ፣ ፊቱን ለነጨ
- በጣም ላዘነ ለተከዘ

ራሱን የማይችል አንገት፣ ባለቤቱን የማያስገባ ቤት
- ለላም ቀንዷ አይከብዳትም

ራሴን መትቶ እግሬን፣ ቢያከኝ አይገባኝም
- ቢሸነግለኝ አልቀበለውም

ራስ ሲመለጥ፣ ነገር ሲያመልጥ
- አፍ ሲያድጥ ከተልባ ይብሳል

ራስ ሳይጠና ጉተና
- ውታፍ ሳይሆኑ ዝቋላን ለመሆን መሞከር

ራስ ተላጭቶ ወለባ፣ ልባልማ ታጥቆ አዛባ
- የማይሆን ነገር

ራስ ተከናንቦ፣ ሙርጥን ገልቦ
- ሥራ የተባለውን ትቶ ያልታዘዛውን መሥራት

ራስን አይችል በድጋፍ፣ ኋላም ለጉድፍ
- ቢመክሩት ቢዘክሩት የማይሰማ

ራስ ከተመለጠ፣ ነገር ካመለጠ
- ካፍ ከወጣ አፋፍ

ራስ ከዋለ፣ ሰምድ አይገድም
- አደባባይ ከዋለ የክብር ልብሱ እንደምንም መገኘቱ አይቀርም

ራስ ከዋለበት እግር ይሰበሰባል
- ሁነኛ ሰው ከዋለበት ማንም የኔ ቢጤ አይውልም



ራስ የት ትሔዳለህ? ካንተ ጋር፣ ስንቅህሳ አንተሳ
- የተያያዘና አንዱ ካገኘ ያው ላንዱ ሊሆን እንደሚችል

ራስ ያለ አንገት፣ ጽድቅ ያለ እውነት
- ያለእነዚህ የተባለው ሊሆን አይችልም

ራስ ይሸብታል እንጂ፣ ልብ አይሸብትም
- ፍቅር አያረጅም ሰውነት ቢጃጅም

ራቁቱን ለተወለደ ልጅ፣ ሰምድ እነሰው ወይ
- ምንም ለሌለው ትንሽ ነገር አነሰው ወይ

ራቁቱን ለተወለደ፣ ጥብቆ መቼ አነሰው
- ምንም ለሌለው ትንሽ ነገር አነሰው ወይ

ራብን ባለቤቱ ያውቀዋል፣ ማን ይጠይቀዋል
- ችግሩን የሚያውቀው ባለቤቱ ነው

ራብን የማያውቅ፣ ለተራበ አያዝንም
- ያልተቸገረ ሰው ችግረኛን አይረዳም

ራብን ያማርራል ሰው፣ ቁንጣንን ያልቀመሰው
- ከርኃብ ይልቅ ከፉ የሚያሠራ ጥጋብ ነው

ራብ ይከላከላል ባቄላ፣ ከጥፍ ያደርሳል ነጠላ
- ለጊዜ ማሳለፊያ ይሆናል

ራብ ይከላከላል ባቄላ፣ ጥቃት ያወጣል ዲቃላ
- የተጠላው ወገን ውጤት ያለው ሥራ ይፈጽማል

ራት በዳረጎት አይለወጥም
- በጉርሻ ሰው አያድርም

ራት ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ፣ ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይውደቁ
- መናቅ ጥሩ ስላልሆነ ያዋርዳል

ራት ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ፣ ዳኛ ቢንቁ፣ የተያዘ እህል ይውቁ
- መናቅ ያዋርዳል

ራት የለህም ቢሉት ከወጡ አውጡልኝ አለ
- አቅምን አለማወቅ

ራት የላት፣ ምላ አማራት
- አጉል መቀናጣት

ራት የሌለው ቄስ፣ ከልቡ አይቀድስ
- ለመኖር ምግብ ያስፈልጋል ስለዚህ ካልበላ መሥራት አይችልም

ራት የሰማይ መብራት
- ከወዲሁ ለድሃ የመጸወቱት ለላይኛው ቤት ያገለግላል

ሬሳ በምን ከበደ? ሐሳቡን በሰው ላይ ጥሎ
- አስከሬን ራሱን ስለማይቆጣጠር ለተሸካሚው ይከብዳል

ሬሳ በዝምታው ይፈራል
- ዝም ያለ የሚያስበው ስለማይታወቅ ይፈራል

ሬሳ ባልጋ ጥሬ በመንጋጋ
- ሁሉንም በመልክ በመልኩ ማከናወን

ርስት በሺ ዓመቱ ለባለቤቱ
- እውነትና ንጋት እያደር ይታያል

ርስት ያዳግማል፣ አቀበት ያዳክማል
- አቀበትና ክፉ ሐሳብ አካልንና መንፈስን ያደክማል

ርጎ መስሎሽ፣ እርሾ ጥልቅ
- ያልጠረጠረ ተመነጠረ

ርጥብ ሬሳ፣ ደረቁን አስነሳ
- ርጥብ ከደረቅ ይነጻል

ርጥብ ከደረቅ ይነጻል
- ደረቁ ርጥቡን ሊያነጻው በመቻሉ ነው

ሮሮ የሚያምረው፣ ኮሶ የማያሽረው የለም
- ማንኛውም ሰው ጥቃትን አይወድም

ሮቃ የዘሆን አለቃ፣ ስምሳር አይበቃ
- አለቃ ለራሱም አይበቃ

## ሰ

ሰላሳ መላላ
- የማይረባ፣ መልክ የሌለው ሥራ

ሰላም ሰላም ለቅኔ ስራቂ ናሁዳ፣ ዳር ዳሩን ኮርመም መሃሉን ሳይጎዳ
- ወደ ውስጥ ጠለቅ ከማለት በፊት ዙሪያገባውን ማየት

ሰላም ሰው፣ በርበሬ አይሰርቅም
- ግጭትን በሩቅ ይሸሹታል

ሰሚ ልብ ነው፣ ጆሮማ ቅጠል ነው
- ልብ ካለየ ዐይን አያይም

ሰማሁት ያሻማል፣ ዐየሁት ያመሳክራል
- ማየት እርግጠኛ ያደርጋል ከመስማት

ሰማህ? አልሰማሁም አየህ? አላየሁም
- ከሰው ጋር ተስማምቶ ለመኖር

ሰማንያ ለማገኛ፣ ስለት ለማረኛ
- ሰምምነት አስተማማኝ ነው

ሰማንያ አንድ መጽሐፍ፣ ከተማረው መከራ፣ የመከረው ይሻላል
- መጣፍ ከመከረው መከራ የመከረው

ሰማንያ የጎሰመው
- በዕድሜ የገፋ ሰው

ሰማይ ላይ ጤፍ ይወቃል ቢሉት፣ እብቁ ዐይኔ ገባ አለ
- የተጋነነ ውሸት ተናገረ

ሰማይ ምን ይርቅ፣ መንገደኛ ምን ይጨነቅ
- ለማያስጨንቅ ጉዳይ አላግባብ መጨነቅ

ሰማይ ሲጠና፣ ምድር ሲቀና
- ከጥንት ጀምሮ



ሰማይ ቢያኩ፣ ጤፍ ቢለኩ፣ አይደርስም ከልኩ
- ምንም ቢጥሩ አይሆንም

ሰማይ ብልጭ፣ ወፍ ጭጭ
- ጥንት፣ ድሮ፣ በጠዋት

ሰማይ ተቀደደ ቢሉት፣ ሽማግሌ ይሰፋዋል አለ
- ማንኛውም ጸብ በሽማግሌ መታረቅ ይቻላል

ሰማይን ያህል ዳቦ ባገኝሁ ቢለው፣ ኮከብን ያህል በላተኛ ያዝብሃል አለው
- ማጣትና ማግኘት ጆሮ ለጆሮ ነው

ሰማይ አያርሱ፣ በአፍ አይለግሱ
- የማይሞከር ነገር

ሰማይ አይላጥ፣ የሥስት ፍርድ አይለወጥ
- የማይሞከር ነገር ነው

ሰማይ አይታረስ፣ እርኩስ አይቀደስ
- ፈጽሞ ሊሆን የማይችል

ሰማይ አገሬ፣ ምድር ወንበሬ
- ሁሉም የእኔ ነው

ሰማይ ከነዳመናው፣ ምድር ከነጉተናው
- አንድም ሳይቀር

ሰማይ ከነጉሙ፣ ምድር ከነልብሱ
- አንድም ሳይቀር

ሰማይ ከነግሱ ምድር ከነልብሱ
- አንድም ሳይቀር

ሰማይ ያለደመና ብረት፣ ቤት ያለ ሴት መሠረት
- ቤት ያለ ክዳን ከምንም አያድንም

ሰማይ ያለ ደመና ብረት፣ ነገር ያለዳኛ ተረት
- ቤት ያለ ክዳን ከምንም አያድን

ሰማይ ይወድቃል ብሎ ባላ ተከለ
- በማያገባው ጉዳይ ይጨነቃል ይጠበባል

ሰሞቱ መቻል፣ ለእግዚአብሔር ይመቻል
- መተው ነገሬን ከተተው

ሰሞቶ ዝም፣ ዓይቶ ዝም፣ በሆድ ያለ ነገር አይነቅዝም
- የሰሙትን ሁሉ መናገር አይገባም

ሰርቶ ከማሰብ፣ እጅን መሰብሰብ
- ከመጸጸት መጀመሪያ መጠንቀቅ

ሰርቶ የጉም ሌባ፣ ጉም ሲለቅ የት ሊገባ
- አልያዝም ብሎ በተጋለጠ ጊዜ ይዋረዳል

ሰሳ የናቷን አትረሳ
- እባብ ጉድጓዱን፣ ውሻ ጌታውን

ሰባት ወልዶ አቃቢነት
- የልብን ሠርቶ ጨዋ ለመምሰል መጣር

ሰባት ወልዶ ዕቃ ቤትነት
• የልብን ሠርቶ ጨዋ ለመምሰል መጣር
ሰባት ዓመት እንዳይማሩ፣ ሰባ ዓመት ይደናቆሩ
• በጊዜው ማድረግ በሚገባ ያለማድረግ
ሰባት ዓመት የታወረ ዕውር፣ ነገ ዐይንህ ይበራል፣ ቢሉት ዛሬ እንደምን አድሬ አለ
• የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
ሰባኪ መፈለጉ፣ ለሰሚ መርፌ መፈለጉ ለጠቃሚ
• ሥራና ሠራተኛን ማገናኘት
ሰነፍ ሰው ናቂ፣ ሞኝ ሰው ሳቂ
• ሰነፍ ሰው መሥራት አይሆንለትም
ሰነፍ ሰው ያሳንፋል
• እሱ አይሠራ ሌላውንም ያደክማል
ሰነፍ ሲኮራ፣ ማጭድ ይታጠቃል
• የማይሆን ነገር ለማድረግ መሞከር
ሰነፍ ሳያከብር ይሞታል
• ካልሠሩ ሀብትና ንብረት አይገኝም
ሰነፍ ቤት ዕድል የላትም ለንብረት
• ሰነፍ ሥለሆነች ንብረት አይኖራትም
ሰነፍ ሴት ያገባ፣ በሬው በሰኔ ገደል ገባ
• ለቤቷ የማትቆረቆር ሴት ያገባ ትዳሩ ጥሩ አይሆንም
ሰነፍ ሥራ ሲያይ ወደጎን ይሔዳል
• ሰነፍ ሰው ሥራ ሲታዘዝ በምክንያት ያሳብባል
ሰነፍ በዓል ያበዛል
• ሥራ ላለመሥራት ምክንያት ያበዛል
ሰነፍ ቢመክሩት ውኃ ቢወቅጡት
• ቢመክሩት ለውጥ የለውም
ሰነፍና እጋራ፣ እራሱን ሲነቀንቅ ይኖራል
• ከሚሠሩት ጋር አይስማማም
ሰነፍና ዋንጫ ከወደ እፉ
• ተግባር ሳይሆን ወሬ ያበዛል
ሰነፍን ከመውለድ፣ ይሻላል ማስወረድ
• የማይጠቅምን አይመኙትም
ሰነፍ እረኛ፣ ከሩቅ ይመልሳል
• ቢከማች ዕዳው ላንቺ
ሰነፍ ይጸድቃል ቢለው፣ ገለባ ይበቅላል ወይ አለው
• ያልደከሙበት ነገር ውጤት አያመጣም
ሰነፍ ገበሬ፣ በመስከረም ያርማል
• ወቅቱን ጠብቆ ሥራውን አይሠራም



ሰነፍ ጸሐፊ፣ ከሙሴ ይገድፋል
• ማድረግ የሚገባውን በጊዜው አለማድረግ
ሰናፍጭ ትቀምሽ፣ ተልባ መስሎሽ
• ያገኘሽውን መቅመስ ጉዳት ላይ ይጥላል
ሰኔ መቃጠሪያ፣ ሕዳር መገናኛ
• ለሥራ አመቺ ጊዜ አስፈላጊ ነው
ሰኔ ሲመጣ፣ ድግር ቆረጣ
• ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
ሰኔ፣ ነግ በኔ
• በሌላው የደረሰው በእኔም መድረሱ አይቀርም
ሰኔና ሰኞ ሆነበት
• መጥፎ አጋጣሚ ሆነበት
ሰንበሌጥ ለቤት፣ ቀሚስ ለባለቤት
• ማንኛው ነገር እንደአግባብነቱ ያገለግላል
ሰንበት ሲጠም፣ ከዓርብ ረቡዕ ይብሳል
• ባልታሰበ ቀን ያልታሰበ ችግር ያጋጥምሃል
ሰኞ በማክሰኞ ይሥቃል
• ደካማው በጎበዙ ይሥቃል
ሰአሊ በስዕሉ፣ ፈጣሪ በፍጡሩ
• ሁሉም የራሱ የሆነ ነገር ያስደስተዋል
ሰክሮ ከጌታ መገናኘት፣ ከሹመት መለየት
• የወደፊቱን ሁኔታ ማበላሸት
ሰው ሆኖ አይሰት፣ ዕንጨት ሆኖ አይጨስ የለም
• ሰው ሆኖ የማይሳሳት የለም
ሰው ሆኖ የማያስብ፣ ዕንጨት ሆኖ የማይጨስ
• ሰው ሆኖ የማያስብ የለም
ሰው ሆኖ የማይበድል፣ ዕንጨት ሆኖ የማይጨስ
• ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት
ሰው ለሰው መድኃኒቱ ነው
• ለሰው ሰው ነው ልብሱ
ሰው ለወደደው፣ ዘንጋዳ ጤፉ ነው
• ከወደዱ ወዲያ ገደሉ ሜዳ
ሰው ለወዳጁ፣ መኮንን ለጠጁ
• ለሚወዱት ሰው መጨነቅ ያለ ነው
ሰው ለወዳጁ ሜጩት ያርዳል
• ሰው እንደአቅሙ እህል እንደቃርሙ
ሰው ላማን፣ እግዜር ለለማን
• እግዚአብሔር ቸር ነው
ሰው መሳይ፣ በሸንጎ
• ጥሩ ሰው ይመስላል ግን መጥፎ ሰው ነው

ሰው መስሎኝ፣ ድንጋይን ቆነጠጥኩ፣ አለ የሰለቸው
- ያለቦታው የሚደረግ ነገር ትርጉም ያጣ ይሆናል

ሰው መታፈሩ በከንፈሩ፣ መሬት መከበሩ በድንበሩ
- መታፈር በከንፈር

ሰው መኖሩ ለመከበር፣ የመሬት ወሰኑ ድንበር
- መታፈር በከንፈር

ሰው መጣ ነገር መጣ፣ ነገር ከመጣ፣ አለ ጣጣ
- ከሰው ጋር ሲኖሩ ተጠንቅቆና ተቻችሎ ነው

ሰው ማለት፣ ሰው የሚሆን ሰው የጠፋ ዕለት
- በችግር ጊዜ የሚገኝ ነው ሰው ማለት

ሰው ማመን ገደለኝ፣ የእኔ እየመሰለኝ
- የማምነው ሰው ሁሉ እየከዳኝ ተቸግሬያለሁ

ሰው ማማት፣ የሰው ሥጋ መብላት
- ኃሜት ጥሩ አይደለም

ሰው ማንን ያህላል፣ የተናገውን
- ማንነቱን በንግግሩ መገምገም ይቻላል

ሰው ማጀራቱ፣ አይታየውም
- የራሱ ስሕተት አይታየውም

ሰው ምን፣ በሠራ፣ መቅረቱ ይወራ
- ሥሕተት ሳይኖርበት ለምን እንደ ስሕተት ይቆጠርበታል

ሰው ምን ቢዋሽ፣ እውነትን ፈጽሞ አያጠፋትም
- እውነትና ንጋት እያደር ይጋለጣል

ሰው ምን ቢዋሽ እግዜርን አያታልልም
- ከእግዜር የተሠወረ ነገር አይኖርም

ሰው ምን ይመስላል ቢሰው ኑሮውን
- ሀብታም በወርቁ፣ ድሃ በጨርቁ

ሰው ሠራሽ፣ በዓምላክ ሥራ ፈራሽ
- ትንሹ በትልቁ ሥራ መሆን ይኖርበታል

ሰው ሥራ ሲፈታ፣ ወዳጁን ያማል
- ሰው ሥራ ሲፈታ ኃሜተኛ ይሆናል

ሰው ሰውን የሚበልጠው ለተወሰነ ጊዜ ነው
- ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁሉም በሞት ይስተካከላል

ሰው ሲሔድ ሳገር፣ ንብ ሲሔድ ሳጥር
- ሰው የሚኖረው ለሌላውም ጭምር ነው

ሰው ሲታጣ፣ ይመለመላል ኅባጣ
- ተፈላጊ ነገር ሲጠፋ የማይፈለገው ይጠቅማል

ሰው ሲወድ ልብ ሥር ይሰድ
- ከውዴታ መተዛዘንና መተሳሰብ ይከተላል

ሰው ሲያረጅ ከርስቱ፣ ባል ሲያረጅ ከሚስቱ
- አቅም ሲያጥር ረዳት መፈለግ ተገቢ ነው



ሰው ሳይቸግረው፣ ከሰው ቤት ይሔዳል
- የራሱ እያለው የሰው ይመኛል

ሰው ቁመቱን ዓይቶ፣ ደጃፉን ይሠራል
- ሰው የሚያመቸውን ለራሱ ያዘጋጃል

ሰው በሰው ላይ፣ ቅቤ በጨው ላይ
- ተረዳድተው የሠሩት ውጤት አሰው

ሰው በሰው የተጠጋ፣ ሰው ወጋ
- በዘመድ የቀረቡት ዘመድ ወዳጅነቱን አበላሸ

ሰው በእህል፣ እህል በገዘርገዘር ያምራል
- ተሰማሚ ነው

ሰው በከንቱ አያጎነብስም፣ ዕቃ ሊያነሳ፣ ወይ ሊፈሳ
- ደኅቺ ተፍ ተፍ እኔን ሰመመንተፍ

ሰው በወሬ፣ ዱቄት በሙሬ
- ሰው በወሬ ይሸበራል

ሰው በወደደው ይገድፋል
- የወደደውን ይመርጣል

ሰው በዋሰበት፣ ውኃ በወረደበት
- ሰው አካባቢውን ይመስላል

ሰው በዘመድ፣ አህያ በገመድ
- ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

ሰው በዘና፣ ገዘናብ በደመና ይታወቃል
- ሰው በገዘና ይታወቃል

ሰው በየወንዙ ብዙ ነው መዘዙ
- እያንዳንዱ ሰው የተለያየ ችግር ይኖርበታል

ሰው በዱር፣ ዐይኑ ቫንጉርጉር
- የሰው ባህርይ በጣም የተለያየ ነው

ሰው ቢሰባ ለመሬት፣ አህያ ቢሰባ ላራዊት
- ሰው ቢገዘፍ ዋጋ የለውም ዕውቀት እንጂ

ሰው ባላወቀው ይፈርዳል፣ እግዜር ባወቀው ይቀጣል
- የሰው ዕውቀት ውሱን ነው

ሰው ባገሩ ሰው ነው
- በሀገርህ ትከበራለህ አትናቅም

ሰው ባገሩ፣ ቤት በበሩ
- በሀገርህ ትከበራለህ አትናቅም

ሰው ባገሩ፣ እንበሳ በዱሩ፣ አሣ በባሕሩ
- ሁሉም በየቦታው በየአካባቢው ይታወቃል

ሰው ባገሩ፣ ወይራ ነው፣ ያለ አገሩ ግን ጉሎ ነው
- ክብር በሀገር ነው

ሰው ባፉ፣ አሞራ በክንፉ
- ሰው በመልካም ንግግሩ ከሰው ጋር ተስማምቶ ይኖራል

ሰውነቱን ቢንቁ፣ ልብሱን ይጠይቁ
- ሰው በልብሱ ይከበራል

ሰውነቱ ከንጽሕና፣ ልቡ ከትሕትና፣ ያልተለየ ደህና
- ጨዋ ሰው ነው

ሰውና ዓመሉ ሳይተዋወቁ ይኖራሉ
- የራሱን ባህርይ አያውቀውም

ሰውና ዕንጨት ተሰባሪ ነው
- ሰው ሟች ነው

ሰውን ማመን ቀብሮ ነው
- ሰውን ማመን አይገባም

ሰውን ሰው፣ አማው፣ የራሱን ባይሰማው
- የራሱን ሳያውቅ የሌላውን ስሕተት ያወራል

ሰውን አትመኑ፣ አብዷል ዘመኑ
- ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

ሰውን አትናቀው፣ እህልን አትራቀው
- ሰውን መናቅ አያስፈልግም

ሰውን እጎዳ ባይ፣ እመድ ተንከባላይ
- ሰውን እጎዳለሁ ባይ እራሱ ጉዳት ላይ ይጥላል

ሰውን ከመስመን፣ ፈጣሪን ማመን
- ሰው ላይ ዕምነት መጣል አያስፈልግም

ሰውን ከነዓመሉ፣ ድሪቶን ከነቅማሉ ወዲያ በሉ
- መጥፎ ዓመል ያለውን ሰው ማቅረብ አያስፈልግም

ሰውን ካልናቁ፣ አጥሩን አይነቀንቁ
- የሰው ንብረት ላይ አደጋ ማድረስ ባለንብረቱን ከመናቅ የተነሳ ነው

ሰውን ውደደው፣ እንጂ አትመነው
- ያደርግልኛል ብለህ በተስፋ አትጠብቀው

ሰውን የሚያስረጅ ሐሳብ፣ ልብስን የሚያስረጅ ሰብሳብ
- ሐሳብ ችግር ላይ ይጥላል

ሰውን ያመነ ጉም የዘገነ፣ አንድ ሆነ
- በሰው አትተማመን

ሰው አለቀ፣ ምድር ተደበለቀ
- ሰዎች ተጋደሉ

ሰው አሰብልሃቱ ገደል መግባቱ፣ አሰጉልበቱ ውኃ መግባቱ
- አቅም ሳይኖርህ አንድ ነገር ለማድረግ መሞከር

ሰው አለወንዙ፣ ብዙ ነው መዘዙ
- በባዕድ አገር መቀመጥ ችግር ያስከትላል

ሰው አላባው፣ የሰው በቅሎ መሳቡ
- በሰው ጉዳይ የሚገባ በማያገባው ነገር ይገባል

ሰው አላገሩ፣ ምነው መኖሩ
- በአገር መኖር እየተቻለ በባዕድ አገር ለምን ትቸገራለህ



ሰው ያለአገር፣ መሬት ያለ ዘር
- ሁሉም በቦታው ያምራል

ሰው ዐየ እግዜር ዐየ
- ከሰው የተሠወረ ነገር የለም

ሰው አይወድም በደል፣ ከብት አይወድም ገደል
- ጥቃትን ማንም አሜን ብሎ አይቀበልም

ሰው አሚበላ ቡዳ፣ አጉድጓድ ሆኖ ይጠብቃል
- ምስጥ ከምድር ውስጥ

ሰው እንደቤቱ እንጂ፣ እንደጎረቤቱ አይኖርም
- ሰው እንዳቅሙ መኖር አለበት

ሰው እንደአቅሙ፣ እህል እንደቃርሙ
- ሰው እንዳቅሙ መኖር አለበት

ሰው እዳነጋገሩ፣ በቅሎ እንዳስጋገሩ
- ሰው ከአነጋገሩ ሊገመት ይችላል

ሰው እንግዳ ቢሆን፣ እግዜር ባላገር ነው
- ሰው ወደየትም የሚሠማራው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው

ሰው ከሐሜት፣ ፋሲካ ከሰንበት ወጥቶ አያውቅም
- ምንም ጥሩ ሥራ ቢሠራ ከመታማት አይድንም

ሰው ከመከረው፣ መከራ የመከረው
- ሕይወት ጥሩ ትምህርት ቤት ናት

ሰው ከሚጠላህ ድንጋይ ይጫንህ
- ሰው የሚጠላውን ነገር አትፈጽም

ሰው ከሞተ የለ ንስሐ፣ ከፈሰሰ አይታፈስ ውኃ
- ከሆነ በኋላ መቆጨት አይገባም

ሰው ከራበው፣ የሰይፉን ሰገባ ይበላል
- ረኃብ ክፉ ነው

ሰው ከቆየ መዛመድ፣ አህያን በገመድ
- አብሮ ከመኖር መቀራረብ አይቀርም

ሰው ከቆየ፣ ከሚስቱ ይወልዳል
- ትዕግስት መልካም ነው

ሰው ከተኮተኮተ፣ ጅብ ካኮተኮተ
- የማይሆን አካሔድ

ሰው ካሰቤቱ፣ ልፋት በከንቱ
- ያሰባለቤቱ አይነደም እሳቱ

ሰው ካሰእህል፣ ምን ያህል
- ሰው ያለምግብ አይኖርም

ሰው ካላማ፣ ጀነበር አይጠልቅም
- ሰውን ማማት ይወዳል

ሰው ካልሞተና ካልሔደ አይመሰገንም
- መልካምነት እጠገብ እያለ አይታወቅም

ሰው ወጣኒ፣ እግዜር ፈጻሚ
- ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ቸርነት ይፈጸማል

ሰው የሠራው፣ መሬት አወራው
- አንድ የተፈጸመ ተግባር ተደብቆ አይቀርም

ሰው የተጠጋ፣ ሰው ወጋ
- ምንንም ሳታውቅ ካቀረብከው ሊያጋልጥህ ይችላል

ሰው ያለበት አገር፣ ሰው የሌለበት ዱር
- ሰው የሚኖረው ያው ከመሰሉ ጋር ነው

ሰው ያሰቤቱ፣ ያንሳል ጉልበቱ
- ሁሉም በቤቱ ባለሥልጣን ነው

ሰው ያሰው፣ አርፍዶ ይሞታል
- ሐኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል

ሰው ያሳገሩ፣ መሬት ያለዘሩ
- አይሳካም፣ አያምርም

ሰው ያሳገሩ፣ ይበዛል ነውሩ
- ሰው አሰወንዙ ብዙ ነው መዘዙ

ሰውን ያመነ፣ ውኃ የዘገነ
- ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

ሰው ያሰባል፣ እግዛብሔር ይፈጽማል
- ሰው ወጣኒ እግዛብሔር ፈጻሚ

ሰው ያሰገድላል ዓባይ፣ ውኃ ያሰጮሃል ድንጋይ
- ቀጣፊ ሰው በውሸት ሰውን ያሰገድላል

ሰውዮው ውኃ ሲወስደው፣ እኔም ወደቆሳ እወርዳሰሁ ብዬ ነበር አለ
- ተሆነ ወዲያ መመሰሰ አይቻልም

ሰው ይሰፋል፣ ዕድል ይሠራል
- ብትሠራም ዕድል ከሌለህ የሰህም አያልፍልህም

ሰው ይውደድህ፣ ድንጋይ ይጫንህ
- የሰው መውደድ ያለው ቢቸገር እንኳ ሰው ይደርሰለታል

ሰው ይጥራል፣ ዕድል ይሠራል
- ብትጥርም ዕድል ከሌለህ የሰህም አያልፍልህም

ሰው ይጨርሳል እንጂ፣ ሐሳብ አያልቅም
- ሐሳብና መንገድ ማለቂያ የሰውም

ሰው ይጨነቃል የሚሆነውን እግዚአብሔር ያውቃል
- መጨነቅ መፍትሔ አይሆንም

ሰው ጠባቂና ጾም ገዳፊ፣ ሰጥቂት ይሳሳታል
- መሳሳት ያለ ነው

ሰው ጠባቂና፣ ጾም ገዳፊ፣ አንድ ነው
- መሳሳት ያለ ነው

ሰው ጤፉ
- ሰው ይንቃል



ሰው ጊዜውን፣ ዕቃ ቦታውን፣ ምንጊዜም አያጣውም
- ሁሉም የራሱ የሆነን ነገር አያጣውም

ሰዎች በማያገባቸው ነገር ለጋቦች ናቸው
- በሰው ቁሰል ዕንጨት ሰደድበት

ሰይጣን ሰወዳጁ፣ ድርብ ነው
- በል በል፣ አድርግ አድርግ ይለዋል

ሰይጣን ሳመሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል አሉ
- አጭበርባሪና መጥፎ ሰው የሚያታልለው መልካም ሰው መስሎ
  በመቅረብ ነው

ሰይጣን ቢያረምም፣ ባህታዊ ይመስሳል
- ሐምሌ ቢያባራ በጋ ይመስላል

ሰደ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ሰውጥ
- ልጓም ለቆ ቼቼ

ሰደ ከማሳደድ፣ የያዙትን ማጥበቅ
- የያገኘከውን አጥብቀህ ያዝ

ሰደ ከማሳደድ፣ የያዙትን አሰመሰደድ
- የያገኘከውን አጥብቀህ ያዝ

ሰጥቶ በእጅ፣ መለመን ከሰው ደጅ
- የነገን አለማወቅ፣ አለመገመት

ሱሪ በአንገት፣ አውልቁ
- የማይሆነውን ነገር ፈጽም ብሎ ማሰጨነቅ

ሱሪ አውሶ፣ አትቀመጥበት
- ሥጋ ሰጥቶ ቢለዋ መከልከል

ሲሔዱ አገር፣ ሲተኙ ነገር አወይ የዓሰም ነገር
- የሰው ጠባይ ተነግሮ አያልቅም

ሲሆን በውድ፣ ሳይሆን በግድ
- መፈጸሙ የማይቀር ሲሆን

ሲሱ ሰምታ ዶሮ፣ ሞተች! ኪጪሰ ገብታ
- እንዳየን ጤፍ አጋየን

ሲል ነበር፣ ደግሞ ከወግ ይጨመር
- ወጉሳ ማዕረጉሳ

ሲመሽ ወደ ቤቴ፣ ሳረጅ ወደርስቴ
- ሰው ሲያረጅ ከርስቱ ባል ቢያረጅ ከሚስቱ

ሲሙትሩሰት፣ ይነጭ
- ሀመለቢስ፣ መልካሙን የማያውቅ

ሲመች ያማት ተገዛካር ይወጣል፣ ሳይመች ያባት ይቀራል
- ሁሉም ነገር እንደአመቺነቱ ይሠራል ሳይመች ደግሞ ይቀራል

ሲመክሩት ሰማይሰማ፣ ሲያበሉት ለሚከሳ፣ ለዚያም ምክር፣ ለዚያም
እህል ነሳ
- ምከረው ምከረው እንቢ ካለው መከራ ይምከረው

ሲመክሩት አይመከር፣ በደም ይነከር
- ሰው ከመከረው መከራ የመከረው

ሲመክሩት ያጠፋል ልጅ፣ ሲያጥቡት ያድፋል እጅ
- ቢመክሩ ቢመክሩት የማይሻሻል

ሲመክሩት ይረሳል፣ ሲከድኑት ይፈሳል
- ቢመክሩት መሻሻል ያልቻለ

ሲምር ያስተምር
- ከድርጊት ከስሕተት ትምህርት ማግኘት

ሲሞላ ይፈሳል፣ ሲከር ይበጠሳል
- ከልክ በላይ የሆነ ነገር ችግር ያስከትላል

ሲሞቱ ቢያይ ያንቀላፋል
- አስመሳይ

ሲሞቱ ገመድ፣ ሲገዙ ዘመድ አይታጣም
- የማይቀርና የተለመደ ተግባር

ሲሠሩ ሎሌን መስሎ፣ ሲበሉ ጌታን እህሉ
- ሥራን ማክበርና መሥራት

ሲረዝም ይጠር፣ ሲሰበር ይሰንጠር
- መላቅጡ የጠፋ ነገር

ሲርበኝ ታነቅሁ፣ ሲጨንቀኝ ታረቅሁ
- መፈናፈኛ መውጫ ቀዳዳ ሲጠፋ

ሲሮጡ የታጠቁት፣ ሲሮጡ ይፈታል
- የቸኮለ እፍሶ ለቀመ

ሲሮጥ የመጣ እህያን፣ አጥብቀህ ጫነው
- ከመጣሽ ማረያም ታምጣሽ

ሲሰማ የሞተውን፣ ሲያይ ቅበረው
- ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም

ሲሰርቀኝ ያየሁት፣ ሲሰጠኝ ጠላሁት
- ምኑ ይታመንና ነው

ሲሳይ በርምጃ ይገባል፣ በሩጫ ይወጣል
- ሀብት ጥረት ይጠይቃል በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ በፍጥነት ይባክናል

ሲሳይ ያለቀበት አንበጣ፣ ከድንጋይ ላይ ያርፋል
- ሀብታም ሲወድቅ ከሰገነት፣ ድሃ ሲወድቅ ከመሬት

ሲስሟት ቀርቶ፣ ሲስቧት
- የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

ሲሻሩ ከላሽ፣ ሲሞቱ ወራሽ አይታጣም
- የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል

ሲሻኝ፣ ጢስ ወጋኝ
- ክፉ አጋጣሚ
- እያወቅሁ የገባሁበት ነገር እያሰቆጨኝም



ሲቀላውጡ ዓይን አፍጦ፣ ሲቆፍሩ እግር አንፈራጦ
- አንድ ነገር ሥትሠራ በትኩረት መሆን አለበት

ሲቀመጡ ዐውቃለሁ፣ ሲነሱ፣ አፍራለሁ
- የሁኔታዎች መለዋወጥ የሚፈጥሩት ጭንቀት

ሲበሉ መደንደን፣ ሲያጡ መቅጠን
- ጥሩ ካልበሉ ጉልበት ከየት ይገኛል

ሲበሉ በሰዓት፣ ሲናገሩ በሥርዓት
- ሁሉን ነገር በሰዓትና በሥረዓት መሆን አለበት

ሲበሉ አድርሰኝ፣ ሲጣሉ መልሰኝ
- መልካም ምኞት መመኘት

ሲበሉ የላኩት
- ችኩል

ሲበሉ የላኩት፣ ሲናገር ያሳስታል
- ችኩል ሰው መልእክት ያሳስታል

ሲበዛ ማር ይመራል
- ከመጠን ያለፈ ነገር ይመራል

ሲበዛ ይገነፍላል
- ሲሞላ ይፈሳል፣ ሲከር ይበጠሳል

ሲበደሉ ማሩኝታ፣ ቢበደሉ ይቅርታ
- የበደለውም የተበደለውም ይቅር ማለት ይገባዋል

ሲተኙ ነገር ያገኙ፣ ሲነሡ ነገር ይረሱ
- ብስጭት ክጊዜ በኋላ ይዘነጋል

ሲታሰር ያልተሰማው፣ ሲፈታ ጎረበጠው
- በወቅቱ ያልተሰማው ጉዳይ በኋላ ቆይቶ ቆይቶ ስሜቱን ነካው

ሲታጠቡ ከክንድ ሲታረቁ ከሆድ
- ሲታረቁ ከልብ መሆን አለበት

ሲቸገሩ ያልሰጠ፣ ቸር አይባልም
- በችግርህ ጊዜ ያልደረሰ ምስጋና የለውም

ሲነግሩት የሚዘነጋ፣ ሲያምኑት የሚያስጋ፣ የለውም ዋጋ
- የማትተማመንበት ሰው አታስጠጋው

ሲነግሩት የማይሰማ፣ ሲቀልቡት አይድንም
- ምክር የማይሰማ አይሻሻልም

ሲነግሩት ያልሰማ፣ ሲመቱት ያልደማ
- የማይሰማ ሰው ዋጋ የለውም

ሲኖሩ ለጠቅ፣ ሲሔዱ መንጠቅ
- ከሰው ጋር ሲኖር መስሎ ካለያም ቆርጦ መሄድ ነው

ሲከር ይበጠሳል
- ሲበዛ ማር ይመራል

ሲከሱ የከሰሱ፣ ሲሔዱ ይመለሱ
- ያጣን ማንም ያጠቃዋል

ሲወሰድ ያጠለቀው፣ ሲሞት አወሰቀው
- አብሮት የኖረውን እጦት

ሲወልዱ እየሁ ብላ በጠጧን ጣሰች
- ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

ሲወርዱ ይዋረዱ
- ከሥልጣን ሲነሱ ውርደት ነው ትርፉ

ሲወጣ ባቱን፣ ሲገባ ደረቱን
- የወደዱትን ሲወጣም ሲገባም በፍቅር ይመለከቱታል

ሲዋጥ በመረቅ
- የተሰሳለሰ ችግር የሌለበት

ሲሆሩ በመኖር ጽድቅ፣ ሲመኙ በመኖር ወርቅ አይገኝ
- ላሊበላ ሔደሽ ከሕንፃው ብትሰፍሪ፣ ጽድቅ አይገኝ አሰባህሪ

ሲሆር ውሎ እራቱ ጥሬ
- ያሰመታደል ሆኖ

ሲያልቅ አያምር
- መጨረሻው የማያምር ሆነ

ሲያልፍ ዋዛ
- ሲያስጨንቅ የቆየ ጉዳይ ካለፈ በኋላ እንደቀላል ነገር ይወራል

ሲያምርህ ይቅር
- አታገኘውም

ሲያምኑት መክዳት ሲወዱት መጥላት
- አስቸጋሪ ባህርይ

ሲያምኑት የከዳ፣ አሰበት ዕዳ
- የሠራው ክፉ ሥራ ይጠብቀዋል

ሲያረጁ፣ እንባር ይዋጁ
- ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚያደርጉት ድርጊት እንዲያው ከንቱ ልፋት

ሲያብል የተኛ፣ ሲጠሩት አይሰማም
- ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም

ሲያከሩት ይበጠሳል
- ሁሉን በልክ በመጠኑ መያዝ ይበጃል

ሲያወላውል፣ ቀረ ባጉል
- የሚያመነታ ሰው ከአንዱም ሳይሆን ይቀራል

ሲያውቅ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም
- ሲያብል የተኛ ሲጠሩት አይሰማም

ሲያውቅ ያሟገት ዳኛ
- ጉዳዩ እየታወቀ ሰውን በከንቱ ማድከም አይገባም

ሲያውቅ ያጠፋ ሰይጣን
- ሰው እያወቀ ራሱን ለጥፋት አይዳርግም

ሲያዝሉት ይነክስ ሲያወርዱት ያለቅስ
- በጣም አስቸጋሪ ባህርይ ያለው ሰው



ሲያዩት ያላማረ፣ ሲበሉት ያቅራል
- መልካም ነገር በዐይን ይገባል

ሲያዩት ያምር፣ ሲይዙት ያደናግር
- የማያውቁት ሙያና ተግባር ሲሆን

ሲያዩት ያፈረ ኋላም አላማረ
- ከመጀመሪያው ቅሬታ የፈጠረ መጨረሻውም አያምርም

ሲያጋድል ያልታየ ሲወድቅ ታየ
- በዝግሜው ያልተደረሰበት መጨረሻው ውድቀቱ ይከሠታል

ሲያጌጡ ይመላለጡ
- በመጠኑ መጠቀም ያስፈልጋል

ሲያጎርሱት የማይጎርስ፣ ከቀማኛ አንድ ነው
- ሲያዝኑለት የማያዝን ሰው ክፉ ነው

ሲያጡ እጅ ላፍ ይጠናል
- ማጣት ያስጨንቃል

ሲያጥቡት ያድፋል፣ እጅ፣ ሲመክሩት ያጠፋል ልጅ
- አይሻሻልም ይብሰበታል

ሲገረገድ ያልበጀው፣ ሲዋቀር አሳት ፈጀው
- ምንም ምንም የማያምር

ሲገዙ ይገዙ
- ሹመት፣ ሺ ሞት

ሲጎርሱ በልክ፣ ሲታጠቁ ጠበቅ
- በአቅምህና በመጠንህ ኑር

ሲጠላ ይጠና
- ይቀላል ያሉት ተቸነከረ

ሲጠሩህ ዝም በል፣ ሳይጠሩህ አቤት በል፣ ነገሩ እንዲዘናበል
- ሳይጠሩት አቤት፣ ሳይሉኩት ወዴት ነገር ለማዘናጋት

ሲጠሩት አቤት፣ ሲልኩት ወዴት
- ታዛዥ ነው

ሲጠሩት የቀረ፣ ለምኖ ይሔዳል
- በክብር ሲጠራ አልመጣም ብሎ ከአንደገና ልመና

ሲጠሃ ያደገ ጥጃ፣ ቢያዙት ያጓራል
- ያለሥርዓት ያደገን ልጅ ሥርዓት ለማስያዝ ሲሞከር ያስቸግራል

ሲጥል እንጂ፣ ሲቆርጥ አይታይም
- የእግዚአብሔር ቁጣ ነው

ሲፎክሀ እንዳንበሣ፣ ሲሔድ እንደሬሳ
- የጦር መሣሪያ ጠብመንጃ ነው

ሲፈሩ አይከሱ፣ በጉጥ አያርሱ
- ወፍ የሚፈራ ዘንጋዳ አይዘራ

ሲፈራገጡ ይመለለጡ
- አጉል መፍጨርጨር ጉዳት ያመጣል

ሳለቅስ ሳነባ፣ ውል ሳሰማ፣ የሰጠኸኝ ሸማ ከደጅህ ተቀማ
- ለሌላ ሳደባ ያችኑ ያለችኝን ተነጠቅሁ

ሳሰው የሚያበድር ገዳይ፣ ተበድሮ የማይመልስ አባይ
- እያለው የማያበድር እንደገዳይ ይቆጠራል፣ የተበደረውን የማይመልስ ደግሞ ውሸታም ነው

ሰላም ሰው፣ በርበሬ አይሰርቅም
- መጥፎ ባህሪው ያጋልጠዋል

ሳላውቀው እኔ፣ ሰንት ያመጣ ሰኔ
- በሰኔ የእርሻ ሥራዬን ባለመሥራቴ ተጎዳሁ

ሳላይ ሙዙን፣ ዓየሁ መዘዙን
- ጥቅሙን ሳይሆን ጉዳቱ ነው የተረፈኝ

ሳል ያለበት ጎልማሳ፣ ዘንጋዳ ያለበት ዳጉሳ፣ አይጠቅምም
- እንከን ያለበት ነገር አይጠቅምም

ሳል ይዞ ሰርቆት፣ ቂም ይዞ ቅጥፈት
- ሳል ይዞ ሰርቆት ሞት ይዞ ቅጥፈት

ሳማና አሉብሳቢት፣ ውሽማና ሚስት
- ሁለቱም አሰቸጋሪዎች ናቸው

ሳቃዳው ፈሰሰ
- አንድን ነገር ከአንዱ ወደ አንዱ ዕቃ ማገለባበጥ ጉዳት አለው

ሳቢውን ግረፈው
- ጥፋቱ ከመሪው ስለሆነ መሪውን መግራት ይኖርብሃል

ሳብል ብሥቀው የምር መሰለው
- ብሥቅለት ጊዜ እኩያው አደረገኝ

ሳታት በግርግርታ ዳዊት በቀሰታ
- በግልና በሕብረት የምትሠራውን ሥራ አኳኋን ለይተህ ዕወቅ

ሳታድፈ፣ አጉራፈ
- ሳይቆሸሽ ማጠብ

ሳትበጡ አግሙኝ፣ ሳትመክሩ እርሙኝ
- ጸጉሬን ሳጩኝ ምላጭ አታሰነኩኝ

ሳትታመም ተፈወስ፣ ሳትረክስ ተቀደስ
- አደጋ እንዳያደርስብህ በቅድሚያ እራስህን ጠብቅ

ሳትወልድ ብላ
- ሳትወልድ እንደልብህ ሁን

ሳትዋጋ ንገሥ ቢሉት ግድ ተዋግቼ አለ
- አጭሩን መምረጥ ሲችል ዙሪያው ጥምጥም ሔደ

ሳትጋደም ፈሷ ቀደም
- ከመድረሷ ነገር መለኮሷ



ሳትጠራ ምሰክር ልሁን አትበል
- በማያገባህ ጉዳይ አትዘባርቅ

ሳነባ ለድመት፣ ገለባ ለኩበት
- ተስማሚ ነው

ሳነባ ፍየል ሳርባ
- አንድ ነገር ከመጀመርህ በፊት የሥራውን አድካሚነት ግምት ውሰጥ አስገባ

ሳያረዱ፣ አይሰደዱ
- ስደት መረዳዳት ሲጠፉና ችግር ሲጠና የሚፈጸም ድርጊት

ሳያረጋግጡ ወሬ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ
- ያልተረጋገጠ ወሬ ያዋርዳል

ሳያርሱ ግርድ፣ አለዳኛ ፍርድ
- ሁሉም በባለሙያ ያምራል

ሳያሰረግጡ ወሬ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ
- ያልተረጋገጠ ወሬ ያዋርዳል

ሳያሸረው የበላ ኮሶኛ፣ ሳይፈርድ የበላ ዳኛ
- ፍጹም ጥሩ አይሆንም

ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ፣ ሲስል ያድራል
- በጥንቃቄ ያልሠሩት ሥራ ችግር ያመጣል

ሳያቃጥል በቅጠል
- ፈጥነው የደረሱበት ጉዳይ መልካም ነው

ሳያተርፍ ያበደረ፣ ሳይቀበል ተቀበረ
- ለራሱ ሳይበቃው ለሌላው የረዳ ችግር ላይ መውደቁ አይቀርም

ሳያውቅ የተረተ፣ ሳይዘራ ያመረተ
- የተገላቢጦሽ ነገር የፈጸመ

ሳያድጉ ማደግ፣ ያዳግማል
- የቸኮለ አፍሶ ለቀመ

ሳያገቡ ማርገዝ፣ ሳያረጁ መፍዘዝ
- ያለወቅቱ የሚፈጸም ተግባር ያደናግራል

ሳያጠፉ ምክር ሳይሞቱ ተዝካር
- ጠቀሜታውና ተቀባይነቱ ምን ያህል ይሆን

ሳያጣሩ ወሬ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ
- ያልተጣራ ወሬ ማውራት ያዋርዳል

ሳይሆን ሆነ፣ ሳይሰበር ተጠገነ
- ያልተደረገ ነገር ሆነ አለ

ሳይሆን ለጉም፣ ሳይሰበር ጠግን
- አደጋ ሳይደርስ ተጠንቀቅ

ሳይሆን መረጃ ለቃልቻ፣ ሳይቀደሙ መታገል ለሙትቻ
- ከጠላትህ ጋር ልትፋለም ስታሰብ ሳይቀድምህ ቅደመው

ሳይሆን ይመስላል፣ ሲሆን ይገርማል
- አንድ ሁኔታ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲፈጸም ያስገርማል

ሳይሰማ በደልማ፣ ሳይቃጠል በቅጠል
- ችግሩ ሳይብስ ቶሎ መቀጨት አለበት

ሳይለግሙ፣ ይግሙ
- ሥራውን ችላ አይበሉ

ሳይማሩ መተርጎም፣ ሳያም ማገም
- ያለሙያ በማይሰፈልግበት ቦታና ሁናቴ አንዳች ነገር ልፈጽም ማለት ትርፉ ችግር መፍጠር ነው

ሳይማሩ ማገበብ፣ ሳይበሉ መጥገብ
- የቀን ቅዠት

ሳይሞቅ ፈላ
- ሳያድግ ያደገ

ሳይረቱ አይሞቱ፣ አለዳኛ አይሟገቱ
- ሁሉም ነገር መነሻና ሥርዓት አለው

ሳይረቱ አይበረቱ
- ውጤት ብርታትን ያስገኛል

ሳይርቅ በቅርቡ፣ ሳይደርቅ በርጥቡ
- ልጅን በጡት እህልን በጥቅምት

ሳይርበው የሚበላ፣ ረኃብን አያውቅም
- የረኃብን ትርጉምና ምንነት የሚያውቀው ያው የተራበው የደረሰበት ነው

ሳይሠሩ ማግኘት፣ ሳይጸድቁ ገነት አይገኝም
- ሥራ ሳይሠራ ገንዘብ አይገኝም

ሳይሰሙ ማውራት፣ መዋረድ አለበት
- ያልሰሙትን ካወሩ ይዋረዳሉ

ሳይቀሱ መምሬ፣ ሳይጠምዱ ገበሬ
- ምንም ዕውቀት ሳይኖርህ ባለሙያ መስለህ አትታይ

ሳይቀሰሱ፣ አይናዘዙ፣ ሳይሾሙ አያዙ
- ዕውቀት ከሌለህ ሥልጣኑ የለህም

ሳይቃጠል በቅጠል
- ልጅን መቅጣት በጡት

ሳይቆጥር የሰጠ ሰጭውም ሌባ፣ ተቀባዩም ሌባ
- ሳይቆጥርም፣ ሳያስቆጥርም የተቀበለ ሌባ ነው

ሳይቆጥር ያኖረ፣ ሌባ ሳይቆጥርም፣ የተቀበለም ሌባ
- ሁለቱም ሌባ ናቸው

ሳይበሉ ማግሳት፣ ልከበር ብሎ መኳኳት
- ለክብር መኳኳት በምኞት አይገኝም

ሳይባርክ ያርዳል፣ ሳይታየው ይፈርዳል
- ቅደም ተከተሉን ያላወቀ ስሕተት ላይ ይወድቃል



ሳይተርፋት ያበደረች፣ ሳትቀበል ሞተች
- አቅምን ማወቅ ይጠቅማል

ሳይታሰም የተፈታ
- ድሮም የታወቀ ነገር ነው

ሳይታደሉ አይገዙ፣ ሳያልቡ አይወዙ
- ሁሉም ነገር መነሻ ምክንያት ይኖረዋል

ሳይታገል ጣይ፣ ሳይወጋ ገዳይ
- በወሬ ብቻ እንዳደረገው የሚቆጥር ሰው

ሳይታፈሩ መገሰል፣ ዕብድ ያሰኛል
- ሰው የሚከበረው በዕድሜው፣ በዕውቀቱ ወይም ባሰው ሥልጣን ነው

ሳይቸገር የተበደረ፣ ሳይከፍል ተቀበረ
- አስመሳይነት ነው

ሳይቸግር ጤፍ ብድር
- ሌላ ምኞት መመኘት አይገባም

ሳይነገር ይፈርዱታል፣ ሳይጽፍ ያነቡታል
- መቀባጠር ጥሩ አይደለም

ሳይከካ፣ ተቦካ
- ሳይጀመር አለቀ

ሳይወዱ ቢያጎርሱ፣ አጥንት አስነከሱ
- ወዳጅ መስሎ ጠላት

ሳይዋጉ፣ ተንዘራጉ
- መስሎ ለመታየት

ሳይውሉ ያዋዋሉ፣ ይሰብሩ ላይጠግኑ
- አንዳችም መልካም ተግባር የማይፈጽሙ

ሳይውሉ ይዋዋሉ፣ ሳይተማመኑ ይማማሉ
- የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል

ሳይውል ሳያድር፣ የሰው ልጅ ብድር
- ብድር በምድር

ሳይዘሩ ማጨድ ሳይራመዱ መሔድ
- ተጨባጭነት የሌለው ነገር

ሳይያዙ ገና፣ ዛር ልመና
- ወድዶ በራስ ላይ ችግር ማምጣት

ሳይደውል ቅዱስ
- የጅብ ችኩል

ሳይደግስ አይጣላም
- ላይጠግን አይሰብርም

ሳይጠሩህ መጣህ፣ ሳትጠግብ ወጣህ
- ሳይጠሩት የመጣ፣ ሳይጠግብ የወጣ

ሳይጠሩት እማካሪ፣ ሳይሾሙት ፊት አውራሪ
- በማይመለከተው ጉዳይ የሚዘባርቅ

ሳይጠሩት አቤት፣ ሳይልኩት ወዴት
- በማይመለከተው ጉዳይ የሚዘባርቅ

ሳይጠሩት አቤት ባይ፣ ሳይሰጡት ተቀባይ
- በማይመለከተው ጉዳይ ጥልቅ የሚል

ሳይጠሩት የመሰከረ፣ ሳይጠጣ የሰከረ
- ቀዥቃዣ፣ ሰው

ሳይጠሩት ይመጣል፣ ሳይዘሩት ይበቅላል
- የማይፈለግ ነገር

ሳይጠይቁ አያውቁ
- ከመጠየቅ ብዙ ምሥጢርና ዕውቀት ማግኘት ይቻላል

ሳይጠጡ መስከር፣ ሳይሞቱ መቃብር
- የማይሆንና የማይታመን ነገር

ሳይጣሉት የተጣላ፣ ሲርብ ያበላ አይረሳም
- በረኃብ ጊዜ ያበላ ሰው ምንጊዜም ትዝታው ከልብ አይፋቅም

ሳይጾሙ ይጸድቃሉ፣ ሳይታመሙ ይጠየቃሉ
- ሳም ባልዋሰበት ኩበት ሰቀማ

ሳይፈታ ሚስቱን፣ ሳይረታ ርስቱን
- ጥንካሬና ወኔው የፈሰሰ ሰው የሥራ ውጤት ነው

ሴት ለቤት፣ ወፍጮ ለዱቄት
- ሴት ከቤት ውጪ በአደባባይ መታየት የለባትም

ሴት ማገዶ ቢቸግራት፣ ምሰሶ ትንቅላለች
- ችግር የማያደርገው ነገር የለም

ሴት ሲያፏጩላት ያረሱላት ይመስላታል
- በቀላል ነገር ትደሰታለች

ሴት በማጀት ወንድ በችሎት
- ሴት ከቤት ውጪ በአደባባይ መታየት የለባትም

ሴት በጳጳስ፣ ኳደሬ በንጉሥ
- ሊመሰሉ ይችላሉ

ሴት ታውቅ፣ በወንድ ያልቅ
- ሴት ምንም ብታውቅ የሚያልቀው በወንድ ነው

ሴትና መሬት የማይችሉት የለም
- ሴት መከራን ችላ ቤቷን ታስተዳድራለች

ሴትና ቄስ፣ ቀስ በቀስ
- ቄስና ሴት መቸኮል የለባቸውም

ሴትና በቅሎ፣ እንደገሪዋ ነው
- ሴት ፊት እንዳሳዩዋት ነው

ሴትና ቤት፣ አይታመን
- ሴት በቀላሉ ልትታለል ስለምትችል



ሴትና አህያ በዱላ
- ሴትን በዱላ ነው መግራት የሚቻለው

ሴትና ዶሮ፣ ሳያብድ አይውል
- ሳትበሳጭ አትውልም

ሴትና ዶሮ ዱር ከሔዱ፣ ቤታቸውን ይከዱ
- ሴት ከባሏ ውጭ ወንድ ከለመደች አርፋ አትቀመጥም

ሴትና ፈረስ፣ እንደኩሬ ውኃ እያደር ማነስ
- ሴት ብዙ ስትወልድ እንክብካቤ ካልተደረገላት ሰውነቷ ሊቀንስ ይችላል

ሴትና ፈረስ፣ ያቀረቡላትን ይቀምስ
- ለቤቷ የምታስብ ሴት ብዙ ነገር አያምራትም

ሴትን ከቤት፣ ብርን ከማድቤት
- ጠቃሚውን ብር የዱሮ ሰዎች በማድቤት ውስጥ በማሰሮ ይቀብሩ ነበር

ሴትን ያመነ፣ ጉም የዘገነ
- ሴት እምነት አይጣልባትም

ሴት አማት የመረዘው፣ ኮሶ የነዘዘው
- ከሴት አማት የተጣላ ትዳሩ አይስምርለትም

ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ፣ የትአስ ንግዱ
- በቤተሰብ ውስጥ ወንድ ሲወለድ ደስታው የበዛ ነው

ሴት ከበዛ፣ ጎመን ጠነዛ
- ሴት ከተሰበሰበ ሥራው አይሠራም

ሴት ከወንድ፣ እህል ከሆድ
- ሴትና ወንድ አብሮ የመኖር ግድ ነው

ሴት ከጠላች በቅሎ ከበላች፣ ዓመል አወጣች
- ሴት ባሏን ከጠላች ልቧ ወደሌላ ይኮበልላል

ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም
- ሴት ካልወለደች ንብረት በቤት ውስጥ አታኖርም

ሴት ካልዋሸች፣ ባልዋን ትወልዳለች
- በባሏ ላይ ዝሙት ካልፈጸመች ባልዋን የመሠለ ልትወልድ ትችላለች

ሴት የላከው ሞት አይፈራም
- ሴቲቱን ለማስደሰት ብሎ እሳት ውስጥ ይገባል

ሴት የወደደ ገሃነም እሳት ወረደ
- እንዴ ከወደደ ለእሷ ሲል የማይሆነው የለም

ሴትየዋ በገዛ እረሟ እባብ ይዛ ታስፈራራ
- ነገ የሷው ችግር መሆኑን በመዘንጋት

ሴት ያመጣችው ጠብ ቶሎ አይበርድም
- በሴትና በውሻ የመጣ ጠብ ቶሎ አይበርድም

ሴት ይወዷል፣ ማጀት ይንጎዳጎዷል
- የወደዷትን ለማግኘት በየጉዳንጉዱ መገኘት

ሴት ጅብ ትፈራለች፣ አጥር ትመዛለች
- የኋላውን አታመዛዝንም

ለለ ላቂ ውል አያውቂ
- በሥልጣን ከፍ በላሉ የተዋዋሉትን ውል አያከብሩም

ስል ልብስ፣ ይኮራል ነፍስ
- ጥሩ በመልበስ ፍሥሐ፣ ሐሴት ያስገኛል

ለለ ትዕግለቱ ይጸሙ፣ ለለ ሥረዓቱ ይቆሙ
- አንዳች ጠቃሚ ተግባር ለማከናወን በትዕግስትና በሥርዓት መሆን አለበት

ሰለት ይቆርጣል፣ ምላስ ያስቀጣል
- መቀባጠር፣ ችግር ላይ ይጥላል

ለለት ድግሱን፣ ደባ ራሱን
- ክፉ ሥራ ተመልሶ ባለቤቱን ይጎዳል

በለ ናቂ መላ አያውቂ
- አንዳች ነገር ላይ ንቀት ካደረብን ማስወገጃው ዘዴ ላይ አናተኩርም

ለለ ከለሱ አይፈወሱ
- የከለሰ ሁሉ አይረታም

ለለ ጨስ አይነድም፣ በለዳመነ አይዘንብም
- የሚመስል ነገር ሁሉ ላይሆንም ይችላል

ለለ ፍቅር በሰመአብ ይቅር አለ ሰይጣን
- የተደሰተ መስሎ ታየ ሳያስደስተው

ለላንጋጠጡ፣ አይገጡ
- ያንጋጠጠ ሁሉ አይገኝም

ስልቻ ለሥጋ መከተቻ
- ዞሮ ዞሮ ያው እንደዱሮ

ስልቻና አቁማዳ፣ ቆራጣና ጎማዳ
- ያው ያው ነው

ስልጡን እንግዳ፣ ይውላል ከጓዳ
- የሔደበትን ቤተሰብ ሲያገለግል ይውላል

ስሕተትና እበባ በትምህርትና በጥቅምት ይታረማል
- ሁሉም በጊዜና በዕውቀት ይስተካከላል

ለመስክርልህ ዋልኩ ቢለው፣ ለታዘብህ ዋልሁ አለው
- ያው ነገም በኔ ይኸው ነው በማለት

ስሙ ለባለቤት፣ ቤተሰብ ናኘበት
- ሠሪው ሌላ ተመስጋኝ ሌላ

ስሙን ለሰው አወረሰው
- የተባለው ቀርቶ ያልተባለው



ስሙን ጠርቶ፣ ራሱን ቆርጦ
- እንዳይታወቅ በማድረግ

ስሙ እኩል፣ ሥራው ለንኩል
- ሥራውን አቃንቶ የማይሠራ ስንፍ

ስምህ ማነው ላገር አይመች፣ ማን አወጣልህ ጎረቤቶች
- ስምን መልዐክ ያወጣዋል

ስምንተኛው ሺ ሰው አበላሺ
- የዚህ ዘመን ሰው በጣሙን አስቸጋሪ ነው

ስም ከመቃብር በላይ፣ ልብስ ያምራል በሰው ላይ
- መልካም ሥራ የሠራ ሰሙ ሁልጊዜም ሲዘከር ይኖራል

ስም ከመቃብር በላይ ይውላል
- መልካም ሥራ የሠራ ሲታወስ ይኖራል

ስም ያለው ሞኝ ነው
- ሳይጠሩት አቤት ይላል/ ሞክሼው ሲጠራ አቤት ይላል/

ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጎረቤት
- ውሻ በቀደደው፣ ጅብ ይገባል

ስም ጥራ ቢሉት፣ እመተ ዘይኗ
- ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ

ስምታ የውርርድ እኩሌታ
- የኔ ከአንተ ወይም ካንቺ ብሶ በማለት

ስርቆት የሚለምድ፣ ማጀት የገቡለት
- ሁኔታዎች ሲገፋፉ

ስሱ መኳንቱን፣ ቆዳ መንኳንቱን አይተውም
- በስታም ያየው ነገር በሙሉ ያኳኳዋል

ስሱ ሲበላ ይታነቃል፣ በሽተኛ ሲናገር ይታወቃል
- መስገብገብ ለአደጋ ያጋልጣል

ስሱ አንድ ያንቀው፣ አንድ ይወድቀው
- አንዱንም ሳያገኝ ይቀራል

ስሰላ ቢመሽብኝ፣ ጥንቅር ይበልብኝ
- ከሆዴ የሚብስብኝ የለም

ሱሀ ያርዱ ጉፋያ ይነዱ
- ይሄ ሌላ ያ ሌላ

ሰታበይው፣ በልተሽ ታይው
- አምረሽ፣ ተውበሽ ታይው

ሰታበጀው ውላ፣ አበላሸችው ባተላ
- ሲያልቅ አያምር

ሰታቦካ ውላ፣ ባተላ
- ሲያልቅ አያምር

ስትሔድ ቀንጣ ቀንጣ፣ ሰትበላ እንደአንበጣ
- አበላሏ እንደአንበጣ ኃይለኛ ነው። አንበጣ ያገኘውን ሁሉ ጥርግ ያደርጋል

ስትሞት የሚያለቅስልህን፣ ታመህ እየው
- የሚወድህንና የሚጠላህን በሕመምህ ጊዜ ስይተህ ታውቀዋለህ

ስትወልድ የምትበላውን፣ በእርግዝናዋ ጨረሰችው
- ለአስፈላጊው ጊዜ የሚሆነው ቀድሞ ካለቀ የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑ ነው

ስትግደረደሪ ጠምሽን እደሪ
- መግደርደር ጠሚን አሳደራት

ስትግደረደሪ ጦምሽን እንዳታድሪ
- መግደርደር ጥሩ አይደለም

ስትፈጭ የነበረች፣ ማንጓስል አቃታት
- ከባዱን ሥራ ሠርታ ቀላሉ አቃታት

ስንቁን በተቀማ ነጋዴ፣ ዋግ የመታው ሥንዴ
- ብርታት የሚገኘው ጤና ከመሆንና ከምግብ ነው

ስንቃችን በልባችን፣ እለ አሞራ
- የምናደርገውን እናውቃለን

ስንቅህን ባህያ፣ ዓመልህን በጉያ
- ባህርይህን እርም

ሰንቅና ማህሌት እንደያዥው ነው
- ሲያጥርም ሲርዝምም ይችላል

ሰንቅና ዓባይ እያደር ይቀላል
- ውሽታም ሰው ሲነቃበት ይዋረዳል

ስንቅ ያለው ጦም አያድርም ዋስ ያለው አይታሰርም
- ጥሪት ያሰቀመጠ ወድቆ አይወድቅም

ስንት ያመጣ ሰኔ
- በሰኔ ያረሰ ብዙ ምርት ያገኛል

ስንኳን ረኃብ፣ ጥጋብም እችላለሁ
- ለምንም ነገር አልጨነቅም

ስንኳን ከጦርነት፣ ከወሬም አልፈራ
- ለምንም ነገር አልጨነቅም

ስንዝር ሲለቁለት ክንድ ፈለገ
- ፊት ሳሳየው፣ ጭንቅላቴ ላይ ወጣ

ስንዝርና ጋት አባትና እናት
- ሁለቱም ልክ ልክ አላቸው

ስንፍ የዶባ፣ ላም የጋለሞታ
- አንድ ዓይነት ናቸው ይመሳሰላሉ

ሰደቡኝ ባይ፣ እመንገድ ላይ ያራል
- በራሱ ላይ ችግር ይጠራል



ስደተኛ ሲሰነብት፣ ይሆናል ባላባት
- እየቆዩ ሲሔዱ እንግድነት ይቀራል

ስደት ለወሬ ያመቻል
- ጅብ የማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ

ስደት ከጨዋ ልጅ፣ መንገድ ከአገር ልጅ
- እየተጫወቱ የሚሔዱት መንገድ ርቀቱ አይታወቅም

ስደብ በልጅ ያምራል
- ትልቅ ሲሳደብ አያምርበትም

ስድብሽና ስድቤ እኩል ነው ትርፉ ሰው መስማቱ ነው
- እኩል ተሰዳድበናል ሰውም ታዝቦናል

ስድ የለመደ ጥጃ፣ ሲይዙት ይጓጉራል
- በሥርዓት ያላደገ ልጅ ችግር ይፈጥራል

ስጡኝ አለማለት ከወዳጅ መሰንበት
- ሰው ሁሉ አምጣ ሲሉት አይወድም

## <u>መልመጃ 3 / ሬ፣ ሰ /</u>

ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ስምቶ መቻል __________
   ሀ. ለእግዚአብሔር ይመቻል
   ለ. በንጉሥ ያምራል
   ሐ. ለፍርድ ይመቻል
   መ. በድሃ ያምራል

2. ረኸምና ቀፋፋ __________ ።
   ሀ. ሲሔድ ፈፋ ለፈፋ ሐ. ሲሔድ ቀርፋፋ
   ለ. ገደልና ፈፋ መ. ይከብዳል

3. ሩዋጭና በራሪ __________ ፈሪ
   ሀ. ብልጥና ሐ. ንፉግና
   ለ. ሰነፍና መ. ሞኝና

4. ራሱን ለተሳጨ __________ ።
   ሀ. ባርኔጣ ሐ. ነጠላ
   ለ. ጥምጣም መ. ፈቱን ለነጨ

5. ሲሻሩ ከላሽ __________ ።
   ሀ. ሲሾሙ አመልካች
   ለ. ሲሞቱ ወራሽ አይታጣም
   ሐ. ሲሾሙ ፈራጅ አይታጣም
   መ. ሲጎርሱ ቀዳሽ አይታጣም

6. __________ ሲከር ይበጠሳል።
   ሀ. ሲመዙት ይሳባል ሐ. ሲሞላ ይፈሳል
   ለ. ሲላላ ይረግባል መ. ሲስቡት ይጠብቃል

7. ላይማሩ መተርጎም __________ ።
   ሀ. ላይጽፉ ማረም ሐ. ላያም ማገም
   ለ. ላይለሉ መተለም መ. ላያርሙ መከርከም

8. ራስ ላይጠና __________ ።
   ሀ. ጉተና ሐ. ለው ማገም
   ለ. ቁመና መ. ከሰማና

9. ራት ቢንቁ __________ ።
   ሀ. አንድ እጅ ይለቃለቁ ሐ. አይለቃለቁ
   ለ. ይጠነቀቁ መ. መልሱ የለም



10. ረኸሮም ጦር ባይወጉበት __________ ።
    ሀ. ይፎክሩበት ሐ. ያባርሩበት
    ለ. ያስፈራሩበት መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

11. ሰው ለወደደው __________ ።
    ሀ. ይሞታል ሐ. ዘንጋዳ ጤፉ ነው
    ለ. ሙከቱን ያርዳል መ. ሁሉም መልስ ነው

12. ረባዳ ቤቱ __________ ሚስቱ
    ሀ. ጮሌ ለ. ሞኛሞኝ ሐ. ሰነፍ መ. ገራም

13. ራስ ተከናንቦ __________ ።
    ሀ. ሙርጥ ገልቦ ሐ. ሌብነት
    ለ. ሱሪውን አሰጦፎ መ. መልሱ የለም

14. ራስ ተላጭቶ ወለባ __________ ።
    ሀ. ልባልባ ታጥቆ አዛባ ሐ. ቤት ሳይሠሩ እንጋባ
    ለ. ጩቤው ሳይኖር ሰገባ መ. ሚስት አግብቶ ጡት ልጥባ

15. ስታቦካ ውላ __________ ።
    ሀ. ቆመጠጠ ለ. ባንከላ ሐ. ባተላ መ. ፈላ

16. ሲመትሩለት __________ ።
    ሀ. ይለብስ ሐ. ይነጭ
    ለ. እኩፋዳው ይከት መ. ይቀድ

17. ሰው ከራበው __________ ።
    ሀ. አይመርጥም ካገኘው ሐ. ርሱቱን ይሸጣል
    ለ. ጥራቱን አያየው መ. የሰይፉን ሰገባ ይበላል

18. ሳይሠሩ ማግኘት __________ ።
    ሀ. ሳይጸድቁ ገነት ሐ. ሳይጸድቁ እምነት
    ለ. ሳይጸድቁ ሥርየት መ. ሳይጸድቁ ጸሎት

19. __________ የሰው ልጅ ብድር።
    ሀ. ያላንዳች ግርግር ሐ. ያላንዳች ጥርጥር
    ለ. ሳይውል ሳያድር መ. መክፈሉ ላይቀር

20. ሳይታደሉ አይገዙ __________ ።
    ሀ. ሳያርሱ አይቀምሱ ሐ. ሳይገዙ አይጠዙ
    ለ. ሳያውቁ አይገዙ መ. ሳያልፉ አይወዙ

21. ሰነፍ እረኛ __________ ።
    ሀ. ገሳ አቅፎ ይተኛ ሐ. ከጥር ሥር ይተኛ
    ለ. የሰው ዱተኛ መ. መልሱ አልተሰጠም

22. ሰይጣን ለወዳጁ ________ ።
ሀ. ብቅ ይላል ካመዱ ሐ. ቅርብ ነው
ለ. ይደግሳል በጁ መ. ድርብ ነው

23. ለማይ አገሬ ________ ወንበሬ።
ሀ. ምድር ሐ. እግዳሚ
ለ. ኮከብ መ. መልሱ አልተሰጠም

24. ሰምቶ መቻል ________ ይመቻል።
ሀ. ለሎሌ ሐ. ለድሃ
ለ. ለእግዚአብሔር መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

25. ሰላ የእናቷን ________
ሀ. ትበላ ለ. ታጠፋ ሐ. አትረሳ መ. ትረሳ

26. ለባት ወልዶ ________ ።
ሀ. ማንዛረጥ ሐ. ዕቃ ቤትነት
ለ. መገልፈጥ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

27. ሰነፍ ሰው ናቂ ________ ሰው ሣቂ
ሀ. ኀበዝ ለ. ብልጥ ሐ. ሞኝ መ. መልሱ የለም

28. ሰነፍ ሲኮራ ________ ይታጠቃል።
ሀ. ድንጋይ ለ. ጎራዴ ሐ. ማጭድ መ. ጦር

29. ሰነፍ ቢመክሩት ________ ቢወቅጡት።
ሀ. ቡና ሐ. ጌሾ
ለ. ውኃ መ. ሁሉም መልስ ነው

30. ሰነፍ ________ ያበዛል።
ሀ. ጉራ ለ. ማልቀስ ሐ. በዓል መ. መልሱ የለም

31. ሰንበሌጥ ለቤት ________ ለባለቤት።
ሀ. ገንዘብ ለ. ዕዳ ሐ. እጥር መ. ቀሚስ

32. ራት ________ አይለወጥም።
ሀ. በዕዳ ለ. በይሉኝታ ሐ. በሰው መ. በዳረጎት

33. ሬሳ ባል ጋ ________ ።
ሀ. በሽተኛ ባልጋ ሐ. ጥሬ በመንጋጋ
ለ. በሽተኛ በእንቡላንስ መ. መልሱ የለም

34. ሰነፍና ________ ከወደ አፉ
ሀ. ጥንጫ ሐ. ጠርሙስ
ለ. ቆንጆ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ



35. ሰኔ መቃጠሪያ ________ መገናኛ
ሀ. ሆቴል ለ. ግንቦት ሐ. ቤት መ. ሕዳር

36. ሰው ማንን ያህላል ________ ።
ሀ. እራሱን ሐ. የተናገረውን
ሰ. ጓደኛውን መ. መልሱ የለም

37. ሰው ________ አይታየውም።
ሀ. የኋላው ሐ. ማጅራቱ
ለ. የወደፊቱን መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

38. ሰይጣን ቢያረምም ________ ይመስላል
ሀ. ቆንጆ ለ. መልካም ሐ. ክፉ መ. ባህታዊ

39. ሲሆን በውድ ________
ሀ. ሳይሆን በልምምጥ ሐ. ሳይሆን በግድ
ለ. ሳይሆን በእማላጅ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

40. ሰዶ ከማሳደድ ________ ።
ሀ. እርፎ መቀመጥ ሐ. የያዙትን ማጥበቅ
ለ. ሽጦ እርፍ መ. መልሱ የለም

41. ሲመክሩት አይመከር ________ ።
ሀ. በነገር ይነከር ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
ለ. በደም ይነከር መ. መልሱ የለም

42. ሲማር ________ ።
ሀ. ይመራመር ለ. ይደነቁር ሐ. ያስተምር መ. ይታሰር

43. ሰው በሰው ላይ ________ ሳይ
ሀ. ቅቤ በጨው ሐ. ሥጋ በሥጋ
ለ. ወጥ በእንጀራ መ. ሁሉም መልስ ነው

44. ሰው በዘመድ ________ ።
ሀ. ዱቄት በሙሬ ሐ. እህያ በገመድ
ለ. ዘመድ በዘመድ መ. አንበሳ በድርጊት

45. ሰውና ዓመሉ ________ ይኖራሉ።
ሀ. ተከባብረው ሐ. ሳይናናቁ
ለ. ተዋውቀው መ. ሳይተዋወቁ

46. ሰው የተጠጋ ________ ።
ሀ. ከሰይጣን የተጠጋ ሐ. ሰው ወጋ
ለ. ያልፍለታል መ. መልሱ የለም

47. ሲሰርቀኝ ዐየሁት __________ ጠላሁት።
ሀ. ሲሰጠኝ ሐ. ሲሥቅ
ለ. ሲያመልጠኝ መ. መልሱ የለም

48. ሲበዛ __________ ።
ሀ. ይመራል ሐ. ይጣፍጣል
ለ. ይገነፍላል መ. ይከብዳል

49. ሲያጡ እጅ __________ ።
ሀ. ያጥራል ሐ. ላፍ ይጠናል
ለ. ይለምናል መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

50. ሲጠባ ያደገ ጥጃ __________ ያጓራል።
ሀ. ሲመቱት ለ. ቢከለክሉት ሐ. ቢሰጡት መ. ቢይዙት

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ የሚሆኑትን ምረጡላቸው</u>

1. ሲያይ የሞተን ሲሰማ ቅበረው
ሀ. አጥፊን እንዳላየ አይተህ አሰፈው
ለ. አጥፊን አበረታታው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ አልተሰጠም

2. ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አያድርም
ሀ. ጉትቻ ለጆሮ ጥሬ ለዶሮ
ለ. ሰው ከመከረው መከራ የመከረው
ሐ. ሰው እንደሀቅሙ እህል እንደቃረሙ
መ. አማቱን ምታ ቢለው ሚስቱን በየት አልፌ

3. ሲሮጡ የታጠቁ ሲሮጡ ይፈታል
ሀ. ሲሸኝ ጠኢስ ወጋኝ
ለ. አለባበሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ
ሐ. ሲያዝኑለት ይነክስ፣ ሲያወርዱት ያለቅስ
መ. ሲርበኝ ታነቅሁ፣ ሲጨንቀኝ ታነቅሁ

4. ራስዋን ሹሩባ ልትሠራ ሔዳ ፀጉሯን ተነጭታ መጣች።
ሀ. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
ለ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

5. ሳያቃጥል በቅጠል
ሀ. አረምን መንቀል ሥር ሳይሰድ ነው
ለ. ልጅን መቅጣት በጡት
ሐ. ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቆረጠምም
መ. ሁሉም መልስ ነው



ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያዳምጡ ወሬ
ሀ. እያገባው ገብቶ እያወዛው ተቀብቶ
ለ. አንበሳ ሳይገድሉ ቆዳውን ያስማማሉ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

ለነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል
ሀ. ሰንዘር ሲለቁለት ክንድ ፈለገ
ለ. ሰው በየወንዙ ብዙ ነው መዘዙ
ሐ. ሞኝ ወታደር ሚስቱን ጥሎ መንደር
መ. ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል

ሲያጌጡ ይመላለጡ
ሀ. ለማጌጥ ሲባል ተመላለጠች
ለ. ከመጠን ካለፈ መጥፎ ነው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ
ሀ. ሩቅ ለመሔድ ስታስብ ቀረብ ብለህ እደር
ለ. እንዳሰቡት ላይሳካ ይችላል
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

ራብን የማያውቅ ለተራብ አያዝንም
ሀ. ራብን የማያውቅ ሰው ሰስታም ነው
ለ. ያልተቸገረ ተቸግሮ የማያውቅ ሰው ችግረኛ አይረዳም
ሐ. ራብን የማያውቅ ሀብታም ነው
መ. መልሱ የለም

ሐ. **በ "ሀ" ሥር ካሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በ "ለ" ክፍል ካሉት ጋር አዛምዱ**

| | ሀ | | ለ |
|---|---|---|---|
| 1. | ራት የለሀ ቢሉት ከወጡ አውጡልኝ አለ | ሀ. | እውነትና ንጋት እያደር ይታያል |
| 2. | ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጎረቤት | ለ. | ወጌሻ ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል |
| 3. | ሳይደውል ቅዱስ | ሐ. | ወንድምና፣ ወጥ ማለፊራሪያ ነው |
| 4. | ርስት በሺ ዓመቱ ለባለቤቱ | መ. | ከሆዱ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህ |
| 5. | ሳይደግስ አይጣላም | ሠ. | ሳይሰሙ መናገር ከሐሜት ይቆጠራል |
| 6. | ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ | ረ. | ሳይጠሩት ይመጣል፣ ሳይዘሩት ይበቅላል |
| | | ሰ. | ሳይጠግን አይሰብርም |
| 7. | ራስ ሲመለጥ ነገር ሲያመልጥ | | |
| 8. | ስምህ ማነው ላገር አይመች፣ ማን አወጣልህ ጎረቤቶች | ሸ. | ጅብ እማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ያላል |
| 9. | ስም ጥሬ ቢሉት፣ እመት ዘይና | ቀ. | ሲያልቅ አያምር ሰምን መልዐክ ያወጣዋል |
| 10. | ራት የሌለው ቁስ እንደልቡ አይቀደስ | በ. | ካፍ ከወጣ አፋፍ |
| 11. | ሰው ሆኖ የማይበድል፣ ዕንጨት ሆኖ የማይጨስ | ተ. | ቀለብ የሌለው ውሻ ጠዲቅ አምጡልኝ ይላል |
| 12. | ለው ለወደደው፣ ዘንጋዳ ጤፉ ነው | ቸ. | ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል |
| 13. | ረዥም ሠር ባይወጉበት ያሰፈራሩበት | ኀ. | የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ |
| 14. | ሲያብል የተኛ፣ ሲጠሩት አይሰማም | ነ. | ለሰው ሰው ነው ልብሱ |
| 15. | ሰው ያለሙ፣ አርፍዶ ይሞታል | ኘ. | የሴትና የቄስ ችኩል አያምርበትም |
| 16. | ራስ ከተመለጠ፣ ነገር ካመለጠ | አ. | ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ |
| 17. | ሳይጠሩት አቤት፣ ሳይልኩት ወዬት | ከ. | ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ |
| 18. | ለው እሚበላ ቡዳ፣ እጉድጓድ ሆኖ ያጠብቃል | ወ. | ምስጥ ከምድር ውስጥ |
| | | ዘ. | ከወደዱ ወዲያ ገደሉ ሜዳ |



## ሸ

ሸማ ለብሶ ስልቻ፣ በቅሉ ጭኖ ለብቻ
- ሥራን በትክክል ካልሠሩት ለአሠራር ያስቸግራል

ሸማ ማዋስ ለባላገር፣ በቅሉ ማዋስ ለወታደር
- አጠቃቀሙን ለሚያውቅ መስጠት

ሸማ በውኃ፣ ሰው በንሰሐ
- ልብስ በውኃ እንደሚነጻ ኃጢያትም በንሰሐ ይነጻል

ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል
- ሁሉንም እንደየጠባዩ ማስተናገድ

ሸማኔ በመኑ ጠይብ በከሰሉ
- ማንኛውም ሰው የሚታወቅበት ሞያ አለው

ሸማኔ በድሩ፣ ጠይብ በመንደሩ
- በየሥራው ባህርይ ይታወቃሉ

ሸማኔ ድውሩን፣ ባለሥልጣን ክብሩን
- ሲነኩበት አይወድም

ሸማን በውኃ፣ ሰውነትን በንስሐ
- ማንጻት ይቻላል

ሸማን ጠምዞ ያስጧል፣ እህልን አላምጦ ይውጧል
- ነገርን በሚገባ ማገናዘብ ይገባል

ሽምበቆ በመርዘሙ ምሰሶ አይሆንም
- የአንድ ነገር ይዘት ወሳኝ ነው

ሸርሙጣ ስታረጅ አቃጠሪ ትሆናለች
- የተለመደ ባህርይዋን ለሌሎች ለማስተላለፍ

ሸርሙጣን የወደደ ልብሱን ጥሎ ያበደ
- ከሴተኛ አዳሪ ጋር የተወዳጀ ሕይወትን ያበላሻል

ሸኚ ቤት አያደርስም
- ከንቱ ልፋት

ሸኚና ጥላ ቤት አይገባም
- በውጪ ይቀራሉ

ሸክላ ቢጥሉት ገለባ
- ሸክላ ከእጅህ ከወደቀ እንክትክት ይላል

ሹመት ሳውቀው ይከብደዋል፣ ላላወቀው ያሳብደዋል
- ሹመት ከባድ ኃላፊነትን ይጠይቃል

ሹመት ሲገኝ፣ ዘመድ አይገኝ
- አልጋው ሲገኝ ባሉ አይገኝ

ሹመት ሺህ ሞት
- ሹመት ከባድ ኃላፊነትን ይጠይቃል

ሹመት በተርታ፣ ሥጋ በገበታ
- ሁሉም እንደየማዕረጉ

ሹመትና ቁመት አይገኝም በምኞት
- አንድም ከደግ ተወለደ አንድም ከደግ ተጠጋ

ሹመትና ቁመት፣ ከልኩ አያልፍም
- ምን ብትደክም ከተወሰነለት መጠንና ወቅት አያልፍም

ሹመት የለመደ ወንዝ ዳር ይጠርዳል
- የውኃውና የድንጋዩ ቻቻታ የሕዝብ አቤቱታ ይመስለዋል

ሹም ሰመነ፣ አዘዘ
- ሹም አድርጉልኝ ካለ ማንም እንቢ አይለውም

ሹም ለሹም ያወርሳል፣ ጉም ተራራ ያለብሳል
- ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ፣ ድሃ ለድሃ ይለቃቀሱ

ሹም ለሹም ይጎራረሳል፣ ድሃ ለድሃ ይለቃቀሳል
- ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ፣ ድሃ ለድሃ ይለቃቀሱ

ሹም መክሰስ፣ ወዳጅ ማረስ አይቸግርም
- ችግሩ የሚመጣው ከወደኋላ ነው

ሹም ሲቆጣ ማር ይዞ እደጁ፣ ደስ ሲለው ማር ይዞ ከደጁ
- ባለሥልጣን ገጸ በረከትን ይወዳል

ሹም ሳይለፈልፍ፣ ይደፈድፍ
- ሥልጣን ስላለው የፈለገውን ማድረግ ይችላል

ሹም ቢሞት ቀባሪው ሃምሳ፣ የሹም ልጅ ሲሞት መቶ ሃምሳ
- ሹሙ ሲሞት ማን ያየኛል ልጁ ሲሞት ግን ከሹሙ አንዳች ነገር መጠበቅ

ሹም ነገር ሲፈልግ፣ የዶሮ ሻኛ አምጡልኝ ይላል
- አለቃ ሊጎዳ ሲያስብ የሌለ ምክኒያት ይፈጥራል

ሹምና ማር፣ እያደር ይከብዳል
- በሕዝብ ላይ እየተማነ ይመጣል

ሹምና የጋማ ከብት፣ በጊዜ ይከተት
- ጠላት ስለሚኖረው እራሱን መጠበቅ አለበት

ሹምና ጥጥ እያደር ይከብዳል
- ቀስ በቀስ አገዛዙ እየከበደ ይመጣል

ሹሩባ ልትሠራ ሔዳ፣ ጠጉሯን ተላጭታ ተመለሰች
- አትርፍ ባይ አጉዳይ

ሹክሹክታ የጠብ ወለምታ
- አንድ ቀን ማገርሸቱ አይቀርም

ሹም ያዛል፣ ቄስ ያናዝዛል
- ሙሉ ሥልጣን አላቸው

ሺህ በመከረ፣ አንድ በወረወረ
- ያለውን ከወረወረ ቢስ አይባልም



ሺህ ቢታለብ፣ ያው በገሌ አለች ድመት
- ሞልቶ ቢትረፈረፍ ከተለመደው ውጭ አይሰጠኝም

ሺህ አውል ከሚሞት፣ ሺህ ይሙት
- አውራ ሰው ለአገር ይበጃል

ሺህ ዝንብ፣ መስብ አይከፍትም
- አቅመ ቢስ ቢሰበሰብ መፍትሔ አያገኙም

ሺህ ያጭሽ፣ አንድ ያግባሽ
- ሁሉ ቢመኝሽ የሚያገባሽ ግን አንድ ነው

ሻማ እራሱ ነዶ፣ እራሱ ብርሃን ይሰጣል
- እራሱን እየጎዳ ሌላውን ይጠቅማል

ሽል ከሆነ ይገፋል፣ ቂጣ ከሆነ ይጠፋል
- ውሎ አድሮ ምንነቱ መለየቱ አይቀርም

ሽመልና ዘንግ፣ ቂልና በግ
- ይመሳሰላሉ፣ ብዙ አይለያዩም

ሽማግሌ ሳለ ምክር አይጠፋም፣ ጎልማሳ ሳለ ላም አይነዳም
- ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ከምግብ መለየት

ሽማግሌ በምክሩ አርበኛ በሰናድሩ
- ሁሉም በየሙያውና በየችሎታው ሲገኝ

ሽማግሌ ካለበት ነገር አይሰረቅ ጎበዝ ካለበት በትር አይነጠቅ
- ሁሉም እንደየችሎታውና እንደየዕውቀቱ ሲገኝ

ሽማግሌ ካለበት፣ ነገር አይናቅበት
- ሽማግሌ ሁሉን አስተካክሎ ያስማማል

ሽማግሌ ካልሞተ፣ ሥንዴ ካልሸተ
- ሥንዴ ካላሸተና ካልበሰለ እንደማይታጨድ ሁሉ ሽማግሌ ካልሞተ ነገር አይበላሽም

ሽማግሌና ለልቻ፣ ሳይሞሉ አይቆሙም
- ደጋፊ ያስፈልጋቸዋል

ሽማግሌና ጅብ፣ በበላበት ይገባል
- ጅብ በበላበት ሰባት ጊዜ ይመላለሳል

ሽማግሌን ከምክር፣ ከመለየት ከምግብ መለየት
- ሽማግሌ ዋናው ሥራ ምክር፣ ሐሳብ፣ ልምድ ማካፈል ስለሆነ ነው

ሽማግሌ ይገላግል፣ የተጠቃ አቤት ይላል
- የተጠቃ አቤት ባለ ጊዜ ሽማግሌ ይዳኛል ያስታርቃል

ሽሽት፣ ከአሉታ በፊት
- ቃሙ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

ሽበት እኖር ብሎ፣ መጥቻለሁ አለ
- ወቅቱን ጠብቆ ማንኛውም ነገር መከሰቱ አይቀርም

ሽታና ግማት፣ ሳልሰማ ማውራት
- ብዙም ጠቀሜታ የለውም

ሽንብራ፣ መኖር በመከራ
- የሽንብራ እርሻ ሥራ አሰቸጋሪ ነው

ሽንኩርት አንድም በሉት ገማ፣ ደገሙትም ገማ
- መስማቱ አይቀርም ማንኛውም የታማ ነገር

ሽንኩርት የባሕሪውን፣ ይሸታል
- ልማደኛ የልምዱን አይተውም

ሽያጭ፣ ገኘርን ይገምታል
- ማንነትህን ከሁኔታህ ማወቅ ይቻላል

ሾላ፣ በድፍን
- ጉዳዩ በምስጢር ይያዝ

ሾተልህን ወደ አራዊት፣ ቁጣህን ወደ ትዕግሥት
- ሾተልህን ወደስገባህ፣ ቁጣህን ወደ ትዕግሥት

ሾተልህን ወደ አፎት፣ ቁጣህን ወደ ትዕግሥት
- ሾተልህን ወደስገባህ፣ ቁጣህን ወደትዕግሥት

## <u>ቀ</u>

ቀለም ሲበጠበጥ፣ ብዕር ቅረጹልኝ
- ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ

ቀለብ የሌለው ውሻ፣ ጣዲቅ አምጡልኝ ይላል
- ራት የሌላት፣ ምሳ አማራት

ቀሊል አማት፣ ሢሶ በትር አላት
- ክብሩን የማይጠብቅ ሰው ይዋረዳል

ቀላጅ፣ የሰይጣን ወዳጅ
- ቀልደ ሁልጊዜ ስብ ያስከትላል

ቀልድና ቅዘን፣ ቤት ያበላሻል
- በጊዜ መጫወት አይጥባም

ቀሙን ላይቀር፣ ከነጫማቸው
- ተወስዶብን ማለታቸው ስለማይቀር ሁሉንም መውሰድ

ቀማኛና ሽፍታ፣ ጭለማና ማታ
- ይስማማሉ

ቀርቅሬ ወርጄ፣ ማር ስልስ፣ ማር ልከፍል
- በትንሽ ዕዳ ብዙ ልከፍል

ቀስ፣ በመቀስ
- ቀስ ብለህ ሥራ

ቀስ በቀስ፣ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል
- ማንኛውም ሰው የሚሻሻለው ቀስ በቀስ ነው

ቀስ፣ እንዳይደፈርስ
- ቀስ ብለህ ሥራ



ቀስ፣ እንዳይፈስ፣
- ቀስ ብለህ ሥራ

ቀበሮ ናት የገጠሬ፣ ሚዳቋ ናት የለፈሬ
- ከሁኔታዎች ጋር ራስን ለማመሳሰል ሞክር

ቀበሮ የበሬ ቆለጥ፣ ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች
- የማይሆን የማይቻል ነገር ላይ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ነው

ቀበቶ ለማፈኛ፣ ሰንሰለት ለማቆራኛ
- ማያያገርያ አስፈላጊ ነው

ቀበኛ ማስረያውን በልቶ ያሳጥረዋል
- ራሱ በራሱ ላይ ችግር ፈጠረ

ቀበኛ ከብት፣ ዋጋውን ያደርስ
- ጥፋቱ ከፍተኛ ይሆናል

ቀባሪ፣ በፈጣሪ
- ፈጣሪ ዓምላክ እያለ አልጨነቅም

ቀብረው ሲመለሱ፣ እግዜር ይማርዎ
- ጀብ ከሄደ ውሻ ጮኸ

ቀብሮ የሚመለስ፣ የሚመለስ አይመስለውም
- ነዋሪ የሚሞት አይመስለውም

ቀኑ የጨለመበት፣ መንገዱ ዘንግ ነው
- በጣም የተቸገረ ሰው መሔጃው ሁሉ ይጠብበታል

ቀና ሲታጣ፣ ይመለመላል ኅባጣ
- ደህና ሰው በሌለበት ቦታ ባለጌ ይሾማል

ቀናውን ብነግራት፣ ውልግድግዱን አለችኝ
- መልካሙን ብነግራት መጥፎውን መንገድ አሳየችኝ

ቀን ሰው መስሎ፣ ማታ ጅራት አብቅሎ
- ጠባዩ ተለዋዋጭ ነው

ቀን ሲደርስ፣ አምባ ይፈርስ
- ሁሉም ያለጊዜው አይፈጸምም

ቀን ሲጥለው፣ ሁሉ ይጠላው
- ጊዜ ብዙ ነገር ያስከትላል

ቀንበር ታንቆ፣ ጣውንት ታርቆ፣ ምን ይሆናል
- ከሚጠሉት ከማይፈልጉት ጋር እንዴት ይኖራል

ቀን በበቅሎ፣ ማታ ቆሎ
- ከፍ ብሎ ኖሮ በደረጃ ዝቅ ማለት

ቀን ቢረዝም፣ ልብ ያደክም
- ተስፋ የጣሉበት ቀን ፈጥኖ አይደርስም

ቀን ቢቆጥሩ፣ ውሻ ቢጠሩ፣ ደረሰ በእግሩ
- አይሆንም አይመጣም የተባለ ነገር ጊዜውን ጠብቆ ይደርሳል

ቀን ባጅብ፣ ሌት በዘብ
- ከፍ ያለ ማዕረግ ያለው ሰው

ቀንና ጨርቅ፣ እንደምንም ያልቅ
- ጊዜና ጨርቅ ሳይታወቅ ያልቃል፣ ያልፋል

ቀንና ጨርቅ፣ ያልቃል፣ ብልህ ያውቃል
- ብልህ ሰው ችግርን ታግሶ ያሳልፋል

ቀን አይጥለው፣ የቀለም ሠረገላ፣ አያለናክለው
- ራሱን የሚጠብቅ ጠንቃቃና ሀዋቂ ስው ነው

ቀን አይጥለው፣ ጠጅ አያስክረው የለም
- ሰው ሆኖ የማይቸገር የለም

ቀን እስኪወጣ፣ ያባቴ ገበሬ ያግባኝ
- እስኪያልፍ ያለፋል

ቀን እንደ ተራዳ፣ ሌት እንደ ግድግዳ
- ለመከራ የጣፈው፣ ቢነግድ አያተርፈው

ቀን ከሕዝብ፣ ሌት ከጅብ
- ቀን ከዳኛ፣ ሌት ከቀማኛ

ቀን ከጣለው፣ ሁሉ ይጥለው
- ቀን የጣለውን ለውም ይጠለዋል

ቀን ካልለቀመ፣ ሌት አይቀመ
- ሥራ በጊዜው ካልተሠራ ዋጋ የለውም

ቀን የለጠው ቅል፣ ድንጋይ ይሰብራል
- ጊዜ የሰጠው ሰው ከማንም በላይ ነኝ ይላል

ቀን የጎደለበት፣ ጠገራ አይጥ ይበላዋል
- ጊዜ የጣለው ሰው በቀላሉ ይጠቃል

ቀን ያልፋል፣ እስከዚያው ግን ያለፋል
- ለጊዜው ያስቃይሃል እንጂ ማለፉ አይቀርም

ቀን ይነዳ፣ እንደፍሪዳ
- ቀን የጣለው ማንም ወደፈለገው ይነዳዋል

ቀንዱ ስማይ ጠቀሰ፣ ጭራው ምድር አበሰ
- ጠረንገሎ ነው

ቀንድ ካላት ላም፣ ጎዳ ትከፋለች
- ድሃ ለድሃ ይጨካከናል

ቀንድ ገብቶ፣ ጅራት አይቀርም
- አንዱ ከገባ ሌላው መከተሉ የማይቀር ነው

ቀኝም ስረሩ፣ ግራም ስረሩ፣ መገናኛው ኮሩ
- በዚህም በዚያም ቢሉ መድረሻው አንድ ነው

ቀይ መላሱ፣ ጥቁር እራሱ
- ለሰው ሞት አነሰው

ቀይና ወርቅ፣ ሲብለጨለጭ ያልቅ
- ተወዳጅ ሰው ሳይለለች ይሞታል

ቀይ እንደበርበሬ፣ ጥሩ እንደብርሌ
- ዛላው፣ ወዘናው ያማረ



ቀድሞ፣ ሰኞ አለመሆን ነው
- ያለመቀደም ጥሩ ነው

ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ
- ቀድሞ ነበር መጠንቀቅ አሁን ማዘን አያስፈልግም

ቀድሞ ያሸተውን ወፍ ይበላዋል፣ ቀድሞ የተናገረውን ሰው ይጠላዋል
- ቀደም ቀደም ማለት ጥሩ አይደለም

ቀጶ ያለበሰ፣ ቆርሶ ያጎረሰ
- ጥሩ ወዳጅ ነው፣ የሚረሳም አይደለም

ቀጥኝ ቢያዩኝ፣ ጅማት ለመኑኝ
- መክሳቴን አይተው ናቁኝ

ቁልቢጥ የላት፣ ቁና አማራት
- እራት የላት ቁርስ አማራት

ቁመህ ተከራከር፣ ዙረህ ተመሳከር
- የነገር ውሉ ማስረጃ ሲገኝለት ነው

ቁም ነገረኛ መምሰል፣ የተለመደ ዓመል
- ስው መሳይ በሸንጎ

ቁም እንዳላማ፣ ጥብ እንደጫማ
- በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ራስህን አጠናክረህ ተገኝ

ቁራ ሲነጣ፣ አህያ ቀንድ ያውጣ
- የማይቻል ነገር

ቁራ፣ ስሙን ይጠራ
- አንዳንዱ የራሱን ነውር ይገልጣል

ቁርበት ምን ያንቋቋሃል ቢሉት፣ ባያድለኝ ነው እንጂ፣ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ
- በወገንና ባለፉት ሁኔታዎች መመካት

ቁርባን፣ ውጭ ክርስትና
- ክፉና በጎን በየተራ

ቁርጥ ያጠግባል፣ ተስፋ ያቃልላል
- የለም ያሉት ለማኝ የሰጡት ያህል ነው

ቁና ለመስፈሪያ፣ ብርብራ ለማስከሪያ
- መግሪያ ለተገቢው ነገር መጠቀሚያ ነው

ቁንጥጫ፣ ይሻላል ከግልምጫ
- ከክፉ ንግግር ዱላ ይሻላል

ቁንጫ መሔድ ሳትማር፣ መዝለል ተምራለች
- የኋላው ወደፊት

ቁንጫ ሞኝ ናት፣ ቀን ትበራለች፣ ተለቃቅማ ታልቃለች
- ራስን ለአደጋ መስጠት አይገባም

ቁንጫ በበላ፣ ዳውላውን በዱላ
- ያጠፋው እያለ ያላጠፋውን መምታት

ቁጡና ብበጩ፣ እልማችሁ ፍጩ
- መቆጣትና መበሳጨት አይገባም

ቁጥቋጦ ሲያድግ ዛፍ ይሆናል
- ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ከትንሽ ነገር በመነሳት ነው

ቁጥቋጦ፣ ያለ ዛፍ አይሆንም
- ለትንሹ ሞገስ የሚሆነው ትልቁ ነው

ቁጭትና መረቅ፣ ለጊዜው ይጣፍጥ
- ንዶት ለችግር ይዳርጋል

ቁጭትና መጠጥ፣ ለጊዜው ይጣፍጥ
- ንዴት ለችግር ይዳርጋል

ቁፍ ቁፍ ያለኝሽ እንደ ቄብ ዶሮ፣ ለመከራ ላሳርሽ
- ለትንከወከዊ መከራ እንዳይደርስብሽ

ቂል ሲረግሙት፣ የመረቁት ይመስለዋል
- ክፉውንና በጎውን መለየት ያስቸግረዋል

ቂልን፣ ለብቻው ስደበው፣ እራሱን በአደባባይ እንዲለድብ
- ሞኝና ቆቅ በራሱ ይናገራል

ቂልን አንድ ጊዜ ስደበው ሲሰደብ ይኖራል
- የራሱን ጉድ ያበጀ እየመሰለው ለሁሉም በለሚያወራ

ቂል አይሙት፣ እንዲያጫውት
- ያዝናናል ያጫውታል

ቂል ከጠገበበት አይወጣም
- ነገን አያስብም

ቂል ያገኘው ፈሊጥ፣ ውሻ የደፋው ሊጥ
- ቂል ያማረለት እየመሰለው ያገኛትን ነገር ሲደጋግም ይኖራል

ቂምህን እትርሣ፣ የወደቀ እንሣ
- የወደቀ አንሱ የሞተን አትርሱ

ቂም ይዞ ጸሎት፣ ሳል ይዞ ስርቆት
- ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ሥራ
- ከጸሎት በፊት የልብ ንጽህና ያስፈልጋል

ቂም ያዞ ጸሎት፣ ጭድ እዝሎ ወዘት
- ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ሥራ
- ከጸሎት በፊት የልብ ንጽህና ያስፈልጋል

ቂጡ የቆሰለ ውሻ፣ እንደልቡ አይጮህም
- ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም

ቂጥ ቢወድል፣ ፈስ እያድን
- መወፈር ጥቅም የለውም

ቂጥ ቢያብጥ፣ ልብ አያሆንም
- ውፍረት ወኔ አያሆንም

ቂጥኛም ከውርዴ፣ ይማከራል
- በባህርይ የሚመሳሰሉ ይፈላለጋሉ



ቂጥኛም ከውርዴ፣ ይውላል
- በባህርይ የሚመሳሰሉ አብረው ይኖራሉ

ቂጥ ገልቦ ተከናንቦ
- ራበ ተከናንቦ፣ ሙርጥ ገልቦ
- ወገኛ

ቃልህ ሳይዘጋ፣ እግርህ ሳይዘረጋ
- ሳታርፍ /ሳትሞት/
- ክንድህን ሳትንተራስ

ቄሱም ዝም፣ መጽሐፉም ዝም
- ሁሉም ጸጥ አሉ እስተ·ያየት የሚለጥ ጠፋ

ቄስ ለትዛዜ፣ ፍቅር ለሚዜ
- ሁሉም በየሙያው ቢውል

ቄስ ምን ይሻል ጠላ፣ ነገር ምን ይሻል ችላ
- መተው ነገሬን ከተተው
- እይቶ ማለፍ

ቄስና ንብ፣ እያዩ እሳት ይገባሉ
- ለሌሎች ጥቅም መሥዋዕትነት መክፈል

ቄስ ኤረክስን መምህሩ፣ እናት አያስቀብሩ
- የእናትን ውለታና ጥቅም መረዳት

ቄለ እበር፣ እረመኔ ከማነበር
- ቄስ ከበርቆም በመጸለይ ቤተሰቡን ጸበል ያረጫል

ቄስ ካናዘዘው፣ ዕድሜ ያናዘዘው
- ሰው ከመከረው መከራ የመከረው

ቄስ ካፈረሰ፣ ዲያቆን ከረከሰ
- ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ

ቄስ ያዘዘህን አርግ፣ ቄስ ያረገውን አታርግ
- የእነሱን ባህርይ አትከተል

ቅል በአገሩ፣ ድንጋይ ይሰብራል
- ውሻ በስፈሩ አንበሳ ነው

ቅልና ድንጋይ ተማቶ፣ ሎሌና ጌታ ተሟግቶ፣ የማይሆን ነው ከቶ የማይቻል ነገር ነው

ቅልውጥ እላስቦ፣ ይጥላል ከዘመቻ
- አንድ ነገር ላይ በማተኮር ሌላውን ሳያስተውሉ አደጋ ውስጥ ይዘፍቃል

ቅመሙ የበዛበት ወጥ፣ አይፋጅ እይኮመጥጥ
- ከልክ ያለፈ ነገር አይጥምም

ቅማል በጥፍር ቢድጧት፣ ራስ ደህና አለች
- ዋናው ደህና ከሆነ ሌላ ሌላው ብዙ ጉዳት አይኖረውም

ቅማል ከእካላት፣ ምሥጢር ከቤት
- የሁሉም ነገር መነሻው ከውስጥ ከቤት ነው

ቅማል ውኃ ውረጂ ቢሏት፣ ስንኳስስ መቼ ልደርስ
- እቅምን ማወቅ ትልቅ ነገር ነው

ቅርብ ያለ ጠበል፣ ልጥ ይነከርበታል
- ነቢይ በሀገሩ አይከበርም

ቅርናታም ለቅርናታም፣ ስንቡሌ ስንቡሌ ይባባላል
- ቢጤ ከቢጤው ይውላል

ቅርንጫፍ እንደዛፉ
- ከጨዋ የተወለደ ጨዋ፣ ከባለጌ የተወለደ ባለጌ

ቅቤ ሻጭ፣ ድርቅ ያወራል
- ቅቤውን ለማስወደድ ሲል ብዙ ያወራል

ቅቤ ተነጥሮ ለመብላት፣ ያባት የእናት
- ያባትና የእናትን ሀብት ለማግኘት እንዲህ ቀላል አይደለም

ቅቤና ቅልጥም፣ ወዴት ግጥምጥም
- በፍጹም አይመሳሰሉም

ቅቤ እንጣሪቱ እያለች፣ መቅመቆ ማሽቱን ምታት መተት
- የምጣዱ እያለ፣ የእንቅቡ ተንጣጣ

ቅቤ ይፍሰስ፣ ከገንፎ አይተርፍ
- ሁሉን ባንድ ጊዜ መፍጀት

ቅናት ያደርሳል፣ ከሞት
- ቀናተኛ ከሁሉ ጠበኛ

ቅናት ጥናት፣ አይገናኝም ከእናት ካባት
- የሚቀና ሰው ከቤተሰቡ ጋርም አይኪኪንም

ቅና ያለው በእናቱ ብልት ይቀናል
- በከንቱ ተጨንቅ ተጠበብ ያለው

ቅን በቅን ከማገልገል፣ ፊት ለፊት ማውደልደል
- ከሠራተኛው ይልቅ እውደልዳዮች ይጠቀማሉ

ቅንቡርስ የት ትሔዳለህ? መተማ፣ ትደርሳለህ ልብማ
- የእንካማ ልቡ ኢየሩሳሌም ነው

ቅንነት፣ ለነፍስ መድኃኒት
- እግዚአብሔር የሚወደው ነገር ነው

ቅዝምዝም ሲወረወር፣ ጎንበስ ብለህ እሳልፈው
- የሚመጣብህን ነገር በትዕግስት እና በብልሃት እሳልፈው

ቅዝምዝም ወዲያ ፍየል ወዲያ
- የማይገናኝ ሐሳብ

ቅገርት ተፈርቶ፣ ሳይተኛ አይታደርም
- እሳስታለሁ ብለህ ሥራህን አትተወውም

ቅጡም የምንከስና ነው
- የሚሆን ይመስላል ግን አይሳካም

ቆላና ደጋ፣ እመቤትና እልጋ
- ቆላና ደጋ እንደሚራራቁት እመቤትና እልጋ አይራራቁም



ቆሎ ለዘር፣ እንዶድ ለድግር
- ለተባለው ዓላማ ሊውል የማይችል የማይሆን

ቆሎን ቢቆረጥሙት እንጂ፣ ቢያሹት አያልቅ
- ማንኛውም ሥራ በስልት ሲሠራ ይቀላል

ቆማጣ ቤት፣ አንድ ጣት ብርቅ ነው
- ድሃ ቤት ጎመን የተቀቀለ እለት ጭፈራ ነው

ቆማጣ ብለው ያው ቁምጥና ነው፣ ሌላ ምን ይመጣል አለ
- አካፋን አካፋ እንጂ ሌላ ምን ይሉታል

ቆማጣን ቆማጣ ካሉት ገብቶ ይፈተፍታል
- ባለጌን ባለጌ ካሉት ያስቸግራል

ቆሩ መቀበሪያው ያው ፈሩ
- ሩቅ አይሔድም፣ እዚያው እቅርቡ ይገኛል

ቆሩ በማን ምድር ትለፋ
- መሔጃ፣ መድረሻ የለህም

ቆርሶ ያላጎረሱትን፣ ቀዶ ያላለበሱትን፣ ብላቴና፣ ማዘዝ አይገባም
- ምንም እስተዋጽዖ ባላደረጉበት የባለቤትነት ስሜት ሲኖር አይገባም

ቆቅ ወዲህ፣ ቅዝምዝም ወዲያ
- ግንኙነት የሌለው ጉዳይ ተፈጸመ

ቆቅና ባላገር በራሱ ያወራል
- የራሱን ገመና ራሱ ይገልጠዋል

ቆንጆና እሸት አይታለፍም
- ሁሉም የሚሻው የሚፈልገው ነገር

ቆዳ ሲወደድ፣ በሬህን እረድ
- ለማንኛውም ወቅቱን ማወቅ ተገቢ ነው

ቆጥሮ የማይሰጥ ሌባ፣ ቆጥሮ የማይቀበል ሌባ
- መተማመን ሊመጣ የሚችለው ግልጽነት ሲኖር ነው

ቋንጧና ባለሟል ሳያር አይቀርም
- እስው ቤት እየሠራ የሚያበሳጭ ነገር የማይገጥመው የለም

## መልመጃ 4 / ሽ,ቀ /

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገር አሟላ

1. ቀይ እንደበርበሬ፣ ጥጥ እንደ ________
ሀ. ብርሌ ለ. እሞሌ ሐ. አገሬ መ. ጥራጥሬ

2. ሽመልና ዘንግ ______ በግ
ሀ. ሎሌና ለ. ብልጥና ሐ. ቂልና በግ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

3. ሹምና ጥጥ ______
ሀ. እያደር ይከብዳል ሐ. እያደር ያነብዛል
ለ. እያደር ያስንፋል መ. መልሱ የለም

4. ቀሳጅ ______ ወዳጅ
ሀ. የመልአክ ለ. የሰይጣን ሐ. የጥሩ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

5. ሹክሹክታ ______ ወለምታ
ሀ. የአፍ ሐ. የጠብ
ለ. የእግር መ. ሁሉም መልስ ነው

6. ሽሽት ________ በፊት
ሀ. ከመጠቃት ለ. ላይሆን ሐ. ሳይደርስ መ. ከኡኡታ

7. ሽኒና ________ ቤት አይገባም
ሀ. ጓደኛ ለ. ጥላ ሐ. ከንቱ መ. ሴት

8. ቀስ ________
ሀ. ላይቀደስ ሐ. እንዳይፈስ
ለ. ሳይደፈርስ መ. ሁሉም መልስ ነው

9. ቀን ባጅብ ________ በፃብ
ሀ. ነጎ ለ. አቻምና ሐ. ዘንድሮ መ. ሴት

10. ቀን በበቅሎ ________
ሀ. ማታ ቆሎ ሐ. ማታ አሽሽገዳሜ
ለ. ማታ ጮማ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

11. ሹም ያፀል ________ ያናዝዛል
ሀ. ዳኛ ለ. ፓሊስ ሐ. ቄስ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

12. ሽማግሌ በምክሩ ________
ሀ. ዳኛ በተግሳጽ ሐ. ጦረኛ በጦሩ
ለ. አርበኛ በስናድሩ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ



13. ቀሙን ሳይቀር ________
ሀ. ከንቁራቁንቦው ሐ. ከንጫማቸው
ለ. እስከመጨረሻው መ. ከነ ካልሲያቸው

14. ቀን ካልለቀሙ ________
ሀ. ሌት አይቀሙ ሐ. ከሰው አያገኙ
ለ. ሌት አያገኙ መ. መልስ የለውም

15. ቀን እንደተራዳ፣ ሌት ________
ሀ. እንደመሬት ሐ. እንደግርግዳ
ለ. እንደ ምንጣፍ መ. ሁሉም መልስ ነው

16. ቂጥ ቢወድል ________ አያድን
ሀ. ከሞት ሐ. ከቅዘን
ለ. ከፈስ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

17. ሽማኔ በድሩ ________ በመንደሩ
ሀ. ውሻ ለ. ድመት ሐ. ጠይብ መ. እሀያ

18. ቄስ ለኑዛዜ ________
ሀ. ፍቅር ካገር ልጅ ሐ. ፍቅር ለሚዜ
ለ. ሥጋ ያለ አዋዜ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

19. ቂጥ ቢያብጥ ________ አይሆንም
ሀ. ለቀለብ ለ. ውበት ሐ. ልብ መ. መልሱ የለም

20. ቅማል ከአካላት ________ ከቤት
ሀ. ምስጢር ሐ. ምክር
ለ. ምግብ መ. ሁሉም መልስ ነው፥

21. ሺህ በመከረ ________
ሀ. ሰው መሰከረ ሐ. ባርጩማ መከረ
ለ. ዘመድ አበደረ መ. አንድ በወረወረ

22. ሽማግሌ ካልሞተ ________
ሀ. ሥርቶው አይበሉ ሐ. መንደር ሰላም አይሆን
ለ. ሥንዶ ካልሸተ መ. መልሱ የለም

23. ________ እግርህ ሳይዘረጋ
ሀ. ሐሳብህ ሳይዘነጋ ሐ. ክንድህ ሳይፍታታ
ለ. እጅህ ሳይናጋ መ. ቃልህ ሳይዘጋ

24. ቂጥ ገልቦ ________
ሀ. ሩጫ ለ. ተከናንቦ ሐ. ጨዋታ መ. መኝታ

25. ቁንጫ መሔድ ሳትማር ________
ሀ. ቀረች ሐ. መዝለል ተማረች
ለ. ሞተች መ. ማጥቃት ተማረች

26. ቅቤ ሻጭ ________
ሀ. ችግር ያወራል ሐ. ይከስራል
ለ. ያልፍለታል መ. መልሱ የለም

27. ሹም ሳይለፈልፍ ________
ሀ. ይደፈድፍ ለ. ይሠራ ሐ. አይውልም መ. አይሠራም

28. ሽል ከሆነ ይገፋል ________
ሀ. ዱባ ከሆነ ይጠፋል ሐ. ቂጣ ከሆነ ይጠፋል
ለ. ዘመድ ከሆነ ይከፋል መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናል

29. ቋንጣና ባለሟል ________
ሀ. ሳያር አይቀርም ሐ. ይደነቁራል
ለ. ይደርቃል መ. መልሱ የለም

30. ሹመት ________
ሀ. ቡብልጠት ሐ. ሺህ ሞት
ለ. በመንግሥት መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናል

31. ቆንጆና እሸት ________
ሀ. ሳያልፍበት ሐ. ቶሎ ይቀጠፍ
ለ. ሲያስደስት መ. አይታለፍም

32. ቆዳ ሲወደድ ________
ሀ. በሬህን እረድ ሐ. ሽጥ
ለ. ቆዳ ግዛ መ. ጅብ ያመልጥ

33. ሽንኩርት አንድም በሉት ገማ ________
ሀ. ለሆድ እይስማማ ሐ. ከወዳጅ አጣላ
ለ. ሰው እንዳይሰማ መ. ደገሙትም ገማ

34. ሻማ እራሱ ነዶ ________
ሀ. እራሱ ያልቃል ሐ. እራሱ ብረሃን ይሰጣል
ለ. ይቀልጣል መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናል

35. ሽበት እናር ብዬ ________
ሀ. መና መሆኔ ሐ. ሀረጀሁ
ለ. እናት ላይ ወጣሁ መ. መጥቻለሁ አለ



36. ቆቅና ________ በራሱ ያወራል
ሀ. ብልጥ ሐ. ከተሜ
ለ. ሞኝ መ. ባላገር

37. ቅልውጥ አሳሰበት ________ ዘመቻ
ሀ. ይሔዳል ሐ. ይደፍራል
ለ. ይቀራል መ. ይጥላል

38. ቄስ እበር ________ ከማኅበር
ሀ. ባለጌ ሐ. አረመኔ
ለ ጨዋ መ. ዘመድ

39. ቅማል በጥፍር ቢድጧት ________
ሀ. ተገላገለች ሐ. ምስጢር ከቤት
ለ. ለው ታበላሽ መ. ምስጢር ከጎረቤት

40. ቅርብ ያለ ጠበል ________ ይነከርበታል
ሀ. ገመድ ሐ. ቃጫ
ለ. ልጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

## መልመጃ 4 ሸ,ቀ

ለ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገር ፍቺ ፈልግ</u>

1. ሹሩባ ልትሠራ ሔዳ፣ ተነጭታ መጣች
ሀ. ሲያጌጡ ይመላለጡ ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
ለ. አተርፍ ባይ አጉዳይ መ. መልሱ የለም

2. ሸማ በየፈርጁ፣ ይለበሳል
ሀ. ሁሉንም እንደጠባዩ ማስተናገድ
ለ. ሁሉም እንደ አቂሚቷ ይለብሳል
ሐ. ሸማ በየቦታው ይለበሳል
መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

3. ቂል ሲረግሙት፣ የመረቁት ይመስለዋል
ሀ. ሞኝ ሲያከብሩት የፈሩት ይመስለዋል
ለ. ከፋውንና ደጉን መለየት ያስቸግረዋል
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

4. ቂም ይዞ ጸሎት፣ ሳል ይዞ ስርቆት
ሀ. ከጸሎት በፊት የልብ ንጽህና ያስፈልጋል
ለ. ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ሥራ
ሐ. ለስርቆት ያመቻል
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

5. ቃልህ ሳይዘጋ እግርህ ሳይዘረጋ
   ሀ. ሳትደክም　　ሐ. ሳትሞት
   ለ. ሳታረጅ　　መ. ሳትሰለች

6. ቆማጣን ቆማጣ ካሳሉት ገብቶ ይፈተፍታል
   ሀ. ቆማጣ ደፋር ነው
   ለ. ቆማጣ ከጨበጠህ ቆማጣ ትሆናለህ
   ሐ. ባሰጌ ሰው ብልግናው ካልተነገረው አጉል ነገር ይሠራል
   መ. ባለጌ በብልግናው ይሰደባል

7. ቄሱም ዝም መጽሐፉም ዝም
   ሀ. ሁሉም ክፉ ሆነ　　ሐ. አስተያየት የሚሰጥ ጠፋ
   ለ. ሁሉም ዝምታ አበዙ　　መ. ሐ እና ለ መልስ ይሆናሉ

8. ቀጥኜ ቢያዩኝ፣ ጅማት ለመኑኝ
   ሀ. አሾፉብኝ　　ሐ. አከበሩኝ
   ለ. ናቁኝ　　መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

9. ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ
   ሀ. ሥራን መሥራት ከሰው ተማክሮ ነው
   ለ. ደህና ሰው በሌለበት ቦታ ባለጌ ይሾማል
   ሐ. ቀና ከአገር ከጠፋ አገር ይጠፋል
   መ. መልሱ የለም

10. ሾላ በድፍን
   ሀ. ወሬው ባደባባይ
   ለ. ምስጢሩን ከአንድ ሰው ጋር
   ሐ. ጉዳዩን በምስጢር ያዝ
   መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



## <u>መልመጃ 4 ሸ,ቀ</u>

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1. ቂጡ የቆሰለ ውሻ እንደልቡ አይጮህም | ሀ. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ |
| 2. ሹመት ሲገኝ ዘመድ አይገኝ | ለ. የወደቀ እንቡ የሞተን አትርቡ |
| 3. ሽሽት ከእሉታ በፊት | ሐ. ውሻ በስፈሩ አንበሳ ነው |
| 4. ቀለብ የሌለው ውሻ፣ ጣዲቅ አምጡልኝ ይላል | መ. አልጋው ሲገኝ ባሉ አይገኝ |
| 5. ቅል በአገሩ ድንጋይ ይሰብራል | ሠ. ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም |
| 6. ሾተልህን ወደ አራዊት፣ ቁጣህን ወደ ትዕግሥት | ረ. ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ |
| 7. ቂምህን አትርሳ፣ የወደቀ እንሳ | ሰ. ቀን ከዳኛ ማታ ከቀማኛ |
| 8. ቀን ከሕዝብ ሌት ከጅብ | ሸ. ራት የሌላት ምሳ አማራት |
| 9. ሽማግሌና ጅብ በበላበት ይገባል | ቀ. ሾተልህን ወደ ሰገባህ ቁጣህን ወደትዕግሥት |
| 10. ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ | በ. ጅብ በበላበት ሰባት ጊዜ ይመላለሳል |
| 11. ቀለም ሲበጠበጥ፣ ብዕር ቅረጹልኝ | ተ. ጦር ሲመጣ፣ ዛቢያ ቆረጣ |
| 12. ሹመት ለሹም ያወርሳል፣ ጉም ተራራ ያለብሳል | ቸ. አተርፍ ባይ አጉዳይ |
| 13. ሹርባ ልትሠራ ሔዳ ጠጉሯን ተነጭታ ተመለሰች | ኀ. ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ፣ ድሃ ለድሃ ይለቃቀቡ |
| 14. ቀን ከጣለው ሁሉ ይጥለው | ነ. እስኪያልፍ ያለፋል |
| 15. ቀይ መላሱ፣ ጥቁር አራሱ | ኘ. ለተሾመ ይመስክሩለት ለተሻረ ይመሰክሩበት |
| 16. ቀን አበኪወጣ፣ የእባቴ ገበሬ ይግዛኝ | አ. አራት የላት፣ ቁርስ አማራት |
| 17. ቁም ነገኛ መምሰል፣ የተለመደ ዓመል | ከ. ለበው ሞት እነሰው |
| 18. ቁልቢጥ የላት ቁና አማራት | ኸ. ምኝና ቆቅ በራሱ ይናገራል |
| 19. ቂልን ለብቻው ሰደበው፣ እራሱን በአደባባይ እንዲሳደብ | ወ. ራበ ተከናንቦ፣ ሙርጥ ገልቦ |
| 20. ቂጥ ገልቦ ተከናንቦ | ዘ. ሰው መሳይ በሸንጎ |
| 21. ቁስ ካፈረስ ዲያቆን ከረከሰ | ዠ. ሰው ከመከረው መክራ የመከረው |
| 22. ቅርናታም ለቅርናታም፣ ሰንቡሌ ሰንቡሌ ይባባላል | የ. ቢጤ ከቢጤው ይውላል |
| 23. ቂስ ካናዘዘው፣ ዕድሜ ያናዘዘው | ደ. ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ |
| 24. ቅቤ አንጣሪ፣ እያለች፣ መቅመቆ ማሽተን ምታት መታት | ጀ. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ |
| 25. ቅንቡርስ የት ትሔዳለህ? መተማ፣ ትደርሳለህ ልብማ | ገ. የእንክሣ ልቡ እየፋሳሌም ነው |

## በ

በሁለት በትር አይማቱ፣ በሁለት ዳኛ አይሟገቱ
- ሁሉም ነገር ሥርዓት አለው

በለምለም (በለሰለሰ) ምላሴ፣ ኮሸሽላ በላሁ አለች አህያ
- በዘዴ የምፈልገውን አደረኩ

በሉት እለቀ ፈጩት ደቀቀ
- ባዶ ቀረ አለቀ

በላይ በላዩ ያጎርሳታል፣ የበላችው ያስገሳታል
- በላይ በላዩ የሆነ ነገር ጥቅም የለውም

በል በል ይላሉ፣ ሲፈርዱ፣ ጣል ጣል ይላሉ፣ ሲያርዱ
- ያዋከቡት ነገር

በልብ አምኖ፣ በአፍ መንኖ
- በልብ የታሰበውና በአፍ የሚነገረው ሲለያይ

በልተው ከጨረሱ፣ ከመኝታ ይነሱ
- ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ

በልተው ካልጠበ እረር፣ ወልደው ካላኩ አነር
- በሥርዓት ያላሳደጉት ልጅ ችግር ይፈጥራል

በልቶ መጠጥ ያጣ፣ ተበድሎ ፍርድ አጣ
- የፍትሕ መታጣት

በልቶ እንዳንበሳ፣ ተኝቶ እንደሬሳ
- ሐሳብ የሌለው፣ የተሟላለት

በልቶ የማይመርቅ፣ ገብቶ ወጥቶ የማይጠይቅ
- ለተደረገለት ውለታ የማይውል ጥሩ አይደለም

በልቶ የማይበርደው፣ የሰው ነገር የማይከብደው፣ አንድ ነው
- ምንም ቢሆን ሰው ይሉኝታ አለው

በልቶ የከሳ፣ የነገሩትን የረሳ
- ዝንጉ ሰው አይረባም

በልቼ እንደአንበሳ፣ ተኝቼ እንደሬሳ
- ሁሉ ነገር የተሟላልኝ

በል ያለው የበላው፣ ተው ያለው የአተተው
- ሁሉም እንደየራሉ ሁኔታ የሚፈጸም

በልጅ ቆዳ፣ የተቀበረ የለም
- መጨነቅ የለብኝም

በልጅነት ወደ ገዳም፣ በእርጅና ወደ ዓለም
- የተገላቢጦሽ ሥራ

በልጅነት ያልተወለደ ልጅ፣ በአባቱ ተዝካር ፈኛ ይለምናል
- እንኳን ሊጦር ይጦራል



በልጅ አመካኝቶ፣ ይበላል አንጉቶ
- በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

በሐምሌ በነሐሴ፣ ቀረችልኝ ነፍሴ
- የችግሬ ጊዜ አለፈ

በሐምሌ ወጨፎ፣ በሰኔ እርከፍክፎ
- ቀስ በቀስ ሁኔታው እየከበደ መሔድ

በሐምሌ ጤፍ ይዘሩ፣ ቤት ይሠሩ
- ቆቅ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

በመልካም፣ አንገት እንቅርት
- በጥሩ ነገር ላይ እንከን

በመረጡት ዳኛ ቢረቱ፣ በቆረጡት በትር፣ ቢመቱት በማን ያጉተመትም
- በመጀመሪያ መጠንቀቅ ነው እንጂ በራስህ ጥፋት ማዘን አይቻልም

በመሰለው ይናገራል፣ ከበላው ይበላል
- እንደልቡ ነው የሚያድረው

በመስታወት ቤት የሚኖሩ አይወራወሩ
- በቀላሉ ሊበላሽ የሚችልን ነገር በእንክብካቤ መያዝ

በመስከረም የሚያብድ፣ በሰኔ ቡሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል
- ከሁኔታው ያስታውቃል

በመስከረም ጤዛ እንኳን አባቴ ጥጃ አልገዛ
- ቀርቀሬ ወርጂ ማር በልስ ማር ልከፍል

በመሸታ የተገዛ ጦር፣ ቢወረውሩት ከድፍድፍ
- አይተማመኑበትም

በመከሩት ምክር፣ በሸመቁት ጦር
- ተንኮል ሠሪውን ያጠፋዋል

በመዘንከው ሚዛን፣ በሰፈርከው ላዳን
- አንተው ባነሰኸው አንተው ተጎዳህ

በመጀመሪያ የመቀመጫዬን፣ አለች ዝንጀሮ
- መጀመሪያ እራሴን

በመጠቃቀም የቆመ ፍቅር፣ አይውል አያድር
- ጥቅም ሲቀር መፍረሱ አይቀርም

በሙቅ ውኃ የታጠበ፣ በሰው ገንዘብ የተቸረ
- አምጡ ድገሙኝ ይላል

በሚያዚያ ኀመን የዘራ፣ ክረምቱን ሁሉ በላ
- ሁሌ ቀደም ብለህ ከተዘጋጀህ አትራብም አትጠቃም

በማር ላይ ወተት፣ ሲረባም ቢሰባም
- አይገኝም እንጂ ከተገኘ መልካም

በማር አጠገብ ውኃ ጥገብ
- በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

በማታየው፣ እጅህን አታድርስው
- ራስህን ጠብቅ

በማን ላይ ተቀምጠሽ፣ እግዜርን ታሚያለሽ
- እኔ እየረዳሁህ እኔኑ ታማለህ

በማያድሩበት ቤት፣ አያመሻሹበት
- በጊዜ ተነስተው ይሂዱ

በምን በላህ በሳማ፣ ባይፈጅህማ
- ካልፈጀህ፣ ካልጎዳህ እሱማ ጥሩ ነበር

በምን ተነሳ በጣቁሳ ምን በጣቁሳ በዳጉሳ
- እርስ በርስ የሚደጋገፉ

በምንቸት ጠላ ታፈላ፣ ከጎረቤት ትጣላ
- የማይጠቅምን ተግባር አትፈጽም

በምን የተነሣ፣ ይህ ሁሉ ጠባሳ
- አንዱን አይተህ ከአንዱ ተማር

በምድር መጠቅጥቅ፣ በሰማይ መጠየቅ
- ምድር ላይ የሠራኸው ግፍ በሰማይ ያስጠይቅሃል

በምድር ዓለም፣ አለገንዘብ የለም
- ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ

በምድር እይቀር ብድር
- እንደሥራህ ብድርህ ይከፈልሃል

በምድር ድንበር፣ በሴት ከንፈር
- ዋናው መከለያና መታፈሪያ ነው

በምግባሩ እይታወቅ ማማሩ
- በሚሠራው ሥራ ውበቱ አይታወቅም

በሞጥ በጣሽ፣ በአንግዴ ልጅ አልጣሽ
- ምንጊዜም ከኔ ጋር ሁኚ

በሞኝ ክምር፣ ዝንጀሮ ልጅዋን ትዳር
- ብልጦቹ በሞኝ ንብረት ይጠቀማሉ

በሞኝ ክንድ የዘንዶ፣ ጉድጓድ ይለኩበት
- እራሱ የማይደፍረውን ነገር ሌላ ሰውን አደፋፍረው ጎል ማስገባት

በረጅም ጦር ባይወጉበት፣ ያስፈራሩበት
- ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው

በራቸውን ከፍተው፣ ሰውን ሌባ ይላሉ
- በጨለማ እየሄዱ ጅብን ነገረኛ ያደርጋሉ

በሬ ሆይ፣ ሣሩን እየህና፣ ገደሉን ሳታይ
- እበላ ብዬ ተበላሁ፣ ምነው ሳልበላ በቀረሁ

በሬ ሲያረጅ፣ ከጥጃ ጋር ይውላል
- ያለቦታው ወደኋላ መንተት

በሬ በሙቶ፣ ያውስ የት ተገኝቶ ምድር በዶሮ፣ ያውስ ማን ገብሮ
- በሌለ ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ



በሬ በጭብጦ ተገዛ ቢለው፣ ያላቦካ ከወዴት ያገኛል አለው
- ቅድሚያ ዝግጅት ያላደረገ ይቸገራል

በሬ ተንሾካሽኮ ቀንበር፣ ገበሬ ተቾካችኮ ከድንበር
- በድንበር አካባቢ ችግርና ንትርክ አይቀርም

በሬና ሴት፣ ካገርህ መሬት
- ሁሉ ነገር በአገር ያምራል

በሬና በሬ መከሩ፣ ቀንበር ሰበሩ
- ራስን ከችግር ለማውጣት የሚደረግ ጥረት

በሬ አርዶ በበለት፣ ከብት አርብቶ በበረት
- ሁሉንም በሥርዓቱ ሲይዙት ይጠቅማል

በሬ እንኳ ሰወጉ፣ በፈረስ ያጓራል
- ዘመድ ለወገኑ ይደግፋል

በሬ ከአንጀቱ እንጂ፣ በአንገቱ አያበብም
- ሰው ጠግቦ ከበላ ሥራውን በሚገባ ይሠራል

በሬ ከጎለበተ፣ አሽከር ስነበተ
- የሚጠቀምበትን መሣሪያ በአግባቡ የያዘ ይመስገናል

በሬ ካራጁ፣ ይውላል
- ሰው ሳያውቀው ከባላንጣው ይውላል

በሬ ወደአገሩ፣ ይስባል
- ለሀገርህ መቆርቆርህ አይቀርም

በሬዎች ተረት ለመዱ፣ ዝም ብለው እንዳይጠመዱ
- ወሬ ብቻ ሆነ ሥራውን ትተውት

በሬ ያርሳል፣ ምርቱን አህያ ያፍሳል
- በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ

በሬ ግዙ ግዙ፣ አንድ አሞሌ ሳይገዙ
- መካሪው ብዙ ደጋፊ ግን የለም

በርቄ አሞታለሁ ታንቄ
- ሥራ ላይ ሊውል የማይችል

በርበሬ በገዛ እጁ ገብቶ ይፋጃል
- በገዛ እጁ ነገር ፈልጎ ችግር ገጠመው

በርበሬ ታልፈጀ፣ ጠበቃ ታረጀ
- በሚፈለግበት አገልግሎት ላይ ሊውል አይችልም

በርበሬና ሚጥሚጣ፣ ሥጋና ቋንጣ
- ሁሉም ለየቅል ነው

በርበሬ አይሆን ዕጣን፣ ነገር አይሆን ሥልጣን
- ያለቦታው ያደረጉት ነገር ጠቀሜታ የለውም

በርቦ ያበድራል፣ በቁና ያስከፍላል
- ስግብግብ ነው

በርኖስ ሳይገዙ ካባ
- መነሻ ነገር ሳይዙ የተሻለ ነገር መመኘት

በርጥብ አያቃጥሉ፣ በሰማንያ አይቀጥሉ
- በማይሆን ነገር ተቀባይነት በሌለው ነገር ላይ አታተኩር

በስለ እንብላ፣ በለገ እንዝራ
- ሁሉም ነገር በወቅቱ ሲከናወን ጥሩ ነው

በሰላም ጊዜ አለሁልህ፣ ያላሉት በመከራ ጊዜ ቢጠብቁት አይገኝም
- በሰላም ጊዜ ካልሆኑት፣ በችግር ወቅት አይሆንህም

በሰላም ጊዜ ያልሞከሩት፣ በመከራ ጊዜ ልሞክርህ ቢሉት አይሆንም
- በሰላም ጊዜ ካልሆኑለት በችግር ወቅት ቢጠብቁት አይገኝም

በሰማንያ የተረታ፣ መሃል አገዳውን የተመታ
- ሕጉ የወሰነው ተወሰነ ማለት ነው

በሰማንያ ያለቀ፣ በፀሐይ የደረቀ
- በሕግ የተወሰነ ጉዳይ ተመልሶ አይነሳም

በሰማኸው ተማከር፣ በሳልከው ተመተር
- በተዋዋልከው ውል መሠረት የሚወሰንብህን ተቀበል

በሰማይ የለም ጸጸት፣ በአባት የለም ቅጣት
- ያለቦታው እንዳች ነገር መጠበቅ አይገባም

በሰም ያጣበቁት ጥርስ፣ ቢያኙኩበት አያደቅ፣ ቢስቁበት አያደምቅ
- እንከን ያለበት ነገር ግልጋሎቱ ጥሩ አይደለም

በሰበቡ፣ መምሬ ተሳቡ
- ትንሽ ቆሎ ይዘህ ወደ አሻሮ ተጠጋ

በሰባት ዓመቷ፣ ብትሠራ፣ አንገት ልብስ
- ጊዜዋን ጨርሳ ውጤቱ የማይረባ ሆነ

በሰባት ዓመታቸው እንዳይማሩ፣ ሰባት ዓመት ይደናቆሩ
- በማይሆን ጉዳይ ላይ መከራከር ትርፉ ድካም ነው፣ ውጤት የለውም

በሰኔ ካልዘሩ በጥቅምት ካልቀሙ፣ እህል አይገኝም በድንበር ቢቆሙ
- በጊዜውና በወቅቱ ካልሠሩ ውጤት የለውም

በሰኔ ዘርን ይዘሩ፣ ቤትን ይሠሩ
- በጊዜውና በወቅቱ የተሠራ ሥራ ውጤት አለው

በሰኔ የገሰገሰ፣ ላማቱ ያገለገለ
- በጊዜውና በወቅቱ የሠራ እንኳን ለራሱ ለሁሉም ይተርፋል

በሰንበት ላይ ደብረዘይት፣ በሥጋ ላይ አሞት
- ተዳራራቢ ነገሮች ተከሰቱ

በሰው፣ ላይ ቄስ
- መሥራት ሳይችሉ ሌላው ሲሠራ ማናናቅ

በሰው ልጅ ይሥቁ፣ በራስ ልጅ ግን ያፍሩ
- የራስ ልጅ ሲያጠፋ ያሳፍራል በሰው ልጅ ላይ ግን ሥቀው ያልፋሉ

በሰው ምድር፣ ልጇን ትድር
- በሰው ገንዘብ ትደግሰበት



በሰው ቁስል፣ ዕንጨት ስደድበት
- ጨካኝ ነው

በሰው ቂጣ፣ እጅዋን ትቃጣ
- በሰው ገንዘብ ለመጠቀም ሞከረች

በሰው ቡሃቃ፣ አሚጦ አይጋገርም
- ይሉኝታ መኖር አለበት

በሰው አገር ማግኘት፣ ዱር ገብቶ ዘፈን
- በሰው ሀገር ብታገኝም ደስታ የለም

በሰው አገር፣ አለመናገር
- እንደልብ መሆን አይቻልም

በሰው ፊት አይበሉ፣ በፀሐይ አይኮበልሉ
- በሚታወቅ ነገር ላይ መዋሸት አይቻልም

በሰጡበት አገር፣ ለምኖ ማደር፣ የማይመች ነገር
- ህብት ባገኙበት፣ በተከበሩበት አገር ቢከስሩ እርዳታ መጠየቅ ያሳፍራል

በሰፈሩት ላዳን፣ በመዘኑት ሚዛን
- ያው የሠራኸው በጎም ሆነ ክፉ ሥራ ይጠብቅሃል

በሰፈሩት ቁና፣ ሳይሰፈሩ አይቀሩም
- ሰውን ቢተናኮሉ ተመልሶ መጎዳቶት አይቀርም

በሰፌድ ያሰጣ፣ በእንቅብም ያሰጣ፣ እኩል ለኩል ወጣ
- ያሰውም የሌለውም የችግሩን ጊዜ እኩል አለፉት

በሴት የከበረ፣ ከእግዜር የተማከረ
- ለትዳሯ ቀና የሆነች ሴት ያጋጠመው ዕድለኛ ነው

በሴትና በውኃ፣ የማይደርስ የለም
- ሴት ለቤተሰብ መድኃኒት ነች

በሰለት የተመተረ ባለቤይሙቱ የተከተረ
- አንዴ ችክ ያለ ማንም የማይመልሰው

በስርቆት ከመክበር፣ ይሻላል ደህይቶ መኖር
- ሌባ ሆኜ ከሚያልፍልኝ ድህነቴ ይሻለኛል

በስተርጅና፣ ሙሽርና
- በዕለቱ በጊዜው ያልሆነ ነገር አያምርም

በስተርጅና፣ ድቁና
- በዕለቱ በጊዜው ያልሆነ ነገር አያምርም

በሺህ ዓመቱ፣ ርስት ለባለቤቱ
- እውነትና ንጋት እያደር ይታያል

በሽማግሌ የታረቀ፣ በፀሐይ የደረቀ፣ አለቀ ደቀቀ
- አንዴ በሽማግሌ ከታረቅህ እርቁ አይበላሽም

በሽምብራው፣ ትል አለበት
- መጠርጠር አለብህ

በሽሮ ላይ ቅቤ ተጨምሮ አማረ፣ በእሁድ ላይ በዓል ተጨምሮ ከበረ
- ያማረ፣ የተሰካ ሆነ

በሽታውን የደበቀ፣ መድኃኒት የለውም
- ችግሩን ካልተናገረ ማንም አያውቅለትም

በሽታውን የደበቀ፣ ሬሳው ይዘልቃል
- ችግሩን ካልተናገረ አስቀለት

በቀና ልቦና፣ በንጹህ ሕሊና
- ሸር ሳይኖር

በቀን ብዛት እንቁላል በእግሩ ይሄዳል
- ቀስ በቀስ ማደጉና ትልቅ ደረጃ መድረሱ አይቀሬ ነው

በቀኝ ቁሜ እንደክርስቶስ፣ በግራ ቆመህ እንደ ዲያቢሎስ
- ነገራችን ሁሉ የሚጣጣም አልሆነም

በቁርበትም ያስጣ፣ በደላጎም ያስጣ፣ እኩል ቀን ወጣ
- ያስውም የሌለውም የችግሩን ጊዜ እኩል አሰፋት

በቂል ከምር፣ ዝንጀሮ ይማታበታል
- በቂል ንብረት ብልጦቹ ይጫወቱበታል

በቃል ያስ ይረሳል፣ በጽሑፍ ያስ ይወርሳል
- በጽሑፍ ያለ ለብዙ ጊዜ ይቆያል

በቅል፣ እንገት ይገባል
- እስኪሳካልህ ድረስ ታዛዥ መስለህ ታይ

በቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰጭ፣ በራስዋ አሳጠረች
- ሌላውን እጎዳለሁ ሲሉ ጉዳት በራስ ላይ ይደርሳል

በቅሎ፣ ሳይገዙ ኮርቻ
- የተገላቢጦሽ ነገር ተፈጸመ

በቅሎ ሽንቷ አጠራ ብላ፣ ኃፍረቷን አሳየች
- ጥሩ አደርጋለሁ ብሎ መቸገር

በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት፣ እናቴ ፈረስ ነች አለ
- ያልበላውን የሚያክክ

በቅሎ እንደ ገሪው፣ ሕዝብ እንደመሪው
- ዋናውና ወሳኙ የሐገር መሪ ነው

በቅሎ እንዳስገሩት፣ ዕውር እንደመሩት
- ዋናው የሚመራውና መንገዱን የሚያሳየው ነው

በቅሎ እንዳስኃገሩ፣ ሎሌ እንዳስተዳደሩ
- ሁሉም ሰው እንዳስተዳደጉ ነው

በቅሎ ከሸጠ፣ የሸመጠጠ በለጠ
- ገንዘብ አላፊ ጠፊ ነው ችግርን ችሎ ያቆዩት ሁሉ ጠቃሚ ነው

በቅሎ ያስ ኮርቻ፣ ለማኝ ያለ ስልቻ
- ማንኛውም ሰው መሣሪያውን ካላሟላ ዋጋ የለውም



በቅሎ ጌታዋን እንጂ፣ የጌታዋን ጌታ አታውቅም
- ሠራተኛው ሰው የቅርብ ተጠሪውን እንጂ ሌላ አለቃውን አያውቅም

በቅሎ ግዙ ግዙ፣ አንድ አሞሌ ላይገዙ
- የአፍ ዘመድ ከገበያም አይገድ

በቅሎ ጭኖ መጭ መጭ፣ ሚስት አግብቶ ምሳዬን አምጭ
- ይኼ የማይቀር ነገር ነው

በቅጣት ይመስሳል ጥፋት
- ጥፋት በቅጣት ይካካሳል

በቅጥ የኖረ፣ በቅጥ ያገኛል
- በፕሮግራም የሚኖር ሰው አይቸገረም

በቆረጡት በትር ቢመቱ፣ ባወጡት ዳኛ ቢረቱ፣ የእግዜር ግቡ ከብቱ
- በተስማሙበት ጉዳይ ችግር ቢደርስቦት አይጸጸቱ

በቆብ ላይ አብርጣም፣ በመስቀል ላይ ውኸርም
- ያላስፈላጊ ተጨማሪ ነገር

በቆፈሩት ጉድጓድ፣ ይገቡበታል
- በሰፈሩት ቁና ሳይሰፈሩ አይቀሩም

በበላህ ገብር፣ በሰማህ መስክር
- የሰማኸውንና ያየኸውን ብቻ መስክር

በበርበሬ የተገዛ ፈረስ፣ መደቆሻ አይዘልም
- በትንሽ ሒሳብ የገዙት ነገር አስተማማኝነቱ ያህን ያህል ነው

በበሽታው የተጎዳ፣ በጥንስሱ የተቀዳ
- የተጎዳ ሰው አቅሙ ደካማ ነው

በበትሩ እማይማታ፣ በዘመዱ እማይረታ
- በያዝከው መሣሪያ በትክክል መጠቀም ይገባል

በበዛብህ ጊዜ የደነቆረ፣ በበዛብህ ዓምላክ ሲል ይኖራል
- ሞኝ የያዘውን አይለቅም

በበጋ እሞኝ ቤት ተንጋጋ፣ በክረምት እቤትህ ተከተት
- በበጋ ከሌሎች ቤት እየሔድክ ተመገብ፣ በክረምት ያለችህን ይዘህ እቤትህ ተከተት

በቡሐ ላይ ቆሮቆር
- በችግር ላይ ችግር

በቢላዋ ያርዷል፣ በውል ይማገቷል
- ሁሉም ነገር በሥርዓት ቢካሔድ ያስደስታል

በባዳ ቢቆጡ፣ በጨስማ ቢያፈጡ
- ምንም ጠብ አይልም

በቤት ዘመድ ገናኘ፣ በቄስ እናዛኘ
- ድርጊቱ ጠንከር ያስ ይሆናል

በቤት ይለምዱታል፣ ባደባባይ ይደግሙታል
- ሥም ይወጣ ከቤት ይደገም ከጎረቤት

በቤቷ ቀጋ፣ በውጭ አልጋ
- ለውጭ ሰው ደህና ነች ለቤቷ ግን አትመችም

በብረት ከመመርኮዝ፣ በእህል መተከዝ
- ምግብ አስፈላጊ ነው

በብርሃን ካልለቀሙ፣ በጨለማ አይለቅሙ
- ሥራን በጊዜው ካልሠሩ የኋላ ኋላ ችግር ይከታላል

በብዙ ከማረስ፣ ከተቀባቢው መቀነስ
- ኑሮ በዘዴ ጾም በሑዳዴ

በተለሙ ያርሷል፣ በጀመሩ ይጨርሷል
- የያዙትን ጭብጥ አይለቁም

በተለይ ንዳ፣ በጠራ ቅዳ
- ሁኔታዎችን እያየህ እያስተዋልክ ሒድ

በተረገዘ ባመት፣ በተወለደ በዕለት
- ያልተለመደና እንግዳ ነገር

በተርታ፣ የለውም ቅሬታ
- በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አሠራር ቅሬታን አያስከትልም

በተባለ ያርዷል፣ በታየ ይፈርዷል
- ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል

በተሾመ ይከራከሩበታል፣ በተሻረ ይመሰክሩበታል
- ባለው የማይሰግድ ያጣውን የማይንቅ የለም

በተተከለው ግንድ፣ በተፈተለ ገመድ
- የሰው መጨረሻው በሣጥን ተከትቶ፣ በክር ተገንዞ ወደመቃብር ይወርዳል

በተወረሱበት ዘመናት፣ አይረሜጨበት
- ንብረት ከእጅ ከወጣ ወዲህ እንደጥንቱ ልዘዝበት አይቻልም

በተጀመረው ነገር፣ በተጣበቀው ማገር
- በዚያው በጅምሩ በአቅጣጫው መሔድ እንጂ ወዲያ ወዲህ ማለት አይገባም

በትር ለገና፣ ውኃ ለዋና
- ለየተግባሩ የሚያስፈልጉትን ሁሉ ለይቶ ማወቅ ጠቃሚ ነው

በትር ከእጅህ፣ አባብ ተግርህ
- ሌባ ተይዞ ዱላ ጥየቃ

በትንሽ መንገድ፣ ንጉሥም አይሔድ
- በማያስኬድ ዘዴና ብልሃት! አትጠቀም

በትንሽ ማረሻ፣ ትልቅ እርሻ
- በትንሽ ወጪ ብዙ ትርፍ ማግኘት

በትንባሆ የገዙት ጦር፣ ቢወረውሩት ጋያ ይወጋል
- ያው ተመልሶ ወዳጄን ይፈልጋል

በትኩስ ሥጋ፣ በርጥብ ፍለጋ
- የልብን ለማሟላት የሚደረግ ጥረት



በችኮላ ያፈቀሩት፣ በችኮላ ተጣሉት
- ሲሮጡ የታጠቁ ሲሮጡ ይፈታል

በኋላ የመጣ፣ እጅ ይዞ አሰወጣ
- የፊተኞች የኋለኞች ይሆናሉ

በኋላ የመጣ፣ ሀይን አወጣ
- ይሉኝታ ቢስ

በኋላ የበቀለ ቀንድ ጆሮን በለጠው
- ከኋላ ተነስቶ የፊቱን ቀድሞ መገኘት

በናት ላይ ሞግዚት፣ በራት ላይ ዳረጎት
- ምንም ፋይዳ የሌለው

በናትና ልጅ መካከል፣ መርፌ ጠፋ
- እናትና ልጅ ይተማመናሉ፣ አይተማሙም

በኔውም ጥርስ አልተሣቀበት
- የእኔ ከሁሉም የተሻለ ነበር ግን ሥራ ላይ አልዋለም

በንብ ጊዜ፣ ዝንብ ይነከባል
- ዘመዴ ከተሾመ የፈለኩትን ሁሉ ያደርግልኛል

በንጉሥ ሞት አይዘበት፣ በዝሆን ሃሞት አይፈተፈትበት
- መልካም መሪ ሲሞት በመሪ ላይ መቀለድ፣ መዘባበት የማይሆን ነገር ነው

በንጉሥ ሰው አይፈርድ፣ በውኃ ላይ እሳት አይነድ
- የማይሆን ነገር አለመሞከር

በንጹሕ ዕቃ ላይ ዝንብ የምትቀምበው አታገኝም
- በምትሠራው ሥራ እንከን ከሌለብህ የምትወቀስበት ሁኔታ አይኖርም

በአህያ ጠፍር (ቆዳ) የተሠራ ቤት መሠረቱ ድቡሽት
- አይረባም

በአል ሽሮ የከበረ፣ ጦም ገድፎ የከበረ የለም
- መሠረት የሌለው ነገር ከባድ ችግር ሲገጥመው ይፈርሳል
- በአሸዋ ላይ የተሠራ ቤት፣ መሠረቱ ድቡሽት
- አይረባም

በአበያ የተዘራ ዘንጋዳ፣ እንደታሰበው አይረዳ
- ውጤት የለውም

በአንድ ቀበሌ፣ ሁለት ምሰሌ
- አንድ ሎሌ ለሁለት መግዛት ያስቸግራል

በአንድ ቅል፣ ጀንበር ጥልቅ
- በትንሽ ሥራ ጊዜን ማቃጠል

በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ
- በአንድ ነገር ሁለት ጉዳዮችን አጣምሮ መፈጸም

በሀይኑ ሰው አይሞላ
- ሰው የሚንቅ ነው

በዐይኗ ገረፈችው
- በፍቅር ተመለከተችው

በአጤ ይሙቱ የተከተረ፣ በስለት የተመተረ
- የቀድሞ አስተሳሰቡን ያልቀየረ

በአፉ ያመነ፣ ከሥሩ የመነመነ
- በአፍ ብቻ የሚኖር በተግባር ግን የሌለበት

በአፍ ስሕተት፣ በአገር መንሻተት
- በተነገረ ስሕተት አገርን መጉዳት

በአፍ ይጠፉ፣ በለፈለፉ
- በገዛ ንግግሩ ችግር ላይ ወደቀ

በእርሻ ጊዜ ያልዘራ፣ በመከር ጊዜ አይለበለብም
- በወቅቱ ያልሠራ ውጤቱ ዜሮ ነው

በእርጅና የተወለደን ልጅ፣ ከነአባቱ እንደ ሰው ያጠቃዋል
- አንዱ እንዱን አይከላከልም
- በልጅነት መውለድ ይጠቅማል

በእርጅና፣ ይመጣል ምንኩስና
- ሰው ሁሉ በመጨረሻው ለነፍሱ ያድራል

በእርጅና፣ ይመጣል ጣጣ
- በእርጅና ወቅት ብዙ ችግሮች ይኖራሉ

በእርጎ ላይ ጠላ፣ እግዜር ሲጣላ
- ሁለቱም የማይጣጣሙ ነገሮች ስለሆኑ አንዱን መውሰድ

በእንቅርት ላይ፣ ጆሮ ደግፍ
- በችግር ላይ ችግር

በዕውር ቢፈርዱ፣ ዕውር ይወልዱ
- ተንኮል መሥራት ዞሮ ዞሮ ባለቤቱን ይጎዳዋል

በዕውር ቤት፣ አንድ ዐይና ብርቅ ነው
- በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው

በዕውር ይጠቃቀሉበታል፣ በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል
- በወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል

በዕውር ጎዳና፣ ብርቅ ነው አንድ ዐይና
- በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው

በዕውቀቱ የሚኩራራ፣ ጥንቸል ነው
- አላዋቂ ነው

በዕውቀት የጎለመሰ፣ ብቻውን ነገሠ
- ዕውቀት ያስከብራል ያኮራል

በዕድሜህ ዕወቅበት፣ ሠርተህ ክበርበት
- ጊዜህን በአግባቡ ተጠቀምበት

በእጅ፣ አግብቶ ቁንጣን
- በገዛ እጅህ መቸገር



በእጅ የያዙት ወርቅ፣ ከመዳብ እኩል ነው
- በእጅህ ካለ እንደቀላል ነው የምትቆጥረው

በከብቱ የለገሰ በወለዱ የከሰሰ
- ብዙ ሰጥቶ ለጥቂቱ መቆጨት

በከብቱ የለገሰ፣ በፈረሱ የገሰገሰ፣ ካሰበው ደረሰ
- ጥሩ ኑሮ ይኖራል

በካሣ የከበረ፣ ባንት የከበረ
- ተከሶ የበለጸገ ጓያ በልቶ ያደገ

በካብ ላይ ብሠራ እባቡ መከራ፣ በዛፍ ላይ ብሠራ፣ አሞራው መከራ
በምድር ላይ ብሠራ እረኛው መከራ የት ውዬ የት ልደር አለች ወፍ
- ብዙ ምቀኞች እሉብኝ አላሠራም አሉኝ

በክረምት በርኖስክን፣ አታውል እቤት
- የሚመጣውን አታውቅምና ጠቃሚ የሆነውን ሁሉ ከራስህ አትለይ

በክረምት ካረሰ፣ እናቱን ያስመነኮሰ
- ብዙ ከማረስ በላተኛን መቀነስ

በወሌ ደጃዝማች ነው ባሌ
- በትዝታ መኖር

በወሬ አትጥላኝ፣ በስሙ ጅብ አትውጋኝ
- ወሬ ሰምተህ አትጥላኝ ተጠግተህ እየኝ ተመልከተኝ

በወሬ እይነግሡ፣ በእጅ አይካሱ፣ በቁንጫ አያርሱ
- መሥራት ነው እንጂ ወሬ ምንም አይጠቅምም

በወሬ እኔም አለኝ ቁስል፣ ያንተን የሚመስል
- በሁለታችን ላይ የተወራው ሁሉ ተመሳሳይ ነው

በወር ልቅ፣ በዓመት ቀሚስ ጥልቅ
- ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል

በወተት ላይ ውኃ መጠጣት ያበዛዋል ያነጣዋል
- በነገር ላይ ነገር መጨመር ነገሩን ያገነዋል

በወንድሜ ግንባር፣ ደም አልይበት
- ክፉ ነገር እንዲገጥመው አልመኝም

በወደቀ ግንድ፣ ምሣር ይበዛበታል
- ሰው ሲያጣ በችግር ላይ ችግር ይገጥመዋል

ቢዋስ ያለ ከብት፣ በጣት ያለ ቀለበት
- ርቆ አይሄድም

በዋጋ ከእናትህ ልጅ ተዋጋ
- ገበያ ገበያ ነው

በውል ከሄደች በቅሎዬ፣ ያለውል የተበላች ቆሎዬ
- ያለ ስምምነት የሚደረግ ነገር ይቆጫል

በውርርድ ላይ ውርርድ፣ ከነብር ላይ ሰማርድ
- የከፋ ሁኔታን መጋበዝ ያሆናል

በውሻ ሆድ፣ ቅቤ አያድርም
- ወሬኛ ምስጢር አይደብቅም

በውሽማ ሞት ፊት አይነጭም
- ድብቁን ነገር ይፋ አያወጡትም

በውሽማዋ ዳኝነት፣ ባሏን ሁለት ጊዜ ረታችው
- በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት

በውድ ሸጥልኝ፣ በሐቅ መዝንልኝ
- አንተ ስእኔ፣ እኔም ስአንተ እንተሳሰብ

በዘመኔ፣ ይድላው ስወገኔ
- በኔ ጊዜ ዘመዶቼን መጥቀም አለብኝ

በዘር የላኩ በዝርዝር፣ በጠዋት የላኩ በቀትር
- ተልኮ ቶሎ የማይመለስ

በዘጠና፣ የስም ጤና
- በስተርጅና በሽታ ይጫጫናል

በዚህም አዳርህ፣ ግብር አለብህ
- ይሄም ኑሮ ሆኖ መጨነቁ

በዝሆን አፍ ቅርፊት
- የማይመጣጠን ነገር

በገዝሆን፣ ጆሮ ትንኝ
- የማይመጣጠን ነገር

በዝምታ፣ የለበት ሐሜታ
- ዝምታ ወርቅ ነው

በዝምታ፣ ይገኛል ከበሬታ
- ዝም አይነቅዝም

በዝንጋታ፣ ብዙ ጊዜ ይረታ
- ስለሚዘነጋ ይረታል

በየቤቱ ያለ ጥንስስ ጋን ይፈነቅላል
- ሁሉም በየቤቱ የራሱ የሆነ ሐሳብ አለው

በየዕለቱ፣ ይወርዳል መዓቱ
- በየቀኑ የሚሆነው ብዙ ነው

በየወንዙ ሐሴ
- በየደረሱበት ለጌታ ምሥጋና ማቅረብ

በየወንዙ መቀደስ፣ የተኛ ሰይጣን መቀስቀስ
- የማይፈለግ ነገር ለችግር ይዳርጋል

በየወንዙ፣ ብዙ ነው መዘዙ
- በየቦታው ያለው ሁኔታ ብዙ ችግሮች አሉበት

በያዘው በትር አይመታ፣ በወንድምና በእኅቱ አይረታ
- ግትር ሐሳብ ይዞ የሚከራከር የአስታራቂን ሐሳብ የማይቀበል



በደህና መንገድ፣ ዓመት ዙር
- አጭር ነው መንገዱ ብለህ አደጋ ውስጥ ከምትወድቅ በቀናው መንገድ ብትዘገይ ይሻላል

በደል ዋና፣ አጥታ ትኖራለች
- ግፍን የሚያስወግድ ሁነኛ ሰው አልተገኘም

በደመና ጊዜ፣ ስለመብረቅ አይወራም
- በሚጨት ፊት ስለፈንግል አይወራም

በደረቅ አበባ፣ እርጥብ ይራዳል
- ለኃጥእን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል

በደረቅ ይበላ፣ በእርጥብ ይከላ
- ጊዜን ለማሳለፍ የማይሆነውን በመቀበል ውሎ አድሮ ግን ያን ሁኔታ በተሻሻለ ሁኔታ መተካት

በደቦ የተሠራ፣ በደቦ ይፈርሣል
- የነቶሎ ቶሎ ቤት፣ ግርግዳው ስንበሴጥ

በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
- እንኳን ዘንቦብሽ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

በደግነቱ፣ ተቀረጠ አንገቱን
- ጥሩ በሠራ ጉዳት ደረሰበት

በዱር ጥገት፣ በጥፊ ዱቄት
- ምንም ሊያሠራ እለመቻሉ

በዱባስ ሞት፣ ይግባ አለች ጃርት
- ጥቅም ስለማይሰጥ ይሙት

በዳቦ ላይ ሙልሙል
- በራት ላይ ዳረጎት

በድህነት ላይ ስንፍና፣ በቂጥኝ ላይ ቁምጥና
- ሁኔታዎቹን የሚያባብስ ገጠመኝ ነው

በድሉ ማሩኝ፣ ተበድሎ ይቅርታ
- ስሁሉም ይቅር ማለት ይገባል

በድቡሽት ላይ፣ የተሠራ ቤት፣ ዕድሜ የለውም
- ጥሩ መሠረት የሌለው ቤት ዕድሜ የለውም

በድንገት እህያ ገባ፣ ከጅብ ቤት
- ሳይታሰብ አደጋ ላይ መውደቅ

በዶሮ ፈንጢጣ፣ በሽንብራ ቂጣ
- የማይመስል ነገር ለሚሰትህ አትንገር

በጅብ ሆዳምነት፣ በእህል ጣፋጭነት፣ ሳይተዋወቁ ያኖራሉ
- የሚጠቅመውን የሚያውቅ ከሰንት እንድነው

በጅ ያገኘሽ አያጣሽ፣ ያጣሽ አያገኝሽ
- ካለችበት የምትኖር ወደሌላ የማትሔድ

በገቡበት፣ እይወጡበት
- ሁሉ ነገር ለየቅል ነው

በገና በሰው እጅ ያምር፣ ሲይዙት ያደናግር
- ለተቀማጭ ስማይ ቅርቡ ነው

በገና ጨዋታ፣ አይቆጡም ጌታ
- ጨዋታው አለቃና ምንዝር የለውም

በገንዘብ የተገኘ ወዳጅ፣ ለመከራ አይበጅ
- እውነተኛ ወዳጅ አይደለም

በገዛ አረሟ፣ እባብ ይዛ ታስፈራራ
- ልፍጭልሽ ያሏት አገልጋይ መጇን ትደብቃለች

በገዛ አራሱ፣ እባብ ጠመጠመ
- በራሱ ላይ ችግር ፈጠረ

በገዛ ዳቦዬ፣ ልብ ልቡን አጣሁት
- የኔውን ሌሎች ተጠቀሙበት

በገዛ ጌታ፣ እግር እግሩን ይመታ
- ችግርን በራስ ላይ መፍጠር

በገደል ያለ፣ ዝንጀሮ ይኖራል ተከብሮ
- በአገር መኖር ያስከብራል

በጉዳዩ ላይ፣ ውኃ አፈሰሰበት
- ችላ አለው አላተኮረበትም

በጊደር ጥገት፣ በጥሬ ዱቄት
- ያሰቡትን ማሟላት ያስቸግራል

በጊዜ የገባ እንግዳ፣ እራቱ ፍሪዳ
- ለመጠቀም በጊዜ መገኘት

በጋለሞታ ቤት፣ ሁሉ ይጣላበት
- ክብር የሌለበት ቤት ሁል ጊዜ ውርደት

በጋ ትቃ ክረምት ቧገቃ
- በጊዜ ያለመጠቀም

በግ ባልበላሽ፣ ትበይኝ አለ ጅብ
- ዝም በማለቴ ተጠቃሁኝ

በግ ከበረረ፣ ሞኝ ካመረረ፣ መመለሻ የለውም ነገሩ ከረረ
- ሞኝ ስለማያመዛዝን አንዴ ከተቀየመ መመለሻ የለውም

በግ የሌለው፣ ቀበሮን እውሬ አይላትም
- ችግር ያላገጠመው ችግር የሚደርስበት አይመስለውም

በግዜር ቢቆጡ፣ በጨለማ ቢያፈጡ፣ ምን ያመጡ
- ለውጥ አያመጡም

በግድ እንት ጠበ፣ የፋሲካ ዕለት
- የማይስማማ ግብግብ

በጎመን ያበጠ ሆድ፣ በድንች ይፈተናል
- ማሽላ ለማሽላ ተያይዞ ቆላ

በጎ እማሆጮን መጦር፣ ክፉ እማጮን በጦር
- ጥሩ ላደረገልህ ጥሩ መጥፎ ለሠራብህ መጥፎ ሥራበት



በጎደሎ ቀን የገዛሁት ጋሻ፣ ሳያስገድለኝ አይቀርም አለ ፈሪ
- ሙያ በሌለውና አጠቃቀሙን ባለማወቁ

በጠላ ላይ ወተት፣ የግዜር ቸርነት
- በጣም ተስማሚ ነው

በጠረጠሩ ጠጠር፣ ይጥሉ
- መጠራጠር ስላለ ማረጋገጥ ያስፈልጋል

በጠራ ተሻገር፣ በተሳለ መትር
- በሚያስተማምን መሣሪያ መሥራት ያረካል

በጠይቆ ዕውቀት፣ ይገኛል ክብረት
- ማወቅ ይገኛል በመጠየቅ

በጠጅ ተጀምሮ፣ በጠላ ያልቅ ድግስ
- ሲያልቅ አያምር

በጠገብሁ፣ ጠብ የለም
- በቃኝ በማለቱ ግጭት አይፈጠርም

በጠፍር የተሠራ ቤት፣ ጅብ ሲጮህ ይፈርሳል
- አጥፊና ጠፊ

በጣም ሀብታም፣ በጣም ድሃም
- እያለው የማይጠቀምበት

በጣይ፣ ቅቤ አያበሩበት
- አንድን ነገር ለመፈጸም ወቅት ወሳኝ ነው

በጣይ በጉባኤ፣ / በፀሐይ በጉባኤ/
- በሕዝብ ፊት / በአደባባይ/

በጥር ሠርግ፣ በግንቦት በልግ
- ተስማሚና ወቅቱ ነው

በጥቂት በጥቂት፣ ይሞላል ልቃቂት
- ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሯ ትሔዳለች

በጥባጭ ካለ፣ ማን ጥሩ ይጠጣል
- የሚያስቸግር ካለ ማን በሰላም ይኖራል

በጥንስሱ የተቀዳ፣ በጮርቃው የተጎዳ
- ከጅምሩ የተበላሸ

በጦም ቆሎ፣ በዳገት በቅሎ፣ ቆሎው ይከካል በቅሎውም ይነካል
- ለጊዜው ለሁኔታው ተስማሚውን ሥራ ላይ ማዋል

በጨለማ እየሔዱ፣ ጅብን ነገረኛ ያደርጋሉ
- በራቸውን ሳይዘጉ ሌላውን ሌባ ይላሉ አለች ውሻ

በጨዋታ ያልተረታ፣ ታጥቆ ያልተመታ፣ ይናደዳል ወደማታ
- ያሰበው ስላልተፈጸመለት

በጨው ደንደሰ፣ በርበሬ ተወደሰ
- አንዱ በሠራው ሥራ አንዱ ይመሰገን

በጫማ የሚሔድና፣ በቃሪያ የሚበላ፣ ሰውን አይጠብቅም
- በጫማ የሚሔድ ስለማይቆረቁረው፣ በቃሪያ የሚበላ ስለሚለበልበው ቶሎ ይጎርሰበታል

በጭቃ የተመራ፣ በቅቤ የተሠራ
- ሁለ ነገሩ ያማረለት፣ የተሳካለት ነው

በፈረሰ የፈለጉት፣ በእግር ይገኛል
- በከባድ የተፈለገ ኋላ ላይ በቀላሉ ይገኛል

በፊት ዕወቁኝ ዕወቁኝ፣ በኋላ ደብቁኝን ያስከትላል
- አጉል መንጠራራት ኋላ ለውድቀት

በፊት የወጣውን ጆሮ፣ በኋላ የወጣ ቀንድ በለጠው
- ከመምህሩ፣ ደቀመዝሙሩ

በፊት የደረሰን ወፍ ይበላዋል፣ በፊት የተናገረውን ሰው ይጠላዋል
- ከሰው በፊት ቀደም ቀደም በማለት አትናገር

በሩሲካ የተቀጠረች ገረድ፣ ሁልጊዜ ሩሲካ ይመስላታል
- በዚያ ዓይነት የሚቆይ ይመስላታል

በፍርድ ከሔደች በቅሎዬ፣ ያለፍርድ የሔደች ጭብጦዬ
- ያለስምምነት የሚሆን ነገር ይቆጫል

ቡሉኮና ጋቢ፣ አቢላምና አላቢ
- ተቀራራቢዎች ናቸው

ቡቃያ አይታጨድ፣ እንቦሳ አይጠመድ
- የማይቻል ነገር

ቡቃያው አንድ ማሳ፣ አራሚው አምሳ
- ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ

ቡና በአቦሉ፣ ሰጦታ ከአቀባበሉ
- ከፍትፍቱ ፊቱ

ቡናና ፍቅር፣ በትኩሱ ነው
- የቡና ለባቱ መፋጀቱ

ቢርበኝ ለረቅሁ፣ ቢጨንቀኝ ታረቅሁ
- የሁኔታዎች አስገዳጅነት

ቢሰናከል መንገዴ፣ ጣለኝ ከወንበዴ
- የፈጠርኩት ስሕተት፣ ችግር ላይ ጣለኝ

ቢሰጡኝ እነዳ፣ ቢነሱኝ እረዳ
- መልካሙን ነስተው የማይሆነውን ቢሰጡኝ ምን ልሆን እችላለሁ

ቢስ የቢስ ላት፣ ክፉ የክፉ ለት
- ሁሉም በዚያው በወትሩ

ቢቆጡት የማይፈራ፣ ቢናገሩትም አይሰማ
- እንዲያው ከንቱ ልፋት

ቢቆጡት ያልሰማ፣ ቢመቱቱም ያው ነው
- ቢደበድቡትም ጸባዩ አይሻሻልም



ቢበላ ገነት፣ ቢኖሩ ዓመት
- ለጊዜው ተብሎ የሚፈጸም ተግባር

ቢበርድ በእጅ፣ ቢተኩስ በማንኪያ
- እንደየአስፈላጊነቱ መጠቀም ይገባል

ቢበይኑለት ቀጠነኝ፣ ቢፈርዱለት ይግባኝ
- አስቸጋሪ ተሟጋች

ቢተኙ ነገር ቢሔዱ፣ አገር አይታጣም
- ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ

ቢተኙ ነገር ያገኙ፣ ቢነሡ ነገር ይረሱ
- ሐሳብ በመኝታ ጊዜ ማስቸገሩ አይቀርም

ቢነግሩሽ ትናገሪብኝ፣ ቢያጥቡሽ ትሰክሪብኝ
- መላቅጡ የጠፋ

ቢናገር የማያምር፣ ሲቀመጥ አይከበር
- መታፈር በከንፈር

ቢከማች፣ ዕዳው ላንቺ
- ከሥር ከሥሩ መሥራት ሲገባ ከተከማቸ ዞሮ ዕዳው ለኋው ነው

ቢከፍቱት ተልባ
- የማይረባ

ቢወዱኝ ብሎ ሞት፣ ቢጠሉት ምን ሊመጣበት
- የማይጎዱት ባላጋራ

ቢዋደዱ ጦም ገደፉ፣ ቢጣሉ ተዋረፉ
- የጅል ፍቅር ያመናቅር

ቢዘል ማጀት፣ ቢወጋ ምንቸት
- አቅመ ቢስ ሰው ነው

ቢያበቀምጥም፣ ጮማ ይሻላል
- ጥርት ያለ ነገር ይሻላል

ቢያብዱም ቢሞቱም፣ የእንዱን ነገር እያሜውቱም
- ምንም አልፎ ቢሔዱም በደህና ጊዜ የተጫወቱትን ለሌላ ሰው አያሜውቱም

ቢያብዱም ቢጨምቱም ያንዱን ነገር ላንዱ አያወጡም
- ምሥጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም

ቢያንጋልሏት ጡት የላት፣ ቢደፏት ቂጥ የላት
- ሲንቢሮ ናት ምንም የሴት ቅርጽ የላትም

ቢያዝሉት ያለቅስ፣ ቢስሙት ይነክስ
- ቢንከባከቡትም እንቢ አለ አሻፈረኝ አለ

ቢያዩኝ እሥቅ፣ ባያዩኝ እሰርቅ
- የጎረቤት ሌባ የሚያደርገው

ቢጠረጥሩ፣ ጠጠር ይጥሉ
- የጥንቆላ ተግባር መፈጸም

ቢጠሩት ያልሰማ ቢጠቅሱት አያይም
- ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም

ቢጠሩኝ አቤት፣ ቢልኩኝ ወዴት
- ታዛዥ ነኝ

ቢጠናባት ጠናች፣ የልጅዋን ባል ቀማች
- ማድረግ የማይገባትን ነገር አደረገች

ቢጨንቀን፣ ሸጤ ሆንን
- ወገበ ዐረቄ መሆን

ቢፈሩት አይቀር፣ ሞትና ነገር
- ነገር ይመጣብኛል ብለህ ሳታስበው ይመጣብሃል

ቢፈትጉት ይነጣል፣ ቢመረምሩት ይወጣል
- ነገር እንደያኸርው ነው

ቢፈጀኝ በማንኪያዬ፣ ባይፈጀኝ በጄ
- እንደሚያመቸኝ አደርጋለሁ

ባህር ዛፍ ከተከሉት ይጸድቃል፣ ገንዘብ ካላኖሩት ያልቃል
- ለነገ ያሉት ያገለግላል

ባሰማ ፍረዱኝ፣ ባጠፋ ስደዱኝ
- ሥራዬን ግብሬን ተመልከታችሁ ሐሳብ በጡኝ

ባለርስት የርስቱን፣ ያህል ያከብራል
- ርስት ከፍተኛ ሀብት ነው

ባለቁርጥ አትደንግጥ፣ ባለ አንቀልባ አታግጥ
- ሺ ቢታሰብ ያው በጎሌ አለች ድመት

ባለቤቱን አፈቱ ማመስገን፣ የማማት ያህል ነው
- ማታለልና ሽንገላ ይመስላል

ባለቤቱን ካልናቁ፣ አጥሩን አይነቀንቁ
- የተናቀን ሰው ማንም ይደፍረዋል

ባለቤቱን ካልናቁ፣ ውሻውን አይመቱ
- የተናቀን ሰው ማንም ይደፍረዋል

ባለቤት ሲተዋወቅ፣ የሠርገኛ ልብስ ይደርቅ
- ብዙ ጊዜ ይፈጃል ማለት

ባለቤት ሲያፍር፣ እንግዳ ይጋብዛል
- ያለቦታው የተፈጸመ ተግባር

ባለቤት ካልጮኸ፣ ጎረቤት አይረዳም
- ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

ባለቤት የወደደው፣ አሞሌ በሬ ይለውጣል
- ባለቤት የከበሩት ነገር ከፍተኛ ከበሬታ ይሰጣል

ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ፣ ባለዕዳ አይቀበለውም
- ባለቤቱ የናቀው ነገር ሌላ ሰው አይበላውም

ባለቤት ያከበረው እህያ፣ በቅሎ ይለውጣል
- ባለቤት ያከበሩት ነገር ከፍተኛ ከበሬታ ይሰጣል



ባለ ነገር ከቤት፣ ጠበቃ ከችሎት
- ሁሉም በተመቸው ሥፍራ

ባለንብረት፣ አያደርስ ከበረት
- ማንም ሰው ንብረቱን ይጠብቃል

ባለአደራ፣ ጮኸ ከተራራ
- አደራውን ለመወጣት ሰው እንዲሰማለት አደረገ

ባለ ኩል ያበናክል
- ኩሉ ዐይንን ጋርዶ ለእንቅፋት ሲዳርግ

ባለካባ ከባለካባ፣ ባለዳባ ከባለዳባ
- እርስ በርሱ

ባለጌ ማማቱን፣ ቆዳ መኝንቱን አይተውም
- ባለጌ ሰው ሁሌ ባለጌ ነው ከማማት አያርፍም

ባለጌ ሲሞት፣ ሬሳውን በሽመል
- ባለጌ ሲሞት ግልግል ነው

ባለጌ ሲቀመጥ፣ ቂጡን ገልቦ ነው
- የሚያሳፍር ተግባር ነው የሚፈጽመው ሥረዓት የለውም

ባለጌ ሲወዱት፣ ከልጅህ አኩል አድርገኝ ይላል
- ፊት ካሳዩት አይቻልም

ባለጌ ቁም ነገሩን፣ ቧልት ያደርገዋል
- ላም ያልዋለበት ኩበት ለቀማ

ባለጌ ባለሟል፣ ልብስ ገልቤ ልይ ይላል
- አስቀያሚና አስጸያፊ ሥራ ልሥራ ይላል

ባለጌና የቆቅ አውራ፣ በራሱ ያወራ
- የራሱን ገመና በራሱ ያወጣዋል

ባለጌን አንድ ጊዜ ለደበው፣ ሁልጊዜ ራሱን ይሰድባል
- እገሌ እንዲህ አለኝ እያለ ሲያወራ ይኖራል

ባለጌን ካሳደገ፣ የገደለ ጸደቀ
- ባለጌን ተንከባክቦ ማሳደግ አያስፈልግም

ባለጌን ገንዘቡ፣ አያኮራውም
- አጠቃቀሙን ስለማያውቅበት

ባለጌ አያዝንም ለገበረ ያዝናል ባልንጀራው ለቀረ
- ገብሬ እሱ ሳይገብር እንዴት ይበላል በሚል ይመቀኛል

ባለጌ አፉ እንጂ፣ እግሩ አያድጠውም
- ባለጌ የሚያስቀይመው በንግግር ነው

ባለጌ ከበቅሎ፣ የወጣ እንደሆን፣ ከሰማይ የደረሰ ይመስለዋል
- አይቶ የማያውቅ ሰው

ባለጌ ካወራው፣ የሰው ልጅ የገመተው
- ባለጌ አይታመንም

ባለጌ ካወራው፣ የጨዋ ልጅ ያሰበው
- የባለጌ ወሬ አይታመንም

ባለጌ የተመከረለት፣ ቁንጫ የተጠረገለት ይብሳል
- ባለጌ የተመከረ ዕለት ይብሰበታል

ባለጌ ያለበት ሸንጎ፣ ዝንብ ያለበት እርጎ
- አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል

ባለጌ ጆሮው ከለበሰ፣ አዋሽ ከደፈረሰ
- ካቅሙ በላይ መኮፈስ ይሿል

ባለጠጋ ሲቀናጣ፣ የድሃ ልጅ ይሞታል
- ያንን እያየ እንደዚያ ልሁን ሲል

ባለጠጋ በከብቱ፣ ድሃ በጉልበቱ
- ሁሉም እንደዐቅሙ

ባለጠጋ በድሉ ይቀጣል፣ ድሃ ተበድሉ ይለማመጣል
- የት ይደርሳል፤ መሔጃ ስለሌለው

ባላወቀው ፈርዶ፣ እደረገው ባዶ
- በማይመለከተው ጉዳይ ገብቶ ከፍተኛ ስሕተት ፈጸመ።

ባላዋቂ ቤት፣ እንግዳ ናኘበት
- ባላዋቂ ቤት ንብረቱ ሁሉ እንደባከነ ነው

ባላገር ሆደ ገር፣ ክፉ አይናገር
- ሁሉን ችሉ አዳሪ

ባላገር የሚበላው ቢያጣ፣ የሚከፍለው አይቶ አያውቅም
- ባላገር የሰው ገንዘብ አይፈልግም

ባላጋራ ያለው፣ እንቅልፍ የለውም
- ባላንጣ ያለው ሰው ጥላውን እንኳን አያምንም

ባሌን ጎዳሁ ብላ፣ ብልቷን በዕንጨት ወጋች
- በራሷ ላይ ጉዳት አደረሰች ሰውን የጎዳች መስሏት

ባልበላ ጭሬ፣ አላፈስም ወይ አለ ዶሮ
- እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል

ባልነቃ ሰንጥቆ፣ ባልዳመነ ባርቆ
- የማይሆን ነገር ሆነ

ባልነበረ፣ ይሻል ነበረ
- ጭርሱኑ ቢቀር

ባልና ሚስት ሊተዋወቅ፣ የሠርገኛ ልቡ ይወልቅ
- እሱ ሊያገባ ያኛው ገገባ

ባልና ሚስት፣ ካንድ ባሕር ይቀዳል
- ተመሳሳይ ባሕሪ አላቸው

ባልና ሚስት፣ ፍትህና መንግሥት
- ስምምነት ሊኖር ይገባል

ባልንጀራህ ሲላጭ፣ አንተም አብረህ ቅረብ
- ጥንቃቄ አድርግ

ባልንጀራህ ሲበልጥህ፣ ቁንጣን ይምለጥህ
- ሊቆጭህና ልትታትር ይገባል



ባልንጀራህ ሲታማ፣ የኔ ብለህ ስማ
- ነግ በኔ ነውና

ባልንጀራው ቢያጠቃው፣ ወደሚስቱ ሮጠ
- ከሸንጎ ቢረታ ሚስቱን ከቤት መታ

ባልንጀራዬ ከሚበልጠኝ፣ ቁንጣን ይፍለጠኝ
- ሳለመበለጥ ተግቶ መሥራት

ባል ካላጎረሰ፣ በሬ ካላረሰ
- መነሻውን መምጫውን ማወቅ ይገባል

ባልወልድልሽ፣ ታከትሁልሽ
- ባይሳካልኝም ጥረት አድርጊያለሁ

ባልዋጁት ጣት፣ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት
- የማትፈልገውን ነገር ቢበላሽም ምንም አይመስልህም

ባልጋ የሚለያይ፣ በፍቅር ይራራቃል
- ተራርቆ የሚኖር ሰው እያደር ፍቅር እየቀነሰ ይሔዳል

ባልፈሱበት፣ ቂጥ አያፍሩበት
- ባላደረከው ነገር አታፍርበትም

ባልፈጨሽ በኖብሽ፣ ባልነበርሽ ባርቆብሽ
- ባላደረግሽው ነገር ተወቀስሽ

ባመጣሽው ዳኛ፣ ትሆን አሣረኛ /እስረኛ/
- በራሱ ላይ እባብ ጠመጠመ

ባረገዘች፣ ክታቡን ያዘች
- በመጸነሷ ምክንያት መሠረት ያዘች

ባሩድ በከምሱር ይነሳል፣ አንበሳ በዱር ያገሳል
- ሁሉም እንደየጠባዩና ባህርይው

ባሪያና ቃሪያ፣ እንዳቃጠለ ይኖራል
- ሁልጊዜ ጌታውን ያናድዳል

ባሰር ጣቱ፣ በሰፊው ደረቱ
- እምነቱን ሲያረጋግጥ

ባበብ ባስብ አግሬን፣ ቆርጦ በራሴ አሸከመኝ
- ብዙ ማሰብ መፍትሔ አይሆንም የባሰ ችግር ላይ ይጥላል

ባስተጋባ፣ ባሕር ሆዴ ገባ
- ሥር ሰድዷል

ባቄላ ሳይሰበር፣ መነኩሴ ሳይቀበር
- ባቄላን ሳይቆረጥሙ እይዋጥም

ባቄላ አለቀ ቢለው፣ ፈስ ቀለለ አለ
- ለችግሩ በዚያው መፍትሔ ተገኘ

ባበደሩበት አገር ተበድሮ፣ በሰጡበት ተቀባጥሮ
- ሀብታም በለገሰበት አገር ቢከስር መለመን አይችልም

ባባቱ ከተማ፣ ልጁ ተቀማ
- በራሱ ቤት ባይተዋር መሆን

ባባቱ ፊት የሚናገር፣ አፉ ለምጣም ነው
- ክፉ ንግግር የሚናገር ልጅ አባቱን ያስከፋል፣ የተረገመ ነው

ባባትህ አገር አትቀማ፣ በናትህ አገር ጦም አትደር
- በወገኖቹ መሀል ያለ ሰው አይቸገርም

ባት መልካም ሲሆን ለመሮጥ፣ ባይሆን ለጌጥ
- አንድ ነገር የተለያዩ ጥቅሞችን ሊሰጥ ይችላል

ባትዋጋ፣ እንኳን ትሰለፍ
- ወኑ ይድረስህ

ባንዱ ታዘብ፣ ባንዱ ተለዘብ
- ሰው የሚልህን ስማ

ባንድ ሁለት፣ በጥሬ ዱቄት
- ቀስ በቀስ

ባንድ ራስ፣ ሁለት ምላስ
- ቀባጣሪ በአንዱ የማይረጋ

ባንድ ቀን ስሕተት፣ ዓመት ጸጸት
- የአንድ ቀን መዘዝ ያለ አንድ ዓመት አይመዘዝ

ባንድ አልጋ፣ ሁለት አራስ
- ባልና ሚስት

ባንድ ዐይን ጉድፍ
- የችግር መፈጠር

ባንድ አፍ ተናጋሪ፣ ባንድ ምላስ መስካሪ
- የማያወላውል ሰው

ባንድ እፍ ተናጋሪ፣ ባንድ በቅሉ ሰጋሪ
- የማያወላውል ሰው

ባንድ ከፈጩ፣ የለም እመቤት
- የላመውን እመቤቲቱ ትፈልገዋለች

ባንድ ወናፍ፣ ሁለት አፍ
- በአንድ እፍ ሁለት ምላስ

ባንድ ዙፋን፣ ሁለት ንጉሥ
- በአንድ አፍ ሁለት ምላስ

ባንድ ደብር፣ ሁለት መምህር
- ባንድ ወናፍ ሁለት አፍ

ባንድ ጎራ፣ ሁለት አውራ
- ባንድ ወናፍ ሁለት አፍ

ባዕድ ሥር የለውም
- ከዳተኛ ስለሆነ አትተማመንበትም

ባዕድ ከላመው፣ ዘመድ የነከሰው
- ምንም ቢጠብ መንገድ፣ ምንም ቢከፋ ዘመድ

ባዕድና ጨለማ፣ አንድ ነው
- ከዳተኛ ስለሆነ አይታመንም



ባወጡት ዳኛ ቢረቱ፣ በቆረጡት ጨንገር ቢመቱ፣ የእግዜር ግብ ከብቱ
- ተማምነው ያደረጉት ነገር አይቆጭም

ባዋቂ ፊት፣ መናገር መታገም
- ዐዋቂ ሌላውን ያስተካክላል

ባይሰጡት፣ ፈገጡት
- ተው እንዳይሆን

ባይቆጭ፣ ያንገበግባል
- በጣም የሚያበሳጭ ነገር

ባይብ እንጂ፣ በቅቤ አይወፍሩ
- የቱን ከየቱ ማስቀደም

ባይኔ መጣህብኝ
- በምወደው ነገር መጣህብኝ

ባድኋዊ ያድላባት፣ ባመጣኝ ሰይፍ ይዘዝበት
- ክፋውን ክፉ ያጋጥመው

ባገኘህ ቀን ቅቤ ዋጥ፣ ባጣህ ቀን ድንጋይ ጋጥ
- እንደሁኔታው እንደጊዜው ኑር

ባጉራ ጠናኝ የተረታ፣ መሃል አገዳውን የተመታ
- የተረታ ሰው ሞራሉ ይወድቃል

ባግባቡ፣ በደጃፉ ይግቡ
- በፊት ለፊት በወግ በማዕረግ

ባጎረስኩ፣ እጄን ተነከስኩ
- በጦርኩ በደል ደረሰብኝ

ባጠፋ ወታደር፣ ይክሳል ባላገር
- ያጠፋው እያለ ያላጠፋው ይክሳል

ባጭር ታጥቆ ጋሻ ነጥቆ፣ ዘገር ነቅንቆ፣ ይዋጋዋል አጥብቆ
- ጀግና የጀግናን ተግባር የሚፈጽም

ባፈላ ይታፈላል፣ /በንጥጥር/ በነጠር ይመለሳል
- ያላግባብ የተፈጸመው ተጣርቶ እርምጃ ይወሰድበታል

ባፌ ማን በላበት፣ አለ እርኩም
- እኔ እንደሁ አንጀቴ ጠብ ያለ ነገር የለም ማለቱ ነው

ባፍ ይጠፉ ይለፈልፉ
- መለፍለፍ ችግር ላይ ይጥላል

ቤተ ሥራ፣ በኋላ ይመጣል
- ነገሩ ሁሉ እያደር ነው፣ እያደረ ዕውቀት ይገኛል

ቤተክርስቲያን ለማላጅ፣ ገበያ ሳርፋጅ
- አርፍዶ ገበያ የገባ ደህና ይሸምታል

ቤተክርስቲያን ቢደርስ የጠላቴ ሬሳ፣ የኔ ከቤቴ ይነሳ
- ያው ለእኔም አይቀርልኝም ማለት ነው

ቤተክርስቲያን ተኳሽ፣ ዕርቅ አፍራሽ
- ቤተክርስቲያን አካባቢ መኳሸት /ሐሰትን ቀላቅሎ/ መናገር አይገባም

ቤተክርስቲያን አቃጥል ቢሉት፣ ደጀሰላም አቃጠለ
- የእሱ ብሶት ያለው ከደጀሰላሙላይ ነውና ወደዛ አተኮረ

ቤተክርስቲያን፣ የገባ ውሻ
- ሁሉም የሚጠላው

ቤቴ ከባለስልጣኖች፣ እንድቀድም አደረግሽኝ
- ቤቴ ከብር አሰጠችኝ

ቤት ለሌላው ቤት ይሰጠው፣ ችግሩን እንዲቀምሰው
- ትዳር ብዙ ሁኔታዎች የሚታዩበት ነው

ቤት ለእንቦሣ፣ እንቦሣ እሰሩ
- አዲስ ቤት ሠርቶ የገባን ሰው ለመጠየቅ ደጃፍ ሲደርሱ

ቤት ሠርቶ ያለመውጫ፣ ፊት ያላፍንጫ
- እስቸጋሪ ሁኔታ ነው

ቤት ሲሰፋ፣ የሰው ሁሉ ተሰፋ
- ፍሥሐ፣ ሐሴትና ደስታ ያስገኛል

ቤት በማገር፣ ንጉሥ በባላገር
- መሠረቱ ባላገር በመሆኑ ነው

ቤትን መመሥረት፣ በባለገር እንጀት
- እሱ በደከመውና ባመጣው ውጤት

ቤት አለክዳን፣ ከምንም አያድን
- ቤት ያለከዳን ቤትነቱ አይታወቅም

ቤት ከነጉልላቱ፣ ምድጃ ከነማዘንቱ
- እንዲያ ተሟልቶ ሲገኝ ምንኛ ያስደስታል

ቤት ካሉት፣ መቃብር ይሞቃል
- ኑሮ እንደነዋሪው ነው

ቤት ዘግተው የደበደቡት፣ ውሻ ባለቤቱን ይነክሳል
- ሲሞላ ይፈሳል፣ ሲከር ይበጠሳል

ቤት ያለ ሴት፣ ከብት ያለ በረት
- እንጀራ ያለወጥ ቤት ያለ ሴት

ቤት ያለ ቁልፍ፣ አልጋ ያለምንጣፍ
- የተሟላ ነው ለማለት ያስቸግራል

ቤት ያለበር ፊት ያለ አፍንጫ፣ ያ መውጫ ያ ማጌጫ አይኖረው
- ተሟልቶ ሲገኝ እንዴት ያምር

ቤት ያለአጥር፣ ሬሳ ያለመቃብር
- ቤትን ቤት ወይም ክብር የሚያስገኝለት አጥር ነውና አጥር መከበሪያ ነው

ቤት ያለአጥር፣ ሰው ያለ ልብስ
- ሰው ያለልብስ ክብር የለውም። ነውሩን መሸፈን ይገባዋል

ቤት ያለአጥር፣ ቤተክርስቲያን ያለቅጥር
- ለቤተክርስቲያን ቅጥር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው

ብላ ቢለኝ፣ እንደ አባቴ ሰቆመጠኝ
- እንደነሱ ሆኜ ብኖር ይሻለኝ ነበር



ብላ የበሰለ፣ ተናገር የመሰለ
- አሳማኝ የሆነ ነገር ተናገር

ብላ ያለው ቀርቦ፣ ተሸከም ያለው ተሰብስቦ ይቆየዋል
- ሁሉም እንደየዕጣ ፈንታው ነው

ብልህና ቅባት፣ ብረሃንና መብራት
- ብልህም ብርሃንም ቀና ናቸው

ብልህን ማሞኘት፣ ቂምን ማቆየት
- ብልህን ማሞኘት ትርፉ ቂም ነው

ብልህን አይረቱ፣ ከአጥፊ አይዘምቱ
- ብልህን መርታት አስቸጋሪ ነው

ብልህ የዓመቱን፣ ሞኝ የዕለቱን ያስባል
- ብልህ አርቆ ያስባል

ብልጥ ለብልጥ፣ ዓይን ብልጥጥ
- እባብ ለእባብ፣ ይተያያል ካብ ለካብ

ብልጥ ልጅ የሰጡትን እየበላ ያለቅሳል
- የተገኘውን ይዞ በዚያ ማዝገም ይበጃል

ብልጥ ሰው፣ ይታወቅበት አይመስለው
- አንዳንዱ ያለእኔ ብልጥ የለም ይላል

ብልጥና ምስጥ፣ ውስጥ ለውስጥ
- ውስጥ ውስጡን የሚሠራ
- የጭቃ ውስጥ እሾህ

ብልጥ ዐይን፣ አስቀድሞ ያለቅሳል
- ብልጥ ሰው በከንፈሩ ይሥቃል

ብልጥ እይጥ ከባለቤት፣ እኩል ስትበላ ትኖራለች
- ብልጥ ሰው ሳይነቃበት አብሮ ይኖራል

ብልጥ ጓደኛ የሰዎቹን የጋራዬ፣ የራሱን የብቻዬ
- ከሰዎቹ ይጠቀማል የራሱን ግን አይሰጥም

ብሉ ብሉ የዶሮ አንገት፣ ከማለሮ
- መጨረሻው ያው ነው፣ የማይቀር ነው

ብመታው ሰደበኝ
- አጠፈታ መመሰስ

ብረት ለብረት ሲፋጭ፣ ሰለት ይወጣዋል
- መመካከር ከጥሩ ነገር ላይ ያደርሳል

ብረት ሲግል ቀጥቅጠው፣ ንፋግ ሲወድ መጥምጠው
- በዘዴ ቀስ እያልክ ገንዘቡን ውሰድ

ብረት ብረትን ይሠራዋል፣ ዕውር በሰው ይመራል
- ሰውን ሰው ያስተካክለዋል

ብረት ብረትን ይስላል
- ሰውን ሰው ያስተካክለዋል

ብረትን መቀጥቀጥ እንደጋለ ነው
- አንድን ነገር በጊዜው በወቅቱ መፈጸም መልካም ነው

ብረት ካልፈላ፣ አይላላ
- አንድ ነገር ለመሥራት ስልት፣ ዘዴ ያስፈልጋል

ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ
- በግ ከበረረ ፍየል ከቀዘነ መመለሻ የለውም

ብርቅና ድንቅ፣ ያለ አንድ ቀን አይደምቅ
- ጉድ አንድ ሰሞን ነው

ብርና ወርቅ፣ ያምራሉ ግን ሰው ያጣላሉ
- ገንዘብ ሰው ያጣላል

ብርድ ቆላ ወረደ፣ ልጅ አባቱን ወደደ
- መልካሙን ሁሉ እንዲያደርግለት

ብርድ ምን ያመጣል ከማንቀጥቀጥ፣ በቀር
- ያው የሚታወቅ ነው

ብቅ ብቅ እንደ፣ ሥንዴ ምርቅ
- ልታይ ልታይ ማለት

ብቸኩል ያንችንም፣ የኔንም በላሁ
- የወደደ መሳይ

ብቻውን የሚሮጥ፣ የሚቀድመው የለም
- እህያ ጩኸቱን ያደንቃል

ብቻውን የሚሟገት፣ የሚረታው የለም
- ከንቱ ድካም

ብቻውን የበላ፣ ብቻውን ይሞታል
- ማሕበራዊ ኑሮን አያውቅ

ብነጨው ፈቴን፣ ብመታው ደረቴን
- ራሴን ጎዳሁ እንጂ ያገኘሁት ፋይዳ የለም

ብንከባለል መንገዴ፣ ጣለኝ ከወንበዴ
- እግር ወስዶ አንዳች ነገር ላይ ይጥላል

ብዙ ሀብት፣ ያመጣል ብዙ ጠላት
- ሲያገኙ ጠላት መፈጠሩ አይቀርም

ብዙ መሳም፣ ልብ አይነካም
- በወረት ሲሆን ይሻላል

ብዙ መናገር፣ ምላስን ያስለቻል
- መዘብዘብ አዳማጩንም ያስለቻል

ብዙ ሰው ሲበላ፣ አንድ ሰው ይጣላ
- አንዱ ለሌሎች ብሎ ችግር ውስጥ ይወድቃል

ብዙ ስንቅ የሚሸከም፣ ሳይበላ ይወድቃል
- የሚበሉት ሌሎች በመሆናቸው እሱን የተረፈው ሸክም ብቻ ነው

ብዙ፣ ቢተቹ ይሰለቹ
- ነገር ቢበዛ በእህያ አይጫንም

ብዙ ቢወልዱ፣ ሙያውን ዓይተው አንዱን ይወዱ
- የእናት ሆድ ዥንጉርጉር

ብዙ ቢያወጉ፣ ይዘነጉ
- ብዙ የሚያወራ ሰው ወሬውን ለማን እንኳ እንዳወራ ይዘነጋል

ብዙ ቢልት፣ ያፈርሳል ጎበረት
- ቀልድና ቅዘን ቤት ያጠፉል



ብዙ ቸርነት፣ ያመጣል ድህነት
- ያለውን አሟጦ ከቸረ ነገን በምን ይኖራል

ብዙ ዕውር ዐየሁ፣ እንዳንቺ የፈሰሰ የለም
- ከዕውራን ሁሉ ያንቺ ዐይን የተለየ ነው

ብዙ ከመናገር፣ ማዳመጥ ይበልጣል
- የነገር ወጡ ማዳመጡ

ብዙ ከማውራት፣ ጥቂት መሥራት
- ከወሬ ተግባር ይበልጣል

ብዙ ከብት ለማርባት፣ አልቅትን ጠብቆ፣ ውኃ ማጠጣት
- እንደ ሥራ ከመሥራትህ በፊት እንቅፋት በሚሆኑት ላይ ጥንቃቄ ውሰድ

ብዙዎች ለብዙ ሲያውቁ፣ ለራሳቸው አይጠነቀቁ
- ሰዎች ሰዎችን ይመክራሉ ለራሳቸው ግን ይቸገራሉ

ብዙዎች ይሰጡሀ፣ ብዙዎች አይጥሉሀ
- ከሰዎች ጋር ተስማምተህ ኑር

ብዙ ዝምታ፣ ይሆናል በሽታ
- ብዙም ዝም ማለት ሐሳብን እለመግለጽ ከችግር ላይ ይጥላል

ብዙ ያይሻል፣ አንዱ ይወድሻል
- ከዚህ ሁሉ ሰው አንድ ለአንቺ የሚሆን አታጪም

ብዛት፣ አይደለም ጥራት
- ከብዛት ይልቅ ጥራት ጠቃሚ ነው

ብጤ፣ ከቢጤው
- ሁሉም ከተመሳሳዩ ጋር ይሄዳል

ብጥለው፣ ገለበጠኝ
- ያሰብኩት ሳይሆን ቀረ

ቧልትና ቅዘን፣ ቤት ያጠፉል
- ብዙ ቀልድ ለችግር ይጋብዛል

ቧልተኛ ሰው፣ እንቱ ሳይባል ያረጃል
- አጭር ሰው አንቱ ሳይባል ያረጃል

## መልመጃ 5 በ

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አሟላ

1. ብቻውን የሚሮጥ __________ ።
ሀ. ይደክማል ሐ. ልኩን አያውቅም
ለ. ዕብድ ነው መ. የሚቀድመው የለም

2. ብላ ቢለኝ __________ በቆመጠኝ
ሀ. እጄን ለ. እግሬን ሐ. አፌን መ. እንደአባቴ

3. ቤት ቢሰሩ የለው ሁሉ __________
ሀ. መጠቀሚያ ሐ. መናኸሪያ
ለ. ተሰፋ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

4. ቤት በማገር __________ በባላገር
ሀ. ሹም ለ. ባላባት ሐ. ዳኛ መ. ንጉሥ

5. በእናት ላይ ሞግዚት __________
ሀ. ከንቱ ልፋት ሐ. በገዛ ራስ ጥቃት
ለ. በራት ላይ ዳረጎት መ. በራስ ላይ ጥፋት

6. __________ ኮርቻ
ሀ. በቅሎ ሳይገዙ ሐ. ሆድ ሳይሞሉ
ለ. ለጌጥ ብቻ መ. መልሱ የለም

7. __________ መቃብር ይሞቃል
ሀ. ኑሮ ካሉት ሐ. ቤት ካሉት
ለ. ይሁን ካሉት መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

8. በዕውር ይጠቃቀሱበታል __________
ሀ. በደንቆሮ ያመለክቱበታል ሐ. በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል
ለ. በዲዳ ይንሾካሾኩበታል መ. በዲዳ ይጠራሩበታል

9. __________ ጅብን ነገረኛ ያደርጋሉ
ሀ. በራቸውን ሳይዘጉ ሐ. በጭለማ እየሔዱ
ለ. አህያቸውን ውጭ እያሰሩ መ. አጥራቸውን ሳያጠብቁ

10. __________ ለውን ሌባ ይላሉ
ሀ. ፊለፊት አለቀምጠው ሐ. አጥራቸውን ሳያጠብቁ
ለ. በራቸውን ከፍተው መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

11. __________ ቢወጋ ምንቸት
ሀ. ቢሠራ ቅርጫት ሐ. ቢገዛ ማረሻ
ለ. ቢዘል ማጀት መ. ቢሠራ ጋን



12. በሬና በሬ መከሩ __________
ሀ. ቀንበር ሰበሩ ሐ. ወደቁ ካፈሩ
ለ. አገር ጥለው በረሩ መ. ዱር ገብተው አደሩ

13. በአህያ ቆዳ የተሠራ ቤት __________
ሀ. ይፈርሳል እንደዘበት
ለ. ይበታተናል ጅብ የጮኸለት
ሐ. አይቆይም ዓመት
መ. ይበሰብሳል ዝናብ የጣለለት

14. በቤቷ ቀጋ __________
ሀ. በውጭ አልጋ ሐ. በውጭ ታላጋ
ለ. በውጭ ባለአልጋ መ. በውጭ ባለጸጋ

15. ባቄላ አለቀ ቢለው __________
ሀ. ፊበ ቀለለ ሐ. ደበ አለው
ለ. አሳዘነው መ. መልሱ የለም

16. በጊዜ የገባ እንግዳ __________
ሀ. እይሆንም ዕዳ ሐ. ይገባል ጓዳ
ለ. እራቱ ፍሪዳ መ. እንቅልፍ ይሆት ጥርግ

17. በጥባጭ ካለ __________
ሀ. ተቃለለ ሐ. ማን ጥሩ ይጠጣል
ለ. ተንከባለለ መ. ድፍርስ ውኃ አለ

18. ባለጌ ባለሟል __________
ሀ. ልብስ ገልቤ ልይ ይላል ሐ. ታላቁን ይነቅፋል
ለ. ታናሹን ይኮረኩማል መ. አባቱን ይሰድባል

19. በኋላ የመጣ __________
ሀ. ሀይን አወጣ ሐ. ተኮፈሰ
ለ. እጅ ይሆ አሰወጣ መ. መልሱ የለም

20. ቧልትና ቅዘን __________
ሀ. ቤት ያጠፋል ሐ. ቤት ያበላሻል
ለ. ቤት ያገማል መ. ሁሉም መልስ ነው

21. በልጅ አመኻኝቶ __________
ሀ. ይሔዳል ለንብቶ ሐ. መቼ ተገምቶ
ለ. ይበላል አንጉቶ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

22. ቢከፍቱት ________
ሀ. ተልባ ለ. ወተት ሐ. ባዶ መ. መልሱ የለም

23. በፊት የወጣ ጆሮን ________
ሀ. አስቀረው ፎክሮ
ለ. በኋላ የወጣ ቀንድ በለጠው
ሐ. በኋላ የወጣ ጭራ በለጠው
መ. መልሱ የለም

24. ባልና ሚስት ሲተዋወቅ ________
ሀ. ማን ያፈጸጽም
ለ. የሥርገኛ ልቡ ይወልቅ
ሐ. መተናነቅ
መ. ሁሉም መልስ ነው

25. በፈረስ የፈለጉት ________
ሀ. በእግር ይገኛል
ለ. ሔደው አገኙት
ሐ. ቶሎ አገኙት
መ. ምንም ሊገኝ አልቻለም

26. ባላደራ ________
ሀ. ጨኸ በተራራ
ለ. ቆመ በተራራ
ሐ. ሆነ ጭራ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

27. በትር ከጅህ ________
ሀ. ማንም ይፈራሃል
ለ. እባብ ተግርህ
ሐ. ማን ሊጠጋህ
መ. መልሱ የለም

28. በውኘ ሆድ ________
ሀ. ቅልጥም አያድርም
ለ. ሥጋ አያድርም
ሐ. ቅቤ አያድርም
መ. ሁሉም መልስ ነው

29. ቢልተኛ ሰው ________
ሀ. አስቂኝ ነው
ለ. ያስለቻል
ሐ. አንቱ ሳይባል ያረጃል
መ. ይከበራል

30. ቤት ከነጉልላቱ ________ ከነማዘንቱ
ሀ. ወለሉ ለ. ቋሚው ሐ. ማገሩ መ. ምድጃ

31. ቤት ያለአጥር ሰው ________
ሀ. አለትዳር
ለ. ያለሥራ
ሐ. ያለልብስ
መ. ሁሉም መልስ ነው

32. ብዙ ከማውራት ________
ሀ. ትንሽ መለመን
ለ. ቆሞ መጠበቅ
ሐ. ትንሽ ማውራት
መ. ጥቂት መሥራት

33. ብላ ያለው ቀርቦ ________ ያለው ተሰብስቦ ይቆየዋል
ሀ. ይለፍልሀ ለ. ተሸከም ሐ. አትሸከም መ. ዕድል



34. ቤትን መመሥረት ________ እንጀት
ሀ. በአህያ ለ. በባላገር ሐ. በውሻ መ. በከተሜ

35. ብልህን አይመክሩ ________
ሀ. ከአጥፊ አይዘምቱ
ለ. አንበሳን ብድር አይጠይቁ
ሐ. ለነብር አያበድሩ
መ. መልሱ የለም

36. ብረት ብረትን ይስላል ________ በሰው ይመራል
ሀ. ሞኝ
ለ. ባላገር
ሐ. ዕውር
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

37. ብረት ________ አይላላ
ሀ. ካልተቀጠቀጠ
ለ. ካልፈላ
ሐ. አለመሟሪያ
መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

38. ብቅ ብቅ እንደ ________
ሀ. ጋለሞታ
ለ. ቆንጆ ሴት
ሐ. ሥንዴ ምርቅ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

39. ብቸኩል ________ በላሁ
ሀ. የሁሉንም
ለ. የእህቴን
ሐ. የወንድሜን
መ. ያንችንም የኔንም

40. ብዛት ________ ጥራት
ሀ. ይሆናል ለ. አይሆንም ሐ. ካለ መ. መልሱ የለም

## መልመጃ 5

ለ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ስጥ

1. በሬ ያርማል አህያ ምርቱን ያፍሳል
ሀ. ለፍቅር ብተኛት፣ ለጠብ አረገዘች
ለ. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን
ሐ. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ
መ. በሚያዚያ ጎመን የዘራ ክረምቱን ሁሉ በላ

2. በሬ ሆይ ሣሩን እየህና ገደሉን ሳታይ ገደል ገባህ ወይ
ሀ. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል
ለ. እጅማም ስለት ይቀዳል እፎት
ሐ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
መ. መልሱ የለም

3. ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም
ሀ. ባለቤት ያቀለለውን እሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም
ለ. መታፈር በክንፈር
ሐ. ካፍ የወጣ አፋፍ
መ. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

4. ባልንጀራ ቢያጠቃው ወደሚስቱ ሮጠ
ሀ. እህያውን ፈርቶ ዳውላውን
ለ. እህያ በበላ ዳዋ ተመታ
ሐ. የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

5. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
ሀ. እንኳን ዘንቦብሽ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
ለ. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

6. ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ
ሀ. ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች
ለ. ያሳደግሁት ውሻ ነከሰኝ
ሐ. እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
መ. ሁሉም መልስ ነው

7. በግዛ እራሱ እባብ ጠመጠመ
ሀ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ለ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሐ. ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል፣ የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
መ. ሁሉም መልስ ነው

8. በሞኝ ክምር ዝንጀሮ ልጇን ትዳር
ሀ. ብልጦች በሞኝ ንብረት ይጠቀማሉ
ለ. በሞኝ ክንድ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበታል
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

9. ብዙ ዝምታ፣ ይሆናል በሽታ
ሀ. ዝም አይነቅዝም
ለ. ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም
ሐ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም
መ. ዝምታና በሽታ ብዙ ናቸው



10. በግ ባልበላሽ ትበይኝ
ሀ. አህያ ወደ ጅብ ለቅሶ ሔደች
ለ. ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ
ሐ. እሳት ቢያንቀላፉ፣ ገለባ ጎበኘው
መ. ሁሉም መልስ ነው

11. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ
ሀ. በልጅ አመካኝቶ ይበሏል እንጉቶ
ለ. ሰው በካሕን፣ በላተኛው ማይም
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

12. በቅሎ እናቴ እናቴ ይላል፣ ፈረስ ግን ግድ የለውም
ሀ. ራስ ሳይጠና ጉተና
ለ. ግዛኝ ግዛኝ ብለው ሊሸጡኝ አሰቡኝ
ሐ. በቡሀ ላይ ቆረቆር
መ. መልሱ የለም

13. በቅሎ ለኮዋን በጠሰች በራሷ አሳጠረች
ሀ. ዳባ ራሱን ስለት ድግሱን
ለ. ሥራ ለሠሪው፣ እሾሀ ላጣሪው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

14. በቡሃ ላይ ቆረቆር
ሀ. እምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
ለ. የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
ሐ ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሉ የለም

15. በርበሬ በገዛ እጅ ገዝቶ ይፋጃል
ሀ. እህል ላበደረ ዐፈር፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር
ለ. ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ
ሐ. ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ፣ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
መ. ሁሉም መልስ ነው

## መልመጃ 5

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ብዙ ከመናገር ማዳመጥ ይበልጣል | ሀ. | አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ |
| 2. | ቤት ያለ ሴት ከብት ያለበረት | ለ. | በሬ ያርሳል፣ አህያ ምርቱን ያፍሳል |
| 3. | በልተው ከጨረሱ ከመኝታ ይነሱ | ሐ. | በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም |
| 4. | በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ | መ. | ለሂያጅ የለውም ወዳጅ |
| 5. | ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም | ሠ. | አቤቷ ዐመሏ መጥፎ፣ ውጪ ግን ጥሩ መሳይ |
| 6. | ብልጥ ለብልጥ፣ ዐይን ብልጥጥ | ረ. | የነገር ወጡ ማዳመጡ |
| 7. | በወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል | ሰ. | በአንድ ራስ ሁለት ምላስ |
| 8. | ባንድ ወፍ ሁለት አፍ | ሸ. | ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ |
| 9. | በቤቷ ቀጋ በዱር አልጋ | ቀ. | እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለሴት |
| 10. | በጣይ ቅቤ አያበሩበትም | በ. | በዕውር ቢፈርዱ፣ ዕውር ይወልዱ |
| 11. | በደንበሯ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ | ተ. | ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይመቱ |
| 12. | በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቡበታል | ቸ. | የተከፋ ተደፋ |
| 13. | በቤት ይለምዱታል፣ ባደባባይ ይደግሙታል | ኀ. | ጉድ አንድ ሰሞን ነው |
| 14. | ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ | ነ. | ሰም ይወጣ ከቤት ይከተል ጎረቤት |
| 15. | ብሰጭት የሚጎዳው ባለቤቱን ነው | ኘ. | እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ |
| 16. | ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ | አ. | ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል |
| 17. | በችኮላ ያፈቀሩት፣ በችኮላ ተጣሉት | ከ. | የአፍ ዘመድ ከነበያም አይገድ |
| 18 | በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ አሞሌ ላይገዙ | ኸ. | በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው |
| 19. | ብርቅና ድንቅ ያለአንድ ቀን አይደምቅ | ወ. | ዘም አይነትዘም |



## <u>ተ</u>

ተሁለት ዛፍ የወደቀ
- ያልተሳካለት

ተሁሉም ያው ወንድም፣ ቢከፋም ቢበጅም
- ለጥቃት ከወንድም የሚበልጥ የለም

ተለመደና ዶሮ መከሽከሽ፣ እኝህ እናትሽ ሐሙስ ሐሙስ ከች
- የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጣጣ

ተለማማጭ፣ አልማጭ
- ሥራ የማይወድ ልምምጥን ያዘወትራል

ተለማበት፣ የተጋባበት
- ከዋነኛው የሌላኛው በልጦ ታየ

ተለጣጭ፣ የጎረቤቷን ድልህ አሚጣጭ
- የራሷን አኑራ የሌላውን ማጫረስ

ተላም የዋለ በሬ፣ ተሴት የዋለ ገበሬ
- መደበኛ ሥራውን ይዘነጋል

ተሌባ ሌባ ቢሰርቀው፣ ምን ይደንቀው
- ከለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ

ተልባ መሰሎሽ፣ ሰናፍጭ ትቀምሽ
- ጥሩ መስሎሽ ጥሩ ያልሆነ አጋጠመሽ

ተልባ በቅባኑግ፣ ለበሚው ግራ፣ ለበይው መልካም
- በሁለት ወገን የቀረበ ድጋፍ አስደሳች ነው

ተልባ በጥባጭ እያለች፣ ጎመን ቀንጣሽ ምች መታት
- ነገሩ የሚመለከተው ሰው እያለ የማይመለከተው ሰው ችግር ውስጥ ገባ

ተልባ ቢንጫጫ፣ በአንድ ሙቀጫ
- ድር ቢያብር አንበሳ አያሰር

ተመልከት ዓላማህን፣ ተከተል አለቃህን
- ቆራጥ ሰው ሁን

ተመልከኛ ዳኛ፣ መልካም ፈራጅ
- ፍትሕ የሚያውቅ ትክክለኛ ፍርድን ይሰጣል

ተመመራመር፣ ይገኛል ቁም ነገር
- ከመመራመር ዕውቀት ይገኛል

ተሞሞት ይሻላል መሰንበት
- ከጊዜ ብዛት ሊያልፍልህ ሥለሚችል መቆየት ደግ ነው

ተመምሩ፣ ደቀመዝሙሩ
- ከዋናው ተከታዩ በልጦ ታየ

ተመረቅሁ ብለህ፣ ተተረገመ ጋር አትዋል
- ጓደኛ አጥፊ ነውና መጥፎ ባህርይ እንዳያወርስህ ተጠንቀቅ

ተመሮጥ፣ ይሻላል ማንጋጠጥ
- ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም

ተመንግሥት አመልጣለሁ፣ ከሞት እድናለሁ ማለት ዘበት ነው
- የጊዜ ጉዳይ እንጂ ሞት እንደሁ የማይቀር ነው

ተመክሮ ልብ ተሸምቶ፣ ድልብ አይሆንም
- ያው ነህ ቢመክሩህም አትሰማም

ተመዋረድ፣ ጌታን መውደድ
- ጌታውን ያመነና ከመጥፎ ሥራ የራቀ ይወደዳል

ተማሪና ዶሮ በሞቱ ክቡር ነው፣ በቁመናው ራቱ ጥሬ ነው
- በሕይወት እያስ የማይከበር ሰው ከሞተ በኋላ ክብሩ ይነገርስታል

ተማሪ፣ ውሻ ቀባሪ
- የቆሎ ተማሪ ውሻን ስለማይወድ፣ ሁሌ እንደተጣሉ ነውና ነው

ተማሪ፣ ዘኬ ለቃሚ
- የቆሎ ተማሪ ከቤተክርስቲያን ግቢ ከደጀሰላም ምግቡን ያገኛል

ተማክሮ የፈሱት፣ ፈስ አይገማም
- ተስማምተው ያደረጉት ነገር ጉዳት እንኳን ቢኖረው አይቆጭም

ተምሮ የማይጽፍ፣ አከፍሎ የማይገድፍ
- የተማረውን ተግባራዊ የማያደርግ ከተማረ አይቆጠርም

ተምሮ ያላስማረ፣ ዘርቶ ያላጠረ
- የጋን መብራት

ተሞተች ሚስቴ፣ ምን አለኝ ካማቴ
- ግንኙነታችን፣ ዝምድናችን ተቋርጧል

ተሚጋች እኔ እረታ ይመበለኛል፣ ሰውም ይመለከተኛል
- የሚሚገት ሰው እሱ የሚረታ እንጂ ሌላ ሰው የሚረታ አይመበለውም

ተረታን እንዳይሉ ይግባኝ እንዳይሉ
- መረታታቸውን እንዳይታወቅባቸው ይግግባኝ ጥያቄ አያቀርቡም

ተረቴን መልስ አፌን በዳቦ አብስ
- የተረተረት የመጨረሻ እባባል ነው

ተረት ለነገር፣ ይሆናል መሠረት
- ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ

ተራራ ለጥናት፣ ውኃ ለጥማት
- በፈለከው ጊዜ ያገኘኸው ነገር ያረካሃል

ተራስ በላይ፣ ነፋስ
- ቅድሚያ ለራሴ

ተራጋሚ፣ ራሱን ደርጋሚ
- ሰውን ሲረግም ርግማኑ ተመልሶ ራሱን ያጎዳዋል

ተርቦ ያወጡት ደሞዝ፣ ለመደኛ አይሆንም
- ሳይርቅ በቅርቡ፣ ሳይደርቅ በርጥቡ

ተርጅና ተሞት፣ ቢሸሹ አያመልጡ
- የማይቀርን ነገር እያወቁ መዘናጋት አይገባም



ተሰብሮ ቢጠገን፣ እንደነብር አይኮን
- ሙሉ በሙሉ እንደበፊቱ ሊሆን አይችልም

ተሰው ተመርጦ፣ ለሹመት፣ ተንጨት ተመርጦ ለታቦት
- ከሰው ተመርጦ ለሹመት ይበቃል

ተሰውጋ አለሁ ብዬ፣ ተጅብ ተዳብዬ
- ከክፉ ሰው ጋር ነው ያለሁት

ተሰግዳዳ ቦታ፣ ታዳጊ ጌታ
- ዘወር ካለ ቦታ ከመደበቅ ለአንድ ታዳጊ ጌታ ሎሌ መሆን ይመረጣል

ተሳዳቢ ጥርስ፣ ነጭ ነው
- ተሳዳቢ ሰው ምን ይለኛልን አያውቅም

ተሴትን ትበሱ፣ ትመልሱ
- ሁኔታን ተመልክቶ ለባሰበት መልሰው ይስጡታል

ተሰበታም አንድ ያንቀው፣ አንድ ይወድቀው
- ስሰበታታ ምንም ቢሆን በሰስተው ነገር አይጠቀምም

ተስፋ መስጠት፣ እያዩ ዕዳ መግባት
- ካፍ የወጣ ቃል ከእጅ የወደቀ እንቁላል

ተስፋ ቆርጦ አንድ ላይ ከመቆም፣ ይሻላል በተስፋ ሲጓዙ መክረም
- ጥረት መጣር እንጂ ተስፋ መቁረጥ አይገባም

ተስፋ ያልቆረጠ መነኩሴ፣ ምናኔ ሲሔድ ሴቲቱን ይሰናበታል
- አልቆረጠም ሁኔታው ያስታውቅበታል

ተስፋ ያድናል፣ ክህደት ያመነምናል
- ሕሊና ከፍተኛ ዳኛ በመሆኑ፣ የከሃዲ ሕሊና ከሃዲን ይፈታተነዋል

ተሸፋፍነው ቢተኙ፣ ገልጦ የሚያይ ዓምላክ አለ
- የተሸፋፈነ ሥራ አንድ ቀን መጋለጡ አይቀርም

ተሹም ከመታለል፣ ጥሎ መኮብለል
- በሰው ተመርቶ ስሕተት ላይ ከመውደቅ እርግፍ አድርጎ ሁሉን መተው

ተሻገር ከወንዙ፣ ጉድ እንዳያበዙ
- ያልሆኑ ሐሳቦች እንዳይስነዘሩብህ ትክክል ነው በምትለው መንገድ ሒድ

ተቀመጥ በወንበሬ፣ ተናገር በከንፈሬ
- ሥልጣን ተሰጥቶሃል እንደፈለክ ሁን

ተቀማጭ፣ አፉ ምላጭ
- ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው

ተቀማጭ የሌለው ተሚጋች፣ ስልቻ የሌለው ቢጋች
- ስክፉ ጊዜ የሚሆን ገንዘብ ቆጥበህ ማስቀመጥ አስብህ

ተቀምጠው የሰቀሉት፣ ቁመው ለማውረድ ያስቸግራል
- ቀላል መስሎ የታየ ነገር በኋላ ላይ ሊከብድ ይችላል

ተቀምጦ ከመላከ፣ ተነስቶ መሥራት
- መሥራት እየቻልክ ሌላ ሰው ማስቸገር አይገባም

ተቀባሬ ወዲያ፣ ማን ያርዳ
- ጉዳዩን ካየው ሰው በላይ ማን ይናገር

ተቂመቱ ማጠር፣ የልቡ መጠርጠር
- ተጠራጣሪ ሰው ነው ማንንም አያምንም

ተቁም ዶሮ፣ ከሽከላ ማስሮ
- ምንም የሌለው ድሃ ምስኪን

ተቂል አትጫወት፣ ዐይንህን ያወጣሃል በዕንጨት
- ሞኝ ሰው ፊት ካሳዩት ጭንቅላትህ ላይ ይወጣል

ተቅበላ ጥጋብ፣ የስቅለት ጦም ማደር ይሻላል
- ጥጋብ ብዙ አላስፈላጊ ሥራዎችን ያሠራል

ተቆብ ላይ ሚዶ
- መሆን የማይገባው ቦታ ላይ ማድረግ

ተበድሮ ቅቤ፣ ታርዞ ጎፈሬ
- መበደር አላስፈላጊ ነው

ተባለ ቀትር አትቀታተር
- ከባለ ጊዜ ጋር አትጨቃጨቅ ችግር ላይ ትወድቃለህ

ተባቄላ አይጠፋ ዲቃላ፣ ከጠላ አይታጣ አተላ
- ከደጎች መካከል ክፉ አይጠፉም

ተተላለ የማይበርድ፣ ተታዘለ የማይወርድ
- በሰው ትከሻ የሚኖር ችግር አይሰማውም

ተተናገረ አያባራ አፉቸው፣ ከያዘ አይለቅ ምንቸታቸው
- አፋቸው መናገር ከጀመረ አያባሩም

ተተናገረ አያባራ አፉቸው፣ ከያዘ አይለቅ እጃቸው
- ማውራት የሚወዱ ናቸው

ተተያዙ፣ ብዙ ነው መዘዙ
- መጠንቀቅ ነው እንጂ ከተያዝክ መላቀቅ አይቻልም

ተተያዙ ወዲያ ቄስ ጥሩልኝ ማለት ሳያደላድሉ በሺ ብር ጭነት
- ፊቱን ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ

ተቃመሙ መክሳት፣ ካቡ መንጣት
- ሰው ኑሮውን ይመስላል

ተነስቶ የሚንቀኝና ፣ ቁጭ ብሎ የሚያከብረኝን ሀውቃለሁ
- አክብሮቱንም ሽንገላውንም ለይቼ እረዳለሁ

ተናት፣ ቀን ይሻላል
- ጊዜ ከከዳህ ኑሮ አስቸጋሪ ነው የሚሆንብህ

ተናካሽ ውሻህን፣ ተዋጊ በሬህን እሰር
- ኃይለኛን ውሻን ማሰር ተገቢ ነው ያለበለዚያ ጉድ ያደርግሃል

ተናካሽ ውሻ፣ የጅብ መቋደሻ
- እልህ ምላጭ ያስውጣል



ተናዞ ይሞቷል፣ አምኖ ይሟገቷል
- ሰው በሚከራከርበት ጉዳይ ላይ ሙሉ እምነትና ማስረጃ ሊኖረው ይገባል

ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በወንበሬ
- እንደኔ ሁነህ ትምህርቱን አስተምር ማለት ነው

ተናግሮ አናገረኝ ይወደኝ ይመስል፣ ሔዶ ተናገረ የሳኩት ይመስል
- ጥሩ ሰው መስሎኝ ያጫወትኩትን ለሌላ ሰው አሳልፎ ተናገረ

ተናግሮ ከመጨነቅ፣ የቀልቀሎዬን አፉን እንቅ
- ዝም አይነቅዝም

ተናግሮ ከማስብ፣ ከንፈርን መሰብሰብ
- ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም

ተናግሮ ያጣ ሰው፣ ሦስት ጊዜ ሞቱ ነው
- ጠይቆ ማጣት ያስቆጫል

ተንከትክተሽ ሥትሥቂ፣ የጥርስሽ ወገብ እንዳይቀጭ
- ያማረልሽ መስሎሽ፣ ስትገለፍጪ ሌላ ጉዳት እንዳያስከትልብሽ

ተንኮለኛ በመበለት፣ በጦም ዶሮ፣ በፋሲካ እልበት
- ተው እንዳይሆን - ተቃራኒ ሥራን መፈጸም

ተንኮለኛ፣ ተሰባብሮ ተኛ
- ተንኮል እራስን ያጠፋል

ተንኮለኛ ናቸው፣ አርቃችሁ ቅበሯቸው
- ተንኮለኛን ማራቅ ያስፈልጋል

ተንኮለኛ፣ የሰይጣን እርበኛ
- ተንኮለኛ ሰውን በመጉዳት በማጥፋት ይረካል

ተንኮለኛ ገደል፣ ዝንጀሮን ይጥላል፣ በሬን ያሳልፋል
- ማደናገር ይችልበታል

ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
- በትክክል ያልተሠራ ሥራ ተመልሶ እንቅፋት ይሆናል

ተንጋሎ የተፉ፣ ከራሱ ከፋ
- በትክክል ያልተሠራ ሥራ ተመልሶ እንቅፋት ይሆናል

ተኛ ወዲያ ጎራሽ፣ እህል አበላሽ
- እራስን ከፍ ከፍ ማድረግ

ተኝ ብልሽ፣ አትነሺ አልኩሽ
- የምነግርሽን በትክክል ፈጽሚ

ተከበሩ፣ ሰው አይፈሩ
- የጠገበ ሰው ልቡ ድፍን ነው

ተኩብሮ ያደርጋል ደንቆሮ
- ሀብት ያለው ሰው ሀብቱን ብቻ ስለሚመለከት ለዕውቀት ግድ የለውም

ተኩብት እንስት፣ ከሀብት ርስት
- እንስት ከብትና ርስት ሀብትን በላይ በላዩ እንዲጨምር ያደርጋሉ

ተከናንቦ የሚበላውን፣ አጎንብሰህ ግባበት
- በግብግብ ሰውን በዘዴ ተጠቀምበት

ተከፈት ያለው ጉሮሮ፣ ጦም አያድርም
- እግዜር የከፈታትን ጉረሮ ሳይደፍናት አያድርም

ተኩላ እንደ አንበሳ፣ እጮሀ ብላ ተተረተረች
- ያለአቅም መንጠራራት ጥሩ አይደለም

ተኩላ፣ ፍየል በላ
- ተኩላ የፍየል ጠር ነው

ተከፉ ተወልጄ፣ በፈጭ አደርኩ
- ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል፣ ሲያለቅስ ይኖራል

ተከፉ ጎረቤት፣ አይሠሩም ደህና ቤት
- ተከፉ ጎሬቤት ጋር ሁሌ ሰላም የለም

ተኩሶ ማለ፣ ወጋ ነቀለ
- ግዳጁን ተወጣ

ተኳሽ በሁለት ዐይኑ አያነጣጥርም
- ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም

ተወደዱ ወዲያ፣ ገደሉ ሜዳ
- ፍቅር ዕውር ነው

ተወገብ በላይ ታቦት፣ ከወገብ በታች ጣዖት
- ሰው መሳይ በሸንጎ

ተወገብ በላይ ጥጋብ፣ ተወገብ በታች ራብ
- እየራበው እንዳልተራበ ዓይነት ሆኖ ያስመስላል

ተወጭት አፍ፣ የወንጭት አፋፍ
- ከአንዱ ሌላኛው እስፈሪ ነው

ተዋቅሶ ወዳጅነት፣ የቂም ጠባሳ ባንገት
- ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ

ተዋጊ በሬ፣ ተጭድ ይጣላል
- ከማይጣሉት ጋር አትጣላ፣ አትጋጭ

ተው አትርባ፣ ተሠርቶልሃል የሳት ገባ
- መልካም ሥራ ሥራ ያለበለዚያ ክፉ ሥራህ ሲያል ይከትሃል

ተው ፈረሴ ለጉምና ለሴት አይዘነጉም
- በሴት ተማምነህ ከተዘናጋህ ችግር ውስጥ ትወድቃለህና አትዘናጋ

ተዝካር ያየ ተማሪ፣ ሸቀጥ ያየ እጣሪ ዐይን የለውም
- ከሁሉ ነገር በልጦ የሚታየው ያው የራሱ ፍላጎት ብቻ ነው

ተይዛ ትዝፈን ጠጣ
- ያሉበትን ሁኔታ መዘንጋት

ተይ!! ከመለማመጥ፣ እርፎ መቀመጥ
- ፊቱኑ ራስን ከእደጋ መጠበቅ

ተደርቦ መጣላት፣ ሥራ ማጣት
- ተገቢ አይደለም



ተደብቃ ትደንሳለች፣ በሰው ስብሳብ ትወልዳለች
- ግመል ሰርቆ አጎንብሶ

ተዳኛ ተሟግቶ፣ ሳያደማ ተዋግቶ
- መንፈራገጥ ለመሳሳጥ

ተድረው ቢመስሉ፣ የውኃ መንገድ ረሱ
- ዕያወቁ እንዳላወቁ ሆኑ

ተጀመሩ መጨረስ፣ ካረገዱ ማልቀስ
- እንዴ አለመጀመር እንጂ ከጀመሩ ወዲያ ወደኋላ ማለት እጉል ነው

ተጄ በጉንጨ
- የሩቁን ከመመኘት የቅርቡን መጠቀም ይሻላል

ተገናኝተው ሳሉ፣ ምን ጊዜ እንገናኝ ይላሉ
- የሌላውን ጊዜ ሲመኙ በእጃቸው ያለው ያመልጣቸዋል

ተገዳዩ፣ ሟች ይጣደፋል
- ጥሪው ስለደረሰው ይሆናል

ተጋበዙና ብሉ፣ ሃይ በሉ ከልከሉ
- ምግብን አብሮ መብላት፣ ግጭትን ጥልን መከላከል ተገቢ ነው

ተጋፊ ውኃ፣ ሽቅብ ይሔዳል
- ኃይለኛ ሰው አደርጋለሁ ያለውን ያደርጋል

ተግደርዳሪ በለጠብ ሽሮ ተበዳሪ
- ያልሆኑትን ሆኖ ለመታየት መሞከር

ተግደርዳሪ ጦም አዳሪ፣ ቀላዋጭ ቀባጣሪ
- መግደርደር ራስን መጉዳት ነው

ተጎሽ እበት፣ ተንጨት ሽበት
- ተፈጥሮአዊ ሁኔታን መቃወም አይገባም

ተጎንብሶ የሚበላን፣ ተኝተህ ቀላውጠው
- ለማንኛውም ነገር ዘዴና ስልት ያስፈልገዋል

ተጠማኝ ቢስነብት፣ ባለርስት ይሆናል
- የቆየ ከሚስቱ ይወልዳል

ተጠንቀቅ ወደል፣ እንዳትገባ ገደል
- ሁኔታዎችን እያየህ እንጂ ምንም አይነካኝም ብለህ ብዙ አትተማመን

ተጥዶ የማይፈላ፣ ተሹሞ የማይበላ
- ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል

ተጠረኛ፣ በንቅ አይደባልቁ
- የሚሆነው ስለማይታወቅ ጥንቃቄ ያሻል

ተጠጣ የዋለ ጉሬዛ፣ እህል ፈጅቶ ገባ
- ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ መጣች

ተጨንቆ ኩራት፣ ተንጠራርቶ ራት
- በመኩራት ምንም አይገኝም

ተጫውቶ መማረር፣ አለ ጉዳይ መብረር
- ከሁሉ በፊት ሊሆን የሚችለውን መገመት ይገባል

ተፈጣሪ ይበልጣል፣ ቂጠ ጫሪ
- ጊዜያዊ ፍላጎትን በማሟላቱ ብቻ

ተፈጥሮ ሞት፣ ተሾሞ ሽረት
- ሁለቱም የአህያ ጆሮ ናቸው። እኩል በእኩል የሚጠበቁ።

ተፈጥሮን ተመክሮ፣ አይመልሰውም
- አብሮ ያደገውን ባህርይውን መለወጥ አይቻልም

ታለቀ መቆጠብ፣ ተሞተ መንጠብጠብ
- ላለቀ ክረምት፣ ቤት አይሠራም

ታላቁን ነገር እየተመኘሁ፣ ቢከፍቱት ተልባ ሆኜ ቀረሁ
- ያለዕውቀት የሚሆን ነገር የለም

ታላቅ ወንድም፣ እንደአባት ይቆጠራል
- ተተኪ በመሆኑ ኃላፊትን ስለሚረከብ

ታልተናገሩ፣ አይከፈት በሩ
- እሹ ታገኛላችሁ፣ ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል፣ ነው የሚለው መጽሐፍ ቅዱስ

ታልጠገቡ አይዘሉ፣ ታልዘለሉ አይሰበሩ
- ጥጋብ ልብን ይደፍናል

ታሞ ከመማቀቅ፣ አስቀድሞ መጠንቀቅ
- ከችግርህ በፊት መፍትሔ መፈለግ

ታሞ የተነሳ፣ እግዜርን ረሳ
- ችግሩን ረስቶ ጥጋበኛ ሆነ

ታረጁ፣ አይበጁ
- ብዙ ነገሮችን ወደማበላሸቱ ስለሚሔዱ

ታረጁ ወዲያ ጎፈሬ፣ አዝመራ የላተው ገበሬ
- ጊዜው ያለፈበት፤ ብዙም ጠቀሜታ የሌለው

ታርቄ ተመርቄ፣ ታጥቤ ተለቅልቄ
- በሁሉም መልኩ ተስተካክያለሁ

ታርቆ መግት፣ በልቶ ሰሰት
- ላላቀ ነገር መጨነቅ አያስፈልግም

ታላጭ፣ መካሪ ይሻላል
- ከስም አጥፊ ተው አታድርግ የሚል ይከበራል

ታቀበት በረዶ፣ ተቁልቁለት ዘንዶ
- በዚህም በዚያም ኑሮ ያልተሳካለት

ታባ ቁፍር እሸት፣ ተበልቶለት
- ከዚችው ተነስቶላት ምን ሊቀር

ታባቱ የተረፈ፣ ተጠለፈ
- ምንም አልቀረም



ታቦተ ክፉ፣ ዐይነ መልካም
- ምንም እንኳ በአንድ በኩል አስቸጋሪ ቢሆንም በጎ ነገር ደግሞ አያጣም

ታቦት በራሱ፣ ቃጭል በጥርሱ
- ብዙ መሥዋዕትነት የከፈለ

ታከረሩት፣ ይበጠሳል
- ነገርን በልኩ መያዝ መልካም ነው

ታዝበው ሲጠሉህ፣ ታዝበው ይውደዱህ
- በሥራህ ለመወደድ፣ ለመፈቀር ሞክር

ታየው ትመለከተው፣ ትታነቀው ትሞተው
- በነገሩ መመለጥና እስከ መጨረሻው ድረስ መከታተል

ታዳጊ ያለው በግ፣ ላቱን በውጭ ያሳድራል
- መከታ ያለው ሰው ይዘናጋል

ታጉል ጉልበት፣ እዩልኝ ስሙልኝ ማለት
- ምስክር ማበጀቱ ይጠቅማል

ታጉል ጥንቆላ፣ የጨዋ ልጅ መላ
- የጨዋ ልጅ ምክርና ዘዴ የበለጠ ነው

ታጥቀህ ታገል እንዳትንገላታ፣ አስተውለህ ተሟገት እንዳትረታ
- የምታደርገውን በትክክል ዐውቀህና አምነህበት ይሁን

ታጥቦ ጭቃ
- የማይሻሻል

ትለብሰው የላት፣ ትከናነበው አማራት
- እራት የላት ደግሞ ምሳ አማራት

ትላንት ልጄን፣ ዛሬ እናቴን፣ ምን ይበጃል ዘንድሮ፣ አለ አውራ ዶሮ
- የሚበጀውን አምጣልን

ትልቁ ዓሣ፣ ትንሹን ዓሣ ይውጣል
- አንዱ በአንዱ ሕይወት ይኖራል

ትልቅ ብልሃት፣ ለንጉሥ መገዛት
- ሕግን አክብሮ የኖረ ሰው ችግር አይገጥመውም

ትልቅ ጥቃት፣ ለሃምሳ ማጣት
- ምሥጢርን፣ ገመናን ከገለጡ በኋላ ያስመረዳት ትልቅ ሐፍረት ነው

ትልቅ ጦር፣ ባይወጉበት ያስፈራሩበት
- ወገን መመከያ ነው

ትልና መጋዝ፣ በሽታና ጓዝ
- የማይጠቅምህን ተሸክመህ አትዙር

ትምህርት በልጅነት፣ አበባ በጥቅምት
- ሁሉም በወቅቱ ያምራል

ትምህርት፣ የማያልቅ ምርት
- ዕውቀት የራስ ነው

ትራሱን ከፍ አድርጎ ተኛ
- ደላው የሚያስጨንቀው ነገር የለም

ትርፉን ገልጸህ መከራውን ሳትነግረኝ
- ጥቅሙን እንጂ ውጣ ውረዱን አልገለጽክልኝም

ትሻልን ትቼ፣ ትብሰን አገባሁ
- መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

ትተውት የሚሔዱትን፣ ባልንጀራ አይቅደሙት
- አንዴ የተወሰነ ጉዳይ ማገላበጡ ትርፍ የለውም

ትናንሽ ልጆች፣ ትናንሽ ሀብቶች
- ልጆች ለፊ አገልግሎትና እርዳታ ለቤተሰብ ያበረክታሉ

ትንሣኤ ትንሣኤ ቢሉኝ፣ ጸሎተ ሐሙስ መስሎኝ
- ከትንሣኤ በፊት ጸሎተ ሐሙስ ይመጣልና

ትንሽ ምላጭ፣ አገር ትላጭ
- የናቁት ነገር ይጎዳል

ትንሽ ሰው፣ ትንሽ ነው
- ባለጌ ሁሌም ባለጌ ነው

ትንሽ ሥጋ፣ እንደመሬ ትወጋ
- የሥጋ ዘመድ ሲጠቃ ያንገበግባል

ትንሽ ቆሎ ይዞ፣ ከአሻሮ ተጠጋ
- ትንሽ ቆሎ ያደርሳል ካሻሮ

ትንሽ በመናገር፣ እውነት ትከበር
- ለእውነት ሲባል መናገር ይገባል

ትንሽ፣ አበላሽ
- ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

ትንሽ ጎልማሳ፣ ትቢያ ታነሳ
- ትንሽም ቢሆን ኃይል አለው

ትንሽ ጭላንጭል ታለይዛለች ምንጭር
- በጭላንጭሉ ታግዞ የሚፈልጉትን ማግኘት ያስችላል

ትንቢት ይመራል፣ ልጓም ይገራል
- ምንጊዜም የሰው ልጅ በሕግ ይመራል ሰውን ሕግ ይገራዋል

ትንኝም ለሆዱ፣ ዝሆንም ለሆዱ፣ ተያይዘው ወንዝ ወረዱ
- ለሆዱ የማያስብ የለም

ትዕቢት ከስስት፣ ምን አገናኝቶት
- ሁለቱ ለየቅል ናቸው

ትዕግሥተኛ፣ ከፈለገበት ይደርሳል
- የቻለ ሰው፣ የታገሰ ሰው ዓላማውን ያሳካል

ትዕግስት፣ ፍሬቻ እይደለም
- ባለጌን ሲያከብሩት የፈሩት ይመስለዋል

ትከሻ ሬሳ፣ ደረቁን አስነሳ
- በትርብ የሞተውን ለመቅበር ሲኬድ ሰዎች ያለፉ ለሞቱ ዘመዶቻቸው ያለቅሳሉ



ትጉህ ከአንድ፣ እንጀራ ይጠግባል
- ትጉህ ሥራው በሚገባ ይሳካለታል

ትጸድቅ ትኮነን ቢለው፣ ቆይ መከሬ አስታውቅሃለሁ አለ
- በጎውንና ከፉውን ለይቶ የማያውቅ ንዝህላል

ትፈጭ የነበረች፣ ማንጓለል ተሳናት
- ትልቁን ሥራ መሥራት የምትችለው ትንሿ ሥራ አደከማት

ቶሎ ቶሎ ቢቆጡ፣ አብረው አይቀመጡ
- እንዲያው ከንቱ ልፋት መሆኑ ነው

ቶፋ በማን፣ ምድር ትለፋ
- በሌላው ተቀጥሮ የሚሠራ በየትም ሥፍራ ያገለግላል

## ቸ

ቸር ተመኝ፣ ቸር እንድታገኝ
- መልካም ነገር ተመኝ መልካም ነገር እንድታገኝ

ቸርን ቢያጠቁት፣ ቢስ ይሆናል
- ለጋስን ሁሌ ሲያስቸግሩት ለጋስነቱን ይተወዋል

ቸር ይመጻውታል፣ ጠላት ያጠፋል
- ሥራው ከክፉ ነገር ይጠብቀዋል

ቸኩለው ያፈሱታል፣ ተቀምጠው ይለቅሙታል
- የቸኮለ አፍሶ ለቀመ

ቸኩሉ ከተጠቀመ፣ ዝግ ብሉ የተጎዳ ይሻላል
- ረጋ ብለው የሠሩት ነገር ውጤት አለው

ቻቻታ የለመደ ሰው፣ ዓባይ ዳር ቅበሩኝ ይላል
- ግርግር የለመደ ጸጥታ ቅር ያሰኘዋል

ችኩል ሰው፣ ጠንቋይ ይጠይቃል
- ችኩል የማይሆን ነገር ይፈጽማል

ችኩል ቅቤ ያንቀዋል
- በችኮላ የሚያደርገው ለአደጋ ያጋልጠዋል

ችኩል አደንጓሬ፣ ሳይበሉት ሆድ ያማል
- እንዲያው በሩቁ ችግር ያስፈራራል

ችኩል አፍ፣ ሞትን ይጠራል
- መቸኮል ለአደጋ ያጋልጣል

ችኩል እግር ከዘንዶ፣ ጉድጓድ ይገባል
- ችኩል ሰው ያልተሰበ ችግር ላይ ይወድቃል

ችኮ የጠም ሥጋ
- ሞዛዛ፣ የተሟዘዘ ማለት ነው

ችግረኛ ሲናገር ውሸት፣ ሲደነፋ እውነት
- ችግረኛን ማንም ሐቀኛ አድርጎ አይመለከተውም

ችግር ነው ጌትነት፣ በቅቤ ያስበላል
- አጉል ጥጋብ የማይሠራ ሥራ ያሰራል

ችግርን ለወዳጅ፣ ሲያዋዩት ይቀላል
- የተወያዩበት ነገር መላ አያጣም

ችግር የገፈፈው፣ ውጤቱ ያማረ፣ ካልተንቀባረረ

- ችግር የተወገደለት ሰው ያማረና በውጤቱም የሚረካ ነው

## ኃ

ኃዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ

- ኃዘን ተደራረበብሽ

ኃዘንና ደስታ፣ ጎን ለጎን ናቸው

- ሁልጊዜ ደስታ እንዳለ ኃዘንም መኖሩ ሊያስቡት ይገባል

ኃዘንን የፈራ፣ በደስታ የተጠራ

- ለችግር ጊዜ የሚሆን መፍትሔ አስቀድሞ ማመቻቸት ተገቢ ነው

ኃይለኛ /ተጋፊ/ ውኃ፣ አሸቀበ ይፈሳል

- ኃይለኛ ሰው በግንባሩ ያስታውቃል

ኃይለኛ ዱቄት፣ ከነፋስ ይጣላል

- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

ኃይማኖቱ ተጅማት፣ ጉልበቱ ከብረት የጠና

- ጠንካራ እቋም ያለው ሰው

ኃይማኖት ከግብር ጸሎት ከፍቅር

- የአንድ ሰው እምነትና ጥንካሬ የሚለካው በመልካም ሥራው ነው

ኃይማኖቱ ተጅማት፣ ጉልበቱ ከብረት የጠና

- ጠንካራ እቋም ያለው ሰው

ኃይማኖቱ ከግብር ጸሎት ከፍቅር

- የአንድ ሰው እምነትና ጥንካሬው የሚለካው በመልካም ሥራው ነው

ኃጢያተኛን፣ ኃጢያቱ ያሳድደዋል

- በዳይ ሰው ትክክል እንዳልሆነ የእራሱ ሕሊና ይወቅሰዋል

ኃጢአት ሲደጋገም፣ ጽድቅ ይመስላል

- ውሸት ወይም ሐሰት ሲደጋገም እውነት ወይም ሐቅ ይመስላል

ኃጢአት ሳያበዙ፣ በጊዜ ይጓዙ

- ሞት ላይቀር በጊዜ መጠናቀቂ ይበጃል

ኃጢአት በንሰሐ፣ በደል በካሳ

- ለጨለማ ጊዜ ሙብራት ለመከራ ጊዜ ብለሃት

ኃጢአት በንስሐ፣ እድፍ በውኃ

- ኃጢአት በጸሎት ምህረት ማግኘት እንደሚቻል ልብስ በውኃ ይነጻል

ኃፍረት ያከሳል፣ ያመነምናል

- ይሉኝታ ነፍስን እረፍት ያሳጣል

ኀዳር መግረሪያ፣ ሰኔ መቃጠሪያ

- ሁሉም ጊዜሙን ጠብቆ ይፈጸማል

<u>መልመጃ 6 / ተ፣ ቸ፣ ኃ</u>

ሀ. <u>የሚከተለውን ምሳሊያዊ አነጋገሮችን አሟሉ</u>

1. ________ ተሹሞ የማይበላ
   ሀ. ተከሶ የማይደማ ሐ. ተነጥሮ የማይረጋ
   ለ. ተጥዶ የማይፈላ መ. ተገርፎ የማይተላ



2. ኃዘንና ደስታ ________
   ሀ. ይፈራረቃሉ ሐ. ለየብቻ ናቸው
   ለ. ጎን ለጎን ናቸው መ. መልሱ የለም
3. ኃጢአት በንሰሐ ________
   ሀ. እድፍ በውኃ ሐ. ጽድቅ በኩነኔ
   ለ. በደል በካሳ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
4. ቸር ተመኘ ________ እንድታገኝ
   ሀ. ጠላት ለ. ሲሳይ ሐ. ቸር መ. ቆንጆ
5. ችኩል ________ ያንቀዋል
   ሀ. ሥጋ ለ. ቆሎ ሐ. ሰው መ. ቅቤ
6. ችግር ነው ጌትነት ________ ያስበላል
   ሀ. በሽሮ ለ. በድንች ሐ. በቅቤ መ. ሁሉም መልስ ነው
7. ችኮ ________ ሥጋ
   ሀ. እኛ ለ. የኛኛ ሐ. የጠም መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
8. ተሰው ተመርጦ ለሹመት ________ ።
   ሀ. ተዕጣን መርጦ ለታቦት ሐ. ተሕብስት መርጦ ለታቦት
   ለ. ተንጨት መርጦ ለታቦት መ. ተወይን መርጦ ለታቦት
9. ትለብሰው የላት ________ ።
   ሀ. የምትበላው አላት ሐ. ራት አማራት
   ለ. ትከናነበው አማራት መ. መልሱ የለም
10. ተንጋለው ቢተፉ ________
    ሀ. ለራሱ ከፉ ሐ. ተመልሶ ባፉ
    ለ. የሰው ቀርፋፋ መ. ጠግቦ የተረፈው
11. ተንከትክተሽ ስትሥቂ ________ እንዳይቀጭ
    ሀ. ወገብሽ ለ. አግርሽ ሐ. ጎንሽ መ. የጥርስሽ ወገብ
12. ተኚ ብልሽ ________ አልኩሽ
    ሀ. አንቀላፊ ለ. እትነሺ ሐ. ተንጋለይ መ. አትውረጂ
13. ተከበሩ ________
    ሀ. ይወፍሩ ለ. ያስከብሩ ሐ. ያከብሩ መ. ሰው አይፈሩ
14. ተከፋ ተወልጄ ________ አደርኩ
    ሀ. ሰሰቃይ ለ. ሳልተኛ ሐ. በፈጭ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

ለ. <u>የሚከተለውን ምሳሊያዊ አነጋገሮችን ፍች ስጡ</u> ተ፣ቸ፣ኃ

1. ኃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ
   ሀ. ኃዘን ተደራረበብሽ ሐ. ኃዘን የለብሽም
   ለ. ኃዘን ቤት ሆነ መ. መልሱ የለም

2. ትለብለው የላት ትከናነበው አማራት
ሀ. አንድ የሌላት፣ እንቅልፍ የላት
ለ. ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ያደርሳል
ሐ. ታልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይበሩ
መ. እራት የላት ደግሞ ምሳ አማራት

3. ተናዳጅ እንጂ አናዳጅ አይሞትም
ሀ. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሐ. ዝም አይነቅዝም
ለ. የተከፋ ተደፋ መ. ነገርን አዳምጦ፣ እህልን አላም

4. ተልባ ቢንጫጫ ባንድሙቀጫ
ሀ. ዝንብ ቢለበለብ፣ መግላሊት አይከፍትም
ለ. የሽሮ ድንፋታ፣ እንጀራ እስኪቀርብ ድረስ ነው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

5. ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
ሀ. አለባብሰው ቢያርሱ በዐረም ይመለሱ
ለ. ድንጋይ ቢያጎኑት ተመልሶ ባናት
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

6. ተናካሽ ውሻ የዝንብ መቋደሻ
ሀ. ፊት የደረሰውን ወፍ ይብላው
ለ. ፊት የተናገረውን ሰው ይጠላው ፊት የበሰለውን ወፍ ይበላው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ መልሱ የለም

7. ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም
ሀ. ተመክሮ ልብ ተሸምቶ ድልብ ሐ. እርጥብ ከደረቅ ይነዳል
ለ. ከርሞ ጥጃ መ. መልሱ የለም

8. ተኩላ እንደ እንበላ እጮሃለሁ ብላ ተተረተረች
ሀ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ለ. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
ሐ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
መ. ሁሉም መልስ ነው

9. ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ
ሀ. አንድ ሰው ካገኘ ሌላውም ያገኛል
ለ. መልካም ነገር ተመኝ፣ መልካም ነገር እንድታገኝ
ሐ. ሸር ተመኝ ሸር እንድታገኝ
መ. መልሱ አልተሰጠም

10. ታሞ ከመማቀቅ፣ አስቀድሞ መጠንቀቅ
ሀ. በችግር ላይ ችግር እንዳይደርስብህ
ለ. መታመም ያለ ነውና አትጨነቅ
ሐ. ከችግሩ በፊት መፍትሔ ፈልግ
መ. መልሱ የለም



## መልመጃ 6 / ተ፣ ቸ፣ ኀ/

ሐ. የሚከተለውን ምሳሊያዊ አነጋገሮችን አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ | ሀ. የቸኮለ አፍሶ ለቀመ |
| 2. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ | ለ. የቸገረው እርጉዝ ያገባል |
| 3. ቸኩለው ያፈሱታል፣ ተቀምጠው ይለቅሙታል | ሐ. ድንጋይ ቢያጎኑት ተመልሶ ባናት |
| 4. ኃይለኛ ዱቄት ከነፋስ ይጣላል | መ. ለጨለማ ጊዜ፣ መብራት፣ ለመከራ ጊዜ ብለሃት |
| 5. ተሌባ ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው | ሠ. ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ |
| 6. ኃጢያት በንስሐ፣ በደል በካሳ | ረ. የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጣጣ |
| 7. ተለመደና ዶሮ መከሸከሸ፣ እኝህ እናትሽ ሐሙስ ሐሙስ ከች | ሰ. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም |
| 8. ተናካሽ ውሻ፣ የጅብ መቋደሻ | ሸ. ከለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ |
| 9. ተቀማጭ አፉ ምላጭ | ቀ. ለተቀማጭ በማይ ቅርቡ ነው |
| 10. ተመሮጥ ይሻላል፣ ማንጋጠጥ | በ. የቆየ ከሚበቱ ይወልዳል |
| 11. ተጦጣ የዋለ ጉሬዛ፣ እህል ፈጅቶ ገባ | ተ. እልህ ምላጭ ያስውጣል |
| 12. ተጠማኝ ቢለነብት ባለርስት ያሆናል | ቸ. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ |
| 13. ትሻልን ትቼ ትብሰን አገባሁ | ኀ. ከእህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች |
| 14. ተጥዶ የማይፈላ፣ ተሹሞ የማይበላ | ነ. ትንሽ ቆሎ ያደርሳል ካሻሮ |
| 15. ትንሽ ቆሎ ይዞ ከአሻሮ ተጠጋ | ኘ. ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል |
| 16. ትዕግስተኛ ከፈለገበት ይደርሳል | አ. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል |
| 17. ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም | ከ. ተመክሮ ልብ፣ ተሸምቶ ድልብ |
| 18. ተናግሮ ከመጨነቅ፣ የቀልቀሎዬን አፉን እንቅ | ኸ. ዝም አይነቅዝም |
| 19. ተረት ለነገር፣ ይሆናል መሠረት | ወ. የጋን መብራት |
| 20. ተምሮ ያላስተማረ፣ ዘርቶ ያላጠረ | ዘ. ካፍ የወጣ ቃል፣ ከእጅ የወደቀ እንቁላል |

## ነ

ነበርንበት፣ አትኩሩበት
- ከናንተ በላይ ነበርን፣ እናውቀዋለን

ነበር እንጂ ይኖራል፣ የሚባል ፍጡር የለም
- በዚህች ምድር ላይ ዘላለማዊ የሆነ ነገር የለም

ነቢያት በቀየሱ፣ ሐዋሪያት ገሠገሡ
- አንዱ በቀየሰው ነገር ሌላው ተጠቅሞበት ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ

ነቢይ በአገሩ፣ አይከበረም
- ደጅ ያለ ጠበል፣ ልጥ ይነከርበታል

ነቢይ ቢኖር፣ በከበረ ነበር
- ኖሮ ቢሆን ይከበር ነበር

ነብር ቢያንቀላፋ፣ ዝንጀሮ ኀበኘው
- ኀበዝ ሰው ዝም ቢል የፈራ መስሏቸው ይዳፈሩታል

ነብር ባየለበት ዘመን፣ ድመት ይኮርታል
- በንብ ጊዜ፣ ዝንብ ይናከሳል

ነብርን ሲይዙት ተጠንቅቆ፣ ኅመሮ ሲገቡ ደኮ ታጥቆ
- ማንኛውም ሥራ ሲሠራ በጥንቃቄ መሆን አለበት

ነብር ሳይገድል፣ ቆዳውን ያስማማል
- እህል ሳይዘራ ባሰ አገዘመራ

ነብር አየኝ በል
- ወዮልህ! አታመልጠኝም

ነብር ዐይኑን ታመመ፣ ፍየል መሪ ሆነ
- አጥፊና ጠፊ

ነብር ካልነኩት፣ አይነካም
- ሰው ክብሩን ካልነኩት ካልደረሱበት ሌላውን አይነካም

ነብር የሞተለት፣ ፍየል ልጅዋን ትድራለች
- ያንዱ ቤት ካልፈረሰ ያንዱ ቤት አይቀናም

ነዋሪ ለዘላለም፣ አለ ዓምላክ የለም
- ቋሚ የሆነ የለም ሁሉም ሟች ነው

ነውር ለባለቤቱ፣ እንግዳ ነው
- ራሱ የሚፈጽመው መጥፎ ተግባር መጥፎ መስሎ አይታየውም

ነገረኛ ሰው፣ ከቤቱ አይሞትም
- ነገር ሲያነፈንፍ በሔደበት ይቀራል

ነገረኛ፣ ቃሞ አይተኛ
- የነገር ሱስ ያለበት ሰው አርፎ አይቀመጥም

ነገረኛ ናቸው አጥልቃችሁ ቅበሯቸው፣ የተነሱ እንደሆን ብዙ ነው ጣጣቸው
- ነገረኛ ሰውን በጣም መራቅ ያስፈልጋል



ነገረኛ ዝንጀሮ፣ ውሻ ታረባለች
- የአህያ ቀበጥ፣ ከጅብ ጡት ይጣባል

ነገሩ ነገር ነው፣ ውስጡ ጉራንጉር ነው
- ነገሩን ከተከታተሉት ብዙ ጣጣ የሚያመጣ ነውና ተጠንቀቅ

ነገሩ ነገር ነው፣ ውስጡ ጥቅንጥቅ ነው
- ነገሩ ውስጡ ብዙ ውጥንቅጥ ነገር ስላለበት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

ነገሩን በልጥ፣ አሠረው
- ትኩረት ሳይሰጠው ቀረ

ነገሬ በሆዴ፣ መንገዴ ባመዴ
- የሆዴን ምሥጢር ለማንም አልናገር

ነገሬ፣ በከንፈሬ
- ዝም ነው አልናገርም

ነገርህና ነገሬ ልክ ነው፣ ሰው መስማቱ ትርፍ ነው
- በሐሳብ የተግባባን ስለሆነ ሰሰው ጉዳያችንን ማስማት የሰብንም

ነገርህን በጠጂ ርስትህን በልጂ
- ነገርህን በአክብሮት ይዠዋለሁ፣ ተቀብየዋለሁ

ነገር ለሰሚ፣ ውኃ ለተጠሚ
- ማንኛውም ነገር በትክክለኛው በው ሲሠራ ያምራል

ነገር ለበሰጠ፣ ውድማ ለመለጠ
- በክርክር ወቅት በቂ ምክንያቶችን የሚያቀርብ ሰው ክርክሩን ይረታል

ነገር ለጀማሪ፣ እሳት ለጫሪው
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው ይባላል

ነገር ላም ጫ፣ ይግደደው
- ነገር የፈለገው ይጨነቅበት

ነገርም ይበረከታል፣ ባላጋራም ይታክታል
- ነገር እየተንዛዛ ሲሔድ ማታከቱ፣ ማስልቸቱ የማይቀር ነው

ነገር ሲበዛ፣ ይሆናል ዋዛ
- ነገር ሲበዛ ትኩረት ያጣና እንደዋዛ ፈዛዛ ይታያል

ነገር ሲያመልጥ፣ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም
- በድንገት የሚሆን የሚያመልጥ ነገር

ነገር ሲጀመር፣ እህል ሲከመር
- ነገር ሲጀምሩና እህልን ሲከምሩ መሠረቱን ማሳመር ያሻል

ነገር ሳያውቁ፣ ሙግት፣ ሳይኀለብቱ ትዕቢት
- አቅምህን ማወቅ አሰብህ

ነገር ሳያውቁ ሙግት፣ አቅም ሳይኖር ትዕቢት
- ጉልበትህን አመዛዝነህ ማወቅ አለብህ

ነገር ስንት ነው? ሁለት፣ ምን ያበዛዋል ውሸት?
- አንድ ጊዜ የተነገረ ነገር ወደሌላ ቦታ ሲዛመት ያለ የሌለው ሁሉ ይጨመርበትና ይበዛል

ነገር በሆዴ እየተመኘሁ፣ ቢከፍቱት ተልባ ሆኜ ተገኘሁ።
- ያለዕውቀት ምን ይሠራል፣ ዕውቀት የለኝም

ነገር በለዛው፣ ጥሬ በለዛዛው
- ለዛ ያለው ነገር አድማጭ አያጣም

ነገር በልክ፣ ሙያ በልብ
- ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም

ነገር በመልከኛ፣ ጠላ በመክደኛ
- ነገርን የሚያውቅ መልከኛ፣ ዳኛ ነው

ነገር በምሳሌ፣ ጠጅ በብርሌ፣ ዜማ በሐሌ
- ለሁሉም ነገር ተስማሚ ነገር ያስደስተዋል

ነገር በቀጠሮ፣ ዘፈን በከበሮ
- አስበውበት የመጡት ነገር ውል ይኖረዋል

ነገር በትኩሱ፣ ጨዋታ በወዙ
- ሁሉም ነገር በትኩቡ ነው የሚጥመው

ነገር በነገር ይጠቀሳል፣ እሾህ በእሾህ ይነቀሳል
- ነገር በነገር ሲነሳ ሌላ ሚስጥር የሆነ ነገር ይገለጻል

ነገር በዐይን ይገባል
- ፊት ለፊት መነጋገር ጥሩ ነው

ነገር በእርቅ፣ መንገድ በደረቅ
- በስምምነት የሚያልቅ ነገር መልካም ነው

ነገር በእርቅ፣ ወይፈንን በድርቅ
- በድርቅ ጊዜ የገሩት ወይፈን አያስቸግርም

ነገር በወቀሳ፣ በደል በካሣ
- በዳይ ተበዳይን ክሶ ሲታረቅ ያስደስታል

ነገር በዋስ፣ እህል በነፋስ
- ዋስትና ያለው ክርክር በነፋስ ጊዜ የሚያዘራ እህል ስጥራቱ አስተማማኝነት አለው

ነገር በዋና፣ ሜዳ በእረኛ
- አንድ ቁምነገር የሚመራው በኃላፊ ሲሆን ከብቶች በሜዳ ውስጥ የሚጠበቁት በእረኛ ነው

ነገር በዋና፣ ዘፈን በገና
- ለሁሉም የሚያመች መሣሪያና ኃላፊ ያስፈልገዋል

ነገር በዋናው፣ ንብ በአውራው
- ንብ በአውራው እንደሚመራ ሁሉ የነገር መሪው ኃላፊው ነው

ነገር በዳኛ፣ ሚዶ በእረኛ
- ማንኛውም ክርክር ያለበት ነገር የሚያልቀው፣ የሚወሰነው በዳኛ ነው

ነገር ቢሳሳት ከጥንቱ፣ ሰይፍ ቢመዝ ከአፎቱ
- የአንድ ነገር ስሕተት ከአወጣጡ ከመሠረቱ ነው
- ጅምሩ ካላማረ መጨረሻው አያምርም

ነገር ቢሳሳት፣ ከሟቱ፣ ጥሻ ቢሳሳት ከናቱ
- ጅምሩ ካላማረ ውጤቱ ወይም መጨረሻውም አያምርም



ነገር ቢበዛ፣ በአህያ አይጫንም
- ፍሬ ሐሳቡን ብቻ ተናገር

ነገር ባዋቂ፣ ብረት በጠራቂ
- ሁሉም ነገርም ሆነ ሥራ በባለሙያ ያምራል

ነገር ነገርን ያመጣል፣ ድግር ዐፈርን ያወጣል
- አንድግ ነገር ሲያብራሩ በውስጡ ሌላ አዲስ ነገር ሲከሠት ይችላል

ነገር ነገርን ያነሳል፣ ጥጋብ ሞትን ያስረሳል
- የተመቸው፣ የደላው ሞት ያለ አይመስለውም

ነገርና መጫኛ እንዳሳጠሩት ወይም፣ እንዳስረዘሙት ነው
- ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል

ነገርና ገመድ፣ አለውሉ አይፈታም
- ሁሉም ነገር ሲካሔድ የሚገባው በሥርዓት ነው

ነገርን አዳምጦ፣ እህልን አላምጦ
- በጥሞና አዳምጥና ተናገር

ነገር አለኝ ከማለት፣ ሥራ አለኝ ማለት
- ነገር አለኝ ብለው ወደደኛ ሲመላለሱ የእለት ሥራው ይቀርና የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ ቤት ይፈታል

ነገር አለዳኛ፣ ነዶ አለመጫኛ
- ለማንኛውም የሚሆነው ነገር ሲኖር ይገባል

ነገር አንሽውን፣ እሾህ አጣሪውን
- ተመልሶ ባለቤቱን ይጎዳዋል

ነገር እንዲጠፋ፣ ዳኛውን ግደል
- ነገርን የሚያራዝመው ነገሩን የሚመለከተው ወገን ነው

ነገር እንዳገቡት፣ ሙክት እንዳሰቡት
- ነገር እንዳያያዙና እንደያገርው ነው

ነገር እንዳፉ፣ ዛፍ እንደቅርንጫፉ
- ነገር እንዳቅራቢው፣ እንደችሎታው ነው

ነገር ከመጀመሪያው፣ እህል ከመከመሪያው
- የነገር አመሠራረቱ ወሳኝ ነው

ነገር ከመጀመሪያው፣ ውኃ ከመሻገሪያው
- መሻገሪያው ቀና ካልሆነ ሊሻገሩበት አይቻልም

ነገር ከመጀመሪያ፣ ፍሊጋ ከመሸጋገሪያ
- አስቀድሞ ነገርን በጥሩ ውል ላይ መመሥረት

ነገር ከመፈለግ፣ ይሻላል ኑግ ፈረግ
- ጊዜን በጠቃሚ ሥራ ላይ ማዋል ጠቃሚ ነው

ነገር ከሰነበተ፣ ቅራሪ ከሆመጠጠ
- ነገር እየዋለ እያደረ ሲሔድ ወደአልተጠበቀ አቅጣጫ ያመራል

ነገር ከሥሩ፣ ውኃ ከጥሩ
- የነገር መነሻዋ ዋናው መታወቅ አለበት

ነገር ከዕብድ ይገኛል
- መፍትሔው ሩቅ ሳይሆን በእጅ ውስጥ ያለ ነው

ነገር ከዋለ፣ ምላስ ከጥርስ እያልፍም
- ክርክር ሔዶ ሔዶ ዋስ እስከማስጠራት ይደርሳል

ነገር ከውሉ፣ ጋሻ ከእንግቡ
- ከእያያዝ ይቀደዳል ክአነጋገር ይፈረዳል

ነገር ከግቡ፣ ጋሻ ከእንግቡ
- የነገር ዋናው የተነሳበት ዓላማ ወይም መድረሻ ግቡ መጤን አለበት

ነገር ከፈቱ፣ ዱቄት ከወንፊቱ
- ሁሌም ነገር፣ ሙግት አያጣውም

ነገር ካምጪ፣ ውኃ ከምንጩ
- የነገሩ ጭብጥ ያለው አምጪው ዘንድ ነው

ነገር ካንሺው፣ ሥጋ ከጠባሹ
- ነገር እንዳቅራቢው ነው

ነገር ወዳድ ሰው፣ ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ ይላል
- ነገረኛ ሁሴ ነገር ይናፍቀዋል

ነገር ወዳጅ፣ ከቤቱ አይሞትም
- ነገር የሚወድ ሰው ነገር ሲያነፈንፍ የትም ወድቆ ይቀራል

ነገር ወዴት ትሔዳለህ? ጎንደር፣ መጨረሻህ? ታገር
- ነገር ካሚሚቁት መጨረሻ የለውም

ነገር የሚከረው፣ ጎንጓኙን ሲያገኝ ነው
- ነገር ጎንጓኝ ካለ ነገር እየተባባሰ ይሔዳል

ነገር የዋለበት ዳኛ ያውቃል፣ ከብት የዋለበት እረኛ ያውቃል
- ዳኛ የነገርን ብልት ያውቀዋል

ነገር የፈራ ይቃጠራል፣ እውሬ የፈራ ያጥራል
- እስኪ እስበንበት እንገናኝ ለማለት

ነገር ያለ ዳኛ፣ ትብትብ ያለመጫኛ
- ለነገር መፍትሔ የሚሰጥ ባለሙያ ዳኛ ነው

ነገር ያሻ ዳኛ፣ እምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ
- ጠብ የፈለገ ሰው ለመጣላት ካሰበ ምክንያት አያጣም

ነገር ፈጣሪውን፣ እሾህ አጣሪውን
- መልሶ ያንኑ አድራጊውን

ነጋሪ የሌለው፣ ይታማ አይመስለውም
- ተቆርቋሪ የሌለው ሰው የራሱ ጥፋት አይታየውም

ነጋዴን ተዛማች፣ ምን አቀላቀለው
- ያለቦታው የተገኘ

ነጋዴ ወረቱን፣ ዘላን ከብቱን፣ ገበሬ ምርቱን
- ሁሉም የሚያተኩረው በሚሠራው ሥራ ላይ ነው

ነጭ እንደሸማ፣ ትክል እንደአክርማ
- የአክርማ ትክልነት ለተወሰነ ወቅት እንጂ ዘለቄታ የለውም



ነጭ ድሃ፣ ነጭ ማር ይከፍላል
- ድሃ ዕዳውን ለመክፈል አያመነታም

ነፃነት ያኮራል፣ ሥራ ያስከብራል
- በአገርህ ነፃ ሆነህ ስትኖርና ሥራ ከሠራህ ሁሉም ሰው ያከብርሃል

ነፋስ ሲነሳ፣ እሳት አይጭሩም
- ነገርን የሚያባብስ ነገር ስታይ ተጠንቀቅ

ነፍስ በፈጣሪዋ፣ ሴት ባሳዳሪዋ
- ነፍሳችን በፈጣሪያችን እጅ ነው ሴትም በባሏ

ነፍስ ካለ፣ መንቀሳቀስ አይገድም
- የአቅማችንን ያህል መፍጨርጨር አለብን

ነፍጥ ቢያጓራ የጌታውን ጎን ይሰብር
- መሣሪያ ባለቤቱን አያውቅም

ኑር ባገር ጥፉ ካገር
- ከሕዝብ ጋር ተስማምተህ ኑር እለበለዚያ ካገር ራቅ

ኑሮ በዘዴ፣ ጾም በሑዳዴ
- ውኃ በብልሃት፣ ይቆላል በእሳት

ኑሮ በደጋ፣ መተኛት ባልጋ፣ ታላቅ ጸጋ
- ለመኖር ጸጋ በጣም ይመቻል

ኑሮ ቢያምርህ ችላ፣ ጥጋብ ቢያምርህ ባቄላ
- ለኑሮህ እጅግም መጨነቅ በውነትን ይጎዳል

ኑሮ ኑሮ ከመሬት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት
- ከሞት ማንም ሰው አያመልጥም

ኑሮ ከመናደድ፣ ሔዶ መናፈቅ /መመስገን/
- አብረው እየኖሩ ከመናናቅ ርቆ መኖር ያነፋፍቃል

ኑሮ ካሉት፣ መቃብር ይሞቃል
- ተከባብረው መኖር ይገባል

ኑሮ ያኗኑራል፣ ሕግ ያከባብራል
- የሰው ልጅ በሕግ ጥላ ሥር ተከባብሮ ይኖራል

ኑ ባይ አክባሪ፣ እንቢ ባይ ቀላይ
- ሰው ወዳጁን የሚጋብዝ አክብሮ ነው እልጋበዝም ባይ ወራዳ ነው

ና ብላ ሳይሉት፣ ከወጡ አውጡልኝ
- በማያገባው ገብቶ መዘባረቅ

ና ያሉት እንግዳ፣ ራቱ ፍሪዳ
- በራሱ ፍላጎት የተዘጋጀ ዝግጅት ሙሉ ነው

ናዳ መጣልህ ቢሉት፣ ተከናንቢያለሁ አለ
- ምክር የማይሰማ

ንቡን አባሮ፣ ማሩን
- ቀፎ የሚቆረጠው በብልሃት ነው

ንብ ሳጥር፣ ሳያረዳ አይሔድም
- ንብ ከቀፎው ሲሰደድ አጥር ላይ አርፎ ነው

ንብ ቢሔድ ካጥር፣ ሰው ቢሔድ ካገር
- ሁሉም ነገር ከልኩ አያልፍም

ንብ ባውራው፣ ገበሬ ባዝመራው
- ሁሉም ሰው የራሱ የሚመካበት ሥራ አለው

ንብን ዐይተሀ፣ ተገዛ ብሏል እግዜር
- ለአለቃህ ታዛዥ ሆነህ ሥራህን ሥራ

ንካ ያለው፣ አይቀርም
- ከላይ የታዘዘ ነገር ምን ቢሆን አይቀርም

ንዳማ ቢያጭዱት፣ ከምር አይሞላ
- የማይላካ ነገር መሞከር ትርፉ ድካም

ንገሥ ቢሉት፣ ሳልዋጋ አልነግሥ አለ
- በአጭሩ መንገድ መጠቀም ሲችል ረዥሙን መንገድ መረጠ

ንጉሥ ሲብያኔ፣ አቡን ለኩነኔ
- አንዱ ምድራዊውን ሌላው ሰማያዊውን ሕይወት በሚመለከት

ንጉሥ ሲቆጣ፣ ቀስ ብለህ ውጣ
- ንዴቱ እስኪበርድለት ከፊቱ ጥፋ

ንጉሥ በመንግሥቱ፣ እግዜር በመለኮቱ፣ ጎልማሳ በሚስቱ
- ማንኛውም ሰው የኔ ነው በሚለው ነገር ይቀናል እንዲያከብሩለት ይፈልጋል

ንጉሥ በድንኳናቸው፣ እኔም በጎጆዬ፣ ንጉሥ ነኝ አለ ድሃ
- ማንኛውም ሰው በቤቱ የተከበረ ነው

ንጉሥ አንጋሹን፣ ቤተክርስቲያን ቀዳሹን
- ሁሉም የሚሆንለትን ይንከባከባል

ንጉሥ አይከሰስ፣ ሰማይ አይታረስ
- የማይቻል ነገር አለመሞከሩ ይመረጣል

ንጉሥ ከተነፈሰ፣ ሀይን ከፈሰሰ
- የንጉሥ ፍርድ ፈጽሞ አይሻርም

ንጉሥ ከግንቡ ውጭ፣ ይታማል
- መታማት ምንጊዜም አይቀርም

ንጉሥ የቆረጠው፣ እጅ ካለ ይቆጠራል
- ንጉሥ ያደረገው ነገር በሙሉ እንደመልካም ይቆጠራል

ንጉሥ የፈረደበት፣ መርከብ የተሰበረበት
- የንጉሥ ፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ ነው

ንጉሥ ይተከላል፣ ንጉሥ ይነቀላል
- የመሾም የመሻር ሥልጣን አለው

ንጋትና ጥራት፣ እያደር ይታያል
- እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል

ንጋትን አውራ ዶሮ ያውቃል፣ ወፍ ያረጋግጣል
- ሰው የማያውቀውን ሰው ጠይቆ ይረዳል

ንግድ ለወረት፣ ወዳጅ ለችግር ዕለት
- ለችግርህ ደራሽ የሚሆን ወዳጅ ማፍራት አስፈላጊ ነው

ንግግር ሲበዛ ያጠፋል፣ ማር ሲበዛ ያስተፋል
- ሲሞላ ይፈሳል፣ ሲከር ይበጠሳል

ንፉግ ለግሶ ቢሰጥ፣ እጁ ይንቀጥቀጥ
- ከልብ ያልሆነ ነገር ከድርጊቱ ይታወቃል

ኖሮ ካንገት፣ ወገብ ሥራ አለበት
- ከልብ ያልሆነ አክብሮት

ኖሮ ኖሮ ከሞት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት
- ሞት የማይቀር ዕዳ ነው



## መልመጃ 7 / ነ/

**ሀ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አሟላ**

1. ነገር ከሥሩ ____________ ።
   - ሀ. በሬ ካገሩ
   - ሐ. ውኃ ከጥሩ
   - ለ. በውል ይመረምሩ
   - መ. ሰው ከምግባሩ

2. ነበርንበት ____________ ።
   - ሀ. ማለት ዋጋ የለውም
   - ሐ. አትኩሩበት
   - ለ. ዘነጥንበት
   - መ. መልሱ የለም

3. ናዳ መጣልህ ቢሉት ____________ ።
   - ሀ. ፈረጠጠ
   - ሐ. የራሱ ጉዳይ አለ
   - ለ. ተከናንቢያለሁ አለ
   - መ. አልፈራም አለ

4. ኑሮ ኑሮ ከመሬት ____________ ።
   - ሀ. ዞሮ ዞሮ ከቤት
   - ሐ. ዞሮ ዞሮ ከአገር ቤት
   - ለ. ዞሮ ዞሮ ከቡናቤት
   - መ. መልሱ የለም

5. ነገር ከለነበተ ____________ ።
   - ሀ. ቅራሪ ከኮመጠጠ
   - ሐ. ጠጅ ከኮመጠጠ
   - ለ. አይሆንም ጥሩ
   - መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናል

6. ነገር ቢበዛ ____________ ።
   - ሀ. ይመጣል ነዝናዛ
   - ሐ. ሆነ ጠምዛዛ
   - ለ. በእህያ አይጫንም
   - መ. መልሱ የለም

7. ነጭ ድሃ ____________ ።
   - ሀ. ይታዘንለታል
   - ሐ. አይጠማውም ውኃ
   - ለ. አይታዘንለትም
   - መ. ነጭ ማር ይከፍላል

8. ንፉግ ለግሶ ቢለጥ ____________ ።
   - ሀ. ደስ ይለዋል
   - ሐ. ያበሳጨዋል
   - ለ. እጁ ይንቀጥቀጥ
   - መ. መልሱ የለም

9. ____________ ብረት ጠራቂ።
   - ሀ. ነገር ባዋቂ
   - ሐ. ነገር ቢበዛ
   - ለ. ነገር አለዳኛ
   - መ. ነገር ቢሳሳት

10. ነገር እንዳገቡት ____________ እንዳለቡት
    - ሀ. ወጠጤ
    - ሐ. ሙክት
    - ለ. ወይፈን
    - መ. ሁሉም መልስ ነው

11. ነገር ________ ይገኛል
ሀ. ከዕብድ　　ሐ. ከዐዋቂ
ለ. ከወረኛ　　መ. ሁሉም መልስ ነው

12. ነብር ሳይገድል ________።
ሀ. ፎከረ　　ሐ. ቆዳውን ያለማማል
ለ. ቀብድ አምጡ አለ　　መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

13. ነቢያት በቀየሱ ________ ገሠገሡ።
ሀ. ኃጢያኖች　　ሐ. ሐዋሪያት
ለ. ጻድቃን　　መ. ሁሉም መልስ ነው

14. ነብር ቢያንቀላፋ ________።
ሀ. ዝንብ አፉን ላሰው　　ሐ. ድመት ይኮርታል
ለ. ዝንጀሮ ነበኘው　　መ. ፍየል ነበኘው

15. ነቢይ ቢኖር ________
ሀ. ለላም ነበር　　ሐ. ረብሻ ነበረ
ለ. ደሃ በከበረ　　መ. በከበረ ነበር

16. ነገረኛ ናቸው አጥልቃችሁ ቅበሯቸው ________።
ሀ. አታመናጭቋቸው
ለ. የተነሱ እንደሆነ ብዙ ነው ጣጣቸው
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

17. ነገር ሳያውቁ ሙግት ________።
ሀ. አጉል ትዕቢት　　ሐ. እቅም ሳይኖር ትዕቢት
ለ. ለመረታት　　መ. ኃይለኛ ድፍረት

18. ንጋትና አውራ ዶሮ ያውቃል ________።
ሀ. ውሻ ያረጋግጣል　　ሐ. የለሊት ወፍ ያረጋግጣል
ለ. ወፍ ያረጋግጣል　　መ. ሁሉም መልስ ነው

19. ንብ ባውራው ________።
ሀ. ገበሬ ባዝመራው　　ሐ. ጀግና በፉከራው
ለ. ነጋዴ በኪሣራው　　መ. ሥራ በሠሪው

20. ነብር ________ አይነካም
ሀ. ዶሮ　　ሐ. ካልነኩት
ለ. የፍየል ግልገል　　መ. ያለ ሥራሀ



21. ነፍስ ቢነሳ ________።
ሀ. ነገር ትንኮሳ　　ሐ. አቤት አበሳ
ለ. እሳት አይጭሩም　　መ. ነፍበ ይሳሳ

22. ነጋዴን ተዘማች ________።
ሀ. ማን አነጋገረው　　ሐ. ማን አዋዋለው
ለ. ማን አሳረረው　　መ. ምን አቀላቀለው

23. ነጭ እንደሻማ ________።
ሀ. ዘፈን በገና　　ሐ. መንገድ በደረቅ
ለ. በደል በካሣ　　መ. ትከል እንደአከርማ

24. ነብር ዐይኑን ታመመ ________
ሀ. ውሻ መሪ ሆነ　　ሐ. ፍየል መሪ ሆነ
ለ. ተኩላ መሪ ሆነ　　መ. መልሱ የለም

25. ነፍስ ካለ ________
ሀ. መንቀሳቀለ አይገድም　　ሐ. ሩጦ መኖር አያቅትም
ለ. ኑሮሀን ትመስላለሀ　　መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

26. ንጉሥ ሲቆጣ ________።
ሀ. ባለሟል ተንጣጣ　　ሐ. አገልጋይ ይርበድበድ
ለ. ድሃ ይንጣጣ　　መ. ቀስ ብለሀ ውጣ

27. ንጉሥ በድንኳናቸው ________ ንጉሥ ነኝ አለ ድሃ
ሀ. እኔም በቀየዬ　　ሐ. እኔም በጎጆዬ
ለ. እኔም በቀበለዬ　　መ. ሁሉም መልስ ነው

28. ንብን ዐይተሀ ________።
ሀ. ተባበር ብሏል እግዜር　　ሐ. ተገዛ ብሏል እግዜር
ለ. ሥራ ሥራ ብሏል እግዜር　　መ. መልሱ የለም

29. ነገር ለጃማሪ፣ ________
ሀ. ማገዶ ለጫሪ　　ሐ. ወሬ ላውሪ
ለ. ውኃ ለተጠሚ　　መ. እሳት ለጫሪው

30. ነገር በቀጠሮ ________።
ሀ. ሙያ በልብ　　ሐ. ዘፈን በከበሮ
ለ. ጨዋታ በወዙ　　መ. መልሱ የለም

## መልመጃ 7 /ካ/

ለ. <u>የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች ፍቺ ስጡ</u>

1. ነብር ባየለበት፣ ድመት ይኮርታል
   ሀ. ንብ ሲነግሥ፣ ዝንብ ይነግሥ
   ለ. በንብ ጊዜ ዝንብ ይናከሳል
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. መልሱ የለም
2. ነገረኛ ዝንጀሮ፣ ውሻ ታረባለች
   ሀ. ጎዳው ፍየል፣ ቀንዳሙን ወጋው
   ለ. ለነገረኛ ነገርን መተው ለሆዳም እህልን መተው
   ሐ. ያሀያ ቀበጥ ከጅብ ጡት ይጠባል
   መ. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል
3. ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ
   ሀ. የቡና ስባቱ መፋጀቱ ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   ለ. የነገር ወጡ ማዳመጡ መ. መልሱ የለም
4. ነብርን ሳይገድል፣ ቆዳውን ያስማማል
   ሀ. ሲሸኝ ጢስ ወጋኝ ሐ. እህል ሳይዘራ ባለ አዝመራ
   ለ. የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ነገር በልክ፣ ሙያ በልብ
   ሀ. የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
   ለ. እሳትና ጭድ አንድ ቤት አያድርም
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. ነገር ሲበዛ በአህያ አይጫንም
6. ነገር ከውሉ፣ ጋሻ ከእንግቡ
   ሀ. ሰው ከመከረው መከራ የመከረው
   ለ. አመስጋኝ አማላኝ
   ሐ. ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል
   መ. መልሱ የለም
7. ኑሮ በዘዴ፣ ጾም በሑዳዴ
   ሀ. ውኃ በብለሃት፣ ይቆላል በእሳት
   ለ. ሰው እንደአቅሙ እህል እንደቃርሙ
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. መልሱ የለም



6. ንጋትና ጥራት፣ እያደር ይታያል
   ሀ. ብልሀ ልጅ እየበላ ያለቅሳል
   ለ. እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል
   ሐ. ጉትቻ ለጆሮ፣ ጥሬ ለዶሮ
   መ. መልሱ የለም

## መልመጃ 7 / ነ /

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ነብይ በአገሩ አይከበርም | ሀ. | በንብ ጊዜ፣ ዝንብ ይናከሳል |
| 2. | ንግግር ሲበዛ ያጠፋል፣ ማር ሲበዛ ያስተፋል | ለ. | እህል ሳይዘራ ባለአዝመራ |
| 3. | ነገር ከውሉ፣ ጋሻ ከእንግቡ | ሐ. | ውኃ በብለሃት፣ ይቆላል በእሳት |
| 4. | ነገርና መጫኛ እንዳላጠሩት ወይም፣ እንዳስረዘሙት ነው | መ. | ደጅ ያለ ጠበል ልጥ ይነከርበታል |
| 5. | ነብር ባየለበት ዘመን፣ ድመት ይኮርታል | ሠ. | እውነትና ንጋት እያደረ ይገለጣል |
| 6. | ነገር በእርቅ፣ ወይፈን በድርቅ | ረ. | ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል |
| 7. | ንጋትና ጥራት፣ እያደረ ይታያል | ሰ. | ነገር ሲበዛ በአህያ አይጫንም |
| 8. | ነብር ሳይገደል፣ ቆዳውን ያስማማል | ሸ. | ሲሞላ ይፈሳል፣ ሲከር ይበጠሳል |
| 9. | ነገርን በልክ፣ ሙያን በልብ | ቀ. | በድርቅ ጊዜ የገሩት ወይፈን አያስቸግርም |
| 10 | ኑሮ በዘዴ፣ ጾም በሑዳዴ | በ. | ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል |

## **አ**

አሁን ሊደርቅ ውኃ፣ አደረገኝ ድሃ
- የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ይሰጣል

አሁን የሚያልፍ ውኃ፣ አደረገኝ ድሃ
- የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ይስጣል

አህያ ለማኘን፣ አህያ ለማኝ ቀደመው
- ተመሳሳይ ሐሳብ ያላቸው በአንድ ጎዳና ይጓዛሉ

አህያ ለሰርዶ፣ ባላገር ለመርዶ
- ለአንዱ በጎ ለሌላው ክፉ ያጋጥማል

አህያ ላህያ ቢራገጥ፣ ጥርስ አይሣበር
- ዘመድ ለዘመድ ቢጣላ አይጨካከኑም

አህያም እንደአባቱ ይፈረጥጥ፣ ኾርብም ይዘርጥጥ
- እያንዳንዱ እንደተፈጥሮው ይኖራል

አህያም የለኝ፣ ከጅብ አልጣላ
- ከሌላው የሚያጋጨኝ ምንም ነገር የለኝ

አህያ ሞተች ተብሎ፣ ጉዞ አይቀር
- ችግር ደረሰ ተብሎ ከቁም ነገር ቦታ አይቀርም

አህያ ስባ፣ ምን ረባ
- አህያ ቢሰባ ካልተበላ ምን ይረባል

አህያ ሲጠግብ አምቦ ልጅ ሲጠግብ ሽንኑ
- ባልተፈለጉበት ቦታ መገኘት

አህያ ሲጠግብ፣ ከጅብ ይጫወታል
- ጥጋብ ለችግር ይዳርጋል

አህያ ሲጭኑት ሦስት ሆኖ፣ መንገድ ሲሔድ ሁለት ሆኖ
- በመተባበር ሥራን መሥራት ይገባል

አህያ ቀንድ ቢያወጣ፣ ቁራ እንዴት በነጣ
- ሊሆን አይችልም እንጂ ሁሉም እንደተመኘው ቢሆንለት ደስ ይለው ነበር

አህያ በሞተች፣ ባመቷ ኩር ኩር
- መጸጸት አይገባም

አህያ ቢሞት ጉዞ አይቀሩም፣ ገኸ ቢጠፉ ተገኸ አይጠፉም
- ችግር ቢያጋጥምም ከአሰቡት ቦታ መሔድ የግድ ነው

አህያ ተማሉ፣ ኾርብን አወረደ
- ምን ይረባኝ፣ ምን ይፈይድልኝ ብሎ

አህያና ጓያ ባምሳያ
- ተመሳሳይ ናቸው

አህያና ፋንድያ፣ አራዳና ገበያ
- የአንዱ የመገኛ ምክንያት አንዱ ነው



አህያን ሥጋ ጭነህ፣ ጅብን ጎዳ ብለህ፣ እንጃ ይሆን ብለህ
- ሀብትህን በጥንቃቄ ካልያዝክ ይሆናል ብለህ

አህያን በመንገድ፣ ካህንን በማርገድ
- ብርታቱን ታየዋለህ

አህያን ባመድ፣ ካህንን በማዕድ
- ማዕድ በቀረበ ቁጥር ካህን ባለበት ቡራኬ አይቀርም

አህያ አታመኻኛብኝ፣ ትበላኝ እንደሆነ እንዲያው ብላኝ አለች
- ምክንያት አታበዛ የምታደርገውን ልታደርግ ትችላለህ

አህያ እንኳ፣ በወለደች ታርፋለች
- ልጅ ያለው በልጆቹ ይጦራል

አህያ እንደምትታሰብ፣ ከላሞች ፊት ፊት ትቅለበለብ
- እንዲያው ደርሶ ፀዋቂ ወይም ባለሙያ መሳይ

አህያ እጅብ፣ ለቅሶ ሔደች
- ያልሆነ ወዳጅነት

አህያ ከመሞቷ መንተቷ
- አገልግሎቷ ሲያልቅ አላስፈላጊ ናት

አህያ ወደ ሜዳ፣ ጅብ ወደ ጓዳ
- የተገላቢጦሽ ነገር

አህያውን ቢፈሩ፣ መደላድሉን ሰበሩ
- ዝሆኑ ሳለ ዱካውን

አህያውን ቢፈሩ፣ ዳውላውን መቱ
- ዝሆኑ ሳለ ዱካውን

አህያውን አመስግን ብሎ ፈረሱን አዋረደ
- በቅሉ ሽንቷን አጠራ ብላ ብልቷን አሳየች

አህያ የሌለው፣ በቅሉ ይንቃል /ያንኳሰሳል/
- ምንም የሌለው ግን የሰው ይንቃል

አህያ የተጫነችውን፣ አትበላም
- አደራ መጠበቅ አለበት

አህያ ያለ ዕውቀት፣ ከጅብ ቤት ገባች
- ሳይታሰብ ለከባድ አደጋ መጋለጥ

አለሴን በጉማሬ፣ መንገድን በወሬ
- ባለጌን መቅጣት ተገቢ ነው መንገድ ደግሞ እያወሩ ከሔዱ አይታወቅም

አለ መባ፣ ቤተክርስቲያን አትገባ
- ለሚወዱት ሰጦታ ገጸበረከት ማቅረብ የተለመደ ነው

አለማረፌ፣ እንተን ማንከርፈፌ
- ብቻዬን ብሔድ ይሻለኝ ነበር እንቅፋት ሆንክብኝ

አለማረፍ፣ የተርብ ቤት መቆሰቆስ
- ያለማረፍ እራሱን እችግር ላይ ይጥላል

አለማወቄ፣ በላሁ ተጨንቄ
- ያለማወቅ ችግር ውስጥ ይጥላል

አለማወቄ፣ ከዘመድ መራቄ
- ከዘመድ መራቄ ለችግር ዳረገኝ

አለሥራ አይበላ እንጀራ፣ አለባል ቆጥ አይሠራ
- ሥራን ካልሠሩ ከየት አምጥተው ይመገባሉ

አለቃ ለራሱ አልበቃ
- አንዳንዱ ራሱንም ማስተዳደር አይችልም

አለቃ ቢለቅ ለሻለቃ፣ ምንዝር ቢለቅ ላለቃ
- ችግር ቢደርስብህ በቅርብ ላለ አለቃ አቤት ትላለህ

አለቃ የሌለው ሕዝብ፣ አውራ የሌለው ንብ
- መልካም መሪ የሌለው ሕዝብ ይበታተናል

አለቃ የሰጠው፣ እጣሪ የሸጠው
- ለማጣራት የሚሸጥ ነጋዴ ገፋ እያደረገ በመሆኑ በብዛት ማግኘት ማለት ነው

አለቃ ያውቃል፣ ድሃ ይጠይቃል
- ምንም እንኳ የበታች ቢጠይቅም የሚወስነው በበላይ እካል ነው

አለ በለኝ ቀልቤን፣ ሞተ በለኝ ከፈኔን
- በሕይወት እያለሁ ምግቤን ከሞትኩም የምገነዝበትን ጨርቅ አዘጋጅልኝ

አለባለቤቱ፣ አይነድም እሳቱ
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

አለባል ሴት ወይዘሮ፣ አለማንገቻ ከበሮ
- ሚስት በባሏ፣ ባል በሚስቱ ይከበራል

አለባበሰው ቢያርሱ፣ ባረም ይመለሱ
- ቢከማች ዕዳው ባንቺ

አለብልሃት ገደል መግባት፣ አለ ጉልበት ውኃ መግባት
- እቅምን ዐውቆ መኖር ጥሩ ነው ያለበለዚያ ለእደጋ ያጋልጣል

እለት ለረገጠ ፍለጋ የለውም፣ ውኃ ለጠጣ ሽታ የለውም
- ያለምክንያት መልፋት አያስፈልግም

አለ ንጉሥ ሰላም፣ አለደመና ዝናብ
- ለሁሉም መነሻ ምክንያቶች ይኖሩታል

እለ ንጉሥ፣ ዘመድ፣ እለምሳር ግንድ
- አንዳች ሥራ ለመሥራት የሥራ መሣሪያ ወሳኝ ነው

አለንጋ ለፈረስ፣ ጅራፍ ለሰነፍ
- ለማንኛውም ማነቃቂያ አስፈላጊ ነው

አለንጋ እስኪገዙ፣ በክርን ይተክዙ
- የሚፈለገው መሣሪያ እስኪገኝ ባለው መጠቀም

አለኝ ብሎ ከማፈር፣ የለኝም ብሎ መድፈር
- ኋላ እውነቱ ሊገለጽ አጉል ውሸት አዋራጅ ነው



አለኝ እንጂ፣ ነበረኝ አይጠቅምም
- ስላለፈው ማውራት አይጠቅምም በለአሁኑ እንጂ

አለ አቁማዳ መጫኛ፣ አለ ከብት እረኛ
- የማትጠቀምበትን መሣሪያ ይዘህ ብትቀመጥ ምን ይረባሃል

አለ አቅማቸው እንዋጋ ብለው፣ ጀግኖችን አስገደሉ
- አቅምን አለማወቅ ትልቅ ጉዳት ያስከትላል

አለ አቡኑ ቄስ፣ አለዘውድ ንጉሥ
- አስፈላጊው መሣሪያ በሌለበት የሚፈለገውን ጉዳይ ማከናወን ያዳግታል

አለ አቡኑ ክህነት፣ አለ ንጉሥ ሹመት
- ለሁሉም ባለቤትና የሚመለከተው ይኖረዋል

አለ እባት፣ ጎመን ባጓት
- ሁሉ ሞልቶ ሁሉ ተርፎ የማይረባ ነገር መመኘት

አለ አቻ ጋብቻ፣ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
- ያለ አቻ ጋብቻ ያለመግባባትን ይፈጥራል

አለ አንድ የላት ጥርስ፣ በዘነዘና ትነቀስ
- አንድ ፀጉር ያላት ልትሠራ ሔዳ ፀጉሯን ተነጭታ ተመለሰች

አለ እህል አቁማዳ ይሞላሉ፣ አለ ዘር ይቀራሉ
- የሌለውን በሌለበት ፍለጋ

አለ ካሉት አይርብም
- አጋር የሆነ ነገር ተስፋ ነው

አለወንድም ጋሻ፣ አለ ድግር እርሻ
- ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው

አለዋንጫ አይስማት፣ አለ ቀንጠፋ አይለባት
- አንድን ነገር ለመፈጸም መነሻ የሚሆን ነገር ያስፈልጋል

አለዋዛው ዋዛ፣ ማቄን ትቀጂያለሽ
- በማይመስል ሁኔታ ጥቅምንና መጠቀሚያህን እንዳታጣ

አለዋዛ ዋዛ፣ ቅቤም አይዋዛ
- ያለቦታው የሚደረግ ነገር እንደተፈለገው ሊሆን አይችልም

አለው አለውና፣ ሳይመታው ቀረ
- ሞከሮ ሞከሮ እንደተመኘው ሳይሆንለት መቅረት

አለ ዳኛ ሙግት፣ አለገመድ እክት
- አንድ መፍትሔ የሚሰጥ ወሳኝ ያስፈልጋል

አለዳኛ አይካሱ፣ አለጥርስ አይነክሱ
- አንድን ተግባር ለመፈጸም ለዚያ ተግባር የሚሆን የሥራ መሣሪያ አስፈላጊ ይሆናል

አለ ድሃ ዘውድ፣ አለገበሬ ማዕድ
- ገበሬ ካላረሰ ምግብ ከወዴት ይገኛል

አለ ጉልበት ስኮና፣ አለራስ ጉተና
- ለአንድ ለሚፈለግ ነገር ዋና መናሻ ነገር ያስፈልግሃል

አለጨለማ ፍረሃት፣ አለዘመድ ኩራት
- ለሁሉም መናሻ ምንክንያት ይኖረዋል

አለፈ በዋዛ፣ ልብ ባልገዛ
- በልጅነቴ ሳልጠቀምበት ያለፈው ነገር ይቆጨኛል

አለፈቱ አይቆርሱ፣ አለረጂቱ አይወርሱ
- የአንድ ነገር መገኘት ወላኝነት ሲገለጽ

እሉ ባሉ ዕዳ፣ አዎን ባሉ ሜዳ
- የሰማኸውን እንደምታውቀው አድርገህ ብታወራ ችግር ሊንጥምህ ይችላል

አሉ ቧልተኛ፣ ሌት ተቀን አይተኛ
- ሐሜተኛ ሰው ሲያማ ነው የሚውል

አሉ ብለህ፣ ካላሉህ አትገኝ
- ያላሉህን አታውራ ችግር ውስጥ ትወድቃለህ

አሉ ብሎ የተረታ፣ መሀል አገዳውን የተመታ
- በአሉ መከራከር ትርፉ ውርደት ነው

አሉን ያህል፣ ነገር ማሉን ያህል ምስክር
- በአሉ ምለህ መመስከር ያስቸግራል

እላህንም እምናለሁ፣ አህያዬንም እሠራለሁ
- ወተቷንም አልለቅ፣ ጥጃዬም አይከሳ

አላርፍ ያለች ጣት፣ እር ጠንቁላ ትወጣለች
- የአህያ ቀበጥ ከጅብ ጡት ይጣባል

አላሸከር በቅሉ፣ አለወንድም አምቧጓሮ
- ያለረዳት አንዳች ነገር መፈጸም አዳጋች ነው

አለ አቁማዳ መጫኛ፣ አለከብት እረኛ
- በሌላ ሁኔታ ላይ መጨነቅ የሚገባ አይደለም

አለአቅሙ፣ ጥሬ መቃሙ
- አለአቅም መንጠራራት

አላባት ነገር፣ ዝንጀሮን ከባህር፣ ዓሣን ከገደል
- አንድን ነገር ያለቦታው ያለባህርዩ መጠበቅ አይገባም

እላባት ቢዛቁን፣ ይላክን
- ያላግባብ የተጠቀሙበት ነገር መጠቀም ባደሆን ማባከን ነው

አላባት ጆሮ፣ በጡጫ
- ያላግባብ የፈጸሙት ተግባር ጎጂ ነው

አላባት ጎመን ባጓት
- ያልተለመደ ሁኔታ

አላቻ ጋብቻ፣ ቆይብቻ ቆይ ብቻ
- እንዲያው ዛቻ ብቻ

አላንኮበር ሾላ፣ ሜዳ አይገኝም
- የምትፈልገውን ነገር የተወሰነ ቦታ እንጂ የትምቦታ አታገኘውም

አላዋቂ ለባሽ፣ ልብሰ አበላሽ
- ላያውቁ የሚሠሩት ሥራ ውጤቱ ጥሩ አይደለም

አላዋቂ ላሚ፣ ንፍጥ ይለቀልቃል
- ሳያውቁ የሚሠሩት ሥራ ውጤቱ ጥሩ አይደለም



አላዋቂ አጉራሽ፣ አፍ ያበላሽ
- ባያውቁ የሚሠሩት ሥራ ውጤቱ ጥሩ አይደለም

አላዋቂ ካረደው፣ አዋቂ ያወራረደው
- አላዋቂ ከሠራው ሥራውን የሚያውቀው የሠራው ይሻላል

አላውቅም፣ አስገድሎ አያውቅም
- የማታውቀውን አላውቅም ማለት ተገቢ ነው

እላየናት፣ እንዲያው ገበያ ናት
- የማትረባ ናት

አላጋጭ አልማጭ
- አላጋጭ ሰነፍ ነው

አላጋጭ ገበሬ፣ ይሞታል በሰኔ
- በነፍ ሰው በቁም ነገር ላይ የለም

አሌ ብሎ የተረታ፣ መሃል አገዳውን የተመታ
- በማያንሰራራ ሁኔታ ጉዳዩ ውድቅ የሆነበት

አልሞትም ብሎ ሔዶ፣ ከማይቀበርበት አገር ደረሰ
- ትሻልን ትቼ ትባስን አመጣሁ

አልሞት፣ ባይ ተጋዳይ
- እራሱን ከአደጋ ለመከላከል የሚያደርገው ትግል

አልበሜን፣ ግባ በለው
- ሁኔታውን ሰባልሰማ እንዳዲሰ ይጠይቃል

አልሰሜ፣ የእናቱን ተንዞካር ይበላል
- ያለዕውቀት የሚደረግ ነገር

አልሸሹም፣ ዞር አሉ
- ያው ነው እንደቀድሞው ነው

አልቀባም ብትል ትመስክር
- ከሁለት አንዱን መምረጥ ይኖርብሃል

አልቅትና ድሃ፣ ውኃ ለውኃ
- ድሃ ሁልጊዜ ከእጅ ወደአፍ ነው

እልበላ እልጠጣ፣ ጎንደር ሔዶ ቀረ እንደወጣ
- እንዲያው ምንም ሳያገኝ ጉዳቱ ብቻ ተረፈው

አልጋው ሲገኝ፣ ባሉ እይገኝ
- እህሉ ሲገኝ ወፍጮው ይደንዛል

አልጠግብ ባይ፣ ሲተፉ ያድራል
- ሰሰታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

አመሰጋኝ፣ አማላኝ
- ያመሰገኑ አስመሰለው መርገም

አመንዝራ ስታረጅ፣ አቃጣሪ ትሆናለች
- በእስተርጅናም ቢሆን መጥፎ ባህርይ አይለቅም

አመንዝራ ካሏት፣ ብትቆርብም አያምኗት
- መጥፎ ሥራውን ቢያሻሽልም የበፊቱ ሥራውን ስለሚታወቅ ማንም አያምነውም

አመካከት፣ ዝንጀሮን ተመልከት
- ሙያን ከሌሎች ይማሩታል

አመድ በዱቄት ሢሥቅ፣ በነፋስ ልብ ውልቅ
- አላስፈላጊ ንቀት

አመድ በዱቄት ይሥቃል
- የራሱን ሳያውቅ ስለሌላው ማውራት

አመድ ባሰበት በስመአብ ማለት፣ የተኛ ጋኔን መቀስቀስ
- የማይሆን ሥራ መሥራት ተገቢ አይደለም

አመድ ያጠለቀው፣ ጉልቻ የላቀው
- ፍጹም ድሃ የሆነ ሰው

አመግል ብላ፣ አባበጠች
- የባሰ ችግር ላይ ወደቀች

አመጸኛ ሎሌህን፣ ከሰው ፊት አትዘዘው
- ያዋርድሃልና ነው

አሙኝ ብለህ፣ ካሙህ አትገኝ
- በራስህ መንገድ ሒድ

አማቱን ምታ ቢለው፣ ሚስቴን በየት አልፌ
- የኋላ ኋላ የሚያመጣውን ጉዳት አስቀድመህ ዕወቅ

አማትና ምራት፣ እሳት እራት፣ ሳይስማሙ መሬት
- አይስማሙም

አማቻችን አፈኛ፣ ቢመስስ ወደኛ፣ ወይ እኛ እንሁን አባረኛ
- በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መቆየት ማስቸገሩ

አማችና ቂጥ፣ ትርፍ ነው
- ለአንተ ያስኸው አንተ ነህ

አማች የበላው፣ እሳት የበላው
- እንደጠፋ ይቆጠራል

አማጭ ለልማዱ፣ የበቅሎ ከባድ፣ የሐር ገመድ አለኝ ይላል
- አማጭ የሌለ ነገር እየተናገረ ለማቀራረብ ይሞክራል

አማጭ ረማጭ
- አማጭ ጥሩ ጥሩ ነው እያለ እሳት ውስጥ ይከታል

አምራለሁ ብላ ተኩላ፣ ዐይኗን አጠፋች ቸኩላ
- ሲያጌጡ ይመላለጡ

አምሣ ሎሚ ላንድ ሰው ሸክሙ፣ ላምሣ ሰው ጌጡ ነው
- አንድ ግንድ ለሺህ አይከብድም

አምሣ ሰማ፣ ጀሮ ገማ
- ምስጢር ሊሆን አይችልም

አምሣ ዳቦ ከመላስ፣ አንዱን መግመጥ (መጉረስ)
- የሚጠቅመውን መምረጥ

አምባ ያለው ፈላሽ፣ ወንዝ የለው መላሽ
- አንድ ነገር ወደፊት እንጂ ወደኋላ አይመለስም



አምቦ ወርዶ፣ ጭቃ አይንካኝ አይባልም
- በአንድ ነገር ውስጥ ገብተው ከደሙ ንጹህ ነኝ አያስብልም

አምነው የሞገቱት አያስረታ፣ ዝግ ብሰው የታጠቁት አይፈታ
- ተማምነው ያደረጉት ነገር ያስተማምናል

አምና ከላሞቹ፣ ዘንድሮ ከጥጆቹ
- እያደር ቁልቁል

አምኖ ለሚሟገት፣ ረቺ የለው፣ ብቻውን ለሚሮጥ ቀዳሚ የለው
- በሚከራከርለት ጉዳይ ላይ እምነትና ማስረጃ ያለው አይረታም

አምኖ ይሟገቷል፣ አጠገቡበት ይሸምቷል
- ሰው ደስ የሚለው ቦታ ላይ የሚፈልገውን ይፈጽማል

አሞሌ ሲወፍር፣ አወንዝ አውርዳችሁ አጠቡኝ ይላል
- ሙከት ሲሰባ ሾተል ይልሳል

አሞራ በበላ፣ ጥፍ ጥሬን በዱላ
- ያጠፋውን ትተው ያላጠፋውን

አሞራ በዛፍ፣ ውርርድ ባሜፍ
- ሰው በሚወደው ስፍራ ላይ ይገኛል

አሞራና ቅል ተጋቡ፣ አሞራው በረረ፣ ቅሉም ተሰበረ
- አላቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ

አሞራን ሲበሉ፣ ስሙን ጅግራ ይሉ
- አራስን ማሞኘት

አረመኔ በጭካኔ፣ ሙግት በውጣኔ
- ሙግትን ከውጥኑ ማጠናከር ይገባል

አረምና ጠላት፣ ሳይዘሩት ይበቅላል
- ጠላትም ባላሰቡት ጊዜ ያጋጥማል

አረምን መንቀል፣ ሥር ሳይሰድ ነው
- ክፉን ነገር ማስወገድ ፈጥኖ ነው

አረረም መረረም፣ ማኅበሬን ከፈልኩ
- ችግሬን ተወጣሁ

አረጉን ሲሰቡት፣ ዛፍ ይወዛወዛል
- አንዱን ሲነኩት ሌላው ይነካካል

አራምባና ቆቦ፣
- የማይገናኝ ነገር

አራስ የጂን፣ ድመት የልጅዋን
- ሰው ባለ አቅሙ የሱ የሆነውን ይከላከላል

አራት ቁና እጃ ቢጠፉት፣ ሁለት ቁና ሥንዱ ይዛ ከጠንቋይ ቤት
- እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ

አርሶ ያልበላ፣ ሆነ ነሁላላ
- ሥራ የሌለው ፈዞ ይውላል

አርሶ ያልጠገበ፣ ነግዶ አይሆንለትም
- እጁ ውስጥ ባለው ያልሆነለት ሩቅ ምኞት መመኘት እንዲያው ዘበት

አርባ ዓመት ከሆነው ጋር ምክር፣ ከሠላሳ ዓመት ልጅ ጋር መክት
- ሁሉም ነገር ከዕድሜ ጋር የሚሔድ ነው

አርጂ፣ ጥኑ ነው
- መርዶ ነጋሪ ጨክን ብሉ ነው

አሮጌ መጥረጊያ፣ ቤት አያጠራም
- ባረጀ ዕቃ መጠቀም አያረካም

አሮጌ ማሳ ያረሰ፣ ለአንጀራ ልጅ ያጎረሰ
- ባረጀ ዕቃ መጠቀም የልብ አያደርስም

አሮጌ ውሻ በከንቱ አይጮህም
- የሚጮህበት ምክንያት ይኖረዋል

አሰሩት ተበተቡት፣ በኋላ ፈቱት
- እውነትና ንጋት እያደር ነው

አሰተኛ ሲናገር ይታወቃል፣ በሶ ሲበሉት ያንቃል
- ከአነጋገሩ የነገሩን እውነትና ሐሰት ትለያለህ

አሰት ቢናገሩት ውቃቢ ይርቃል
- ሐበት መናገር ያዋርዳል

አሰትና እውነት፣ የቱ ይረታ ጧት
- የትኛው ቀድሞ ይረታል

አሰት አያድንም መራቆት፣ መልከ አያሳምርም
- የአንድ ሰው ውበቱ ከነልብሉ

አሰድ፣ ያየውን አይሰድ
- አባራሪ የሚያባርረውን ሰመያዝ ይጥራል

አሳማ በበላ፣ ጎፍናኔ በዱላ
- አሞራ በበላ ጥፍ ጥሬ በዱላ

አሳሳች ከላይ፣ ሲሉ ከታች
- አሳሳች ሰው መሔጃው አይታወቅም

አሳይ ብላ፣ ታየባት
- የሰው ገበና አወጣ ብላ የራሷ ገመና ታየባት

አሳይቶ መሳሳት፣ የሰጭ ቅሌት
- ለመበጠት እሰበህ መከልከል ከንቱ ነገር ነው

እባዳጊ ለበደለው፣ ፊትህን አትስጠው
- አሰተዳደጉ ሰተበላሻ ልጅ ፊትህን እታሳየው

አሳዳጊ የበደለው፣ ለክፋት ያደለው
- አሰተዳደጉ ያላማረ በሕይወቱ እይሳካለትም

አሳፋሪ ሉሌህን፣ እሰው ፊት አትላከው
- በለሚያዋርድህ ተጠንቀቀው

አሥር የሚመኝ፣ አንድም አያገኝ
- ብዙ የሚመኝ አንዱንም አያገኝ

እሥር ጊዜ ሰካ፣ አንድ ጊዜ ቁረጥ
- ከማድረግህ በፊት አስብ



አሥራ ሁለት ሆኖ፣ እንድ ነብር ፈጃት
- ሕብረት ማጣት

አሰቀድሞ ማመሰገን፣ ለሐሜት ያስቸግራል
- መጨረሻውን ሳታይ ቀድመህ አታመበግን

አሰብ ሁለቴ፣ ከመናገር አንዴ
- ከመናገርህ በፊት ደጋግመህ አሰብ

አሰብ ያለው የመገዘዝ አይጥ፣ ምን ትበላሰች እያሰ፣ እንቅልፍ ያጣል
- በማያስጨንቅህ ለምን ትጨነቃሰህ

አሰተካክሉ ይቀዷል፣ ለእግዜር ብሉ ይፈርዷል
- ፍርድ የእግዚአብሔር ነው

አሰተውሉ ላየው፣ የሽምብራ አፍንጫ አለው
- በትኩረት ያየ ያላየውን ነገር ይገነዘባል

አሰቸጋሪ እንግዳ፣ ተዘቅዝቆ ይተኛል
- አሰቸጋሪ የሆነን ሰው ማስተናገድ አይቻልም

አሰጨነቀኝ ገንፎ፣ ከራቴ ተርፎ
- አንዳንድ ነገሮች ወዲያው በትኩሉ እንጂ ከዋሉ ካደሩ አይመቹም

አሰፍቶ ከማረስ፣ ከበላተኛው መቀነስ( ከተቀላቢው ማሳነስ)
- የሚበጀውን ከወዲሁ ማሰብ

አሽከሩን አይዳኝ፣ በገናውን አይቃኝ
- ማስተዳደር አይችልበትም

አሽከር ባንደበቱ፣ ውሻ በኸራቱ ይታወቃል
- የመልካም አቀባበልን ሁኔታ ማወቅ

አሾክሿኪ፣ አነካኪ
- ነገር ከወዲያ ወዲህ የሚሉ ግጭትን በሰው መሃል ይፈጥራሉ

አቀማመጥ ያላወቀ፣ ከባልና ሚስት መካከል ይቀመጣል
- በባልና ሚስት መካከል መግባት ከንቱ ነው

አቀበት ያደክማል፣ እርሻ ያዳግማል
- ሥራ ሰአንድ ጊዜ ብቻ ተሠርቶ አያበቃም

አቀፈም አዘለም፣ ለባለቤቱ ያው ሸክም ነው
- ሰዚህም በዚያም ያው ድካሙ ድካም ነው

አቃቢ በተልባ በበላች፣ ንበዙን ተጋረፈው
- መልከኛ ኮሶ ቢጠጣ ጭሰኛውን አሰቀመጠው

እቃቢ ኮሰ ቢጠጡ፣ ገበዙን አሻራቸው
- የሚመሰከተው ባለ ያልደከመው ውጤት እገኘ

አቅሙን አያውቅ፣ ቶሎ አይታረቅ
- ጉዳቱ እየከፋበት ይሔዳል

አበልጂ፣ አትድረስ ከደጂ
- ለህይንና ለወዳጅ ትንሽ ይበቃዋል

አበቢላ፣ የመስከረም ጠላ
- ተወዳጅና ተናፈቂ

አበባ፣ እያገርህ ግባ
- ጊዜው እልፎብሃል

አበድረኝ አይማረኝ፣ ተዋሳኝ ግዝት ነኝ
- እየተሰማመጡ ማስፈራራት የተነሱበትን ጉዳይ ማበላሸት

አበጀሁ ያላሰብኩት፣ ጆሮዬ ደነቆረ
- ጉዳት እየደረሰበት እያለ የጉዳቱን መጠን አለማጤን

አቡን ቄስ ናቸው ወይ? ቢሉት፣ ተርፏቸው ይናኞሉ አለ
- ከዚያ በላይ ሆነው ሌሎችን በብዛት ያፈራሉ

አቡካቶ፣ አሳብ
- የጠበቃ ሐሳብ

አቡጊዳ፣ የተማሪ ዕዳ
- ያንን ለማወቅ ብዙ ችግር አለበት

አባ ላዩ ዳባ፣ ውስጡ ደባ
- ውስጥ ውስጡ ክፋት ነው

አባም ሰው ሆኑና፣ ፋኖ ገደላቸው
- አቅም እንደሌላቸው እየታወቀ ያጠቁናል ብለው ማጥቃት ባልተገባ ነበር

አባሪ፣ ተነባባሪ
- በአንድ ላይ ሆነው

አባ በሌሉበት፣ ተገዞካር ተበላ
- የደከመው ቀርቶ ያልደከመው ተጠቀመ

አባ ቢዛሉ፣ እስከ ንፍሮ
- የትም ርቀው አይሔዱም

አባ ከበሉ፣ እመን አነሳቸው
- መተዛዘን ይገባል

አባቱ ሲላጨው፣ እናቱም ስታቅፈው
- በዚህም በዚያም ሲንከባከቡት

አባቱን ሳይመስል፣ የተወለደ ልጅ ጎረቤት ያሳማል
- አብረው ሲኖሩ መተማማት አይቀር

አባቱን አያውቅ፣ እናቱን ናፈቀ
- እጠገብ ያሰን ነገር ሳታደንቅ የሩቁን መናፈቅ

አባቱን የጠላ፣ የሰው አባት ይላደባል
- እንደራሱ እየመሰለው

አባቱን ገድሎ ላማቱ ይነጭ፣ እማቱን ጋርዶ እናቱን ያሰፈጭ
- ሰወገኑ ርኅራኄ የሌለው ለሌላው የሚያሳየው ከአንገት በላይ ነው

አባቱ ያልበላውን ኑግ፣ ልጁ አማረው ቅባኑግ
- ያልታየ፣ ያልተሰማ አዲስ ደራሽ ሐሳብ

አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ
- አይቡ ዳኛ ቅቤው መልከኛ

አባቴ ትንሽ ነው፣ ብልቴ ትልቅ ነው የሚል የለም
- ሁሉም የራሱን አክብሮ ይኖራል



አባት ሲታማ፣ ልጅ አይሰማ
- ጆሮ ለባለቤቱ ባዕድ ነው

አባት ሳሰ እጊጥ፣ ጀንበር ሳለ ሩጥ
- ጊዜህን አታጥፋ በአግባቡ ተጠቀምበት

አባት በነውሩ ይከሰሳል፣ ሰማይ በመብረቅ ይታረሳል፣ ውኃ በምንቸት ይጠበሳል
- ሁሉም እንደየባህሪውና እንደቦታው ይፈረድበታል

አባትና ጋሻ፣ ምስክር አያሻ
- መልካም አባት ለልጁ መመኪያ ነው

አባትና ጋሻ፣ በውጭ ያስታውቃል
- መልካም አባት ለልጁ መመኪያ ነው

አባትና ጋሻ፣ አይሸሸግም
- ፊት ለፊት ስለሚውሉ

አባት ከነሳው፣ ምግባር ያነሰው
- አባት የሌለው ልጅ መጥፎ ሥነምግባር ይኖረዋል

አባት የሌለው ልጅ፣ መዝጊያ የሌለው ደጅ
- አባት የሌሰው ልጅ መካር የሌሰው ነው

አባት የያዘውን ልጅ ይወርሳል፣ እጅ የያዘውን አፍ ይጎርሳል
- ልጅ ከአባት የተላለፈለትን እንጂ ሌላ ውርስ ከወዴት ያገኛል

አባት ያበጀው ሰልጅ ይበጀው
- አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀዋል

አባት ያጠፋው፣ ልጁን ያለፋው
- ያባት ዕዳ ሰልጅ ይተርፋል

አባት ጨርቁን በጎረሰ፣ የልጅ ጥርስ አጠረሳ
- ድሃ አባት ለማጌጥ ሲፈልግ ሆዱን አስሮ ነው

አባ ከበሉ፣ ለምን አነሳቸው
- ቄስ ትንሽ ነገር አይወድም

አባያ ቢቀና፣ ቤት ያቀና
- የሥራ ልግመኛ ሁሉ ሰሥራ ቢነሳሳ አገር ይቀና ነበር

አባያ፣ ከሰው ሁሉ ፊት ይተኛ
- ልግመኛ ቀድሞ ሰበብ ይፈልጋል

አባይ ለእለቱ፣ ደስ ማሰኘቱ
- እብሰት ለዕሰት እንጂ ዘለቄታነት አይኖረውም

አባይ በቃሉ ያስታውቃል፣ በእጁ ሲበላ ይታነቃል
- ውሸታምን ከአነጋገሩ ታውቅበታሰህ

አባይ ነፍስ ገዳይ
- ውሸታም ሰውን ከሰው በወሬ ያጋድላል

አባይና ሰንቅ፣ እያደረ ይቀላል
- ውሸታም ሰው እያደረ እየተዋረደ ይሔዳል

አባይ ጠንቋይ፣ ቤት ያስፈታል
- የሆነ ያልሆነው እየተናገረ ቤተሰቡን ጥርጣሬ ውስጥ ይከታል

አብሉ መብላት፣ በእሳት
- ዋሽቶ መብላት ገንነም ያስገባል

አብረህ ብላ ቢሉት፣ ቆሞ አጉርሱኝ ይላል
- ጥቅሙን ፈላጊ

አብረው የተጠመዱ፣ አብረው ይፈቱ፣ አብረው የበሉ አብረው ይሞቱ
- አብረው የሠሩት ሥራ በአንድነት ያስጠይቃል

አብሮ መብላት ያናንቃል
- አንዳንዱ ሲያቀርቡት ወሰን ያልፍና ያስቀይማል

አብሮ መኖር ያናንቃል፣ አብሮ ማደግ ያሣሥቃል
- ብዙ ከመተዋወቅ መናናቅ ሊመጣ ይችል ይሆናል

አብሮ የበላን ቅዱስ፣ የሐንስ አይሽረውም
- በፍቅር አብረው የኖሩት ኑሮ አይረሳም

አብ ሲነካ ወልድ የነካ
- የአባት መደፈር ልጅን ያስቆጫል

አብስሉ መብላት በእሳት
- የበሰሰ ነገር ሰበሽታ አይዳርግም

አብን ያየ፣ ወልድን ሀየ
- የአባትና ልጅ ተግባር ተመሳሳይ ነው

አብዝቶ ከማረስ፣ ከተቀባጢ መቀነስ
- ኑሮህን በዘዴ ምራው

አቦን አይጠምቅ፣ ወር አይጸድቅ የለም
- በአቦ የማይጠመቅ ጻድቃን አይደለም

አቦን አይጠምቅ፣ ፍልሰታን አይጥድ የለም
- አቦን ያልደገሰ ፋሲካን አያከብርም

አተር መዝራት፣ አቦ በብልሃት
- አንድ ነገር ሰመሥራት ብልሃትና ዘዴ ያስፈልጋል

አተር ቢጎድል፣ ሽንብራ ይበረክታል
- አንዱ በሚከፍለው መሥዋዕትነት ሌላው ይኖራል

አተርፍ ባይ አጉዳይ
- የበሰጠ አገኛለሁ ብሎ የራስን እስከሙራሹ ማጣት

አታላይ ሰጊዜው ያመልጣል፣ በኋላ ይሰምጣል
- ለጊዜው ያታልል እንጂ በኋላ መጋለጡ አይቀርም

አታላይ ባለማል፣ ባቄላ አሽቶ ያበላል
- አታላይ ማስመሰል ይችልበታል

አታላይ እታች፣ ሲሉት እላይ
- የአታላይ ደብዛው አይገኝም

አታላይ፣ ጉድባ ዘላይ
- የማይሆነውን እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ



:

አታማርጪው፣ አንዱን አምጪው
- መስጠትሽ ላይቀር ጊዜ አትፍጂ

አታርፍ አትሠራ፣ አትጾም አትበላ
- ከሁለት ያጣች

አታሰሰምዷቸው፣ አትክልክሏቸው
- አገም ጠቀም

አታበድር፣ እንዳትቸገር
- ራስህን ጠብቅ፣ ለሌላው ስትል እንዳትጎዳ

አታበድር፣ ካበድርክም አታስቸግር
- አስቀድሞ ሁኔታዎችን መረዳት እንጂ ከሆነ ወዲያ ማማረር ተገቢ አይደለም

አታንቀላፋ ንቅተህ ተኛ፣ ይህ ሁሉ መንገደኛ
- ምንጊዜም ሥራህን በንቃት አከናውን

አታወላውል፣ እንዳትቀር ከመሃል
- አታመንታ፣ ካመነታህ አንዱንም አትይዘውም

አታግባና፣ የሰው አጥር ዝሰል
- ትዳር መሥርት የሰው ሚስት ከምታማግጥ

አትማታ በበትር፣ ተከራከር ባጤ ሥር
- በሕግ ተጠቀም በጉልበት መጠቀም አያዋጣም

አትረፍ ያሰው በሬ፣ ቆዳው ከበሮ ይሆናል
- ላሣር የጻፈው ቢነግድ አያተርፈው

አትቁም ያሉት ለማኝ፣ ክሰጡት አንድ ነው
- ጊዜውን በመጠቀም ወደሌላ ቦታ ይሔዳልና

አትትረፊ ያላት ወፍ፣ በጥቅምት ትሞታለች
- እድሰ ቢስ ሰው ሰሚበላበት ጊዜ ይሞታል

አትናገረው፣ ምስህ ቅበረው
- የቃላት ልውውጥ ሳይሆን የሚበጀውን ሥራ ሥራ

አትኩራ ገብስ፣ ጎመን ባወጣው ነፍስ
- ሥራውን የሠራው ሰው እያሰ ያልሠራው ይኩራራል

አትክልት በውኃ ይሰመልማል፣ እህል ከፈጩት ይልማል
- አንድ ሥራ ምንም ያህል ቢከብድ ቆርጠው በስልት ከሠሩት መከናወኑ አይቀርም

አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩብህ፣ እንዲያው ያወጣሃል ቅን ከሆነ ልብህ
- ተገፉ እንጂ አትግፉ

አትግደርደሪ፣ ጦምሽን እንዳታድሪ
- መግደርደር ጦም ያሳድራል

አትጥላኝ በወሬ፣ ሳይጣራ ነገሬ
- ለማንኛውም መቻኮል ተገቢ አይደለም

አትፍራ ጋብዘኝ፣ አትናገር ሸኘኝ
- ፍርኃትና ክፉ ንግግር ጠቃሚዎች አይደሉም

አነለ ሲሉት ተቀነሰ
- የአሁኑ ይባስ

አነከለ ብዬ በቅሎ ገዛሁ፣ ዐይነ ይጠፋ ብዬ መሬ አበጀሁ፣ ያላሰብሁት ጆሮዬ ደነቆረ
- ያለቡበት ቀርቶ ያላሰቡበት ጉዳይ ያጋጥማል

አነጋገሩ ባሕታዊ፣ አወሳሰዱ እንደነአባይ
- ለማመንም ላለማመንም የሚያስቸግር

አነጋገራችን፣ እንደ ጠባያችን
- የሰው ጸባይ ይለያያል

አነጋገር ቢያምር፣ አሚሚት ይከፋል
- ለውን በአነጋገሩ ብቻ ማመን ያስቸግራል

አነጋገር አያውቅ፣ ምርቃት ያበዛል
- አጉል ማደናገር

አንቃ፣ ለራሱ አይበቃ
- አቅመ ቢስ ነው

አንቃ ላንቃ ቢደጋገፍ፣ ተያይዞ እንዘፍ
- ደካማ ለደካማ ቢረዳዳ ተያይዘው መውደቃቸው አይቀርም

አንበሳ ላንበሳ፣ ቢያገሳ ሞቱ ለኮላሳ
- ገዥዎች ቢታገሉ የሚጎዳው ሣሩ ነው

አንበሳ ምን ይበላል፣ ተበድሮ፣ ምን ሊከፍል ማን ተናግሮ
- ካንበሳ መንጋጋ ማን ያወጣል ሥጋ

አንበሳ ለባሪ፣ አሞራ በራሪ
- በተፈጥሮ የተገኘ

አንበሳ ሲያረጅ ኮሳላ፣ ምለጢር ሲያረጅ አፈላ
- እንዳማሩ አይሞቱም

አንበሳ ሲያረጅ፣ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
- ጉልበት ሲደክም ሁሉ ነገር ያስቸግራል

አንበሳ ሳይገድሉ፣ ቆዳውን ያለማማሉ
- ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

አንበሳ የለበረው፣ ለኅሩብ ይተርፈው
- አንድም ከደግ ተወለደ አንድም ከደግ ተጠጋ

አንበጣና ፌንጣ፣ ሰንጠረኘና ገበታ
- ተመሳሳይነት የሚታይባቸው

አንተም ሌባ እኔም ሌባ፣ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ
- በራሳችን ባልሆነ ነገር ለምን እንጨቃጨቃለን

አንተም አራዳ እኔም አራዳ፣ ምን ያጣላናል በሰው በረንዳ
- በራሳችን ባልሆነ ነገር ለምን እንጨቃጨቃለን



አንተ ሰው ና ግንቡን ጣለው
- አለቸጋሪውን አልፈህ ወዲህ ና

አንተ ቀውላላ፣ መኖህ ባቄላ
- ምግብህ ባቄላ አንተ ቀውላላ

አንተን ብዬ፣ መጣሁ አንተን አጣሁ
- የተማመንኩበት ነገር ባይሳካልኝ ቀረ

አንተ አለበሃል፣ ሥላሴ ያውቁልሃል
- ሰው ያለባል ዓምላክ ይፈጽማል

አንተ አብጀው፣ አስቤም አልፈጀው
- በምን አቅሜ እወጣዋለሁ

አንተ ውለታ ቆጣሪ ቢለው፣ አንተ ውለታ አስቆጣሪ አለው
- አንተ እኔን ትላለህ እንጂ አንተ ከእኔ ትብሳለህ

አንተ ግፋኝ ከላይ፣ እኔ እወድቃለሁ ከሥጋ ላይ
- ድጋፍ ካገኘሁ የፈለኩትን ነገር አገኛለሁ

አንቱ ትራገሙ፣ አንቱ ትደረገሙ
- ተራጋሚ እራሱን ደርጋሚ

አንቺማ ታቦኪያለሽ፣ ውሻ ይደፉብሻል
- አንቺ ትጥሪያለሽ ከሥርሽ ያለ ጠላት ያበላሽብሻል

አንቺ ምን ቸገረሽ ሁለት አባት አለሽ፣ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
- ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም

አንቺ ለትጎተጉቺ፣ እህያ ቀንድ ታወጣለች
- የሚነግሩሽን ሥራ ላይ ለማዋል ጊዜ ትፈጂያለሽ

አንቺን ማመን፣ ጉም መዝገን
- አንቺን ማመን በፍጹም አይቻልም

አንቺን ቢጠሉሽ አጥመዝምዘው ጣሉሽ፣ አለቻት ትኋን ለቁንጫ
- የራሷን አታውቅ በሰው ትሥቅ

አንቺን ጣመሽ እንጂ እኛንስ አስረጀን
- ለአንቺ የሆነው ለእኛ አልጠቀመንም

አንቺ ከምር አለሁ ብለሻል፣ ተበልተሽ አልቀሻል
- ጸጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል

አንቺው ሲላይ የተጫንሽው ሲሳይ፣ አለ ኸርብ
- በዳቦ ላይ ሙልሙል

አንቺው ታመጭው፣ አንቺው ታሮጭው
- አንቺው ሐሳብ አቅርበሽ አንቺው ሐሳቡን ትቃወሚያለሽ

አንካላ በልቡ፣ ኢየሩሳሌም አሳቡ
- ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ

አንካሳን ማገም፣ ድንጋይ መቆርጠም
- ለውጥ ሊያመጣ በማይችል ነገር ጊዜ ማጥፋት ጥሩ አይደለም

አንካላ ያለው ደብር፣ እዞ ያለው ባሕር፣ ሳይበጠበጥ አያድር
- ነገረኛ ያለበት መንደር ላይበጠበጥ አያድርም

እንደበቱ ሰውን ከመበደል፣ እጁ ሰውን ከመግደል
- ዘላለም ሰውን እንደበደለ ይኖራል

እንደበቱ ከጸሎት፣ እጁ ከምጸዋት
- መልካም ሥራ

እንደኛው ልብ እብርድ፣ ሁለተኛው ልብ አንድድ፣ ሦስተኛው ነገር ቀስቅስ፣ አራተኛው ጎራዴ ምዘዝ
- መልካሙን ዓምላክ ሲወድ ከፋትን ግን አይቀበለውም

እንዱ ሲበላ፣ ሌላው ያነበጉባል
- ምንም ሳይተርፈው እንዲያው ያሽቃብጣል

እንዱ ልብ መካሪ፣ እንዱ ቃል ተናጋሪ
- እርስ በርስ የሚስማሙ

እንዱ ሲሻር፣ እንዱ ይሾማል
- የእንዱ ኃዘን ለሌላው ደስታው ነው

እንዱ ሲናገር ያፈገዝ፣ እንዱ ሲናገር ያደነግዝ
- የትኛው ይሆን እውነተኛው

እንዱ ባንዱ ሲሥቅ፣ ጀንበር ጥልቅ
- የፉከክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

እንዱን ሳይዘው፣ ደረሰ ጊዜው
- የታዘዘውን ሥራ ምኑንም ሳይጀምር ደረሰበት

እንዱን ጥሳ፣ እንዱን እንጠልጥሳ
- ያንንም ያንንም መነካካት

እንዳንድ ጊዜም፣ በዋልድባም ይዘፈናል
- ዛሬ እንኳ እንደፈለገን እንሁን

እንዴ ያበደረ፣ ሁሌ ተከበረ
- በችግር ጊዜ የሚደርስ ሰው የተከበረ ነው

እንድ ሁለት ተባባሉ
- ተሰዳደቡ

እንድ ለዘጠኝ፣ እንዲያውም ሰጠኝ
- በችግር ጊዜ ትንሽ ነገር ካገኘህ ተመስገን ማለት ይገባል

እንድ ሎሌ፣ ለሁለት ጌታ አይገዛም
- በእንድ ጊዜ ለሁለት ሰው መሥራት አይቻልም

እንድ ማጭድ ወደቀ
- እንድ ችግር ተቃሰለ

እንድም ምረጥ፣ እንድም ቁረጥ
- ከሁለት ባንዱ ጽና

እንድ ምስክር አያስደነግጥ፣ እንድ ዐይን አያበረግጥ
- ያልተሟላ ምስክር ተቀባይነት የለውም

እንድ ሰኔ የተከለው፣ ካመት ዓመት አተረፈው
- በእንድ ወቅት የተሠራው ሥራ ጥሩ ትርፍ አበገኘለት



እንድ ሰኔ የጣሰው፣ ሦስት ሰኔ አያነሣውም
- እንዴ የተበላሸን ሥራ ለማስተካከል በጣም ያስቸግራል

እንድ ሲናገር ሁሉ ይሰማ፣ ሁሉ ሲናገር ማን ይሰማ
- የጨረባ ተዝካር፣ አለመደማመጥ የበዛበት

እንድ ሳይሉ፣ ሁለት አይሉ
- ቁጥር የሚጀምረው ከእንድ ነው

እንድ ቀን ቢስቱ፣ ዓመት ይጸጸቱ
- ያንድ ቀን መዘዝ ያለእንድ ዓመት አይመዘዝ

እንድ ቅማል፣ ሉሪ ታስፈታለች
- የናቁት ነገር ከፍተኛ፣ ችግር ያስከትላል

እንድ በሬ ሰቦ፣ እንድ ሰው አበበ
- እንድ አይነድ፣ እንድ አይፈርድ

እንድ በቀል፣ እብሮ በቀል
- ብቸኛ ሆኖ የተወለደ ከሌሎች ጋር ያድጋል

እንድ ባይሞት፣ ሺ አይጎለት
- የእንድ ሰው መስዋዕትነት ለብዙ ሰው ደስታ ይሆናል

እንድነት፣ ያገባል ገነት
- ሕብረት ለሁሉም ደስታና ሐሴትን ያመጣል

እንድ ዓመት በወገዝ፣ እንድ ዓመት በደሞገዝ
- በምንዳና ያለምንዳ ማገልገል

እንድ ዓመት እንዳይማሩ፣ ዕድሜ ልክ ይደንቁሩ
- ጥቂት መሥዋዕትነት ሳይከፍሉ በመቅረት ዘለዓለም መጸጸት

እንድ ዓመት ከርተት፣ እንድ ዓመት ሸርተት
- ጊዜን እንደሁኔታው ያሳልፉታል

እንድ ዓመት ወር፣ እንድ ድንጋይ ጠጠር አይሆንም
- የማይሆነው ሳይሆን አጉል ድካም

እንድ አይነድ፣ እንድ አይፈርድ
- እንድ ዕንጨት ይጨሳል እንጂ ነዶ ጉዳይ አይሞላም

እንድ ዐይና ሰው፣ ባፈር አይጫወትም
- ጉዳቱን ከመጀመሪያው ዐውቆ መጠንቀቅ አለበት

እንድ እግረኛ ያወራውን፣ እንድ ሺህ ፈረሰኛ አይመልሰውም
- ወሬ እንዴ ከተሰራጨ ለማስተካከል ያስቸግራል

እንድ ወሬኛ፣ አገር ይፈታል
- እንድ ወሬኛ ብዙ ሰው ያደናግራል

እንድ ወናፍ፣ ሁለት አፍ
- በተናገረው የማይረጋ

እንድ የሌላት፣ ሁለት አማራት
- ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት

እንድ ያላት፣ እንቅልፍ የላት
- ለዚያችው ትጨነቃለች

አንድ ግንድ ለሺ፣ አይከብድም
- ሃምሣ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ነው፣ ለሃምሣ ሰው ግን ጌጡ ነው

አንድ ጣት፣ ቁንጫ አይገልም
- እንድ በሬ ሰቦ፣ አንድ ሰው አሰቦ

አንድ ጣት በቆማጣ ቤት ብርቅ ነው
- በዕውር ቤት አንድ ዐይና ብርቅ ነው

አንገት ለምን ተሠራ፣ ዞሮ ለማየት
- አዙሮ ለማየት ለማገናዘብ

አንገቷን ደግፈው ቢያዘፍኗት፣ ያለች መሰላት
- ያልሆነውን እንደሆነ መቁጠር

አንጋጣጭ፣ ዱላ ዋጭ
- የበላዩን ትዕዛዝ የሚጠባበቅ ሰው ክስና ወቀሳ አያጣውም

አንጣሪያ ለአንጣሪያ፣ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ
- አንቃ ላንቃ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ

አኝከህ አኝከህ፣ ወደ ዘመድህ ዋጥ
- ከዘመድ ጋር የሠሩት ሥራ አያጋልጥም

አከፋፈል ለዕለት፣ አሰባሰብ ለጥንት
- ጥሪት ሀብት በብዙ ጊዜ በመሰብሰብ የሚገኝ ነው

አካሄዱን አይተህ፣ ጭብጦውን ቀማው
- አያያዙን አይተው ስንቁን ይቀሙታል

አካሄዱ አባበኛ፣ አኳኋኑ ድንገተኛ
- በሁለቱም መንገድ አስቸጋሪ ነው

አካልና አምሳል
- ይመሳሰላሉ

አካልና ከብት፣ሚስትና ቁርበት
- እነዚህ አስፈላጊዎች ናቸው

አካል የወለደው፣ ዘመድ የወደደው
- በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ

አክንባሎና ዕዳ፣ ተሽራርፎ ያልቃል
- ችግር ለጊዜው ነው እንጂ ቀስ በቀስ ያልፋል

አወላለድ ያለው፣ አከፋፈል አይቸግረው
- ለሚያተርፍ ነገር ክፍያ ለመስጠት አንቸገርም

አወይ ልጅ በማን እጅ፣ አለች ቆማጣ
- አንድን ነገር ምን ቢወዱት የሚገኝበት ሁኔታ ከሌለ አስቸጋሪ ነው

አወይ ብልሃት፣ ለንጉሥ መገዛት
- ለሳማዊ ነዋሪ ችግር አይገጥመውም

አዋጅ ቢያስነግሩ፣ ልዩ ነው ምክሩ
- ሕግን ከምክር ጋር አብሮ ይዞ መጓዝ ጠቃሚ ነው



አውሬ ከዋሻ፣ በሬ ከእርሻ
- ውሎአቸው ለየቅል ነው

አውራ የሌለው ንብ፣ አለቃ የሌለው ሕዝብ
- ሕዝብ መልካም መሪ ይሻል

አውድማ እንደነፋስ፣ አገር እንደ ንጉሥ
- በጣም አስፈላጊዎች

አዎን ማለት መረታት፣ አለመመከት መመታት
- ለተነሳህበት! ዓላማ ቆርጠህ መታገል ይኖርብሃል

አዎን ባይ ዕዳ ከፋይ፣ አሌ ባይ ሞት ተቀባይ
- የማትቋቋመውን ጉዳይ አምነህ መቀበል ይኖርብሃል

አዎን ብለህ ተሟገት፣ ክጠገበበት ሸምት
- የሚሉህን እሺ እያልክ የሚጠቅምህን ውሰድ

አዎን ብሎ የተረታ፣ መሃል አገዳውን የተመታ
- አንዴ ከተረቱ ወዲያ መፈናፈኛ አይኖርም

አዎን ያለች ምሳለ፣ እናት የሌሳት አራስ
- ደጋፊና መካሪ ማጣት ችግር ላይ ይጥሳል

አዎን ያለን አይሟገቱ፣ እሺ ያለን አይመቱ
- ያመነን ሰው ምንም አያደርጉት

አዘኑ ሳይለቅህ፣ ድግሱ አይራቅህ /አያምልጥህ/
- ችግሩ ሳይቀርልህ ሊኖር የሚችለው መልካሙ ነገር አያምልጥህ

አዘንጊ ወጥ፣ ከእንጀራ ይተርፋል
- የሰው ልጅ መከራ እንጀራው ያልቅና ወጡ ይተርፍና

አዘዞ አንድም ተናዞ፣ አንድም ስንቅ ይዞ
- ለአንድ ዓላማ የተነሳ ሰው አስፈላጊውን ሁሉ መያዝ ይገባዋል

አዙሮ ሳየው፣ ብሳም ነገር ነው
- መልካሙን ነገር ወደጠብ መተርጎም

አዛኝ ቅቤ፣ አንጓች
- አስመሳይ

አዛዩን ነካሽ
- በጣም አስቸጋሪ ባህርይ
- መጥፎ ባህርይ

አገዘመራ በቁንጫ፣ ሰማይ በጡጫ
- የማይሆንና ተግባር ላይ ሊውል የማይችል

አዞ ሲውጥ ያለቅሳል
- የልቡን እየሠራ የሚያስመስል

አየሁ ያለ ጣጣ ያመጣል፣ አላየሁም ያለ ከጣጣ ያመልጣል
- እንዳንዴ እውነተኛ ሰው ችግር ላይ ይወድቃል

አያርም አራሽ፣ አያጥብ ለባሽ፣ አይረታ ከሳሽ
- ሁሉን በጅምር የሚተው፣ ዳር የማያደርስ

አያርስ አይነግድ፣ አይተች፣ አይፈርድ
- መሥራት የማይወድ ድንግርግሩ የወጣ

አያስብ ቀበኛ፣ ተንኮለኛ
- በተንኮል የተካነ ለሚሠራው ተንኮል አይጨነቅም

አያስገኣ ኮሶ፣ የት ደርሶ
- የማይጠቅም ነገር አይፈለግም

አያተርፍ አይነግድ፣ አይተች አይፈርድ
- መሥራት የማይችል ድንግርግሩ የወጣ ሰው

አያ ተዋሰኝ፣ ስትሔድ እስነሳኝ
- ሐሳብ የለሽ ግድየለሽ ሰው

አያውቅ ቢዳኝ፣ ከቤቱ ይናኝ
- አንዳንዱ ያለበትን ቦታ በመዘንጋት ቤቱ ያለ ይመስለዋል

አያውቅ እንደኛ፣ የበግ እረኛ
- ሰው በዕውቀት ይበላለጣል

አያድሩበት ቤት፣ አያመሻሹበት
- ስጊዜ መንገድ መግባት ይሻላል

አያድርስ የባል ቢስ፣ አያቅፍ አያንተርስ
- የተማመንኩበት ሰው ደንታ ቢስ ሆነ

አያድን አገሬ፣ ጎድን ያሰብር
- ፈጥኖ እርምጃ የማይወስድ ሰው አደጋ ይጋብዛል

አያድን ጋሻ፣ ቂጥ ያስወጋል
- እያስጥል ገራ ገራ፣ ጎን ያስብራል

አያ ጅቦ፣ ሳታመኸኝ ብላኝ
- ምክንያት አታብዛ የምትፈልገውን ፈጽም

አያገባት ገብታ፣ አያወዛት ተቀብታ
- በማይሆንበት ቦታ የተገኘች

አዬ ሌላ፣ ወዬ ሌላ
- ኃዘንና ደስታ ለየቅል ናቸው

አዬና ወዬን፣ ምን አገናኘው
- በምንም አይገናኙም

አዬ ጉዴን አታበላሽ፣ ለባስ ቀን ይሆናል
- ለከንቱ የፈሰሰ እንባ ያሳዝናል ለአንድ ዘመድ ኃዘን ይጠቅም ነበርና

አይሆንም እንጂ ከሆነማ፣ ከመጋዞ ይሻላል ጉልማ
- ቢኖርማ የተሻለ ነው

አይመረው አይተኩሰው፣ ውጦ ውጦ ጨረሰው
- ሁሉንም ችሎ ታግሶ የሚኖር ሰው

አይመጣምን ትተሽ፣ ይመጣልን በያዝሽ
- ይሆናል ብሎ መገመት አለብሽ



አይረቢትን፣ አረቧት
- የማትጠቀመውን ትጠቅማለች ብለው አመጧት

አይስጥ አባኝ፣ ከነፍስ ገዳይ አንድ ነው
- ሲርበኝ ያላጎረሰኝ የገደለኝ ያህል ነው

አይበላ የለ፣ አይጠጣ ይባስ
- ጥቃቅን የሆኑ ነገሮች ሁሉ የታጡበት

አይበላ ዳኛ፣ በሙግት /በእግት/ ይመረር
- የሚያዋዛ ነገር ስመጥፋቱ መማረር፣ ደረቅ በደረቅ በመሆኑ

አይቡን ሲያዩ፣ እንቁን ጨለጡት
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

አይቡ ዳኛ፣ ቅቤው መልከኛ
- ጠላትህን ለማጥቃት እርስ በእርስ መተባበር ያስፈልጋል

አይብ ሲያድር፣ አጥንት ይሆናል
- ጥሩ ነገር ቶሎ ካልተጠቀሙበት ይበላሻል

አይብ ከአንቱ፣ ልጅ ከናቱ
- ሁሉ ነገር መቆየት የሚያምርበት ከመሰሉ ጋር ሲሆን

አይብ የጠላ፣ ጎመን የበላ
- ጠቃሚውን ያልፈለገ የማይጠቅመውን ቢፈልግ የባሰቤቱ ምርጫ ነው

አይተህ ቁረስ፣ ከጥርስህ እንዲደርስ
- አስተውለህ ሥራ

አይተፋሽ ማር ነሽ፣ አይውጡሽ ምርቅ ነሽ
- ለመቀበልም ለመተውም የሚያስቸግር ጉዳይ

አይታ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ፣ ተመለሽ ቢሏት ወዴት ተመልሳ
- ታይቶ የማይታወቅ ጥሩ ነገር ያጓጓል

አይታፈሩበት ቤት፣ ገላጋይ እይሁኑ
- ለማይሆንልህ ነገር አትሞክረው

አይቶ እያውቅ፣ ዳቦ ፍሪዳው
- አይቶ የማያውቅ ሁሉ ብርቁ ነው

አይቶ አጣ ቤት፣ ጎመን የተቀቀለ ዕለት ሲጨበጨብ ያድራል
- በቆማጣ ቤት አንዷት ጣት ብርቅ ናት

እይቶ ያጣ፣ ጠምዶ ፈታ
- ሀብታም የነበረ የከሰረ ሰው

አይችሉት ድንጋይ ቢሸከሙት፣ ከፍ ብሎ ደረት ይመታል፣ ዝቅ ብሎ እግር ይቆርጣል
- የማይችሉትን ሥራ እሠራለሁ ብሎ መሞከር ለጉዳት ይዳርጋል

አይችል ዳኛ፣ በቤቱ ይናኝ
- ሙግት የማይሆንለት ሰው በቤቱ ተሟጋች ይመስላል

አይነጋ መስሏት፣ እቋት አራች
- ሁሉ ነገር በዚያው የሚቀጥል መስሏት ነበር

አይዋስ ቢዋሰኝ፣ ከባለ ዕዳው ባስኝ
- በስንት መከራ ዋስ ቢሆነኝ ክባስጋራዬ ባስብኝ

አይዋጋ ብላቴና፣ አይዘንብ ደመና
- የሚሆን ቢመስልም የማይሆን ነገር ያጋጥማል

አይዋጥ አይተፋ መላው የጠፋ
- ለመቀበልም ለመተውም የሚያስቸግር ጉዳይ

አይዞህ አይዞህ ማለት፣ ከመውደቅ ያድናል
- ማበረታታት የሰውን ሞራል ያድሳል

አይዞህ ካሉት፣ ውኃ አይወስድም
- ማበረታታት የበውን ሞራል ያድሳል

አይጠቅም ጠላ፣ ባልና ሚስት ያጣላ
- የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ያበጣል

አይጠቅም ጠላ፣ ክጎረቤት ያጣላ
- የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ያስከትላል

አይጥ ለሞቷ፣ የድመት አፍንጫ ታሸታለች
- እጉል መቅበጥ አደጋ ላይ ይጥላል

አይጥ በበላ፣ ዳዋ ተመታ
- ያጠፋው እያለ ያላጠፋው ተመታ

አይጥ በበላ፣ ዳዋን በዱላ
- ያጠፋው እያለ ያላጠፋው ተመታ

አይጥ በድመት አፍንጫ ወርዶ፣ እህያ ታስሮ በስርዶ
- የአጥፊና ጠፊ በአንድ ቦታ መገናኘት

አይጥ በጉድጓዱ፣ በው በዘመዱ
- መመኪያ የሚሆን ዘመድ ያስፈልጋል

አይጥ ነሽ እዩት ከንፈሬን፣ ወፍ ነሽ እዩት ጥርሴን
- የሌስውን በሌስበት ቦታ ፍለጋ

አይጥና ዝሆን ቢዋደዱ፣ ዓሣ ወለዱ
- የወላጆችና የልጆች ባህርይ ሊለያይ ይችላል

አይጥና ድመት ታገሉ፣ ማንኛቸው ጣሉ
- አጥፊና ጠፊ ታግለው አጥፊ መጣሉ አይቀሬ ነው

አይጥና ፍልፈል፣ ሸክላና ገል
- ይመሳሰላሉ

አይጥ ወልዳ ወልዳ፣ ጅራቷ ሲቀር ደርሶ ሲጥ
- ደክሞ ደክሞ መጨረሻውን ለማየት ትዕግሥት ማጣት

አይጥ ጣረ ሞት ይዟት፣ ትጫወታለች ድመት
- የአንዱ ኃዘን ለአንዱ ጨዋታ ሆነ

አይጽፍ ደብተራ፣ ክንፍ የሌለው አሞራ
- የተማሩትን ሥራ ላይ ካላዋሉ መማሩ ጥቅም የለውም



አይፈስ ውኃ፣ አይበደድ ድሃ የለም
- ድሃ ሁሌ እየተንከራተተ ነው የሚኖረው

አደራ ቢሏቸው፣ ይብባሉ እሳቸው
- አደራ የማይጠብቅ ሰው አደራ በላ ነው

አደራ፣ ጅብም አይበላ
- አደራ አይነካም

አደራ ጥብቅ፣ በማይ ሩቅ
- አደራ ከባድ ኃላፊነት ነው

አደባባይ፣ አይውል አባይ
- ዋሾ አደባባይ ከሰው መሃል አይውልም

አደናግር፣ እንደነብር
- የነገር ግራ ማጋባት

አደንጓሬ፣ የእህል አውሬ
- አንዱ ከሌሎች ሰየት ብሎ ሲታይ

አዲስ ወጠ ሠሪ፣ ዝንጅብል ታበዛለች
- አዲስ ሠራተኞች ስመሥራት ይቸገራሉ

አዳራሹ ተመላሽ፣ ቀበና ድንጋይ ላሸ
- መልካም ነገር እንደማታገኝ ከወዲሁ ተረዳው

አዳኝ ውሻ፣ ጭገር ባፏ፣ በትር ትርፏ
- እርሱ እየሠራ የሚጠቀመው ሌላው

አድሏዊ ዳኛ፣ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ
- የማይሆን ነገር ከአቅም በላይ የሆነ ነገር መጠየቅ

አድል እልኩህ እንጂ፣ ጨልጥ እልኩህ
- ሰው ጥራ ቢሉት እራሱ መጣ

አድረው ሲስያዩ፣ ዓመል አባዩ
- የተስመደ ጠባይ ቢደብቁት አይደበቅ

አገሩ ሩቅ፣ ስንቁ ደረቅ
- በጣም ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታ

አገሬ ሩቅ፣ ጭብጦዬ ደረቅ
- በጣም ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታ

አገርህ ወዴት ነው? ማርያም ውኃ፣ እንግዲያው ዘመዴ ነሃ
- ከመጠያየቅ አንዳች ጠቃሚ ነገር ጠብ ይላል

አገርህ ወዴት፣ ነገርህ እንዴት
- መሠሚውን ካወቅህ ሁኔታውን ልትገምት ትችላለህ

አገር ላጣ ስሜን፣ ምግብ ላጣ ጎመን
- የጎመን ምግብ ጊዜን ያባልፋል

አገር ሲያረጅ፣ ጃርት ያፈራል
- ሰው ከሸመገለ ጸባይ ያወጣል

አገር፣ ቀሚስ ናት
- ሀገር መከበሪያ ናት

አገር በጤና፣ ለማኝ በጭራ
- ሁሉ ነገር በአገር ያምራል

አገር ቢያብር፣ ለንጉሥ ያስቸግር
- ሕዝብ አንዴ ካመጸ አስቸጋሪ ነው

አገር ቢጠላህ፣ እልፊህ እልፊህ ታረቅ
- ከሁሉ አትራቅ

አገር አላት ይበሉኝ፣ ማኅደረ ማርያም ቅበሩኝ
- ከሰው እኩል ልሁን፣ ልስተካከል

አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ፣ ማጭድ የሌለው፣ መስክ ሰፋሪ
- ያለአገር መከበር ያለመሣሪያ ተግባር አይኖርም

አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ፣ ማጭድ የሌለው፣ ወራሪ
- ያለአንዳች መሣሪያ አንዳች ተግባር መፈጸም አይቻልም

አገር ያለምክር፣ ቤት ያለማገር
- ምክር የማይሰማ ለአደጋ ይጋለጣል

አገር ያደረው፣ ዘንዶ የወደረው
- ክፉ ነገር ወጥሮ የያዘው ሰላም አያገኝም

አገር ጥሎ፣ ቁርበት ጠቅሎ
- ለኩብለላ መነሳሳት

አገባሻለሁ ያለ ላያገባሽ፣ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
- ስዶ ከማሳደድ የያዙትን ማጥበቅ

አገኘሁ ብልሃት፣ እርሾ መብላት
- ሠርቶ መብላት ጥሩ ነው

አገኝ ባይ፣ ልብ የለህም ወይ
- ለማግኘት የሚጥር ልቡ ትልቅ ነው

አጋም ተደግፎ፣ ይዋጋል እንቧጮ
- በንብ ጊዜ ዝንብ ይናከሳል

አጋሰስ በጭነት፣ ወገብ በመቀነት
- ሁሉም ለየተግባሩ ይፈለጋል

አጋዘን ሲጠግብ፣ የነፍጠኛ ጎጆ ይታከካል
- አጉል ጥጋብ ችግር ውስጥ ይጥላል

አጋጩው፣ እንደ ነጋዴ ጨው
- በለው

አግኝቶ ከመዋረድ፣ አጥቶ መኩራት
- ኩራት እራቱ

አጎንብሶ በላን፣ ተኝተህ ቀላውጠው
- ሁሉን ነገር እንደየአመጣጡ ተቀበለው

አጓት ጠጥቶ የሰከረ፣ ካሣ በልቶ የከበረ የለም
- የተሻለ ሥራ መሥራት ጥረት ማድረግ ይበጃል

አጣሪ እንደለጋስ፣ ከመንገዱ ዳር ተቀምጣለች
- ሰው መሳይ በሸንጎ



አጤን መደብ፣ እቴጌን ገደብ
- ሁሉም ወሰንና ልክ ይኖረዋል

አጤን፣ ያሻል ቀላጤ
- የበላይ ትዕዛዝ የሚያስተላልፈው በደብዳቤ ነው

አጤ ከሞቱ፣ በማን ይሟገቱ
- ዳኛ ሲኖር ተሟገት ፣ ውኃ ሲጎድል ተሻገር

አጥልቆ የሚያርስ፣ ከበሮ የማይጨርስ
- ሥራውን በጥሩ ሁኔታ የሠራ ይከብራል

አጥልቆ የማያርስ፣ ጀምሮ የማይጨርስ
- ሥራውን በጥሩ ሁኔታ ያልሠራ አይጠቀምም

አጥር ቆስቋሽ ነገር፣ አመላላሽ አያድርግሽ
- ሰውን አታጋጪ

አጥር ጥሶ፣ ቅጥር አፍርሶ
- የሰውን መብት መድፈር

አጥባቂ፣ ደን፣ ጠባቂ
- የተመደበበትን ሥራ በአግባቡ የሚወጣ

አጥባቂ ፈረስ፣ ከገደል ያደርስ
- ያመኑት ፈረስ በደንደስ ወደ ችግር ያደርሳል

አጥብቀህ ጉረስ፣ ወደ ዘመዶችህ ተመለስ
- ወገንህን አስታውስ

አጥብቆ ያሰረ፣ ዘቅዝቆ ይሸከማል
- አስተማማኝ ነው

አጥብቆ ጠያቂ፣ የናቱን ሞት ይረዳል
- አጥባቂ ፈረስ ከገደል ያደርስ

አጥፊና ጠፊ፣ ወናፍ እናፊ
- ቅርብ ለቅርብ

አጥፊው እልሚ፣ መስሎ ይታየዋል ለበው
- አንዳንዴ መባሳት ይኖራል

አጥፎቶ ይርቋል፣ አልሞቶ ይሞቋል
- አጥፊ ሁልጊዜም ጥፋቱን ስለሚያውቅ ይርቃል

አጭላጊ፣ ሠራቂ
- አታላይ መውሰድ የመስረቅ ያህል ነው

አጭር ባይኮራ፣ ረጅም ባይፈራ
- አጭር ሰው ዘዴኛ ነው

አጭር ባይኮራ፣ ነፋስ በወሰደው ነበር
- እራስን ገዝቅ ማድረግ ያዋርዳል

አጭር አህያ፣ ሁል ጊዜ ውርንጭላ
- አጭር ሰው አንቱ ባያባል ያረጃል

አጮላቂ፣ ሠራቂ
- ተሠርቆ ሰውን ማየት ያው የሌብነት ያህል ነው

አፈ ምላጭ፣ በደረቁ ይላጭ
- አፈቅቤ ልበጩቤ

አፈረች፣ ድብኝት አከለች
- ተሸማቀቀች

አፈ ቅቤ ልብ ይሰብር፣ አፈ ጩቤ አጥንት ይሰብር
- አታላይ

አፈኛ ባፉ፣ ኃይለኛ በመዳፉ
- ሁሉም ባለው ሙያ

አፉ ቅቤ፣ ልቡ ጩቤ
- በአፉ ጥሩ መስሎ በልቡ ግን ተንኮለኛ ሰው ነው

አፉን የረቱ፣ እጁን የመቱ
- ማስመሰል

አፉን ጠቅሞ፣ ወርቁን ቅሞ
- በአፍ እየለፈለፉ መጠቀም

አፉ ከኛ፣ ልቡ ከነኛ
- በአካል እንጂ በሐሳብ ከዚህ የለም

አፉ ከኛው፣ ልቡ ከወሬኛ
- መልካም መስሎ እያወራ የሚወራውን ወሬ ለሌላ ወስዶ ይናገራል

አፍላ ያለወጉ ፈላ
- ያለደንቡ ያለሥርዓቱ የሆነ ነገር

አፍ ሲነድ ሆድ ይንደድ
- ሁሉም የተያያዘ ነው

አፍ ሲናገር፣ ልብ ይንቃል
- ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት

አፍ ሲናገር፣ አፍንጫ ያሸሚጥጣል
- አፍ ሲናገር ልጅ ይንቃል

አፍ ሲከዳ፣ ከሎሌ ይብሳል
- ከአፍ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አያስታውቅም

አፍ ሲዋሽ፣ ሆድ ይታዘባል
- ሕሊና እውነትና ሐሰቱን ይገነዘባል

አፍ ሲያርፍ፣ ወዳጁን ያማል
- አላርፍ ያለች ጣት እር ጠንቁላ ትወጣለች

አፍ ሲያብል፣ ልብ ዳኛ ነው
- ሕሊና ምንጊዜም እውነትንና ሐሰቱን ያውቃል

አፍ ሲያድጥ ከዕዳ፣ እግር ሲያድጥ ከአንጋዳ
- ላያስቡት ተናግረው ችግሩ ውስጥ መግባት

አፍ ነገር፣ ሀይን አገር አያጣም
- ነገርን ካልረሱት ማየቱ አይቀርም



አፍና ቅብቅብ፣ ሁልጊዜ አይበላም
- ብልጠት ሁልጊዜ አያዋጣም

አፍና እጅ ዐይን የላቸው፣ ምንው አለመላላታቸው
- ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

አፍና እጅ፣ እጅና ፍንጅ
- ዘመድ ከዘመዱ

አፍንጫን ሲመቱት፣ ዐይን ያለቅሳል
- አብ ሲነካ ወልድ ይነካ

አፍ እላፊ፣ ያስከትላል ጥፊ
- ያልሆነ ንግግር ችግር ላይ ይጥላል

አፍ አኩል፣ ጉልበት ስንኩል
- ወሬ እንጂ ሥራ ላይ የለም

አፍ ካልተናገሩበት፣ እዳሪ ነው
- ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል

አፍ የሚጎርስውን እጅ ይመጥነዋል
- የሚሆነውን ሰው ገምቶ ሥራ ላይ ያውላል

አፍ ያለው ያግባሽ
- በአፉ አዳሪ ሥራ የማያውቅ ያግባሽ

አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል፣ ራሱ ተናግሮ ሰውን ያናግራል
- ሁሉም ነገር ይላካለታል

አፍ ያበዛ፣ ጥበቡ ዋዛ
- አፈኛ ሰው የሐሳብ ጥልቀት የለውም

አፍ ዳገት፣ አይፈራም
- መናገርና መሥራት ለየቅል

አፍጣኝና አቅጣኝ፣ አመዳሮው እንገናኝ
- ሆዱን ያመመው ሰው ወደ እዳሪ ሲሮጥ

## መልመጃ 8 /እ/

**ሀ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አሟላ**

1. ________ ሁልጊዜ አይበላም
   ሀ. ትምህርት　　ሐ. ሌብነት
   ለ. ገበያ　　መ. አፍና ቅብቅብ

2. አውሬ ከዋሻ ________ ።
   ሀ. አእዋፍ ከጢሻ　　ሐ. ጨነቀው መድረሻ
   ለ. በሬ ከርሻ　　መ. ጠመንጃው ከትከሻ

3. አለአንድ ጥርስ የላት ________ ትነቀስ
   ሀ. በግንዲላ　　ሐ. በወስፌ
   ለ. በእሾህ　　መ. በዘነዘና

4. ዐውቆ የተኛ ________ ።
   ሀ. ቢቀሰቅሱት ይነሳል　　ሐ. ሲቀሰቅሱት ይቆጣል
   ለ. ቢቀሰቅሱት አይሰማም　　መ. ዐውቆ ይነሳል

5. አትረፍ ያሰው በሬ ________ ።
   ሀ. ቆዳው ከበሮ ይሆናል　　ሐ. ሞቶ ሥጋው ይበላል
   ለ. ቆዳው ገበያ ይሸጣል　　መ. እንዳረሰ ይሞታል

6. አፍ ያሰው ________ ።
   ሀ. ሁሉም አለው　　ሐ. ይበረታል
   ለ. ጤፍ ይቆላል　　መ. ጮማ ይቆርጣል

7. ________ አንድ ሰው አሰቦ።
   ሀ. አንድ በቅሎ ሰቦ　　ሐ. አንድ አህያ
   ለ. አንድ በሬ ሰቦ　　መ. መልሱ የለም

8. አገር ያሰምክር ________ ።
   ሀ. ቤት ያለማገር　　ሐ. ዕዳ ያለብድር
   ለ. ትዳር ያሰ ፍቅር　　መ. ቤት ያሰ በር

9. አይቡ ዳኛ ________ ።
   ሀ. ሰውየው ሰቅሶኛ　　ሐ. ልጁ ;ነይሰኛ
   ለ. ቅቤው መልከኛ　　መ. እሬራው ጤነኛ



10. አንዱ ባንዱ ሲሥቅ ________ ።
   ሀ. ጊዜው ጥልቅ　　ሐ. ጀምበር ጥልቅ
   ለ. ምሽት ጥልቅ　　መ. ፀሐይ ጥልቅ

11. አህያ እንኳን በወለደች ________ ።
   ሀ. ትረገጣለች　　ሐ. ትጦራለች
   ለ. ታርፋለች　　መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

12. አሰሌ በጉማሬ ________ በወሬ።
   ሀ. ጥቅም　　ሐ. መንገድ
   ለ. ጉርሻ　　መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

13. አለማረፍ ________ መቆሰቆስ
   ሀ. ነገር　　ሐ. የተርብ ቤት
   ለ. እሳት　　መ. መልሱ የለም

14. አህያ የተጫነችውን፣ ________
   ሀ. አትበላም　　ሐ. ታሳርፋለች
   ለ. ታገኛዋለች　　መ. ሌላው ይበላዋል

15. አይጥ ሰሞቷ ________ ።
   ሀ. መፍራቷ　　ሐ. የድመት አፍንጫ ታሸታለች
   ለ. መከሳቷ　　መ. ሰትሔድ ታድራሰች

16. አካሔዱን ዐይተህ ________ ።
   ሀ. ናቀው　　ሐ. ጭብጦውን ቀማው
   ለ. አድንቀው　　መ. አስተምረው

17. አውራ የሌለው ንብ ________ ።
   ሀ. ይበታተናል　　ሐ. አለቃ የሌለው ሕዝብ
   ለ. ማር አይበጥም　　መ. መልሱ የለም

18. አይቶ አያውቅ ________ ።
   ሀ. ዳቦ ፍሪዳው ነው　　ሐ. አለቃውን ይንቅ
   ለ. ሰውን ይንቅ　　መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

19. አንድ እግረኛ ያወራውን ________ ።
   ሀ. ጥቂት ሰው ሰማው　　ሐ. ሺህ ፈረሰኛ አይመልሰውም
   ለ. ማንም እያዳምጠው　　መ. መልሱ የሰም

20. አታማባና ________ ።
   ሀ. ተንዘላዘል　　ሐ. አንጋጥጥ
   ለ. የሰው አጥር ዝለል　　መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

21. አትኩራ ገብስ ________ ።
ሀ. ጎመን ባወጣው ነብስ    ሐ. ባቄላ ባወጣው ነብስ
ለ. እንዳትወቀስ    መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

22. አመግል ብላ ________ ።
ሀ. አሳበጠች    ሐ. ጠነቀለች
ለ. ሌላ አቆሰለች    መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

23. አበተውሉ ላየው ________ ።
ሀ. ረኃብ አይኖርም    ሐ. ባቄላ ዐይን አላት
ለ. የሽንብራ አፍንጫ አለው    መ. ለ እና ሐ መልበ ይሆናሉ

24. ዓባይ ማደሪያ የለው ________ ።
ሀ. ግንድ ይዞ ይዞራል    ሐ. ምን ይበጃው
ለ. ዐፈር ይዞ ይዞራል    መ. ጭራሮ ይዞ ይዞራል

25. አለ አባት ________ ።
ሀ. ልጅ    ሐ. ጎመን ባጓት
ለ. አያምር ቤት    መ. ኩር ኩር አለ ባለቤቷ

26. አላጋጭ ገበሬ ________ ።
ሀ. ይሞታል በሰኔ    ሐ. አያጋጥም በሬ
ለ. አያርበም በበሬ    መ. አያርሰም

27. አባት ሳለ አጊጥ ________ ።
ሀ. ዘንጥ    ሐ. በጨለማ አትሯሯጥ
ለ. ጀንበር ሳለ እሩጥ    መ. መልሱ የለም

28. አንድ አይነድ ________ ።
ሀ. አንድ አይፈርድ    ሐ. አንድ አይገድል
ለ. ሦስት ይነድ    መ. ነፋስ ያጠፋል አመድ

29. አምና ከላሞቼ ________ ከጥጆቼ
ሀ. ዝንጀሮ    ለ. ውሻ    ሐ. ዘንድሮ    መ. አቻምና

30. አሞራ በዛፍ ________ በጫፍ
ሀ. ወፍ    ለ. ጦጣ    ሐ. ጉሬዛ    መ. ውርርድ

31. አለድሃ ዘውድ ________ ማዕድ
ሀ. አለባለቤት    ሐ. አለ እንግዳ
ለ. አለልጅ    መ. አለ ገበሬ

32. አለ ጨለማ ፍረኃት ________ ኩራት
ሀ. አለ ራስ    ሐ. አለ ፓሊስ
ለ. አለ ልጅ    መ. አለ ዘመድ



33. አሉ ቧልተኛ ________ አይተኛ
ሀ. ቀን ቀን    ሐ. ማታ ማታ
ለ. ሌት ተቀን    መ. ሁሉም መልስ ነው

34. አላሽከር በቅሉ ________ አምቧሮ
ሀ. አለ ፓሊስ    ሐ. አለ ጠብ
ለ. አለ ዘመድ    መ. አለ ወንድም

35. አላንኮበር ሾላ ________ አይገኝም
ሀ. ዐፈር    ለ. ሜዳ    ሐ. ከብት    መ. ዛፍ

36. አላሀንም አምናለሁ ________ እሥራለሁ
ሀ. አሀያዬንም    ሐ. ጥጃዬንም
ለ. ውሻዬንም    መ. ሁሉም መልበ ነው

37. ________ ልብስ አበላሽ
ሀ. አላዋቂ ልጅ    ሐ. አላዋቂ ሳሚ
ለ. ጋራዥ ሠራተኛ    መ. አላዋቂ ለባሽ

38. ________ ንፍጥ ይለቀልቃል
ሀ. አላዋቂ ልጅ    ሐ. አላዋቂ ሰሚ
ለ. አላዋቂ አጉራሽ    መ. ሁሉም መልሰ ነው

39. አላዋቂ ካረዳው ________ ያወራረደው
ሀ. ዐዋቂ    ለ. ብልጥ    ሐ. ሞኝ    መ. ባላገር

40. አላጋጭ ________ ።
ሀ. ያናድዳል    ሐ. አልማጭ
ለ. ሽርዳጅ    መ. ሁሉም መልበ ነው

41. አልበሜን ________ ።
ሀ. ሒድ በለው    ሐ. አምልጥ በለው
ለ. ተደበቅ በለው    መ. ግባ በለው

42. አልቀባም ብትል ________ ።
ሀ. ትመሰክር    ሐ. ትቀባ
ለ. ታቃጥር    መ. መልሱ የለም

43. አልቅትና ድሃ ________
ሀ. ወንዝ ለወንዝ    ሐ. ውኃ ለውኃ
ለ. ጅረት ለጅረት    መ. ሁሉም መልሰ ነው

44. አልጋው ሲገኝ ________ ።
ሀ. ዕቃው አይገኝ    ሐ. ብርድልብሱ አይገኝ
ለ. ፍራሹ አይገኝ    መ. ባሉ አይገኝ

45. አመሌ አወጣኝ ________ ።
ሀ. ከሥራዬ ሐ. ከማኅበሬ
ለ. ከከርቸሌ መ. ከበሽታዬ

46. ________ ዝንጀሮን ተመልከት
ሀ. አካሔድ ሐ. አዘላለል
ለ. አኗኗር መ. አመካከት

47. አመድ ________ ይሥቃል
ሀ. በአመድ ሐ. በሸርክት
ለ. በጥሬ መ. በዱቄት

48. አማች የበላው ________ የበላው።
ሀ. ጠላት ለ. ውኃ ሐ. ወንበዴ መ. አላት

49. አሞራ በበላ ________ በዱላ
ሀ. ዳውላ ሐ. አህያ
ለ. ጥፍ ጥሬ መ. ሁሉም መልስ ነው

50. አርሶ ያልጠገበ ________ አይሆንለትም።
ሀ. ኮትኩቶ ለ. ልመና ሐ. ነግዶ መ. አወናብዶ

## መልመጃ 8 /ለ/

ለ. <u>የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች ፍቺ ስጡ</u>

1. አትርፍ ባይ አጉዳይ
ሀ. ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል፣ የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
ለ. በገዛ ራሱ አባብ ጠመጠመ
ሐ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
መ. ሁሉም መልስ ነው

2. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ
ሀ. እንበላ ሳይገድሉ፣ ቆዳውን ያስማማሉ
ለ. ሳይገድሉ ጎፈሬ ሳያዳምጡ ወሬ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

3. አገባሻለሁ ያለሽ ሳያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
ሀ. የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም
ለ. የማያድን ጋሻ ጎን ይሰብራል
ሐ. ከእጅ አይሻል ዶማ
መ. ሁሉም መልስ ነው



4. አለባብሰው ቢያርሱ በዐረም ይመለሱ
ሀ. ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
ለ. ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

5. አሞራን ሲበሉት ለሙን ኾርግራ ይሉ
ሀ. አያጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ
ለ. ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ስሟን ይሏታል ኾርግራ
ሐ. ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

6. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
ሀ. ተኩላ እንደአንበሳ እጮሃለሁ ብላ ተተረተረች
ለ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሐ. አትርፍ ባይ አጉዳይ
መ. ሁሉም መልስ ነው

7. አፍ ሥራ ሲፈታ ወዳጁን ያማል
ሀ. ሥራ ከመፍታት ልጄን ላፉታት
ለ. ሥራ ያጣ መነኩሴ፣ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
ሐ. ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይገባል
መ. ሁሉም መልስ ነው

8. አያ ጅቦ እንኳን ድኅ፣ በልተህ ድሮውኑ ጪሂ ነህ
ሀ. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
ለ. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

9. አረምን መንቀል ሥር ሳይሰድ ነው
ሀ. ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቆረጠምም
ለ. ሳይቃጠል በቅጠል
ሐ. ልጅን መቅጣት በጡት
መ. ሁሉም መልስ ነው

## መልመጃ 8 /ሾ/

### ሐ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | እይጥ ሞትዋን ሰትሻ ስታበዛ ፋጫ፣ ሄዳ ታሽታለች የድመት አፍንጫ | ሀ. | ውሻ ወደ ጥጥ፣ ሚዳቋ ወደሊጥ |
| 2. | አሥር ያባረረ አንድ አይዝም | ለ. | ሳይገድሉ ጎፈሬ፣ ሳያደምጡ ወሬ |
| 3. | እህያ ወደ ጅብ ውሻ ወደግጦሽ የተገላቢጦሽ | ሐ. | የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ያስጣል |
| 4. | አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል | መ. | ጮሌ ሲያረጅ መጋጃ ይሆናል |
| 5. | አንበሳ ሳይገድሉ፣ ቆዳውን ያስማማሉ | ሠ. | ወዴት ትሔዳለህ? ወደበለሳ ሰሴን የለህምሳ? |
| 6. | አለባለቤቱ አይነድም እሳቱ | ረ. | ሙከት ሲሰባ ሾተል ይልሳል |
| 7. | አይጠትም ጠላ ባልና ሚስት እጣላ | ሰ. | መሬት ሲያረጅ፣ መጅ ያበቅላል |
| 8. | አዞ እንድም ተናዞ እንድም ሰንት ይዞ | ሸ. | ሁለት የተመኘ አንዱንም አላገኘ |
| 9. | አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል | ቀ. | ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም |
| 10. | አንድ ግንድ ለሺህ እይከብድ | በ. | አህያውን ፈርቶ ዳውላውን |
| 11. | እልሞት ባይ ተጋዳይ | ተ. | አምና የሞተውን ጥጃ ሰደዱ |
| 12. | አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም | ቸ. | አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል |
| 13. | አላዋቂ ተራች፣ የራሉን እመልካች | ኀ. | ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራል |
| 14. | አብ ሲነካ ወልድ ይነካ | ነ. | ኸብ ከሚበላኝ ኸብ በልቼ ልቀደስ |
| 15. | አዶጥ በበላ ዳዋ ተመታ | ኘ. | ሃምሣ ሎሚ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ለአንድ ሰው ግን ሸክሙ ነው |
| 16. | አህያ በሞተች ባመቱ ኩርኩር | አ. | የዘመድ ጥል የሥጋ ትል |
| 17. | ዐዋቂ ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል | ከ. | ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም |
| 18. | አፍንጫ ሲመቱት ዐይን ያለቅሳል | ኸ. | ሐሰተኛ በውሸተኛነቱ ራሱን በራሱ ይነቅፋል |
| 19. | እንዱን ሳይዘው፣ ደረሰ ጊዜው | ወ. | ከአንበሳ መንጋጋ ማን ያወጣል ሥጋ |
| 20. | አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው | ዘ. | የሰው እባት የሚሰድብ አባቱን ያሰድብ |
| 21. | እንቺ ምትችገረሽ ሁለት አባት አለሽ እንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ | ዠ. | ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ |
| 22. | እንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ | የ. | ሁሉ አማረሽን ገበያ እታውጧት |
| 23. | አፍ ሲዋሽ ሆድ ይታዘባል | ደ. | የተጠቃ ሳለ፣ ያልተጠቃ ያማርራል |
| 24. | አህያውን ሲፈሩ ዳውላውን መቱ | ጀ. | የሚያልፍ ቀን፣ የማያልፍ ስም ይሰጣል |
| 25. | አሁን የሚያልፍ ውኃ፣ አደረገኝ ድሃ | ገ. | ዝሆን ሳለ ዱካውን |



## እ

እሄድ ባይ፣ ስንቅ ፈጅ
- ሳይሔድ ከወዲሁ ስንቁን የሚጨርስ

እህል ለቀጠና፣ ወርቅ ለዝና
- ለችግር ጊዜ እህል ለዝና ደግሞ ጌጥ ያስፈልጋል

እህል ላራሹ፣ ርስት ለወራሹ
- ሁሉም ለባለቤቱ ጥቅም ነው

እህል ላበደረ ዐፈር፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር
- መልካም ሥራ ለሠራ መጥፎ ነገር ማድረግ

እህል ሲያጡ፣ የናት ልጅ ያጡ
- በችግር ጊዜ ወዳጅ የለም

እህል ሲገኝ፣ ወፍጮ ይሟልጣል
- አልጋው ሲገኝ ባሉ እይገኝ

እህል ሲጠፋ ወፍጮ ይሰላል፣ እህል ሲገኝ ወፍጮ ይደንዛል
- ድሃና ገበያ ሳይገናኙ ይኖራሉ

እህል ሲጠፋ፣ ወፍጮው ይቀራል
- ባልሆነ ጊዜ የሚገኝ ጥቅም ላይ የማይውል

እህል በቀርበቦ፣ እንቁላል በወታቦ
- ለእህል የሚሆነውን ለእንቁላል፣ ለእንቁላል የሚሆነውን ለእህል ማድረግ የተገላቢጦሽ

እህል በጥቅምት፣ ልጅ በጡት
- በወቅቱ የተደረገ ነገር ውጤቱ ጥሩ ነው

እህል ከበዩ፣ ሰው ከገዳዩ
- በሬ ከአራጁ ይውላል

እህል ከባዶ፣ ልጅ ከጎዶ
- አንዳንዴ መልካም ነገር ከእጉል ቦታ ይገኛል

እህል ከውድማ ብቻውን ዋለ፣ እያሌ ሰዎችን እንዳገለለ
- ተፈላጊው ነገር እንደማይፈለግ ሁሉ ብቻውን መዋሉ

እህል ከዘባጣ፣ ልጅ ካርጣጣ
- መልካም ነገር ካልሆነ ቦታ የሚገኝበት ጊዜ እለ

እህል ከዱር፣ ልጅ ካጉል
- መልካም ነገር ካልሆነ ቦታ እንዳንዴ መገኘቱ

እህል ካልተለወጠ፣ ነገር ካልተደመጠ
- የነገር ወጡ ማዳመጡ

እህል ወዳዱን ይጎዳል
- እንዳንዴ የሚወዱትን ሳይውቁ መጉዳት ይኖራል

እህል የበቀለበትን ያስታውቃል
- መልካም ቤተሰብ ውስጥ ያደገ ልጅ ከሥነምግባሩ ያስታውቃል

እህል የያዘ ፈርዛዛ፣ ወርቅ የያዘ ቀበዝባዛ
- ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ዕቃ የያዘ ሰው ይነጥቁኛል በሚል ይቅበዘበዛል

እህል ያለ ውኃ፣ ንጉሥ ያለድሃ
- እንዱ ያለእንዱ አይኖርም

እለት ቆይቶ ላመት
- ትንሿ ተጠራቅማ ትልቅ ወይም ብዙ ትሆናለች

እልልታ ለደስታ፣ እሪታ ለርዳታ
- የበጎና የክፉ ነገር መገለጫዎች ለየቅል ናቸው

እልከኛ መኻገር፣ ከላም ጡት ተጣብቆ ይገኛል
- ተንኮለኛ መልካሙን ሁሉ ለመጉዳት ያሸምቃል

እልክ ምላጭ፣ ያስውጣል
- እልህ እራስን ይጎዳል

እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል፣ ድሃ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል
- ያልተገላበጠ ያራል

እማን ላይ ቆመሽ፣ እግዜርን ታሚያለሽ
- ያለሽበትን ሁኔታ ተረጂው

እማኝ ሲገዙ፣ ነገር እያብዙ
- ፍሬ ነገር እንጂ ዝርዝር አይጠቅምም

እምብዛም ስለት፣ ይቀዳል አፎት
- መጠንን ያለፈ ነገር ችግር ያስከትላል

እምብዛም ብለሃት፣ ያደርሳል ከሞት
- መጠንን ያለፈ ነገር ችግር ያስከትላል

እምድር የወደቀ ሥጋ ዐፈር ሳይዝ አይነሳም
- ግጭት ካለ በግጭቱ የሚጎዱት ከዚህም ከዚያም ነው

እረባዳ ቤቱ፣ ገራም ሚስቱ
- የተመቻቸ መልካም ኑሮ

እረኛ ቢያኮርፍ፣ እራቱ ምሳው ይሆናል
- ዞሮ ዞሮ የሚጎዳው ራሱ ነው

እሩቅ አሳቢ፣ እቅርብ አዳሪ
- ሰው ባሰበው መጠን ላይሳካለት ይችላል

እሪ በከንቱ፣ ማን ሲሰማው ነው ጩኸቱ
- መፍትሔ ለሌለው ነገር መድከሙ አላስፈላጊ ነው

እራስ ከተመለጠ፣ ነገር ካመለጠ
- ከአፍ ከወጣ አፋፍ

እራቁቱን የተወለደ ልጅ፣ ለምድ አነሰው ወይ
- ምንም ለሌለው ጥቂት ቢያገኝ መች ያንሰዋል

እራት ሲበሱ፣ የመጣ እንግዳ እራቱ ፍሪዳ
- ሁሉ ነገር ከተሟላ ቤት እንግዳ ከመጣ ለማስተናገድ አይቸግርም

እራት ሲበሉ የመጣ፣ ይቆጠራል ፍሪዳ እንዳመጣ
- አሰደሳች እንግዳ

እራት ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ፣ ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ
- በንቀት ምክንያት የሚመጣ ጦስ ከባድ ነው



እራት የለህም ቢሉት፣ ከወጡ እውጡልኝ አለ
- ተጨማሪ ነገር ተመኘ ያንንም ሳያገኝ

እራት የሌላው ቄስ፣ እንደልቡ አይቀድስ
- ምግብ ካለገኘህ መሥራት አትችልም

እራት የሌላት፣ ምሳ አማራት
- ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት

እራት፣ የለማይ መብራት
- እራት በልቶ ማደር ተገቢ ነው

እሬት ለቀመሰው፣ እንጂ፣ ላልቀመሰው አይመርም
- ጉዳትን የሚያውቅ ጉዳት የደረሰበት ነው

እርም፣ ለትህትና
- ከእንግዲህ ትህትና የሚሉትን አልደግመውም

እርሟን ብታፈላ፣ አንድ ቁና አተላ
- የመጀመሪያ ቀን ብትሠሪ አበላሸሽው

እርሟን ብታፈላ፣ ጋን ሙሉ አተላ
- የመጀመሪያ ቀን ብትሠራ አበላሸችው

እርሟን ጠምቃ፣ ፈጀችው ጠልቃ ጠልቃ
- ማዳረስ አልቻለችም አባከነችው

እርሱ ራሱ ጊዜ መሆኑን ባያውቀው፣ ጊዜ ጊዜ ይላል ሞኝ ሰው
- ጊዜን ሊጠቀምበት ወይም ላይጠቀምበት የሚችለው ሰው ነው

እርሱ ካለው ላያልፍ፣ ምነው በሽተኛው ባይለፈልፍ
- ለማይቀር ዕዳ መጨነቅ አይገባም

እርስ በርሱ፣ ሥጋን በኩበት ጠበሱ
- ተደጋገፉ ተረዳዱ

እርስ በርሱ የተከፋፈለ፣ ቤት አይቆምም
- እርስ በርሱ ሲናቆር ለጠላት የተመቻቸ ይሆናል

እርስ በርሱ ያልተደጋገፈ፣ ግድግዳ አይቆምም
- ካልተባበሩ ሁኔታዎች አይሟሉም

እርሱ አይወደኝ፣ መከራው አይለቀኝ
- መከራና ችግሩ ለእኔው ይተርፈኛል

እርሻ ለባለ ከብት፣ ርስት ለባለርስት
- ላለው ይጨመርለታል

እርሻ ላጥማጅ፣ መሬት ለተወላጅ
- ዞሮ ዞሮ የቤተሰብ ሀብት ያው ለተወላጅ ነው የሚከፋፈለው

እርሻ ሲሉ፣ ሞፈር ቆረጣ
- ሥርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

እርሻ ቢያለሰልሱ፣ እህል ያሳምራል፣ ገንዘብ ቢያከማቹት ያኮራል
- ማንኛውም ነገር በሥርዓት ከተሠራ ውጤት ይገኝበታል

እርሻ ቢያርሱ፣ እንደልብ ያጎርሱ
- ሥራውን በደንብ የሠራ ሀብት ያገኛል
- ለሌላ ሰውም ይተርፋሉ

እርሻው ሲያምር፣ ዳቦው ያምር
- ሲያዩት ያማረ ነገር መጨረሻው ጥሩ ነው

እርሻ ያውቋል፣ ይጠብቋል
- አዋቂ ሰው ያለውን ንብረት ይንከባከባል

እርሻ ደጉ፣ ሳይደገድጉ
- ጠንክሮ የሠራ የሰውን እጅ አያይም

እርሻ ጋራ ፀሮ፣ የጎረቤት ዶሮ
- ተለፍቶ፣ ተደክሞ የሚገኝን ያልለፋው ሊበላ ይመኛል

እርኩም ይህን እስክበላ፣ ዕድሜ ስጠኝ ይላል
- የነገውን ነገ ያውቃል

እርኩም ጉድ ባይ፣ ጠጣ አታላይ
- አንዱ ሲያታልል ሌላው በመታዘብ ጊዜውን ይፈጃል

እርያ በሬ፣ አይደለም
- የሚበላውንና የማይበላውን ለይተህ ዕወቅ

እርጅና፣ ብቻህን ና
- ሕመምና ድህነትን አታምጣብኝ

እርጉዝ ላም ያለው፣ ደረቅ አያንቀው
- ተስፋ ያለመልማል

እርጉዝ ሲያርዱ፣ በወዳጅ ቢፈርዱ፣ ሆድ መርበድበዱ
- በወዳጅህ ላይ አትጨክን

እርጉዝ ያቅፉ ይደግፉ
- አቅመ ደካማን መርዳት ተገቢ ነው

እሠራለሁ ብላ ሔዳ፣ ተላጭታ መጣች
- ሲያጌጡ ይመላለጡ

እስር በፍንጅ፣ ጣል በደጅ
- አንዴ ከያዝክ አጥብቅ አትልቀቅ

እቡ እርጥብ፣ ነገሩ ደረቅ
- ስውዬውና ተግባሩ የተለያየ ነው

እሳት ለፈጀው፣ ምን ይበጀው
- ለተቸገረ ሰው መፍትሔው ምን ይሆን

እሳት መጣብህ ቢሉት፣ ሣር ውስጥ ገብቻለሁ አለ
- ክፋውንና በጎውን ለይቶ የማያውቅ

እሳት በሌለበት፣ ጢስ አይኖርም
- ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

እሳት ቢቀርቡት ያሳክካል፣ መነኩሴ ቢቀርቡት ይልካል
- መልካም ነው የሚባለው ሁሉ ሲበዛ ወይም ሲቀርቡት ጉዳት ይኖረዋል

እሳት ቢያንቀላፋ፣ ገለባ ጎበኘው
- በግ ባልበላሽ ትበይኝ

እሳት ቢዳፈን፣ የጠፋ ይመስላል
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል



እሳት ቢፈጃት፣ ወደልጇ ጣለች
- ህ - ራስን ማዳን

እሳትና ነገር ቢያጋንኑት ይጋነናል
- ነገር እንዳደረጉት ነው፤ ሲተዉት ይተዋል

እሳትና ነፋስ፣ ማርና መላስ
- አንዱ ላንዱ ጠቃሚ ነው

እሳትና ነገር፣ ትንሽ ይበቃዋል
- ነገር ካጋነኑ ይጋነናል

እሳትና ድሃ፣ ሲነካኩት አይወድም
- ድሃ በቀላሉ ሆድ ይብሰዋል

እሳትና ጥል የቀረበውን ያቃጥል
- እሳት ጠቃሚ ቢሆንም ሲቀርቡት ጉዳት ሊያስከትል ይችላል

እሳትና፣ ጭድ ናቸው
- አይስማሙ

እሳት እስ ዕንጨት አይስማ፣ ጆሮ ዕዳውን አይሰማ
- ያስባለቤቱ አይነድም እሳቱ

እሳት፣ አመድ ይወልዳል
- ጎበዙ ስነፍ ሰው ወለደ

እሳት ከበላው፣ ወራሪ የዘረፈው
- በእሳት የተቃጠለ ነገር ወደቀድሞ ይዞታው ሊመለስ አይችልም

እሳት ከበረበረው፣ ሴት የመከረው
- ሴት የላከው ሞት አይፈራም

እሳት ካልነደደ፣ አይበራም
- የአንድን ሰው ማንነት የሚታወቀው ቀርበው ሲያዩት ነው

እሳት ካየው፣ ምን ለየው
- በእሳት የተቃጠለ ነገር ዋጋ የለውም

እሳት፣ የገባ ቅቤ
- መልስህ የማታገኘው

እሳት ጭሮ፣ ከነፋስ ላይ
- የሚመጣውን አስቀድመህ ለማወቅ ሞክር

እስላም ሲከብር ሴት፣ ክርስቲያን ሲከብር መሬት ያበዛል
- የሚጠቅመውን ባለቤቱ ያውቃል

እስራኤልና ፀሐይ እማይደርስበት የለም
- በየትኛውም ክፍለዓለም እሥራኤላውያን ይኖራሉ

እስኪያልፍ ያለፋል
- ትዕግሥት ያስፈልጋል

እስክትመጣ እህያ፣ ቀንድ ታበቅላለች
- ከሔደችበት ቶሎ አትመጣም

እሷ ሠርታ፣ እሷው ታፈርሰዋለች
- አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው

እሷ ሰንፋ ራቷን ገንፎ አድርጋ፣ ቢያጎርሷት ተኮሳት
- ያነደድኩት እሳት ፈጀኝ

እሷ ነፍጋ ራቷን ገንፎ አድርጋ፣ ቢያጎርሷት ተኮሳት
- ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ

እሷ በፈሳችው፣ በኔ ለከከችው
- ጥፋትን በሌላው ላይ ማሸጋገር

እሷው ሞታ፣ እሷው መርዶ ጠርታ
- የማይታመንና ሲሆን የማይቻል ነገር

እሷው ወልዳ አልመሰሰም፣ እሷው ጋግራ አልበሰለም
- ሞኝና ቆቅ በራሱ ያወራል

እሷ ጣፋጭ፣ ልጅቱ ቆንጣጭ
- በተግባር የማይገናኙ

እሸት በወረት፣ እህል መውቃት በከብት
- በዘዴ በስልት የሠሩት ሥራ አያደክምም ውጤትም ይኖረዋል

እሺ ባይ አክባሪ፣ እምቢ ባይ አቅላይ (አሳፋሪ)
- እሺ ይበልጣል ከሺ

እሺና ገለባ፣ አይከብድም
- እሺ ይበልጣል ከሺ

እሸት አርገህ ቅዳው፣ እንዳይጎሽ ጠላው
- እንዲሆን የምትፈልገውን አስቀድመህ አሰብበት

እሾህ ለረጋጩ፣ ነገር ላምጪው
- ነገር የሚጎዳው ነገር አምጪውን ነው

እሾህ በሾህ ይነቀሳል፣ ገንዘብ በገንዘብ ይመለሳል
- እርስ በርሱ

እሾህ በሾህ ይወጣል፣ ሰው በሰው ይመጣል
- ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው

እሾህን በሾህ
- እርስ በርሱ

እሾህ አጣሪውን፣ ነገር ፈጣሪውን
- እሾህ ላጣሪው ነገር ለሠሪው

እበላ ባይ ቃል አቀባይ
- ያጣ ሰው ለማግኘት ሲል የማያደርገው ነገር የለም

እበላ ብዬ ተበላሁ
- አገኛለሁ ብዬ ጉዳት ደረሰብኝ

እበላ ብዬ ተበላሁ፣ ምነው ሳልበላ በቀረሁ
- እንዲህ ያለ ችግር ውስጥ ከምወድቅ ፊቱኑ በቀረብኝ

እበላ ያለ ዳኛ፣ እገደል ያለ ደመኛ
- ሁሉቱም አድብተው ይጠባበቃሉ

እበት ትል፣ ይወልዳል
- ከወላጆቹ አንዱ የማይረቡ ናቸው



እበት ትል ይወልዳል፣ ድሃ እብሰት ይወዳል
- ለመኖር ሲል የሚያደርገው ነው

እበትና ኩበት፣ ወገንና ኩበት
- ሁበትና ወገን እንደሚያስፈልጉ ሁሉ ኩበት ለማገዶነት ያስፈልጋል

እባብ ለእባብ፣ ይተያያል ካብ ለካብ
- ምላጭን ምላጭ አይቆርጠውም

እባብ ላይበላው አብላላው
- ላይጠቀምበት ለካከፎት ወይም ነካከቶት ተወው

እባብ ሲያዩት ይለሰልሳል፣ ጌታ ቢሜወት ባልንጀራ ይመስላል
- ጉድና ጅራት ከወደኋላ ነው

እባብ ስለሆዱ፣ ይሔዳል በሆዱ
- አንዳንዱ ስሆዱ ሲል ያላመነበትን ይፈጽማል

እባብ ቀጭን ነው፣ ተብሎ ራሱ አይረገጥም
- በአቋሙ ሰውን መናቅ አያስፈልግም

እባብ በምድር ተጋድሞ፣ ሰው በትር ይዞ ቆሞ
- ጠላት በእጅህ ገብቶ ምን ትጠብቃለህ

እባብ በራሱ ላይ የጠመጠመው፣ ከሰይፍ ላይ እግሩ የቆመ
- ችግርን ሆን ብሎ በራሱ ላይ የፈጠረ

እባብ በእግርህ፣ በትር ከጅህ
- ጠላትህ በእጅህ ገብቶ ምን ትጠብቃለህ

እባብና ጓንቸር፣ ባንድ ይኖራሉ
- ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

እባብን ሞቶ ብሎ፣ ራሱን መርገጥ መቅበጥ
- ጠላትህን መናቅ የለብህም

እባብ ሀፈር ያልቅብኛል፣ ብሎ ሲሰት ይኖራል
- የሕይወቱ መገኛ በመሆኑ ነው

እባብ እንደ መለሰለስሽ፣ ቅናት ዮሐንስ በሆንሽ
- ተንኮል ያሰበት ጥሩ ይመስላል አይታወቅበትም

እባብ የልቡን፣ አይቶ እግር ነሳው
- እግር ቢኖረው ኖሮ ፍጥረቱን ሁሉ ምን ያደርገው ነበር

እባብ የሚገለው፣ በምላሱ እኮ ነው
- ክፉ ንግግር ለትልቅ ወንጀል ያነሳሳል

እባብ ያየ፣ በልጥ በረየ
- ሥጋ ያንገፈገፈው ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል

እባብ ጉድጓዱን አይስት
- ቀማኛ ዋሻውን፣ ድሃ ስልቻውን

እባብ ጉድጓዱን፣ ሙሻ ጌታውን
- ቀማኛ ዋሻውን፣ ድሃ ስልቻውን

እባብ ግደል፣ ከነበትሩ ገደል
- ተንኮለኛን እስከመጨረሻው ማስወገድ ይገባል

እባብ ጥበስልኝ፣ ይብረድልኝ
- ተንኮለኛን በጊዜው ካላስወገዱት ያልታሰበ ነገር ያመጣል

እባክህ አታጋልጠኝ፣ ለጠላት አትስጠኝ
- በጠላት እጅ ከገባሁ መትረፊያ የለኝም

እባክሽ ያሏት ጎረቤት፣ ትሆን እመቤት
- ሰው ሲለማመጡት ጌታ ወይም እመቤት የሆነ ይመስለዋል

እቤት ሆኖ ካሰበ፣ ሔዶ ያልሰጠ በለጠ
- ከሐሳብ ጥቂትም ቢሆን ተግባር ይበልጣል

እቤት ዶሮ ሲታረድ፣ እዱር ቆቅ ይያባል
- አንዴ ጥሩ ነገር ካጋጠመህ በላይ በላዩ ይመጣል

እታከል ከግመል
- እጉል የማይሳካ ፉክክር

እቴ ከሆንሽ ካለስሜ እታልቅሽ
- የምታደርጊውን ሁሉ ለማን እንደምታደርጊ ዕወቂ

እናቱ የሞተችበትና፣ ውኃ የወረደች፣ እኩል ያለቅሳሉ
- ከባድ ችግር የደረሰበትና ቀለል ያለም ችግር የደረሰበት እኩል ያለቅሳሉ

እናቲቱን አይተህ፣ ልጅቷን አግባ
- ቅርንጫፉ እንደባፉ

እናቲቱ ዶሮ፣ ልጅዋን ይፃ ጓሮ ለጓሮ
- ለልጅዋ የሚጠቅመውን ለማፈላለግ

እናቴን ላህል፣ በጠኝ ወር ቀረኝ አለች
- እጉል ውድድር

እናቴን ላይ ሴት ማግባቴ፣ ቤቴን ላይ ትምባሆ መጠጣቴ
- ለቤቴ የማይጠቅመውን ተግባር መፈጸሜ ያስቆጨኛል

እናት ለልጅዋ፣ ነቢይ ናት
- እናት ለልጅዋ ታስባለች

እናት ትረገጣለች፣ እንደ መሬት
- ለልጇ ስትል እራሷን ትበድላለች

እናትና ልጅ ቃል ተባሉ
- ተካካዱ

እናት የሌለው ተጓዳጅ፣ እርሻ የሌለው ጠላ ወዳጅ
- ሥራ ሳይሠራ የሚገኝ ነገር የለም

እናንተ ዘንድ ሔዳ ከመጣች፣ ከእንብላው በቀር ሥራ አጣች
- መጥፎ ምክር ኑሮህን ያበላሽዋል

እናያለን ሲሉ ይታያሉ፣ እናማለን ሲሉ ይታማሉ
- በሌላው ላይ ሊፈጽሙት የሚያስቡት ሁሉ በእነሱ ላይ ይደርስባቸዋል



እኔ ልብላ አንተ ጦም እደር
- ራስ ወዳድነት

እኔ መሞቼ፣ እኔው ቂስ ጠርቼ
- እሱ ሞቶ እራሱ መርዶ ጠርቶ

እኔ ሳጣ፣ ልጇ ጥርስ አወጣ
- በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

እኔ በልጇ ሳዝን፣ ልጇ በልጁ ያዝን
- ሰው የእጁን አያጣውም

እኔ ባልኩ፣ ይልኩና ይላኩ
- ባልኩት መሠረት ይፈጸማል

እኔን ሲፈጅኝ፣ ልጇን ያቃጥለው
- እሱን በደንብ አድርጎ ጉዳቱ ይሰማው

እኔን አይተህ ተቀጣ፣ በጉድህ እንዳትወጣ
- ከእኔ ትምህርት ውሰድ

እኔን የወደደ ከንጀት፣ ልጇን የወደደ ከንገት
- መውደድ ለየቅል ነው ሁሉን እኩል አይወዱ

እኔ አለኝ ቁስል፣ ያንቱን የሚመስል
- እኔም እንዳንተው ነኝ

እኔ እውነት እናገራለሁ፣ ሌላውን አስኮንናለሁ
- እውነትን በመናገሬ በሌላው ላይ እንዲፈረድበት አደርጋለሁ

እኔ ከሞትኩ፣ ሰርዶ አይብቀል፣ አለች አህያ
- ከራስ በላይ ነፋስ

እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ፣ ገብስ የሚደርሰው ለፍልሰታ
- ለችግሬ የሚደርስልኝ የለም ከሞትኩ በኋላ እንጂ

እንሒድ ዘገዩ ይሉናል፣ ግድ የለም ስንገባ ያምኑናል
- ከመቅረት መዘግየት

እንሰራዋን ረስታ፣ ውኃ ወረደች
- ሥራ የምትሠራበትን መሣሪያ ረስታ ለሥራ ባዶ እጇን ሄደች

እንሰራዋን ጥላ፣ ወንዝ ወረደች
- ሥራ የምትሠራበትን ዕቃ ረስታ ባዶ እጇን ሔደች

እንቅልፍ ታበገር፣ ከነበር ትፋዘሻ
- ስለነበር፣ ስላለፈው ስታወሪ ጊዜሽን በከንቱ ታጠፊዋለሽ

እንቅልፍና ሞት፣ እሬትና ሃሞት
- አንዴ ከተኙ በኋላ ምንም ነገር አይታወቅም

እንበለ ገንዘብ መዝናናት፣ ያመጣል ውርደት
- ገንዘብ ሳይዙ መዝናናት ውርደት ላይ ይጥላል

እንባ ሲሻኝ፣ ዐይኔን ጢስ ወጋኝ
- እንኳን እናቴ ሞታ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል

እንኩን የማያውቅ፣ ስጡኝን ማን አስተማረው
- ሌላ ሰውን የማይረዳ ሰው እንዴት ዕርዳኝ ይላል

እንኳን ለህቴ ለሌላም ይዘፍናል አንገቴ
- እንኳን ለሚቀርበኝ ሰው ሌላም ሰው ቢሆን አገለግላለሁ

እንኳን ለራሱ፣ ለሰው ይተርፋል እሱ
- እንኳን ለሚቀርበኝ ሰው ለሌላም ሰው ቢሆን አገለግላለሁ

እንኳን ለቤቱ፣ ይተርፋል ለጎረቤቱ
- እንኳን ለዘመዴ ለሌላም ሰው ቢሆን አገለግላለሁ

እንኳን ለገንፎ፣ ለሙቅም አልደነግጥም
- ምንም የሚያጓጓኝ ነገር የለም

እንኳን ሲያበሉኝ፣ ገርፈው ለደዱኝ
- እጠቀም ብዬ ብሔድ አስቃይተው ሰደዱኝ

እንኳን ሲሸጡኝ፣ ሲያስማሙኝ ዐውቃለሁ
- ማንም ሊያታልለኝ አይችልም

እንኳን ተልባ ሸቶሽ፣ እንዲያውም ዘጠኝ ቂጣ ትፈጃለሽ
- መልካም ነገር ካገኘሽ ከዚህ ተመለሺ አትባይም

እንኳን ልመነኩስ፣ አልከናነብም
- ምንም አልለወጥም

እንኳን እናቴ ሙታ፣ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል
- ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው

እንኳን ከፎከረ፣ ያድናል ዓምላክ ከወረወረ
- እንኳን ከቀላል ከእሳት ያወጣል ዓምላክ

እንኳን ዘንቦብሽ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
- በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ

እንደ ልብ የለም ነዳጅ፣ እንደልብ የለም በራጅ
- የልብን የሚያደርስ ነገር ሲገኝ ያስደስታል

እንደ ልጅ በቀለበት፣ እንደድመት በወተት
- አንድን ሰው በማይረባ ነገር መሸንገል፣ መደለል

እንደ መረብ ሸፍኖ፣ እንደ እንቁላል ደፍኖ
- አንድ ነገር ሳይታይና ሳይመረመር ገፋ ገፋ ማድረግ

እንደ ርግብ የዋህነት፣ እንደ እባብ ብልህነት
- አስተዋይና ብልህነት ይኑርህ

እንደ ሣር ነጭቶ፣ እንደ ውኃ ተጎንጭቶ
- ያልሆነን እንደሆነ በመቁጥር

እንደ ሰው ትመጪ፣ እንደ አውሬ ትሮጪ
- ባሕርይሽ አይታወቅም አስቸጋሪ ነሽ

እንደ ሻሽ ተነጥፎ፣ እንደቅጠል ረግፎ
- አንድ ነገር ለማግኘት የመለመንና የመለማመጥ ሁኔታ

እንደ ሸመላ፣ በሁለት ይበላ
- በሁለት ቢላ የሚበላ

እንደ ቆጫት ተነሥታ፣ የበው ልቅሶ አጥፍታ
- በንዴት አንድን ጉዳይ ለመፈጸም ማሰብ ችግር ሊያስከትል ይችላል



እንደ በሶ አንቆ፣ እንደ ርጉዝ አስጨንቆ
- የግድ ያለውድ የሚፈጸም ተግባር

እንደ ተተከለ፣ ትርሽማ፣ እንደተሰጣ ሸማ
- ይበጃል ያሉት በፍጥነት ከጥቅም ውጪ ሲሆን

እንደ ንብ ቀስሞ፣ እንደወጥ ቀምሞ
- ተጨንቀው ተጠብበው የሠሩት ሥራ ጥሩ ውጤት ያስገኛል

እንደ ንጉሡ፣ አጎንብሱ
- ሂድ ካገር ኑር ካገር

እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናገሪ
- የአንድነትና የስምምነት መኖር መገለጫ

እንደ አገሩ ይኖሩ፣ እንደወንዙ ይሻገሩ
- ሂድ ካገር ኑር ካገር

እንደ እጤ ሥረዓት፣ እንደ እብረሃም እራት
- ሥረዓት በታጣበት ውጤት ያለው ሥራ ማስመዝገብ አይቻልም

እንደ አጥር፣ እንደ ቅጥር
- አንዱ እንደ ብዙ ነገር ሲያገለግል

እንደ አሸት ፈልፍሎ፣ እንደ ዘንግ መልምሎ
- የሚፈልጉትን ነገር መልካም እንዲሆን ያስተካከሉታል

እንደ አንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ
- በድንገት የሚከሰት ነገር

እንደ እንግዳ ጥልቅ፣ እንደ ውኃ ፍልቅ
- በድንገት የሚከሰት ነገር

እንደ ካሕን አናዞ፣ እንደ ንጉሥ አገዞ
- የበላይ ሆኖ የኖረ ወይም የሚኖር

እንደ ወርቅ አንከብሎ፣ እንደ ሸማ ጠቅሎ
- በሰዎች ዘንድ ተፈላጊ የሆነ መልካም ነገር

እንደ ወንድማማች ተበዳድሮ፣ እንደ ባዕድ ተቆጣጥሮ
- እንደዘመድም እንደባዕድም ሆኖ ተጠቃቅሞ አብሮ መኖር

እንደ ወይን መልምዬ፣ እንደ ዕንጩት ተክዬ
- ጥሩ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስተዋጽኦ ማድረግ

እንደ ውሌ፣ ደጅ አዝማች ባሌ
- እንደውለታዬ ባለበቴ ደጃዝማች ናቸው

እንደ ውኃ ይፍሰስ፣ እንደ ጋዝ ይንፈስ
- በአካባቢው ሁሉ እንደፈለገው ይሁን

እንደ ዐይን ፈሪ፣ እንደ እግር ደፋር የለም
- በዐይን ሲያዩት የሚያስፈራ የሚመስለው ነገር ደፍረው ሲገቡበት ቀላል ይሆናል

እንደ ዕውር አፍጣጭ፣ እንደ ጉግ ቀላዋጭ
- በሌላው ባሕርይ ላይ የሰውን ስም ማንሳት

እንደ ዝንጀሮ በአፉፍ፣ እንደ ጦጣ በዛፍ
- ሁሉም በሚኖሩበት ሁኔታ ይኮራሉ

እንደየቤቱ፣ ብዙ ነው ብልሃቱ
- ሁሉም በቤቱ ዘዴኛና ብልሃተኛ ነው

እንደ ዳኛ በውል፣ እንደምስሶ መሃል
- እንደዋነኛው ተፈላጊ ሰው ሆኖ መገኘት

እንደ ገና፣ ይመታል በገና
- ተደጋግሞ የሚፈጸም ተግባር

እንደ ጴጥሮስ በጵላሎት ርዕስ፣ እንደ ጳውሎስ በዘፈረ ልብስ
- የተንዘረፈፈ ልብስ የሚጎትተው ነገር አያጣምና ተጠንቀቅ

እንደ ፀሐይ የሞቀ፣ እንደ ጨረቃ የደመቀ፣ እንደ አበባ ያሸበረቀ
- የታወቀ ይፋ የሆነ ነገር

እንደ ፈረስ ጆሮ፣ እንደ ሰላጢን ጉሮሮ
- እንደፈረስ ጆሮ ያልተበላለጡ እኩል የሆኑ ነገሮች

እንደ ፈታሒነቱ፣ ሁላችን እንኮነናለን፣ እንደ መሐሪነቱ፣ ሁላችን እንማራለን
- ከጌታ መሐሪነት ባሕርይ ሁላችን እንጠቀማለን

እንዲህ ሊተርፈን፣ ለሚስቴ ነፈግኋት
- ለዚሁ ነው በሬዬን ያረድኩት አለ አሉ

እንዲህ ልጠግብ፣ በሬዬን አረድኩ
- ብዙ የሚበላ፣ የማይጠግብ መስሎት በትንሹ መጥገቡን ያመለከታል

እንዲህ ነድጄ ልሙት፣ የፊቱን በኋላ አድርጎት
- መቅደም የነበረበት ኋላ መጥቶ እንዲህ መከራዬን አሳየኝ

እንዲያውም በመላ፣ ፈስ ዳለቻ ነው
- ያልተረጋገጠ፣ በይሆናል የተነገረ

እንዲያው ብትመለሺ፣ የገንፎ ዕንጨት ላሺ
- ዋናውን ስለማታገኚ የተሰጠሽን ውሰጂ

እንዲያው ከምትቀሪ፣ ምንቸቱን እንቃሪ
- ከማጣት ትንሽም ብትሆን የተገኘውን መውሰድ መልካም ነው

እንዳልበላ ባፌ፣ እንዳልበር በክንፌ
- በገዛ ዕቃዬ እንዳልሠራበት ተከለከልኩ

እንዳልተወው ወለድኩ፣ እንዳልሰው ነደድኩ፣ አለች ላም
- የወለደችው ልጅ ባለጌ ሆነባት

እንዳትበላ ለጎሚት፣ እንዳትሄድ ቀየዷት (አሠሩዋት)
- ምንም እንዳትሠራ ከለከሏት

እንዳየን፣ ጤፍ አጋየን
- ሲሉ ሰምታ ዶሮ ሞተች ከጢስ ጉብታ

እንዳዩ መብላት፣ ሆድ ያስፋል
- እንዳቅም መኖር ይገባል

እንዳያማህ ጥራው፣ እንዳይበላ ግፋው
- ሥጋ ሰጥተው ቢላዋ ነሱት



እንዳይወልዱ ይመነኩሱ፣ እንዳይጸድቁ ይልከሰከሱ
- ከሁለት ያጣ ጎመን

እንዳገሩ፣ ይናገሩ
- ሒድ ካገር ኑር ካገር

እንዳገሩ ይኖሩ፣ እንደ ወንዙ ይሻገሩ
- ሒድ ካገር ኑር ካገር

እንዶዶ በገርነቱ፣ ውኃ ወሰደው
- የአህያ ገርነት ሸክም ማብዛት

እንጀራ ለራብ፣ ድንጋይ ለካብ
- ሁሉም በየሚፈልግበት ቦታ ማገልገል

እንጀራ በማየት አይጠገብም
- አሥር ዳቦ ከመላስ አንዱን መጉርስ

እንጀራ በሰፌድ፣ አሞሌ በገመድ
- ለሁሉም የሚበጀው ነገር ይፈለግለታል

እንጀራን ምን ይጨርሰዋል መጉረስ
- ሥራን ከግብ የሚያደርሰው ጥረት ነው

እንጀራ ከባዕድ፣ መከራ ከዘመድ
- ለመከራ ጊዜ ዘመድ ደራሽ ነው

እንጀራ የለም እንጂ፣ በወተት አምገህ ትበላ ነበር
- ሁሉም ስለሌለ አትድከም

እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለ ሴት ኩበት ያለበረት
- ቤትን ሞቅ ሞቅ የምታደርግ ሴት ነች

እንጀራ ያለው ክቡድ፣ እንጀራ የሌለው ዕብድ
- ሀብት ያለው የተከበረ ነው የሌለው እንዲያው ነው

እንጀራ ይጋግሯል፣ እማድ ቤት መላ ያማክሯል ለሴት
- ሴት መላ ሀዋቂ ናት

እንጃ በሰማያት፣ በምድርስ የለም ምክንያት
- በምድር የሚሆነው ሁሉ ያለምክንያት ነው

እንግዲህ፣ ነገሬን ከንፈሬ
- ምንም አልናገርም

እንግዳ ሆነህ ብትመጣ፣ ሳይሰለችህ ውጣ
- አትሰልች

እንግዳ ሲወደስ፣ ባለቤቱን ያጎርስ
- እንግዳ ሲያፍር ባለቤትን ይጋብዛል

እንግዳ ሲያዘወትር፣ ቤተሰብ ይሆናል
- መለማመድ ይመጣል

እንግዳ ሲያፍር፣ ባለቤት ይጋብዛል
- መቅለብለብ ጥሩ አይደለም

እንግዳ ሳይመጣ ሁሉ ሴት፣ ዝናብ ሳይጥል ሁሉ ቤት
- ጊዜ ሁሉን ይፈትናል

እንግዳና፣ ሞት በድንገት
- ሳይታሰብ ነው የሚመጣው

እንግዳ ደራሽ፣ ውኃ ፈሳሽ
- እንግዳ የሚመጣው ሳታስበው ነው

እንግዳ ፊት ወርቅ፣ ኋላ ብር ኋላ ጨርቅ
- እንግዳ እያደር መከበሩ ይቀንሳል

እንጎቻ የበላ፣ ከራት ይታገሳል
- ከረኃቡ ገርገብ ሰላለ

እንጣጥ እንደ ፈቆ፣ ሙልጭ እንደሰብቆ
- የሚጠቅምህን በሚያመችህ መንገድ ለማግኘት ጥረት አድርግ

እንጥስ ቢሉ ቅንጥስ
- ደካማ ሰው በትንሽ አደጋ ይሞታል

እኖር ባይ ተጋዳይ፣ እድን ባይ ተከላካይ
- ሁሉም ራሱን ለማዳን ጥረት ያደርጋል

እኛ በአገራችን፣ ዳቦ ፍሪዳችን
- ችግረኞች ነን

እከሌ እባብ ነው፣ መሔጃው አይታወቅም
- ልቡ በፍጹም አይገኝም ተንኮለኛም ነው

እከክን የሰጠ ጌታ፣ ጥፍሩን አይነሳም
- እከክን ያመጣ ጥፍርንም አላሳጣ

እኩሉ በዶሮ፣ እኩሉ በሽሮ
- ሁሉም እንደየአቅሙና ባለው መጠን

እኩሉን ተላጭታ፣ እኩሉን ተቀብታ
- ያልተሟላ ነገር

እካስ ያለ ታግሶ፣ እጸድቅ ያለ መንኩሶ
- አንድን ያሰቡትን ነገር ለማግኘት ትዕግሥት ያስፈልጋል

እወቅ ያለው፣ በአርባ ቀኑ ያውቃል፣ አትወቅ ያለው ባርባ ዘመኑ
- አንዳንዱ ከጊዜው በፊት ሌላው ከጊዜው ዘግይቶ ያውቃል

እወዳለሁ እያለ የሚጠላ፣ እጾማለሁ እያለ የሚበላ
- አፍና ተግባር አልተገናኙም

እወደዋለሁ እንጂ፣ ይወደኛል አትበል
- ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው

እውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም
- ወሬኛ ሰው ምስጢር መደበቅ አይችልም

እውነተኛ ሚስት፣ ባሏን ትወልዳለች
- የማታመነዝር ሚስት ባሏን የመሰለ ትወልዳለች

እውነቱን ተናግሮ፣ እመሸበት ያድሯል
- እውነትን ለኑሮ፣ ለጥቅም ብሎ መለወጥ አይገባም

እውነት ለእግዜር፣ ውሸት ለሳጥናኤል
- ትክክለኛውንና ጠቃሚውን መንገድ ምረጥ



እውነትና ንጋት፣ እያደረ ይጠራል እንደ ወርቅ
- ዞሮ ዞሮ እውነት አይደበቅም

እውነት የተናገረ፣ በመርከብ የተሻገረ
- እውነተኛ መንገዱ የቀና ነው

እውነት ይመስላል፣ ልብን ያቆስላል
- እውነት መራራ ናት

እዚያ ማዶ ጠብ ብታደርስኝ፣ አሞሌ ጨው አገባለሁ
- ነገረኛ ሆን ብሎ ጸብ ይፈልጋል

እዚያም ቤት፣ እሳት አለ
- አጠቃለሁ ብለህ መጠቃትም አለ

እዚያው ሞላ፣ እዚያው ፈላ
- የችኮላ ሥራ፣ ለውጥ የሌለበት

እዚያው ዘንቦ፣ እዚያው ያባራ
- ሁሉ ነገሩ እዚያው ብቻ ሆኖ ቀረ

እየቆረጣችሁ አንበሳውም ሔዶ፣ ነብሩም ሞተላችሁ
- የአራዊቱን መኖሪያ አወደማችሁት ከንግዲህ የምትፈሩት የላችሁም

እየቤትህ ግባ፣ እየራስህ ተቀባ
- በራስህ ሀብት ራስህን ጥቀም

እየተፈጨ እየተቦካ፣ እየሞተ እየተተካ
- የሰው ዘር ሰው እስካለ ድረስ ሁኔታው ይቀጥላል

እየታጠቡት ያድፋል፣ እየመከሩት ያጠፋል
- የማይሻሻል ሆነ

እየወገንህ ቢሉት፣ አከንባሎ ጋጣ ገባ
- ሁሉም የሚመስለውን ፍለጋ

እየወገንህ ቢሉት፣ የመቶ ዓመት ቆዳ አከብት ተራ ቆመ
- እየወንንህ ቢሉት አከንባሎ ጋጣ ገባ

እየፈለገው ዕወቀኝ ብሎ መጣ
- በፈረስ የፈለጉት በእግር ይገኛል

እያለው የማይከፍል፣ ጥሮ የማያደላድል
- የሰው ነገር የማይከብደው

እያየህ ተናገር፣ እየዋኘህ ተሻገር
- ለምትሠራው ሥራ ትኩረት ስጥ

እያየኋት የምታሥቀኝ፣ ሚስት አገባሁ
- ሁኔታዋ ሁሉ የሚያስገርም ነው

እያወቁ ቢሰቁ፣ ምንድር ነው መድኃኒቱ
- ዐውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም

እዬዬ፣ ሲዳላ ነው
- ሁሉ ነገር ሲሟላ ነው

እያደር ይቃቃር

- እየቆዩ ሲሔዱ መቀያየም የማይቀር ነው

እያደፈ በእንዶድ፣ እየጎለደፈ በሞረድ

- ክፉውን ወደ መልካም የምትለውጥበትን ሁኔታ አስተውል

እደን ገብተህ፣ እምሳያህን ቁረጥ

- የሚመስልህን አይተህ ተናገር፣ ወስን

እዳሪ ሳይወጣ የበላ፣ ዕዳውን ሳይከፍል ጎታውን የሞላ

- ዕዳን ሳይከፍሉ ጎታን ሞሳሁ ማለት ነገ በዕዳ ምክንያት መጉደሉ አይቀርም

እዳሪ ያረሰ፣ ለልጁ አጎረሰ

- አዲስ እርሻ ሰፊ ምርት ይሰጣልና

እድር፣ እሰከ በጌምድር

- የትም ቦታ የሚገኝ እንጂ አዲስ ነገር አይደለም

እጁ ተበትር፣ እፉ ከነገር

- መደባደብና መሳደብ ይወዳል

እጁን የሚጠባ አይደለም

- ሕፃን ልጅ ያሰመሆኑን ለመግለጽ

እጄን በእጄ ቆረጥሁ

- ራሴን በራሴ ጎዳሁት

እጅህን በባሕር እግባ፣ ብታገኝ ዓሣ ታወጣለህ፣ ባታገኝ ታጥበህ ትወጣለህ

- ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት ጥረት አድርግ አንዳች ጥቅም ማግኘትህ አይቀርም

እጅ ለነገር ያግዛል፣ ልብ እንደ ንጉሥ ያዛል

- ልብ ከመሳው የሰውነት ብልቶች ሁሉ ወሳኝ ነው

እጅ ሳፍ ሚዛኑ ነው፣ ባፍ የገባ ለእጅ ኃይሉ ነው

- አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥናል

እጅ ሲነድ፣ ልብ ይነድ

- ሁለነገራችን የተያያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው

እጅ ሲያጥቡት ያድፋል፣ ልጅ እየመከሩት ያጠፋል

- ጥፋት መፈጸም የልጅነት ባሕርይ ነው ሆኖም ውሎ አድሮ መሻሻሉ አይቀርም

እጅና አፍ አይተጣጡም

- መጋቢና ተመጋቢ በመሆናቸው

እጅና ጭራ፣ አፍና እንጀራ፣ ሥጋና አሞራ

- አንዱ ለአንዱ አገልጋይ

እጅን በሰንሰለት፣ እግርን በእግር ብረት

- ለሁሉም እንደየባሕርዩ

እጅ እሾህን ይነቅለዋል፣ ጥጋብ ሞትን ያሰረሳዋል

- የጠገቡ ዕለት ሞት አይገኝም



እጅ ከልብሰ፣ ምላስ ከጥርስ

- የልብሰ መኖር ብቻ ሳይሆን የእጅ መኖር ልብሰን አስተካክለን እንድንለብሰ ያደርጋል

እጅ ይዘው ያስገቡት፣ እጅ ይዞ ያሰወጣል

- ኋላ የመጣ ዐይን አወጣ

እጅግ ማግኘት፣ ያመጣል ትዕቢት

- ከመጠን በላይ ማግኘት ኩራትና ትዕቢት ያመጣል

እጅግም ሰለት ይቀዳል አሮት/እጅግም ብለሃት ያደርሳል ከሞት

- መጠኑን ያለፈ ነገር በሙሉ ይጎዳል

እገሌ የዋሰበት ሸንን፣ ዝንብ የገባበት እርጎ፣ እርጎውም ለውሻ እርሱገም ለውርሻ

- ሁለቱም አይጠቅሙም

እግረ መንገዳቸውን፣ ይሸጣል በሬያቸው

- ለመሸጥ ዓላማ ኖሯቸው ሳይሆን ከሆነ ልሞክረው ዓይነት

እግረ ቀጭን እንደ ሰሳ፣ ልበ ሙሉ እንደ አንበሳ

- ልበደፋር፣ ሐሞተ ኮሰታራ

እግረ ቀጭን ይሞታል ሲሉት፣ እግረ ደንዳና ይሞታል

- ያልታሰበው ሆኖ ይገኛል

እግሩ ለጠጠር፣ ግንባሩ ለጦር

- ቁርጠኛ የሆነ ሰው

እግሩ ከርካብ፣ እጁ ከዛብ

- ቅምጥል፣ ከበቅሎ ወርዶ የማያውቅ የተመቸው

እግር ሔዶ ሔዶ፣ ከእር ጉድጓድ ይገባል

- ሰው ሔዶ ሔዶ አልፈለገው ቦታ ይደርሳል

እግርህን በፍራሽህ፣ ልክ ዘርጋ

- አቅምህን ዕወቅ

እግር ለጠጠር፣ ደረት ለጦር

- ምንም ፍርኃት አታሳድር

እግር ሲደርስ፣ እግት ይመለስ

- አይተው እንዳላዩ መሆን

እግር ቢሳሳት ከአንጋዳ፣ አፍ ቢሳሳት ከዕዳ

- የአፍ ወለምታ ላልታሰበ ችግር ይዳርጋል

እግር ተርካብ፣ እጅ ተዛብ

- የተመቸው ቅምጥል፣ ምቹ ሁኔታ

እግርና ራስ እኔ እለብስ፣ እኔ እለብሰ ይጣላሉ

- ለሁሉም አሳቢያቸው አንድ አካል ሆኖ እነሱ ይሮክከራሉ

እግር ዜጋ ነው

- ምንም ይሁን ምን አንዱ አካል ነው

እግር ከሸሸ፣ ልብ ሸሸ

- ከዐይን ሲርቅ ከልብ ይርቃል

እግር የላት፣ ክንፍ አማራት
- ትለብስው የላት ትከናነበው አማራት

እግዜር ሲሰጥ፣ እንጀራ በወጥ
- እግዜር አሟልቶ ይሰጣል

እግዜር ሲቆጣ፣ በዝናብ እር ያመጣል
- በጣም የሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ መግባት

እግዜር ሲጥል፣ እናት አታነሣም
- ኃይል ያለ በእሱ በእንድዬ እጅ ነው

እግዜር በመለኮቱ፣ ጎልማሣ በሚስቱ
- ሁሉም ባለው፣ የሱ በሆነው መቅናቱ አይቀርም

እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም
- ከየት አመጣኸው አይባልም

እግዜር ባወቀ፣ ሰማይን አራቀ
- የሰውን ተንኮል በማወቁ ይመስላል

እግዜርን ሳይጨምር የቆጠረ፣ ሁል ጊዜ ሲቆጥር ይኖራል
- እግዜር ካልተጨመረበት የሰው ድካም ከንቱ ነው

እግዜርን ያህል ጌታ፣ ገነትን ያህል ቦታ
- መልካሙ ዓምላካችን መልካሙን ቦታ አዘጋጅቶልናል

እግዜር የተናገረውን አያስቀር፣ የሚያደርገውን አይናገር
- የለመኑትን አይነሳ የነገሩትን አይረሳ

እጠጣ ሲል ይዋኛል፣ እበላ ሲል ይዳኛል
- የሚሆነውን ሁሉ እሱ ያስብለታል

እጣ ያስታርቃል፣ ሙግት ያደርቃል
- ሙግትን በእጣ መለየት ያስፈልጋል

እጭን ያለ ኮርቻውን፣ እለምን ያለ ስልቻውን
- መማሪያውን ትቶ አይሆንም

እጸድቅ ብዬ፣ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
- ለፍቅር ብተኛት ለጸብ አረገዘች

እፍረት ያከሳል፣ ያመነምናል
- ያልሆኑትን ሆንኩ ማለት ከስውነት ተራ ያወጣሉ

ኧረ በከንቱ ማን ሊሰማው ነው ጩኸቱን
- እርዳታ የማያገኙበት ጩኸት እንዲያው ለመታከት

ኧረ ጉዴ፣ ባሌ ገደለ በጎራዴ
- ወንድ ወጣው

ኧረ በከንቱ ማን ሊሰማ ነው ጩኸቱን
- ከንቱ ልፋት



## መልመጃ 9 (እ)

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. እርጉዝ ላም ያለው ሰው ________
   - ሀ. ደረቅ እያንቀው
   - ለ. ወተት እያምረው
   - ሐ. ቅቤው በሽበሽ ነው
   - መ. ተስፋው ሁለት ነው

2. እንዶድ በገርነቱ ________
   - ሀ. የሰው እድፍ ያጸዳል
   - ለ. ውኃ ወስደው
   - ሐ. ወንዝ ዳር መብቀሉ
   - መ. ስፍነግ በቅስቱ

3. ________ የመቶ ዓመት ቆዳ ከብት ተራ ቆመ
   - ሀ. እየወገንህ ቢሉት
   - ለ. እየሮጥህ ቢሉት
   - ሐ. እያስብህ ቢሉት
   - መ. እያዘገምክ ቢሉት

4. ________ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል
   - ሀ. እንኳን ሚስቴ ሞታ
   - ለ. እንኳን ዘመዶቼ አልቀው
   - ሐ. እንኳን ልጄ ሞታ
   - መ. እንኳን እናቴ ሞታ

5. እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ ________
   - ሀ. እህል የሚደርስ በልደታ
   - ለ. ደሞዝ የሚደርስ በልደታ
   - ሐ. እህል የሚደርስ በፍልሰታ
   - መ. ደሞዝ የሚደርስ በፍልሰታ

6. ዕድላም እሞሌ ________
   - ሀ. ደረስ ቀበሌ
   - ለ. ጌጥ ይሆናል
   - ሐ. በቅሉ ይስውጣል
   - መ. በግመል ይጫናል

7. እራት የሌለው ቄስ ________
   - ሀ. እንደልቡ አይቀድስ
   - ለ. አይተኛም
   - ሐ. ያዝናል
   - መ. መልሱ የስም

8. እሳት ቢያንቀላፋ ________
   - ሀ. ውኃ ወሰደው
   - ለ. ገለባ ጎበኘው
   - ሐ. እመድ እጠፋው
   - መ. ጭራሮ ጎበኘው

9. እባብ የልቡን አይቶ ________
   - ሀ. እግር ነሳው
   - ለ. ከለከለው እግር
   - ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   - መ. መልሱ የስም

10. እዚያው ሞላ ________
    ሀ. እዚያው ፈሰሰ    ሐ. እዚያው ፈላ
    ለ. እዬዬ ሲዳላ    መ. እዚያው ተንተከተከ

11. እበት ________ ።
    ሀ. ፍግ    ሐ. ትል ይወልዳል
    ለ. ኩበት    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

12. እባብ ግደል ________
    ሀ. ከነበትሩ ገደል    ሐ. እንዳትገደል
    ለ. እንዳትነደፍ    መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

13. እርሚን ብታፈላ ________
    ሀ. ከሰው ልትጣላ    ሐ. አንድ ቁና አተላ
    ለ. ማንንም አትጠራ    መ. መልሱ የለም

14. እሳት ________
    ሀ. የቤት ጠላት    ሐ. አመድ ወለደ
    ለ. የገለባ ጠላት    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

15. እባብ ያየ ________
    ሀ. በረገገ    ሐ. እግሬ አውጭኝ አለ
    ለ. በልጥ በረየ    መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

16. እውሻ ሆድ ________
    ሀ. አጥንት    ሐ. ገንፎ
    ለ. ሳንባ አያድርም    መ. ቅቤ አያድርም

17. እጸድቅ ብዬ ባዘላት ________
    ሀ. ተንጠልጥላ ቀረች    ሐ. እትዘሉኝ አለች
    ለ. አልወርድም አለች    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

18. እሺ ________
    ሀ. ማንም አይሸሽ    ሐ. ይሻላል ከሺ
    ለ. ይበልጣል ከሺ    መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናለ

19. እራት የሌላት ________
    ሀ. ባል አማራት    ሐ. ምሳ አማራት
    ለ. ጓደኛ አማራት    መ. መልሱ የለም

20. እርጅና ________
    ሀ. ብቻህን ና    ሐ. ጉለቁልና
    ለ. ሽምግልና    መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

21. እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ________
    ሀ. ድሃ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል
    ለ. ሃብታም ሞቱን ይመኛል
    ሐ. ሰው ሞቱን ይመኛል
    መ. ሁሉም መልስ ነው



22. እሾህን ________
    ሀ. ማጥፋት  ለ. በእሾህ  ሐ. ማውጣት  መ. ሀ እና ለ

23. እውነትና ንጋት ________
    ሀ. እያደር ይገለጣል    ሐ. ሀ እና ለ
    ለ. ቆይቶ መውጣቱ አይቀርም    መ. መልሱ የለም

24. እጅና ________ አይተጣጡም
    ሀ. እግር  ለ. አፍ  ሐ. ሆድ  መ. ዐይን

25. እጅ ሲነድ ________ ይነድ
    ሀ. እንጀት  ለ. ፊት  ሐ. ልብ  መ. ሁሉም መልስ ነው

26. እጄን በእጄ ________
    ሀ. በላሁ    ሐ. አስተካከልኩ
    ለ. ቆረጥኩ    መ. መልሱ የለም

27. እጁን ________ አይደለም
    ሀ. የተቆረጠ    ሐ. የሚነከለ
    ለ. የሚጠባ    መ. ሁሉም መልስ ነው

28. እርጉህ ________ ይደግፉ
    ሀ. ያቅፉ  ለ. ይንከባከቡ  ሐ. ይሸኙ  መ. ይምከሩ

29. እሰር በፍንጅ ________
    ሀ. እለፍ በደጅ    ሐ. አትለፍ በደጅ
    ለ. አትረብሽ በደጅ    መ. ጣል በደጅ

30. እሱ እርጥብ ________
    ሀ. ልብሱ ደረቅ    ሐ. ነገሩ ደረቅ
    ለ. ምግቡ ደረቅ    መ. ሁሉም መልለ ነው

31. እሳት በሌለበት ________ እይኖርም
    ሀ. እመድ  ለ. ዕንጨት  ሐ. ገለባ  መ. ጢስ

32. እሳትና ነገር ________ ይበቃዋል
    ሀ. መጫር    ሐ. ማርገብገብ
    ለ. ትንሽ    መ. ሁሉም መልስ ነው

33. እሳት ከበላው ________
    ሀ. የተረፈው    ሐ. ወራሪ የዘረፈው
    ለ. ውኃ የወሰደው    መ. ፖሊስ የዘረፈው

34. እለኪያልፍ ________
    ሀ. ያለፋል    ሐ. ተበደር
    ለ. ተወዳደር    መ. መልሱ የለም

35. እሳትና ________
    ሀ. ውኃ ናቸው    ሐ. አመድ ናቸው
    ለ. ጭድ ናቸው    መ. መልሱ የለም

36. እሷው ሠርታ ________
    ሀ. እሷው ታፈርሰዋለች    ሐ. እሷው ታባርር
    ለ. እሷው ታመሰግን    መ. መልሱ የለም

37. እሷ በፈሳችው ________
ሀ. በእህቷ ለከከችው   ሐ. በኔ ለከከችው
ለ. በልጇ ለከከችው   መ. ሁሉም መልስ ነው

38. እሺና ________ አይከብድም
ሀ. ማንድ   ሐ. ገሰባ
ለ. ጭራሮ   መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

39. እሾህ ስረጋጩ ________ ላምጪው
ሀ. ዳቦ   ለ. ገለባ   ሐ. መርዶ   መ. ነገር

40. እበትና ኩበት ________
ሀ. አይነጣጠሉም   ሐ. ወገንና ከብት
ለ. ይነጣጠላሉ   መ. መልሱ የለም

41. እንዳገሩ ________
ሀ. ይናገሩ   ሐ. ይደንሱ
ለ. ይፎክሩ   መ. ሁሉም መልስ ነው

42. እንጀራ ________
ሀ. ያስከብራል   ሐ. ያዋርዳል
ለ. ያኖራል   መ. በማየት አይጠገብም

43. እበላ ባይ ________ እቀባይ
ሀ. ገንዘብ   ለ. ሥራ   ሐ. ዱባ   መ. ቃል

44. እንጀራ ለራብ ________
ሀ. ወጥ ስጥጋብ   ሐ. ድንጋይ ስካብ
ለ. ንፍሮ ስጥጋብ   መ. መልሱ የለም

45. እንጀራ ከባዕድ ________ ከዘመድ
ሀ. ትብብር   ለ. ደስታ   ሐ. ገንዘብ   መ. መከራ

46. እንግዳና ________
ሀ. ኃጢያት በድንገት   ሐ. ባለቤት በድንገት
ለ. እንጀራ በድንገት   መ. ሞት በድንገት

47. እንሳቻ የበላ ________ ይታገሳል
ሀ. ከጥጋበኛ   ለ. ከራት   ሐ. ሰውን   መ. ጎረቤት

48. እንዳየን ________
ሀ. ጠላትን አጋየን   ሐ. የሣር ከምር አጋየን
ለ. በቆሎ አጋየን   መ. ጤፍ አጋየን

49. እኛ ባገራችን ________
ሀ. ዳቦ ፍሪዳችን   ሐ. በሽበሽ ነው ምግባችን
ለ. ኬክ ፍሪዳችን   መ. መልሱ የለም

50. እጅ ከልብስ ________
ሀ. ብዕር ከወረቀት   ሐ. ምላስ ከጥርስ
ለ. ወጥ በድስት   መ. ሁሉም መልስ ነው



## መልመጃ 9 (እ)

ለ. ለሚከተሉት ምሳሊያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው

1. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
ሀ. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
ለ. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
ሐ. የእብዬን እከክ ወደምዬ ልከክ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
2. እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
ሀ. ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች
ለ. ያሳደግሁት ውሻ ነከሰኝ
ሐ. ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ
መ. ሁሉም መልስ ነው
3. እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ እህል የሚደርሰው በፍልሰታ
ሀ. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
ለ. ላም እለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም
4. እህል ላበደረ ዐፈር፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር
ሀ. ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ
ለ. ያነደድኩትን እሳት ጠበሰኝ
ሐ. ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ
መ. ሁሉም መልስ ነው
5. እጅና እፍ አይተጣጡም
ሀ. ዘመድ ከዘመዱ እህያ ካመዱ
ለ. ዘር ከልጓም ይስባል
ሐ. ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
6. እርሾው ቢያምር ዳቦው ያምር
ሀ. የማሽላ ዘር ከነእገዳው ቸር
ለ. ቅርንጫፉ እንደዛፉ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም
7. እህል ሲገኝ ወፍጮው ይደንዛል
ሀ. ሳይቃጠል በቅጠል
ለ. እፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል
ሐ. ደሃና ንበያ ሳይገናኙ ይኖራሉ
መ. መልሱ የለም
8. እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ
ሀ. ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
ለ. ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

## መልመጃ 9 (እ)

ሐ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | አርስ በርሱ ሥጋን በኩበት ጠበሱ | ሀ. | ደግ ብውልላት ውስታ ረሳች |
| 2. | እጅግም ስለት ይቀዳል አፎት | ለ. | ርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ |
| 3. | አጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች | ሐ. | ለኃጥእን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል |
| 4. | አርጥብ ከደረቅ ይነዳል | መ. | እግር የላት ክንፍ አማራት |
| 5. | አውነትና ንጋት እያደር ይታያል | ሠ. | ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል |
| 6. | እንጀራ የሰም እንጂ በወተት አምገሀ ትበላ ነበር | ረ. | አሾህን በሾህ |
| 7. | አጅግም ብስሃት ያደርሳል ከሞት | ሰ. | ብልጥ ለብልጥ ዐይን ብልጥጥ |
| 8. | አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ | ሸ. | ደባ ራሱን ስለት ድግሱን |
| 9. | እጅ አላቸው እይዳስሱም | ቀ. | ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው |
| 10. | አሬት የቀመሰው አንጂ ያልቀመሰው መራራነቱን አያውቅም | በ. | አይሠሩም አይጥሩም አይለፉም |
| 11. | አምበላው ሳጣ ልጁ ጥርስ አወጣ | ተ. | በቡሃ ላይ ቆረቆር |
| 12. | እርሾው ቢያምር ዳቦው ያምር | ቸ. | ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ |
| 13. | እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ | ኃ. | ቅርንጫፉ አንደዛፍ |
| 14. | እህል ሲገኝ ወፍጮው ይደንዛል | ነ. | ደሃና ገበያ ሳይገናኙ ይኖራሉ |
| 15. | አሚሱሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ | ኘ. | መርፌ የምትሾልክበትን እንጂ የሚከተላትን ክር አታይም |
| 16. | አጅና አፍ አይተጣጡም | አ. | ዘር ከልጓም ይስባል |
| 17. | እህል ሳበደረ ዐፈር፣ ወርቅ ሳበደረ ጠጠር | ከ. | ባጎረኩ አጁን ተነከሰኩ |
| 18. | እህል ካልተለወጠ፣ ነገር ካልተደመጠ | ኸ. | የነገር ወጡ ማዳመጡ |
| 19 | አራስ ከተመሰጠ፣ ነገር ካመለጠ | ወ. | ከአፍ ከወጣ አፋፍ |
| 20. | አራት የሌሳት ምሳ አማራት | ዘ. | ትሰብሰው የላት፣ ትከናነበው አማራት |
| 21. | እሳት በሌለበት ጢስ አይኖርም | ገ. | ሲያኄጡ ይመላሰጡ |
| 22. | አሠራስሁ ብላ ሄዳ ተላጭታ መጣች | የ. | ላም ባልዋሰበት ኩበት ለቀማ |
| 23. | አሳት ቢያንቀላፉ ገሰባ ጎበኘው | ደ. | በግ ባልበላሽ ትበይኝ |
| 24. | እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል | ጀ. | ያሰባለቤቱ አይነድም አሳቱ |
| 25. | እሳት አስዕንጨት አይለማ፣ ጆሮ ዕዳውን አይሰማ | ገ. | ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል |



## ከ

ከሀብታም ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ
- በድህነት ከመቆራመት ካለው ሰው ጋር መጠጋት ይመረጣል

ከሁለት ዓይነት ደረቅ አንድ ዓይነ አፋር
- ከማይረቡ ነገሮች አንድ የሚረባ ነገር

ከሁለት ያጣ ጐመን
- ከሁለቱም ሳይሆንለት የቀረ

ከሁሉ ልብ ይበርድ ከሁሉ ልብ ይነድ
- ከሌላው አካል ሁሉ በዋናነኛነት የሚጠቀሰው አንዱ ነው

ከሁሉ መጣላት ቀባሪ ማጣት
- ተስማምቶ መኖር ይገባል

ከሁሉ ክፉ የመበለት አራስ
- ያስዕድሜ የሚሆን ነገር ሁሉ አስቸጋሪና አስነዋሪም ነው

ከሆነ ወዲያ ንዴት ለሽበት
- ከሆነ በኋላ ትርፉ እራስህን መጉዳት ነው

ከሆድ የመጣ ትፋት የጥርስ መግጠም አያድነውም
- ከውስጥ ያለን ሕመም በመሸፋፈን ማስተካከል አይቻልም

ከሆድ የሚማከር ባባት አገር አይቀበር
- ራስ ወዳድ ሰው አይወደድም

ከሆድ የገባውን የእናት ልጅ እንኳን አያገኘውም
- ጥቃትህን ቻለው ታጋሽ ሁን ለማንም አታውራ

ከሆድ ያኖሩት ያድናል የተናገሩት ያስገድላል
- የተመሰከትከውን ሁሉ መናገር አደጋ ላይ ይጥልሃል

ከለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ
- ድሃ ሆኜ ሣለሁ ሌላ ድሃ አጋጠመኝ

ከላይ እንዳይፈስ ከታች እንዳይተነፍስ
- ነፋስ እንዳይገባው ጠበቅ አድርጐ መያዝ

ከላይ ከደፈረለ ከታች አይጠራም
- ከዋናው ከተበላሸ ታቹም ያው እንደዋናው ነው

ከሌለ ባለቤት አይረዳም ጐረቤት
- ትዳር መከበሪያ ነው

ከሌለ ባካፋ የለኝም ተሰፋ
- በብዛት ካላገኘሁ ቅር ይለኛል

ከሌባ ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው
- ከለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ

ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመትም አይቆዩ
- አታዳላ ሁሉንም በእኩል ዐይን እይ

ከልጅ አትጫወት ይወጋሃል በዕንጨት
- ችግር ውስጥ ይከትሃል

ከልጄ ሆዴ ከባዕድ ዘመዴ
- ለሁሉም ደረጃ በደረጃ ለመውደድም ለማቅረብም

ከሔዱ አይቀር ጥርግ ነው
- አንድ ሥራ ለመሥራት ከፈለግህ በሙሉ ልብ መሥራት ነው

ከሕፃን አይዋዋሉ ከጠላት አይበሉ
- ጠሳትን በትኩረት መከታተል ይገባል ያለዚያ አደጋ ላይ ትወድቃለህ

ከመሃል አይደርስ ከዳር አይመለስ
- አይወሰንም ወላዋይ ነው

ከመሆን ፋቂ ይሻላል ነጣቂ
- አጉል ቦታ አለመገኘት

ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይበልጣል
- መልካም ነገር ሠርቶ ማለፍ ጥሩ ነው

ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ
- ምንም ቢጠብ መንገድ ምንም ቢከፋ ዘመድ

ከመልካም ጠሳት ክፉ ጠጅ
- ጠላት እንቅልፍ ይነሳል ክፉ ጠጅ ግን ራስን አስረስቶ እንቅልፍ ያስወስዳል

ከመመሳለስ ይሻላል ማረስ
- ጊዜን ጠቃሚ ሥራ ላይ ቢያውሉት ጠቀሜታ አለው

ከመመስከር ማስመስከር
- ብዙ ከመናገር ብዙ ማድመጥ ዋጋ አለው

ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ
- ተማሪው ስለመምህሩ የበለጠ ዐዋቂ ሆነ

ከመሞቱ ያሟሟቱ
- የሚዘገንን አሟሟት ነው

ከመሞት መሰንበት
- ማምሻም ዕድሜ ነው

ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጾመኛ ነኝ
- አልሸሹም ዞር አሉ

ከመሬት የወደቀ ሥጋ ዐፈር ሳይዝ አይነሳም
- በግጭት ውስጥ ከዚህም ሆነ ከዚያ ወገን ጉዳት ሳይደርስ አይቀርም

ከመሠረት አትጣሳ ለጥንት እንዲሆን ከግድግዳ አትፋቀር ንዶ እንዳይጫንህ
- ሁሉንም ብዙም ሳትርቅ ብዙም ሳትቀርብ እንደጠባዩ ያዘው

ከመቃለል መጠቃለል
- ከውርደት ሞት ይሻላል

ከመቅረት ማዝገም ይሻሳል
- በጥቂት በጥቂት ይሞሳል ልቃቂት

ከመቅናት መፍታት ከመፍታት አለማግባት
- የቅናት ቤት ቤት አይሆንም በየዕለቱ ጭቅጭቅ ብቻ



ከመቆም መቀመጥ ከመቀመጥ ማላመጥ
- ውሻ በየደረሰበት ቁጢጥ ካለ ባለቤቱን በለጠ ይባላል
- እንዲያው ዝም ብለው ሲቀመጡ ያንቀላፋል ሲያላምጡ ግን እንቅልፍ ይጠፋል

ከመታማት ይሻላል መሥራት
- የሠሩ ከበሩ

ከመታገል መታደል
- አትሩጥ አንጋጥ

ከሙቶ ቅል አንድ አርኮት
- ከማይረባ ብዙ አንድ የተሻለ ነገር

ከሙቶ ሃምሣ ዳዊት የልብ ቅንነት
- እግዚአብሔር የልብ ነው ይባላል

ከሙቶ ውሸት አንድ እውነት
- መዋሸት ጥሩ አይደለም

ከመቸገር ለእግዜር መንገር
- በቅን ልቡና የለመኑትን አይነሳምና

ከመቸገር ሠርቶ ማደር
- ካልሠሩ አያበሉ

ከመነሻው መድረሻው ይታወቃል
- ጥሩ አጀማመር ለጥሩ አጨራረስ ዋስትና ይሰጣል

ከመነቃቀፍ ይሻላል መተቃቀፍ
- በፍቅር መኖር ይበልጣል

ከመነኩሴ ቤት ዝተት ከሸማኔ ቤት ቁጢት
- ከሸማ ሥራ ባለሙያ ቤት ቁጢት አይታጣም

ከመነኮሰች ባለች ከቆረበች አፈረሰች
- ምንም ምንም ያልተሳካ

ከመነኮሰች ባለች ከተተኮሰች አነከሰች
- ባሕሪዋ ምንም ሊሻሻል አልቻለም

ከመናገሩ ይሻላል ጠም ማደሩ
- ከመናገር ዝምታ ይሻላል

ከመናገር ማዳመጥ ከመዋጥ ማላመጥ
- በጥሞና ማዳመጥ ይገባል

ከመናፍቅ ትርጓሜ ከትንባሆ ልምላሜ
- ትንባሆ በድርቅ ጊዜ እንደሚለመልም ከሃዲያንም ትክክለኛውን ቃል በማጣመም መተርጎም ልማዳቸው ነው።

ከመንታ ቅርንጫፍ የተንጠለጠለች ወፍ ሁለት ክንፏን ትነደፍ
- ሁለት ነገር ባንድ ጊዜ መመኘት አደጋ ላይ ይጥላል

ከመንቻካ ተሰናባች ደህና ከዳተኛ ይሻላል
- ዘጠኝ ጊዜ ጤና ይስጥልኝ እንደ ለነገር ነው

ከመንደር አደባባይ ከነጋሪት ደባይ
- አደባባይ የሚውል መልካም ጠባይ ያለው ሰው ይታወቃል

ከመንግሥት ልብ ያዛል
- በግል ፍላጐት የምታርገው ነገር ውጤታማ ያደርጋል

ከመወሰድ መዛመድ ከመዛመድ መላመድ
- መወሰድ ቋንቋ ነው

ከመውሰድ ስነፍ ይሻላል መጨንገፍ
- ስነፍን ከመውሰድ ቢቀር ይሻላል

ከመውደቅህ በፊት ተጠንቀቅ ከመሞትህ በፊት ጽደቅ
- ችግር ከመውጣቱ በፊት ሕይወትህን አስተካክል

ከመደባደብ ይሻላል ማደብ
- ኋላ ከመጸጸት አስቀድመህ መጠንቀቅ ይገባል

ከመገፋት ይሻላል መገፋት
- በሰው ላይ ግፍ ከመሥራት በራስ ላይ ቢደርስ ይሻላል

ከመጠምጠም መማር ይቅደም
- ቀድሞ ዕውቀትን መገብየት ይሻላል ዐዋቂ ለመምሰል ከመሞከር

ከመጣህ ኃዘን ልንገርህ
- መቸኮል የማይወጡት አደጋ ላይ ይጥላል

ከመጣሽ ማሪያም ታምጣሽ
- እንኳን መጣሽልኝ

ከመጥፎ የተጋባ ገደል ገባ
- ዘለዓለሙን በችግር በስቃይ ይኖራል

ከመጫን ከመተብተብ ይሻላል መሸከም
- የማያውቁበትን ጭነት ለመጫን ከመሞከር መሸከሙና መሔዱ ይቀላል

ከሚሰፈልፍ ጉበዝ ዝምተኛ ፈሪ ይበልጣል
- ዝምታ ወርቅ ነው

ከሚስቱ ጋር ያበረ ከአግዜር የተማከረ
- የሚስቱን ምክር የሰማ በትዳሩ ደስተኛ ይሆናል

ከሚያስፈልገው በላይ የሚሰማመጥ ሊያታልልህ ወይ ሊገድልህ
- በአጠገብህ ያሰውን አፈጮማ በጥንቃቄ ተመልከተው

ከመህል ደርሶ አደርስ ከዳር አይመለስ
- ወላዋይ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ የማያደርስ

ከማርከኝ ሞቴን አታለየኝ
- ሞት ከባድ ዕዳ ነው

ከማሽላ ቢያስወጧት ሰዘንጋዳ ገባች
- ከአንዱ ጥፋት ወደ ሌላው ጥፋት ተሸጋገረች

ከማሽላ ገንጠል ከአገዳ ጠልጠል
- የተገኘውን ሁሉ ማግበስበስ



ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል
- ያልለመዱት ነገር ምንም መልካም ቢሆን ስጊዜው ለመቀበል ይቸግራል

ከማይም ጕረምሳ የተማረ ሽማግሌ
- ዘዴና ብልሃት ስላላቸው ብዙም ጉልበት አያሻቸውም

ከማይረባ ሎሌ ወደል ውሻ ይሻላል
- ከማይረባ አሽከር ወደል ውሻ ባለቤቱን ከአደጋ ይጠብቃል

ከማይሰማህ ደብር አትማል ከአቅምህ በላይ አትዝለል
- ከአቅምህ በላይ አትንጠራራ

ከማይናገር ከብቱን ከማይራገጥ ወተቱን
- በቀላሉ የምጠቀምበትን መንገድ ወይም ዘዴ ፈልግ

ከማይጠቅም ኑሮ መቃብር ይሻላል
- በቁም ከመሰቃየት መሞት ይሻላል

ከማደር ማስተዳደር
- ታዛዥ ከመሆን አዛዥ መሆን ብዙ ጥቅም ያስገኛል

ከማጠቢያ ሁሉ ሳሙና ከሥራ ሁሉ ትሕትና
- ትሕትናና አክብሮት የሰውን ልጅ ከሰው ጋር የሚያኖሩት ጠቃሚ ባሕርያት ናቸው

ከምላ የለዩት ደብተራ ውቅር ይሠራ
- ባለማወቅ ሊጐዱት ያስጡት ጠቃሚ ሰው ሊሆን ይችላል

ከምላ የተውት ደብተራ ያደርጋል ሴራ
- በጥቅሙ ላይ የመጡበት ሰው እንዲሁ በቀላሉ አይሰቁትም ችግር ፈጣሪ ሊሆን ይችላል

ከምን ላይ ቁመሽ አግዜርን ታሚያለሽ
- የት ሆነሽ ማንን ተማምነሽ ነው እንዲህ ያለ እርምጃ ስመውሰድ የተነሳሽው

ከምክር የለዩት ደብተራ ነገር ይሠራ
- አንድን ሰው ስታርቀው በአንተ ላይ ማሴሩ የማይቀር ነው

ከምድር አብለ ከሰማይ ዳብሶ ይሰጥ
- ከየትም ከየትም ብሎ የጠየቁትን ያቀርባል

ከምድር አይስጡም ስንዝር
- ርስት ሰባለቤቱ እንጂ ለሳልፎ ስሌላ አይሰጥም

ከምድር አደላድሎ ከአህያ ከቡላድ አደላድሎ ከቋያ
- አንድን ነገር በመጀመሪያ እንዲሆን ካደራጁ በኋላ ወደሚፈስግበት ያደርሱታል

ከሞተ በኋላ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ
- መፍትሔ ስሌለው ነገር እራስን ማስጨነቅ አይገባም

ከሞተ ንጉሥ የቆመ ባላምባራስ
- ከመሞት መሰንበት

ከሞተ አንበሳ ያለ እንሰሳ
- ከጠፋው ሁሉ በእጅ ያለች ትንሿ ገንዘብ ትበልጣለች

ከሞተች እቴቴ ምን አለኝ ካማቴ
- ከሞተች ሚስቴ ምን አለኝ ካማቴ

ከሞቱ በኋላ መድኃኒት ካረጁ በኋላ አቤት አቤት
- ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ

ከሞት ወዲያ ሐኪም አይጠየቅም
- ካለፈ ክረምት ቤት አይሠራም

ከሞት የተረፈ ከጥላ ያረፈ
- በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ

ከሞኝ ሸክም ሞፈር ቀንበር ይቆረጥበታል
- ያላዋቂ ውኃ ውስጥ ሆኖ ይጠማል

ከሞኝ ክብረት የብልህ ድህነት
- ሞኝ ቢከበርም ንብረቱን ማስተዳደር አያውቅበትምና ክብረቱ አይዘልቅም

ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል
- ያላዋቂ ውኃ ውስጥ ቆሞ ይጠማል

ከሞኝ ጋር ከመነጋገር ከብልህ ጋር መቸገር
- የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር

ከሩቁ በቅርቡ ከደረቁ በርጥቡ
- ችግሩ ቶሎ ሊቀረፍ ይገባል

ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት
- ለችግርህ ጊዜ ቶሎ የሚደርሰው ጎረቤትህ ነውና ተስማምተህ ኑር

ከራስ በላይ ነፋስ
- ለራስ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

ከራስ ወዲያ መስካሪ ካምላክ ወዲያ ፈጣሪ ከጠጅ ወዲያ አስካሪ
- ሰው ምንጊዜም ስለራሱ ትልቅነት ያወራል

ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር
- ሙሉ በሙሉ ያልተጓደለ

ከርሞም ነገ ነው
- ቀን ቢቆጥሩ ደረሰ በእግሩ

ከርዛት ክፉ ስራ ማጣት ከአካላት ክፉ የሆድ ጅማት
- አንድ ሰው ስራ ካጣ ነውሩ ገመናው መገለጡ ነውና ስራ አስፈላጊ ነው

ከርጠ ያንጋጠጠ በለጠ
- ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም

ከሰልስተኛ ይሻላል ትናንትና
- ሳይርቅ በቅርቡ

ከሰማ የነበረ ካለቀሰ የቀበረ
- በቦታው ተገኝቶ ጉዳዩን መፈጸም ከሁሉም በላይ ነው

ከሰማይ የወረደ ለምድር አይከብድም
- ምድር ሁሉን ቻይ ናት



ከሠሪው አሠሪው
- ከአንዱ አንደኛው ይበልጣል

ከሥሩ የተነቀለ ወይራ አለ ብሎ የተረታ ባላጋራ
- ነገርን በሩቅ ሳይሆን በቅርብ ተገኝተው ካላዩት ካላወቁት መሳሳት አይቀርም

ከሥሥትም ዐፈር ይጠግባል
- ከሥሥታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

ከሥጋ ብስና ጉመን በጤና
- ከአጉል ምቾት በሰላምና በጤና ተራ ኑሮ መኖር ይሻላል

ከሰቀላ ወደ ጥላ
- ሰውጥ የሌለው ነገር

ከሰው ለሰላሳ የራስ አንካሳ
- ከሰው አዲስ ዕቃ የራስ አሮጌ ዕቃ ይሻላል

ከሰው መልካም ገበሬ ከእህል መልካም ጥሬ
- ገበሬ አርሶ ፍጥረቱን ሁሉ ስለሚመግብ ከሱ የተሻለ መልካም ማን አለ?

ከሰው መርጦ ለሹመት ከዕንጨት መርጦ ለታቦት
- ሁነኛውና አስፈላጊው በሰው ዘንድ ይታወቃል

ከሰው ምቀኛ ይሻላል የእባብ መርዘኛ
- ምቀኛ ለሕይወትህ አስጊ ነው

ከሰው ሲያድሩ አንድ ጥፊ ተበልጦ ነው
- ከፋውንም ደጉንም ችለው ነው

ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት አይጠፋም
- ሰው ሆኖ የማይሳሳት የለም

ከሰው ቀለብላባ ከመሬት ገብጋባ
- የሚቅለበለብ ሰው አይወደድም

ከሰው እድር ብዬ ቀረሁ ተታልዬ
- እራሴን ዝቅ ባደርግ አስቀናኝ

ከሰው አገር መልከኛ ያገር ምንደኛ
- ከሰው ለሰላሳ የራስ አንካሳ

ከሰው እንደ ሪዐይት ከዛፍ እንደ በቀልት
- ተቀጥላ ሁኖ የሚበቅል ተክል የዋናውን ዛፍ ምግብ መሻማቱ አይቀሬ ነው

ከሰው እንደ ቡዳ ከከብት እንደ ጉዳ
- እኒህ ሁለቱ ጉዳትን ያስከትላሉ

ከሰው ክፉ የሚያማ ከዕንጨት ክፉ ጠማማ
- ሐሜተኛ ነው ከዳተኛ

ከሰው ክፉ ደባል ከእንጨት ክፉ ደጎል
- ጥገኛ የሆነ ሰው የሰው ገበና ያወጣል

ከሰው ክፉ ባል ከጭነት ክፉ እሳል
- ጥገኛ ሰው የሰውን ስም ያጠፋል

ከሰው ከፉ ደብተራ ካውሬ ከፉ ዳሞትራ
- ደብተራ መተት ስለሚመትት ሰዎች ይፈሩታል

ከሰው ጋር ሲኖሩ ደግ ሆኖ አህያ ሲጭኑ ሦስት ሆኖ
- ከሰው ጋር የሚኖር ሰው ያሰውን አካፍሎ እንጂ ተቆናቁኖ አይሆንም

ከሰው ፊት አይበሱ ሥጋን አይበድሉ
- ገንዘብ አጠራቅማለሁ ብለህ ሥጋህን አትበድል

ከሰው ፊት ውኃ በወንፊት
- የሰው ፊት ያንገበግባል ይጠብሳል

ከሰጡህ አትሰፍ በሰጡህ አትስነፍ
- የተሰጠህን በሚገባ ተጠቀምበት

ከሰጭው አሳጭው
- አንዱ ሰሚስጠው ሌላው የሌላውን ስም በማንሳት ሰውን ያሳጣል

ከሱሪ የተሸሸገ ብልት እንቅልፍ የሌሰበት ሌሊት
- እንቅልፍ ያጣ ሰው ሌሊት አይነጋለትም

ከሳሽና ተከሳሽ የመረጠን ያሽ
- የተመረጠው ወገን የመረጠውን ወገን እንደፈለገው ያደርገዋል

ከሳሽ ከአሳት ጠባሽ
- ወንጀል ላለመሥራት ሞክር ተጠንቀቅ

ከሳሽ የተከሳሽን ልብ ቢያውቅ ከቤቱም አይነሳ ነበር
- አንደኛው የሌላኛውን ሐሳብ ሊያውቅ አይችልም

ከሳቱ ወዲያ ይገኛል ምክር ያ ካመሰጠ ይሰበሰባል እግር
- ካለፈው በመማር ስሕተት ላለመፍጠር ይጠንቀቁ

ከሴት ሆዳም ያንድ ዓመት በረዶ ይሻላል
- ሰራሷ ብቻ የምታስብ ሴት ቤተሰቡን ትበድላለች

ከሴት መምከር ደግሶ መስከር
- ሴት ምስጢር ስለማትይዝ አትማከር

ከሴት ነገር ከበቅሎ መንበር አይታጣም
- ሴት መላ አታጣም

ከሴት ነገር ከበቅሎ መደንበር
- ሴት ነገረኛ ናት

ከስስታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው
- ስስታም የሰሰተውን ምግብ አይበላውም

ከስስታም ዐፈር ይጠግባል
- ስስታም ሁሉ ነገር አያጠግበውም

ከስብ ስም ይሻላል
- ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይበልጣል

ከስቼ ቢያዩኝ ዥማት ሰመኑኝ
- መከሳቴን አይተው ናቁኝ

ከስድብ ከፉ አቅሙን ዐያውቅ
- አቅምን ዐውቆ አለመገኘት ለችግር ይዳርጋል



ከሶ ነገር ያጣ ቀብቅቦ ዘር ያጣ
- መጨረሻው ያላማረ ሥራ

ከሸማኔ ቤት ቁጢት ከመነኩሴ ቤት ዝተት አይጠፋም
- ባለሙያ ከሙያው ጋር የተያያዙ መሣሪያዎችና ውጤቶች ሊኖሩት ይችላል

ከሽንጉ ቢረታ ሚስቱን ከቤት መታ
- የምችሰውን ምታ ቢሉት ወደሚስቱ ሮጠ ይባላል

ከሹመት ግብዝና ከሕመም ቁምጥና
- ሥር የሰደደ ችግርን ለማስወገድ ጊዜ ይፈልጋል

ከሹምና ከእሳት እጅግም ሳይቀርቡ እጅግም ሳይርቁ
- ከሹም ጋር ሲሠሩ በሩቁ እንጂ ከቀረቡት አደጋ ሊኖር ይችላል

ከሹም አይጣሉም ከግንብ አይታገሉትም
- ከአለቃ ጋር ተስማምቶ መሥራት ነው

ከሹም ፊትና ከመጥረቢያ ፊት አይቆሙም
- አለቃህን ልታከብረው ይገባል

ከሺህ ሎሌ አንድ በሬ
- ሎሌ ተቀላቢ ሲሆን በሬ ግን አርሶ ያበላል

ከሺህ መካሪ አንድ ቋጣሪ
- አንድ መልካምና የተጨበጠ ነገር የተሻለ ነው

ከሺህ ምስክር የታቦት እግር
- ብዙ ምስክር የሚሻውን በእምነቱ ስትመጣበት በቀላሉ ይሸነፋል

ከሺህ በቅሎኛ አንድ ፈረሰኛ
- ከብዙ እያዘገሙ ከሚሠሩ ጥቂት ፈጣን ሠራተኞች ይበልጣሉ

ከሺህ ነፍጠኛ አንድ መልከኛ
- ከብዙ ምንዝሮች አንድ ኃላፊ ፈጥኖ ይወስናል

ከሺህ አብራሪ አንድ አምራሪ
- ከብዙ ተበደልኩ ባይ አንድ ቆራጥ ይበልጣል

ከሺህ አብሰት አንድ እውነት
- ሺህ ሐሰት መደርደር ሚዛን አይደፋም

ከሺህ ወሬኛ አንድ ልበኛ
- ብዙ ከሚያወራ አንድ አስተዋይ ይበልጣል

ከሺህ ዋስ ራስ ቀራቢ
- በብዙ ዋስ ከሚመካ ተከሳሽ በራሱ የሚተማመን አንድ ተከሳሽ ይበልጣል

ከሺህ ደብተራ አንድ ቄስ መንኳሳ
- ከብዛት ሳይሆን አንድ ጠቃሚ ሰው ሊበልጥ ይችላል

ከሺህ ደብተራ የቄስ ዳንኪራ
- የቀሳውስቱ ዝማሬ ከደብተራው የተሻለ ነው

ከሺህ ገበና አንድ ቀጣፊ ልበኛ
- ከብዙ ሰው ይልቅ አንድ ዋሽ አስተዋይ ይሻላል

ከሸማግሌ ምክር ከሽበታም ከጉበዝ ወረር ከጉልበታም
- ለዓላማህ የሚያመችህን እየመረጥክ ሥራ ላይ አውል

ከሾህ ወጥቶ አጋሬጣ

- ከድጡ ወደማጡ

ከቀበጡ ሞት አይቀርም

- ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ

ከቀኑ ያለፈ ሥጋ መግማቱ አይቀርም

- ሁሉ ነገር በጊዜው በወቅቱ ነው

ከቀናተኛ ሰው ሽሽ እንዳትበላሽ

- ቅናተኛ ከመግደል ወደኋላ አይልምና ተጠንቀቅ

ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ

- ከምንም ይሻላል ትንሽ

ከቀጥቃጭ ያረፈደ ቀጥቃጭነት ለመደ

- ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች

ከቁርባን ውጭ ክርስትና

- የኋላው ወደፊት

ከቁንጫ ሌጦ ያወጣል

- የማይሆን የማይደረግ ነገር ይፈጽማል

ከቁንጫ መላላጫ

- የማይሆን ነገር

ከቂል ፈገግታ የወዳጅ ቁጣ

- ትርጉም ያለው ስለሚሆን ይመረጣል

ከቂጡ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም

- ችግር ያለበት ሰው እንደልቡ መሆን አይችልም

ከቃጫ ወዲያ ገመድ ከእናት ወዲያ ዘመድ

- ከእናት የበለጠ አዛኝ ሊኖር አይችልም

ከቅርቡ የወደቀ መሰበሩ አልታወቀ

- ስሕተቱን ያረመ ችግሩን መከላከል ይችላል

ከቅርብ የወደቀ ከስብራት ያድናል

- ስሕተትን ፈጥኖ ማረም ከጉዳት ያድናል

ከቅርብ የወደቀ ከቁስል ያድናል

- ስሕተትን ፈጥኖ ማረም ከልፋት ይሰውራል

ከቅዱሳን እፍ ምስጋና ከሰማይ ደመና

- መልካም ሰዎች ሁልጊዜም መልካም እንጂ ክፉ ነገር አይታያቸውም

ከቆረሰ የጐረሰ

- ከተስፋ በእጅ ያለ ይበልጣል

ከቆረጠ አትምከር

- ትርፉ ድካም ነውና

ከቆጥ የተለቀለ ከማገር የተንጠለጠለ

- ሁኔታዎች አንድ ናቸው

ከቆፈሩት ጉድጓድ ላይገቡ አይቀሩም

- ሰው ራሱ ባዘጋጀው ተንኮል ውስጥ መግባቱ አይቀርም



ከቋት የሚዘግንለት ከምርት የሚነፈግለት አለ

- ፈጥኖ እንዲያልቅ የማይፈለገውን ለማቆየት ሲባል

ከበላህ ብላ ከሰው አትጣላ

- ከሰው ጋር ተመሳስለህ ኑር

ከበሬ ፊት መቆፈር

- ከእኛ ወዲያ ማፏጨት ለማሞጥሞጥ

ከበሬ ፊት የምትገኝ ጥጃ የሣር በሽታ ይገላታል

- ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር

- ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው

ከበሽታ ላይ ችግር መሪ የሌለው ዕውር

- በችግር ላይ ችግር መደራረብ በጣም ያስቸግራል

ከበቀለ ያልተነቀለ ከተነቀለ ያልተተከለ

- ከተስማሙ አብረው ይኖሩ ካልተስማሙ ለምን ጊዜውም ይለያዩ

ከቡሃቃ መስታወት ያድንሽ

- ከችግር ያውጣሽ

ከቡቃያ ሲገባ አፈላማ

- አጥፊ ባጠፋው መጠን በሕግ እንዲከፍል ይገደዳል

ከባለቤቱ እጅ የዋለ እንቁላል አይሰበርም

- ባለቤት የዕቃን አያያዝ ያውቃል

ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

- እራሱን የሚያውቀው ባለቤቱ ብቻ ነው

ከባለ ቀትር አትቀታተር ከባለጊዜ አትሮካከር ከነገረኛ አትነጋገር

- ነገረኛን በሩቁ ነው

ከባለጌ መጋባት የጨዋ ልጅ መፋታት

- ያልተመጣጠነ ጋብቻ ዘላቂነት የለውም

ከባለጌ ክቡር የድሃ ስልጡን ይሻላል

- ከባለጌ ሰው የድሃ ኩሩ ይሻላል

ከባለጌ ጡጫ ከዳገት ሩጫ ከዕውር ግልምጫ ያድናችሁ

- ከአስከፊና አስቃቂ ሁኔታዎች ተጠበቁ

ከባላገር ንብ የከተማ ዝንብ ትበልጣለች

- የባላገር ሰው የሥራ ሰው ቢሆንም ንቃት ይጉለዋል

ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ

- በባሏ እየተኩራራች ትለምናለች

ከባልሽ ታረቂ ቢሏት ልመና መሰላት

- እላዋቂ ሲመክሩት የለደቡት ይመስለዋል

ከባል በፊት ልጅ ይሰጥሽ

- ክፉ ነገር ያጋጥምሽ ተዋረጂ /እርግማን/

ከባልንጀሮቿ ከፍ ያለች ማሽላ ወይ ለወፍ ወይ ለወንጭፍ

- ይህ ቀደም ቀደም ኋላ ለመጋደም

ከባሕር አይቀዳ፤ ለንጉሥ አይረዳ የለም
- ለንጉሥ የማይሠራ የማያጉበድድ የለም

ከባሕር ወጥታ፤ ጤዛ ላሰች
- በሰፊው ለምዳ አጣች

ከባሕር ጠልቆ፤ ከገደል ወድቆ
- ከአጉል እሚሟት ተጠበቅ

ከባቄላ አይጠፋም ዲቃላ
- ከጥሩ ነገር መሃል መጥፎ አይታጣም

ከባእድ ሰሰላ የራስ ከርካሣ
- ከሰው አዲስ ዕቃ የራስ የሆነ አሮጌ ዕቃ ይሻላል
- የተውሶ ይሔዳል ተመልሶ

ከባእድ እየጉረስክ ወደ ዘመድ ዋጥ
- ዘመድህ ለችግርህ ጊዜ ደራሽ ስለሆነ ባገኘህ ጊዜ አካፍለው

ከባእድ ወደ ዘመድ ከጫካ ወደ መንገድ
- ውጭ አገር ከመኖር በትውልድ አገርህ መኖር ጥሩ ነው

ከባእድ ጋር የበሉት በሶ ይወጣል ደም ጉርሶ
- ከማይሆን ሰው ጋር የፈጸሙት ተግባር የኋላ ኋላ አስከፊ ይሆናል

ከቤተ ቀሲል ቤተ ቆማጣ ይሻላል
- ከቅሌታም ቤተሰብ ራሱን ያስከበረ የቆማጣ ቤተሰብ ይሻላል

ከቤት ዶሮ ሲገኝ ከበረሃ ቆቅ ይያዛል
- ቤትህ ሲሟላ ከውጭም ይቀናሃል

ከብልህ የሚወጣው ስሕተት ተራራ ያህላል
- ብልህ እይሳሳትም ከተሳሳተ ግን የሚላላተው ቀላል አይሆንም

ከብልህ ያለ ሞኝነት ተራራ ያህላል
- ብልህ በሰው ላይ እምነት ይጥላል ይህ ደግሞ በሌሎች ዘንድ እንደሞኝነት ይቆጠርበታል

ከብልህ ጠበቃ ሞኝ ሰራሱ ያውቃል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

ከብቱን በእግት እጁን በሰንሰለት
- ለመከራ የተዳረገ ሰው

ከብት በሰማይ ይከፍት
- ሀብት ካለ በሰማይ መንገድ እለ

ከብት ቢወፍር ሰልደት ሰው ቢወፍር ለመሬት
- መወፈር ዋጋ የለውም የእዕምሮ ብስለት እንጂ

ከብት አይቶ ከቱ ማግባት ከብቱ ቢያልቅ ሁለት ጥፋት
- ጋብቻን ከሀብት አኳያ ማየት ተገቢ አለመሆኑ

ከብት አይወድም ገደል ሰው አይወድም በደል
- ሰው ጥቃትን ፈጽሞ አይቀበልም

ከብት ያስአረኛ ሕዝብ ያለዳኛ
- እንጀራ ያለወጥ ቤት ያለሴት



ከብዙ ሐሰት አንድ እውነት
- ምንም ቢያስቀዝን ጮማ ይሻላል

ከብዙ ሺ ይበልጣል አንድ እሺ
- እሺ ከሺ ይበልጣል

ከብዙ ጉልበት ትንሽ ብልሃት
- ሥራን መሥራት በብልሃት

ከብዙ ጸሎት የልብ ቅንነት
- ቀናን ሰው እግዚአብሔር ይወደዋል

ከተመቱ መጠርጠር ጅብ ከወሰደ አጥር ማጠር
- ከሞቱ በኋላ መድኃኒት ካረጁ በኋላ አቤት አቤት

ከተማረ የተመራመረ
- ላይ ላዩን ከሚያነበንብ ጠለቅ ብሎ የተመራመረ ብልጫ አለው

ከተሜ አይጦም አይበላ
- የከተማ ሰው ለጾም ትኩረት የለውም ሁሌም እንዳይበላ የሚበላው ነገር የለውም

ከተሚጋች ታራቂ ከአጣቢ አድራቂ
- ነገር አሰኘ ከማለት ሥራ አሰኘ ማለት ይበልጣል

ከተራብ አዝናለሁ ለጠገበ
- ጥጋበኛ ሰው ለአደጋ የተጋለጠ ነው

ከተቀረበ ይበላዋል ሳይወድቅ ይታገለዋል
- አንድን ተግባር ለመፈጸም በቅድሚያ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል

ከተባሉ የኛ ከተጋደሉ ደመኛ
- ግጭት ሳይኖር እንደቤተሰብ ግጭት ሲኖር መለያየትና በደም መፈላለግ ይመጣል

ከተናጋሪ ሰሚ ከሰሚ ተርጓሚ
- ነገርን አድምጦ እህልን አላምጦ

ከተናጋሪ ዝምተኛ ያስቆጫል
- ምንም አስተያየት የማይሰጥ ዝምተኛ ሰው ያናድዳል

ከተናጋሪው ደጋሚው ከተርጓሚው ደርጋሚው
- አንድን ክፉ ነገር ከተናገረው ይልቅ ደጋሚውና ተርጓሚው ነገሩን ያባብሱታል

ከተንከሰኛ የዋህ እይወጣም
- ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልም

ከተዘጋ ቤት ከተዳፈነ እሳት
- ጥንቃቄ ካደረክ ለአደጋ አትጋለጥም

ከተዛመደ የተዋደደ
- ፍቅር ከሁሉም በላይ ናት

ከተዛመዱ የተወለዱ
- በሥጋ በደም መገናኘት ይበልጣል

ከተያዙ ወዲያ ቁስ ጥሩልኝ ማለት

- መጀመሪያ ሳትጠነቀቅ ከተያዝክ በኋላ መጨነቅ ምንም አያመጣም

ከተጋደሉ ደመኛ ከተማማሉ ማለኛ

- ሁለቱም ከተገዳደሉ ደመኛ አይኖርም

ከተፈሩ እንደ አንበሳ ከፈሩ እንደ ሬሳ

- መፈራት እንደ አንበሳ መፍራት ደግሞ እንደ ሬሳ ሊያስቆጥር ይችላል

ከታዘለ የማይወርድ ከሞቀ የማይበርድ

- በነበረበት የሚቆይ ለዘለዓለም የሚኖር የለም

ከታዳጊ ጌታ ለግደድ ያለ ቦታ

- አጉል ጌታ ፊት መቆም አስቸጋሪ ስለሆነ ዘወር ያለቦታ መቆሙ ይሻላል

ከታገልህ አባት አይጥልህ

- አባትህን በሚገባ ካገለገልክ አባትህ ለአንተ ያስብልሃል

ከትንሽ በላተኛ ይሻላል ጦመኛ

- በትንሽ ነገር ከመደሰል ጨርሶ ማጣቱ ይሻላል

ከኋላ ጸጸት ፊት መጠንቀቅ

- ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

ከነጂው የተጣላ በሬ ቀንድ ቁርፋርፌ

- ከአለቃው የማይስማማ ሠራተኛ ጉዳት ያጋጥመዋል

ከነገረ-ቀደሙ ይሻላል አፈ-ገራሙ

- ቀደም ቀደም እያለ በመናገር ሰው ከሚያስቀይመው ዝም ያለው ይመረጣል

ከነገረኛ ሰው ስንቅ አይደባልቁ

- የጠንቀኛ ፊስ ዐይን ያፊስ

ከነገሩ አይጉርስ

- በነገሩ ለመሳተፍ አስቸጋሪ የሆነበት ሁኔታ

ከነገሩ ጦም እደሩ

- ነገርን መራቅ ይገባል

ከነገር ማን ይቀድም የደም

- ከሁሉ በፊት የወገን ጉዳይ ቅድሚያ ሊስጠው ይገባል

ለነገር ተው ባይ ከጦር አግባ ባይ

- ሰዎች ነገር እንዳይባባስ ሐይ ማለታቸው ተገቢ ነው

ከነገር ከፉ ቁጭት ከወፍ አስደንጋጭ ድርጭት

- ነገርን ካልተውት በቀር መቆጨት አያስፈልግም

ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ

- የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ

ከናበላሽ ማን ይግዛሽ

- መጥፎ ባሕሪ አለሽ

ከናት ልጅ አይበልጡ ከሞት አያመልጡ

- ምንም መቀራረብና መፈቃቀር ቢኖር ከሞት መቅረት አይኖርም



ከናት ትሻል ሞግዚት

- ከእናት የምትሻል ሞግዚት ልትኖር ትችላለች

ከናቷ ልጅዋ ትብስ ባቄላ አርባት እጅዋን ትልስ

- በማይሆን ሁኔታ የሚፈጸም ተግባር

ከኔ ከወሰድሽው ተቀምጠሽ ልበሽው

- እንዴ ሁኔታውን ከፈጸምሽው አትቻኮይበት

ከንጉሥ በላይ ሰው አይፈርድ ከባሕር ላይ እሳት አይነድ

- እሳትና ውኃ አጥፊና ጠፊ በመሆናቸው አብረው አይሔዱም

ከንፋግ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

- ስስታም በሰለተው ነገር አይጠቀምበትም

ከአህያ ባልነት የፈረስ ውሽምነት

- ካገቡ አይቀር ደህና የተሻለ ሰው

ከአህያ አፍለኛ የጅብ አሮጌ ይበልጣል

- ከጅብ ጉፈሪያም ያንበሳ መላጣ

ከአህያ የዋለች ጊደር ፊስ ተምራ ትገባለች

- ከባለጌ የዋለ ብልግና ተምሮ ይመጣል

ከአህያ ያረፈደ ያህያን ዐመል ለመደ

- ከባለጌ የዋለ ብልግና ለምዶ ይመጣል

ከአማት መኖር መጋማት

- ተስማምቶ ለመኖር አስቸጋሪ ነው

ከአምናው ቢሻላት ቁንጣን ገደላት

- አቅምን ዐውቆ አንድን ተግባር መፈጸም ተገቢ ይሆናል

ከአርባ ዓመት አትመከት ከሃምሣ ዓመት አትሚገት ከስልሣ አመት አትዶልት

- ከአቅም በላይ መንጠራራት ለጉዳት ይዳርጋል

ከዓርብ ሮብ በፊት እጅ ይጹም ከፉ ነገር ካፍ አያወጡም

- ከጾም ይልቅ መጥፎ ድርጊት አለመፈጸሙ ይመረጣል

ከአሰብሽው አልተውሽው

- በነገሩ ላይ ብዙ ካሰብሽበት በተግባር መተርጉምሽ አይቀርም

ከአባቱ ፊት የሚናገር አፉ ለምጣም ይሆናል

- አውቃለሁ አውቃለሁ በማለት ቀደም ቀደም የሚል ውጤቱ አስከፊ ይሆናል

ከአባያ ቤት እህል ከአይት ቤት ብቅል

- ሥራን በደንብ ካልሠሩና ንብረትህን ካልተጠነቀከለት ምንም አይገኝ

ከአብሮ አደግህ አትለደድ

- መተዋወቅ ያናንቃል

ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ

- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

ከአዋቂ ጠያቂ ከጠያቂ አጥባቂ ከአጥባቂ አድራቂ

- ዕውቀት የሚገኘው በመጠየቅ ነው

ከአውሬ ክፉ ዘንዶ ከዝናብ ክፉ በረዶ
- ከክፉ ነገር መጠበቅ ራስን ማዳን ነው

ከአድራጊቱ በለጠ ቃላቱ
- ከተግባር ይልቅ ወሬው በዛ

ከአጉል ጥንቅላ፣ የጨዋ ልጅ መላ
- ከአጉል ዓምልኮ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ስልትና ዘዴዎች ይበልጣሉ

ከአጋም የተጠጋ፣ ቁልቋል ሲያስቅስ ይኖራል
- ከመጥፎ የተጠጋ ሲሰቃይ ይኖራል

ከአጭር ምክር፣ ከኃይለኛ ውረር
- እንደየሁኔታው ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር አብሮ መሥራት ጠቃሚ ነው

ከአፈርኩ፣ አይመልሰኝ
- እንዴ ከተናገርኩ በሚል ችክ፣ ድርቅ ማለት

ከአፍሽ ይለቡልሽ፣ አይገባ ከሆድሽ
- በቃላት የሚያዝኑልሽ፣ የሚቆጩልሽ የሚመስሉሽ ለአንቺ ተግባራዊ ውጤት የሰውም

ከእህል ክፉ እኛ፣ ከነገር ክፉ እንኛ ከሣር ክፉ ሙኛ
- አንድ ሰው ሲጠየቅ የሚሰጠው የእንኛ መልስ አታካች መሆኑ ነው

ከእርስት፣ መልክ ይበልጣል
- ከሚሸጥ ከሚሰወጥ ርስት አብሮ የሚኖር መልክ ከመልካም የትዳር ጓደኛ ጋር ያጐዳኛል

ከእባብ እንቁላል፣ ርግብ አይፈለግም
- ከመጥፎ ሰው ቅንነት አይገኝም

ከእናት፣ ቀን ይሻላል
- ቀን እንዴ ያነሳል እንዴ ይጥላል ቀን ለመልካም ቦታ ያሳጫል

ከእንግዲው፣ ማቅ ይሻላል
- ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ

ከእጅ፣ አይሻል ዶማ
- የተሻለ ነገር አይደሰም

ከእግዚአብሔር ወዲያ ፈጣሪ፣ ከአባት ወዲያ መካሪ ከናት ወዲያ መስካሪ
- በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ፈጣሪ፣ አባትና እናት ከፍተኛ ቦታ ይኖራቸዋል

ከኩተት እስከ ሽበት፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት
- ከድሮ ጀምሮ

ከካሕን ይዋደዷል፣ ከላም ይሰደዷል
- የራስ የሆኑ እንስሳትን ስማኖር ምግብ ወደሚገኝበት ሥፍራ መጓጓዝ ተገቢ ነው



ከክፉ ሎሌ፣ ጌታው ኮበለለ
- ከማይላቀቁ ካልሆነ ታዛዥ ጋር ከመኖር መኖሪያ ቦታን መለወጡ ይሻላል

ከክፉ ባለዕዳ፣ ተልባም አይጐዳ
- ከአስቸጋሪ ባለዕዳ ያገኘኸውን መቀበሉ ይመረጣል

ከክፉ ባለ ዕዳ፣ ጉመን ዘር ተቀበል
- ከክፉ ባለዕዳ ሌላ እንኳ ቢቀር የጉመን ዘርም ቢሆን መቀበል ይመረጣል

ከክፉ ተወልጄ፣ ስፈጭ አደርኩ
- ከአጣ፣ ከነጣ ቤተሰብ የተወለደ ታታሪ ካልሆን በስተቀር ለክፉ ችግር መዳረጉ አይቀርም

ከክፉ ጉረቤት፣ አይሠሩም ደህና ቤት
- ካልሆነ ሰው ጋር ብዙም መቆየት ስለማይቻል ዘላቂ ነገር መመሥረት አይገባም

ከወረወረ የመከረ፣ ከመከረ የሰነዘረ
- ጠባየ ብልሹ የሆነውን በምክር ያጣን ደግሞ ከእጃችን በመሰንዘር መደገፍ ይገባል

ከወሰን፣ ቢያልፍ ይቀሰፍ
- ለሁሉም ነገር ልክ ወይም ወሰን እንዳለው ተገንዘብ

ከወንድም ደረቅ፣ ከወጥ መረቅ
- ከማንኛውም ሁሉ ለስለስ ያለውና የማይቆረቁረው ይመረጣል

ከወደቁ ወዲያ፣ መንፈራገጥ ለመላላጥ
- ችግር ከደረሰብህ በኋላ ብትንፈራገጥ ትርፉ ድካም ነው

ከወደቁ ወዲያ፣ መንፈራንጥ ወገብን መምለጥ
- ትርፉ ድካም ነው

ከወዳጅ መስንበት፣ እንጡ አለማለት
- በወዳጅነት አብሮ ለመቆየት የሰጠኸውን ብድር አምጣ ብለህ አታስጨንቅ

ከወዳጅ የቀደመ፣ ከጠጅ የከረመ
- የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርክ፣ በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ

ከወንብ በላይ ታቦት፣ ከወገብ በታች ጣዖት
- ውስጡን ለቁስ

ከወገኑ የተለየ እንበጣ፣ ይሆናል ፈንጣ
- ከወገን ተለይቶ ምቾት አይኖርም

ከወፈሩ ስው አይፈሩ
- በአንድ ነገር ወይም በገንዘቡ የተማመነ ሌላውን ስው ይንቃል

ከወፈሩ ፈጣሪን አይፈሩ ሰው አያፍሩ
- ገንዘብ አለኝ ብሎ በገንዘቡ የሚኩራራ ሰው ፈጣሪውንም ስውንም አይፈራም

ከዋለች አደረች፣ ካደረች ለመደች
- ቀስ በቀስ ወደሚፈለገው ሁኔት መዳረስ

ከውኃ የቀጠነ፣ ከዐይን የፈጠነ
- ለመያዝ ለመጨበጥ ረቂቅነት ያለው ነገር

ከውኃ ዳር ያለች ንብ፣ ማር አትሠራም
- መሠረታዊው ነገር ስላልተሟላ የተፈለገው ነገር ሊገኝ አይችልም

ከውርርድ ላይ ውርርድ፣ ከነበር ላይ ስማርድ
- በውርርድ ላይ ውርርድ መጨመር በወጥመድ ውስጥ እንደተያዘ አውሬ ተቀስፎ መያዝ ነው

በውትር ውትር ይነሳል በትር
- ቀስ በቀስ እድገት ይገኛል

ከውነት የሚሻል ሐሰት፣ ከመውጋት የሚሻል መሳት
- እጉል የማይጠቅም ነገር ስማድረግ ከመሞከር አለመሞከሩ ይመረጣል

ከዐይን ማየት የልብ ዕውቀት
- ልብ ካላየ የዐይን ማየት ዋጋ የለውም

ከዐይን የራቀ ከልብ ይርቃል
- በሩቅ ያለ ነገር ሁሉ ይረሳል

ከዕንጨት እጥር የሰው እጥር
- ጠንካራ ሰዎች ያለው ግቢ አጥርም ባይኖረው በማንም አይደፈርም

ከዕንጨት እጥር የበው አጭር
- አጭር ዕንጨትን ስመሰበር እንደሚያዳግት ሁሉ አጭር ሰውም በነገር የማይችል ነው ይባላል

ከዕውር ቤት አንድ ዐይና ብርቅ ነው
- ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው

ከዘመድ አጠገብ የተዳረች፣ ልጅ ትዳር አትይዝም
- ዘመድ አካባቢ በመኖርዋ ባልዋ ትንሽ ሲናገራት ወደ ዘመዳችዋ ትሮጣለች ቤቷን አጠንክራ አትይዝም

ከዘር የሚሰጡት፣ ከእውድማ የሚነፍጉት አለ
- ሁሉም እንደየአገባቡና እንደየቅርበቱ ይሆናል

ከዘፈን፣ ይሻላል ማዘን
- ዘፈን፣ ደስታ ሲበዛ ያልታሰበ ነገር ሊደርስ ይችላል

ከዚሁ፣ ብሶ እጉንብሶ
- ከወትሮው ሁኔታዎች ወደጉዳት እየተባባሱ መሔዳቸው

ከዚህ የወደቀ ሬሳ፣ ማን ያንሣ
- እልሆነ ቦታ ላይ በተፈጸመ ድርጊት ላይ ተባባሪ አይገኝም

ከዝምታ ያለ ደስታ፣ ከፍቅር ያለ ጨዋታ
- የፍቅር ጨዋታ ሁለቱ ተፈቃቃሪዎችን ያረካል፣ ያስደስታል



ከዝንብ፣ ማር አይገኝም
- ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

ከዝንጀሮ ቆንጆ፣ ምን ይመራርጧል
- አንድም የተሻለ የለም

ከዝንጀሮ ጋሜ፣ ያንበሳ መላጣ
- ከእህያ እፍለኛ፣ የጅብ እሮጌ ይበልጣል

ከይበሉኝ አይል፣ አይብ አትብላ
- ይሉኝታ ከሌለው ሰው ጋር ብዙ መጓዝ አይቻልም

ከደሀና ቢደርሱ፣ ያደርጋል እንደሱ
- ደሀና ቦታ የደረሰ ሁሉ አንዱ እንደሌላው የመሆን ባህርይ ያሳያል

ከደረቀ ዱርት፣ ከጉደጉደ ምድር
- ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ራስን መጠበቅ

ከዳሰ ዳሰ፣ ይሻላል ማረሰ
- ያረሰ፣ የደከመ መቸውንም ውጤቱ ማማሩ አይቀርም

ከደባል ሆድ፣ ቁርጠት ይሻላል
- እምጣ እምጣ ከሚልና ከሚያስጨንቅ ሁኔታ ጥቂት የሚያሳስብ ጉዳይ ላይ ብታተኩር ይመረጣል

ከደብረታቦር ወዲያ የለ ክረምት፣ ከዶሮ ጩኸት ወዲያ የለ ሌሊት
- ጊዜው ወደ መልካም ሁኔት በመለወጥ ላይ መሆኑ

ከደግ ተወለድ ወይንም፣ ከደግ ተጠጋ
- ከሀብታም ተወለድ፣ ወይ ካለው ተጠጋ

ከደጃዝማች፣ ማን ተሚጋች
- ከባለ ቀትር አትቀታተር

ከዲዳ፣ ላም ንዳ
- ከማይናገር ሰው ጋር ከምትጉዳኝ ላም ብትነዳ ይሻላል

ከዳቦ የተገኘን ወጥ፣ አብረህ ግመጥ
- የሌባን ጠበቃ አደባለቀህ ውቃ

ከዳኛ የደረሰ፣ ከልቡ የጉረሰ
- በዳኛ ፊት በደልን ሁሉ እፍረጥርጦ መናገር ስለሚችል

ከዳኛ ፊት አይተነፍሱ፣ እምዛ ከሰው ፊት አይቆርሱ
- ከዳኛ ፊት መዘላበድ የለም

ከዳኛ ፊት አይናገሩም ዋዛ፣ ከልጅ ፊት አይቆርሱ እምዛ
- ከዳኛ ፊት መዘላበድ የለም

ከድሃ ቤት ሠርግ፣ የባለጠጋ ቤት ኃዘን ይደምቃል
- ላለው ቅንጭብ ያረግድስታል

ከድሃ ቤት ጉመን፣ ሲቀቀል ከበሮ ይመታል
- ድሃ ቤት ሁሉ ነገር ብርቅ ነው

ከድሃ ከመበደር፣ ከባለጠጋ መለመን
- ትንሽ ያለው በጣም ያስጨንቅሃል

ከድስት እፍላል፣ ከቅመም ድንብላል
- ለተመረጡበት ዓላማ ብቃት ይኖራቸዋል

ከድጡ፣ ወደ ማጡ
- የባሰ አታምጣ

ከጀመሩ መጨረስ፣ ካረገዱ ማልቀስ
- ሥራን መጨረስ ተገቢ ነው

ከጀርባ፣ ሆድ ይቀርባል
- ከጁ በጉንጩ

ከጃጁ፣ አማራቸው ሊቆነጁ
- ዕድሜ ካለፈ በኋላ መሽሞንሞን ፈለጉ

ከጁ በጉንጩ
- ከጀርባ ሆድ ይቀርባል

ከጅብ የተጠጋ ፈረስ ኋላውን አያይም
- ጠላቱን በቅርብ በመቆጣጠር ላይ ያለ ወደ ሌላ አቅጣጫ አይመለከትም

ከጅብ ጉሬ ሸሽቶ እጅብ ዋሻ
- የባሰ አታምጣ

ከጅብ ጉፈሪያም፣ ያንበሳ መላጣ
- ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ

ከገበያ ሔዶ ማንቀላፋት፣ ባፋፍ ላይ ሆኖ መንጠራራት
- ራስን ለከፋ አደጋ መጋበዝ ነው

ከገንዘብ ዋና እርሰት፣ ከከብት ዋና እንሰት
- ታርሶ እንሰት ከብትም ረብታ ቤት ስለምትሞላ

ከጉሽ አተላ፣ ከዕንጨት ሽበት አይታጣም
- ውሎ አድሮ የተባለው ሁኔታ መታየቱ አይቀሬ ነው

ከጌታህ አትከራከር፣ ከልጅ ጋር አትማከር
- ከልጅ ብትማከር የምታገኘው ብዙ ሐሳብ አይኖርም ከጌታህም ብትከራከር ትርፉ ግጭት ስለሚሆን ጊዜህን አትጥፋ

ከጌታህ አትሮካከር፣ ከውሻ አትሽቀዳደም
- ከአለቃ ብትሮካከር ቆይቶ ያጠቃሃል

ከግቡ የተጐዳ፣ ከጥንስሱ የተቀዳ
- ከመሠቱ የተጐዳ

ከጠላቱ የሚዋደድ፣ እያደር ይናደድ
- ጠላት ጠላትነቱን አይለትምና

ከጠላት መላም፣ የወዳጅ መንከስ ይሻላል
- የወዳጅ መንከስ ወይም ከፉ ሥራ እያደር በጥሩ ሁኔታ ሊታደስ ይችላልና

ከጠላት ምክር የፊተኛውን፣ ትተህ የኋለኛውን ያዝ
- የጠላትን ምክር ጠርጥረህ መቀየር ይገባል

ከጠጅ ወዲያ አስካሪ፣ ከባለቤት ወዲያ መስካሪ
- ምንጊዜም ባል ለሚስቱ፣ ሚስትም ለባሏ ቅርብ ናቸው



ከጡጫ የዳነ፣ በርግጫ
- ከቁንጫ ባመልጥ በቡጥጫ

ከጢስ የተቀመጠን፣ ልጅ አትንካው
- ድሃና እሳት ሲነካኩት አይወድም

ከጤፍ የደቀቀ፣ ከመርፌ የረቀቀ
- ጥልቀትና ርቀት ያለው ሐሳብ

ከጥላ ያረፈ፣ ከሞት የተረፈ
- ወደ ትልቅ ሰው የተጠጋ ጉዳት አያገኘውም

ከጥቅምት ማለዳ፣ ይሻላል የጊደር ዕዳ
- በጥቅምት አንድ አጥንት

ከጦጣ የዋለ ጉሬዛ፣ እህል ፈጅቶ ገባ
- ከእህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች

ከጨለመ ዱር፣ ከጉደጉደ ምድር
- ጊዜ አለ ጊዜ መጓጓዝ አደጋ አለው

ከጨረቃ የደመቀ፣ ከፀሐይ የሞቀ
- ጥርትና ፍንትው ያለ እውነት ወይም ሐቅ

ከጨርቅ ነጩ፣ ከቡሃ ልጩ
- ነጣ ያለ ነገር ለዐይን ያስደስታል

ከጫጩት ፊት፣ ፈንግል አይወራም
- መጥፎ ነገር በሰው ፊት አይሠራም

ከጭቅጭቁ ከንዝንዙ፣ የሌባ ገንዘብ ምነው ባይገዙ
- የሚመጣውን አስቸጋሪ ሁኔታ አስቀድሞ መገንዘብ ይጠቅማል

ከጮማ ብስና፣ ጎመን በጤና
- ከሚያጠግበኝ እስኪበርድ ይራበኝ

ከፈታኋት ሚስቴ የተወለዱ ሁሉም የኔ ናቸው
- ቀደም ሲል ከተወለዱት ልጆች አንጻር ዝምድናው ይታያል

ከፈጣሪ የወረደ፣ ለመሬት አልከበደ
- ሳያስችል አይሰጥም

ከፊት ተወጣ ጆሮ በኋላ፣ የወጣ ቀንድ በለጠው
- ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ

ከፍላት እጅ ጥልቅ መልቅቅ
- ጠብ ውስጥ ዘሎ መግባት ችግር ላይ ይጥላል

ከፍታቱ፣ መሻማቱ
- በግብዓተ መሬት ወቅት ሰው ዐፈር በመመለስ ይረባረባል

ከፍትፍቱ ፊቱ፣ ከጠላው ማቶቱ
- ፈገግታ ጥሩ ነው

ከጮከረ የጠረጠረ ይሻላል
- ያልጠረጠረ ተመነጠረ

ኩላሊት ያለሰውን፣ ልብ ያመላለሰውን፣ መርምሮ የሚያውቅ የለም
- በሰው ውስጥ የሚካሔደውን መርምሮ የሚያውቅ ፈጣሪ ብቻ ነው

ኩሩ ሰው አይሸሽም፣ አይዋሽም፣ ቢሸሽም አያመልጥም
- ራሱን የሚያከብር ሰው የሚያዋርድ ተግባር አይፈጽምም

ኩራት ለጉንደሬ እድር ለበጌምድር
- የጉንደር ሰው ራሱን ያኮራል

ኩራት እራት ነው
- እራስን ዝቅ ማድረግ አይገባም

ኩራትና ሀብት፣ አይገናኙ አንድነት
- ለመሥራት የሚጠየፍ ኩሩ ሰው ሀብታም ሊሆን አይችልም

ክብት፣ ለማይ ይከፍት
- ሀብት ካለ በሰማይ መንገድ አለ

ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል
- ምኞቱንና ፍላጐቱን ያልተናገረ ሊያገኝ የሚችለውን ያጣል

ካለ ሥራው፣ ምን አገባው
- በማያገባው መግባት ጥሩ አይደለም

ካለ ስንቅ መንገድ፣ ካለ ገንዘብ ንግድ
- መነሻ ነገር ሳይኖር አንድ ተግባር ለመፈጸም አይቻልም

ካለቀ መቆጠብ፣ ከመሸ መጠብጠብ
- ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ

ካለ ክርሞ ዶሮ፣ እንቁላል ለዘንድሮ
- ከፈረሱ ጋሪው ቀደመ

ካለጓደኛ መግፋት፣ ከንቱ ልፋት
- በሕብረት በአንድነት መቆም ብርታትን ያስገኛል

ካለፈ ወዲያ፣ ነገር ይቆጫል
- ላለፈ ነገር መቆጨት አይገባም

ካለ ፈጣሪ፣ ጨልጠሽ ጋግሪ
- በእግዛብሔር ተማመኝ

ካለፈ ጌትነት፣ የቆየ ድህነት
- ያለፈን ታሪክ ቢዋሩት ዋጋ የለውም

ካላረፉ፣ መከራ ነው ትርፉ
- ካላረፉ አደጋ ላይ መውደቅ ያመጣል

ካላስተዋሉ አይገኝ ሁሉ
- አስተዋይ መሆን ትልቅ ደረጃ ላይ ያደርሳል

ካላበበ አያፈራ፣ ካልለማ አያወራ
- የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል መኖርን ያረጋግጣል

ካላባት፣ ዶሮ በጓት
- ያለወጉ ያለ ደንቡ የሚፈጸም ተግባር

ካላወቁት መንፈስ ቅዱስ፣ ያወቁት ሰይጣን
- በቅርብ የሚያውቁት ይበልጥ ይቀርባል

ካላዋቂ ቤት፣ እንግዳ ይዋኝበታል
- በበጋ ሞኝ ቤት ተንጋጋ፣ በክረምት እቤትህ ተከተት



ካላዩም አይነድ፣ ካልሰሙ አይቆም
- አንድን ድርጊት ካላዩና ካልሰሙ ንዴትና ብስጭት አይኖርም

ካላዩ አያሳዩ
- ካላወቁ አያሳውቁ

ካላዩ አይቆጭ፣ ካልሰሙ አይበሳጩ
- ካላዩና ካልሰሙ ቁጭትና ብስጭት አይኖርም

ካልረባ አዝማሪ፣ ጥሬ ቃሚ ይሻላል
- ውጣ ውጣ ከሚሉት በሬ ዶማ ይሻላል

ካልረባ ጉልበት እዩልኝ ጦም ማደር
- ከማይጠቅም ስጦታ እጦት ይመረጣል

ካልረባ ጉበዝ ይሻላል ቀበሮ፣ ግልግል ያመጣል ተራራ ዞሮ
- አህያ ስባ ካልተበላ ምን ረባ

ካልሠሩ፣ አይገኝ መከሩ
- ካልሠራህ መብላት አትችልም

ካልሠሩ፣ አይገኝ ብሩ
- ካልሠራህ ገንዘብ ማግኘት አትችልም

ካልለጡ አይጸድቁ፣ ካልተማሩ አያውቁ
- ካላረሱ አይጉርሱ፣ ካልፈተሉ አይለብሱ

ካልቀመሱ፣ የደገመ ባስ
- ካልበላው የበላው ባሰበት

ካልበሉበት ደጃ ሰላም፣ ከበሉበት ቤት ነው
- ባይበሉበትም ሁሌ ለማሚበላበት እንደበሉበት ይቆጠራል

ካልተናገሩ፣ አይከብድም ነገሩ
- ዝም ማለት ነገርን ያበርዳል

ካልተዋጋሁ አልነግሥም አለ
- ጀግንነት ያማረው

ካልተረደ አይታይ ስባቱ፣ ካልተናገሩ አይገኝ ብልሃቱ
- የአንድን ሰው ማንነት ለማወቅ ቀረብ ካላሉ አይታወቅም

ካልታዘልኩ አላምንም አለች ሙሽራ
- ሁሌ እየተቃለለች በመቆየቷ መጠራጠሯን ለማመልከት

ካልታጣ ገበያ፣ ጓያ ሸመታ
- ሥራ ጠፍቶ ጢስ ይሞቃል

ካልቸኮሉ፣ ቀስ በቀስ ይገኛል ሁሉ
- ቀስ በቀስ እንቁላል በእግር ይሔዳል
- ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል

ካልቸኮሉ፣ እንቁላል ይሔዳል በእግሩ
- ሁሉም ነገር ጊዜውን ጠብቆ ይፈጸማል

ካልወደቀ አይሰበር፣ ካልሞተ አይቀበር
- ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለለ አይሰበሩ

ካልደፈረስ አይጠራም፣ ካልጠራ አይጠጣም
- በችግር ውስጥ ካልታለፈ መልካም ነገር ተመቻችቶ አይገኝም

ካልጠበቁ፣ አይጠይቁ
- አላገኝም ብለው ከገመቱ አትስምኑ

ካልጠየቁ አያውቁ፣ ካላወቁ እይጸድቁ
- ዕውቀት በመጠየቅና በመመራመር ይገኛል

ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሠበሩ
- ጥጋብ ለአደጋ ይዳርጋል

ካሕን ቢመንን፣ ከርስቱ ይስምን
- ለእግዜር ያደረ ጾም ጸሎት እንጂ ሥራ ለለማይሠራ ከራሱም ርስት ይለምናል

ካሕንና ሽምላ፣ ያልዘራውን ይበላ
- ካሕን ኃይማኖታዊ አገልግሎትን ለሕዝብ ስለሚሰጥ ሕዝብ ይመግበዋል

ካመት ልፋት፣ ያንድ ቀን ጥፋት
- የአንድ ቀን ስሕተት ብዙ ነገር ያበላሻል

ካመት በሽታ፣ ያንድ ቀን ድንጋጤ
- ያንድ ቀን ድንጋጤ ለሞት ይዳርጋል

ካማራሪ፣ አባራሪ ይሻላል
- ቁጭ ብሎ ምሬትን ከሚገልጽ የታገለ፣ የጣረ ያሸንፋል

ካምና ይሻላል ዘንድሮ
- የጊዜ መለዋወጥ መሻሻልን ሊያመጣ ይችላል

ካሚጋች አስታራቂ፣ ካጣቢ አድራቂ
- ነገሮችን ከማባባስ ስምምነት እንዲገኝ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል

ካረጁ መንገድ፣ ከመነኮሱ መውሰድ
- በስው ዘንድ ተቀባይነት የሌለውን ተግባር መፈጸም ውግዘትን ያስከትላል

ካረጁ፣ እንባር ይዋጅ
- ከጊዜና ከዕድሜ ጋር የማይሔድ ተግባር መፈጸም

ካረጁ አይበጁ
- ሁሉ ነገር ካለፈበት በኋላ ውበቱ ይደበዝዛል

ካረጁ ወዲያ ጉፈር፣ አዝመራ የሳተው ገበሬ
- ሁሉ ነገር ካስፈበት በኋላ ውበቱ ይደበዝዛል

ካረዘች ክታብ ያዘች፣ ፈሷን ፈስታ ቂጧን ያዘች
- ከተሳሳቱ በኋላ ጸጸት አይገባም ቀድሞ መጠንቀቅ ይገባል

ካራ ከስለቱ፣ ጨዋታ ከውነቱ
- ስለትያለው ካራ ለአንድ ተግባር እንደሚፈለግ እውነት ያለው ጨዋታም ተወዳጅ ነው

ካሥር ቡልኮ ይልቅ፣ ግማሽ እንጀራ
- መሠረታዊና ዋነኛ እንጀራ ነው



ካስተዋይ ይልቅ፣ ዕብድ በጤናው ይኖራል
- ዕብድና ዘበናይ የልቡን ይናገራል

ካበደው ያገረገረው ይበዛል
- ካበደው ወደ ዕብደት በመምጣት ላይ ያለው ይበዛል

ካባቱ የተረፈ ተከሸፈ
- ሌላ ሌላው በአጋጣሚ የቀረ ነው

ካባት ልጅ አይበልጡ፣ ከሞት አያመልጡ
- የማይቀር ዕዳ ነው

ካብታም ካብታም፣ አንተ ለኔ አንተ ለኔ፣ ይባባሉ ምነው
- ሀብታም ለሀብታም ይሟሟቁ ድሃ ለድሃ ይስቃቀሱ

ካብነት ሁሉ ኮሶ፣ ለቤት መቆሚያ ምሰሶ
- ኮሶ ይመራል ሆኖም ሆድ ያጠራል

ካብ እይገባ ድንጋይ
- አገልግሎት የማይሰጥ የማይረባ

ካነጋገር ይፈረዳል፣ ካያያዝ ይቀደዳል
- የነገርን ውል ውሉንና አካሔዱን የሚያውቅ ያሸንፋል

ካንበሳ መንጋጋ፣ ማን ያወጣል ሥጋ
- ኃይለኛ ነው አይዳፈርም

ካንበሳ ቤት፣ አጥንት አይጠፋም
- አንበሳ ጾሙን አያድርም

ካንተ አፍ ወሬ፣ ከዝንጀሮ አፍ ጥሬ
- አንተ ወሬ አታጣም

ካንቺ የተሻለች ቤት ባላገኝ፣ ሌላ እንዳታገቢ ጠብቂኝ
- ባጣ ቆየኝ

ካንገት ነው ካንገት
- ከልብ ነው ወይስ ለይስሙላ

ካንገት ካለቀሱ፣ እንባ አይገድም
- ካሰቡበት አንዳች ተግባር ለመፈጸም የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም

ካንድ ልጃገረድ፣ ይገኛል ሁለት ዘመድ
- ልጆቿና እሷ እራሷ

ካንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ
- መተባበር አንድነት ኃይል ነው

ካንገት በላይ ፍቅር፣ እያደር ያቃቅር
- ካልተማመኑ መጣላት አይቀርም

ካዋቂ ጠራቂ፣ ካጣቢ አድራቂ፣ ከሒያጅ ጠያቂ
- ከመጀመሪያው ሁለተኛው ብርቱ ሆኖ የሚታይበት ሁኔታ

ካዋቂ፣ ጠያቂ
- ካዋቂ ነኝ ባይ ጠያቂ ብዙ ነገር ጠይቆ ያውቃል

ካይን የፈጠነ ከውኃ የቀጠነ
- በጣም ቅጽበታዊ ፍጥነት ያለው

ካይጥ ሸሽቶ ከባብ፣ ከቤት ወጥቶ ከጠብ
- ከድጡ ወደ ማጡ

ካይጥ ቤት ብቅል፣ ከውሻ ቤት ጠፍር
- የማይሆንና የማይታመን ነገር

ካገለገለ ያውደለደለ፣ ካማከረ ያገለለ
- ከሠራው ሰው ያልሠራው አገኘ

ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢሰጉሙት ፈረስ
- ሁሉን እሺ ብሎ መሥራት አለበት

ካገር ሆድ ይሰፋል
- ትዕግስት ጥሩ ነው

ካገር ደጋ፣ ከመኝታ አልጋ፣ ታላቅ ጸጋ
- ደግ ለኑሮ አመቺ ነው ይስማማል

ካጉል ብልሃት፣ እርሶ መብላት
- እርሶ መብላት ትልቅ ሙያ ነው

ካጣቢ ሳሙና፣ ከምግባር ትህትና
- ትህትና የሌለው ሰው ከመልካም ሰው ጋር አይኖርም

ካጤ ቃል በላይ ዐወቅ ዋና አታላይ
- ከንጉሡ ቃል ውሳኔ በላይ ምንም ሊኖር አይችልም

ካጨደ፣ የሰበሰበ
- የጀመሩትን መጨረስ ተገቢ ነው

ካፈር በላይ ተንጋሉ፣ ድሃን ማን ተቀብሉ
- ጥሩ ውኃ የጥቅምት ነበርሽ ማን ቢጠጣሽ ጥሩ ምክር የድኃ ነበርሽ ማን ቢሰማሽ

ካፋፍ ላይ ነፋስ፣ ካፍ ላይ አስትንፋስ አይቋረጥም
- ለሕይወት እስካለ ድረስ መተንፈስ አይቀርም

ካፍ ከወጣ አፋፍ
- አንዴ ከተናገሩ ወዲያ የተናገሩት ንግግሩ ብዙ ርቆ ይሔዳል

ካፍ ወለምታ፣ የእግር ወለምት ይሻላል
- የእግር ወለምታ ትሽቶ ይድናል፣ ሳት ብሰው የተናገሩት ንግግር አጉል ነው

ካፍ የወጣ ቃል፣ ከእጅ የወደቀ እንቁላል
- ከአፍ የወጣ ቃል መመለሻ የለውም

ካፍ የወጣ፣ ከልብ የመጣ
- ልብ ያሰበውን ነው አፍ የሚናገረው

ካፍ የወጣ፣ ከጥርስ የነጣ
- አንዴ ካፍ የወጣ ንግግርን መመለስ አይቻልም

ካፍሽ እርጉልሽ፣ አይገባ ሆድሽ
- የማይጠቅም ነገር ማድረግ ተገቢ አይደለም

ክረምትና በጋ ቆላና ደጋ
- አንዱ ካንዱ የማይገናኝ



ክረምትና ወሳድ፣ ሲጠሉት ያከብራል
- የጠሉትም አንዳንዴ ይጠቅማል

ክረምትን የፈጀ በጋ፣ ዕዳውን የፈጀ ዜጋ
- ዕዳውን ከፍሎ የጨረሰ ሰው አይናቅም አይዋረድም

ክረምት እንደ ግርግዳ፣ በጋ እንደ ተራዳ
- ሁለቱ በኅብረት ለሰው ልጅ የሚጠቅመውን ያስገኛሉ

ክረምት ከጭቃ፣ በጋ ከግሜ
- መልካሙ ነገር የሚገኘው አስቸጋሪውን ጊዜ ችለው ሲያልፉ ብቻ ነው

ክርስትናም እነሳለሁ፣ ስንደዶና ወስፌ
- በጣም ይስማማሉ

ክርና ነገር ባጭር
- ነገር ከማንዛዛት በአጭሩ ማስረዳት ጥሩ ነው

ክበድ ላም ያለው ጥርሽ ያንቀው
- የነገው ተስፋ ለዛሬ አይሆንም

ክብረት ከሥምረት፣ ነፃነት ከአንድነት
- ነፃነት በአንድነት በኅብረት ይደምቃል

ክንፉ የተሰበረ አሞራ፣ ክሥሩ የተነቀለ ወይራ
- አሞራውም አይበር ወይራውም አያቀጥልም

ክንፍ የሌለው አሞራ፣ ቀንድ የሌለው አውራ
- አሞራውም አሞራ አውራውም አውራ አይደለም

ክዶ ከመሟገት፣ አምኖ መረታት
- እውነቱን ተናግሮ እመሸበት ያድራል

ክፉ ለመናገር፣ ቂጣ ለመጋገር
- ክፉ ቢናገሩት ጠቀሜታ አይኖረውም

ክፉ ሎሌ፣ ከሰው ፊት ያሳፍራል
- ሥርዓት የሌለው በሰው ፊት ያልተገባ ተግባር ይፈጽማል

ክፉ መልስ፣ ያስብራል ራስ
- ክፉ ንግግር ለጠብ ይጋብዛል

ክፉ ሰው፣ ለክፉ ቀን ይሆናል
- ምንም ቢሆን ሰው የሚኖረው ከሰው ነው

ክፉ ሰው፣ በከንፈሩ ያስቅሳል
- አጉል አዛኝ ቅቤ ጠባሽ

ክፉ ሰውን ከመሬት፣ በግን ከበረት
- ንብረትህን እንዳይወስዱብህ በሚጠበቅበት ቦታ አኑር

ክፉ ሰው ከፍቶ ያስከፋል፣ አተላ ያስተፋል
- ክፉ ሰው ሌላውን መልካሙን ሰው አጉል ባህርይ ያስተምረዋል

ክፉ ቤት፣ ጧት ወተት ማታ ፊት
- የክፉ ሰዎች ባህሪያቸው ተለዋዋጭ ነው

ክፉ ቀን አይምጣ ዘመድ እንዳላጣ
- ክፉ ቀን ሲመጣ ዘመድ የነበረው ሁሉ ይሸሻል

ክፉ በሬ፣ ያስቸግራል ለገበሬ
- እርሻን የማያውቅ ያልተገራ በሬ ገበሬን ያስቸግራል

ክፉ በትር፣ ነው ትርፉ
- አንዴ ጠባዩ የተበላሸን ሰው በቅጣት አስተካክላለሁ ማለት ከንቱ ልፋት ነው

ክፉ ነገር ከከርስ፣ ክፉ ሥጋ ከጥርስ
- ክፉ ንግግር ምንጊዜም ከሆድ አይወጣም

ክፉ አይረሱም፣ አይነሱም
- ክፉ ንግግር ልርሳህ ቢሉትም አይረሳም፣ ለክፉ የሚገባውን አይነሱትም

ክፉን እስከ ክንፉ
- ክፉን ከነምናምኑ ወዲያ ማራቅ ነው

ክፉ አሽከር እሰው ቤት ሲደርስ፣ ወደ ኋላ ይቀራል
- አሽከርነቱን ላለማሳወቅ ከኋላ ኋላ አይከተልም

ክፉ አሽከር፣ ከመንደር ይቀራል
- ከኋላ ኋላ ተከትሎ አሽከርነቱ እንዳይታወቅ ወደ ኋላ ይቀራል

ክፉ አውሬ አይለምድ፣ ከለመደም አይውለድ
- ክፉ ሰው ያንኑ ክፋቱን አይተውም

ክፉ እንደ አፉ፣ ዛፍ እንደ ቅርንጫፉ
- እባብን በእንጭጩ

ክፉ ከማድረጋቸው፣ ክፉ ማስለመዳቸው
- እነሱ ከፈጸሙት ይልቅ ሌሎችን በዚህ ተግባር ላይ ማሠማራታቸው ተገቢ አይደለም

ክፉ የከፉ ዕለት ቢስ የባስለት
- ክፉ ሰው በክፉ ቀን የባሰ ክፉና አስቸጋሪ ይሆናል

ክፉ ያከፋል፣ ጉሽ ያስገሳል
- ክፉ ሰው ሌላውንም እንደክፉ ያደርጋል

ክፉ ይነካል፣ በክንፉ
- ክፉ ሰው ሳትደርስበት ይደርስብሃል

ክፉ ጌታ፣ ከዳገት ያስግራል
- ተከታዩ፣ አሽከሩ እሥር እሥሩ እየሮጠ ላቡን እንዲጨርስ ለማድረግ

ክፉ ጉረቤት፣ ዶሮና ፍየል ያረባል
- ዶሮና ፍየል የጉረቤትን ሰጥና አትክልት በመብላት ችግር ውስጥ ይጥሉታል

ከፋት የሌለበት፣ የለም ኃጢአት
- ማንኛውም ህብት ያለ አንዳች ኃጢአት የተገኘ አይደለም

ኮሶ ላልቀመሰው፣ ይመር አይመስለው
- ችግርን ላልቀመሰው ስለችግር ቢወራለት ችግር ምን እንደሆን አያውቀውም

ኮስ ላፍ ይመራል፣ በኋላ ጠላት ይገድላል
- የጠሉት ነገር አንዳንዴ ለችግርህ ጊዜ ጠቃሚ የሚሆንበት ወቅት አለ

ኮሶ ሲጠጣ ስቅጥጥ፣ ወተት ሲጠጣ ሽምጥጥ
- ከባድ ሥራ ሲመጣ ስለሚከብድ መሸሽ ቀለል ያለና ጥቅም የሚገኝበት ሲሆን መጣደፍ

ኮሶ ሳይመር አያሽር
- ካለፋ፣ ካልደከሙ ውጤት አይገኝም

ኮሶ በኮሶ ይሞታል
- አሾህን በሾህ

ኳደር በንጉሥ፣ መበለት በቄስ መቅናት አይቻልም
- ሰው በማይችለውና በሌለው ሙያ መቅናት ምን ትርፍ ይኖረዋል



## መልመጃ 10 /ከ/

ሀ. **የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሟሉትን ምረጡላቸው**

1. ካፍ የወጣ ቃል ______
   - ሀ. በነቀርሳ ላይ ሳል
   - ለ. የሞተን ሰው መቀበል
   - ሐ. ክሩ የተበጠሰ አምፓል
   - መ. ከእጅ የወደቀ እንቁላል
2. ከመፈቅፈቅ ______
   - ሀ. ቀስ ብሎ መንስቅስቅ
   - ለ. ማለቅለቅ
   - ሐ. መነቅነቅ
   - መ. ቀስ ብሎ ማስለቀቅ
3. ክፉ ጉረቤት ______
   - ሀ. ዶሮና ፍየል ያረባል
   - ለ. ውሻና ድመት ያረባል
   - ሐ. ላምና በሬ ያረባል
   - መ. ብዙ ልጆች ይመልዳል
4. ከጅ ጉፈሬያም ______
   - ሀ. የውሻ መላጣ ይሻላል
   - ለ. ያንበሳ መላጣ ይሻላል
   - ሐ. የውሻ ጉፈሪያም ይበልጣል
   - መ. ያንበሳ ጉፈሪያም ይሻላል
5. ከወጡ የለሽ ከጠላው የለሽ፣ ከእንጀራው የለሽ ______
   - ሀ. በለጠች ለ. አማረች ሐ. በላይነሽ መ. አልማዝ
6. ከስብ ______ ይሽታል
   - ሀ. መቅኒ ለ. ጉፉያ ሐ. ስም መ. ስም
7. ______ አላምንም አለች መሽራ
   - ሀ. ካላገባሁ
   - ለ. ካልታዘልኩ
   - ሐ. መቀነቴን ካልፈታሁ
   - መ. ካልተዳርኩ
8. ከማር መሃል የበቀለ ጤፍ ______
   - ሀ. ወፍ ዘራሽ
   - ለ. ሳይታጨድ ይረግፍ
   - ሐ. ከመኖነት አያልፍ
   - መ. አራሙቻ ነው
9. ከመልካም ሽቶ ______
   - ሀ. መልካም ስም ይሻላል
   - ለ. መልካም ሀብት ይሻላል
   - ሐ. መልካም ሥራ ይሻላል
   - መ. መልካም ታሪክ ይሻላል
10. ክረምትና ወላድ ______
    - ሀ. ሰው አይወደው
    - ለ. ይሔዳል በመንገድ
    - ሐ. ሲጠሉት ያከብራል
    - መ. መልሱ የለም
11. ከመሞት ______
    - ሀ. መስንበት ለ. ማስለቀስ ሐ. ማልቀስ መ. ማባረር

12. ካፍ ከወጣ ________
ሀ. አፋፍ ሐ. ወሬ አለቀ
ለ. ነገር አመጣ መ. መልሱ የለም

13. ኮሶ ሲጠጣ ስቅጥጥ ________
ሀ. ወተት ሲጠጣ ሽምጥጥ ሐ. ቅራሪ ሲጠጣ ሽምጥጥ
ለ. ጠላ ሲጠጣ ሽምጥጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

14. ከፍትፍቱ ________
ሀ. ፊማው ሐ. ገንዘቡን
ለ. ፊቱ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

15. ከዝንጀሮ ቆንጆ ________
ሀ. ይሻላል ጦጣ ሐ. ምን ይመርጧል
ለ. መሯሯጡ መ. መልሱ የለም

16. ላፍ ይመራል ________
ሀ. ተማሪ ትምህርቱን ይማራል
ለ. ገበሬው እርሻውን ያርሳል
ሐ. በኋላ ጠላት ይገድላል
መ. ጎረምሳ ትግል ይገጥማል

17. ካገር ________
ሀ. ተፋቀር ሐ. ከወጡ አፋፍ
ለ. ሆድ ይሰፋል መ. ተማከር

18. ኩራት ________
ሀ. እራት ነው ሐ. ምሳ ነው
ለ. ያስጠላል መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

19. ከእጅ አይሻል________
ሀ. ድንጋይ ለ. ጋሻ ሐ. አካፋ መ. ዱማ

20. ከጦጣ የዋለ ጉሬዛ ________
ሀ. ፈስ ተምሮ መጣ ሐ. ዝላይ ይወዳል
ለ. እህል ፈጅቶ ገባ መ. መልሱ የለም

21. ከባለቤቱ ያወቀ ________
ሀ. ሌባ ነው ሐ. ቡዳ ነው
ለ. የጩዋ ልጅ ነው መ. ጠንቋይ ነው



22. ከተራብ ________
ሀ. አዝናስሁ ስጠገበ ሐ. ይበሏል
ለ. ስተራቆተ መ. ይከሷል

23. ከሞተች ሚስቴ ________
ሀ. ምን አሰኝ ከእቷ ሐ. ምን አሰኝ ካጉቷ
ለ. ምን አሰኝ ካማቴ መ. መልሱ የሰም

24. ከሰቼ ቢያዩኝ ________
ሀ. ጅማት ስመኑኝ ሐ. ልሸከምህ አሉኝ
ለ. ናቁኝ መ. ገላመጡኝ

25. ከቀዳዳ ________
ሀ. አይገኝም ዕዳ ሐ. ይሻላል ጨምዳዳ
ለ. ይሻላል ከርዳዳ መ. መልሱ የሰም

26. ከቁንጭ ________
ሀ. ሌጦ ያወጣል ሐ. መላላጫ
ለ. ይሻላል ጉንዳን መ. መልሱ የሰም

27. ክርና ነገር ________
ሀ. ይሻላል መዋደድ ሐ. አትዋደድ
ለ. የቅርብ ዘመድ መ. ባጭር

28. ከመጠምጠም ________
ሀ. ማውሰቅ ሐ. መከናነብ
ለ. መማር ይቅደም መ. መልሱ የለም

29. ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ________
ሀ. ሽሮ አበድሪኝ ሐ. ሰው ይመስክር
ለ. እንወራረድ መ. አትወዳደሪኝ

30. ከአብሮ አደግህ ________
ሀ. እብረህ ኑር ሐ. አብረህ አትሰደድ
ለ. እትከራከር መ. አትማከር

31. ከእባብ እንቁላል________
ሀ. ዳክዬ አይፈለፈልም ሐ. እባብ ይፈለፈላል
ለ. ዶሮ አይፈስፈልም መ. ርግብ አይፈስፈልም

32. ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ________
ሀ. ሰሰው ጉድጓድ ይምስ ሐ. ዝምታ ያበዟል
ለ. ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ መ. ሆድ ይብሰዋል

33. ኮሶ በኮሶ ________
ሀ. ይሞታል ለ. ተኮስ ሐ. ይወገራል መ. ይሻላል

34. ከባቄላ ________
ሀ. ይሻላል ዲቃላ ሐ. አይጠሩም ዲቃላ
ለ. የሽንብራ ቆሎ ይሻላል መ. መልሱ የሰም

35. ከማያውቀት መላከ ________
ሀ. የሚያውቁት መላክ ይሻላል
ለ. የማያውቁት ሰይጣን ይሻላል
ሐ. የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል
መ. መልሱ የለም

36. ከሥጋ ብስና ________
ሀ. ይሻላል ጉብዝና
ለ. ይሻላል ቡና
ሐ. አይገኝ ጤና
መ. ጉመን በጤና

37. ከልጅ ልጅ ቢለዩ ________
ሀ. ዓመትም አይቆዩ
ለ. ጉረቤት ይለዩ
ሐ. እስከ ሐሙስ አይቆዩ
መ. መልሱ የለም

38. ከሰው ምቀኛ ይሻላል ________
ሀ. የቀበሮ መርዘኛ
ለ. የእባብ መርዘኛ
ሐ. የጦጣ መርዘኛ
መ. ሁሉም መልስ ነው

39. ከሰው መልካም ገበሬ፣ ከእህል መልካም ________
ሀ. ባቄላ ለ. ስንዴ ሐ. ጥሬ መ. ሁሉም መልስ ነው

40. ከሰው እንደ ረሀይት፣ ከዛፍ እንደ ________
ሀ. ቱሩማንቱሪ ለ. ጥድ ሐ. ግራር መ. በቀልት

41. ከሰው ከፉ ደብተራ ካውሬ ከፉ ________
ሀ. ዳሞትራ ለ. አንበሳ ሐ. ነብር መ. መልሱ የለም

42. ከሰው ፊት አይበሉ ________ አይበድሉ
ሀ. ልጅን ለ. የእንጀራን ልጅ ሐ. ሥጋን መ. ራስን

43. ከሰጭው ________
ሀ. ለማኙ ለ. አበሳሹ ሐ. አሳጭው መ. አምጭው

44. ከሳሽና ተከሳሽ________
ሀ. አበላሽ ለ. ተተናኳሽ ሐ. ይካካስ መ. የመረጠን ያሽ

45. ከሴት ነገር ________ መንበር አይታጣም።
ሀ. ከቄስ ለ. ከዳቆን ሐ. ከበቅሎ መ. መልሉ የለም

46. ከሽንጉ ቢረታ________ ከቤት መታ።
ሀ. ልጁን ለ. የእንጀራ ልጁን ሐ. ዘመዱን መ. ሚስቱ

47. ከሺህ በቅሎኛ ________
ሀ. አንድ እግረኛ
ለ. ሺህ እግረኛ
ሐ. አንድ ፈረስኛ
መ. መልሱ የለም

48. ከሺህ አብራሪ ________
ሀ. አንድ መካሪ
ለ. አንድ አሽከርካሪ
ሐ. አንድ ደባሪ
መ. አንድ አምራሪ

49. ከሺህ ደብተራ ________
ሀ. አንድ ቄስ መንኳላ
ለ. የቄስ ዳንኪራ
ሐ. የዲያቆን ዳንኪራ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

50. ከሺህ ሎሌ ________
ሀ. አንድ ዶማ
ለ. አንድ ትራክተር
ሐ. አንድ በሬ
መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ



## መልመጃ 10 /ከ/

ለ. **ለሚከተሉት ምሳሊያዊ አነጋገሮች ፍቺ የሚሆኑትን ምረጡ**

1. ከድሃ ቤት ጉመን ሲቀቀል ከበሮ ይመታል
ሀ. ድሃ ጉመን ሲበላ ከበሮ ይመታል
ለ. በድሃ ቤት ሁሉ ነገር ብርቅ ነው
ሐ. በድሃ ቤት ሁል ጊዜ ጉመን ይገኛል
መ. ድሃ ጉመን መቀቀል ይችላል

2. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል
ሀ. ድሃ ጉመን ሲበላ ከበሮ ይመታል
ለ. ሞኝ ሀብቱን አይጠብቅም
ሐ. ሞኝ ሞፈር መቁረጥ አያውቅም
መ. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይገኛል

3. ክስር ያለው ቢነግድ አያተርፈው
ሀ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
ለ. ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል
ሐ. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
መ. የቾኮለ አፍሶ ለቀመ

4. ከኑግ የተገኘህ ሰሊጎ አብረህ ተወቀጥ
ሀ. ተማክረው የፈሱት አይገማም
ለ. በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ
ሐ. የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ
መ. ተመሳሳዩ ለምርጫ አልቀረበም

5. ከእንጀራው የሰሽ ከወጡ የለሽ ከጠላው የሰሽ እንዲያው ባላይ ነሽ
ሀ. በጦሩ ቅበጥ በጠላው ቋጭ
ለ. መልከ ጥፉን በለም ይደግፉ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሉ የለም

6. ከእጅ አይሻል ዶማ
ሀ. የእህያ ባል ከጅብ አያስጥልም
ለ. የማያድን ጋሻ ጉን ይሰብራል
ሐ. አገባሻለሁ ያለሽ ላያገባሽ፣ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
መ. ሁሉም መልስ ነው

7. ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ
ሀ. የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ
ለ. የቡና ስባቱ መፋጀቱ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

8 ከዳቦ የተገኘ ወጥ አብረህ ግመጥ
ሀ. የእህያ ባል ከጅብ አያስጥልም
ለ. የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ
ሐ. ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ
መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

9. ከሞት ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ
   ሀ. ድብ ከሔደ ውሻ ጮኸ
   ለ. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. መልሱ የለም
10. ከእሾህ ወጥቶ ወደ ጋሬጣ
   ሀ. ከኸርብ ጉሬ ወጥቶ ወደ ኸርብ ዋሻ
   ለ. እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ
   ሐ. ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራል
   መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

## መልመጃ 10 /ከ/

ሐ. የማተሉትን ምሳሊያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. ከቆረሰ የጉረሰ | ሀ. ለውሻ ገለባ ለበሬ ወለባ |
| 2. ካላዩ እይነዱ፣ ካልሰሙ አይቆጭ | ለ. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው |
| 3. ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሰበሩ | ሐ. ያላዩት አገር አይናፍቅም |
| 4. ካላባት ዶሮ በእንት | መ. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም |
| 5. ከዘሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር | ሠ. ካጨደ የሰበሰበ |
| 6. ከሰር ያለው ቢነግድ አያተርፈው | ረ. የሰው ጨርቅ አያደምቅ |
| 7. ከሰው ለሰላሳ የራስ ከርካሳ | |
| 8. ካልታረደ አይታይ ሰባቱ፣ ካልተናገረ አይታወቅ ብልሃቱ | ሠ. ካጨደ የሰበሰበ |
| 9. ከሆዱ ላይ ቂስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም | ሰ. መንፈራገጥ ለመላላጥ |
| 10. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው | ሸ. የሆድ ብልሃት የጋን መብራት |
| 11. ከከፉ ባለዕዳ የጉመን ዘር ተቀበል | ቀ. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል |
| 12. ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ | በ. ራት የሌለው ቄስ እንደልቡ አይቀድስ |
| 13. ከሰቀላ ወደ ጥላ | ተ. ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ |
| 14. ከሞት በኋላ መድኃኒቱ ከፈጁ በኋላ አቤት አቤት | ቸ. ከነገሩ ጦመ እደሩ |
| 15. ከሞት ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ | ኀ. ከርሞ ጥጃ |



## ወ

ወለባ ለሹሩባ
- ተስማሚ አብሮ ሲሔድ የሚችል

ወልደው ሳያበቁ በለው ልጅ አይሥቁ
- የራስን የወደፊቱን ምን እንደሚሆን ስለማታወቅ መሣቅ አይገባህም

ወልደውት ያላሳረፈ ነግዶ ያላተረፈ
- ለቤተሰቡ ያላገለገለ ልጅ ልጅ አይባልም

ወልዶ አይሳምለት ተናግሮ እይሣቅለት
- ምንም አስደሳች የሆነ ነገር የለውም

ወልዶ አይሰም ዘርቶ አይቅም የለም
- ሥራ ካልሠሩ ምንም አይገኝም

ወልዶ አይሰም ዘርቶ አይከምር የለም
- ሥራ ከሠራህ ውጤታማ ያደርጋል

ወልጄ አልላኩ መንኩሼ አልጸደኩ
- ብዙ ብለፋም አልተሳካላኝም

ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ዋግ የመታው ሥንዴ
- የተቸገረ ሰው ከድንጋጤው ከሁኔታው ያስታውቃል

ወራሽ የሌለው ባለጸጋ ፍራሽ የሌለው አልጋ
- ወራሽ የሌለው ሀብታም ምንም ደስታ የለውም

ወራት ይገፋል ባቄላ ጠላት ያጠፋል ዲቃላ
- የተናቀ የሚያገለግልበት ወቅት አለው

ወራጅ ውኃ አይውሰድህ ሟች ሽማግሌ አይርገምህ
- ልታሳልፈው የሚገባህን ነገር ተጠንቅቀህ እሳልፍ

ወሬ ለጠያቂ ገበጣ ላዋቂ
- ወሬ የሚገኘው የወሬ ሱሰ ካለበት ሰው ነው

ወሬ ሲነግሩህ መላ ጨምር
- ወሬ ሲነግሩህ ለምን? እንዴት? ብለህ ማስረጃ መኖሩን አረጋግጥ

ወሬ ቢያምርህ በየሎሌህ
- ወሬ የሚገኘው ከበታች ሠራተኞች ነው

ወሬ ብነግርህ በምስጢር መላ ጨምር
- መነሻ ምክንያቱን ለመገመት ሞክር

ወሬ ታሽቶ አይቆረጥም ነገር ተዘግኖ አይቃም
- ለወሬ የለውም ፍሬ ይልቁኑ መሥራት ይበጃል

ወሬን ከባላገር ጦርነትን ከወታደር
- ወሬ ቢያምርህ በየሎሌህ

ወሬኛ ሚስት ዘርዛራ ወንፊት
- ሚስት ወሬኛ ከሆነች ምስጢር ስለማትደብቅ ለትዳር አትሆንም

ወርቁ ቢጠፋ ሚዛኑ አይጠፋ
- ምን ቢሆን እውነት ሙታ አትሞትም

ወርቁን በሚዛን እህሉን በላዳን
- ሁሉም ነገር መለኪያ ይኖረዋል

ወርቁ ከዳተኛ ፊት ይቅረብ መጽሐፍ ከቄሱ ፊት ይነበብ
- ስለመጽሐፍ ቃል የሚያውቁት ቄሱ ስለሆኑ ነገርን ወደሚመለከተው

ወርቅ ላበደረ ጠጠር እህል ላበደረ ዐፈር
- ጥሩ ነገር ለሰራልህ ክፉ ነገር ማድረግ

ወርቅ ላንጣሪ በቅሎ ለሰጋሪ
- ሁሉ ነገር ለባለሙያው ለባለቤቱ

ወርቅ በእሳት መሬት በጣት
- ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ሥራ ላይ እንደሚውል መሬትም ታርሶ ምርት ይታፈስበታል

ወርቅ በእሳት ይፈተናል
- የሰው ልጅም በመከራ ይተፈተናል

ወርቅና ሰም ፊትልና ሰም
- ፍጹም የተባበረ

ወርቅና ጨዋ አስታራቂ ነው
- ምንም ቢሆን ገንዘብ አስማሚ አስታራቂ ነው

ወርቅን ለማግኘት ወርቅ ይዞ መነሳት
- ጥሩ ለማግኘት ጥሩ ዕቅድ ይዘህ መቅረብ

ወርቅ የያዘ ሳጥን በወርቅ አይበለጥም
- ምስጢር ባደባባይ አይነገርም

ወርቅ ያለው ቀበዝባዛ እህል ያለው ፈርዛዛ
- ወርቅ ወይም ብዙ ገንዘብ ያለው ሰው ብዙ ሲጨነቅ ብዙ እህል ያለው ግን የተረጋጋ ነው

ወርቅ ይረክሳል መዳብ ይነሳሳል
- መልካም ነገር በሚረክስበት ጊዜ የተናቀው ከፍ ከፍ ይላል

ወርች አላልፎ ገራፊ ዳኛ ካለ ዘራፊ
- ለሕግና ለደንብ ተገዢ ያልሆነ እብሪተኛ

ወርች የረገጠው አግር አይሰተው
- ተመጣጣኝ ርቀት ላይ ያለ ወይም በእኩልነት ያለ

ወርውረው ቢሰቱት ያልጉዱት ይመስለዋል
- ቢሆንስ ኖሮ ብሎ የማይገምት ገልቱ

ወስፌ ሲሰግም ቅቤ አይወጋም
- ያለፍላጐት የሚደረግ ነገር የለም

ወተት ለእንቦሳ ሥጋ ለአንበሳ
- ሁሉም የሚስማማውን ይመርጣል

ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ቅቤ ተበድሮ ላቁማዳ
- የተበደሩትን ነገር ለቁም ነገርህ ላይ ብቻ አውል

ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ፈረስ ተበድሮ ለሜዳ
- የተበደሩትን ነገር ለቁም ነገርህ ብቻ አውል



ወተት ጠጥቶ ጠላ አግዜር ሲጣላ ጠላ ጠጥቶ ወተት የእግዜር ስጦታ
- ማን ከማን ጋር አብሮ ሲሔድ የሚችለውን ለይቶና አጥንቶ አለማወቅ

ወተቷንም አለቀ ጥጃዬም አይከሳ
- ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት

ወታደር ሲያረጅ አቃቢ ይሆናል
- ዘማዊት ስታረጅ አቃጣሪ ትሆናለች

ወታደር ሲደኸይ ጃኖ ያዘወትራል
- ታላቅና የተከበረ መስሎ ለመታየት

ወታደር ቢሰድብ ባላገር ይካስ
- እሱው በድሎ እሱው ተካሽ መሆን የጨቋኝ ባሕሪ

ወታደር ባለቃው ባላገር በጭቃው
- ሁሉም እንደያለበት ሙያና በታ ኃላፊ ይኖረዋል

ወታደር ዋቶ አደር
- ወታደር ለፍቶ ደክሞ አደር ነው

ወንዝ ለወንዝ መቀደስ ያረፈ ሰይጣን ለመቀስቀስ
- አላስፈላጊ ነገር አለቦታው አትፈጽም

ወንዝ ለወንዝ ሩዋጭ የሰው በግ አራጅ
- ይቺ ተፍ ተፍ የማንን ጭብጦ ለመመንተፍ

ወንድ ሲበላ የሴት ሌባ
- ለሌላው ሌላው መጨነቅ

ወንድ ልጅ በበላበት አንበሳ በሰበረበት
- ወንድን ሆዱ ያታልለዋል

ወንድ ልጅ በተሾመበት ሴት ልጅ ባገባችበት
- ሁሉም ጥቅም ወዳገኘበት ያደላል

ወንድ ልጅ አንዱ እንደአባቱ አንዱ እንደእናቱ
- ወንድ አንዳንዱ ያሸንፋል አንዳንዱ ይሸነፋል

ወንድም ለግርግርታ ጋሻ ለመከታ
- ወንድም መመኪያ ነው

ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው
- ወንድም መመኪያ ነው

ወንድምን አስቀይሞ ከመጾም ይሻላል ሥጋን መከምከም
- ከሥጋ ከወተት ከመጾም ከክፉ ንግግር መቆጠብ

ወንድም ወንድሙን አይበልጠው ምላጭ ምላጭን አይቆርጠው
- ሁሉም እኩል ነው

ወንድ ባለ በዕለቱ ሴት ባለች በዓመቱ
- ውሳኔ ሰጪው ወንድ ነው

ወንድ ተወልዶ ካልሆነ እንደአባቱ አመልማሎ ይስጡት ይፍተል እንደእናቱ
- ልጅ እንደአባቱ ጉብዝ ጀግና መሆን አለበት

ወንድና ወደል አህያ አንድ ነው
- ወንድ ያያትን ሴት ሁሉ ይመኛል

ወንድ እንደያዙት ነው
- አያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል

ወንድ ከዋለበት ከብት ከተሰማራበት
- መልካም ሰፍራ መዋል ከፈለክ እነዚህ ቦታዎች መልካም ናቸው

ወንድ የሞተበት ወንድ አይሻገርበት
- አንድ ዓላማ በከሸፈበት ተመሳሳይ ዓላማ ይዞ መነሳት አስቸጋሪ ይሆናል

ወንጭፉ ባልነበረ የማሽላ አሽት ደግ ነበር አለች ወፍ
- አደጋው ያስፈራል እንጂ ጥሩ ነበር

ወዛም ይገማል ቢሰው የነጭ ወሬ ነው እሱ
- ጠላት ይቀባል ጥላት

ወየው ጉድ ስኳርና ብርጉድ
- አንዱ ለጣዕም አንዱ ለሽታ

ወየው ጉድ አይገርምም ጅል ሰው አያሳዝንም
- ለጅል ማንም ግድ የለውም

ወየው ጉድ ያሰቡት አይገድ
- የሚያስቡት አይጠፋም

ወይ ልጅ በማን እጅ
- ልረዳህ ፈልጌ ነበር እንዴት ልርዳህ

ወይ መሮጫ ሜዳ ወይ መውጫ ቀዳዳ
- ግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ መጨነቅ

ወይም አጥፍቶ ይርቋል ወይም አንድዶ ይሞቃል
- ከሁለት አንዱ የሚበጀውን መምረጥ ይገባል

ወይ ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ
- አንዴ የሆነው ሆኗል

ወይ ባይ እንደጠሪው ነው
- ተጠሪው በጠሪው ዓይነትና ሁኔታ ምላሽ ይሰጣል

ወይ ተሸከመኝ ወይ ግፋ ለደገፋ
- ከሁለት አንዱ የሚሻልህን ምረጥ

ወይኖን ግረፈው ለቡሌ እንዲሰማው
- አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

ወይኖ አረሰው ወይኖ ጐረሰው
- ሲሠሩ አገልጋይ መስለው ሲበሉ ጌታ መስለው

ወይ አለማወቅሽ መራቁ አገርሽ
- ከዘመድ ጋር ተቀራርቦ መኖር ይሻላል ከመራራቅ

ወይ አገርሽ መራቁ ልቤ አለማወቁ
- ሐሳብ ለሐሳብ ያለመተዋወቅ



ወይ አጥብቶ ይርቋል ወይ አንዶ ይሞቋል
- ሲኖሩ ለጠቅ ሲሔዱ መንጠቅ

ወይ ካሰው ተወሰድ ወይ ካሰው ተዛመድ
- ከኃብታም ተወሰድ ወይ ከኃብታም ተጠጋ

ወይ የምድር ሰው እኔ ዘንድ መጥተህ ባየኸው
- ያለውን ችግር መች አያችሁት

ወይ ጉዴ ላግባሽ አለኝ ነጋዴ
- የቀድሞ ነጋዴ ለንግድ ወጥቶ ወደቤቱ የሚመለሰው ከብዙ ጊዜያት በኋላ በመሆኑ

ወይ ጋሻ ቀድሞ ቀረሻ
- ይሔ አሁን የተገኘው ቀደም ብሎ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ እንዴት መልካም ነበር

ወይ ጣጣ ምን ነገር መጣ
- ምን ጉድነው አዲስ ነገር መጣ

ወይ ጣጣ በዚህም አያስወጣ
- እንዴት ያለው ችግር ገጠመኝ

ወይ ጣጣ ዞሮ መጣ
- ያው የምናውቀው ተመልሶ መጣ

ወይዘሪትነት ያንድ ቀን ርቀት
- ያገባች ቀን ወይዘሪት በማግስቱ ወይዘሮ ትሆናለች

ወይዘሮና ሚዶ ገበሬና ምሳር
- አንድ ከአንድ ተዘውትሮ የማይለይ

ወይፈን ለገፋፊ ዓሣ ለጠላፊ
- መንገድ ላማላጅ ገበያ ላርፋጅ

ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል
- ከፍተኛ ደስታ አንዳንዴ ለአደጋ ያጋልጣል

ወይፈን ካረሰው አባት በሬ ያንከላወሰው
- ምንም ቢሆን ትልቅ ሰው የሠራው ሥራ መሠረት አለው

ወይፈን ካሳመረው በሬ ያበላሸው ይሻላል
- ሽማግሌ ያየው ነገር አይበላሽም

ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ
- ወደው ያደረጉት ነገር ቢበላሽም አይቆጭ

ወደቀ ሲሉ ተሰበረ
- አጋኖ ማውራት

ወደው የዋጡት ቅልጥም ከብሩንዶ ይጥም
- ተማምነውበት ያደረጉት ነገር አይቆጭ

ወደ ጐሬ መሔድ መጥፎ አካሄድ
- ወደ ጉድጓድ ከተሔደ መመለሻ የለም

ወዲያ አጥፍቶ ይርቋል አልምቶ ይሞቋል
- ሲኖሩ ለጠቅ ሲሔዱ መንጠቅ

ወዳጁን የሚበድል ሰወንድሙ አይሳሳም
- የሰመደ መደመደ

ወዳጄ ስሰው በሰጠኝ ስሰቴ ስሰው ቆረጠኝ
- ያመንኩት ሰው ከድቶ ጉዳት አደረሰብኝ

ወዳጄ ቢጠላኝ ሽክሙ ቀሰሰኝ
- ከራሱ ከወዳጄ ከመጣ ቢሸኝም አይቆጩኝም

ወዳጅህ ማር ቢሆን ጨርሰህ አትላሰው
- የወዳጅህን ገንዘብ በጥቡጠህ ባዶ እጁን አታስቀረው

ወዳጅህ ሲታማ ሰአኔ ብሰህ ሰማ
- ሰራስህ ስሰሌላ ሰው ሲያማልህ እራስህንም ነገ ያማሃልና ተጠንቀቅ

ወዳጅህ ቢሰክር ይሰማሃል ጠላትህ ቢሰክር ይነክስሃል
- የሚጠላህ ሰው በሁኔታው ይታወቃል

ወዳጅ ሲበዛ ጠላት ይቀንሳል
- አጋር ስላሰህ ጠላቶችና ይፈረከረካሉ

ወዳጅ ሲከዳ ይቀላል ዕዳ
- ወዳጅ ሲርቅ ብዙ መጨነቅ ይቀራል

ወዳጅ ሲያረጅ በደጅ ያልፋል
- የተሰላቸ ወዳጅ ወደቤት ጉራ አይልም

ወዳጅ በንደበቱ ውሻ በጅራቱ
- እያንዳንዱ የራሱ የሆነ የአቀባበል ዘዴ አሰው

ወዳጅና ሥዕል በሩቁ ያምራል
- ወዳጅን በሩቁ ነው

ወዳጅና ጠላት አንድነት ይሰሙሃል አንድነት ይጠይቁሃል
- ሁሉም ይጠይቁሃል የቱ ግን ከልቡ ካንጀቱ እንደሚጠይቅህ አንተ ታውቃሰህ

ወዳጅ ወዳጁን አይከዳም ከጅብ ወዲያ ሆዳም
- ምንም ግሰኝነት ቢጠናብህም ወዳጅህን አሳልፈህ አትሰጥም

ወዳጇን ብታይ ባሏን ጠላች
- የዘሰቀታውን የማታውቅ በጊዜያዊ ነገር የምትደሰል

ወድቆ ይነሷል በአጅ ዘግይቶ ይከብሯል በልጅ
- የኋላ የኋላ የወሰዱት ልጅ ጧሪ ነው

ወዶ ገባ ልብሱ ዳባ
- በራሱ ፈቃድ የገባ አገልጋይ እንክብካቤ አይደረግሰትም

ወዶ ገባ ውሻ ባሰቤቱን አትግባ ይላል
- ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ

ወገን ብዙ ኃዘን ብዙ
- ወገን ብዙ ሰው የችግር ጊዜም ችግሩ ያንተው ያህል ነው

ወገን ያሰው ማንም አይታገሰው
- አጋር ያሰው ሰው ማንም አይናገረው



ወገን ያሰው ያግባሽ
- ወገን ያሰው የሚፈራና ተወዳጅ የሆነ ያግባሽ

ወገኛ በባዳ ምድር ልሁን ይላል ሠርገኛ
- ጅብ ከማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አሰ

ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ
- ውሰጥ ውሰጡን እየተደሰቱ እንደማይፈልጉ መምሰል

ወግ አድራሽ ገበሬ ይሞታል በሰኔ
- በዋናው ሥራ ጊዜ ከሥራ መሰየት

ወግ የጐደሰው ከፈን የሰውም
- የሥርዓት መታጣት ተፈላጊን ነገር ያበላሻል

ወጠጤ ሰወጠጤ ቢማከሩ እንዳይታረዱ
- በሬና በሬ መከሩ ቀንበር ሰበሩ

ወጡ ሳይወጠወጥ ወሰከንባዩ ቂጥ
- ሳይደውል ቅዱስ

ወጣሁ ልጅ ነኝ ፈላሁ ጠጅ ነኝ
- የወጣትነት ሰሜቴ ተነሳሳ

ወጣት የነብር ጣት
- ወጣት ችኩል ነው

ወጥ ማን ያውቃል ቀላዋጭ
- እዚያም እዚያም የሚበላ ጥሩውን ይሰያል

ወጥ ሲታጣ ይበላል በዱባ
- የምትፈልገውን ካላገኘህ ባገኘኸው ነገር ተጠቀም

ወጥ ቢጣፍጥ እጅ ያስመጥጥ
- መልካም ነገር ከተገኘ እስከመጨረሻው አይሰቀቅም

ወጥ ያጣ ዱባ ልብስ ያጣ ዳባ
- የምትፈልገውን ካጣህ ባገኘኸው ነገር ተጠቀም

ወጥ ያጣ ጉመን አገር ያጣ ሰሜን
- ተፈላጊው ነገር ካልተገኘ ፍላጐት ባያረካም አማራጩ ይወሰዳል

ወጥ ይሉሻል በርበሬ ነው
- በርበሬ በዝቶበታል ሰማለት ተቃራኒውን ነው

ወጥቶ አደር ይጓዛል ከገደል
- ዱር የሚያድር በብዙ ችግርና ሁኔታ ውሰጥ ይኖራል

ወጥን የሚጨርስ መጉራረስ ሴትን የሚያስመታት መመላሰስ
- መልካም ቃል ቁጣን ታበርዳለች

ወጭትና ሴት ሲከናነቡ ይሻላል
- መከናነብ ሌላውን ከማየትና ከመሻት ይጠብቃል

ወጮ ቢያገላብጡት ወጮ
- ወዲህ ቢሉት አምስ አራት ወዲያ ቢሉት አምስ አራት አሰች አሉ ገራኘ

ወፍራም ቢከሳ ይቀጥናል ቀጭን ቢከሳ ይመነምናል
- ያሰው ቢሰጥ ትንሽ ከሀብቱ ይቀንሳል አንጂ ጨርሶ አይደኸይም

ወፍ እንደአገሯ ትጮሃለች
- ሁሉም እንደልምዱ ነው የሚኖረው

ወፍ ከድንጋይ ላይ አርፋ ፍለጋዋ ጠፋ
- ያለቦታው ያልተገኘ ነገር ምንነቱን ለማወቅ ያስቸግራል

ወፍ የሚፈራ ዘንጋዳ አይዘራም
- ሲፈሩ አይከሉ በጉጣ አያርሱ

ወፍ ጠባቂ ቢያደርጓት ድንጋይ ለቃሚ ቀጠረች
- ራስን ሳይችሉ ሌላ እረዳት ፈላጊ መፈለግ

ወፍጮና ሴት መቼም አይሞላለት
- ሴት ሥራ ስለሚበዛበት ምንም አይሞላላትም

ዋሉን የሚያወጣ ጢም እያወጣ
- አደርጋለሁ ያለውን የማይፈጽም አክብሮት አይሰጠውም

ዋስ አይሞገት ቆማጣ አይፈተፍት
- ዋስ ለመከራከር መብት የለውም

ዋስ አይወሳወስ በግ አይናከስ
- ዋስ ለመከራከር መብት የለውም

ዋስ ካለህ ዱቄትህን ለነፋስ አበድረው
- ዋስ ያለው ሰው በዋሱ ስለሚመካ ብዙ ነገሮች ይፈጽማል

ዋስ ያለው ያመጣል ዋስ የሌለው ይለምጣል
- ዋስ ያለው ከችግር ያመልጣል

ዋስ ጠርቼ ሹልክ ብዬ መጣሁ
- ዋስ ያለው ከችግር ያመልጣል

ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ነፋስ በወጥመድ እይዛለሁ
- የማይመስለውን ሁሉ ከመናገር አልቆጠብም

ዋሽቶ ከማጣላት ዋሽቶ ማስታረቅ ይበልጣል
- ዋሽቶ ጥሩ መሥራት መልካም ነው

ዋ ቅል ካንተ በኋላ ገደል
- አንዳች ነገር ከገጠመህ የት እንደምትወድቅ አልገመትክም

ዋቢ ተሸሸ ጠላ ከጉሸ
- ምስክር ከከዳ ተከራክሮ መርታት አይቻልም

ዋቢ ያለው ባጤ በቅሎ ይቀመጣል
- ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን እደጅ ታሳድራለች

ዋቢ ያለው ያመልጣል ዋቢ የሌለው ይለምጣል
- ያለው ይጠጣል የሌለው ያፈጣል

ዋቢ ያለው ይወጣል ዋቢ የሌለው ይቀጣል
- ወገን ያለው ከብዙ ችግሮች ሊሸፈን ይችላል

ዋና ከቤት ጠበቃ ከዱለት
- መነሻው ከባለቤት ሲሆን ነገር የማላመሩ ጉዳይ የሌላው ይሆናል

ዋንዛ በልታ ብላና መረቀች
- ያበላትን ትታ ያላበላትን አመሰገነች



ዋንጫ በገበታ ሹመት በተርታ
- ሁሉም በየተራው ይደርሰዋል

ዋዛና ፈዛዛ የለውም ለዛ
- ቀልድና ቅዘን ሴት ያበላሻል

ዋጪው ብላት ትጉርስበት ጠጪው ብላት ትጨምርበት
- የበላችው ያገሳታል በላይ በላይ ያጉርሳታል

ውስታ እስከ ትዝታ ፍቅር እስከ ዝምታ
- ፍቅር ያልቅና ሲሆን ግትቻ ንዝንዝና ጭቅጭቅ ብቻ

ውሳ ከመጣች ነገር አመጣች
- ውጭ መዋል ከጀመረች በኋላ ጸባይዋ ተቀየረ

ውላ ውላ ባሏ ሲመጣ ትበላ
- ባሏን ጠብቃው በላች

ውል እያወላወል ምላት እያሻግር
- ቃልኪዳን ከባድ ነገር በመሆኑ ማፍረስ ያስቸግራል

ውል እያናግር የተከዜ ሙላት እያሻግር
- ቃልኪዳን ከባድ ነገር በመሆኑ ማፍረስ ያስቸግራል

ውል አያፈርስ ዓይን አያፈስ
- ቃልኪዳንን ማፍረስ ዓይንን በገዛ እጅ እንደማፍሰስ ይቆጠራል

ውል ያዋለ ሰንበት ያከበረ
- ቃልኪዳንንና ሰንበትን ያከበረ ሁሉ ክቡር ነው

ውል ያዋውላል ታንኳ ያሻግራል አቤራ ይሰላል
- ውል ላይ የሰፈረ ነገር አስተማማኝ ነው

ውል ያዋውላል ትምባሆ ያስላል
- ውል መልካም ነው ትምባሆ ከጥንባቱ በስተቀር ፋይዳ የለውም

ውሎ ውሎ አህያ ለጅብ
- ለፍቶ ለፍቶ ደክሞ ደክሞ መጨረሻው የማያምር

ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት
- ሞት የማይቀር ዕዳ ነው

ውሎ የበሉት ምሎ የበሉት
- በሰዓቱ ያልበሉቱ ምግብ ጥሩ አይደለም

ውረድ ከማማ ውጣ ከጫማ
- ከተያዝክበት ጣጣ እረፍት አግኝ

ውርርድ ቁምነገር ይጋርድ
- ውርርድ ቁምነገርን ይሸፍናል

ውርርድ እንደጫፉ ዛፍ እንደቅርንጫፉ
- ሁሉም እንደመነሻው እንደመሠረቱ ነው

ውርርድ ከጫፉ አሞራ ከዛፉ /ከክንፉ/
- ምን ቢሆን አሞራ ዞሮ ዞሮ ከዛፍ ያርፋል

ውርደት ካር ይገማል
- የተዋረደ ሰው በሰዎች የተጣላ ነው

ውርጃ የሚበዛበት ሴት ልጆቹን ውኃ ይወስዳቸዋል
- መከራ ሲመጣ በሳይ በሳዩ ነው
ውስጡን ለቁስ
- ተከድኖ ይብሰል
ውስጡን ሲያጥቡት ላዩ ይጠራል
- እውነት ሲናገር ሁሉ ነገር የተቃና ይሆናል
ውሽታም ሰው ማስታወሻው ጣቃ ነው
- ሐሰተኛ ሰው ሐሰት ማውራቱን ከጀመረ አፉን አይዘውም
ውሽታም ቁምነገር ቢናገርም ተቀባይነት አያገኝም
- አንድ ቀን ስትሰርቅ ካይዋት ብትቆርብም አያምኗት
ውሸት ተናግረህ እውነትን አግኝ
- እውነቱን ሐቁን ለማግኘት ዋሽተህም ቢሆን ጥረት አድርግ
ውሸትና ሰንቅ እያደር ይቀላል
- ውሸታም ሰው እያደር ይዋረዳል
ውሸትና ቅራሪ ሽምጥጥ ነው
- ከዋሹ አይቀር ሽምጥጥ አድርጐ መዋሸት ነው
ውሸት ይዳርጋል ለሞት
- መዋሸት ለአደጋ ይሰጣል
ውሸት ደግ ነበር ጣጣው ባልነበር
- ውሸት ይዳርጋል ለሞት
ውሻ ምሳ በማጣት ያረጃል
- ተገቢውን ነገር በተገቢው ጊዜ ማጣት አካልን ይጐዳል
ውሻም በሳው አንቺም በላሽው ካልከደንሽው
- በክብር ካላስቀመጡት በፈለጉት ጊዜ ከወዴት ይገኛል
ውሻ ምን ትበያለሽ አለች ጌኛ ቢበልግም እለቴን ባይበልግም አንችን
- ከሆነልኝ የምፈልገውን ለማግኘት እጥራለሁ ካልተመቸም አማራጭ አፈልጋለሁ
ውሻ ምን አገባሽ እርሻ
- ያለቦታው ያለሙያው ያልተለመደ ቦታ መገኘት
ውሻ ሲመሳለስ የልቡን አያደርስ
- እንዲያው ይደክማል እንጂ በሚጠቅመው ጉዳይ ላይ ትኩረት አለማድረግ
ውሻ ሳይቸግረው ገበያ ወጥቶ ይደባደባል
- በማያገባ ነገር መግባት ችግር ላይ ይጥላል
ውሻ ቀንድ ልታወጣ ሔዳ ጆሮዋን ተቆርጣ ተመለሰች
- አተርፍ ባይ አጉዳይ
ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል
- ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጉረቤት
ውሻ በበላበት ይጮሃል
- ማንኛውም ሰው ለሆነለት ሰው ጠበቃ ይሆናል



ውሻ ቢመላለስ የልቡን አያደርስ
- እንዲያው አጉል ድካም የሚጠቅምን ለማግኘት አለመጣር
ውሻ ቢጠሩ ቀን ቢቆጥሩ ደረሰ በእግሩ
- ቀን ሳያስቡት ከተፍ ይላል
ውሻና ውሻ ባጥንት ይጣላል ባውሬ ይስማማል
- ለጥቅም ከዘመድ ጋር እንኳን ጥል አይቀርም ለጋራ ጠላት ግን ትስማማለህ
ውሻን በእግር መምታት እንካ ብሎ ሥጋ መስጠት
- አባብን ሞተ ብሎ ራሱን መርገጥ መቅበጥ
ውሻ አጥንትን የሚቆረጥመው መዋጥ ቢያቅተው
- አንድን ሥራ በፈርጅ በፈርጁ በቅደም ተከተል ካልተሠራ  ውጤት አይኖረውም
ውሻ ከሲጥ ጦጣ ከጥጥ
- አጥፊን ወደሚያጠፋበት ቦታ አትምራው
ውሻ ከሸሹለት ልጅ ከሣቁለት ያም አይመለስ ያም አይታገስ
- አንድ ችግር ሲመጣ በዘዴና በብልሃት መወጣት እንጂ ቢሸሹት ችግሩ መፍትሔ አያገኝም
ውሻ ካልቀበጠ ጅብ አይበላውም
- ማንም ከተጠነቀቀ አደጋ አያጋጥመውም
ውሻ የሚበላውን እንጂ የተቃጣበትን ዱላ አያይም
- ጥቅሙን እንጂ የሚጐዳውን ነገር አይመለከትም
ውሻ ጌታዋን በለጠች
- ጌታዋን ተከትላ ስትሔድ ጌታዋ ከሰው ጋር ሲያወራ ቁጭ በማለቷና በማረፏ
ውሻ ጌታዋን እንጂ የጌታዋን ጌታ አታውቅም
- የቅርቡን እንጂ የሩቁን አታውቅም
ውሽማ ሲቆይ ባል ይሆናል
- መለማመድ ሕጋዊነት ያለው ሁኔታ እንዲከሰት ይጋብዛል
ውሽማዋን ብታይ ባሏን ጠላች
- አርቃ የማታስብ በጊዜያዊ ደስታ የምትደለል
ውሾች ምን ጊዜ ነው የሚናከሱ? ጅብ አባረው ሲመለሱ
- ውሾች በጅብ ይተባበራሉ በአጥንት እርስበርስ ይናከሳሉ
ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን
- ነገሩን በፍጹም አላነሳም
ውትር ውትር ያነሳል በትር
- አጉል ቀልድ ወደምር ያመራል
ውኃ ለሚወስደው ሰው በትርህን እንጂ እጅህን አትስጠው
- በሥራው ለሚጠፋ ሰው አትተባበረው
ውኃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ
- ቀድሞ የተገኘ ይጠቀማል

ውኃ ለወሰደው ፍስጋ የለውም
- መፍትሔ ስሌለው በከንቱ መድከም አያስፈልግም

ውኃ ሲያንስ ሲል ይገማል ሰው ሲያንስ ሲል ይኩራል
- ኩራት ያስንቃል እንጂ አያስከብርም

ውኃ ላነቀው ባሰቤቱ ሳላወቀው መድኃኒት የለውም
- በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም

ውኃ ልትቀዳ ሔዳ እንስራዋን ረስታ መጣች
- የተነሱበትን ዓላማና ግብ መዘንጋት

ውኃ መልሶ ውኃ ቀልሶ
- እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ

ውኃ ምን ያገሳ ድሃ ምን ያወሳ
- ከድሃ ምን ቁምነገር ይገኛል ብለው ያናግሩታል

ውኃ ሲወስድ እያሣሣቀ ነው
- ውኃና ገደል እያሣሣቀ ነው

ውኃ ሲደርቅ ይሸታል ሰው ሲከዳ ይወሽከታል
- ውኃ ሲያንስ ሲል ይገማል ሰው ሲያንስ ሲል ይኩራል

ውኃ ሲጐድል ተሻገር ዳኛ ሲገኝ ተናገር
- ጉዳይህን ተናግረህ ፍርድ አግኝ

ውኃ ቀጠነ ይላል
- በሆነ ባልሆነው ይጨቃጨቃል

ውኃ በስዘብታ ድንጋይ ይፈነቅላል
- በትዕግስት የፈለጉትን ማግኘት ይችላሉ

ውኃ በብልሃት ይቆላል በአሳት
- አስቸጋሪን ነገር በብልሃት ሊከናወን ይችላል

ውኃ በአሳት ስስ በዳገት ይፈተናል
- ለሁሉም አስቃ አለው

ውኃ ቢወቅጡት እንቦጭ
- ለውጥ አያመጣም

ውኃ ቢደርቅ ዓሣ ያልቅ
- ዋናው መሠረቱና ምንጩ መነካት የለበትም

ውኃና ገደል እያሣሣቀ ይወስዳል
- ውኃ ሲወስድ እያሣሣቀ ነው

ውኃና ጠጅ አኩል ይጠጣሉ
- በፈሳሽነታቸው ቢመሳሰሉም በአርኪነታቸው ይለያያሉ

ውኃን መመለስ ወደሌላ ማፍሰስ
- ከአንዱ ብትከለክለው ተመልሶ ወደአንዱ ይሔዳል

ውኃን ምን ያስሎኸዋል ድንጋይ
- ሰው ብሶቱን ያለምንም ምክንያት አያወራም

ውኃ አያንቅ ነገር አያልቅ
- በጐ ነገር መልካም ነገር ምንጊዜም ይታወሳል



ውኃ እድፍን ያጠራል ትምህርት ልብን ያበራል
- ትምህርት ዕውቀትን በማላበስ ለከፍተኛ ደረጃ ያበቃል

ውኃ ከነቁ አበባ ከአጽቁ
- ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ

ውኃውም እንዳይደርቅ ዓሣውም እንዳያልቅ አድርጐ ነው እርቅ
- በሁለቱም በኩል ያለውን ሁኔታ በማቻቻል መሆን አለበት

ውኃ የሚወስደው ሰው አረፋ ይጨብጣል
- ጥፋ ያለው የማያድነውን ነገር ላይ ያተኩራል

ውኃ የጥቅምት ነበርሽ ማን በጠጣሽ
- እውነትን ሐቅን ለች ለመድፈር ያቅታቸዋል

ውኃ ጭስና ክፉ ሴት ያባርራሉ ከቤት
- ከቤቱ ክፉ ሚስት ያለው ሁልጊዜ ኃዘን ሁልጊዜ ትካዜ

ውዝም ስሹም ጥንብ ለጅብ
- ውዝፍ ዕዳ ያለበት ሰው ሹም ፊት ሲቀርብ ከውዝፉ ሌላም ይጠበቅበታል

ውድሽና ውዴ የለቀሙት ሥንዴ
- ተፈቃቅረን ተዋደንና ተስማምተን የሠራነው ሥራ መልካም ውጤት አለው

ውጣ ከቤት ተነቀል ከመሬት
- ከአካባቢው ጥፋ

ውጣ ውጣ ከሚሉት በሬ ዶማ ይሻላል
- ካልረባ አዝማሪ ጥሬ ቃሚ ይሻላል

ውጦ ውጦ ጨረሰው አይመረው አይተኩሰው
- ምንም ሳያስጨንቀው ጨረሰው

## ዐ

ዐወቅሽ ዐወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች
- አጉል ማበረታቻ መስጠት ሰውን ማሳሳት
- የአንድን ነገር ክንውን ያለማወቅ

ዐዋቂ ሲበዛ አስታራቂ ይሞታል
- ሐኪም ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል

ዐዋቂ አስታራቂ
- ነገርን በደንብ የሚያስተውል ነገሮችን አቅንቶ ያስማማል

ዐዋቂ ይርዳኝ ሸንጐ ይፍረደኝ
- ሸንጐ ትክክለኛውን ፍትሕ አይነፈገኝ

ዐውቀው በድፍረት ሳያውቁ በስሕተት
- ዐውቀውም ሆነ ሳያውቁ ለፈጸሙት ስሕተት ይቅርታ ይደረግላቸዋል

ዐውቆ መተው ነገሬን ከተተው
- ዐውቀህ ነገርን ችላ ማለት ከጥፋት ያድናል

ዐውቆ የሚያጠፋ ኑሮው ምን ይከፋ
- ዐውቆ የሚያጠፋ ሕይወቱ የተጉሳቆለች ትሆናለች

ዐውቆ የተኛን ቢጠሩት አይሰማም
- ቀደም ብለው ወስነው በፈጸሙት ሐሳብ ላይ መወያየት ፋይዳ የለውም

ዐጃ ፈልፍለው ቢዘሩ ተመልሶ ከዘሩ
- ያው እንደቀድሞው

ዐጉል መጋባት መጋማት
- ሰላምና ጤና ስምምነት የሌለው ሁኔታ

ዐጉል ባልንጀራ እንብላ ሲሉት እንራ
- ጠቃሚ ነገርን እንደማስቀደም ማዘግየት

ዐጉል ፍቅር ያመናቅር፣ ዐጉል ንግግር ያደናግር
- ዐጉል የሆነ ሁሉ ምንጊዜም አጉል ነው ፍቅሩም አይጥምም፣ ንግግሩም ግልጽነት አይኖረውም

ዐጥንትና ጅማት በአካላት
- ዋናው ሳይኖር ዝርዝሮች በራሳቸው ዋጋ አይኖራቸውም

ዐጥንት የሚያለሰልስ ወሬ ሰማሁላችሁ ዛሬ
- የሚያስደስት ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ማለት ነው

ዐፈር ማሽ ባንድ እጅ ዐፈር መላሽ
- በሰው ላይ ተንኮል የሚሠራ መሰሪ ሰው

ዐፈር ብለው እያፍሱህ፣ እህል ብለው አያፍሱህ
- ከምንም ውስጥ የሌለህ የማትፈለግ

ዐፈር ፈጭቶ ዝርዝር ቀጭ
- ትናንሾቹን የሚያርም የሚያስተካከል

ዓለም ተልባ ነው ይንሸራተታል
- ሰው እንደተልባ ተንሸራታችና ባስቀመጡበት የማይገኝ ነው

ዓለም አላፊ መልከ ረጋፊ
- ሰው ተለዋዋጭ እንዲሁም ሟች ነው

ዓለም አታላይ እንደ በቅሎ ኮብላይ
- ዓለማዊ ሁኔታዎች ያታልላሉ ሁኔታዎች ከእጅህ የሚያመልጡት ሳታስበው ነው

ዓመሌ አወጣኝ ከማኅበሬ
- መጥፎ ባህሪዬ እንድጠላ አደረገኝ

ዓመልህ በጥፌ ይበልህ
- የራስህ ጠባይ ያጋልጥህ

ዓመልህን በጉያህ፣ ስንቅህን ባህያህ
- መጥፎ ዓመልህን አስወግድ

ዓመል ቤት አይጠብቅ
- ልማድ ከሰይጣን ይከፋል



ዓመልና ጅራት፣ በስተኋላ ይበቅላል
- የተደበቀ ጸባይ ወደ ኋላ ይታወቃል

ዓመል ያላት አገልጋይ፣ ከእመቤቷ እኩል ትቀባለች
- በዓመሏ እመቤቷ ሳትቀር ትወዳታለች

ዓመል ያወጣል ከመሃል
- የሰው ባህርይ ከሰው መሃል ይለያል

ዓመል ያገባል ከመሃል
- በራስህ በጠባይህ ትከበራለህ

ዓመት ሳይበላ ዓመት ያጣላ
- ሰዎች በጥቂት ነገር ይቀያየማሉ

ዓመት አርሶ አይጉርስ፣ ዓመት ፈትላ አትለብስ
- እንዲያው ድካም ትርፉ

ዓመት አስቦ ለልደት
- ያ ሁሉ ድካም አንድ በዓል ለማክበር ነው

ዓመት ዘመን መከሰት መመንመን
- ዕድሜ እያደር እየገፋ ወደ እርጅና ያደርሳል

ዓሣ ለሠጋሪ፣ ነገር ለጀማሪ
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው

ዓሣ በልቶ ውኃ መጠጣት፣ መልሶ ከነበረው ማግባት
- ተመሳሳይ ሁኔታን ደግሞ መፍጠር

ዓሣ በወንዙ ይታረዳል፣ የጨዋ ልጅ በቤቱ ይፈረዳል
- የሰው ልጅ በቤቱ በቤተሰቡ ይዳኛል

ዓሣ ብለምነው ዘንዶ፣ ዝናም ብለምነው በረዶ
- ይብስ አታምጣ

ዓሣን መብላት በብልሀት
- ራስን ከአደጋ መጠበቅ ብልሀነት ነው

ዓሣውም እንዳያልቅ ውኃውም እንዳይደርቅ
- ሁሉንም በመጠን በመጠኑ አድርግ ሌሎችም እንዳይጎዱ

ዓሣ ዓሣን ይበላዋል፣ ወንድም ወንድሙን ይጠላዋል
- ራስን ለማኖር ለጥቅም ሲባል የሚከሰት ከሰተት

ዓሣ የጌቶች ምሣ፣ የገረድ አበሳ
- ምግብነቱ ጣፋጭ ቢሆንም ሥራው ከባድ ነው

ዓሣ ግማቱ፣ ከአናቱ
- የአንድ ነገር ብልሽቱ የሚጀምረው ከላይ ከዋናው ነው

ዓሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል፣ የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
- ለሰው ንብረት ሲያቆበቁቡ የራስን ማጣት ያመጣል

ዓባይ ማደሪያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል
- ለራሱ አያውቅ ነዳይ፣ ቅቤ ለመነ ላዋይ

ዓባይ ቢሞላ ተሻገረ በመላ
- ችግርህን በዘዴ ተወጣ

ዓባይን በጭልፋ
- የማይቻለውን ነገር መሞከር

ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል
- የአላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው

ዓባይ አንተ አየኸኝ ከደረት፣ እኔም አየሁህ ከጉልበት
- በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሁኔታዎች መፈታተሽ

ዓይነ ደረቅ ሌባ፣ ከነቃጭሉ ይገባ
- የሌባ ዓይነደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ

ዓይነ ደረቅ፣ መልሶ ልብ ያደርቅ
- ዓይነ ደረቅ ሌባ ከነቃጭሉ ይገባ

ዓይኔን ሊያመው ጥርሴን አታሥቀው
- አባክህን የማይሆን ነገር ለማድረግ አትሞክር

ዓይን ሕመም ልግም ይወዳል
- በልግመኛ ሰው ላይ ዓይን ሕመም ይጠናበታል

ዓይን ሕመም ክሱት ነው፣ የሆድ ሕመም ሰውር ነው
- የአንዳንድ ሰው ባሕርይ ግልጽ ሲሆን የአንዳንዱ ስውር ነው

ዓይን ሲያይ ብረቱ፣ ጆሮ ሲሰማ መስኮቱ
- የተለያዩ ሕዋሳት ለተለያዩ ተግባራት ይውላሉ

ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
- ምንም እንኳ ዐይን ቢያይም ውሣኔው በልብ ነው

ዓይን አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች
- ዓይን አፋርነት ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ለመፈጸም አያስችልም

ዓይን ከጥርኝ ዐፈር በቀር የሚያጠግባት የለም
- የሰው ምኞች የሚያበቃው መቃብር ሲወርድ ነው

ዓይን ካላዩበት ግንባር ነው
- ካልተጠቀሙበት አያገለግልም

ዓይን የማያየው ልብ የማይሰተው አውነት አለ
- ባይን የማይታይ ግን እውነት የሆነ አለ

ዓይን ያጣ ጠምዶ የፈታ
- አግብቶ ደህናይቱን ሌት የፈታ ዓይን ያጣ ነው

ዓይኗን በዓይኗ አየች
- ጠለደች

ዓይኗን ቢያጠፏት ቅንድቤን አደራ አለች
- ዋናውን ትታ ቀላሉ ነገር ላይ አተኮረች

ዕለት ቆይቶ ላመት
- ትንሹ ተጠራቅሞ ትልቁን ያስገኛል

ዕርቅ ቢፈርስ፣ ካስታራቂው ድረስ
- እርሻ ቢፈርስ ካስታራቂው ድረስ

ዕርቅ አይፈርስ ዓይን አይፈስ
- ዕርቅ የዓይን ያህል ተወዳጅና ተፈላጊ ነው



ዕርቅ ከወርቅ ዛላ ከምርቅ
- በዕርቅ ጊዜ በዳይ ተበዳይን መካስ ጥሩ ነው

ዕርቅ የሰው፣ ደም ያደርቅ
- ዕርቅ የልብ ቂም ያስወግዳል

ዕርቅ የፈለገ ንጉሥን ገበሬ ያስታርቀዋል፣ ዕርቅ ያልፈለገን ገበሬ ንጉሥ አያስታርቀውም
- ሁሉ ነገር በፍላጐት ላይ ይወሰናል

ዕብድ ለዕብድ ቀን ይባጅ
- አንዱ ለአንዱ ቀን ያዛልቀዋል

ዕብድ ለዕብድ፣ አብሮ ይነጉድ
- ተመሳሳይ ጠባያት ያላቸው አብረው ይሆናሉ

ዕብድ ቀን አይመሽም
- ክፉ ቀን እንዲህ በቀላሉ አያልፍም

ዕብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው
- የሰው ጠባይ ለጊዜው ቢደበቅም ይፋ መውጣቱ ግን አይቀርም

ዕብድና ብርድ ያሥቃል በግድ
- ላትወድ በግድ የምታደርገው

ዕብድና ዘመናይ የልቡን ይናገራል
- ማን አለብኝ ባይ

ዕብድና ገር የታየውን ይናገር
- የዋህ ሰው የልቡን ሚስጢር አይደብቅም

ዕብድ እህል ገዝቼ ሚስቴን አሳበድኳት
- አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ሌሎችንም አስቸገርኩ

ዕብድ ከወፈፍተኛ ቤት ያድራል
- ቂጥኛም ከውርዴ እንዲሉ

ዕብድ የያዘው መልክ አይበረክትም
- መልካሙን ነገር በሥርዓት ካልያዙት ይበላሻል

ዕንቁራሪት ዝሆን እህል ብላ ተለንጥቃ ሞተች
- ያለአቅም መንጠራራት

ዕንጨት ሞልቶ ዛቢያ አይገኝበት
- ከሞላ ሰው ቁምነገረኛ መታጣቱ

ዕንጨት ቢያነዱት አመድ ቃጫ ቢፈትሉት ገመድ
- አንዱ ባይጠቅም ሌላው መጥቀሙ አይቀርም

ዕንጨት ቢጠርቡት ይቀጥናል፣ ሰው ቢበልጡት ይቀናል
- ሁሉም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ባሕርይ በውስጡ በመኖሩ

ዕንጨት አይሸከሙ ላመድ እሮጊት አያገቡ ላትወልድ
- ለዓላማህ የማይጠቅም እርምጃ አትውሰድ

ዕንጨት ካልነፈጉት እሳት አይጠፋም
- የነገሩን ውል ክያዝክ አትረታም

ዕወቁኝ ብሎ ደብቁኝ
- አዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያመጣል

ዕወቅ ያለው ባርባ ቀኑ ዕትወቅ ያለው ባርባ ዘመኑ
- የታደለው ገና በጠዋቱ የተሟላ ነገር ያጋጥመዋል

ዕውር ምን ዓይቶ ደንቆሮ ምን ሰምቶ
- ማያም መስሚያም በሌለበት በዚህ ጉዳይ ላይ መነጋገር አይቻልም

ዕውር ምን ይሻል ብርሃን፣ በሽተኛ ምን ይሻል መዳን
- የሁሉም ፍላጐት የሚሟላው እንደየችግሩ መፍትሔ ሲገኝ ነው

ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይገባል
- ሥራ ፈት መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል

ዕውር ሲወበራ በሽማው ላይ አራ
- አጉል መቀናጣት ይጥላል ከጥፋት

ዕውር ሲወበራ ከመሪው ይጣላ
- የኋላውን አለማሰብ

ዕውር በዘንጉ ነጋዴ በወርቁ
- ሁሉም ባለው ኃይልና ባለው መሣሪያ ይጠቀማል

ዕውር ቢጠግብ ዘንጉን ይወርውር
- ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይሔዳል

ዕውር አያፍር ፈሪ አይደፍር
- የሌለውን ከሌለበት ቦታ መፈለግ

ዕውር ዕውርን ቢከተል ተያይዞ ገደል
- ዕውርን ዕውር አይመራውም

ዕውር ከመሪው ሞኝ ከመካሪው አይጣላም
- ምን ይዞ ጉዞ

ዕውር ይወልዱ ዕውር ቢፈርዱ
- በሠሩት ሥራ መልካምም ሆነ ክፉ ይዳኛሉ

ዕውቀት ኃይል ነው ሰላም ጤና ነው
- ዕውቀት ለሁሉ ነገር መክፈቻ ቁልፍ ነው

ዕውቀትና ፍጥረት አንድ ቀን ነው
- ለመተዋወቅና ለመወዳጀት ረጅም ጊዜ አይወስድም

ዕውቀት ያኮራል ሥራ ያስከብራል
- ዕውቀት ያለው በዕውቀቱ ሥራም ያለው በሥራው ክብር ያገኛል

ዕዳ ለቤት ምስጢር ለጐረቤት
- ምንም ቢሆን ምስጢር ለጐረቤት አይነገርም

ዕዳ ልቦና ለጸሎት፤ ዕዳ ለብዕና ለመሥዋዕት
- ለዓምላክህ የምታቀርበው ጸሎትና ስለት ከልብህ መሆን አለበት

ዕድላም እሞሌ፤ በቅሎ ይለውጣል
- ዕድለኛ ሰው የማያገኘው ነገር የለም

ዕዳ ሠርጉ ነውር ማዕረጉ
- ነውርን እንደሽማ የተላበሰ

ዕዳ ቢያምርህ ዋስትና ኩነኔ ቢያምርህ ግብዝና
- ዕዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ አሉ



ዕዳ አለብኝ ብለህ አትቸገር፣ ዕዳ የለብኝም ብለህ አትክበር አይታወቅም የዓምላክ ነገር
- ሉሉ የሚሰጥህን ወይም የሚያመጣውን ማን ያውቃል

ዕዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ
- እንዲያው በድንገት ሳላስበውና ሳልፈልገው

ዕዳ ከፋይ አሉ ባይ፣ ሞት ተቀባይ አዎ ባይ
- በሰው ላይ ለሚደረገው ሐሜት ተባባሪ አትሁን

ዕዳውን ከፍሎ ያካተተ ጌታውን የተለናበተ
- ከዕዳ ነፃ የሆነ ሰው ምንም የሚፈራው አይኖረውም

ዕዳው ዶሮ መጋቢ ያው ዶሮ
- ዞሮ ዞሮ እዚያው

ዕድለ ቢስ ሲዳር ውኃ ይሞላል በጥር
- ነገሩ ሁሉ ተው እንዳይሆን ነው

ዕድለ ቢስ አሞራ አንበጣ ሲመጣ ዓይኑ ይጠፋል
- አትብላ የተመኘኸውን አታሟላ ያለው

ዕድላም አሞሌ በቅሎ ይለውጣል
- በትንሹ ትልቅ ነገር ላይ ወይም ውጤት ላይ መድረስ

ዕድል ተርታውን ዕጣ ፈንታውን
- ዕድል በየተራ ለሁሉም የምትደርስ ናት

ዕድል የሌለው የሚለፋው ለሰው
- ለራሱ ያላለው ለሌለው ይደክማል

ዕድል ፈንታ ጥዋ ተርታ
- ሁሉም የራሱን ዕድል ፈንታ በየተራ ያገኛል

ዕድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍስሐ
- ዕድሜ ካለ ለደስታም ሆነ ለንሰሐ ይበጃል

ዕድሜና መስተዋት አይጠገብም
- ማንም ሰው ዕድሜ በቃኝ የሚል የለም

ዕድሜና ቁረንጮ ተበጣጥሶ ያልቅ
- ዕድሜ ቀስ በቀስ እያለቀ ሔዶ መጨረሻው ነጥብ ላይ ይደርሳል

ዕድሜና ጨርቅ ሲበጣጠስ ያልቅ
- ዕድሜ ቀስ በቀስ እያለቀ ሔዶ ወደሞት ያደርሳል

ዕድሜና ጨርቅ በደህና አያልቅ
- ብዙ ውጣ ውረድ አለበት

ዕድሜ ካላነሰው ጊዜ አለው ለሰው
- ሰው ዕድሜ ካገኘ የተሻለ ሕይወት ሊያጋጥመው ይችላል

ዕድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ከውኃ የገባ እሞሌ
- ውኃ የገባ እሞሌ ማሙቶ እንደሚያልቅ ሁሉ ዕድሜ ያልመከረው ሰውም ቀስ በቀስ ችግር ላይ መውደቁ አይቀርም

ዕድሜ ያስታርቃል ሙግት ያዳርቃል
- በዕድሜ እየገፉ ሲሔዱ ነገሮችን በማስተዋል ለእርቅ ስምምነት ምቹ ይኮናል

## መልመጃ 11 /ወ፣ዐ/

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. ዐዋቂ ሲበዛ _______ ይሞታል
ሀ. እስታራቂ ለ.በሽተኛ ሐ. ሌባ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

2. ዐውቆ መተው______
ሀ. ነገሬን ከተተው ለ. ዐይቶ መፍረድ
ሐ. ከነገር መ. መልሱ የለም

3. ወደው የዋጡት ቅልጥም _______
ሀ. አይቆረቁርም ለ. ከብርንዶ ይጥም
ሐ. ከዶሮ ይጥም መ. ቢያንቅ ደራሽ የለም

4. ወንድምና ወጥ__________
ሀ. ማነገራገሪያ ነው ለ. ማስፈራሪያ ነው
ሐ. ማባበያ ነው መ. መመኪያ ነው

5. ______________ድንጋይ ለቃሚ አገባች
ሀ. ወፍ ጠባቂ ቢያደርጓት ለ. ቤት ሥሪ ቢሏት
ሐ. ልጅ ጠባቂ ቢያደርጓት መ. እህል ጠብቂ ቢሏት

6. ወፍ የሚፈራ ___________
ሀ. ገበሬ አይሆንም ለ. ዘንጋዳ አይዘራም
ሐ. ሠርቶ ሳሞራ መ. የከብቱን ቁስል ያከማል

7. ዓይን አይቶ ___________
ሀ. ልብ ይፈርዳል ለ. ሕሊና ያያል
ሐ. ሆድ ይመኛል መ. እጅ ይመከታል

8. ወሬኛ ሚስት ___________
ሀ. ዘርዛራ ወንፊት ለ. የሚነፋ ወንፊት
ሐ. የሚዘራ ወንፊት መ. የማይነፋ ወንፊት

9. ወርቅ___________
ሀ. ያደምቃል ለ. ያስውባል
ሐ. በእሳት ያፈተናል መ. መልሱ የለም

10. ወደሽ ከተደፋሽ __________
ሀ. ቢረግጡሽ አይከፋሽ ለ. የራስሽ ጉዳይ
ሐ. ወዴት ሔድሽ መ. መልሱ የለም

11. ውላ ከመጣች ___________
ሀ. ነገር አመጣች ለ. እዛው አደረች
ሐ. ከሳች መ. ጠቆረች



12. ወጥ ቢጣፍጥ __________
ሀ. እጅ ያስመጥጥ ለ. ይበላል
ሐ. እንጀራ አይሆንም መ. መልሱ የለም

13. ዕውር አያፍር __________አይደፍር
ሀ. ዓመለኛ ለ. ጉበዝ ሐ. ፈሪ መ. ሌባ

14. ዕዳ ሠርጉ ________ማዕረጉ
ሀ. ጉበዝ ለ. ነውር ሐ. ፈሪ መ. ሌባ

15. ዕዳ ከቤት ________ለጉረቤት
ሀ. ምስጢር ለ. ነገር ሐ. ዶሮ መ. ፍየል

16. ዕድል ፈንታ ___________
ሀ. ለሥራ ለ. ዕጣ ፈንታ
ሐ. ጥዋ ተርታ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

17. ዕድለ ቢስ ሲዳር _________ ጥር፡፡
ሀ. እንጀራ ይጋገራል ለ. ዳቦ ይጋገራል
ሐ. ውኃ ይሞላል መ. ሁሉም መልስ ነው

18. ዕድሜና ቁረንጮ __________
ሀ. ተበጣጥሶ ያልቅ ለ. ተበጣጥሶ እያልቅ
ሐ. በደህና እያልቅ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

19. ዕድሜና ጨርቅ __________
ሀ. ሲበጣጠስ ያልቅ ለ. በደህና እያልቅ
ሐ. ተበጣጠሶ እያልቅ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

20. ወለባ ___________
ሀ. ለሹሩባ ለ. ለጉፈሬ
ሐ. ለሉጫ ፀጉር መ. ሁሉም መልስ ነው

21. ወልጄ እላከ ______እልጸደኩ
ሀ. ሠርቼ ለ. መንኩሼ ሐ. ሣልሠራ መ. አጥፍቼ

22. ወሬ ለጠያቂ _______ሳዋቂ
ሀ. ገበጣ ለ. ምክር ሐ. ነገር መ. ስድብ

23. ወሬ ቢያምርህ __________
ሀ. በየደጅህ ለ. በየመንደርህ ሐ. በየሉሌህ መ. በየሚስትህ

24. ወርቁ ቢጠፋ ___________አይጥፋ
ሀ. ሚዛን ለ. ጀንበር ሐ. ገንዘብ መ. ሥራ

25. ወርቅ በእሳት ___________
ሀ. እንጀራ በወጥ ለ. መሬት በጣት
ሐ. ውኃ በእሳት መ. መልሱ የለም

26. ወርቅ ይረከሳል __________ይነሳሳል
ሀ. ቆርቆሮ ለ. ብር ሐ. መዳብ መ. ጠጠር

27. ወተት ለእንቦላ ________ ሰአንበላ
ሀ. ጠመንጃ ሰ. ጕራዴ ሐ. አሀያ መ. ሥጋ

28. ወርቅና ጨዋ ________ ነው
ሀ. ውድ ለ. እስታራቂ ሐ. የሚያደባድብ መ. አይገኝም

29. ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ________ ተበድሮ ሰሜዳ
ሀ. እሀያ ለ. ፈረሰ ሐ. በቅሎ መ. ሁሰም መልስ ነው

30. ወታደር ሲያረጅ ________ ይሆናል
ሀ. ጡረተኛ ሰ. ጠላ ጠጪ ሐ. አቃጣሪ መ. አቃቢ

31. ወተቷንም አለቅ ________ አይክላ
ሀ. ለውነቴም ለ. ጥጃዬም
ሐ. ልጄም መ. ሀ እና ሐ መልሰ ይሆናሉ

32. ወታደር ቢበደር ________ ይካሳ
ሀ. አለቃው ሰ. ሲቪሉ ሐ. ባላገር መ. ሁለም መልሰ ነው

33. ወታደር ባሰቃው ________ በጭቃው
ሀ. ባላገር ሰ. ጭቃ አቡኪው ሐ. ቤት ሠሪ መ. ባለጌ

34. ወየው ጉድ ________ ብርጉድ
ሀ. ሰኳርና ለ. ጨውና ሐ. ዕጣንና መ. ሁሰም መልሰ ነው

35. ወዳጅና ሥዕል ________ ያምራል
ሀ. በሐሳብ ለ. በቅርቡ ሐ. አካሔዱ መ. በሩቁ

36. ወዳጇን ብታይ ________ ጠላች
ሀ. ጠላቷን ሰ. ባሏን
ሐ. እናቷን መ. ሁሉም መልሰ ነው

37. ወጭትና ሴት ________ ይሻላል
ሀ. በነጠላ ለ. በቤቱ ሐ. ሲክናነቡ መ. በሩቁ

38. ወፍ እንደአገሯ ________
ሀ. ትበራለች ለ. ትጮሃለች ሐ. ትደንሳለች መ. መልሱ የለም

39. ወጥቶ አደር ________
ሀ. ይሔዳል በቆንጥር ለ. ይሔዳል በጫካ
ሐ. ይጓዛል ከገደል መ. ሁሰም መልሰ ነው

40. ወጥ ያጣ ጕመን አገር ያጣ ________
ሀ. ጫካ ለ. ሰሜን ሐ. ገደል መ. ደቡብ

41. ወጮ ቢያገላብጡት ________
ሀ. ወጮ ሰ. ሰብር ሐ. ገደል መ. መልሱ የለም

42. ውኃ አያንቅ ________ አያልቅ
ሀ. አገር ለ. ነገር
ሐ. እንጀራ መ. ሀ እና ሐ መልሰ ይሆናሉ

43. ውዝፍ፡ ለሹም ________ ለጅብ
ሀ. ቆመጥ ለ. አሀያ ሐ. ጥንብ መ. ሁሉም መልሰ ነው



44. ውኃ ጭሰና ክፉ ሴት ያባርራሉ ________
ሀ. ከቤት ሰ. ከት/ቤት ሐ. ከአገር መ. ሁሰም መልሰ ነው

45. ውኃ የሚወስደው ሰው ________ ይጨብጣል
ሀ. አየር ሰ. አረፋ ሐ. ሥር መ. ሁለም መልሰ ነው

46. ውጣ ከቤት ________ ከመሬት
ሀ. ተዳቀል ለ. ኑር ሐ. ሒድ መ. ግባ

47. ውድሽና ውዴ ________ ሥንዴ
ሀ. የበሉት ለ. የዘሩት ሐ. የለቀሙት መ. ሁሱም መልሰ ነው

48. ዓለም ተልባ ነው ________
ሀ. ይቆላል ለ. ሙልጭልጭ ነው
ሐ. ይንሸራተታል መ. ሁሉም መልሰ ነው

49. ዓሣ ለሠጋሪ ________ ለጀማሪ
ሀ. ነገር ሰ. ኮሶ ሐ. ከባድ መ. መልሰ የለም

50. ዓይን ሕመም ________ ይወዳል
ሀ. ፔኒሲሊን ሰ. አዋራ ሐ. መነጽር መ. ልግም

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. ዋርካ በሌለበት ዋጮ አድባር ይሆናል
ሀ. ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል
ለ. ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

2. ውሻ ወደ ጥጥ ሚዳቋ ወደ ሲጥ
ሀ. አጭር አሀያ ሁልጊዜ ውርንጭላ
ለ. አሀያ ወደ ጅብ ውሻ ወደግጦሽ የተገላቢጦሽ
ሐ. ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
መ. መልሉ የሰም

3. ዓሣ ጕርጓሪ ዘንዶ ያወጣል፣ የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
ሀ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ለ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሐ. በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ
መ. ሁሉም መልስ ነው

4. ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
ሀ. ዓይን መሪ ልብ መካሪ
ሰ. ያሳሰበ ተመነደበ
ሐ. ያልጠረጠረ ተመነደበ
መ. ሁሉም መልሰ ነው

5. ዓይን ካላዩበት ግንባር ነው
   ሀ. ሰልድ ከሣቁለት ሰውሻ ከሮጡለት
   ለ. ሱሚን ካልመጠጡት እንቧይ ነው
   ሐ. በኋላ የመጣ ዓይን አወጣ
   መ. መልሱ የለም

6. ውሻ ምናገባው እርሻ
   ሀ. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን
   ለ. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ
   ሐ. ፈረስ ቢያነክሰ አህያ ተኩስ
   መ. ሁሉም መልሰ ነው

7. ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውር ፍለጋ ይገባል
   ሀ. ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
   ለ. ሥራ ከመፍታት ልጄን ላፋታት
   ሐ. እፍ ሥራ ሲፈታ ወዳጁን ያማል
   መ. ሁሉም መልስ ነው

8. ወጥ ሰሠሪው እህል ለዘረው
   ሀ. ሥራ ሰሠሪው እሾህ ላጣረው
   ለ. ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን
   ሐ. የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
   መ. ነገረኛ ዱቄት ከነፋስ ይጣላል

9. ውኃ ቢወቅጡት እንቦጭ
   ሀ. ተመከሮ የማይሰማ፣ የማይሻሻል
   ለ. ውሰታ ቢሰ
   ሐ. ውኃ ሲወርድ ድምጽ ይኖረዋል
   መ. መልሉ የለም

10. ውኃ ሲወስድ እያሣሣቀ ነው
   ሀ. ዓመሰኛ ዓመሉን አይተው
   ለ. ከጉረቤት የተሰወረ ነገር የለም
   ሐ. ሰው በጭንቀት መኖር የሰበትም
   መ. መጥፎ ነገር የሚለመደው መጀመሪያ በቀልድ ነው



ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1.ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል | ሀ. የሀገርንና የወግን ፍቅር |
| 2.ወንድም ለግርግርታ ጋሻ ለመከታ | ለ. ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር |
| 3.ውኃ እድፍን ያጠራል ትምህርት ልብን ያበራል | ሐ. ረኻ'ም ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩበት |
| 4.ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው | መ. ሴት በዛ ጉመን ጠነዛ |
| 5.ወጼት ትሔዳለህ ወደ በሰሳ ለሌን የለህምሳ | ሠ. የመማርን ጠቀሜታ |
| 6.ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት | ረ. ባለቤት ባሳየው ሌላው ይከተላል |
| 7.ወጌሻ ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል | ሰ. ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጉረቤት |
| 8.ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል | ሸ. አዞ አንድም ተናዞ አንድም ሰንቅ ይዞ |
| 9.ዓይን ካላዩበት ግንባር ነው | ቀ. አህያ ካልተጫነ አሳማ ነው |
| 10. ዓባይ ማደሪያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል | በ. ሴት በዛ ጉመን ጠነዛ |
| 11. ውስጥ እግሩን የተሳመ | ተ. የአላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው |
| 12. ዐይን መሬ ልብ መካሪ | ቸ. ባፍ ይጠፉ በሰፈሰፉ |
| 13. ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደ አንድ ቀን እንደ እናቱ | ኀ. ሰራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ አባቱ ለመነ ላዋይ |
| 14. ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመስግናል | ነ. ወንድ ልጅ አንድ ቀን ይሸነፋል አንድ ቀን ደግሞ ያሸንፋል |
| 15. ወጥ ቤቶች ሲበዙ ወጥ ያበላሻሉ | ኘ. ዕድለኛ |
| 16. ዕውር ቢፈርዱ ዕውር ይወልዱ | አ. ዐይን አይቶ ልብ ይፈርዳል |
| 17. ዕዳ ቢያምርህ ዋስትና፣ ኩነኔ ግብዝና | ከ. በፈቃዱ ካልሠራ በግድ ቢያምርህ ሲሠራ አይችልም |
| 18. ወስፌ ሲሰግም ቅቤ አይወጋም | ኸ. ዕዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ አሉ |
| 19. ወዛም ይገማል ቢለው የነጭ ወሬ ነው አለ | ወ. እርሻ ቢፈርስ ካስታራቂው ድረስ |
| 20. ወሬን ከባላገር ጦርነት ከወታደር | ዘ. ወሬ ቢያምርህ በየሉሌህ |
| 21. ዕርቅ ቢፈርስ ካስታራቂው ድረስ | ዠ. ጠላት ይቀባል ጠላት |
| 22. ወዶ ገባ ውሻ ባለቤቱን አትግባ ይላል | የ. ከሀብታም ተወለድ ወይ ከሀብታም ተጠጋ |
| 23. ወፍ የሚፈራ ዘንጋዳ አይዘራም | ደ. ሳይደውል ቅዱስ |
| 24. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባዩ ቂጥ | ጀ. ሲፈሩ አይከሉ በጉጣ እያርሱ |
| 25. ወይ ካለው ተወለድ ወይ ካለው ተዛመድ | ገ. ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ |

# ዘ

ዘመነ ግልምቢጥ ውሻ ወደ ሰርዶ አህያ ወደ ሲጥ
- የተገላቢጦሽ ሆነ

ዘመን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል
- ጊዜ የፈቀደለት ደካማ ሰው የፈለገውን መፈጸም ይችላል

ዘመን የወለደው ንጉሥ የወደደው
- አዲስና በሰው ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፈ

ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው
- ባለብዙ ዘመድ ሀብት አያበጅም

ዘመዱን ያማ ገማ
- ዘመድን ማማት ያስገምታል

ዘመድ ሲጣላ ያረክሳል
- ውስጥ ዐዋቂ ብዙ ገመና ያወጣል

ዘመድ ሲፈራ ላሲበላ ሲከራ
- ዘመድ ለዘመድ መፈራራት የለበትም

ዘመድ በዘመዱ አይጨክንም ሆዱ
- ዘመድ ለዘመድ ይተዛዘናል

ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም አይጐዳ
- መረዳዳት ችግርን ያስወግዳል

ዘመድና መድኃኒት የተቸገሩ ዕለት
- እውነተኛ ዘመድ ለችግር ጊዜ ይደርሳል

ዘመድና ሚዛን ከወገብ ይያዛል
- እውነተኛ ወዳጅን አጥብቀው ይይዙታል

ዘመድና እሳት ሩቅ በሩቅ
- ዘመድን በሩቁ ነው

ዘመድና ዋንጫ እያለቀሰ ይመጣ
- ሰው ሲቸገር ወደ ዘመዱ ይሔዳል

ዘመድና ገንዘብ ሳያስቡት ይገኛል
- ሀብት የሚገኝበት ጊዜ አይታወቅም

ዘመድና ፍየል ቤት አጥፊ ነው
- ዘመድን በጣም ካቀረቡት ችግር ይፈጠራል

ዘመድን ከዘመድ ጋር ማማት ዳቦ መግመጥ ነው
- ምስጢር እንደተጠበቀ ይቆያል

ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጀንፎው አይለቀቅም
- አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሰበር

ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
- ዘመዳሞች ይረዳዳሉ

ዘመድ ያረጀ በልቶ ያፈጀ
- ያረጀ ያፈጀ ዘመድ ጠቀሜታው እጅግም ነው



ዘመዶችዋ ሁሉ ይኗታል ግንድ አልብሰ
- ለማንም ያላትን ሁሉ የምትሰጥ

ዘምቶ ተወረሰ
- ባለውለታው ሲበደል

ዘምቶ ያረጀ በልቶ ያፈጀ
- ብዙ ብዙ ነገሮችን ያየ

ዘረፋና ቀን ካልተሻሙበት ያልቃል
- ጊዜን በአግባቡ ተጠቀሙበት

ዘሩ የጣቴ ምድሩ ያባቴ
- በአባቴ መሬት ላይ ሠርቼ ለፍቼ ያገኘሁት

ዘር ልትበደር ሒዳ እህል ሲሸት መጣች
- ከተላከችበት ቦታ ዘገየች

ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም
- ጠንክሮ የሠራ ውጤቱ ያማረ ነው

ዘርቶ ያልበላ ዓምላክን ጠላ
- ሥራ ሠርቶ ጥሩ ውጤት ያላገኘ ዓምላክን ያማርራል

ዘር ከልጓም ይስባል
- ሰው ከባዕድ ይልቅ ለዘመዱ ያደላል

ዘር ከልጓም ይጠቅሳል
- ሰው ከባዕድ ይልቅ ለዘመዱ ያደላል

ዘባራቂ ላባ ቀረሽ ዕብድ አስተኔ
- ዕብድ ራሷን የሳተች

ዘባራቂ ይወዳል ምራቂ
- የሆነ ያልሆነውን የሚያወራ የሱን ዓይነት ሰው ይወዳል

ዘንዶ የዳገት በረዶ
- ከፉና አስጨናቂ ችግር

ዘንጋዳና ወታደር በመከር ጊዜ ይታይ ነበር
- በሚበላበት ጊዜ የሚታይ

ዘንጋዳ ከቆረጡት አገዳ ሚስት ከፈቷት ባዳ
- አንድ ነገር አንዴ ከተበላሸ መመለሻ የለውም

ዘንጋዳ ከቆረጡት አገዳ ዕዳኛ ከደረሱ ዕዳ
- አንዴ በተፈጸመ ወንጀል ከተከሰሱ መቀጣት አይቀርም

ዘንጋዳ የገለጠበ አባቱን የገላመጠ
- አባቱን የሚገላምጥ ሰድ አደግ ነው

ዘንግ ከተተከለ ልብ ተከፈለ
- ያቺንም ያቺንም ከተመኙ ሐሣብ መከፈሉ አይቀርም

ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር
- አንድ ነገር ላይ ሲያተኩሩ ሌላው ይዘነጋል

ዘገየች ከረመች ቆይታ መጣች
- በሔደችበት ቀልጣ ቀረች

ዘጠኝ ሞት መጣ ቢለው አንዱን ግባ በለው አለው
- የመጣውን ችግር ታግሶ መቀበል ነው

ዘጠኝ ድሃ ዘመድ ያለው በዓመቱ አራሱ አስረኛ ይሆናል
- ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው

ዘጠኝ ጠጥቶ አሥረኛውን የወደደ ነደደ
- መጠኑን ያለፈ ነገር አደጋ ያስከትላል

ዘጠኝ ጠጥቶ አሥር የወደደ ዘጠኙ ተናደ
- አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

ዘፈን በበገና፣ ነገር በዋና
- ሁሉም ነገር ከተሟላ ያስደስታል

ዘፈን በከበሮ አዋጅ በደበሎ
- ሁሉም ነገር ከተሟላ ያስደስታል

ዘፈን አለ በገና፣ ነገር አለ በዋና
- ሁሉም ነገር በወቅቱ ሲደረግ ያስደስታል

ዘፍኖ አያምር፣ አንኳን አልቅሶ
- ሁሉ ነገር ያስጠላበታል

ዘጥ ዘጥ አቁማዳ ቂጥ
- ዘዋሪ አውደልዳይ

ዘር ልመና ሳይዙ ገና፣ ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ
- አንድ መጥፎ ነገር ሥር ሳይሰድ ነው ሥር ከሰደደ በኋላ ያስቸግራል

ዛብ የሌለው ፈረሰኛ፣ ምላ የሌለው ኮሰኛ
- ዛብ የሌለው ፈረሰኛ መቆሚያ መቆጣጠሪያ ስለሌለው ለአደጋ ይጋለጣል

ዛፍ ሊወድቅ ከግንዱ፣ ሰው ሊቸገር ከዘመዱ
- ምንም ቢጠብ መንገድ ምንም ቢከፋ ዘመድ

ዛፍ በሌለበት፣ እንቧጮ አድባር ይሆናል
- ዛፎች ቢጠፉ ቁጥቋጦች ተለሰፉ

ዛፍ ዝናብ ያስጥላል፣ ትልቅ ሰው ከዕዳ ያስጠላል
- ትልቅ ሰው ለአካባቢው ሰው ጥላ ነው

ዛፍ ያለቅርንጫፍ አይደምቅም፣ ሰው ያለሰው አይከብርም
- ሰው ማኅበራዊ እንስሳ በመሆኑ ሰው ያለሰው አይኖርም

ዛፎች ቢጠፉ ቁጥቋጦች ተለሰፉ
- ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል

ዜማ በሐሌ ነገር በምሳሌ
- ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ

ዝሆኑ ሳለ ዱካው
- ግንድ አያለ ቅርንጫፍ ፍለጋ መሔድ

ዝሆን ለቀንድ፣ ብላባት ለትውልድ
- ዝሆን ለቀንዱ እንደሚፈለግ ሁሉ አባትም በልጆቹ ዘንድ ተፈላጊ ነው



ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል
- አስተማማኝ የሆነ ነገር ካለ ምንም ማድረግ ይቻላል

ዝሆን እነሆ ፍለጋው ወዴት
- እጠገብህ እያለ ፍለጋው ለምን ተብሎ

ዝሆን የዋለችበትን ትመስላለች
- ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች

ዝሆን ጥርሱን አዝመራ ገብሱን
- እንዲህ በዋዛ የማይሰጥ

ዝም ማለት ከሞኝ ያስቆጥራል
- ካልታረደ አይታይ ስባቱ፣ ካልተናገረ አይታወቅ ብልሃቱ

ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም
- ዝም በማለት የሚመጣ ችግር የለም

ዝምብ ሲያቆሙ፣ ዝግን አይቅሙ
- አንድን መጥፎ ነገር ለማስወገድ ያ መጥፎ ነገር የሚወደውን አለማቅረብ

ዝምብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም
- አንድን ጠንካራ ሺ ልቃም አይደፍረውም

ዝምብ እሩቅ አይበር የሜዳ ልጅ ዱር አይደፍር
- ያላዩት አገር አይናፍቅም

ዝምብ ከዓይን ጭራ ከዘባን
- ማንኛውም ጥቅም ወደሚያገኝበት ያመራል

ዝምታ ሰበግም አልበጃት አሥራ ሁለት ሆና አንድ ነብር ፈጃት
- ሕመሙን የማይናገር በሽተኛ ፈውስ መጋኛ

ዝምታ ወርቅ ነው መናገር ብር ነው
- ከመናገር ማዳመጥ ይበልጣል

ዝም አይነቅዝም
- ዝም ማለት አያስንቅም

ዝም ያለ ተንኮለኛ ይመስላል፣ እንብላ ያለ ስስታም ይመስላል
- ጠጋ ብለው ሳያጣሩ በግምት መናገር ተገቢ አይደለም

ዝርክርክ ከወንፊት የባሰ ዝክዝክ
- ወሬኛ ነው ምስጢር አይደብቅም

ዝቅ ቢል ከገብርዬ ከፍ ቢል ከዚያ ስውዬ
- ሰውዬው የሚናቁ ሳይሆኑ የተከበሩ ናቸው

ዝባድን ከውሻ አምነትን ከባለጌ አትሻ
- ባለጌን ፈጽሞ አትመነው

ዝናር የሌለው ነፍጠኛ አለንጋ የሌለው ፈረሰኛ
- ለሁሉም መሣሪያ ያስፈልጋል

ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር
- እንደየሥራው ሁኔታ የተለያዩ የአየር ጠባዮች ይመርጣሉ

ዝናብ ሊጥል ሲል ይነፍሳል
- ክፉ ነገር ሊመጣ ሊደርስ ሲል መንፈስ ይጨነቃል

ዝናብ ሲያባራ ከዋሻ ምን ሊሻ
- ጅብ ካለፈ ውሻ ጮኸ

ዝናብ ሳይመጣ ገና የውኃ መንገድ መጥረግ ደህና
- አንድን ነገር በቅድሚያ ከሠሩት ጥሩ ነው

ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሌት
- የአንድ ነገር ትልቅነቱ የሚታወቀው ፊታኝ ጊዜ ሲመጣ ነው

ዝናብና ልጅ ሲጠሉት ያከብር
- የጠሉት ነገር አንዳንዴ ለችግር ጊዜ ይሆናል

ዝናብ ከደመና ነገር ከዋና
- ተባራሪ ወሬ ከመስማት ከምንጩ የሰሙት አስተማማኝ ነው

ዝናብ ካባራ ወደ ዋሻ
- ጅብ ካለፈ ውሻ ጮኸ

ዝንጀሮ መቀመጫዬ ይብሳል አለች
- ቀደምትነት ያለው ነገር ቅድሚያ ይሰጠዋል

ዝንጀሮ ሰው ነበር ይላሉ ዱሮ
- አልፎ አልፎ የሰው ባሕርያት ስለሚታይበት

ዝንጀሮ ቢሰበሰብ ውሻ አይመክትም
- ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም

ዝንጀሮና ጥዋ፣ ካፉ ነው የሚያዝ
- አንድን ነገር ተጠንቅቀው ካልያዙት ከባድ ችግር ያስከትላል

ዝንጀሮን በበግ ለውጠኝ ቢለው ጣፋጩን ትቼ አልማጩን
- የተሻለውን ትቼ ያልተሻለውን

ዝንጀሮ እንሣሣቅ ካልሽ ነዶዬን መልሽ
- ለው ከተማመነ ከልብ መሆን አለበት

ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ በባልንጀራዋ ትሥቃለች
- የራስን ስንፍና ሳያዩ በሰው ስንፍና ማሾፍ አይገባም

ዝንጅብል ማን ጋ ቢሉህ ማነኝ ትል
- ማንነትን አጥርቶ ያለማወቅ ችግር ላይ ይጥላል

ዞር አሉ አልሸሹም
- አልተደበቁም

ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ
- ለውጥ የሌለው ነገር

ዞሮ ዞሮ አራቱ ጥፌ
- ለፍቶ መና

ዞሮ ዞሮ የዶሮ አንገት በማለሮ
- መጨረሻው አያምር



## መልመጃ 12 /ዘ፣ጀ/

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. ዘመደ ብዙ ________ ነው
   ሀ. ድንጉጥ ለ. ኃይለኛ
   ሐ. ጠላው ቀጭን መ. መልሱ የለም
2. ዘመድ ሲፈራ ______ ሲከራ
   ሀ. ጠላት ለ. ድሃ ሐ. ሀብታም መ. ላሲበላ
3. ዞሮ ዞሮ ________
   ሀ. አራቱ ጥፌ ለ. ከቤት
   ሐ. መዝጊያው ጭራሮ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ
4. ዝባድን ከውሻ ______ከባለጌ አትሻ
   ሀ. ውለታን ለ. እምነትን
   ሐ. ገንዘብን መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ዞሮ ዞሮ ________ በማለሮ
   ሀ. ንፍሮ ለ. ድንች
   ሐ. የዶሮ አንገት መ. ሁሉም መልስ ነው
6. ዝናብና ልጅ ______ ያከብር
   ሀ. ሲያቀርቡት ለ. ሲንከባከቡት
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ መ. ሲጠሉት
7. ጅብ እንደ አገሩ ________
   ሀ. ያነከሳል ለ. ይራመዳል
   ሐ. ይጮሃል መ. ሁሉም መልስ ነው
8. ጀሮ ______
   ሀ. ባዳ ነው ለ. ደነቆረ
   ሐ. ይሰማል መ. ለባለቤቱ ባዳ ነው
9. ጅብን ፈርቼ ______
   ሀ. እጉረቤት ተቀምጬ ለ. ከሚያለጥለኝ ተጣልቼ
   ሐ. ዛፍ ላይ ብወጣ ነብር ቆየኝ መ. መልሱ የለም
10. ጆሮ አይጠምም ________
    ሀ. አፍ ተሳዳቢ ነው ለ. ዓይን አይጠግብም
    ሐ. ሆድ አይጠግብም መ. መጠጥ አይጠገብም
11. ዘመድና ገንዘብ ________ ይገኛል
    ሀ. ጸባይ ካለ ለ. ጉልበት ሐ. ከሥራ መ. ሳያስቡት
12. ዘሩ የጣቱ ________ ያባቱ
    ሀ. ውርሱ ለ. ልምዱ ሐ. ጸባዩ መ. ምድሩ
13. ጅብ የኔ ነው ለለው ______
    ሀ. ከዳኝ ለ. በላኝ ሐ. አሾፈብኝ መ. የሌላ ሆነ

14. ዘርቶ መቃም __________ መሳም
ሀ. ሴት ለ. ቆንጆ ሐ. ጋለሞታ መ. ወልዶ

15. ጅብ እስኪነክስ __________
ሀ. ይፈራ ለ. ያደፍጥ ሐ. ይሸሽ መ. ያነክስ

16. ዝናብ ሲጥል ሲል __________
ሀ. ያስታውቃል ለ. ጉም ይሆናል
ሐ. ይነፍሳል መ. ሁሉም መልስ ነው

17. ዝምታ ______ ነው
ሀ. የተቃውሞ መግለጫ ለ. ጥሩ
ሐ. ወርቅ መ. ሁሉም መልሰ ነው

18. ጅብ እንደአባቱ ይዘረጥጥ ______ አንደአባቱ ይፈረጥጥ
ሀ. ሞኝ ለ. ፈሪ ሐ. ፈረስ መ. አህያ

19. ጅብን ሲወጉ ________ ይጠጉ
ሀ. ክውሻ ለ. ከአንበሳ ሐ. ከአህያ መ. መልሱ የለም

20. ዘመን የወለደው __________ የወደደው
ሀ. እግዜር ለ. ሰይጣን ሐ. ንጉሥ መ. መልሱ የለም

21. ጆምሮ ይጨርሳል __________ ይተኩሳል
ሀ. ለጉሞ ለ. በእሳት ሐ. በዘፈቀደ መ. መልሱ የለም

22. ጆርባዬን አከከኝ __________ ራቀኝ
ሀ. ልጄ ለ. ለአኔ ሐ. አባቴ መ. ዘመዴ

23. ጃርት ያስደነገጠው ________ ይመስላል
ሀ. ጉመን ለ. ጫጩት ሐ. ዶሮ መ. ዱባ

24. ____________ ታደርሳለች ካናቷ
ሀ. ጃርት ለ. ጅራፍ ሐ. ጅራቷን መ. መልሱ የለም

25. ጅብን ለመግደል __________ ተጠለል
ሀ. በግንብ ለ. ከምሽግ ሐ. ከውርንጭላ መ. ከአህያ

26. ጅብ ካኮተኮተ _______ ከተከተ
ሀ. ሰው ለ. አህያ ሐ. ፈረስ መ. ሁሉም መልስ ነው

27. ዝምብ ከዓይን ______ ከዘባን
ሀ. የጽድ ቅጠል ለ. የባህር ዛፍ ቅጠል
ሐ. ጭራ መ. ጀንያ

28. ዝም ማለት ________ያስቆጥራል
ሀ. ከብልጠት ለ. መሰሪ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ መ. ከሞኝ



29. ዛፎች ቢጠፉ ______ ተሰለፉ
ሀ. ቁጥቋጦች ለ. ዐረሞች
ሐ. አምቧጮች መ. ሁሉም መልሰ ነው

30. ዘርቶ ያልበላ ________ ጠላ
ሀ. ጠላቱን ለ. ወዳጁን ሐ. ወላጆቹን መ. ዓምላክን

31. ዝንጀሮ አንሣሣቅ ካልሽ __________
ሀ. ነዶዬን መልሽ ለ. ከበሮዬን መልሽ
ሐ. ጸባዬን መልሽ መ. ልጄን መልሽ

32. ጅብ ጥጆቹን ጠብቅ ቢባል ________ አለ
ሀ. አሺ ለ. ይጠፉብኛል
ሐ. ረዳት ይሰጠኝ መ. መልሱ የለም

33. ዘመድ ሲጣላ ______
ሀ. ያባብሳል ለ. ይለማመጣል
ሐ. ያረክሳል መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

34. ዘንዶ _______ በረዶ
ሀ. የሜዳ ለ. የዳገት ሐ. የጫካ መ. ሁሉም መልስ ነው

35. ዘኬውን ሲቋጥር __________
ሀ. ጅብ ጉበኘው ለ. ዝሆን ረገጠው
ሐ. አነቀው ነብር መ. መልሱ የለም

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. ጅብን ፈርቼ እዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ
ሀ. አውሬ ክዋሻ በሬ ከእርሻ
ለ. ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት
ሐ. ሁሉቱን የተመኘ አንዱንም አላገኘ
መ. ብነጨው ፈቴን ብመታው ደረቴን

2. ዘርተሀ ዘርተሀ ሥንዴንና አንክርዳድን ለይ
ሀ. ክፉና ደጉን ለይ
ለ. ሲያጌጡ ይመላለጡ
ሐ. የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ
መ. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

3. ዝም አይነቅዝም
ሀ. የነገር ወጡ ማዳመጡ
ለ. የቡና ለባቱ መፈጀቱ
ሐ. መናገር ብር ነው ዝምታ ወርቅ ነው
መ. መልሱ የለም

4. ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም
   ሀ. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ
   ለ. የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ነው
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ
   ሀ. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ
   ለ. ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ
   ሐ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
   መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
6. ዘር ከልጓም ይስባል
   ሀ. እጅና አፍ አይተጣጡም
   ለ. ልጅን መቅጣት በጡት
   ሐ. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
   መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ
7. ጀርባ ለባለቤቱ ባዕድ ነው
   ሀ. ከርሞ ጥጃ
   ለ. የማሉሽን በለማሽ ገበያም ባልወጣሽ
   ሐ. እግር የላት ከንፍ አማራት
   መ. የጋራ ወንገራ
8. ዛፎች በሌሉበት አንፏጮ አድባር ይሆናል
   ሀ. ጋኖች እለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
   ለ. የደሃ ብርቁ ማለሻ ብርቁ
   ሐ. ከሰው መርጦ ለሹመት ከዕንጨት መርጦ ለታቦት
   መ. ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል
9. ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም
   ሀ. ለጡ ካልተናገረ ክፉ አይወጣውም
   ለ. ከመናገር ማዳመጥ ይበልጣል
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. መልሉ የለም
10. ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው
   ሀ. ባለ ብዙ ዘመድ ገንዘቡ አይበረክትም
   ለ. ባለ ብዙ ዘመድ ጠላው አይጣፍጥም
   ሐ. ባለ ብዙ ዘመድ ጠላጡ ቶሎ ያልቃል
   መ. መልሱ የለም



## የ

የሀር ገመድ የበቅሎ ክበድ
- ሲሆን የማይችል

የሀብታም ልጅ ሲጫወት የደሃ ልጅ ይሞታል
- ያጣ እንደተቸገረ ይሞታል

የሁለት ሴቶች ባል ይሞታል ይበላል ሲባል
- ሳይሳካ ከንቱ ልፋት

የሁለት አገር ስደተኛ
- ከሁለት ያጣ

የሁለት ዕዳ ከፋይ
- ከአቅም በላይ የሆነ

የሆነ አይመለስ እሳት አይጐረስ
- የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ

የሆድ ማበድ ያሥቃል በግድ
- ችግሩ ሲጠና ያስጨንቃል

የሆድ ምቀኛ አፍ ነው
- ፍላጐትን ግልጽ ካሳደረጉት መፍትሔ የለውም

የሆድ ብልሃት የጋን መብራት
- ችሎታን በሥራ ላይ ካላዋሉት ዋጋ የለውም

የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል
- ለሚቀርቡት ለው መከራከር ያለ ነው

የለመነ መነመነ
- የማይጠረቃ የማይሻሻል

የለመነ ያገኛል የነገደ ያተርፋል
- ሰው በጥረቱ የልፋቱን ያገኛል

የለመኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ
- አንድዬ ነው

የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ
- መጥፎ ልማድ ያዋርዳል

የለመደ መደመደ
- የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ
- ዓመል ያለበት ዓመሉን አይተውም

የለመደ እጅ ጆሮ ግንድ ያስመታል
- ሌብነት ያዋርዳል

የለመደ ፈረሰኛ ዛብ አይጨብጥ እርካብ አይረግጥ
- ልምድ ያለው ሰው በሥራው ላይ አይጨነቅም ነገሮችን በቀላሉ ይሠራል

የለማኝ ለማኝ ቁርንጮዬን ቀማኝ
- ለምኜ ያገኘሁትን ሌላ ለው ወለደብኝ

የለማኝ ስልቻ ሲንከባለል ከለማኝ ደጅ ይጠድቃል
- ቂጥኛም ከውርጄ

የለም ቀረ ካለ ፈጣሪ
- የሁሉም ሰጣ ሞት ነው

የለበለ የማንንም ጉረስ
- ልብስ ያስከብራል

የለበሱት ያልቃል የሰጡት ያጸድቃል
- የተቸገረን መርዳት ይገባል

የሊጋስ ምስክሩ መስጡቱ
- ቸር ሰው በደግነቱ ይታወቃል

የሳሚ ልጅ ያውራዬ ውሳጅ
- የሳም ልጅ ወተት በመባል ይታወቃል

የሳም መንጃ የሽማ መከንጃ የማር መቅጃ
- ለሁሉም የሥራ መሣሪያ አስፈላጊ ነው

የሳም ወተቱን የጌታ ኩበቱን
- ዋናው ተፈላጊ ነገር

የሳከ እንደ እፉ ያከከ እንደ እጁ አይሆንለትም
- ሁሉም ባለው አይጸናም

የሳም ለምጡን የውስጥ ዕበጡን ባለቤቱ ያውቃል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

የሳይኛው ከንፈር ለከርከር የታችኛው ከንፈር ለምስክር
- ሽማ በየፈርጁ ይለበሳል

የላይ አልጋ የውስጥ ቀጋ
- እሰስት ጸባይ ነው ያለው

የላጭን ልጅ ቅማል በላው ያናጢን ልጅ ጅብ በላው
- የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው

የሌለው ልብ የለው ወዳጅ የለው
- ድሃን የሚያስጠጋው የለም

የሌለው ሚስት የለው ወዳጅ የለው
- ድሃን እሚወዳጀው የለም

የሌሊት ግስገሳ የቀን ዘለሳ
- አመቺ ጊዜንና ሁኔታን መጠበቅ

የሌሳት አራት ደግሞ ምሳ አማራት
- ምንም ሳይኖራት ደሞ ሌላ ነገር አማራት

የሌባ መኘታው ካመድ መታሰሪያው ገመድ
- የሰው ንብረት የሚሰርቅ ክብር የሰውም

የሌባ ሞኝ ከጐተራ ሥር ይገኛል
- ሞኝ ሌባ ብልጠት ስለሌለው ይያዛል

የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ
- የሌባን ረዳት አብረህ ቅጣ



የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ
- እንዳጠፋ ዕያወቀ ይከራከራል

የሌባ እጁን የፍየል ልጁን
- ሌባን ሁለተኛ እንዳይለምደው አይቀጡ ቅጣት ቅጣው

የልመና በሬ ትክክል አይሔድም
- የልመና በሬ ወደአገሩ ይሰባል

የልመና እንጀራ ምን ጊዜም ከልመና አያወጣም
- የሰው ጥገኛ ሆኖ መኖር ራስን ያስንፋል

የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይሥቃል
- በነገሩ የመግባባትና ካወቁብኝ ዓይነት አሣሣቅ ነው

የልብህን ቢነግሩህ እለ ዕዳ ቢለቁህ
- አንድ ሰው ያለ ዕዳ ሲለቀቅ የሚደሰተውን ያህል የልቡን ሲነግሩት ይከፋዋል

የልብ ሳይደርስ ዕድሜ ይደርስ
- ምኞትና ተግባር አይጣጣሙም

የልብሰ ቀሳል ባለቤቱን ያቀሳል
- ወፈር ያስ ልብስ ሲያስከብር በትትክክለኛ ቋንቋ አለመጠቀም ተናጋሪውን ያቀለዋል

የልጅ ልጅ አህል ፈጅ ኋላም ጅብ ያስፈጅ
- በአጉል አሰተዳደግ ያደገ ልጅ ዳተኛ ይሆንና ለችግር መንስኤ ይሆናል

የልጅ መልክ ጥፉ በስም ይደግፉ
- ከእንጀራው የለሽ ከወጡ የለሽ ከጠላው የለሽ እንዲያው ልኬለሽ

የልጅ ማደጊያ በመስክ ያድራል
- ንብረት ከቤት ውጪ ነው የሚገኘው

የልጅ ሞት የአግር እሳት
- የልጅ ሞት ያንገበግባል ቶሎ አይረሳም

የልጅ ቀሳቢ የአህያ ጋሳቢ
- ዘልቆ አይዘልቅ

የልጅ ብልጥ የፊት የፊቱን እየቀደመ ይውጥ
- ብልጥ ልጅ የለጡትን እየበላ ያለቅሳል

የልጅ ተሟጋች በፊት ሰማይ ያያል ኋላ መሬት
- ልጅ አቅሙን ስለማያውቅ ሁሉን ነገር አድርጉልኝ ይላል

የልጅ ተሟጋች ጧት ሰማይ ሰማይ ማታ ምድር ምድር ያይ
- ልጅ የቤተሰቡን ጓዳ ስለማያውቅ ሁሉን ነገር አድርጉልኝ ይላል

የልጅቷን ሥጋ በእናቷ ቅቤ
- መሠረቱ ከአንድ ምንጭ የሆነ

የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ
- ዐዋቂ ነው ሲሉት ሕፃን ሕፃን፤ ነው ሲሉት ብስለት ያሳያል

የልጅ ነገር ጥሬ በገል
- ከሕፃናት ቁም ነገር አይጠበቅም

የልጅ እንግዳ ማንን ይጎዳ

- ለልጅ የሚወጣ ገንዘብ አይቆጭም

የልጅ ክፉ ዲቃላ የቤት ክፉ ለቀላ የልብስ ክፉ ነጠላ

- ችግር ይገፋል ባቄላ፣ ጥቃት ያወጣል ዲቃላ፣ ከደህና ያደርሳል ለቀላ፣ ቀን ያሳልፋል ነጠላ ካወቁበትስ ሁሉም አይጠላ

የልጅ ፍቅር የሴት ከንፈር እናትም አያስቀብር

- ልጅ በጣም ተወዳጅ ነው

የሎሌ አልቃሽ የሴት ቀዳሽ የቄስ አውደሸዳሽ

- ሰው መሠማራት ያለበት በየሙያው መሆን አለበት

የሐምሌ ብራ የባልቴት ወበራ

- ወቅቱን ጊዜውን ጠብቆ ያልተከናወነ ነገር

የሐምሌን ውኃ የኀዳርን ራብ የሚያውቅ ያውቀዋል

- ያልተቸገረ ሰው ችግርን አያውቀውም

የሕልም ሩጫ የጨለማ ፍጥጫ

- ምንም የማይደረስበትና ውጤት የማይገኝበት

የመልኳን ሲኳት የጠባይዋን

- ሁለ ነገሯ የተበላሸ ነው

የመሬት ሴሰኛ ከመንገድ ዳር ይተኛ

- ሴሰኛ ያያትን ሁሉ የሚመኝ በመሆኑ ለምኞቱ ይረዳው ዘንድ መንገድ ዳር መተኛቱ ለእርሱ ይጠቅመዋል

የመሬት እርጥብ እሸቱን ደረቅ ምርቱን

- እሸቱን በርጥበቱ ምርትን በደረቁ መሬት ትሰግስናለች

የመስከረም ውስጡ በጋ ያረመኔ ልቡ ቀቃ

- መጥፎ ሰው ልቡ በሙሉ በተንኮል የታጠረ ነው

የመቀናጆ በሬ ሲመሽ ወደቤቱ ይስባል

- የእራሰ ያልሆነ ነገር አያረካም

የመበደሪያ አፍ መክፈያ አይሆንም

- የመጀመሪያውና የመጨረሻው ሁኔታ አይመሳሰልም

የመተሩበት እጅ ይወዛል ያማከሩት ዳኛ ያግዛል

- ችግርህን ለሰው ካማከርክ መፍትሔ ታገኛለህ

የመታሰር ምልክቱ ተመያዝ የመሻር ምልክቱ መጋዝ

- አንድ ሰው ከታገዘ ወዲያ ማዕረግ የሌለው ነው

የመታሰር ምልክቱ መጋዝ የመዳኙት ምልክቱ መያዝ

- በሕግ ቁጥጥር ሥር ያለ ሰው መዳኘት የግድ ይላል

የመነነ ከዱር የሞተ ከመቃብር አይወጣም

- አንዴ ቆርጦ ለነፍሱ አድሮ ገዳም የገባ የከተማ ኑሮ አያምረውም

የመነኩሴ ሎሌ የክረምት እሞሌ

- እማይሆን ነገር

የመነኩሴ ፈራጅ

- ያሰቦታው ያለሙያ የሆነ ነገር



የመንማና የሰው ገናና

- የከሰመነ ሰው አይፈራም

የመንታ እናት ተንጋላ ትሞት

- ችግር ሲደራረብ ለአደጋ ይዳርጋል

የመንገድ ዳር እሸት ባል የሌላት ሴት ለማንም ናት

- ትዳር የሌላት ሴት ትደፈራለች

የመከሩበት ሞት የወረወሩበት ተሳት

- ዒላማው ያልመታ ግቡን የሳተ

የመከራ ሌሊት አያልቅም

- ችግር ሲደርስብህ ሌሊቱ አይነጋልህም

የመከራ ልጅ ሁልጊዜ መከራ መሰሎ ይታያል

- በችግር ጊዜ የተወዳጁት ያንኑ የመከራ ጊዜን ያስታውሳል

የመከራ ሎሌ መከራ መስሎ ይታያል

- ያንኑ የመከራ ጊዜን ያስታውሳል

የመከራ ውዝፍ ያለበት ነጋዴ ከሚወረር አገር ይደርሳል

- ለመከራ የፈጠረው ቢነግድ አያተርፈው

የመከራን ጉድጓድ ሚዳቋ አትዘለውም

- ከባድ አደጋን ጉብዝ እንኳን ሊቋቋመው አይችልም

የመኮንን ልጅ በከተማ የድሃ ልጅ በውድማ

- ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

የመኮንን ልጅ አዘን ቢነግሩት አደን

- ችግር ደርሶበት የማያውቅ ሰው ስለችግር ምንም አያውቅም

የመዝሙር መጀመሪያ ሐሌታ የዘፈን መጀመሪያ እስክስታ

- የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው

የመጠጡት ቅልጥም ከብርንዶ ይጥም

- በራስህ ተነሳሽነት የምታደርገው ነገር ይወደዳል

የመጣ ቢመጣ ከቤቱ አልወጣ

- ያግደለኝ እንጂ አልሄድም

የመጥረቢያ ልጅ መዘለፊያ

- የጀግና ልጅ ፈሪ

የሙሽራ ዕድሜ ቢያጥር የሠርጉ ድግስ ሆነ ለተዝካር

- ለእንዱ ያሰቡት ለአንዱ ይሆናል

የሙት ቀናተኛ ሚስቱን አደራ ይላል

- ያልጋ ሴሰኛ ሦስት ያሰተኛ

የሙት አልቃሹ የሙት ወራሹ

- ለሙት አልቃሽ ለንብረትም ወራሽ አይታጣም

የሙት የለውም መብት

- አንድ ሰው ከሞተ ወዲያ በንብረቱ የማዘዝ መብት አይኖረውም

የሚሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ ቢሆን

- ቢቻል ኖሮ ብዙ ሥጋ ነበረው ለማለት

የሚመከተው ጋሻ የሚጠጋበት ዋሻ የለውም
- ለችግር ደራሽ የለውም መጠጊያ የለውም

የሚመጣውን እንድታውቅ ያለፈውን ዕወቅ
- ሁሉም ነገር መሠረት ስላለው ያለፈውን ማወቁ ይጠቅማል

የሚሞት ልጅ አንገቱ ረጅም ነው
- ከሁኔታው ያስታውቃል

የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ
- የሚያልፍ ነገር ስለሆነ ተጠንቀቁ

የሚሮጡበት ሜዳ የሚወጡበት ቀዳዳ
- ከደረሰበት አደጋ የሚያመልጡበት መንገድ ያስፈልጋል

የሚሠራ ምንም አያወራ
- ለወሬ ጊዜ የለውም

የሚሰርቀው ያጣ ሌባ ስላማዊ መስሎ ይገባ
- የፈለጉትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

የሚስት መናኛ የናት አገር ለማኝ
- ዞር ዞሮ ውርደቱ ያው ለባለቤቱ

የሚስት እምባሻ የጉረቤት ውሻ የደጅ እርሻ
- ንብረት በአግባቡ ካልተያዘ የሌላ መጠቀሚያ ይሆናል

የሚስት አሳቢ የጥድ በሬ ሳቢ ይስጥህ
- ትዳርህ ይባረክ ኑሮህ የደስታ ይሁን

የሚስት ወይዘሮ እርሻው ጋራ ዞሮ
- እመቤትነት ከሥራው ባሕርይ ጋር አልተጣጣመም

የሚስት ዘመድ የማር እንጉቻ
- የሚስት ዘመዶች ለባሏ ጥሩ አስተሳሰብ የላቸውም

የሚሸሹበት እምባ ሲሸሽ ተገኘ
- ለችግር ጊዜ ይሆናል ብለው ያስቀመጡት ነገር ሳይገኝ ቀረ

የሚበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
- ከተቸገረው ይልቅ ኖርት አጠቃቀሙን ያላወቀው ይበልጥ ይጐዳል

የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

የሚከርመውም የማይከርመውም በአንድነት ዝናብ ይሰምናል
- የነገውን የሚያውቀው እንድዬ ብቻ ነው

የሚካኤል ለስት ለገብርኤል ምኑ ነው
- ለአንዱ የሚያስደስተው ለሌላ ሰው ትርጉም ላይሰጠው ይችላል

የሚከድ ሰው እደራ ሲያስቀምጡበት እጅ ይነሳል
- ጅብ ላይ ሥጋ አይጫንም

የሚወዱትን አቅፍ የሚጠሉትን ንቅፍ
- የሚወዱትን እቅፎ የሚጠሉትን ነቅፎ

የሚውል ሆድ ማለዳ ያረግዳል
- ሥራን ሳይጀምሩት ተስፋ መቁረጥ



የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል
- ስራን ሳይጀምሩት ተስፋ መቁረጥ

የሚዛንን አባይ ለአሳት የዳኛን አባይ ለሰንሰለት
- አጭበርባሪ ሰው መቅጣት

የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል
- የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ያስጣል

የሚያልፍ ቀን የማያልፈውን ስም ይወርሳል
- የገንቦ ጠላ ባልና ሚስት አጣላ

የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ይስጣል
- የገንቦ ጠላ ባልና ሚስት አጣላ

የሚያልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ አሰች ልጆዋን ጉርፍ የወሰደባት
- ጊዜንና ቅዝምዝምን ጉንበስ ብለው ያሳልፉታል

የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ
- የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ

የሚያማ ጠበኛ ዘወር ይበል ክኛ
- ሐሜተኛ አጠገብህ ሆኖ አያማህም

የሚያስፈራውን ለሚነግርህ የሚያስቀዝነውን ንገረው
- ሳትሸበር የርስን ሸር አጢነህ የባሰ የሚያስፈራውን ንገረው

የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም
- ውጭውን አይተው መገመት አይቻልም

የሚያድግ ልጅ በእናቱ እጅ
- ያስእናት ያደገ ልጅ ጥሩ አይደለም

የሚያድግ ልጅ አትበድል የሚሞት ሽማግሌ አታታልል
- የሚያልፍ ውኃ አይውሰድህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ

የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ
- ለሚያልፍ ነገር ታገስ

የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል
- የሚጠግብ እንጀራ በመሶቡ ያስታውቃል

የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ
- የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታወቃል

የሚያፈስ ቤት ጨቅጫቃ ሚስት
- ከቤት ያስወጣል

የሚዳቋ ብዛት ለውሻ ሠርግ ነው
- የአይጦች ዝላይ ስነውሮ ሲባይ

የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሠርግ ነው
- የአይጦች ዝላይ ስነውሮ ሲባይ

የሚጠጉበት ገደል የሚንጠለጠሉበት ቅጠል
- ምንም ምን በሌለበት እንዳችም ተስፋ በማይገኝበት ሁኔታ

የሚጣፍጥ ምግብ ሲርብ የበሉት ነው
- የምግብ ማጣፈጫው ረኃብ ነው

የሚጮህ ውሻ አይናከስም
- ጉልበቱን በጩኸት ጨርሶታል

የሚፈልግ ያገኛል የሚተኛ ያልማል
- የተጋና የጣረ ሰው የትጋቱንና የጥረቱን ውጤት ያገኛል

የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ
- ዐውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም

የሚፈታ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ
- ዐውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም

የማሽላ ዘር ከነአገዳው ቸር
- ቅርንጫፉ አንደዛፉ

የማታ ማታ እውነት ይረታ
- እውነት ይቆይ እንጂ ይወጣል

የማታ ማታ ጭምት ይረታ
- ትዕግስት ያለው በመጨረሻ ያሰበበት ይደርሳል

የማታ ምግብ ለእንግዳ የጧት መጠጥ ለዕዳ
- ጧት የሚጠጣ ልማደኛ ጠጪ በመሆኑ ከዕዳ አያመልጥም

የማታ ሩጫ እንቅፋት ነው ትርፉ
- ግልጽነት በጐደለው ነገር ላይ ለመሥራት መሞከር አጉል ድካም

የማታርፍ ጣት አር ጠንቁላ ወጣች
- መቅበዝበዝ ያልታሰበ ችግር ማስከተሉ አይቀርም

የማታ አፍ ከጋን ይሰፋል
- በስካር የተወራ ወሬ አያስተማምንም

የማታድግ ውርንጫ እናትዋን ትመራለች
- ምጥ ለእናቷ አስተማረች

የማትሔድ መበለት ዞራ ዞራ ትሰናበት
- ቆራጥ ውሳኔ ያልወሰነ ሰው ከሁኔታው ይታወቃል

የማትረባ ፍየል ሀጠኝ ትወልዳለች ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች
- ከብዛት ጥራት ወሳኝ ነው

የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል
- ያላዩት አገር አያናፍቅም

የማትሸሸውን ባልንጀራ ዙረህ ዙረህ አትየው
- አንዴ የሆነው ሆኗልና አትጨነቅ

የማኅበር አሽከር በልቶም አይጠገን ታሞም አይድን
- የጋራ የሆነ ነገር ብዙ ጊዜ ትኩረት አያገኝም

የማነው እህል? ያሰኘሃል ክምር የማነው ቤት? ያሰኛሃል አጥር
- እህል በክምር ቤት በአጥር ያምራል

የማን እርሻ ብለህ እረስ የማን ሚስት ብለህ ውረስ
- ዋናውን ወይም መነሻውን ጠይቀህ መረዳቱ ተገቢ ይሆናል

የማን ዘር ጐመን ዘር
- በቤተሰቡ ወጥቷል



የማን ገበሬ ሹርባ ይሠራል
- የትኛው ጊዜ ተገኝቶ

የማያመሽ ባል ቅንድብ ይሰማል
- ሥራ ጠፍቶ ጢስ ይሞቃል

የማያምኑበት ተዘግቶ ይታወቃል ተከፍቶ
- ማንኛውም ነገር ምንነቱ ሲገለጥ ምስጢሩ ይታወቃል

የማያስተኛ ነግረውት ሳይተኛ አደረ
- ያሰቡት አይገድም

የማያበላ ቢገላምጥ አያሰደነግጥም
- ለማይጠቅምህ ሰው ቁብ የለህም

የማያበድር ደመኛ የማይመልስ ቀማኛ
- በልቶ ጠጥቶ ዝም የጋን ወንድም

የማያበድር ገዳይ የማይመልስ አባይ
- ውሸታም በተናገረበት አይገኝም

የማያዋጣ ባል ቅንድብ ይሰማል
- አገባሻለሁ ያለሽ ሳያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ

የማያውቁት ስድብ ከዘፈን ይቆጠራል
- የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል

የማያውቁትን መሥራት ከጥቅሙ ጉዳቱ ይብስ
- ያለ ዕውቀት ያለ ሙያ የሚሠራ ሥራ ውጤት አልባ ነው

የማያውቁት አገር አይናፍቅም
- ያላዩትን ያላወቁትን አይመኙትም

የማያውቅ ምን ያውቅ
- ያላዋቂ ምን ይላል ያሉትን መልስ ይላል

የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት
- ከፍፃሜ የማያደርሱት ነገር ለአደጋ ይዳርጋል

የማያድሩበት ቤት አያመሻሹበት
- ጊዜን በከንቱ ማባከን አያስፈልግ

የማያድግ ልጅ ባራሱ ቤቱ ዳንኪራ ይመታል
- የማያዛልቅ ማኅበር በጠጅ ይጀምራል

የማያግዙ በፈር ያግዛሉ በከንፈር
- በገንዘብ በጉልበት ባያግዙም በማስተዛዘን ይረዳሉ

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል
- የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል

የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል
- በሰው ቤት አጉል ድፍረ

የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ያንችን ላንቺ ማን አለሽ
- የአንዱ ለአንዱ የማይሆንበት ጊዜ አለ

የማይመለስ ማር ሹመኛ ይበደረዋል
- አንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ተናግሮ

የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር
- የማይታመን ነገር አታውራ

የማይሙት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
- ሲጠባ ደደገ ጥጃ ሲይዙት ያጓራል

የማይሰማ ሰው ልቡን አፈረሰው
- ቢነግሩት የማይሰማ አብሮት ያለውን ሰው ያስቸግራል

የማይሠራ አይብላ የማይረዳ አይጥላ
- ሠርተህ ጥረህ ግረህ በላብህ ወዝ ብላ ተብሎ ተነግሯልና

የማይስማሙ ዝንቦች ጥንብ ይልሳሉ የሚስማሙ ማር ይጉርሳሉ
- ስምምነት ፈጥረው የሚኖሩ ሰዎች ይጠቀማሉ

የማይቀና ባይወልድ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል
- መሻሻል የሚገኘው ጥሮ ግሮ በእቅድ በመመራት ነው

የማይበሉት እህል ከዐፈር እኩል ነው
- የኔነው የማይሉት ወርቅ ከብረት እኩል ነው

የማይበላ የሰም የማይጠግብ ባለ
- ማንኛውም ሰው ቢበላም የበላው ሁሉ ጠገበ ማለት አይቻልም

የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል
- ተጠራጣሪ ሰዎች እርስ በእርስ እምነት የላቸውም

የማይተች አይፈርድ የማያተርፍ አይነግድ
- ውጤት ለሌለው ነገር አትልፋ

የማይቻል ጠላት ስለወዳጅ ይቆጠራል
- የማትችለውን ጠላት አክብረህ መኖር አስብህ

የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ሲያወርዱት ጉልበት ይመታል
- የማይችሉትን ሥራ አለመሞከር ይመረጣል

የማይከፍል ባለዕዳ የሰጡትን ይቀበላል
- ብድርን እንደ ስጦታ ይቆጥረዋል

የማይዘልቅ ማኅበር በጠጅ ይጀምር
- የማያድግ ልጅ ባራስ ቤት ዳንኪራ ይመታል

የማይደርስበትን አያኩም
- የማይቻል ነገር አይሞከርም

የማይድን በሽታ በጥር እሸት አምጡ ይላል
- የሌለውን በሌለበት ፍለጋ መሔድ

የማይድን በሽታ የማይመለስ ኃጢያተኛ
- በጀመረው የሚቀጥል የማይለቅ

የማይድን ባሕታዊ ወተት አምጡ የማይድን ፋቅራ ጠላ ስጡ
- ካሉበት ቦታና ሁኔታ አንጻር ሊስማሙ የማይችሉ ነገሮች

የማይገባ ሉሪ የማይበቅል ዘር
- ልክነትና ሁኔታን መጠንን ያላገናዘበ

የማይገዙ በፊር ያግዛሉ በከንፈር
- በተግባር ቢቀርም በወሬ ማገዛቸው አልቀረም



የማይጠረጥር ቤቱን አያጥር
- በራስ የሚተማመን ጥበቃን አይሻም

የማይጣሱ መሳዕከት የማይታረቁ አጋንንት
- በአጋንንት ዘንድ ሁልጊዜ ግጭት መኖሩን

የማይጾፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
- ለተግባሩ አስፈላጊ የሆነው መሣሪያ መታጣት

የማይፈርስ ምሽግ የለም
- ሁሱም ፈራሽና ወዳቂ ነው

የማይፈነቅሰው ድንጋይ የለም
- የማይሞክረው ሙከራ የለም

የማይፈወስ ድውይ የማይመሰስ ጊጉይ
- ከከፋቱ ከተንኮሉ የማይመለስ ሰው ሁልጊዜ እንደተጨነቀ ነው

የማይፈጭ ማስጣት ሰዶሮ ማስበላት
- ቆጥ ሳይሠሩ ዶሮ

የሜዳ ንስንሱን የቤት ጉስጉሱን
- ከቤት ውጪ አምሮ መታየትና በቤት ውስጥ የተገላቢጦሽ መሆን

የምላስ ጦር ቢታከም አይድንም
- የዱላ ቁስል ሲድን የክፉ ንግግር ቁስል ምንጊዜም አይድንም

የምሮጥበት ሜዳ የምወጣበት ቀዳዳ የለም
- በዚህም በዚያም ምንም ማምለጫ የለኝም

የምስራች በቃሏ ወጣች
- የምስራች ቢቃሏ መላች

የምስጢረኛ ምላስ የለውም
- ምስጢረኛ ሰው አይናገርም

የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
- እኔውም የምበላው አጥቻለሁ ሌላ በላተኛ ደግሞ መጣብኝ

የምበላው እህል ከሚታየው መሬት ይስቅላል
- አንድ ነገር ከየት እንደሚነሳ ማወቅ አትችልም

የምትመክተው ጋሻና የምትለወርበት ዋሻ
- ከክፉ ነገር መደበቂያ ወይም መለወሪያ አዘጋጅ

የምትታጠቀው የሌላት የምትከናነበው አማራት
- መሠረታዊ ነገር የሌላት ሌላ ተመኘች

የምትነቃነቅ ግንድና የምትሥቅ ሴት ልብ ሩቅ ነው
- ሣቅ የደስታ ምልክት ነውና ብሩህ ቀን ይመጣል በማለት ታስባለች

የምትከነን ነፍስ ጉረቤት ያውቃል
- ከጉረቤት የሚሰወር ነገር የለም

የምትጠላው ሰው ፈሱ ሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል
- የጠሉት ሰው ምኑም አያምርም

የምትጠላውን የምትወደውን ለጥተህ ሸኘው
- በረቀቀ ዘዴ ከአጠገብህ አርቀው

የምትጠባ ጥጃ አትጮህም
- የፈለገውን ያገኘ ሰው ምንም ተቃውሞ አያደርግም

የምኞችን ፈረስ ልጓም አይገታውም
- የሰው ምኞት ሰፊ ነው

የምድሩን በአፍ የሰማዩን በመጣፍ
- በቅርብ ያገኘነውን እየተመገብን በመጽሐፍ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ለሰማዩ አባታችን እንጸልያለን

የምጣዱ እያየለ የእንቅቡ ተንጣጣ
- የተጐዳው እያለ የማያገባው ቡራ ከረዩ አለ

የምጥ መድኃኒቱ አንድ እግር ማስቀደም ነው
- ሁሉ ነገር የሚሠራው በዘዴ ነው

የሞላሰት ድመት ሣንባ ያማርጣል
- የደላው ሙቅ ያላምጣል

የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነው
- ሲያዩት አጅግ ያሳዝናል

የሞተ ቢሞት ያለን እንጫወት
- ከሞተው ጋር አብሮ አይሞትም

የሞተ አይከሰስ የፈሰሰ አይታፈስ
- አንዴ የሆነ ነገር ሲመለስ አይችልም

የሞተውን አያ ይሰዋል
- ያለፈውን ብትጠራው ወይም አይልህም

የሞተው ወንድምሽ የገደለው ባልሽ ኃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽም አልወጣ
- የተቆረጠው እጅሽ የቆረጠው እጅሽ እንግዲህ ምን ይበጅሽ

የሞተ ያልነበረ ይመስላል ያለ የማይሞት ይመስላል
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል

የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ
- ሞትን የሚዳኝ ዳኛ የለም

የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
- ሞኝ ነገር መደጋገም ይወዳል

የሞኝ መንገዱ አንድ ነው
- አማራጭን ያለመጠቀም ከሞኝነት ያስቆጥራል

የሞኝ ሚስት በምልክት
- ሞኝ ካልሆነ ምልክት ሊሸወድ ይችላል

የሞኝ ምስጋና የግንቦት ደመና
- ሞኝ ካመሰገነህ በኋላ መልሶ ይነቅፍሃል

የሞኝን ቂጥ ዶሮ ይጠቀጥቀዋል
- የሞኝን ገንዘብ ማንም ይበላዋል

የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር
- ሞኝ ሲማታ ቦታ አይመርጥም

የሞኝን ጠላ በሰው ባንኮላ
- የሞኝ ንብረት ማንም ነው የሚጠቀምበት



የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው
- በሆነ ባልሆነው በመሣቁ ጉዳት ደረሰበት

የሞኝ አሳሳፊ ለዘመድ አይሰጥም
- ይሉኝታ ዘመድ እንዲበደል ያደርጋል

የሞኝ እጁን ሁለት ጊዜ ነክሰው አንድ ጊዜ ሳያይ ሁለተኛው ሲያሳይ
- ካለፈው ስሕተት የማይማር ሰው ለተጨማሪ አደጋ ይጋለጣል

የሞኝ ዘመድ ያፍራል
- ሞኝ ማፈሪያ ነው

የሞኝ ዘፈን ሁለጊዜ አበባዬ
- ሁልጊዜ አይለወጥም አይሻሻልም

የሞኝ ጀርባ ሲመታ ለዐዋቂ ይስማማል
- ሞኝነት ወይም ድንቁርና ሲጠፋ ዐዋቂ ደስ ይለዋል

የሞኝ ገበሬ አርሻ በሰኔ
- ወቅቱን ጠብቆ አንድን ሥራ አለመሥራት

የሠራው ቢረሳ የተሠራው አይረሳ
- ወርቁ ቢጠፋ ሚዛኑ አልጠፋ

የሣር ክምር የጭሰኛ ክብር
- የሣር ክምር ትንሽ እሳት እንደምትበላው ሁሉ የጭሰኛ ክብርም ይህን ያህል አይደለም

የሥራ ቅሌት ያስለምዳል ሌብነት
- ለአንድ ሠራተኛ ሌብነት ከፍተኛ ቅሌቱ ነው

የሥንዴ ንፍሮ ያተር ድብልቅ፤ከዚያችው ወጥተው እዚያችው ጥልቅ
- እርስ በርሱ የተደበላለቀ የተቀየጠ

የሥንዴ አራራ የሴት መራራ
- የሴትን መራራ ማንም እንደማይፈልጋት ነው

የሥንዴ አራራ የቆንጆ መራራ
- መልክ ታጥቦ አይጠጣም

የሥጋ ልል ጭቅና፤ ያመትባል ትልቅ ገና
- ከዓመት በዓል ትልቁ ገና ነው

የሥጋ መድኃኒት ላም፤ የነፍስ መድኃኒት ማሪያም
- ማሪያም አማላጅ ናት

የሥጋ መጨረሻ አጥንት፤ የነፍስ መጨረሻ ግዝት
- አታድርግ የተባልከውን አለማድረግ ግዝትን መስማትና መቀበል ነው

የሥጋ መጨረሻ አጥንት፤ የነፍስ መጨረሻው የእግዛብሔር መንግሥት
- ከሞት በኋላ ሕይወትን ያመነ ነፍስ የምትኖረው በመንግሥተ ለማየት ነው

የሥጋ ቁራጭ፤ የብርሌ ጭላጭ
- ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ

የሥጋ ትል የዘመድ ጥል
- ከዘመድ ጋር ቂም አትያያዝ

የሥጋዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ
- ከአብራክ የተገኘ ልጅ

የረከሰ አይጠደድ የመነነ አይሰደድ
- መናኝ እንዲ መንኖ ገዳም በመግባቱ ማንም የሚያሳድደው የለም

የረዘመውን በጥፍር ያጠረውን በድግር
- በሚያመች መንገድ ሁሉ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

የረገመ የተረገመ
- ረጋሚ ደርጋሚ
- የሚራገም እራሱ የተረገመ ነው

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል
- እርጋታ ለሁሉም ነገር ጠቃሚ ነው

የሩቁን የሚመስከት የፊቱን ያፈሳል
- ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ

የራሱን ትቶ የሰው አክባሪ የበላበትን ወጪት ሰባሪ
- የራሱን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ

የራሱን እንዳይበላ ገንዘብ የለው የሰው እንዳይበላ ዓመል የለው
- ምንም የሌለው ደሃ ሆኖ በዚህ ላይ ደግሞ ጸባይ የለውም

የራሱን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ
- የራሱን ትቶ የሰው አክባሪ

የራስን ሳያውቁ ለሰው አይጨነቁ
- በሌላው ላይ አስተያየት ለመስጠት ከመነሳሳት በፊት ራስ በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል

የራስ ጌጥ ስለ ጨርቅ የሌለው ያስጨንቅ
- የአደራ ገንዘብ ያስጨንቃል

የራሷ ቢያርባት የሰው ታማስላለች
- የራስን ሳያውቁ ለሰው ይጨነቁ

የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ
- የራሷን ጥፋት በሌላ ሰው ለጠፈች

የራሷን ዐታውቅ የሰው ትንቅ
- አመድ በዱቄት ይሥቃል

የራበውን ገበያ አታውጣው
- ፍላጐት ሲበረከት ችግር መጋበዙ አይቀሬ ነው

የራበው ይጠግብ አይመስለው
- ለዚሁ ነው በሬዬን ያረድኩት እለ እለ /ገበሬ ርቦት በሬውን አርዶ/

የሰሰጠነ ሰየጠነ
- ሥልጣኔ የሰይጣን ሥራ ነው

የሰማዩ ንጉሥ እስኪረዳኝ የመሬቱ ንጉሥ ይጉዳ
- ከሩቅ ያለ የበላይ እስኪወሰን በቅርብ ያለ የቅርብ አለቃ ብዙ ይጉዳ

የሰማዩን ያህል እንጀራ ይስጥህ ብለው የኮከቡን ያህል በላተኛ አለበ፡ አለው
- ሀብት ሲበረከት የዚያኑ ያህል ችግር ሳያስከትል አይቀርም



የሰማይ ርቀቱን የምድር ስፋቱን የፀሐይ ድምቀቱን
- ያህል እንደምን አለሽ /እለህ/ ጥንታዊ የሰላምታ ደብዳቤ መግቢያ ነበር

የሰማ ይስማ ያልሰማ ይግማማ
- ካልሰማህ የራስህ ጉዳይ

የሰባን እርዶ የጠራን አውርዶ
- የቀረበን የተመቻቸን ነገር ጠጋ ብሎ እንደሚሆን ማድረግ ነው

የሰነፍ ምላስኛ የበሽተኛ በላተኛ
- ሥራ በወሬ ሳይሆን በተግባር ነው መሆን ያለበት

የሰነፍ አበላል ይበረድልኝ የሰነፍ ምክር ይማልልኝ
- ደካማ ሰው ሌላው ቀርቶ በሚመገበው ምግብ እንኳ ብርታት ያጣል

የሰከረ አወዳደቁ አያምር
- ራሱን የማይቆጣጠር ሰው አደጋ ያጋጥመዋል

የሰከረ ይተፋል የገደለ ይደነፋል
- ሰካራም እንደሚያስመልስ ሁሳ ገዳይም በሠራው ሥራ መፎከሩ አይቀርም

የሰው ሆዱ የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም
- ሰው ካልተናገረ በስተቀር ምን እንዳሰበ አይታወቅም

የሰው ልጅ መከራው እንጀራው ያልቅና ወጡ ይተርፍና
- አንድ ሰው ከአንድ ቤተሰብ ጋ ሲኖር እህል ውኃው ካለቀ እሱ መኖር ቢፈልግ እንኳ የተደመደመ ጉዳይ ይሆናል

የሰው ልጅ በምን ይታፈራል? በወንበር አይደለም በወንበር በከንፈር
- ከሁሉም በላይ የሚያስከብረው ሥልጣን ሳይሆን ከአንደበትህ የሚወጣው ንግግር ነው

የሰው ልጅ ቢወልድ ሎሌውን ባሰኔ ቢወልድ ጌታውን
- የጨዋ ልጅ ሁልጊዜ ጨዋ ነው

የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ
- ውሻ ጊዜ አይቶ የማይከዳ የጌታው ጽኑ ወዳጅ ነው

የሰው ልጅ ካለአገሩ ጉራዴ ካለሰፈሩ
- የሰው ልጅ በአገሩ እንጂ ከአገሩ ውጪ ክብር የለውም

የሰው መሠረቱ እናትና አባቱ
- ልጅን ኮትኩቶ ለማሳደግ እናትና እባት ወሳኝ ናቸው

የሰው መዋደጃው በየምድጃው
- የቀድሞ መኳንንት ከሠራተኞቻቸው ጋር በየምድጃው ስለሚባልጉ ነው

የሰው ማስጠንቀቂያ የመዝጊያ ማጥበቂያ
- አንዱን በደንብ አድርገው ከቀጡት ለሌላው ትምህርት ይሆናል

የሰው ምላስ መንታ አንዱ ለሙገሳ አንዱ ለሐሜታ
- ሰው እንደሁኔታው የወደደውን ሲያሞግስ የጠላውን ሲያማ ይውላል

የሰው ምኝ አንድ ዕንጨት ያስራል
- ውጤት በሌለው ሥራ ላይ ጊዜን ያባክናል

የሰው ሞኝ የአባቱን ሀብት ያወራል
- የቤተሰብ ሀብትን ከማውራት ራስ ሠርቶ ማግኘት

የሰው ሥጋ ቢጠብሱት ያራል ቢበሱት ይመራል
- ሠርተው ለፍተው ያላገኙ የሰው ገንዘብ ብዙ ትርጉም አይሰጥም

የሰው ቀላል እራሱ ይቀላል የልብስ ቀላል ባለቤቱን ያቀላል
- ባለጌ በራሱ ድርጊት ይቀላል

የሰው ቀላል እራሱ ይቀላል የልብስ ቀላል ለባሹን ያቀላል
- የምትሠራው ሥራ ወይ ያስከብርሃል ወይ ያዋርድሃል

የሰው ቁስል አይነዝርም
- የሰው ችግር እንደራስ ችግር አይታይም

የሰው ቃሪያ አስቲሞት ድረስ አይበስልም
- በተፈጥሮው ቢመከሩት የማይሰማ ሰው ዕድሜ ልኩን አይሻሻልም

የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ
- ደሞዝተኛ አርፌሀ አትተኛ

የሰው ባሕርይ ሳይደርሱ የድንጋይ ሥር ሳይምሱ
- ሰው ካልደረስክበት ባህርዩ ምን ዓይነት እንደሆነ ልታውቅ አትችልም

የሰው ቤት ሲቀጠቅ ቋያ ይመስላል
- በራስ ላይ ያልደረሰ ችግር ችግር መስሎ አይታይም

የሰው ብልሃቱ ለፈጣሪ መንገር ነው መድኃኒቱ
- የሰው ብድር አይቀርም በምድር

የሰው ታናሽ ያደርጋል ታናሽ
- ትንሽ ሰው ትንሽ ነው እንሶ ያሳንሳል

የሰው ታናሽ ይገዛል በግማሽ
- የሰውን ልክ የማያውቅ ሰው ሰውን ዝቅ አድርጐ ይመለከታል

የሰው ታናሽ ይጥላል ጭራሽ
- ትንሽ ሰው ሰውን ያዋርዳል

የሰው ነገር አለመናገር
- ሰውን ማመን ቀብሮ ነው አለች ቀብሮ

የሰውን በአህያ የራስን በጉያ
- ሰው የሰውን ጠባይ በይፋ ያወራዋል የራሱን በጉያው ይደብቀዋል

የሰውን ነገር ስንቱን ልናገር
- ሰው በሰው ላይ የሚሠራው ስንትና ስንት ክፉ ነገር አለ

የሰውን አባት የሚሰድብ አባቱን ያሰደብ
- የሰው አባት የሚሰደብ አባቱን የጠላ ነው

የሰው ዓመሉ ዳውላ ሙሉ መች ያስታውቃል አብረው ታልኖሩ
- አብረው ካልኖሩ የሰው ባሕሪ አይታወቅም

የሰው አባቱ ሸማ የሸማ አባቱ ጥለቱ
- ሸማ ወይም ልብስ ሰውን ያስከብራል

የሰው አትበይ ምግባር የለሽ የራስሽን አትበይ ገንዘብ የለሽ
- ምንም የሌላት ድሃ ሆና በዚህ ላይ ደግሞ ጸባይ የላትም



የሰው አገሩ ምግባሩ
- ሥነምግባር ያለው ሰው ከሰው ተስማምቶ መኖር ይችላል

የሰው አገር ዝናብና የእንጀራ አባት አይምታህ
- የእንጀራ አባት ባልተወለደ አንጀቱ ከመታህ ይጐዳሃልና ተጠንቀቅ

የሰው ዕርስት ከማልማት አይሻልም ወይ ያባት
- ሰሌላ ከማገልገል ሰራስ መልፋት ይሻላል

የሰው እጅ የግዜር ደጅ
- የሰውን እጅ ከመጠበቅ ከግዜር ደጅ መጠበቁ ይበልጣል

የሰው እንግዳ ያገር ባዳ
- የሰው አገር ሰው

የሰው ከማየት የራስን መብላት
- ከመመቅኘት ሠርቶ ማግኘት

የሰው ከርፋፋ ሲሰድቡት አይከፋው
- ክፋውንና ደጉን ለይቶ የማያውቅ

የሰው ኩራቱ በናትና ባባቱ
- አባት ሳለአጊጥ ጀንበር ካለሩጥ

የሰው ክብረቱ ያሰኘዋል እንቱ
- ሠርተው ደክመው ያገኙት ሀብት ያስከብራል

የሰው ክፉ ዋሾ የዕጽ ክፉ አብሾ
- አብሾ ሰውን የሚያሳብድ ዕጽ በመሆኑ ከርሱም ከውሽታምም መራቅ

የሰው ክፉ ጠማማ ነው አፉ
- ነገርን ወደ መጥፎ ሁኔታ እያጣመመ የሚተረጉም

የሰው ወርቅ አያደምቅ
- የወርቅ ጥርስ ቢሥቁበት አያደምቅ ቢያንኙበት አያደቅ

የሰው ግብሩ አይለየው እስከ መቃብሩ
- ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም

የሰው ግብር ቢመለከቱት ደሃ ይከናል ባመቱ
- የሰውን ክፉ ሥራ ላይ ከማተኮር በርትቶ መሥራት ይበጃል

የሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ
- ጠላት ከሩቅ አይመጣም

የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ዓሣ ጕርጓሪ ዘንዶ ያወጣል
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የሰው ፊት አይቆረስ የሰው ገንዘብ አይወረስ
- የሰው ቢመኙ ላያገኙ

የሰው ፊት የሚያፍር በቅሎ አይቀመጥ
- በይሉኝታ ብዙ ቤት ተፈታ

የሰው ፊት ደግነቱ አለመፋጀቱ
- የሰው ፊት ነበልባል ቢሆን ኖሮ ስንቱ ተሰብልቦ አልቆ ነበር

የሰይጣንን አመጣጥ አማያውቅ አይመነኩስ
- የነገሮችን አመጣጥና አካሔድ የማያውቅ ሰው ችግር ያጋጥመዋል

የሰይጣን ክፋቱ ያለመታየቱ
- የሚደርሱብንን ችግሮች አስቀድመን ለማወቅ አንችልም

የሰይጣን ገንዘብ የተበደረ ሳይበላው ተቀበረ
- ከክፉ ሰው ጋር የተዋዋለ መከራው ብዙ ነው

የሰዳጅ ለወዳጅ
- ለብርቱ ወዳጅ መልካም ነገር የሚሰድ

የሰጋ ቤቱን ዘጋ የዘነጋ ተወጋ
- ለሥጋው ሳይሆን ለነፍሱ አደረ ይህን ማድረግ የተሳነው መከራ ይጠብቀዋል

የሰጠ ቢነሳ የሰበት ወቀሳ
- በገዛ ሀብቱ በገዛ ንብረቱ ቢሰጥ ቢከለከል ማንያዘዋል

የሰጠኸኝ ሽማ ከደጅህ ተቀማ
- ነጣቂዎች እዚሁ ደጅህ ላይ የሰጡኸኝን ሽማ ነጠቁኝ

የሰጡህን ተቀበል ያደረጉልህን ችል አትበል
- ውለታን አትዘንጋ

የሰጡህን አትንሳ ያደረጉልህን አትርሳ
- ምንጊዜም የሰው ውለታ ሊዘነጋ አይገባም

የሰጡን ይለጧል የገዙን ይነዷል
- አንድ ሰው በራሱ ሀብት አዛዡ እሱ ራሱ ነው

የሰጡን ይለጧል ያጠቡን ያለጧል
- ሰው ለሰው የፈለገውን ያህል ወይም መጠን ሊሰጥ ይችላል

የሳተ ይምከርህ የዋለ ይንገርህ
- ልምድ ካለው ተማር

የሴት ልቧ እንጂ ሆዷ አይመርጥም
- ያገኘችውን የቀረባትን ሁሉ ትወዳለች

የሴት መልኳ ምንድነው? እጇን ታጥባ እንኩ ስትል ነው
- የሴት ባለሙያነት እንጂ መልክ ብቻ ዋጋ የለውም

የሴት መጠጥ ደፋር የወንድ ዓይን አፋር
- የሴት ጠጪና የወንድ ቅልስልቅ ለትዳር አይሆኑም

የሴት ምክር የሾህ አጥር
- የሴት ምክር ጥሩ ነው

የሴት ሞቷ በማጀቷ
- ትዳር ያላት ሴት ቤቷን ትወዳለች

የሴት ረዥም የማቅ ውዥምዥም አጅግ አያስጉመጅም
- ረዥም ሴት አትስብም

የሴት ለካር ያጭር ሰው ኩራት አይታይም
- የዳመና ውኃ ጥምና የእናት ክፍት አይታወቅም

የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ትወጣለች
- የሴት ወበራ ትታጠቃለች ካራ

የሴት በራ የበቅሎ ደንባራ /ቦራ/
- ፀጉር የሌላት ሴት አትስብም



የሴት ብቻዋን ሒያጅ የቁስ አርፍጅ ሁለቱም ነገር ወዳጅ
- ሴት ብቻዋን ከሔደች ትደፈራለች ለማለት

የሴት አመዳም የአሮጌ ሆዳም
- አመዳም ሴት ቅባትም ብትቀባ አትወዛም

የሴት አመዳም ያህያ ሆዳም
- አመዳም ሴት ቅባትም ብትቀባ አትወዛም

የሴት አገሯ
- ቤቷና ትዳሯ

የሴት አገሯ ባሏ ማደሪያዋ ዓመሏ
- ዓመል ያላት ሴት ባሏ ያከብራታል

የሴት አጭር ወይዘሮ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ
- ወንድ ዘለግ ሲል ይወደዳል

የሴት እንግዳ የመርፌ ጉዳ
- ሴትም መርፌም በደረሱበት ያገለግላሉ

የሴት ክርፋፋ ዕቃውን በዕቃ ደጋግፋ አንዱን ስታነሳ ሁሉም ይደፋ
- የተንከረፈፈች ሴት ሥራዋን በደንብ አትሠራም

የሴት ክፉ ምላሰኛ የበሽታ ክፉ መጋኛ
- ምላሰኛ ሴት ለትዳር አትመችም

የሴት ክፉ አፈኛ የጉረቤት ክፉ ምቀኛ
- የጉረቤት ምቀኛ ጥሩ አይደለም

የሴት ወበራ /ቀበጥ/ ትታጠቃለች ካራ
- እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል

የሴት ዘበናይ የፊቷን እንጂ የኋላዋን አታይ
- በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ገብተህ ቀረህ ወይ

የሴት ዘንገኛ የናት ምቀኛ
- የናት ምቀኛ ከቶውንም አለችጋሪ ናት

የሴት ዶሮ ኩኩሉ ለባለጌ ኩሩ
- አለሁ አለሁ የምትል ነገር ግን ከባለጌ ጋር የማትውል

የሴት ጉልበቷ ምላሷ
- ሴትን በስድብ የሚያክላት የለም

የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ
- የሴት ጠጪን የሚወዳት የለም

የስራት መቋሚያው ፍጥምጥም የሥጋ መቆሚያው ቅልጥም
- የጠቡ መነሻ የቆየ ጉዳይ ነው

የስሱ ልጅ ስሱ መደቆሻ ሲልስ ተሰበረ ጥርሱ
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የሰብሰቴ እርሻ የጠቡ መነሻ
- ላለመግባባት መሠረት የሆነው አንድ ነገር ነው

የስድብ እበጥ የለውም
- የስድብ ጥሩ የለውም

የስድብ ክፉ አባት የበትር ክፉ እናት
- በበትር እናት ከተመቱ አደገኛ ነው

የስጦታ ፈረስ ጥርስ አይታይም
- የስጡህን ሳታመነታ እመስግነህ ተቀበል

የሷ ጊዜ ተንሰቀሰቀች የሰው ጊዜ ሣቀች
- በሰው ቁስል ዕንጨት ስደድበት

የሻማ ጥቅል የወርቅ እንክብል
- ጥሩ ሀብት ይሰጥህ ምርቃት

የሸምበቆ በትር ቢመረኩዙት ይሰበራል ቢመቱበት እጅ ያቆስላል
- የጉሎ ዘንግ ብትር አይሆንም

የሸንጐ ዓይን ጉልበትን ይሰብራል
- የሰው ዐይን እርጥብ ያደርቃል

የሹም ስነፍ አንዱን ሳይጨርስ አንዱን ይወዝፍ
- ስነፍ ሰው የሚጨርሰውን ሥራ ሰነገ እያለ ያስተላልፋል

የሹም ስነፍ ይለፈልፍ
- ድክመቱን በመጮህ ሊሸፍን ይጮሃል

የሹም ክርፋፋ አገር ያጠፋ የአህያ ጀላፋ መስከ ያጠፋ
- የአሰቃ ልል በጥፊ ያወላውል

የሹም ጦር እቅፍ ሙሉ
- የፈሪ ዱላ ዘጠኝ ነው

የሹክሹክታ ግቢ ሰፍች ያስቸግራል ገርጋሪ በቅሎ ይደነብራል
- በድብቅ የተደረገ ነገር ሁሉ በኋላ ሰፈራጅ ያስቸግራል

የሺህ ሞት ሠርግ ነው ያንድ ሞት ጉዳት ነው
- የአንድ ጠቃሚ ዋና ሰው ሞት ኅብረተሰቡን ይጐዳል

የሺህ ቃል ንቁፍ የዋና ቃል ጽሑፍ
- ነፋስ ከነፈስ ንጉሥ ከተነፈሰ

የሺህ አባላት መሰብሰቢያው እናት
- ከሺህ ውስጥ የሚመረጡ መሪዎች እሱ

የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

የሺ ገንዘብ ብላ ከሺ ወንድም አትጣላ
- የጋራ የሆነ ገንዘብ ብዙ ተቆርቋሪ የለውም የሺ ወንድም ግን ተቆርቋሪ አለው

የሺ ገንዘብ ተቀበል የሺ ወንድሙን አትግደል
- ብዙ ወገን ያለውን ሰው አትንካ

የሺ ገንዘብ ብላ ወንድሙን አትንካ
- ወንድም ያለውን አትንካ ከነካህ ተበቃይ ይኖረዋል

የሻፈደች እርግብ መሬት ወርዳ ዶሮ ይደፍራታል
- ክብሩን ያልጠበቀ ሰላማዊ ሰው ማንም ያዋርደዋል

የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪመጣ
- ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም



የሽሮ ፉከራ ከምጣዱ እስኪወጣ እንጀራ
- ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

የሸንኩርት ሌባ አታላይነቱ ልሸተት ማሰቱ
- የሌባ ዐይነ ደረቅ መልሰ ልብ ያድርቅ

የሽከክ ዳቦ ስመስበኪያ ቀጭን ሸማ ስማረግረጊያ
- ተስማሚ የሥራ መሣሪያ ስተስማሚ ሥራ

የሽከክ ጸሎት
- የማይዘልቅ ጸሎት

የሾተላይ ልጅ የገበታ ውኃ ይወስደዋል
- ብርቅ የሆነ ነገር ተጸራሪው ብዙ ነው

የቀማኝ የሰው ልጅ የበቅሎ የሰው ልጅ
- ንጥቂያውን የፈፀመብኝ የሰው ልጅ ነው

የቀበረ ተቀበረ
- ምስጢሩን የደበቀ በዚያው ቀረ

የቀበሮ ባሕታዊ ከበጐች መሃል ይጸልያል
- አስመሳይ ሰው

የቀበጠች አይጥ የድመት አፍንጫ ታሸታለች
- የቀበጠ ዕለት ሞት አይገኝም

የቀበጠ ዕለት ሞት አይገኝም
- አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች

የቀበጠ ዕለት አይገኝም ሞት
- ካልቀበጡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ

የቀባጣሪ አፍ ጠማማ ነው
- ቀባጣሪ ነገሮች እንደፈለገው አጣምሞ ያወራል

የቀና ሲታጣ ይመስመሳል ጐባጣ
- ዋርካ በሌለበት እምቧጮ አድባር ይሆናል

የቀን ጨዋታ አይገኝም ማታ
- ጊዜ በአግባቡ ተጠቀምበት ያለበለዚያ ጊዜ ተመልሶ እንደማይመጣ ዕወቅ

የቀደመ ያገሳል ደግሞ ደግሞ ያጐርሳል
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የቀድሞ አርበኛ የቅምጥ ይዋጋል
- ልምድ አለኝ ባይ

የቀድሞ ወዳጅህን በምን ቀረብከው በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ
- ወዳጅን እንደዓመሉ መያዝ ሌላ ወዳጅ እንዳይርቅ ይጠቅማል

የቀዢ ልጅ ጠጪ
- ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተስተምራ ትመጣለች

የቁራ መልዕክተኛ
- ተልኮ በጣም የሚቆይ

የቁጥር መጨረሻ ዝም
- ዝም አይነቅዝም

የቂል በትር ሆድ ይቀትር
- ቂል ልክንና መጠንን መገመት አይችልም

የቂል ጓደኛው ቂል
- ግም ለግም አብረህ አዝግም

የቂጣ እንደሁ ይጠፋል የማርገገር እንደሁ ይገፋል
- እውነትና ንጋት እያደር ይታያል

የቄስ ልጅ ባገባ በሜሮን ፈትፍቼ እበላ ነበር አለ
- አንድም ከደግ ተወለድ አንድም ከደግ ተጠጋ

የቄስ ሚስት ዐወቅሽ ቢሏት መጣፍ አጠበች
- ብዙ ሙገሳ ለስሕተት ይዳርጋል

የቄስ ምንዳኛ የሴት በትረኛ
- የሴት በትረኛ በራሷ ላይ ችግር ትጋብዛለች

የቄስ ሞገደኛ የሴት በትረኛ አያድርስ ከኛ
- ቄስ የሕዝብ አስተማሪ ሆኖ ሳለ ሞገደኛ ከሆነ ለሕዝቡ አይጠቅምም

የቄስ ቀማኛ የዳኛ ምቀኛ
- አያድርስ ነው

የቄስ ቃል አንድ ይበቃል
- ቄስ ያለው ይሰማል

የቄስ ነጋዴ ይሆናል ወንበዴ
- ዓለማዊ ሥራ የሚሠራ ነጋዴ የጽድቅ ሥራ አይሠራም

የቄስ ነጋዴ ይመስላል ወንበዴ
- ከዓለማዊ ኑሮ ጋር የተዋሃደ ቄስ አጨበርባሪ ነው

የቄስ አባይ የደበሎ ተባይ
- የቄስ ዋሾ ኀብረተሰቡን ያጠፋል

የቅማል ስደት ከራስ ወርዶ አንገት
- ዕውር ቢሸፍት ከጓሮ

የቅርቡን በደጅ የሩቁን ባዋጅ
- በሕግና በደንብ መሥራት ተቀባይነት አለው

የቅርብ አራሽ በእንቅብ አፋሽ
- ወደማሰሮና ወደ እናት የተጠጋ አንድ ነው /የገንፎ ማዕረግ/

የቅርብ አዝመራ ለጤና
- አዲስ ሹም ብዙ አይተናኮልም

የቅርብ ጠበል የልጥ መንከሪያ ይሆናል
- በቅርቡ ያለ መድኃኒት አይንከባከቡትም

የቆለኛ ምስክር ከጥይት ይፈጥናል
- ቆለኛ ተኩሶ አይስትም

የቆመ ሌባ የተቀመጠውን ይቀማል
- ሁኔታውና ጊዜው ያመቸው የማያደርገው የለም

የቆመው እግር ቢሆን አሳቢው ራስ ነው
- ሁሉንም የሚመራው ዋናው አንጎል ነው



የቆረጠ አመለጠ
- ቶሎ መወሰን እንጂ ማመንታት አጉል ነው

የቆቅ ለማዳ የካይላ እንግዳ ከቤት ሲሉት ወደ ሜዳ
- ሁሉ እንደጠባይ እንደባሕርዩ እንደለመደው ነው

የቆቅ አውራ ይውላል ተራራ
- አውራ ሰው ውሎው አደባባይ ነው

የቆዳ ጓንታ ለውሻ ሠርጉ ነው
- የሁኔታዎች ግርግርታ ለሌላ ሰው ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል

የቆጡን ስታይ የብብቷን ጣለች
- ጥሩ ነገር ስትመለከት የራሷን ጥሩ ነገር አጣች

የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
- አተርፍ ባይ አጉዳይ

የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ
- ያገኘውን የማይበላ የሚጠየፍ ሰው ቀስ በቀስ አካሉ እየደከመ ይሔዳል

የበላ ቢያብል ገላው ይናገር
- ግመል ሰርቆ አጐንብሶ

የበላበትን ወጪት ሰባሪ
- ውለታ ቢስ

የበላች ብትዘፍን ያበላች ታዝን
- የሌላዋን ንብረት በመውሰዷ

የበላችው ያገሳታል በላይ በላይ ያጕርሳታል
- በቃኝን አለማወቅ አልጠግብ ባይ

የበላን ሆድ የወጋ ከንድ ያውቃል
- አፍ የሚጐርሰውን እጅ ይመጥናል

የበላውን ያብላላዋል የለበሰውን ይበርደዋል
- ያለበት ይጉላላበት

የበላይ አዳባይ
- ትንሹ ለትልቁ የሚበጅ ነገር መፈጸም

የበላ ዳኛ የወጋ መጋኛ
- ጉቦ የበላ ዳኛ ለሰጠው መፍረዱ አይቀሬ ነው

የበረታ ከራሱ የለነፈ ከዋሱ
- ብርታትና በራስ መተማመን ካለ በራስ ለራስ የሚበጅ ተግባር ይፈጸማል

የበረደውን አሙቆ የረጠበውን አድርቆ
- ሁኔታዎች ምቹ አድርጉ ማዘጋጀት

የበሬ ሆዳም ቢሞት አይጉዳም
- ብዙም የሚጠቅም ባለመሆኑ ቢሔድም ጉዳቱ ይህን ያህል ነው

የበሬም ዋይ ይውላል ገበያ ሥጋው ለመብል ቆዳው ለጠፍር
- ክብት በሕይወቱም ያገለግላል ሲሞትም የሚጣል የለውም

የበሬ ሳቢ የቤት አሳቢ ይስጥህ
- ኑሮህ የተሳካ ይሁን

የበሬ ሻኛማ የላም ግታም
- የተስተካከለ ሀብት ይስጥህ

የበሬ ቀንዱን የወይራ ግንዱን
- ጠንካራና የማይደፈር

የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደችው
- የሠራ እያለ ያልሠራ ተመሰገነ

የበሬ ዕቃ እየራሱ አለቃ
- ሁሉም በራሱ ራሱን የቻለ

የበሬ ዳተኛ እመሀል ይተኛ
- ልግመኛ ሰው እየሠራህ እያለህ ችግር ይፈጥራል

የበሬ ዳተኛ የሴት ምላሰኛ አታምጣ ወደኛ
- ችግር የሚፈጥር ሰው ወደኛ እንዲቀርብ አንፈልግም

የበሬ ዶሰኛ የሴት ምላሰኛ አያድርስ ወደኛ
- ነገረኛን አርቅልን

የበለለ ይበላል ጥሬ በምጣድ ይቆላል
- እንደአመቺነቱ ተግባር ላይ ማዋል

የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም
- የለየለት ምን አለበት

የበሶ አቁማዳ ተፈቶ የሴባ አፍ ነጥቶ
- ሌባ ተይዞ ዱላው አይጠየቅም

የበሶ አቁማዳ ተፈቶ የተሸካሚው አፍ ነጥቶ ይመስላል
- በአደባባይ የተሠራ ወንጀል መሸሸግ አይቻልም

የበሽታ ክፉ ቁርጥማት የኃጢያት ክፉ ቅናት
- ከመቅናት ሠርቶ ማግኘት

የበሽታ ክፉ እህል ያስወድዳል
- በችግር ላይ ችግር ሲደራረብ

የበቅሎ ዕቃ እየራሱ አስቃ
- ሁሉም በራሱ ራሱን የቻለ መሆኑ

የበቅሎ ክባድ የሐር ገመድ
- በእውኑ ዓለም የበቅሎ ከበድን ለማግኘት ያስቸግራል

የበደለ ይከሳል የቀማ ይመልሳል
- እውነት ተናግሮ የመሽመበት ያድራል

የቡና ስባቱ መፋጀቱ
- ቡናና ፍቅር በትኩሱ ነው

የቡና ቀዝቃዛ የሹም ፈዛዛ
- አይጥምም አይፈለግም

የባህር ዳር ሲታረስ ጓጉንቸር ሆድ ይብሳታል
- ትርፍ የሚለጥ የሚያስገኝ ነገር ሲበላሽ ያናድዳል

የባለሥር ምላሱ አሥር
- ወገንና ዘመድ ያለው ያሻውን ይናገራል



የባለቤት ለነፍ ቤቱን ያዋርዳል
- የቤቱ ውርደት የሱ መሆኑን ያለማወቅ ያለማጤን

የባለቤት አዳይ ጦም ያሳድራል
- የነገውን አለማሰብና አለማስተዋል

የባለቤት ዕውር ዕቃውን ያነሳል
- የማያስተውል ሰው የማይጐዳውን እንደሚጐዳ አድርጐ ይወስደዋል

የባለጌ ኃይማኖት ከኸማት ይከራል
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው

የባለጌ ልጅ መብል ያፍር ነገር ይደፍር
- ሥራ ከመሥራት ይልቅ ነገር ማመላለስ ይወዳል

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጃል ከነገር ይጃጃል
- የነገርን ብልት የማያውቅ ሰው በቀላሉ ይሞኛል

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ ነገር አይፈጅ
- የነገርን አካሔድ የማያውቅ በክርክር ወይም በሙግት አይረታም

የባለጌ ልጅ እያደር ይተኛል የጨዋ ልጅ እያደር ይበጃል
- ባለጌ ዕድሜም አያስተምረውም ጨዋ ግን ዕድሜ እያስተማረው ይሔዳል

የባለጌ ባለሟል ቂጥ ገልቦ ያያል
- ባለጌ አጸያፊ ተግባር ይፈጽማል

የባለጌ ባለሟል ካፍ አትለዩኝ ይላል
- ሞኝ ሰው ከወንድምህ እኩል አድርገኝ ይላል

የባለጌ ተለጣጭ ከድንጋይ ላይ ተቀማጭ
- ቂጥ ገልቦ ተከናንቦ

የባለጌ ኃይለ ቃል እንደሽመል ይወቃል
- የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር

የባለጌ ኩራቱ እንዲያው ነው በከንቱ
- ቢከፍቱት ተልባ

የባላባት ልጅ ሲሠራልህ ነው ያሉት እንደሆን ከስቶ ያድራል
- ስጋት አስበት

የባላገር ሥልጡን እሰው ፊት ይቆርሳል
- ዐወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጣፍ አጠበች

የባላገር ሥልጡን እጅ ይዞ ያጫውታል
- ያልሆኑትን መስሎ ለመታየት

የባላገር እንግዳ ሞት የባልቴት ሳዱላ መሬት
- የባልቴት ሳዱላ የማይሆንና የማይታመን

የባላገር ዱለት ይፈታል በኩበት
- በኩበት የተጠበሰ ዱለት ሽታው ጠረኑ አያስበላም

የባልቴት ወበራ የክረምት ብራ
- የማይሆን አንዳንዴ ግን የሚያጋጥም

የባል ዘመድ ባይኑ አመድ
- የባል ዘመድ በሚስቱ ይጠላል

የባል ዘመድ እዳርቻ ሲከስም ቆይ ብቻ
• የባል ዘመድ በዓይኑ አመድ
የባስ አለ ሚስትህን አትፍታ
• በእጅ የያዝከውን አትልቀቅ የሚመጣው አይታወቅም
የባሰ አለ አገርህን አትልቀቅ
• የባሰ አለ ሚስትህን አትፍታ
የባብ ለማዳ ያህያ ፍሪዳ የሰውም
• ምን ቢቸግር ሊሆን የማይችል
የባብ ልጅ በቅን ብቻ ሰንቅ በሰልቻ
• የማይሆንና የማይታመን ስንቅ በአገልግል ሊያዝ ይችላል
የባብና የሴት ፍለጋ ማነው የሚያወጋ
• ብዙ የሚያደከም ስወሬም አይመች
የባብ ዱካ ሆነ
• ፈጽሞ ሊገኝ አልቻለም
የባዳ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ይላል
• የባለጌ ባለሟል ካፍ አትለዩኝ ይላል
የባዕድ ሞኝ ከዘመድህ እኩል አርገኝ ይላል
• የዘመድ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ይላል
የባዕድ ፍቅር የውኃ ጌጥ አንድ ነው
• የባዕድ ፍቅር ከጥቅም ጋር ነው የሚሔደው ጥቅሙ ከቀረበት ፍቅሩም አለቀ
የቤቴ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ
• ችግሩ ባንድ በኩል ሲጐዳኝ በአንድ በኩል ጠቅሞኛል
የቤት ቀጋ የሜዳ አልጋ
• ጥሩ መስሎ አተሳ ፍሬ መበሎ ገለባ
የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ
• ጥሩ መስሎ አተሳ ፍሬ መስሎ ገለባ
የቤት ቤት አለው ማጀት የሆድ ሆድ አለው አንጀት
• ሁሉም እንደአቅሙ የሚኖረው ይኖረዋል
የቤት ዓመል ገበያ ያወጣል
• እቤት የሚያስቸግር ሰው በውጭም ያበቸግራል
የቤት ጥጋብ አለ ሰንቅ ያዘምታል
• አጉል ጥጋብ ለችግር ይዳርጋል
የብልጥ ዓይን አስቀድሞ ያለቅሳል
• አስመሳይ ነው
የብረት ቆሎ የድንጋይ ንፍሮ
• የማይሆን የማይደፈር
የብራ ዳጥ
• የማይታወቅበት መሰሪ
የብርቱካን ውኃውን የሽማግሌ ምክሩን
• የሽማግሌን ምክር ስማ



የብትር ትሕትና ያበመታል የነገር ትሕትና ያስረታል
• ነገርን በአንክሮ መከታተል ተገቢ ነው
የብዙ ሕዋሳት መበብሰቢያው እናት
• የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
የብዙ ኪሎ ሜትሮች መንገድ በአንድ እርምጃ ይጀመራል
• ከፍተኛ ቦታ የሚደረሰው ከትንሽ ተነስተህ ነው
የብድር ሽሮ ምን ሲል ተጀምሮ
• እንዲህ ዓይነቱ ከመጀመሪያውም መታሰብ የሌለበት
የቧልተኛ ሎሌ ሳይለለፍ ያረጃል
• ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል
የተለፋን ቆዳ ሳልተለፋ መለወጥ ትርፉ ዘጥ ዘጥ
• ያለቀለትን ጥሩ ነገር መለወጥ ለመልፋት ነው
የተላከ በአፉ ለከከ
• እሺ ከሺ ይበልጣል
የተሳጠ ዕንጨት ዳግም አይሳጥም ሰው አለ አንድ ጊዜ አይበለጥም
• ሰው የአንድ ጊዜ ስሕተት ስሁተኛው እንዳይሳሳት ይረዳዋል
የተልባ ስፍር የሕልም እንጀራ
• በአንድ ቦታ የማይረጋ
የተመረረ ድሃ ይገባል ከውኃ
• ኑሮ የመረረው ራሱን ያጠፋል
የተመረቀ ከሰይጣን የራቀ
• ከከፉ ሥራዎች መራቅ አለብህ
የተመሰከረ ይፈርዳል የሰባ ይታረዳል
• ያለው አይቀር
የተመታ ዳነ ደም የተፈናጠቀበት ሞተ
• የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ
የተመቸው ገንፎ ያላምጣል
• የደላው ሙቅ ያኝካል
የተመኘ አገኘ
• የምኞቱ ሆነለት
የተማማሉ ማለኛ የተጋደሉ ጠበኛ
• የማይተማመን ጓደኛ በየወንዙ ይማማላል
የተማረ መልካም ጥቃት አያስነካም
• የተማረ ለዘመዶቹ ጥቃትን ይከላከላል
የተማረ ነፍሱን የመረመረ
• የተማረ ከፉና ደጉን ይረዳል
የተማረ ከብሩን የመረመረ
• የተማረ ከብሩን የሚያስነካ ድፍረት አይፈጽምም
የተማረ የተሟረ
• መማር እንዳንዴ ለጉዳት ለችግር የሚዳርግበት ጊዜ አለ

የተማረ ጋፍ መልከ ያጋፍፍ
- ዐዋቂ ነኝ ባይ መልካምን ሲሽ ይኖራል

የተማከሩት ዳኛ ያግዛል የመተሩበት እጅ ይወዛል
- የተማከሩበት ነገር ጥሩ ነው

የተሟጋች ሚስቱ ቧጋች
- ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ነው የተቀዱት

የተረገዘ በሆድ የታዘለ በሰምድ
- የሚያውቁትን በጥንቃቄ በዘዴና በስልት መያዝ

የተራበ አይዘፍንም የጠገበ አያርፍም
- ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይለበሩ

የተራበ ከባቄላ የተበደለ ከሰቀላ
- እያንዳንዱ እንደችግሩ ዓይነት መፍትሔ መሻት ይኖርበታል

የተሳለ ብረት አንገትን ከደረት ሥጋን ከጅማት ይለያል
- እውነት ወይም ሐሰት እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ይለያል

የተሸሸገ ምግብ ሆድ አይጠፋለትም
- ንብረትና ገንዘብ ፈላጊ ወሳጅ አያጣም

የተሸሸገ ምግብ የተሸሸገ ሆድ አያጣም
- የተሸሸገ ንብረትና ገንዘብን ያልታወቀ ሰው ሊጠቀልለው ይችላል

የተሸከመው ከብዶታል እንደገና ይጨመርበታል
- በላይ በላዩ ያጕርሳታል የበላችው ያገሳታል

የተሾመ ወደ ግምጃ የተሻረ ወደ ሙጃ
- ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል

የተሾመን ይሟገቱበታል የተሻረን ይመሰክሩበታል
- ለሒያጅ የሰው ወዳጅ

የተቀመጠ ማርና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም
- ክብሩን ጠብቆ የቆየ በመጨረሻ ላይ ጥሩ ደረጃ ይደርሳል

የተቀማጭ ምላሱ ይላጭ
- የሚሠሩትን መተቸት ቀላል ነው

የተቀማጭ አፉ ምላጭ
- የሚሠሩትን መንቀፍ ቀላል ነው

የተቆለፈ ወርቅ ያልተቆለፈ ጨርቅ
- ትኩረት ይበዛበታል

የተበደለ ከነጋሽ የተጠማ ከፈሳሽ
- ሁሉም ወደሚመለከተው ቦታ ይሔዳል

የተራበ ገመዴ የተቆፈረ ጉድጓዴ
- ያረፈ ያፈጀ ለሞት የተቃረበ

የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አይቀርም
- የተጀመረ ነገር ማለቁ አይቀርም

የተናቀ መንድር ባህያ ይወረራል
- ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ



የተናካሽን ውሻ የጅብ መቋደሻ
- ከዚያም ከዚያም ጋር የሚጋጭ ሠራተኛ ዐይንህ ላፈር ይሉታል

የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ
- ቃልህን አክብር

የተኛውን አንበሳ አስነሳችው ላም ልሳ
- አቅምን ዐውቆ መኖር

የተከፋ ተደፋ
- የሚበሳጭ ሰው ራሱን ነው የሚጐዳው

የተወለዱት ይራባሉ እንደገና ይወለዳሉ
- በችግር ላይ ችግር መጨመር

የተዘጋ ተጠበቀ ያልተዘጋ ተበረቀ
- ግዴለሽ ሰው ችግር ላይ ይወድቃል

የተደረገ ተደርጐ እንዳበመስማት በጐ የለም
- ያልሰሙት ነገር አይቆጭም

የተገኘ ጥበብ ከዶሮና ከንብ
- ለፍቶና ጥሮ ለሕይወት የሚበጅ ነገር መሥራት

የተገዘተች ነፍስ የተለጐመች ፈረስ
- ከወዲያ ወዲህ መላወስ ያልተቻላት

የተጠማ ከፈሳሽ የተጠቃ ከነጋሽ
- ሁሉም ወደሚመለከተው ቦታ ይሔዳል

የተጠራጠሩበት ድንጋይ ይጥሉበት
- ጥርጣሬ ጥሩ ነው

የተጠገነ እጅ እንደቀድሞው አይሆንም
- ተበላሽቶ የተሠራ ነገር እንደአዲስነቱ አይሆንም

የተጣደፈን ቅቤ ያንቀዋል
- ችኰላ ለአደጋ ያጋልጣል

የተጻፈ ይወረሳል በቃል ያለ ይረሳል
- በጽሑፍ የሰፈረ ነገር ጥሩ ነው

የተፈተለ ከሁለት የተታታ ከሦስት
- ከአቅም በላይ ለማድረግ የሚሞክር

የተፈተለ ይለበሳል የተጀመረ ይጨረሳል
- የተጀመረ ነገር ማለቁ አይቀርም

የተፈጠመ አይናገር አንካሳ አይሸገር
- ያለቀለት ነገር መሻሻል አይችልም

የተፈጠመ ያርፋል የተኛ ያኮርፋል
- አንድ ሰው ቃል ከገባ በኋላ ቃሉን ማክበር ይገባል

የተፋትን ነገር መልሰው ቢውጡት ተራራ ያክላል
- ወደ መጥፎ ዓመልህ ከተመለስክበት ከፋቱ የባሰ ነው

የታለህ ያላሉት አዚህ አለሁ ይላል
- ሳይጠሩት አቤት

የታመመውን ሙት ጠየቀው
- ወደዚያው ወደማይቀሩበት መጓዝ

የታመነ ሉሌ ጠጅ የሞላበት ብርሌ
- በሰው ላይ ተአማኝነት ካለህ ያስደስታል

የታቀፈችው እናቲቱ የሚላጨው አባቱ
- በእንክብካቤ ሕፃናትን ማሳደግ

የታነቀ የልቡን ቢናገር የሚያምነው የለም
- ሳይሆን እንጂ ከሆነ ወዲያማ ማን ሊሰማ

የታናሽ ልጅ አሳናሽ የዘንጋዳ ወጥ አህል አበላሽ
- ባሰኔ የሰውን ክብር ያስደፍራል

የታደለ ተደላደለ
- ዕድለኛ የተመቻቸ ኑሮ ይኖራል

የታደለች ሴት በፊት ትወልዳለች ሴት
- ሴት ልጅ እናቷን ስለምትረዳ የመጀመሪያ ልጅ ሴት ቢሆን ይመረጣል

የትሕትና በትር ያስመታል የትሕትና ሙግት ያስረታል
- የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም ጠንክር ማለት ይበጃል

የት ላይ ተቀምጠሽ እግዜርን ታሚያለሽ
- ያለሽበትን በትክክል ያልተረዳሽ ነሽ

የትምህርት ሙግት እንደ ተናግሮ ጉልት
- በቂ ያልሆነ ዕውቀት

የትም ተከለስ አለቃህ ድረስ
- ለውሳኔውም ቢሆን ምንነትህ በግልጽ የምታሳውቅበት ቦታ ይሻላል

የትም ተወለድ እንክብር እደግ
- ልዩ ሙያ ልዩ ባሕርይ ስማዳበር ሲባል

የትም ፍጪው ዱቄቱን እምጪው
- የሚፈለገው ነገር ከየትም ቢሆን መምጣት አለበት

የት ትሔዳለህ? እሑዳዳቸው ምን ያሮጥሃል? ውቃቢያቸው
- የበላን ያብላላዋል ያሯሩጠዋል

የትንሽ ሰው ፍቅር መቀምቀሚያው ጥቁር
- ከስድ እደግ መጋባት መጨረሻው እያምርም

የት ዐውቅሽ ብሎ አጥብቆ ሳመኝ
- በስሕተት የተፈፀመ ተግባር

የትዕቢት መድኀኒት ጭንቀት
- እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል

የትውልድ ጉልበቱ ኀብረቱ የሕዝብ ህብቱ አንድነቱ
- መተባበር ኃይል ነው

የቸኮለ እፍሶ ለቀመ
- የቸኮለ ሰው ዘግይቶ ነው የሚደርሰው

የቸገረው እርጉዝ ያገባል የባለበት እመጫት ያገባል
- አማራጭ ያጣ ሰው ማድረግ የሌለበትን ነገር ያደርጋል



የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል
- የቸገረው እርጉዝ ያገባል

የችግር ክፉ እህል ማጣት የኃጢያት ክፉ ነፍስ ማጥፋት
- የሰውን ሕይወት እንደማጥፋት ያለ ከባድ ወንጀል የለም

የኃጢያት ክፉ ጉቦ የበሽታ ክፉ ተስቦ
- ጉቦ በእግዚአብሔርም የማይወደድ ሥራ ነው

የኃጥእን ዳፋ ጻድቅን እዳፋ
- የአንዱ ጦስ ለሌላው ጦስ ሆነ

የኋላ ኋላ አይቀርም ዱላ
- ይቺ ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም

የነሐሴ ውኃ ጥሩ ነው የሚጠጣው የለም የድሃ ነገር ፍሬ ነው የሚሰማው የለም
- ለድሃ ትኩረት የሚሰጠው የለም

የነቂሎ ቤት ግርግዳው ስንበሌጥ
- የቸኮለች እፍሳ ለቀመች

የነበረ ይናገር ያየ ይመስክር
- ምስክር ሊሆን የሚችለው ያየና የሰማ ብቻ ነው

የነበረ ገብርኤል ተወገረ
- ወንጀል የፈጸመ ፍርዱን አገኘ

የነብር ልጅ አይታቀፍ የጨዋ ልጅ አይነቀፍ
- የጨዋን ልጅ ምንም ስለማያጠፋ አይነቀፍም

የነብር ዓይን ከፍየል የፍየል ዓይን ከቅጠል
- ማንኛውም ነገር ትኩረት የሚሰጠው የሚፈለገው ነገር ላይ ነው

የነብር ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም
- አስቸጋሪ ነገር አይሞክሩ

የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ስንበሌጥ
- በጥድፊያ የተሠራ ነገር አይረባም

የነገሩ ሁነኛ የጦር አርበኛ
- አርበኝነት ከትውልድ የሚጠበቅ ነው

የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ እግዜርን አትርሳ
- ዓምላክ የለመኑትን ስለማይነሳ እግዜርን ልታስበው ይገባል

የነገር ትሕትና ያስረታል የብትር ትሕትና ያስመታል
- ነገርን ስአንክሮ መከታተል ተገቢ ነው

የነገር ወጡ መደመጡ
- ነገርን በጥሞና ካላዳመጥከው መረዳት አትችልም

የነገር ጠማማ በሽማግሌ ይታረቃል
- ከባድ የሆነን ጸብ እንኳን በሽማግሌ መፈታቱ አይቀርም

የነገር ጠማማ ያስከትላል ሳማ
- ጥፋት ማጥፋት ቅጣት ያስከትላል

የነገር ጣዕሙ ዝግታ ያዋቂ ጣዕሙ ዝምታ
- በዝግታ የሚቀርብ ነገር ተደማጭነት አለው

የነገር ጣዕም በጆሮ የእህል ጣዕም በጉሮሮ
- ለሁሉም አስፈላጊ የሥራ መሣሪያ ይጠቅማል

የነገን ነገ ይፍረደው
- ለነገ እግዚአብሔር አለ

የነገደ አተረፈ ያለፈ ተራገፈ
- የሠራ የልፋቱን የጥረቱን ያገኛል

የነጋሪት በቅሎ ከላይሽ ማን ወርዶ
- ነጋሪቱ ተጐስሞ እስኪያልቅ ነጋሪት ጐሳሚው ከበቅሎዋ ላይ አይወርድም

የነፍስ ገዳይ ምልክቱ ደም በጣቱ
- ክፉ ሠሪ ክፋቱ የሚገለጥበት ባሕርይ ነው

የነፍስ ትቶ የገበስ
- ሰው የዕለት የዕለቱን ያስባል

የኑሮ ክፉ ደባል የመንገድ ክፉ በደል
- የደባል ኑሮ አስከፊ ነው

የኑሮ ገለባ እያገርህ ግባ
- ያልተሟላ ኑሮ ጥፋልኝ ዘንድሮ

የናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደ ነብር ጠጉር
- አንዱ መልካም አንዱ ክፉ

የናት ሆድ ዥንጉርጉር ወላጅ ቀይና ጥቁር
- ከአንድ እናት የሚወለዱ ሁሉም አንድ ዓይነት አይሆኑም

የናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ሲሆን በውድ አለበለዚያ በግድ
- የእናትን ልመና ማንም ረግጦ አያልፍም

የናት ልጅ ቢጣላ እውነት ይመስላል
- እህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር

የናት ልጅ የሌለው አይበላ ጆሮ የሌለው ምንቸት አይፈላ
- አንድ እንጀት ተንተርሰው የተወለዱ አይጨካከኑም

የናት ልጅ የጉን እጅ
- አለኝታና ረዳት ነው

የእናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል
- የእናት ሞት እየቆየ ይሰማል

የናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል
- የናት ሞት እያደረ ይሰማል

የናትን ክፋት የደመናን ውኃ ጥማት ባለቤቱ ያውቃል
- ሌላው ማንም ይሆናል ብሎ አይገምትም

የኔህ በለኝ ደስ እንዲለኝ
- በጣም እወድሃለሁ

የኔ ነው የማይል የሞተ የራሱን የማይተው የሞተ
- ለአራሱ የማይሆንና ንብረቱን የማይጠብቅ ሰው አይረባም

የኔን ችግር ለማን ልንገር
- ችግሬን ለማን ሳዋየው



የኔን ወጥ በቀመስሽው ያንቺን በደፋሽው
- የኔን ብትቀምሽ ኖሮ ያንቺ ጥሩ አለመሆኑን ትገነዘቢ ነበር

የንጉሥ ቃል አነሰ ብሎ አይጨመር በዛ ብሎ አይቀነስ
- ንጉሡ ከተናገሩት ነገር ላይ መጨመርም መቀነስም አይቻልም

የንጉሥ አሽከር ስሙ ወርቅ ልብሱ ጨርቅ
- ክብሩ በጣም ከፍተኛ ነው

የንጉሥ እድር እናት አያስቀብር
- ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ

የንጉሥ ግንቡን የሹም ልቡን
- ማንም ሊያውቅ ሊደፍር አይችልም

የንጨት ምንቸት ራሱን አያድን ሰው አያድን
- ለራሱ አይሆን ለሌላው አይሆን

የንጨት ክፉ አባሎ የዳኛ ክፉ መድሎ
- አድልዎን ሕዝብ ፈጽሞ አይወድም

የንጨት ወልጋዳ የመንገድ አንጋዳ
- የማያውቁት ሄደውበት የማያውቁት መንገድ ያስቸግራል

የንፉግ ሰጋስ የሰጠውን ይመልስ
- ያለባሕርዩ የሚደረግ ነገር ዘለቄታ የለውም

የንፉግ ገንዘብ በለጋስ እጅ የጠላት ገንዘብ በወዳጅ
- ገንዘብ ባይኖርህም የጠላትህን ገንዘብ በወዳጅህ በኩል ታገኘዋለህ

የንፍጣም ነገሩ አይጥም
- ልክስክስ ሰው ሥራው ሁሉ ደስ አይልም

የአልኮል ፍቅር እስከ መቃብር
- የአልኮል ሱስ መጥፎ ነው

የአረፋውን ሲሏት የጀጀባውን
- የሰው ምክር የማትሰማ የቀኙን ሲሏት የግራውን ያለኛታል

የአርበኛ ልጅ ይወጋል የአሮጌ ልጅ ያወጋል
- ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደአባቱ ሰጡት አመልማሎ ይፍተል እንደእናቱ

የእሥር እናት ጅብ በላት
- ብዙ ዘመድ እያላት ሳይደርሱላት አደጋ ደረሰባት ወይም ገጠማት

የእሽኮኮ ዳቦ ለመስበኪያ ቀጭን ሽማ ለማረግረጊያ
- ለተወሰነ ተግባር ተስማሚ የሆነ የሥራ መሣሪያ ያስፈልጋል

የእቡን ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ አይታይም ሲወረወር
- ጸሎት ሰይጣንን የሚያሸንፈው ሰይጣን ያደረበት ሰው ሲጮህ ነው

የአባይ ልጅ ወዳቂ የዘማ ልጅ ሣቂ
- ተማሪ ማንን ይመስላል ቢሉ መምህሩን

የአተር ክምር የጢሰኛ ክብር
- የማይረባ ዋጋ የሌለው

የአንበሳ ልጅ ሲሞት ቀበር አንበሳ ሲሞት እቤት ዋል
- የሀብታም ልጅ ሲሞት ቀባሪው ሺ ባለቤቱ ሲሞት ቀባሪው ሣምሣ

የአዋጁን በጆሮዬ
- የአደባባይ ወሬን በምስጢር

የአውሬ ሥጋ ለወሬ
- የአውሬ ሥጋ የሚገኘው በአደን አደን ደግሞ ጀግንነትን ስለሚያመለክት

የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ
- ለውሸታም ውሸታም ነው የሚመሰክረው

የአይጥ ሞትዋ የድመት ጨዋታዋ
- የአንዱ ስቃይ ለሌላው ደስታ ጨዋታ ነው

የአይጥ ሞት የድመት ሠርግ ነው
- የአንዱ ስቃይ ለሌላው ፌሽታ ነው

የአይጥ እርጉቱ የድመት ወቱ
- የማይሆንና የማይታመን

የአይጥ እርጉዟ የድመት ወዟ
- ዞር ዞር በመጨረሻ ማጠቃለያው እዚያው ነው

የአይጦች ዝላይ ለነአቶ ውሮ ሲሳይ ነው
- የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሠርጉ ነው

የአደባባይ ሚስጥር
- ሁሉም ሰው የሚያውቀው

የአዳኝ ውሻ መነጽሩ ከአፍንጫው ነው
- ውሻ ከዐይኑ የበለጠ የሚጠቀመው በአፍንጫው ነው

የአገር ልጅ የማር እጅ
- የአገር ልጅ ለችግር ጊዜ ደራሽ ነው

የአገር ጠላት ሸፍታ የገንዘብ ጠላት መሸታ
- ገንዘብን የሚያባክን የመጠጥ ሱስ ነው

የአጭር ኩራት የቤት ስካር አያዋጣም
- የቤት ጠጪ የግመል ፈንጪ የለውም

የአፍ ብልሃት ጌትነት የእጅ ብልሃት ባርነት
- አፍ ያለው ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳል /የቀድሞ አስተሳሰብ/
- ባለሙያነት ክብር ነው

የአፍንጫ እድፍ ለእጅ ይተርፋል
- ለእግር የፈሩት ለቂጥ ይተርፋል

የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም
- አፍ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም

የአፍ ዘመዶች ከገበያም አይገድ
- የአፍ ወዳጅ ከገበያም ሞልቷል

የእህል ክፉ ክርትፉ
- ያልተስተካከለ ነገር ሁሌም ችግር አለው

የእህል ጌታ ፈርዛዛ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ
- ሀብታም ሰው ለሀብቱ በጣም ይጨነቃል



የእህል ጣዕም በጉሮሮ የነገር ጣዕም በጆሮ
- ሁሉም በተገቢው መንገድ ሲፈጽም ትርጉም ይኖረዋል

የእህት ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ነው
- የእህት ልጅ እንደራስ ልጅ ይታያል

የእረኛ ፈሱ መርዘኛ
- ከከብቶች ጋር ሲሮጥ ስለሚውል ፈሱ የቆነሰ ነው

የእሬትን ምሬት ያልቀመሰ የማርን ጣዕም አያውቅም
- መከራን ያላየ የደስታን ጣዕም በሚገባ አያውቅም

የእርኩስ መውጊያ አደረገኝ
- ሰዎች እንዳይወዱኝ አደረገኝ

የእሳት ልጅ አመድ
- የጀግና ልጅ ፈሪ

የእሳት እራት አያውቅም መብራት
- ጠፊ የሆነ ነገር ጠቃሚ የሆነውን አያውቅም

የእቡይ ልጅ ውዳቂ የዘማ ልጅ ሣቂ
- ተማሪ ማን ይመስላል ቢሉ መምህሩን

የዕብድ ቅል ማንጠልጠያው ፈትል
- ተው እንዳይሆን

የዕብድ በሶ
- እርጋታ የሌለው

የዕብድ አሞራ ሲላ ደንገጡሯ
- የለውን ንብረት የሚያውድም

የዕብድ አጫዋች ሙር ነው
- ሁሉም አምላያውን አያጣም

የዕብድ ዘመድ ሳያማስን አይለድ
- ይሉኝታ ቢስ ሰውን ያስለቻል

የዕብድ ገላጋይ ሸተል አቀባይ
- የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል

የእነሽክሹክታ ግቢ /ጋብቻ/ ለፍቺ ያስቸግራል
- ከመጀመሪያው በሐሜት የተጀመረ ነገር መጨረሻው አያምርም

የእናት ልጅ የጉን አሳጭ
- ያመኑት ፈረስ በደንደስ

የእንቢተኛ መድኀኒቱ ዳኛ
- እንቢተኛን ለሕግ ማቅረብ ነው

የእንባይ ካብ
- ቶሎ የሚፈርስ

የእንጀራ ሲጥ ይበላል
- ትዳሩ ጥሩ ነው

የእንጀራ ቀንጣቢ የድመት አላቢ
- አይጥ ቤት ብቅል

የእንጀራ አብራጃውን የወጥ ለብታውን
- ሁሉም ነገር እንደየአስፈላጊነቱ መጠቀም ያስፈልጋል

የእንጀራ እናት ምን አጠናሽ እንደ ጅማት
- የእንጀራ እናት ዐረመኔ ናት

የእንጀራ ወጡ ረኃብ ነው
- ሲርብህ ደረቅ እንጀራ እንኳን ይጣፍጥሃል

የእንግዳ ሰማዳ ያመጣል ብዙ ዕዳ
- እንግዳ በመመላለስ ባለቤቱን ያከስራል

የእንግዳ ለማዳ ይገባል ከጓዳ
- መለማመድ ቀስ በቀስ ያዛምድ

የእንግዳ ቀበጥ ባለቤት ያጉርሳል
- እንግዳ ሲያፍር ባለቤቱን ይጋብዛል

የእንጦጦ መምህር ሲናገሩ ባመት ያውም ሬት
- ብዙ ጊዜ መልካም ነገር ጠብቆ ክፉ ነገር ሲደርስ ልብ ይሰብራል

የእከክ መድኀኒቱ አለመቅረብ አለመቀራረብ ነው
- ችግር ሊያመጣ የሚችል ቦታ አለመቅረብ ጥሩ ነው

የዕውር ልቡ እየሩሳሌም ሐሳቡ
- የማይሳካን ነገር ሳይ ምኞች መመኘት

የዕውር ሞቱ የጨረቃ ንጋቱ አይታወቅም
- ገጣጣ ሰው ሞቶ የሣቀ ይመስላል

የዕውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል
- አጉል ጥጋብ ችግር ላይ ይጥላል

የዕውር ነፍጠኛ የወንበር ፈረሰኛ
- ዕውር በጦር መሣሪያ የመገልገል አቅም አይኖረውም

የዕውር አለተናባሪ የድውይ አጋፋሪ
- ለየሥራው ዓይነት ተስማሚ ሰው መመረጥ አለበት

የዕውር አዝማሪ የደንቆሮ ተጠሪ
- አንዳንድ ሙያዎች ከአካላዊ ብቃት ጋር የሚሄዱ ይሆናል

የዕውር አፍጣጭ የንጉሥ ቀላዋጭ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕውር ግልምጫ የአንካሳ ሩጫ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የእውነት በትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም
- እውነት ለጊዜው ትጠፋለች እንጂ ዞሮ ዞሮ ሐቁ ይወጣል

የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም
- እውነት ለጊዜው ይለወር እንጂ ዞሮ ዞሮ ሐቁ ይወጣል

የዕዳ ጉደሎ ይንቦጫቦጫል
- ፈልጌ ያደረግሁት ስለሆነ እቀጥልበታለሁ

የእጅ ሌባ ይያዛል የአፍ ሌባ ያስገርፋል
- የአፍ ሌባን ለመያዝ ያስቸግራል ተጨባጭ የሆነ ነገር በእጁ ላይ ስለማይገኝ



የእጅ ብልሀቱ ባርነቱ የአፍ ብልሃቱ ጌትነቱ
- ከእጅ ብልሃት የአፍ ብልጠት ይበልጣል /የቀድሞ አስተሳሰብ/
- ከአፍ ብልሃት ይልቅ ሙያዊ ችሎታ ጠቃሚ ነው /የአሁን አስተሳሰብ/

የእግር ጌጡ መርገጡ
- የአንድን ነገር ትልቅነት በተሰጠው ሙያ በቂ ግልጋሎት መስጠት

የከረረ ይበጠሳል የተበደሰ ይካሳል የበደለ ይወቀሳል
- ተቻችሎ ተስማምቶ መኖር ጠቀሜታ አለው

የከሳ እሪያ ይገራል
- አንድ ሰው አንዳች ሥልጠና ለመውሰድ የሚሠለጥን ዓይነት መሆን አለበት

የከብት አገሩ ባለቤቱ የሰው አገሩ ምግባሩ
- የቤቱ ባለቤት በሥሩ ላሉት ሁሉ የሚያስብና የሚመራ ነው

የከተማ ዳንዴ የበረሃ ወንበዴ
- ጠባዩ አኗኗሩ ለኅብረተሰቡ የማይስማማ

የከተማን ወሬ መስማት ትልቅ አዳራሽ መሥራት
- የከተማ ወሬ ብዙ ነው ምን ቅጡ

የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም
- ዓምላክ ጾም አያሳድርም

የከፋ እውነት የተፈጠረ ነው ከውሸት
- አንዳንዱ እውነት ወይም ሐቅ ለማመን የሚያስቸግርበት ጊዜ አለ

የከፋው ሰው ሲሔድ አይለናበትም
- የተበደለ ሰው ጉዞውን በጨረቃ ይጀምራል

የካሕን ዓይን አፋር የአህያ ዕውር የሴት ደፋር አይረቡም
- ለሁሉም ቦታ ቦታ አለው

የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ራብ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለ
- የውስጥ ችግሩን የሚያውቀው ያው ባለቤቱ ነው

የክፉ ልጅ እናት ሁልጊዜ ታለቅስ
- ልጁ በሚፈጽመው ተግባርና በሚደርስበት ችግር ምክንያት

የክፉ ሰው ተዝካሩ ያቅራል
- የክፉ ሰው ምኑም ምኑም አይጥምም

የክፉ ሰው ተዝካር ውኃ ያስወስዳል በኅዳር
- የክፉ ሰው ጣጣ ያልታሰበ ችግር ውስጥ ሰውን ይጥላል

የኮራ ተጉዳ አይዋጋም የበሬ ቆዳ
- አጉል ኩራት ይገኝ ከነበረ ጥቅም ያስገልላል

የኮሶ ማግስት እናት በሆነች አራት አምስት
- በኮሶ ማግስት ረኃብ ስለሚጠና

የኮሶ እሪያ ይገራል
- በአስፈላጊው ነገር ቀስ በቀስ ለውጥ ማምጣት ይቻላል

የወለደ ይልላል የበደለ ይከላል
- ቅርበትን ወዳጅነትን ለማመልከትና ተፈጥሮአዊና ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ያስገድዳሉ
የወለደውን ሲሰሙለት ያቀረበውን ሲበሉለት ደስ ይለዋል
- ሰው ያቀረበውን ሲበሉለትና ልጁን ከወደዱለት በጣም ደስ ይለዋል
የወለዱት ሁሉ ካደገ የዘሩት ሁሉ በጸደቀ
- ያሰቡት ሁሉ እንዳሰቡት ትክክል ላይሆን ይችላል
የወለፈንድ ሰልቻ ጤፍ ይቋጥራል ባቁላ ያፈላል
- ነገሩ ሁሉ የተምታቢጠሸና የማይታመን
የወለፈንድ ኑሮ በሑዳዴ ቋንጣ በፋሲካ ሽሮ
- ሁኔታዎቹ የተዟዟሩ መሆናቸው
የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ የልጅ ሆድ ቀጥ
- ወላጅ ለልጆቹ በጣም ያስባል ልጅ ግን ምንም
የወረት ኮሶ ይጣፍጣል
- የወረት ነገር ሁሉ ደስ ይላል
የወረት ውሻ ስሟ ወለተ ጴጥሮስ
- የወረት ነገር ሁሉ ደስ ይላል
የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ ለራሴ
- ሌላውን እጕዳለሁ ብዬ እኔኑ መልሶ ጉዳት ላይ ጣለኝ
የወረደ መዓቱን የመጣ ምጣቱን
- የከፋ ነገር መድረሱን ለማመልከት
የወሬ ቆርፋዳ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም
- የሚያሰለች ወሬ መስማት አያስፈልግም
የወርካ ልጅ ሣንቃ የአሰቃ ልጅ አሰቃ
- የአሰቃ ልጅ አሰቃ እንኳ ባይሆን እንደ አባቱ ይከበራል
የወሰን ላይ ሰዎች ሌቦች ወይም ሽፍቶች
- ጠረፍ ያሉ አንዳንዴ ቅሚያ ስለሚያካሒዱ የሚነገር
የወታደር ፈዛዛ የእናት ነዝናዛ የሴት ቀበዝባዛ
- ወታደር ከፈዘዘ እናት ከተነዛነዘች ሴት ከተቅበዘበዘች በማኅበረሰቡ የማይጠበቁ ባሕርያት ናቸው
የወንበዴ ዋሻ የሌባ መሸሻ
- አባሪ ተባባሪ
የወንድ ልጅ ሞት ያደረገውን የዘነጋለት
- ወንድ ልጅ ዝንጉ ከሆነ ምንም ዕድገት የለውም
የወንድምህ ጢም ሲላጭ ጢምህን ውኃ አርስ
- የወንድምህ ዕጣ እንደሚደርስህ አስብ
የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ነው
- ያው እንደራስ ልጅ የሚቆጠር ነው
የወንድ አልጫ የእንዶድ ሙቀጫ
- የማይረባ ፈሪ



የወንዶች ባል አይተህ ማር
- ጀግና ጨካኝ አይደለም
የወንጭፍ ድንጋይ ባልነበር የማሽላ እሸት መልካም ነበር አለች ወፍ
- ሁሉም ለራሱ በማሰብ
የወይራ ዘለላ ጋን ይሞላ የሥንዴ ዛላ እፍኝ ይሞላ
- ወይን ሲጨመቅ ሲበረክትና ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል
የወደቀ ተነጠቀ
- ደካማ የሆነ ሰው በእጁ ያለው ይወስድበታል
የወደቀን አንሳ የሞተን እትርሳ
- ከድንበሩ አትለፍ በሰጡህ አትሰነፍ
የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል
- የተቸገረ ሰው ካለ በላይ በላይ ነገር ይመጣበታል
የወደደ ሰው ዐይንም የለው
- ፍቅር ዕውር ነው
የወደደውን አቅፎ የጠላውን ነቅፎ
- የወደደውን ይንከባከባል የጠላውን ደግሞ ያንጓጥጣል
የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ
- ተፈላጊው ቢጠፋ የማይፈለገውም ነገር ከምንም ይሻላል
የወደድከው ቂጣ ሰተት ብሎ መጣ
- ያመኑት ፈረስ በደንደስ
የወዳጅ ሚዛኑ መከራ ነው
- ወዳጅ ወዳጅነቱ የሚታየው በመከራ ጊዜ ነው
የወዳጅ ሰልቻው ለየብቻው
- እያንዳንዱን እንደባሕርይውና እንደጠባዩ ማስተናገድ
የወዳጅ ተጋፊ የጠላት ደጋፊ
- ወዳጅ መስሎ መሰሪን በጥንቃቄ ይመለከቷል
የወዳጅና የኮርቻ አስመንካቱ ብቻ
- ወዳጅ ለወዳጁ ኮርቻም ለተቀማጩ ምቹ ነው
የወዳጅ ከዳተኛ አዱኛ
- የወዳጅ ከዳተኛ እያድርስ በዓለም ውስጥ ከፍተኛው መጥፎ ነገር
የወዳጅ ወዳጅ ወንዝ ያሻግራል
- ሰው ማወቅ ጥሩ ነው ለችግር ጊዜ ሊደርስ ይችላል
የወጋ መጋኛ መቅበጥ የሰመደ ዳኛ
- የሰመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ
የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ
- ሰውዬው ቢረሳ የተበደለው ሰው አይረሳ
የወጣ ሰው አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ
- ሰው ሁልጊዜ ያሰበው አይሟላለትም
የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል
- ጊዜው እንካ በእንካ ነው

የወፍ ዞላ /ዝላ/ ከቤት ይውላል እሸት /እሸን/ ሲፈላ
- የሚፈለገው በቅርብ ከተገኘ ምን ያለፋል

የወፍጮ እንጉርጉሮ አይሆንም ለሠርግ
- ያ ሌላ ይሄ ሌላ

የዋህ ፊቱን ቢመልስ ማጅራቱ ጋር ይመስለዋል
- በጐ ነገር በጣም ይከብደዋል

የዓመል ታናሽ ይጥላል ጭራሽ
- ዓመሉ መጥፎ የሆነ ሰው ከብዙ ሰዎች ጋር አይስማማም

የዓምላክ ነገር አይመረመር
- ሳትመራመሩ በእምነት ኑሩ

የዓባይ ልጅ ኩሬ
- የእሳት ልጅ አመድ

የዓይን ሕመም ክሉት ነው የሆድ ሕመም ልግም ነው
- አንዳንድ የሰው ባሕሪያት በግልጽ ሲታዩ አንዳንድ ባሕሪያት ግን ድብቅ ናቸው

የዓይን ጨንቋራ ሰው ያየዋል፤ የልብን ጨንቋራ እግዛብሔር ያየዋል
- ሰው ላይ ላዩን እንጂ ውስጡን የሚያይ ዓምላክ ነው

የዕብድ ቅል ማንጠልጠያው ፈትል
- ተው እንዳይሆን

የዕብድ በሶ
- እርጋታ የሌለው

የዕብድ አሞራ ሲላ ደንገጡሯ
- የሰው ንብረት የሚያወድም

የዕብድ አጫዋች ሙር ነው
- ሁሉም አምሳያውን እያጣም

የዕብድ ዘመድ ሳይማለን አይለድ
- ይሉኝታ ቢስ ሰውን ይሰለቻል

የዕብድ ገላጋይ ሾተል አቀባይ
- የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል

የዕውር ልቡ እየሩሳሌም ሐሳቡ
- የማይሳካ ነገር ላይ ምኞት መመኘት

የዕውር ሞቱ የጨረቃ ንጋቱ አይታወቅም
- ገጣጣ ሰው ሞቶ የሣቀ ይመስላል

የዕውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል
- አጉል ጥጋብ ችግር ላይ ይጥላል

የዕውር ነፍጠኛ የወንበር ፈረሰኛ
- ዕውር በጦር መሣሪያ የመገልገል አቅም አይኖረውም

የዕውር አስተናባሪ የድውይ አጋፋሪ
- ለየሥራው ዓይነት ተስማሚ ሰው መመረጥ አለበት



የዕውር አዝማሪ የደንቆሮ ተጠሪ
- አንዳንድ ሙያዎች ከአካላዊ ብቃት ጋር የሚሔዱ ይሆናሉ

የዕውር አፍጣጭ የንጉሥ ቀላዋጭ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕውር ግልምጫ የእንካሳ ሩጫ
- ሊሆን የማይችል ነገር

የዕዳ ጉዶሎ ይንበጫበጫል
- ፈልጌ ያደረግሁት ስለሆነ እቀጥልበታለሁ

የዋለበት ዐሪም በላው
- የለፋንበት ነገር አልሆነልንም

የዋርካ ልጅ ዋርካ ያለቃ ልጅ አለቃ
- የአቡይ ልጅ አቡይ

የዋስ ተሚጋች የቆማጣ ፈትፋች
- እያገባው ገብቶ እያወዛው ተቀብቶ

የዋስ ወንድም አይታገት የአባያ ወንድም አይጐተት
- በአንዱ ሥራ ሌላው አይጠየቅም

የዋኘ ይሸገራል የሠራ ይከብራል
- ሁሉም ነገር በጥረትና በትጋት ይገኛል

የዋጋ ብልጥ ልብ ይግጥ የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ
- ለአንድ ነገር የተሰጠው ዋጋ ከፍ በሚልበት ጊዜ ገዢውን ያበሽቃል

የውሎ መንገድ በሩጫ
- ረጅም ጊዜ የሚፈጀውን ሥራ በአጭር ጊዜ ለመሥራት መሞከር

የውስጥ እንጀቴን የላይ ቁርበቴን
- መከራና ስቃይ አጋጠመኝ

የውሻ ትሕትና የካሕን ዕብድና መች ይጋጥምና
- እንዲህ ዓይነቱ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አያጋጥምም

የውሻን ጥርስ በአጥንት ይፈሯል
- ወዳጅህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ

የውሻ አፍንጫ አለው
- አንድን ነገር ተከታትሎ የመያዝ የመድረስ ችሎታ አለው

የውኃ ውኃ ምን አለኝ ቅዛ
- የዚህ የዚህ ምን አለፋኝ ነበር

የውኃ ጡር በእድፍ ያስታጥባል
- የውኃ ጥቅም የሚታወቀው ምንጩ የደረቀ ቀን ነው

የውድማ ዘንዶ ይቀጠቀጣል እንደ በረዶ
- ሌባ ተይዞ ዱላ አይጠየቅም

የውጭ እልጋ የውስጥ ቀጋ
- በቤት ውስጥ አስቸጋሪ ከቤት ውጪ ላለ ሰው ቸርና ለጋስ ሆኖ የሚታይ ሰው

የዘላን ቤት ሁልጊዜ ስደት
- በየደረሰበት የሚጣል ዳስ /ጐጆ ቤጤ/

የዘላን ጦመኛ ከጥጃ ጓዳ አታስገቡኝ ይላል
- ከሥጋው ጦመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ

የዘመተ ይመለስ የገደለ ይንገሥ
- አሸናፊ ምንጊዜም የበላይ ነው

የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ አንዱ ለፍቅር አንዱ ላሜታ
- ሰው መልካም በተናገረበት ከፉም ነገር ይናገራል

የዘመኑ ሰው ሲያቀርቡት ያርቃል ሲወዱት ይጠላል
- የዘመኑ ለው ጠባይ መላ ቅጡ የጠፋ ነው

የዘመኑ ወሬ ይቀዳል ባቦሬ
- ባዚህ ዘመን ወሬ በዝቷል

የዘመድ ለማኝ ከዝምድናው ወጥቶ የለመነውንም አጥቶ
- ላይሳካ ነገር ራስን ዝቅ ማድረግ አይገባም

የዘመድ ሎሌ የፈረስ ጮሌ ሲወጣ ወጥቶ ነው
- ከባለቤቱ ሥር አይታጣም /ባለቤቱ ሲወጣ አብሮ ይወጣል/

የዘመድ ቂስ እየፈታ ያለቅስ
- የሙያውን ተግባር እየፈጸመ ውስጥ ውበጡን የዝምድናውንም ሁኔታ ያካሒዳል

የዘመድ አዳይ ጦም ያላድራል
- በይሉኝታ የታሰረ ሰው

የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል
- ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ

የዘመድ ጥል የሥጋ ትል
- የዘመድ ጥል ቂም አይያዝበትም

የዘማ ልጅ ሣቂ የእቡይ ልጅ ውዳቂ
- የባለጌ ልጅ ባለጌ ነው

የዘራ ምን ያመጣ ፍሬና ፈንጣጣ
- ሰው የዘራውን ያጭዳል

የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ
- የቤተሰቤን ወግ እከተላለሁ

የዘነጋ በሩን ዘጋ
- የሮጠ አመለጠ የቆመ ቀለጠ

የዘነጋ ተወጋ
- ዝንጉ ሰው ለአደጋ ይጋለጣል

የዘገነ አዘነ ያልዘገነም አዘነ
- ያገኘው አነሰኝ ያላገኘውም አጣሁ በማለት ማዘን

የዘገዪ ተለዩ
- በሰዓቱ ያልተገኙ ከኀብረቱ ራቁ

የዘፈን መጀመሪያው እስክስታ ነው
- የነገር ዳር ዳርታ ማለት ነው



የዚህ ዓለም ፍቅር ሰኞ አዲስ ማክሰኞ ልብስ ረቡዕ ብጥስጥስ
- የዘመኑ ፍቅር ሲጀምሩ ሞቅ ሞቅ ይላል ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቀዝቀዝ መጨረሻ ይከበማል

የዛሬን ለቀባሪ የነገን ለፈጣሪ
- ስለዛሬው አስብ እንጂ ለነገ አትጨነቅ እግዚአብሔር አለልህ

የዛሬ ዘመን ጫጩት ካውራ አኩል ትውጣለች ወይ ያንቃታል ወይ ትሞታለች
- መስገብገብ ለችግር ይዳርጋል

የዝሆን ከላቱ የባለጸጋ ድህነቱ አይታወቅም
- ባለጸጋ ቢደኸይም ሁሌ ያለው ነው የሚመስለው ለለው

የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ
- እንዳልሰማ ሆነ

የዝንብ ሽውታ የነገር ስልት ይበጥላል
- የሰው ንግግርን ካቋረጡበት ውሉ ይጠፋዋል

የዝንብ ተላላ ካንድ በሬ ደም ይቀርባታል
- ትልቁን ትቶ ትንሹ ላይ ማተኮር

የዝንብ ተባቱ የሴት ጭምቱ ሳይታወቁ ሞቱ
- የሴት ጭምት የላትም እንደማለት

የዝንጀሪትዬ ዝንጀሪት ባሌ ገደለ በነጋሪት
- አንድ ነገር በይፋ ሲደረግ ወይም ይፋ ሲሆን

የዝንጀሮ ልጅ ከዛፍ የመምህር ልጅ ከመጽሐፍ
- መልክ ስጠኝ እንጂ ሙያ ከጉረቤት እማራለሁ

የዝንጀሮ መነኩሴ የሰንበሌጥ አንካሴ
- የማይሆንና የማይታሰብ ነገር

የዝንጀሮ መንገድ ከገደል ያደርሳል
- የተንኮለኞች ሥራ ሔዶ ሔዶ ለመከራ ይዳርጋል

የዝንጀሮ ንጉሥ እሱው ይከምር እሱው ያፍርሰው
- አዛዥ ናዛዥ ራሱ ነው

የዝንጀሮ አንካሳ የውሻ እራት ይሆናል
- ደካማን ያገኘው ሁሉ አይለቀውም
- ተናካሽ ውሻ የዝንብ መቋደሻ

የዞረ ምን አመጣ ፌራና ፈንጣጣ
- የዙረት ትርፉ ድካምና በሽታ መሸመት ነው

የየጁ ቂስ ቅኔ ቢጉድልበት ቀረርቶ ሞላበት
- አንዳች ነገር ሲታጣ በሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲተካ ይችላል

የያዘውን ከወረወረ ፊሪ አይባልም
- ሰው ባለው ይሰለፋል

የደላው ሙቅ ያኝካል
- ሐሳብ የሌለበት ሰው የማይሆን የማይደረግ ነገር ያደርጋል

የደላው ውሻ ማር ይቀላውጣል
- የማይሆን ነገር ያልማል

የደመና ውኃ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም
- እናትን ትበድላለች ብሎ ማንም አያስብም

የደበሎ ተባይ የዳኛ አባይ ቢገልጡት አይታይ
- በደበሎ ውስጥ ያለተባይ እንዲህ በቀላሉ ሲታይ ወይም ሲገኝ አይችልም

የደባ ገበያ በሬው ባሥር ቆዳው በሃያ
- ተንኮለኛ የማይሆነውን እንደሚሆን አድርጐ ይናገራል

የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
- ያንኑ አንድን ሐሳብ መላልሶ መናገር ውጤት አይኖረውም

የደንቆሮ ተጣሪ የዕውር አዝማሪ ዘዋሪ
- የአካል ጉዳት ችግር ያለበት ሰው ለአንዳንድ ሁኔታዎች አያመችም

የደንቆሮ ዘፈኑ ያው አንድ ብቻ ነው
- የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ ቀልሶ

የደጃዝማችን ሚስት አይቼ ሚስቴን ጠላሁ
- የማያገኙትን መመኘት ከንቱ ልፋት

የተደገመ ተረገመ
- ሁለቴ መታለል እርግማን ያስከትላል

የደግ ጊዜ ባዕድ የክፉ ጊዜ ዘመድ
- ዘመድ ለችግርህ ይደርስልሃል

የደፋት ሬሳ የጠበሱት ዓሣ
- ለሚቀጥለው ተግባር በዝግጅት ላይ ያለ ማለት ነው

የዳቦ ልብ ልቡን የዳገት ጥግ ጥጉን
- ለጥቅም መሯሯጥ ለሥራ ጊዜ መሸሽ ጥሩ አይደለም

የዳኛ ልል ያማታል የአባል ልል ያፋታል
- የአለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

የዳኛ ጅሉ ያማታል ያመል ክፉ ያፋታል
- ዓመል ከሌላት መጣላትና መፋታት አይቀርም

የዳኛ ጅል ያማታል አባይ ምስክር ያስረታል
- የአለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

የዳገት ሩጫ የባለጌ ጡጫ
- ያዳክማል

የዳገት በረዶ የቆላ ዘንዶ
- በጣም አስከፊ የሆነ ችግር

የዳጉሳ እንጀራ በትኩሱ የባዕድ ፍቅር በአዲሱ
- ፍቅርና ቡና በትኩሱ ይጣፍጣል

የድሃ ሃብቱ እንቅልፋ
- ድሃ የሚጨነቅለት ሀብት ስለሌለው እንቅልፉን ሲለጥጥ ያድራል

የድሃ መድኃኒቱ የድንገቱ
- ድሃ ሲያመው የሚያኘከው ድንገተኛ የተባለው ሥር ነው

የድሃ ማጀት ቃጢ ማር ለማስቀመጥ አይችልም
- አይጥ ቤት ብቅል



የድሃ ቁም ነገሩ ገብስ አስከ አስሩ
- ድሃ ገብስ በመብላቱ እንደጠላም አድርጐ በመጠጣቱ ጥቅም ጥንካሬ አግኝቶበታል

የድሃ ብድር አይውል አያድር
- የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

የድሃ ተዝካር የጉባጣ ስካር
- ምንም ይሁን ያህል የጉላ ነገር የማይታይበት

የድሃ ነገር ማገገቻ የሰው
- የድሃ ነገር የተሟላ አይደለም

የድሃ ጉልበት በገበያ ያልቃል
- ድሃ ሲወጣ ሲወርድ ጉልበቱን ያባክናል

የድሃ ግድርድር ሀብታም ይጋብዛል
- እንግዳ ሲያፍር ባለቤቱን ይጋብዛል

የድሃ ጠላ ጧት አልፈላ ማታ አተላ
- መጠኑ ያነሰ ወይም በቂ ያልሆነ ነገር

የድሃ ጮማ የዱባ ስንጋ ነው
- ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ነው

የድህነት አሸከር ድህነት መስሎ ይታያል
- የፋሲካ ዕለት የተቀጠረች ገረድ ሁሌ ፋሲካ ይመስላታል

የድመት ማንቀላፋት አይጦችን ለማጥፋት
- ጅብ እስኪነክስ ያነክስ

የድመት ትዕግስት አይጥ እስክትይዝ ድረስ ነው
- ጅብ እስኪነክስ ያነክስ

የድንጋይ ልብ የኩበት ግንብ የሰውም
- ያሰሙያ በሰው ሙያ ውስጥ ለመገኘት መሞከር ራስን ማዋረድ

የድንጋይ መቀመጫ የባዕድ ፍቅር እያደረ ይቆረቁራል
- ከባዕድ ከተፋቀሩ በኋላ ቀስ በቀስ ይቀዘቅዛል

የድንጋይ ንፍሮ የብረት ቆሎ
- የማይሞከር ነገር

የድንጋይ ጦርነት የሸሮን ቀለብነት የሚለት ባርነት
- የሚያውቅ ያውቀዋል

የድፍድፍ ኩራት ውኃ እስኪገባበት
- የባለጌ እብሪት በቁጥጥር ሥር እስኪውል ነው

የዶሮ እንገት ክምንቸት
- ዞሮ ዞሮ ይቆያል እንጂ አይቀርም

የጀመሩትን መጨረስ የቆረሱትን መጉረስ
- ተገቢ ነው

የጅብ ሁለት ስበሩ የባለጌ ወታደሩ አስቸጋሪ ነው
- ሥርዓት የሌለው ምንጊዜም ለተነበረተሰቡ ሸክም ነው

የጅብ ለማዳ ያህያ ፍሪዳ የሰውም
- ምን ቢሆን ጅብ ከሰው ጋር ሊያኖር የሚያስችል ባሕሪ የለውም

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
- የአይጥ ችኩል የድመት አፍ ይልሳል

የጅብ እንግዳ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል
- ስደት ለወሬ ያመቻል

የጅብ ገበሬ የጦጣ ዘር አቀባይ የዝንጀሮ ጉልጓይ ሁሉም በየበኩሉ እበላ ባይ
- ለሥራ ሳይሆን ለመቀራመት የተሠማሩ ናቸው

የጅብ ጓደኛ ከጥንብ ያደርሳል
- ውሎም ምኞቱና ፍላጐቱ ያው በመሆኑ

የጅብ ፈሪ የሞት ቀሪ
- ሞት ለማንም የማይቀር ዕዳ ነው

የገላጋይ ትዕግስት የባለቤት መጠቃት
- ነገር ለማብረድ የተነሳ ሰው ቁጡና ተናዳጅ መሆን የለበትም

የገላጋይ ደም የለውም
- ገላጋይ ሲገላግል በሚደርስበት ጉዳት ማንንም መጠየቅ አይችልም

የገማ ሰው ሰውን አይሸሽም ሰው ከሱ ይሸሻል እንጂ
- የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም

የገበያ ሽብር ለሌባ ሠርጉ ነው
- ፍየል በግርግር እናቱን ይሰርራል
- የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል

የገባ ወንድና የታሰረ አንበሳ በብላሽ ያገሳ
- ገሌ የገባ ወንድ ልቆጣ ቢልም አያምርበት

የገብስ ብዙ ነዶ የጤፍ ስሱ ነዶ
- ፍሬ ያለው ቁምነገር ያለው ትንሹ ይበቃል

የገንዘብ አሮጌ ያባት ባለጌ የለውም
- ያበደርከውን ገንዘብ በተገኘበት ጊዜ ተቀበል

የገዛ ጌታ እግር ይዞ ይመታል
- ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ

የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ አዘንሽ ቅጣ አጣ ከቤትሽ አልወጣ
- እዚያው በዚያው አስቸጋሪ የሆነ ነገር

የገደል ማሚቶ ዳቦ ልስጥሽ ድፎ
- ያሉትን መልሶ ማለት ትርፉ ጊዜ ማጥፋት

የጉልበት ገሚሱ ምላስ ነው
- ጠላትን ማዳከሚያ ዋና መሣሪያ ፕሮፖጋንዳ ነው

የጉልበት ግማሽ አፍ ነው
- ጠላትን ማዳከሚያው በአፍ ጉዱን በማፍረጥረጥ ነው

የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም
- የሰዎች መቀያየር ምንም ለውጥ አያመጣም

የጉም ሌባ ጉም ሲጠፋ ወዴት ትገባ
- ተደብቃ ትደንሳለች ሰው ሰብስባ ትወልዳለች



የጉሮሮን መታነቅ ያይን መደንቆል ያስጥለዋል
- ለአንዱ ያሉት አንዱን ይጐዳል ሌላውን ይጠቅመዋል

የጉብል ዱላ በክርከማ ያልቃል
- ሲያሽሞነሙነው ያልቃል

የጋራ እርሻ የፍቅር መጨረሻ
- እርሻው ሳይታረስ ወሬ በማውራት ጊዜውን መፍጀት

የጋራ ወንጋራ
- የፉከክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

የጌታ ሆድ ጠዋት ከባድ ማታ ወላድ
- ሲጀምረው ጉዳዩን አከብዶ ኋላ ግን ቀላሉን ተቀብሎ ይሔዳል

የጌታውን እመካከት ሎሌው ይመልከት
- የጌታውን ባሕርይ ተከታዩ ያውቀዋል

የግመል መጫኛ ቢበጠስ ላህያ ይበቃል
- ጋን ሲያሚጥጡት ምንቸት ይሞላል

የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
- በመከራ ላይ መከራ በችግር ላይ ችግር

የጐረምሳ መልኩ እንጂ አነጋገሩ አያምርም
- በትዕቢት የተወጠረ በመሆኑ ንግግሩ አይጥምም

የጐረቤት ሌባ ቢያውቁበት ይሥቃል ባያውቁበት ይሰርቃል
- ቢያዩኝ እሥቅ ባያዩኝ እሰርቅ

የጐረቤት ሐሣብ ከገበያ አይወጣም
- በአንድ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች አስተሳሰብ ተመሳሳይነት ይኖረዋል

የጐበዝ ልቡ ክደረቱ የፈሪ ልቡ ከፊቱ
- የፈሪ ፍርኃቱ ክፊቱ ያስታውቅበታል

የጐበዝ ሹም የኀዳር ጉም አገር ይደረገም
- ጀብደኛ አለቃ ተከታዮቹን ለአደጋ ይዳርጋል

የጐበዝ አለላ የወሬ አፈሳ ይደርሳል እግር ሳይነሳ
- ወሬ ቶሎ ይደርሳል

የጐበዝ ክምር እያደር ይጨምር
- ጐበዝ ሠራተኛ በሀብት እየበገለጸገ ይሔዳል

የጐበዝ ዲዳ ባመቱ ምድረ በዳ
- ተከታዮቹን በንግግር የማያግባባ ኃላፊ ተከታዮቹ ጥለውት ይሔዳሉ

የጐበዝ ጉልበቱ ከደረቱ
- ጐበዝ ልቡን ሞልቶ ደረቱን ነፍቶ ይናገራል

የጐደለው ሲሞላ የተረፈው ሲከላ
- ባለው ቦታ አዳዲሶችን መቀበል በታው ሲሞላ የተረፈውን መመለስ

የጐጃም አዝመራ ሽምብራ ነው አሉ እኛም እንዳንበላ ተነቀለ አሉ
- የተባለውን እነሱም እኛም አላገኘነውም

የጓደኛ ምቀኛ የከብት ቀበኛ
- ቀን አያስቀምጥ ሌት አያስተኛ

የጓደኛ ወሮ ያጠናግር ዞሮ

- ወሮበላ ጓደኛ አይጠቅምም

የጓጉንቸር ልጅ መሔድ ሳትማር መዝለል ተማረች

- እንደአገሩ ይኑሩ እንደወንዙ ይሻገሩ

የጠሉት ሰው ቢቀር ጠላ ማለቁ አይቀር

- መሆን የሚገባው ነገር ከመሆን ምንም አያግደውም

የጠላቴ ጠላቴ ወዳጄ ነው

- ጠላቴን ስለሚያጠቃልኝ

የጠላ ክፋቱ አለመገኘቱ የልጅ ክፋቱ አለመስማቱ

- ልጅ የመከሩትን አይሰማም

የጠመመውን አቅንቶ የጐደለውን ሞልቶ

- ሁሉን አሳክቶ መገኘት

የጠረጠረ ስንቁን ቋጠረ

- መጠርጠር ጥንቃቄ ማድረግ ደግ ነው

የጠረጠረ ቤቱን አጠረ

- መጠርጠር ጥንቃቄ ማድረግ ደግ ነው

የጠረጠሩበት ድንጋይ ይጥሉበት

- ጥርጣሬ ካለ ወደአንዳች ድርጊት ይመራል

የጠሩት እንግዳ አራቱ ፍሪዳ

- ለወደዱት ሰው እቅም የፈቀደውን ሁሉ ያደርጓል

የጠበቀ ከራራ ባጥና ጣራ

- ሁለቱም ተመሳሳይነት አላቸው /ባጥ-ጣራ ነው/

የጠበኛ ፈስ ዐይን ያፈስ

- ጠበኛ ለው ምኑም ምኑም አይበጅ

የጠብ መነሻ የሰብስቴ እርሻ

- የጠብ መጀመሪያው የማይረባ ነገር ነው

የጠብ መነሾ አበድሪኝ እርሾ

- የጠብ መጀመሪያው የማይረባ ነገር ነው

የጠንቀኛ ፈስ ዐይን ያፈስ

- ጠንቀኛ ሰው ጠንቁ ከባድ ነው

የጠዋት አር እንደመጣ የማታ አር ደም እስኪወጣ

- ለፍቅር ተመቻችቶና ተዘጋጅቶ መገኘት

የጠጅ ቤት አዛዥ እተላ አጋዥ

- ከምኑም ላላገኘ ስሙ ብቻ ተረፈኝ

የጠገበ ሰው ራብን አያስብም

- ዛሬ ያገኘ ሰው ነገ አጣለሁን አያውቅም

የጠገበ ሰው የተራበ ያለ አይመስለውም

- የተመቸው ሰው ለሌላው አያስብም

የጠገበች ዶሮ ከነጭልፊት ማኅበር ትገባ

- ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ



የጠገበ ዐበደ

- የተመቸው ያለሱ ሰው ያለ አይመስለውም

የጠገበ እንግዳ ሳይቶች አይወጣም

- ምን ይለኝን የማያውቅ

የጠገበ ዕውር ዘንግ ይወረውር

- ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይሔዳል

የጠገበ ፍየል ካራ ይልሳል

- ጥጋበኛ ሰው ካለማወቅ ለሞት መንገድ ያበጃል

የጠጉር ጥቁሩ የነገር አጭሩ

- ነገር በበዛ በአህያ አይጫንም

የጢስና የልጅ መውጫ አይታወቅም

- ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም

የጣት ላይ ቅቤ ሆነች

- ይሳሱላታል

የጣመው ቀሰጠመው

- የተሻለ ወይም በብዛት የፈለገውን ለማግኘት መሞከር

የጣታ በሬ ለነገ ብሎ ይጠጣል ዛሬ

- ለነገ ማሰብ ይበጃል

የጣውንት ደግ የእንቧጮ ዘንግ የለውም

- ጣውንታሞች አንዷ ለአንዷ ደግ አታስብም

የጥር በልግ የብር ዘንግ

- በጣም የሚወደድ የሚፈለግ

የጥርስን እድፍ የራስን ጉድፍ፡

- ባለቤቱ አይታየውም ሰው የራሱ ስሕተት አይታየውም

የጥርስ ደም ሆነባት

- የማይነገር ነገር ሆነባት

የጥቁር ሴት ንቅሳት የምንድነው? ቢለው የእግዜር ቁጣ ነው አለው

- የጥቁር ሴት ንቅሳት በደንብ አይታይም

የጥቅምት በረዶ የጫካ ላይ ዘንዶ

- በጥቅምት ወር ላይ በረዶ ከዘነበ የደረሰውን እህል ያበላሻል

የጥቅምት እርሻ የናት ጉርሻ

- ተፈላጊና ውጤት ያለው ሥራ

የጥቅምት እርሻ ያባት ውርሻ

- ተፈላጊና ውጤቱ ያማረ ሥራ

የጥጋብለት ሁሉ አንበሳ የራብ ለት ሁሉ ሬሳ

- ሰውን ሰው የሚያደርገው እህል ነው

የጦመኛ ምቀኛ

- አንደኛውን ባይጾም ይሻለዋል

የጦም ቆሎ የቁልቁለት በቅሎ

- በቁልቁለት በቅሎ መቀመጥ አስቸጋሪ ነው

የጠም ቆሎ የበዓል ዶሮ
- ሁሉም ነገር እንደጊዜውና እንደሁኔታው አስፈላጊነቱ ይጐላል

የጦርነትን ነገር ከፈሪ አትምከር
- ምን ከማን ጋር እንደምትነጋገር አስቀድመህ ዕወቅ

የጠጣ ልጅ በዛፍ የመናፍቅ ልጅ በመጽሐፍ ማን ይችላል
- ከኃዲና ተጣራጣሪ አላግባብ ከመጽሐፍ ውስጥ ጥቅስ ሲጠቅሱ ይታያሉ

የጦጣ ሞኛሞኝ የዝንጀሮ ብልጣ ብልጥ የለውም
- ሁሉም እንደየባሕርዩ እንጂ ከተፈጥሮው ውጪ ሊሆን አይችልም

የጨለማ አፍጣጭ የዕውር ገልማጭ
- ውጤት የማይገኝበት ከንቱ ድካም

የጨረቃ ሒያጅ የምስክር ፈራጅ
- ለትዝብት የተዳረገ ተግባር

የጨረቃ ንጋትና የዕውር ሞት አይታወቅም
- ገጣጣ ለው ሳይሥቅ የሣቀ ይመስላል

የጨርቅ ነጩ የበራ ልጩ
- ሊሆን የማይችል ነገር ለማድረግ መሞከር

የጨነቀው ይዋጋል ያልደረሰበት ያዋጋል
- በሩቅ ያለ ችግሩን በደንብ አይረዳውም

የጨዋ ልጅ ሁሉ እርግዟል በሆዱ
- ሁሉም በሆዱ ቆሻሻ ነገርን ይዟል

የጨዋ ልጅ ሲያዝን ዓሣ በወንዝ ይመክን
- ከቤት ካልቀና በውጪም አይቀና አይሳካ

የጨዋ ልጅ ሲፋታ ይጋባ ይመስላል
- ሁሉንም በሣቅ በጨዋታ በመግባባት ይፈጸማልና ነው

የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው
- ሰው ሁኖ ከሞት የሚቀር የለም

የጨዋ ልጅ ከከተማ የድሃ ልጅ ከውድማ
- ለሥራ ለልፋት የፈጠረው ያው በሥራ ላይ በድካም ላይ ይገኛል

የጨውን ባለዳ በጨው ቢያባብሉት ጨዌን ማለቱ አይቀርም
- ንብረቴን የእኔ የሆነውን ስጡኝ ማለቱ አይቀርም

የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያሰቅሳል ሞኝ ይሥቃል
- ጠቃሚ ነገር ሲበላሽ ተቆርቋሪ ያዝናል ደንታ የሌለው ግን ያሾፋል

የጨጦ ክብት በየወጉ ይከተት
- ማንኛውም ነገር በወጉ በሥርዓቱ ይሁን

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም
- አንድ ሐሳብ በአዕምሮ ውስጥ ከገባ እየዋለ እያደረ መጉላቱ አይቀርም

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም
- በአዕምሮ ውስጥ የገባ ሐሳብ እየዋለ እያደር አሳሳቢ መሆኑ አይቀርም



የፈሳ ጠጅ የደረሰ ልጅ
- የደረሰ ልጅ መመኪያ ነው

የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ የሴት ትንባሆ ጉራሽ
- በጣም አስቀያሚና አስነዋሪ ባሕርይ

የፈረሰ አልጋ የተሸበረ ዜጋ
- አልጋ ፈረሰ የሚባለው ንጉሡ ሲወርዱ ስለሆነ ዜጐች ትንሽ ሲሸበሩ ይችላሉ

የፈረንጅ አሽከር ነጭ ለባሽ ሣሀን አመላላሽ
- ምንም እንኳ የተመቸው ቢመስልም ያው ተራ ሥራ ላይ የተሠማራ ነው ለማለት

የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል
- የጠሉት ነገር ይቆያል

የፈሪ ዱላ ሠላሳ ነው
- የማይጠቀሙበትን መሣሪያ መሰብሰብ ዋጋ የለውም

የፈሪ ገዳይነት ለማታ
- ፈሪ የሚፎክረው ማታ ምናምን ሲቀምስ ነው

የፈሰሰ አልታፈሰ
- የሔደ ካልተመለሰ

የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም የሞተ አይመለስ
- ባለፈ ነገር መጨነቅ አይገባም

የፈሲታ ተቆጢታ
- በራስዋ ስሕተት ሌላውን ትቆጣለች

የፈሳ የጥጋብም አይደል ሲረሳ
- አንድ ሰው ከሳተ መሳቱ አይረሳም

የፈስ ማደናገሪያው ዳቦ
- ሰዎች ትኩረት እንዳይሰጡት ማድረግ

የፈቷት ሚስት ያጠቡት ወጭት የወጡበት ቤት አንድ ናቸው
- ሚስት ከፈቷት ባዳ ማሽላ ከተቆረጠ አገዳ

የፋክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
- ፉክክር ለሥራ መጥፎ ነው

የፊተኛውን አሳረርሽ ቢሏት የኋለኛውን ጥሬ አወጣች
- ተጠንቅቆና ሁኔታውን ተከታትሎ በሥርዓት ያለመሥራት

የፊት መሪ የኋላ ቀሪ
- እዩኝ እዩኝ ማለት

የፊት ምስጋና ለኋላ ሐሜታ ያስቸግራል
- ለማመስገን እትቸኩል

የፊት እድፍ በመስተዋት የኀጢያት እድፍ በካሕናት
- ያለብንን ጉድለት በመስታወት አይተን እንደምናርም ሁሉ ኃጢያትም በካሕናት በሚሰጥ ሉባኤ ሊወገድ ይችላል

የፊት ክብት የእጅ ወረት
- በእጅህ ያለ ክብት እንደገንዘብ ይቆጠራል

የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ
- ጓደኞችህ እንዳይርቁህ በእንክብካቤ ያዝ

የፊት የፊቱ አለ ጓያ ነቃይ
- ያለፈውን ረስተህ የወደፊቱን ሁኔታ ተመልከት

የፋቂ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ
- በላይ በላዩ ሥራ መደራረብ የሰነፎች ተግባር

የፋቂ ቀንጆ ቡድንት አይተወውም
- ያን የተለመደ ባሕርዩን አይለውጥም

የፌጦ መስሎሽ ለናፍጭ ትቀምሽ
- ላይ ላዩን በማለት መታለል

የፌጦ ብቅል የብሳና ጌሾ የተልባ አሻሮ ይህን ጠምቆ ለማ?
- የለው ነገር ሰማይሰማ

የፍቅር ጣዕሙ በመሳሳሙ
- የሚዋደዱ በመሳሳም ፍቅራቸውን ያጣጥማሉ

የፍየል ልጁን የሌባ እጁን
- ሌባ እጁን ከተያዘ ወዴት ሊሔድ ይችላል

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ሐፍረት አይከድን
- እንዲያው ለምልክት ብቻ የሚገኝ

የፍየል ጭራና የሰው ሐሳብ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው
- ሰው ሁልጊዜ ለራሱ የሚመኘው ትልቅ ትልቁን ነው

የፍጅት ወራት እሳት በወንፊት
- በጣም አስጨናቂና የመከራ ወቅት

የፖሊስ ዘመድና የቤንዚን እመድ የለውም
- ምን ዘመድ ቢሆን ፖሊስ ያገኘውን ወደሕግ ከማድረስ አይዘናጋም

ያህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል
- መልካም ባሕርይና መጥፎ ባሕርይ ያላቸው ለየቅል ናቸው

ያህያ ሥጋ ካልጋ ሲሉት ካመድ
- ለእህያ ማር አይጥማትም

ያህያ ሥጋ ውርደተኛ አልጋ ላይ ቢያኖሩት መሬት ይተኛ
- ያህያ ሥጋ ካልጋ ሲሉት ከመሬት ወደለመደው ቦታ

ያህያ ቀበጥ ከጅብ ጡት ይጣባል
- ሰው ሲጠግብ አደጋ ላይ ይወድቃል

ያህያ ባል ከጅብ እያስጥልም
- የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ሐፍረት አይከድን

ያህያ እንግዳ የጅብ ራት ነው
- ከጠላቱ ያልተጠነቀቀ ለጠላቱ ሲሳይ ይሆናል

ያህያ ውኃ ጠጭ ሳይታወቅ መጣጭ
- ዘማዊ ሰው ዘማዊነቱ አንዳንዱ አይታወቅበትም

ያህያ ደግነት ጭነት ማብዛት
- እህያ የተፈጠረችው ለጭነት ነው



ያህያ ጆላፋ መስከ ያጠፋ የሹም ዘፋፋ አገር ያጠፋ
- ያለቃ ልል በጥፊ ያወላውል

ያህያ ፍለጋና የጥሬ ራት በጊዜ ነው
- በጊዜ የሚደረገው ካልተደረገ ጊዜ ካለፈ አደጋ ሊደርስ ይችላል

ያህያ ፍሪዳ የእባብ ለማዳ የለውም
- አህያ ስባ ካልተበላ ምን ረባ

ያለህ ምዘዝ የሌለህ ፍዘዝ
- ያሰው ይጠጣል የሌለው ያፈጣል

ያለመከራ አይገኝ እንጀራ
- ካልሠራህ የሚበላ የለም

ያስመከራ ጸጋ ያለድካም ዋጋ አይገኝም
- ሰፍተው ደክመው ነው ሀብት የሚገኘው

ያስመጥረቢያ ዕንጨት ለባሪ የቆማጣ ዘንግ ወርዋሪ
- ያለሥራ መሣሪያ ሥራን ማከናወን አይቻልም

ያለምቀኛ አይገኝ ፍቅረኛ
- ምን ቢሆን ምቀኛ አይጠፋም

ያለ ሴት ምን ያደርጋል ቤት
- ሴት ሰቤቷ አሳቢ ናት

ያለ ሴት ቤት ያለ በሬ መሬት
- ሴት ልጅ ሰቤቷ አሳቢ ናት

ያስሥራ መብል ያለዳኛ ውል
- ካልሠሩ ከየት መጥቶ ይበላል ያለዳኛ የተዋዋሉት ውል አይጸናም

ያለሥራ አይበላ እንጀራ ያለባል ቆጥ አይሠራ
- አንድን ነገር ለመሥራት ለዚያ ሥራ አስፈላጊው ነገር ካልተገኘ ያዳግታል

ያለስፍራው የተሰበረ ሊጠግኑት አስቸገረ
- ያለአግባቡ የተሠራን ሥራ ለማረም ለማስተካከል በጣም ያስቸግራል

ያለ በሬ ምን ያደርጋል ገበሬ
- ያለሥራ ማከናወኛ የዚህ ሙያ ባለቤት ነኝ ቢሉት ምን ፋይዳ አለው

ያለበት ይብላላበት
- ባለጉዳዩ ይጨነቅበት

ያለበት ይጉላላበት
- ባስጉዳዩ ይጨነቅበት

ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ
- ችግሩን የሚያውቀው እራሱ ባለቤቱ ነው

ያለአባቱ ቢዛቁን አባክኖ ያባክን
- የማይችሉትን ሥራ ለመሥራት መሞከር ማባከን ይሆናል

ያስአቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
- ያልተመጣጠነ ጋብቻ ውጤቱ አያምርም

ያለዕዳው ዘመቻ ዋ ብሎ መቅረት
- በማያገባው ገብቶ ትርፉ ጸጸት

ያለ ክንፍ መብረር ያለሥራ መክበር
- ሣይሠሩ ብልጽግናን መመኘት ከፈረሱ በፊት ጋሪውን ማስቀደም

ያለው ሳይዋደድ ለሞተው መናደድ
- በሕይወት ያሉት ሳይዋደዱ ለሞተው ማዘን

ያለውን ካልሰጡ በስም አይበሉ
- አንድን ሥራ በዘዴ ካልሠሩ ይከብዳል

ያለው ይመዛል የሌለው ይፈዛል
- ያለው ይጠጣል የሌለው ያፈጣል

ያለው ይበላል የሌለው ያፈጣል
- ያለው ሲበላ የሌለው ይቀላውጣል

ያለዘዴ ጋሻ እንቅብ ነው
- ሳላወቀው ፎገራ ዱሩ ነው

ያለዝናብ ነጐዳ ያለብርድ ዕዳ
- ሁኔታው በሌለበት መሻት

ያለ የሚኖር ይመስላል የሞተ ያልነበረ ይመስላል
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል

ያለ ይበዛል አለ ወፍጮ
- አንድ ነገር ቆይቶ ሊበረክት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል

ያለጊዜው የተወለደ ልጅ አባቱን ጥሎ አያቱን ያሰረጅ
- ያለጊዜ የሚሆን ሁሉ ችግርን ማስከተሉ አይቀርም

ያለጐረቤት ቡና ያለሙያ ዝና
- ያለሙያ ታዋቂነት አይገኝም

ያለጐታ ደረባ ያለልብስ ካባ
- መሠረታዊ ነገር ሳይኖር ሌላ ተጨማሪ ነገር አያገለግልም

ያለጐታ ደረባ ምንድነው?
- ምንም

ያለጥርስ ቆሎ ያለጓዳ አምባጓሮ
- ያለአጋር አንድን ሥራ ለመሥራት ውጤታማ አይክንም

ያለጨው በርበሬ ያለሞፈር በሬ
- ለሥራ ጠቃሚ መሣሪያዎችን ማሟላት ይኖርብሃል

ያለፊቱ አይቆርስ ያለቤቱ አይወርስ
- ሁሉም ነገር የሚከናወነው እሱ በተገኘበት ብቻ ነው

ያለፍርድ ማሰር በፈጣሪ ማማረር
- ምሬትን ሰቆቃን ለማስገወገድ ፍትሕን ማስፈን

ያለፍቅር ሰላም ያለደመና ዝናብ
- በሰዎች መካከል ፍቅር ካለ ሰላምም ይኖራል

ያለፍቅር ጸሎት ያለ ዕንጨት እሳት
- ለዓምላኩ እምነትና ጽናት የሌለው ቢጸልይ ጸሎቱ የሽክክ ጸሎት ይሆንበታል



ያሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ
- ስለአንቺ የሚወራው ጥሩ አይደለም

ያላረፈች ምላስ ሽማ ትልስ
- መንቀዥቀዥ ለችግር ይዳርጋል

ያላረፈች እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ትገባለች
- መንቀዥቀዥ ለችግር ይዳርጋል

ያላሰብከውን አግኝ
- በጐ ምኞት ወይም ምርቃት

ያላሳደጉት ውሻ ቤት ዘግተው ቢመቱት ዞሮ ይናከሳል
- የእራስ ያልሆነ ልጅ ቢቆጡት ከማጥቃት አይመለስም

ያላወቁ አለቁ
- ያላወቁ ለችግር ተዳረጉ

ያላዋቂ ቆራሽ ማዕድ አበላሽ
- የማያውቁትን እሠራለሁ ማለት ለማበላሽት ነው

ያላዘረ ሲዞር አደረ
- ይሉኝታን የማያውቅ

ያላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው
- ለድሃ ሁሉ ነገር ብርቁ ነው

ያላዩት አገር አይናፍቅም
- ያልሰሙት ነገር ክፉም መልካምም አይደለም

ያልሞላ ተርፎ አይፈስም
- በልኩ የሆነ ነገር አይበላሽም

ያልሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል
- ካልሞትክ ብዙ ጉድ ታያለህ

ያልሟል ይተረጉሟል
- አንድን ነገር ዐቅዶ በዕቅድ ይሠራል

ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ያጣላል
- ነገርን በጥሞና ያለማዳመጥ ስሕተት ላይ ይጥላል

ያልሰማ ጥጉ ነው ባልሽ ወዳጁ ነው
- አልበማሽም እንጂ ጠላትሽ ነበርኩ

ያልሰጡት ተቀባይ ያልጠሩት እቤት ባይ
- ሳይጠሩት እቤት ሳይልኩት ወዴት

ያልሳሉት አይላጭ ያላዩት አይቆጭ
- የማያውቁት አገር አይናፍቅም

ያልቆረጠ እግቡ አይደርስም
- ካልቆረጠ ታታሪ ካልሆንክ አያልፍልህም

ያልበሉት ዕዳ ያልጠሩት እንግዳ
- በጣም አስቸጋሪና አስጨናቂ ነው

ያልበላ ሬሳ ያልለበሰ እንስሳ
- ሰው ካልበላ መኖር አይችልም

ያልበላኝን ቢያከኝ አይገባኝ
- በማያገባው ነገር የሚገባ

ያልበሳ ዳኛ አያሟግት ያልጠጣ እንግዳ አይጫወት
- እንግዳን መጋበዝ አለብህ

ያልበጀው እሳት ፈጀው
- ሳያዋጣው ጀምሮ ከሰረ

ያልተመታ ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
- ባለጌ ሥርዓት የሌለው ምልቃቃ ልጅ

ያልተማረ አይጸድቅ ያልተወቀረ አያደቅ
- በጥሩ ሁኔታ ያልተዘጋጀ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ ውጤት አይሰጥም

ያልተማረ ዋናተኛ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ
- ከዳኛ ፊት ቀርቦ እንቢተኛ መሆን ሳልታሰበ እርቅና መቀጫ መዳረግ

ያልተረታ አይረታ ያልጠገበ አይማታ
- ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደአባቱ አንድ ቀን እንደእናቱ

ያልተሾመ አያዝ ያልቀሰሰ አያናዝዝ
- ሁሉም የሚመራው በባለሙያና በተፈቀደለት ሰው ብቻ ነው

ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ
- በሥነሥርዓት ያሳደገ ልጅ ባሕሪው ብልሹ ይሆናል

ያልተነካ ግልግል ያውቃል
- ችግርን ያላየ ነገሮችን አቅልሎ ያያል

ያልተገላበጠ ያራል
- እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል

ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ
- ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ

ያልተጠናከረ ድንገት ተሰበረ
- በደንብ ያልተሠራ ነገር ጥንካሬ የለውም

ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኮሰ ሽከላ ነው
- በችግር ጊዜ ያልታየ ወዳጅ አስተማማኝ አይደለም

ያልታረመ አፍ ከዋንጫ ይሰፋል
- ባለጌ ሰው ከአንደበቱ የሚወጣው ሁሉንም ሰው ያስቀይማል

ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ያልተደረገ እንጂ ያልተበላ ነገር የለም
- ያልተዳሰሰ ነገር የለም ነገር ግን ዛሬ ጉልቶ አይታይ እንጂ

ያልታደለ በረዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል
- ዕድለቢስ ሰው መጥፎ ነገር ላይ ይደርሳል

ያልታደለች ወፍ ዓይኗ በጥቅምት ይጠፋል
- ዕድለቢስ ሰው በሚበላበት ጊዜ ይሞታል

ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል
- ዕድለቢስ ሰው ሳይመቸው ያረጃል

ያልነበረ ያፈርሳል ቀዳዳ ያፈሳል
- ቤተሠሪ በኋላ ይመጣል



ያልወለደ አይነሳ የሽንብራ ማሳ
- ሰው ብዙ ጊዜ ስሙ የሚነሳው በልጁ ነው

ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው
- ያልወለደ ሰው እንደወለደ አይራራም ጨካኝ ነው

ያልወለደ እጋድሞ አረደ
- ያልወለደ ሰው እንደወለደ አይራራም ጨካኝ ነው

ያልወለዱ ሁሉ ጊደሮች ይባላሉ
- ከማንም ጋር እየዋሉ ያላገቡት ሁሉ ወይዘሪት ይባላሉ

ያልወለዱት ልጅ ያልወቀሩት መጅ
- ያልወለዱት ልጅ እንደራስ ልጅ አይሆንም

ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ
- የማይመስል ነገር ለሚሰትህ አትንገር

ያልዘሩት አይበቅልም
- የሚወለደው ያው እንደአባቱ እንደእናቱ ነው /የነሱን ባሕሪያት ያንጸባርቃል/

ያልዘራሁት በቀለብኝ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ
- ጥሩ ይሆናል ያልኩት መጥፎ ሆነብኝ

ያልዘራውን የሚበላ ዝንጀሮ ነው
- ሌላ የሠራውን ዘርፎ የሚበላ ሌባ ነው

ያልገደለ በሽታ ምስጋና የለውም
- አንድ ደረጃ ላይ ያላደረሰ ዝምድና ምን ፋይዳ አለው

ያልገደለ ዘማች ያልወለደ አማች
- የተሠማራበትን መለያ ነገር ባለመያዙ አይደነቅም

ያልጋ ሌሰኛ ሦስት ያስተኛ
- የሙት ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል

ያልጠረጠረ ተመነጠረ
- ያልጠረጠረ ሰው ጉዳት ይደርስበታል

ያልጠሩት መካሪ ያልሾሙት ፈታውራሪ
- አንድ ሰው ሳይፈልግ ልምከርህ የሚል ሰው አስቸጋሪ ሰው ነው

ያልጠሩት ሠርገኛ በትረኛ
- ሳይፈቅዱት መጥቶ ችግር የሚፈጥር

ያልጫ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ነው
- ለጥጋበኛ ሕግ ፊት እስኪቀርብ ድረስ ነው

ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል
- ችግር እስኪያልፍ መጨነቅ አይቀርም

ያመል ትንሽ ይጥላል በጭራሽ
- መጥፎ ባሕሪ ለአደጋ ያጋልጣል

ያመነታ ተመታ
- መወላወል ለአደጋ ያጋልጣል

ያመኑት ሲከዳ ይቀላል ዕዳ
- የተማመኑበት ወዳጅ አንድ አንዴ ጠላት ይሆናል

ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ
- የተማመኑበት ሰው ካደ
ያመጣሁት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
- ያሳደኩት ልጅ ጉዳት አደረሰብኝ
ያመጣል አንበሴ ይበላል ኮሳሴ
- ጉብዝ ያመጣውን ሰነፍ ይበላል
ያምላክ ነገር ሰንቱን አውቀሽው ወይ እኔ እበላው አንቺ አርመሽው
- አንቺ እንዳሰብሽው ላይሆን ይችላል /የዓምላክ ጥበቡ ብዙ ነው/
ያምራል ብሰው ሰነብር ልጅ አይድሩም
- የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም
ያምራል ብሰው ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው
- የማይሆን ነገር ከመናገር መቆጠብ ይሻላል
ያምራል ብሎ ይሸልሟል ያውቃል ብሎ ይሾሟል
- ከዕንጨት መርጦ ሰታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት
ያምሯል ይታደሏል
- ውበትን የሚሰጥ ዓምላክ ነው
ያምና ሞኝ ዘንድሮም ደገመኝ
- ያለፈው እንደገና ተመልሶ መጣ
ያምናውን ዘንድሮ አዋጁን በጆሮ
- ሁሉ ያወቀውን ምስጢር አደረጉት
ያሞላቀቁት ልጅ አይሆንም ወዳጅ
- ሞልቃቃ ልጅ ሰቤተሰቡ አስቸጋሪ ነው
ያሞሌ ጥጃ በወንዟ ትፋፋ
- አጥፌና ጠፊ
ያረረበት ያማስል
- ጉዳዩ የሚመለከተው ያስብበት
ያረሮ ልጅ ጠላፎ
- የሌባ ልጅ ሌባ
ያረሰ እንደልቡ ጉረሰ
- ጠንክሮ የሠራ እንደልቡ ያገኛል
ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ያረጀን ጅብ አህያ ይልሰዋል
- ካረጁ አይበጁ
ያረገዘች ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
- እርግዝና አያደር ይገፋል
ያራስ ክፉ መበሰት የአደጋ ክፉ እሳት
- እሳት ብዙ ጊዜ የተደከመበትን ንብረት ያጠፋልና ነው
ያራሷን በርጉዟ
- አንዱን በአንዱ
ያራሷን ገንፎ እርጉዟ ውጣ ሞተች
- ለእራስህ የማይገባህን ነገር ይገባኛል ማለት ለአደጋ ያጋልጣል



ያርጋጅ አንጓጅ
- በኃዘን ላይ ሁና ሌላውን ወደሩቅ ቦታ የምታነጉድ
ያሰረ ይፈታል የሰጠ ይረታል
- ወርቅ የሰጠ የፈለገውን ያደርጋል
ያሰቡት አይገድም ጉኔን ሳርገው ጋደም
- የሚታሰብ እይጠፋም አስቲ ትንሽ አረፍ ልበል
ያሳደግኋት ጥጃ አስችኝ በእርግጫ
- ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደሰ
ያሰለመዱት ሰው ሁልጊዜ እጅ ያያል
- የለመደ ሰው ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስለዋል
ያስታርቀኛል ሙተራ እያንዳንዱ እየኮራ
- ያመኑበት ነገር አንዳንድ ጊዜ ችግር ላይ ይጥላል
ያሽላል ያሉት ኩል ዓይን ያጠፋል
- ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደሰ
ያቀረቡልህን ጉረስ የተረፈህን መልስ
- በሰጡህ አትሰነፍ
ያበረ ወገኑን አስከበረ
- ኅብረት ጥሩ ነገር ነው
ያ በሬ ባላገደደ ያ በሬ ገደል ባልገባ
- ያሰቡት ነገር እንደነበር በቀየ
ያ በሬ ባገደደ ያ በሬ ገደል ገባ
- የማይፈልጉት ሰው ከአጠገብ እንዲርቅ የሚመኙት ምኞት
ያበደ ለኑሮው የፈረደ ለጉሮሮው
- ሰው የሚለፋው ለዕለት ጉርሱ ነው
ያበደች ጋሰሞታ እናቷን ትመታ
- ባጉረስኩ እጄን ተነከስኩ
ያበደና የወደደ አንድ ነው
- ፍቅር የያዘው ሰው ነገሮችን አያገናዝብም
ያበጠው ይፈንዳ
- የሆነው ይሁን
ያባ ሆይ መቋሚያ ላዩ በላ ታቹ ደላ
- ላይ ላዩን ጥሩ ውስጥ ውስጡን መጥፎ ነው
ያባበለሽ ሳያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
- ባልተጨበጠ ተስፋ አብሮ ከኖሩት ሰው አትቃቃሪ
ያባቱን ቢሰጡት ሕይወቱ ያባቱን ቢነሱት ሞቱ
- በአባቱ ንብረት የሚመካ
ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ
- ሳም ሲበዘብዝ ጭራውን ያዝ
ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ
- አታዳላ

ያባት ልጅ የደንደሰ ሥጋ
- ብዙም የማይጠቅም እንደእናት ልጅ የማይሆን

ያባት ልጅና ጆሮ አንድ ነው
- ብዙ ወደ ዋና አካል ያልተጠጋ እንዲያው ላይ ላዩን የሆነ

ያባት ምርቃት አያስገባም ጥቃት
- የአባት ምርቃት ለተሳካ ኑሮ ያመቻቻል

ያባት ሞቱን አይወዱ ረድኤቱን /ረዳቱን/ አይወስዱ
- እቤት የሌለውና መሪ የሌለው አገር አንድ ነው

ያባት አገር ከሞት አያስጥልም
- ከሞት የሚያስጥል የለም

ያባት እርግማን ሲዳና ማልቀስ
- አባት ልጁን ከልቡ አይረግምም

ያባት ዕዳ ለልጅ ያፍንጫ እድፍ ለእጅ የወፍጮ ዕዳ ለመጅ
- አባት ያጠፋው ለልጁ ይተርፈው

ያባት ወርቅ ባለዝና እህል ለቀጠና
- መቼም እህል ለችግር ጊዜ ነው

ያባት ደግ ይደልላል ያባት ክፉ ለእንጀራ ልጅ ያደላል
- የራሱን ትቶ ለውጪ ሰው የሚያደላ የሚያስገርም ሰው ነው

ያባያ ልጅ ወዳቂ ያራኝ ልጅ አጥባቂ
- ዋሾና ቤተሰቡ በሰው ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም

ያባይ ምልክቱ እንደበቱ የገዳይ ምልክቱ ሽልማቱ
- አንድ ሰው በመጥፎም ሆነ በበጐ የሚሰይበት ሁኔታ ይኖረዋል

ያባያ እናት አትታረድም
- ልጇ አባያ በመሆኑ አብሎ ያድናት ይሆናል

ያባያን እናት ውኃ ጠማት
- ሞልቶ ተርፎ ተቸገረች

ያባያ እንባ አይታገድም
- ያዞ እንባ ይስጠኝ

ያባያ ውኃ ተለያየ ሲሉት ተገናኘ
- ዞሮ ዞሮ መገናኘት አይቀርም

ያብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፍራል
- ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ

ያብዬን እከክ ወደ እምዬ ልከክ
- የራሱን ስሕተት ወደሌላው ማላከክ

ያብዬን ወደ እምዬ
- የራሱን ስሕተት ወደሌላ ሰው ላይ ማላከክ

ያተር ክምር የጭሰኛ ክብር
- ገበሬ በከመረው ክምር ብርቱ ገበሬ በሚል ክብር ይሰጠዋል

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ነው
- ኃይለኛን ለማጥቃት በዘዴ ነው



ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ የቁስ ልመና አናዞ
- ኃይለኛን በዘዴና በብልሃት ይቀርቡታል

ያንበሳ አማላጅ ጋማ ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተገን ይዞ
- ኃይለኛን ለማጥቃት በዘዴ ነው

ያንበሳ ኩረዳና የጨዋ ልጅ ሞግዚት ከመሆን ይሰውርህ
- ቀስጥን መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነው

ያንበሳ ገራም ይውላል ከላም
- በሬ ካራጁ ይውላል

ያንተን የሚመስል የኔም አለኝ ቁስል
- እኔም እንዳንተው ቁስል አለብኝ

ያንካሳ ልቡ እየሩሳሌም ነው
- ልብ እንቅርት ይመኛል

ያንዱ በሬ ሲሞት ላንዱ አጋዘኑ ያንዱ ፍስሐው ላንዱ ኃዘኑ
- የአንድ ኃዘን ለሌላው ፌሽታ ነው

ያንዱ ቤት ሲቃጠል ላንዱ ቋያው ነው
- የአንዱ ችግር ለሌላው ምንም አይደለም

ያንዱ ቤት ሳይጠፋ ያንዱ ቤት አይለማ
- የአንዱ ደስታ ለአንዱ ኃዘን ነው

ያንዱ ነገር ላንዱ የእንጀራ ልጁ ነው
- ለአንድ ቁምነገር የሆነው ለሌላው የማይረባ ተደርጐ ይወሰዳል

ያንዱ አገር መልከኛ ላንድ አገር ገባር ነው
- አንዱ አገር አዛዥ ሌላው አገር ታዛዥ ይሆናል

ያንድ ላም ወተት ያንድ እርሻ እሸት
- ከአንድ ምንጭ የተቀዳ

ያንድ ሚስቱን የሺ ከብቱን
- ማንም የእሱ የሆነውን እንዲነኩበት አይፈልግም

ያንድ ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ
- አትቸኩል አገናዝብ

ያንድ ሰው ፍቅር ባንድ እጅ እንደማጨብጨብ ያለ ነው
- ፍቅር ተመጣጣኝ ሲሆን ብቻ ነው

ያንድ ቀን ስሕተት የዘላለም ጸጸት
- መጥፎ ስሕተት እስከ ሕይወት ፍፃሜ ድረስ ጸጸት ያሳድራል

ያንድ በሬ እሸት ያንድ ላም ወተት
- ለብዙ ሰው ሲዳረስ አይችልም

ያንድዋ እለት አንድዋ ባልቴት
- እንዷ በሌላዋ ሠርግ እንደባልቴት ተቆጠራለች

ያንጉራጓሪ ጉልበት የተጋጋጭ ወተት
- የምትራገጥ ላም ብዙ ወተት አትሰጥም

ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል
- ያስቀመጡት ነገር ለችግር ጊዜ ያገለግላል

ያኩራፌ ምሳው አራቱ ይሆነዋል
- ባልሆነ ነገር የሚያኮርፍ ሰው ችግር ላይ ይወድቃል

ያኮረፈ ልብሱን አራገፈ
- ምንም ምንም ይቅርብኝ በሚል ሁኔታ

ያወረደ መዓቱን ያመጣ ምህረቱን
- መዓቱን በምህረቱ ይመልስልን

ያወቀ ተጠነቀቀ የዘነጋ ተወጋ
- ችላ ያለ ሰው አደጋ ይገጥመዋል

ያወቀ ተጠነቀቀ ያላወቀ ተነጠቀ
- እያያዙን አይተው ጭብጦውን ቀሙት

ያወቀ ናቀ
- ሚስጥርን የሚያውቀ ሰው ይንቃል

ያወቀ ዘለቀ ያላወቀ አለቀ
- ያወቀ ይጠቀማል የማያውቅ ግን ይጐዳል

ያወቁ ሲታጠቁ ያላወቁ ተሣሣቁ
- ያወቀ ሲጠነቀቅ ያላወቀው ተዘናጋ

ያዋቂ ሴት ቤት አለው ውበት
- ቤቷን አሰውባ ነው የምትይዘው

ያዋቂ አጥፊ የእስራኤል ጣፊ
- ያዋቂ አጥፊ ምህረት አይደረግለትም

ያዋጁን በጆሮ የዕለቱን በቀጠሮ
- የተነገረውን በሚስጢር ድብቁን በግልጽ

ያውሬ ሥጋ ለወሬ
- አደን ውያለሁ ለማለት ለዝና

ያው በገሌ አለች ድመት
- ትንሽም ብትሆን ዕድሌ በፈቀደልኝ እጠቀማለሁ

ያዙኝ ልቀቁኝ
- እጉል ፋከራ

ያዛኘር ቤተክርስቲያን ላሚ ያጋፋሪ ራስጌ ቋሚ
- አንዱ ወደአንዱ ሲሔድ ሌላው ቤት ያጠፋል

ያየ ልናገር ቢል የሰማ ላውራ አለ
- ያላረጋገጡት ነገር ያሰገምታል

ያየ ቢሔድ የሰማ ይመጣል የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል
- ከሚመለከተው ሰው የማይመለከተው ይብሳል

ያየ ቢሔድ ያልሰማ ይመጣል
- አልሰሚን ግባ በለው

ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል
- ተወላጅ ከቤተሰብ ንብረት ተቀራማች ነው

ያዩትን ሢሠሩ ዓይናቸውን ታወሩ
- ያልተረዳኸውን ነገር ማድረግ መሥራት ስጉዳት ይዳርጋል



ያዩትን ቢያጡ ያላዩትን ይቀላውጡ
- ከንቱ ምኞት መመኘት

ያይንን ጨንቋራ ሁሉ ያየዋል
- የልብን ክፋት ግን ያለዓምላክ ማን ያየዋል

ያይዘጌን ቤት ቡች ታውቀዋለች
- የግዴለሽን ቤት ብልጦች ይጐበኙታል

ያይጥ ምክር ድንቢጥ
- አንድ ዓይነት ተመሳሳይ የሆነ

ያይጥ እርዳታ በጭራንፎ ያልቃል
- ምንም የማይጠቅም ትንሽ የሆነች

ያይጥ ፋከራ ስመከራ ድመት ምን ሊበላ
- ያለአቅም መንጠራራት ስአደጋ ያጋልጣል

ያደለው ጆላ ቀለበት ያሰራል
- የተመቸው ሰው ያለው ሰው የሚያደርገውን ያጣል

ያደረገችውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
- ያላትን እንዲያዩላት ፊት ለፊት ማውጣት

ያደሩበት ጭቃ ከጭድ ይሞቃል
- ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን

ያደፈውን በአንዶድ የጐደለውን በሞረድ
- ያልተስተካከለን ነገር ማስተካከል

ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም
- አብሮ የኖረ መጥፎ ባሕሪ እየባሰ መጥቶ ችግር ላይ መጣሉ አይቀርም

ያዳኘ ውሻ ጠጉር ባፉ በትር ትርፉ
- ሮጦ ሮጦ አድኖ ምንም ሳያገኝ መቅረቱ

ያገሩን ስርዶ ባገሩ በሬ
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

ያገሩን ስርዶ ያገሩ በሬ ይወጣዋል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

ያገርህን ልጅ ብታገባት ሚስትህ፤ ብትፈታት እህትህ
- ካገርህ ልጅ ጋር ውስጥ ለውስጥ ስለምትተዋወቅ ትተባበራለህ

ያገር ልማት የገበሬ ሀብት
- ልማት ሁሉ በገበሬ ትከሻ ላይ ነው

ያገር ልጅ በምን ይመታል በክብት ያም እንዳይሔድ ያም እንዳይሞት
- የአገር ልጅ ከበድ ያስ ቅጣት አይቀጣም

ያገር ልጅ የማር ጠጅ
- የአገር ልጅ አሳቢ ነው

ያገር አድር ለንጉሥ ያስቸግር
- ያገር ደንብ በማንም ሊጣስ አይችልም

ያገባሽ ይፈታሻል ይብላኝ ለወሰደሽ
- አስቸጋሪ ሴት ለቤተሰቦቿ ሸክም ነች

ያገኝ በራሱ ያጣ ከዋሱ
- ያለው በራሱ እምነት ይጣልበታል

ያጓጉት ድንጋይ ተመልሶ ራስን
- ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ካፉ

ያጣ ሰው ያገኝ አይመስለውም
- የተራበ ሰው የሚጠግብ አይመስለውም

ያጣጣመ የቆረጠመ
- ጣዕሙ ያለው ከሚቆረጠመው ላይ ነው

ያጥንት ፍላጭ የሥጋ ቁራጭ
- የሥጋ ዘመድ

ያፈን እስክውጥ ዕድሜ ያሰጠኝ ይላል እርኩም
- የያዝኩትን አንድ ደረጃ ላይ እስክደርስ ጊዜ ስጠኝ እንደማለት

ያፍላ አማኝ አደረገኝ ለማኝ
- አዲስ አማኝ ኃይማኖት አጥባቂ ነው

ያፍላ የለው ቀርፋፋ
- የወጣት ቀርፋፋ የለውም

ይህ ሁሉ ከርከሬሻ ባንቺ የተነሳ
- ይ ሁሉ ችግር ሊደርስ የቻለው በአንቺ ጣጣ ነው

ይህ ሁሉ ጠባሳ ባንቺ የተነሳ
- ይሄ ሁሉ ችግር ሊደርስ የቻለው በአንቺ ጣጣ ነው

ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም
- ስሕተቱ በቶሎ ካልታረመ ከቆየ ችግር ያመጣል

ይህች ተፍ ተፍ እኔን ለመመንተፍ
- ይኼ ወዲያ ወዲህ አዘናግቶ ዘርፎ ለመሔድ ነው

ይሆን ብሰጥ ምን እውጥ
- ለጥቼ እኔ እንዴት እኖራለሁ

ይሆን ፈርቼ ደጅን በቀን ዘግቼ
- ይሄ ታይቶኝ ነው የተጠነቀኩት

ይህ አንበሳ ደም ደም አገሳ
- ለጠብ እየተዘጋጀ ነው

ይህ ከርከሬሻ ዳባዬን ለማንሻ
- ይሄ ሁሉ ጣጣ አንዳች ነገር ለመውሰድ መሆኑ ነው

ይሆናል ብዬ ጉሽ ጠመድኩት የማይሆን ቢሆን ፈትቼ ለደድኩ
- ጥሩ ነው ብዬ የጀመርኩት ሥራ ስላልሆነ ተውኩት

ይሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ በሆን
- አይቻልም እንጂ ቢሆን ኖሮ ሥጋው ብርካቱ ነበረው

ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ
- ወሬውን አልሰማሽ እንጂ ብትሰሚው ኖሮ ሰው ጋር አትደርሽም ነበር

ይሉሽን ብትሰሚ ጐንደር ላይ ክረሚ
- የሚመከረውን የሚሰማ ጥንቃቄ ያደርጋል



ይሉኝታና መጠቀም አንድ ላይ አይገኝም
- ይሉኝታ ከገበያ ጋር አብረው አይሔዱም

ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ
- ይሉኝታ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይጥላል

ይሉኝ አይል ውሽማ ዶሮ ሲጮህ ይማልላል
- ይሉኝታ የሌለው ሰው ሰዓት ቦታ ጊዜ አይመርጥም

ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ
- ይሉኝታ የሌለው ለምንም ለማንም አይጨነቅም

ይሉኝ አይል ጸሐፊ ከሙሴ ይገድፋል
- ይሉኝታ የሌለው ሰው ግልጽ የሆነ ስሕተት ይፈጽማል

ይመሰክረዋል ለነፍሉ ይፈተፍተዋል ለከርሱ
- የሚያደርጉትን ሁሉ በትክክልና በእውነት ማድረግ ይገባል

ይመስል አይመስል የጠይብ እጅ ተከሰል
- ቀጥቃጭ /ቢላዋ ማረሽ/ የሚሠራ እጅ አይጸዳም

ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ይሰማሉ የሚወዱ ይመስል
- አይጠሉምም የዚያኑ ያህል አይወዱምም

ይሙት የገደለ ይካስ የበደለ
- ሁሉም እንደሥራው

ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ
- መልሰህ መሳልለህ ከጥፋት ቦታ አትገኝ

ይሰጠኝ መሰሎኝ ሊሸጠኝ
- ግዛኝ ግዛኝ ብለው ሊሸጠኝ አሰበ

ይሰጡኝ ብሎ ከሰጠ ቆጥቦ የበላ በለጠ
- የበለጠ አገኛለሁ ብሎ የሰጠ ዞሮ ዞሮ ችግር ላይ ይወድቃል

ይሰጣል መሰሎ ይሸጣል
- የሚሰጥ እየመሰለ የራሱን ጥቅም የሚያሳድድ

ይሰበረኝ ይለንጥረኝ የሚሉ የለውን ልብ ሊሰብሩ
- የውሸት መሃላ መደርደር

ይቅር ለእግዜር ወድቆ አይሰበር ሞቶ አይቀበር
- ከተቀያየሙት ሰው ጋር ይቅር ለእግዚአብሔር መባባል ተገቢ ነው

ይቅደም ደግነት ይከተል ቸርነት
- የተቸገሩን ሰዎች ሰመርዳት ሞክር

ይበላ እንደቤቱ ይሠራ እንደጉልበቱ
- በአቅሙ የሚችለውን ነው የሚሠራው

ይበላ እንደቤቱ ይሠራ እንደጐረቤቱ
- በሥራ ከጓደኛ ማነስ የለበትም

ይበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
- ከሌለውና ካጣ ከነጣ ኖሮት አበላሉን ያላወቀው የበለጠ ይጐዳል

ይበጃል ያሉት መድኀኒት ዓይን አጠፋ
- ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደስ

ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሸንብራ

- እኔም ሌባ አንተም ሌባ ምን ያጣላናል በሰው ገበባ

ይታደሏል እንጂ ይታገሏል

- በአድልህ እንጂ በትግል የምታገኘው ነገር የለም

ይችም አንጀራ ሆና ሚጥሚጣ በዛባት

- ይቺም ኑሮ ሆና ምቀኛ በዛባት

ይወደዋል ካሉ ይመከሯል ይወደዋል ካሉ ይመስሏል

- የወደዱትን ክፉ እንዳያጋጥመው መገሰጽ መልካም ነውይወደዋል ካሉ ይመስሰዋል አይገድምከወደዱ አብሮ መምሰል ያለ ነገር ነውይወዷል ከሆድ ይታጠቧል ከክንድ

- ሰውን ከወደዱ እስከምናምኑይውጋህ ብሎ ይማርህ

- ከበደሉ በኋላ ማባበል ተገቢ አይደለም

ይውጋህ ብሎ ይማርክህ

- ከበደሉ በኋላ ማባበል ተገቢ አይደለም

ይደርሳል ባይ ብዙ አብላይ

- ለማግኘት መድከም ያለ ነው

ይደንቃል ይገርማል አህያ ከጅብ ጋር ይከርማል

- የማይመሰል ነገር

ይገርመኛል ገንፎ ከራቴ ተርፎ

- የማይመስል ነገር

ይጠላኝ ይመስል ይመታኛል ይወደኝ ይመስል ይመታኛል

- አይጠላምም አይወድምም

ይጥሉህ አትጥላቸው ይበድሉህ አትበድላቸው

- ዋጋህን ከፈጣሪህ ታገኛለህ



## መልመጃ 13 /የ/

ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ______ ግማቱ ከጭንቅላቱ
   ሀ. የዓሣ ለ. የዓሣማ ሐ. የጉማሬ መ. የሰው

2. የሚውል ሆድ ______
   ሀ. በማለዳ ይበላል ለ. በማለዳ ይጮሃል
   ሐ. በማለዳ ይርበዋል መ. በማለዳ ይጠግባል

3. ______ በሽማግሌ ይታረቃል
   ሀ. የቤተዘመድ ጠብ ለ. የነገር ጠማማ
   ሐ. የትዳር ጉባጣ መ. የተጣላ ጐረቤት

4. ______ ኢየሩሳሌም
   ሀ. ያንካሳ ልቡ ለ. የአማኝ ልቡ
   ሐ. የጸሎተኛ ልብ መ. የኃጢያተኛው ልቡ

5. የሚዜ ፈዛዛ ______
   ሀ. የሰውም ለዛ ለ. ሽቶ አይገዛ
   ሐ. ጥሎሽ አይገዛ መ. አይዘፈንም ለዛ

6. ______ ያፍንጫ ዕዳ ለእጅ
   ሀ. የአባት ዕዳ ለልጅ ለ. የእናት ዕዳ ለልጅ
   ሐ. ያገር ዕዳ ለልጅ መ. የንጉሥ ዘውድ ለልጅ

7. ______ አደባልቀህ ውቃ
   ሀ. የሌባን ዕቃ ለ. የሌባን ጠንቃቃ
   ሐ. የሌባን ጠበቃ መ. የሌባን ጓደኛ

8. የቡና ቀዝቃዛ ______
   ሀ. የሹም ፈዛዛ ለ. የቀን ደንጋዛ
   ሐ. ያልጠራ ጠራ መ. የፋንጋ ፋንጋ

9. ______ መፋጀቱ
   ሀ. የቡና ስባቱ ለ. የቡና ጥቁረቱ
   ሐ. የቡና ጥማቱ መ. የቡና ጣዕሙ

10. የቤት ቀጋ የውጭ ______
    ሀ. አልጋ ለ. ወላንላ ሐ. በርጩማ መ. ወንበር

11. የሚያልፍ ውኃ ______
    ሀ. ያዋርዳል ለ. አደረገኝ ድሃ
    ሐ. ይረጫል ለንስሐ መ. ገንዘቤን ወሰደው

12. የሴት ዘንገኛ ______ ምቀኛ
ሀ. የጉረቤት ለ. የእናት ሐ. የዘመድ መ. የወዳጅ

13. የሴት ጉልበቷ ______
ሀ. ምላሷ ለ. እጇ ሐ. ባሏ መ. መልስ የለም

14. የሴት ጠጪ ______ ፈንጪ
ሀ. የአህያ ለ. የእንቦሳ
ሐ. የግመል መ. ሁሉም መልስ ነው

15. የሥንዴ እራራ ______ መራራ
ሀ. የሬት ለ. የሴት ሐ. የስኳር መ. መልስ የለም

16. የስድብ ______ የለውም
ሀ. ምርቃት ለ. ቡራ ከረዩ
ሐ. አበጥ መ. ሁሉም መልስ ነው

17. የሥጋ ትል ______ ጥል
ሀ. የከብት ለ. የወዳጅ ሐ. የዘመድ መ. ባዕድ

18. የሥጋዬ ቁራጭ ___
ሀ. የብርሌ ጭላጭ ለ. የእጥንቴ ፍላጭ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ መ. መልስ የለም

19. የሸንጉ ዓይን ______ ይሰብራል
ሀ. ጉድን ለ. እጅ
ሐ. ጉልበት መ. ሁሉም መልስ ነው

20. የሹም ሰነፍ ______
ሀ. ያወራ ለ. ይለማመጥ
ሐ. ይለፈልፍ መ. ያሥራል

21. የሺህ አካላት መሰብሰቢያው ______
ሀ. እናት ለ. አቤት
ሐ. እጉረቤት መ. መልስ የለም

22. የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ______
ሀ. ገመድ ለ. ልጥ
ሐ. ሲባጉ መ. ሁሉም መልስ ነው

23. የሽሮ ድንፋታ ______ እስኪመጣ
ሀ. በርበሬ ለ. እንጀራ ሐ. ዳቦ መ. ቂጣ

24. የቀበረ ______
ሀ. ተንሳገለ ለ. አከበረ ሐ. ተቀበረ መ. ከሐሳብ አረፈ

25. የቀበጡ ዕለት ______
ሀ. ሞት አይገኝም ለ. አይገኝ ሞት
ሐ. ይሰባበሩ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



26. የቂል ______ ቂል
ሀ. ጓደኛው ለ. ገንዘብ ሐ. ሀብት መ. ለ እና ሐ

27. የቁጥር መጨረሻ ______
ሀ. ዝም ለ. እልፍ ሐ. ሚሊዮን መ. መልስ የለም

28. የቀጂ ልጅ ______
ሀ. ጠጭ ለ. አስቀጂ ሐ. አጣጪ መ. መልስ የለም

29. የቂስ ምንደኛ ______ በትረኛ
ሀ. የሞኝ ለ. የቂል ሐ. የሴት መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

30 የቂስ ቀማኛ ______ ምቀኛ
ሀ. የጉረቤት ለ. የእናት ሐ. የወዳጅ መ. የዳኛ

31. የቂስ ነጋዴ ______
ሀ. ይመስላል ወንበዴ ለ. ይመስላል ቅልስልስ
ሐ. ይመስላል አትራፊ መ. መልስ የለም

32. የቆቅ አውራ ይውላል ______
ሀ. ጉረቤት ለ. ተራራ ሐ. ጫካ መ. እመንደር

33. የቆረጠ ______
ሀ. ተመነጠረ ለ. አመለጠ ሐ. አስመለጠ መ. ተለማመጠ

34. የበላበትን ______ ሰባሪ
ሀ. እጅ ለ. ወጪት ሐ. ሣህን መ. ምጣድ

35. የቆዳ ጓንታ ______ ሠርጉ ነው
ሀ. ለውሻ ለ. ለጅብ
ሐ. ለአህያ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

36. የበላ ቢያብል ______ ይናገር
ሀ. ፊቱ ለ. ጀርባው ሐ. ገላው መ. ሁሉም መልስ ነው

37. የበላች ብትዘፍን ______ ታዝን
ሀ. ያልበላች ለ. የቀላወጠች ሐ. እያበደች መ. ያበላች

38. የበሬ ቀንዱ ______ ግንዱ
ሀ. የወላጅ ለ. የወይራ ሐ. የግራር መ. የዋንዛ

39. የበሬ ሆዳም ______ አይጉዳም
ሀ. ቢሸለም ለ. ቢሸልሙት ሐ. ቢሞት መ. ቢጠፋ

40. የበላይ ______
ሀ. አካባጅ ለ. አዳባይ ሐ. አዛዥ መ. ተናዛዥ

41. የበሬ ላቢ ______ አላቢ
ሀ. የቤት ለ. የጉረቤት ሐ. የልጅ መ. መልስ የለም

42. የበሬ ዳተኛ ________
ሀ. ተደራርቦ ተኛ    ለ. እመሀል ይተኛ
ሐ. ሮጦ ከተኛ    መ. ይሞታል በዳኛ

43. የበሬ ዕቃ ________ አለቃ
ሀ. የባለቤቱ ለ. እየራሱ ሐ. የአሀያ መ. መልሱ የለም

44. የበሰበሰ _____ አይፈራም
ሀ. ባለቤቱን ለ. አለቃን ሐ. ዝናብ መ. ጀግና

45. የቡና ቀዝቃዛ ______
ሀ. የሹም ፈዛዛ    ለ. የልጅ ፈዛዛ
ሐ. የዐዋቂ ፈዛዛ    መ. መልሱ የለም

46. የባለጌ ባለሟል _____ ያያል
ሀ. ሀብት    ለ. ገንዘብ
ሐ. ቂጥ ገልቦ    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

47. የባሰ አለ _______ አትፍታ
ሀ. ጥጃሀን    ለ. ፍየልሀን
ሐ. ሚስትሀን    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

48. የባዕድ ፍቅር _______ አንድ ነው
ሀ. የውኃ ጌጥ ለ. የክብት ሐ. የነገር መ. የሰው ጌጥ

49. የቤቴ መቃጠል ______ በጀኝ
ሀ. ለልመና    ለ. ለትኋኑ
ሐ. ለእርዳታ    መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል
ሀ. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
ለ. ለተሾመ ይሟገቱለታል ለተሻረ ይመለከሩበታል
ሐ. እግዜር የጣለውን እናት አታነሳውም
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

2. የእነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ
ሀ. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ
ለ. የቸኮለ አፍሶ ለቀመ
ሐ. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነከሳል
መ. ሁሉም መልስ ነው

3. የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
ሀ. ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል
ለ. የላጭን ልጅ ቅማል በላው
ሐ. ራስ ሳይጠና ጉተና
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



4. የአብዬን እከክ ወደእምዬ ልከክ
ሀ. የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ
ለ. ያለዋዛ ዋዛ ቅቤም አያወዛ
ሐ. ለሃምሣ ጋን አንድ አሎሎ
መ. መልስ የለውም

5. የወረወርኩት አንካሴ ተመልሶ በራሴ
ሀ. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
ለ. ድንጋይ ቢያጉኑት ተመልሶ ባናት
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

6. የቸገረው እርጉዝ ያገባል
ሀ. የተቸገረ ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል
ለ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ሐ. በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
መ. መልሱ የለም

7. ያስደግሁት ውሻ ነከሰኝ
ሀ. ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች
ለ. ባጉረስኩኝ እጄን ተነከስኩኝ
ሐ. እጽድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
መ. ሁሉም መልስ ነው

8. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ሀ. በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ
ለ. አተርፍ ባይ አጉዳይ
ሐ. ዓሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
መ. ሁሉም መልስ ነው

9. የሞተ አይከሰስ የፈሰሰ አይታፈስ
ሀ. ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም
ለ. ላለፈ አይጸጸቱም ለሚመጣው አይበለጡም
ሐ. ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ ማቀፍ
መ. ሁሉም መልስ ነው

10. ያላሰበ ተመነደበ
ሀ. ያልጠረጠረ ተመነደበ
ለ. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
ሐ. ከቆረሰ የጉረሰ
መ. መልሱ የለም

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1.ያባይን ልጅ ውኃ ጠማት | ሀ. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ |
| 2.የታጠቀ ሳለ ያልታጠቀ ያማርራል | ለ. የቸኮለች አፍላ ለቀመች |
| 3.ያልተገሳበጠ ያራል | ሐ. ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ |
| 4.የሆድ ምቀኛ አፍ ነው | መ. ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል |
| 5. የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል | ሠ. በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ |
| 6. ያብዬን እከክ ወደ እምዬ ልክክ | ረ. የላጭን ልጅ ቅማል በላት |
| 7. የሺ ፍልጥ ማበሪያው ልጥ | ሰ. ፍየል በልታ በበግ አበሰች |
| 8. ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ | ሸ. በሰው ቁስል ዕንጨት ስደድበት |
| 9. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል | ቀ. የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ |
| 10. ያልጠረጠረ ተመነጠረ | በ. ጅብ የማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል |
| 11. የራሷ ጊዜ አለቀሰች የሰው ጊዜ ሣቀች | ተ. ያሳሰበ ተመነደበ |
| 12. የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም | ቸ. ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ |
| 13. የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ | ኀ. ሰው በመልካም ሥራው ይወደዳል |
| 14. ያይጥ እንግዳ ከስልቻ ውስጥ ጉዝጉዙልኝ አለች | ነ. ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ |
| 15. ይገርማል እህያና ጅብ አብሮ ይከርማል | ኘ. ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ |
| 16. የተከፋ ተደፋ | አ. ማን ያውቃል አገር ምን ይጠብቃል ማገር |
| 17. የሰው አገሩ ምግባሩ | ከ. በሬ ካራጁ ይውላል |
| 18. የነገር ወጡ ማዳመጡ | ኸ. ተናዳጅ እንጂ እናዳጅ አይሞትም |
| 19. የምትኮነን ነፍስ ጉረቤት ያውቃል | ወ. በቡሃ ላይ ቆረቆር |
| 20. የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ | ዘ. ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል አያርፍም ከቀዘነ አይድንም |



# ደ

ደህና ሲታጣ ይመለመሳል ጉባጣ
- ተፈላጊው ነገር ሲታጣ ባለው ነገር መጠቀም ይገባል

ደህና ወገን ያጣ ወየው ያለበት ጣጣ
- ለክፉ ጊዜ የሆነህ ዘመድ ከሌለህ በጣም ትቸገራለህ

ደህና ጦር ያለው ለግንብ ይሞክረው
- ጥንካሬውን ለማየት በግንቡ ላይ ይየው

ደመና ለዝናብ ድግስ ለሆዳም
- ሆዳም ድግስ አይቶ አይመለስም

ደመና በሰማይ የጨዋ ልጅ ባደባባይ
- የጨዋን ልጅ ሁሉም ሰው ያከብረዋል

ደመናን የጨበጠ ሰማይን የቧጠጠ የለም
- ሊሆን የማይችል ነገር ተስፋ መጠበቅ አይገባም

ደም ቢያለቅሱ ድንጋይ ቢነክሱ
- የፈለገ ነገር ቢመጣም የማይሆን ነገር ነው

ደም ተቃብቶ ዝንብ አይፈሩም
- ደፍረው የገቡበት ነገር ምንም አያስፈራም

ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ
- አንዴ ከገባህበት በኋላ የመጣው ቢመጣ ማፈግፈግ የለብህም

ደም ከውኃ ይቀጥናል
- ሰው ለዘመዱ ይቆረቆራል

ደም ካልፈሰሰ ስርየት የለም
- ክብት ካልታረደ ዕርቅ የለም

ደሞዙ ሥንዴ ሥራው የምን ግዴ
- የሚከፈለው ደሞዝና ሥራው አይመጣጠኑም

ደሞዝተኛ አርፈህ አትተኛ
- ሥራ ሠርቶ ማግኘት ይገባል

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ይኮበልላል በሐምሌ
- ሰው ከሠራ ማግኘት አለበት ካላገኘ ደግሞ ይከዳል

ደረስሁ ልጅ ፈላሁ ጠጅ
- ለአቅመ አዳም ደርሻለሁ

ደረቅ ይቀመጠሳል እርጥብ ይጉብጣል
- እያያዙ ካላማረ ወዳልተጠበቀ ሁኔታ ያመራል

ደረቴን ቢያመኝ እግሬን አገመኝ
- የሚሆን እያለ የማይሆን ነገር ማድረግ

ደረጃ ለፍቶ መሔጃ
- በሥልጣን ከፍ ከፍ ሲሉ ፎቶ አንሺ አይጠፋም

ደስታ በሽታ
- ከመጠን ያለፈ ደስታ ያልሆነ ነገር ለመፈጸም ይገፋፋል

ደስታና መከራ ቀኝና ግራተፈራራቂ ናቸው
ደባል ሲሰነብቱ ይሆናል ባለቤት
- አንድ ሰው ራሱጋ አንድ ዕቃ ብዙ ጊዜ ከተቀመጠ የራሱ ይመስለዋል

ደባ ራሱን ስቶ ድጉሱን
- ተንኮል ሠሪውን ያጠፋዋል

ደባልና ሹመት ያለሰበብ አይሔድ
- ያለምክንያት ሰው ከሥልጣን አይወርድም

ደብር ለላስታ ድግድግታ ለጌታ
- ጌታ ፊት ሲቀርቡ ማደግደግ አክብሮት ማሳየት የግድ ነው

ደብተራ ሲኮራ አቤተክርስቲያን ገብቶ ጭራ ይይዛል
- ያስቦታውና ያስሙያ መኮፈስ

ደብተራና ተማሪ ስልፍና ሱሪ
- በሰልፍ ላይ ለሰልፍ የሚሆን ትጥቅ ይዞ መገኘት ተገቢ ነው

ደብተራ የዘኬ ጉተራ ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር
- ደብተራ ከደጀሰላም የማይጠፋ ስለመሆኑ

ደንቆሮ ከሚያጫውትሽ የሚስማ ያውጋኝ
- ከማይም ይልቅ ጥቂት ዕውቀት ካለው ጋር ቢወያዩ መግባባት ይቻላል

ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል
- ስለሰው ስለራሱም ወሬ የማይከታተል ሰው መጥፎ ነገር የሰማ ዕለት በጣም ይበሳጫል

ደወል ለአንበሳ ባማረበት ታዲያ ማን ይሰርበት
- ምን ዕውቀት ቢኖር ከፍ ያለ ሰው ዘንድ ማን ያደርስዋል

ደወል እንደ ጠዋቱ ትጮኻለች
- አሁንም ቀድምም ሁኔታዎች አንድ መምሰላቸው

ደጃቸውን ሳይዘጉ ሰውን ሌባ ይላሉ
- በራቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ይላሉ

ደጃፉን ጥሎ በጓሮ ይመጣል
- ትክክለኛውን መንገድ ሳይሆን ያልሆነውን መንገድ ይዞ ይጓዛል

ደገኛ ሲያርስ ቆለኛ ያነፍስ
- የአርሻው ወቅት ለየቅል ወይም በተለያየ ጊዜ በመሆኑ

ደጉ ነገር ሳያልቅ ክፉ መናገር
- ጥሩው ነገር ሳያልቅ መጥፎ መናገር አይገባም

ደግ ሰው ከእንጀራው ቆርሶ ከወጡ አጥቅሶ
- ደግ ሰው ለደግነቱ ወደር አይገኝለትም

ደግ ሳይበላ ክፉ ይመራ
- ሰው በበላው መጠን እንጂ ከዚያ በላይ እንዲሠራ አይጠበቅም

ደግና ማለፊያ ትግልና ልፊያ
- ደግና ማለፊያ ነገር እንዲሁ በከንቱ አይገኝ



ደግ አባት እርስት ያቆያል ክፉ አባት ዕዳ ያቆያል
- ደግ አባት ለልጁ ቅርስ ለማቆየት ተግቶ ለፍቶ ይሠራል

ደግ ጌታ ሲለግስ እንደፏፏቴ ያርስ
- ለስጋስ ጌታ የሚያርስ ገበሬ ሲያርስ አይለግምም

ደግ ጐረቤት ዕቃ አያስገዛም
- ሁሌ ዕቃ የሚያውስ ጐረቤት ጐረቤቱን ያዘናጋል

ደግ ጐረቤት ውሻና ድመት ያሳድጋል
- ውሻ ከውጪ ድመት ከቤት ጠላትን ይከላከላሉ

ደግ ጐረቤት ያወጣል ከመዓት
- ደግ ጐረቤት ፈጥኖ በችግር ጊዜ ይደርሳል

ደፋር ሴት ጉልቻ ረግጣ ትወጣለች
- የማታገናዝብ ሴት በጥጋቧ የሞቀ ቤቷን አቀዝቅዛ ትሔዳለች

ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
- ጉበዝ ሰው ከችግር በዘዴ በመላ ይወጣል

ደፋር ወጥ ያውቃል
- ያለ የሌለውን ወጡ ውስጥ በመጨመር ያጣፍጣል /ሳይለስት/

ዱላ ለባለጌ ምርኩዝ ለአሮጌ
- አቅመ ደካማን መንከባከብ ባለጌ መቀጣት አለበት

ዱላ የሚጠላው ሽክላ ብቻ ነው
- ቅጣትን የሚጠላ የለም ለሁሉም ቅጣት ይበጃል

ዱላ ይዞ ሌባን መጠየቅ
- ሌባ ከተያዘ በኋላ በዱላ ልቡን ማጥፋት ነው

ዱቄት በአመድ ይሥቃል
- አንዱ በአንዱ ሲሥቅ ጀምበር ጥልቅ

ዱባ ባገሩ ጋን ያህላል አሉ
- ለማንኛውም ቢሆን ኩራት በአገር ነው

ዱባና ቅል አበቃቀሉ አንድ ይመስላል አበላሉ ለየቅሉ
- አዬ ሌላ ወዬ ሌላ

ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል
- አስተዳደጋቸውና ባሕሪያቸው የተለያዩ ናቸው

ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል አበላሉ እየቅል
- ቢመሳሰሉም የተለያዩ ነገሮች ናቸው

ዲያቆን ሲጠግብ በጧፍ ይማታል ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል
- ጥጋብ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት እንድትፈጽም ይገፋፋሃል

ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ
- ጥሩ ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም

ዳሩ ምን ይሆናል ሆነና ሆነና
- እንዴ ሆኗል ምን ይደረጋል

ዳሩ ሲፈታ መሃሉ ዳር ይሆናል
- መካከሉ የተጠናከረ እንዲሆን ዳሩ የተከበረ መሆን አለበት

ዳር ዳር ያለ በመሃል የከበረ
- ክብረት ሀብት ያገኘ ዳር ዳር ይላል እንጂ ደፊር ደፊር ብሎ አይጋጭም

ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን
- ለሥራ ጊዜ መሸሽ ለምግብ ጊዜ መቻኮል መንገብገብ ጥሩ አይደለም

ዳቦ በገና ቡና በጀበና
- ሁሉም በየጊዜውና በአስፈላጊው የሥራ መሣሪያ ሲከወን ያስደስታል

ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ
- ሁሉንም ነገር በየጊዜው ካልተጠቀሙበት አላስፈላጊ ነው

ዳቦውን ጉርሶ ደሙን አብሶ
- የፈሰሰውን ደም የሚያስረሳ ወይም የሚተካ ካሣ አግኝቶ

ዳቦ ያለቅርፊት ጠላ ያለምርጊት
- በምርጊት ያልቆየ ጠላ ይነፍስበትና ጣዕሙ መልካም አይሆንም

ዳተኛ በሬ ሀብታም ነው
- አባያ በሬ በመሆኑ በሥራ ጊዜ ለሽ ብሎ ይተኛል

ዳኛ ሁን እንደኛ
- ከሕዝብ ጋር መመሳሰል ያስፈልጋል

ዳኛ ለዳኛ ያወርሳል ጉም ተራራ ያለብሳል
- አንድ ነገር ለሚቀጥለው ሰው ወይም ባለሙያ ይሸጋገራል

ዳኛ ምን ያደላ ከተረታው ሲበላ
- ሰው ለጥቅም ሲል አድሎ መሥራት ያዘወትራል

ዳኛ ሲመረምር ከራስ ይዞ እስከ እግር
- ሕግ የያዘው ነገር በትክክል ይመረመራል

ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጁ
- ከባለቀትር አትቀታተር

ዳኛ ሲያዳላ በዳኛ እህያ ሲያጋድል በመጫኛ
- ትክክለኛ ፍርድ ከሌለ ለበላይ ማመልከት ይገባል

ዳኛ ሲገኝ ተናገር ውኃ ሲጠራ ተሻገር
- ዳኛ ሲኖር ተናገር ውኃ ሲጉድል ተሻገር

ዳኛ ስበር በእጅ ከበር
- ሠርተህ ለፍተህ ጥረህ ግረህ ሀብት ለማግኘት ሞክር

ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ
- ዳኛ መናቅ ከችግር ላይ ይጥላል

ዳኛ ቢንቁ የተያዘ እህል ይወቁ
- ንቀት ተገቢ ነገር አይደለም

ዳኛ ቢያጉድል በዳኛ
- ለዳኛም ዳኛ አለው

ዳኛና በሬ ሀብታም ነው
- በሬ እርሶ አምርቶ ባለቤቱን ሀብታም ያደርገዋል

ዳኛ እውጥቼ ዘንግ አቅንቼ
- በዳኛ ፊት ከባለጋራዬ ጋር ተከራክሬ



ዳኛ አያነቅፉ እሳት አይታቀፉ
- አንድን ነገር በአግባቡ እንጂ ከአግባብ ውጪ መያዝ አደጋ ያስከትላል

ዳኛ ካዳላ ጭንቱ ቀላል
- ዳኛ ካዳላ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ይቀላል

ዳኛ የወል ምሰሶ የመካከል
- ዳኛ ለከሳሽም ለተከሳሽም የጋራ ነው

ዳኛ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት
- ዙሪያው ገደል የሆነበት

ዳኛ የፈረደው ስለት የቀደደው
- ዳኛ የፈረደው ያለቀለት ጉዳይ ነው

ዳኛ ያደላበት እሳት የበላበት
- ተመልሰው ሊያስተካከሉት የማይቻል እለቶጋሪ ነገር

ዳኛ ያፈሰሱለት ፈረስ የከለከሉላት
- ለጨፈ የሰጠውን ዳኛ ይቀበላል

ዳኛ ይመረምራል ጣዝማ ይሰረስራል
- ቢያጥቡት ይነጣል ቢመረምሩት ይወጣል

ዳኛ ገንዘቡን ተቀማ
- ያባይን ልጅ ውኃ ጠማው

ዳኛ ፍርድ አይከላ እህል ጉታ አይሞላ
- አንድ ሰው ለፍቶ አምርቶ ጉታ ካልሞላ ከንቱ ድካም

ዳኞች ከመረመሩ ይናገራል ምድሩ ይገኛል ነገሩ
- ዳኛ ነገርን መርምሮ የሐቁን ይፈርዳል

ዳከዬ ከውኃው ፈረስን ከገለባው
- እነዚህ ሲገናኙ ያስደስቷቸዋል

ዳዊትን ያህል መዝሙር ጨለማን ያህል ጥቁር
- አይገኝም አይኖርም

ዳገት እርሙ ሜዳ ወንድሙ
- የሚከብድን ሥራ እየሸሸ ቀለል ያለውን ይሠራል

ዳገት ለወዳጁ አይሰንፍ ሀብታም ካለወዳጅ አይተርፍ
- ሁሉም ወዳጁን ያጠብቃል

ድሃ ሲቀልጥ አመድ አመድ ይሸታል
- ወዝ የሚገኘው ከሚመገቡት ነው

ድሃ ሲቀመጥ እጁን ይዘህ አወዛውዘው
- በእጁ የያዛትን ትንሿን እንዲያራግፍልህ

ድሃ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል
- እጉል ቅንጦት ለከፋ ችግር ይዳርጋል

ድሃ ሲቆጣ እግሩ ይፈናጠራል
- ድሃ ሲከፋው የተሻለ ይሆናል ወደሚለው እግሩን አንስቶ ይሔዳል

ድሃ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል መንገዱን ያስልጣል
- ድሃ ችግር ሲደርስበት ወደሌላው መንገዱን ይቀይሳል

ድሃ ሲናገር ሬት ኮሶ ሀብታም ሲናገር የማር በሶ
- ያለው ማማሩ

ድሃ ሲንቀባረር ያለቀለ ይመስላል
- የማታውቅበትን የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሺ ቢሏት ወጼት ተመልሳ

ድሃ ሲያገኝ ያጣ አይመስለውም
- ምኝ የፊቱን ብልህ ያመቱን

ድሃ ቅቤ ወዶ ማን ሲሸከም ነዶ
- ድሃ ጌትነት ከፈለገ ሥራውን ማን ይሥራ

ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ ይወርሰው ነበር
- በእውን የማይገኘውን ምኞች በሕልም

ድሃ በጉልበቱ ባለጸጋ በሀብቱ
- ሀብታም በገንዘቡ ደሃ በጉልበቱ

ድሃ ቢናገር አያደምቅ ቢጨብጥ አያጠብቅ
- ለው አክብሮት ያለው ሳለው እንጂ ለድሃው አይደለም

ድሃ ባይ ዐይኔን አመመኝ
- አጉል መመጻደቅ

ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ
- ባለመሬት በበደለ ጭሰኛ ይክሳል

ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ሀብታም በድሎ መልሶ ይሥቃል
- መሔጃ ማኩረፊያ ስለሌለው ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል

ድሃና እመቤት እልፍኝና ማድቤት
- ሁሉም እንደደረጃው

ድሃና ጌታ ተሟግቶ ቅልና ድንጋይ ተማቶ የማይሆን ነው ከቶ
- አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች

ድሃን ምን ትሠራለህ እንጂ ምን ትበላለህ የሚለው የለም
- የድሃን ጉልበት የማይመኝ የለም

ድሃን ቢያስለቅሱ ከሥላሴ ይወቅሱ መንግሥተ ሰማያት አይወርሱ
- ለድሃ ማዘን መመጽወት ትሩፋትን ያስገኛል

ድሃ ከርሻ ዳቦዬን ለማጎሻ
- ሀብታም እርሻውን የሚያሳርሰው በድሃ ነው

ድሃ ከንቡ ይዳራ
- ድሃ ከመሰሉ ጋር ይፋቀራል

ድሃ ካለቀሰ ቀኑ መች አነሰ
- ድሃ ሲከፋው ሌሊትና ቀን ያለቅሳል

ድሃ ካልጣረ ዶሮ ካልጫረ ማን ያበላው ነበረ
- ድሃ ጥሮ ግሮ ካልሠራ ማንም አያበላውም

ድሃ ውኃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ሀብታም ስለገንዘቡ ይጨነቃል
- የድሃ ነገር ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል

ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም
- ድሃ ለሆዱ ይሰስታል ግብር ክፈል ሲሉት ዘየትም አምጥቶ ይከፍላል



ድሃ ያልፍልኛል ይላል ጌታ ቀኑን ይቆጥራል
- ድሃ የሚኖረው በተስፋ ነው

ድሃ ያመልክት ዳኛ ያሟግት
- የዳኛ ተግባር ከሳሽና ተከሳሽን ማሟገት ነው

ድሃን ፊርቼ ደጀን በቀን ዘግቼ
- ሁኔታው የሚያዛለቅ አይሆንም

ድሀነት ካምላክ መስማማት
- በምድር የተቸገሩ በላይኛው ቤት የተሻለ ሕይወት ያገኛሉ

ድል በመታደል ሙያ በመጋደል
- የአንድ ሙያ ባለቤት ለመሆን ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል

ድል ዕድል በአንድ ድልድል
- ድል ወይም አሸናፊነት አንዳንዴ የሚገኘው በአጋጣሚ ነው

ድል የባለ ዕድል
- አሸናፊነት በለስ ሲቀና ነው

ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ
- ዓመለኛ ሰው ዓመሉን አይተውም

ድመት በታች ከሆነች ውሻን ታሸንፋለች
- ለድል የያዙት ቦታ ወሳኝነት አለው

ድመትና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ባዶ ቦታ ድምጽ ያስተጋባል

ድመትና አይጥ እሳትና ጭድ
- አይስማሙ

ድመትን በቆሎ መጠርጠር
- የማይሆንና የማይታመን ነገር

ድመትን አይጥ ገደለቻት ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት
- ጉልበተኛውን አቅመቢስ ጉዳው ሲባል ለጆሮም ይከብዳል

ድምቢጥ እንደአቅሟ በብር ትታገማለች
- ሁሉም እንዳቅሙና እንደሁኔታው ራሱን ይንከባከባል

ድምጽና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ባዶ ቦታ ድምጽ ያስተጋባል

ድሪቶ ከነቅማሉ መጥፎ ሰው ከነዓመሉ ወዲያ በሉ
- የማይሆንን ሰው አለማስጠጋት ነው

ድሪያ የዝሙት ዋንጫ
- የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
- ካንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ

ድርብርብ እንደደጋ ንብ
- በቦታና በሁኔታ ልዩ ባሕርይን ማመልከት

ድርና ማግ ለሐጭና ልጋግ
- የሚቀራረቡና አብረው የሚኖሩ

ድርጐ ራቱ ድርጐ ቢቀር ሞቱ
- የሰው እጅ ማየት የለመደ ምንጊዜም ያንን ዓመሉን አይተውም

ድርጐ የለመደች መበለት ወተት ያየች ድመት
- ለለመዱት ነገር መንሰፍሰፍ

ድርጭት ፈንጠር ምዝግዝግ ጐንደር
- የእያንዳንዱ ባሕርይና አካሔድ መለየቱ

ድሮ ካያታችን ካጤ ነው ትውልዳችን
- የንጉስ ሐረግ ዘር አለን ለማለት

ድበላ አንዳንድ ጊዜ ይበላ
- የማከማቸቱ ነገር ሁልጊዜ አይሟላም

ድንቁርና ከልብሀ መካከል ተራራ ያህል
- ያለዐዋቂ ሰው ያስማወቁን አይረዳም

ድንቢጥ እንዳቅሟ በብዕር ትታገም
- ሁሉም እንደጊዜውና እንደአቅም ይወሰናል

ድንኳን ገልጦ ዘሩፋን ረግጦ
- ከአቅሙና ከችሎታው በላይ መዳፈር

ድንኳን ገልጦ ዙፋን ረግጦ
- ባለእቅምና ችሎታ ታማኝነትን መግለጥ

ድንገተኛ ስሕተት የቁልቁለት ውድቀት
- በድንገት የሚፈጠር ስሕተት ኃይለኛ አደጋ ያስከትላል

ድንጋይ ለረገጠ ፍለጋ የለውም ውኃ ለጠጣ ሽታ የለውም
- ድንጋይ የረገጠ ሰው ዱካው ሊገኝ ወይም ሊታይ አይችልም

ድንጋይ ላይ ተቀማጭ የባለጌ ተለጣጭ
- ያለአቅምና ያለችሎታ መንጠራራት

ድንጋይ ሲያረጅ መጭ ያበቅላል
- ሰው ሲያረጅ ባሕሪው ይበላሻል

ድንጋይ በድንጋይ ላይ ትልቅ ቤት ይሆናል
- በጥበብ ከያዙት ግዑዙ ነገር የሚያስከብር ሲሆን ይችላል

ድንጋይ ወርዶ እዘብጥ ያርፋል ያገኘው ይተርፋል
- ከሥልጣን ሲወርዱ ያው መገኛው ታች ነው

ድንጋይ ወደሰማይ ቢወረወር ተመልሶ ወደ ምድር
- አሞራ ውሎዋ ሰማይ አዳሯ ምድር

ድግርና ገባር ሲተካከል ያምር
- ሁሉ ነገር ሲስተካከል ሥርዓት ሲይዝ ያስደስታል

ድግስ የሌለው ዋዜማ ምልክት የሌለው ዜማ
- አንድ ነገር መነሻ ያስፈልገዋል

ድጥ ማንሸራተቱን ባለጌ ማሽሟጠጡን አይተውም
- ሰው ማማቱን አይተውም

ዶማ ለመማሻ ማረሻ ለመፈለሻ
- ሁሉም እንደየሥራ ባሕርዩ ሥራ ላይ ይውላል



ዶሮ ላትበላጡ ታፈስ
- ልምድ አይተውም

ዶሮ ልጆቿን ይዛ ጓሮ ለጓሮ
- ከጠላት መሸሸግ አስፈላጊ ነው

ዶሮ ሲሉ ሰምታ ሞተች ከጢስ ገብታ
- ሰው ያደረገው አይቅርብኝ የሚል ሰው እችግር ላይ ይወድቃል

ዶሮ በልቶ ከብሳና ጐመን በልቶ በጤና
- ጥሩ ነገር በልቶ ከመታመም የሚስማማን መመገብ

ዶሮ በልጇ አንጀት ትጫወታለች
- ልጇ እየራባት ቀምታ ትበላለች

ዶሮ በማሰሮ ገደል ለዝንጀሮ
- ለሁሉም ነገር ተስማሚ ዕቃ ተሠርቶለታል

ዶሮ በጋን
- ያልተመጣጠነ ነገር

ዶሮ ቢጠፋ ከቤቱ መነኮሰች እናቱ
- ከልክ በላይ ማቀማጠል ተገቢ አይደለም

ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት
- ለትንሽ ጉዳይ ከፍተኛ ገንዘብ ማውጣት

ዶሮና ቀበሮ ተገናኝተው ጓሮ
- ፈላጊና ተፈላጊ ሲገናኝ

ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

ዶሮን ቢያማት በሬ ተሳሉላት
- ለጥቂት ነገር ብዙ ወጪ ማድረግ

ዶሮ አንዱን እንቁላል በወለደችበት ወታቦ ትሞላለች
- አንድ ቦታ ከለመደች ያለዚያ ቦታ አትወልድም

ዶሮ እኔ ባልበላው ጭሬ አላፈስም ወይ አለች
- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

ዶሮ ከቆጥ በሬ ከጋጥ
- ሁሉም ሠርቶ የሚያርፍበት ምቹ ቦታ ሊኖረው ይገባል

ዶሮ ከቤት ውላ ዝናብ ይመታታል
- ተጠንቅቀው ውለው በትንሽ ስሕተት ችግር ላይ ይወድቃሉ

ዶሮ ከጋጥ አህያ ከቆጥ
- የተገላቢጦሽ የማይስመስል ነገር

ዶሮ ከጮኸ ሌሊት ከደብረታቦር ወዲያ ክረምት የለም
- ከደብረታቦር በዓል በኋላ ክረምት የለም

ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ከቡሄ ወዲያ የለም ክረምት
- ትክክለኛ ነገር

ዶሮ ካልበሏት አሞራ ናት
- ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ

ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች

- የቀበጠ ዕለት ሞት አይገኝም

ዶሮ ጭራ የምታወጣው ሚስጥር

- የምትደብቀውን ነገር ማራቅ

ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ

- በማያገባህ ጉዳይ መግባት ችግር ላይ ይጥላል

ዶክተሮች ሲበዙ በሽተኛው ይሞታል

- ሴት ሲበዛ ጉመን ጠነዛ



## መልመጃ 14 /ደ/

ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ዳኛ ይመረምራል ________
   ሀ. ጣዝማ ይሰረስራል ለ. ጣዝማ ይፈውሳል
   ሐ. ፍርድ ያስተካክላል መ. ምስክር ይመሰክራል
2. ________ ማሩኝ ይላል
   ሀ. ድሃ ተበድሎ ለ. ጻድቅ
   ሐ. እግዜርን በድሎ መ. ወታደር በድሎ
3. ደሞዝ ያጣ ሎሌ ________ በሐምሌ
   ሀ. ቀጠሮ ይይዛል ለ. ይኮበልላል
   ሐ. ይከሳል ሰዳኛ መ. መልሱ የለም
4. ደሞዝተኛ ________ አትተኛ
   ሀ. አርፈህ ለ. እንቅልፍ ሐ. ቀን መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ደመና የጨበጠ ________ የቧጠጠ የሰም
   ሀ. እንበሳን ለ. ሴትን ሐ. ነብርን መ. ሰማይን
6. ደም ቢያለቅሱ ______ቢነክሱ
   ሀ. ልጅን ለ. ጥርስን ሐ. ድንጋይ መ. ጠጠር
7. ደም ካልፈሰሰ ______ የለም
   ሀ. ነፃነት ለ. ጦርነት ሐ. ስርየት መ. መልሱ የለም
8. ደም ተበከሰህ ______ አትጥላ
   ሀ. ወዳጅህን ለ. ሌባን ሐ. ቆሻሻን መ. ዝንብ
9. ደም ________ ይቀጥናል
   ሀ. ከውኃ ለ. ከዘይት ሐ. ከቤንዚን መ. ሁሉም መልስ ነው
10. ደረቴን ቢያመኝ ________ አገመኝ
    ሀ. ቁርጭምጭሚቴን ለ. እግሬን
    ሐ. እጄን መ. ሁሉም መልስ ነው
11. ድሃ ________ ይዳራ
    ሀ. ከሚስቱ ለ. ከጋሰሞታ
    ሐ. ከንቡ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
12. ድሃ ያመልክት ________ ያሟግት
    ሀ. ጉረቤት ለ. ዳኛ
    ሐ. ሽማግሌ መ. ሁሉም መልስ ነው
13. ድንጋይ ላይ ተቀማጭ ________ ተሰጣጭ
    ሀ. የባለጌ ለ. የሀብታም ሐ. የድሃ መ. የስነፍ

ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች

- የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም

ዶሮ ጭራ የምታወጣው ሚስጥር

- የምትደብቀውን ነገር ማራቅ

ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ

- በማያገባህ ጉዳይ መግባት ችግር ላይ ይጥላል

ዶክተሮች ሲበዙ በሽተኛው ይሞታል

- ሌት ሲበዛ ጉመን ጠነዛ



## መልመጃ 14 /ደ/

ሀ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ</u>

1. ዳኛ ይመረምራል ________
   ሀ. ጣዝማ ይሰረስራል   ለ. ጣዝማ ይፈውሳል
   ሐ. ፍርድ ያስተካክላል   መ. ምስክር ይመሰክራል
2. ________ ማሩኝ ይላል
   ሀ. ድሃ ተበድሎ   ለ. ጻድቅ
   ሐ. እግዜርን በድሎ   መ. ወታደር በድሎ
3. ደሞዝ ያጣ ሎሌ ________ በሐምሌ
   ሀ. ቀጠሮ ይይዛል   ለ. ይኮበልላል
   ሐ. ይከሳል ለዳኛ   መ. መልሱ የለም
4. ደሞዝተኛ ________ አትተኛ
   ሀ. አርፈህ ለ. እንቅልፍ ሐ. ቀን መ. ሁሉም መልስ ነው
5. ደመና የጨበጠ ________ የቧጠጠ የለም
   ሀ. አንበሳን ለ. ሴትን ሐ. ነብርን መ. ሰማይን
6. ደም ቢያለቅሱ ______ ቢነክሱ
   ሀ. ልጅን ለ. ጥርስን ሐ. ድንጋይ መ. ጠጠር
7. ደም ካልፈሰሰ ______ የለም
   ሀ. ነፃነት ለ. ጦርነት ሐ. ሰርየት መ. መልሱ የለም
8. ደም ተበክሰህ ______ አትጥላ
   ሀ. ወዳጅህን ለ. ሌባን ሐ. ቆሻሻን መ. ዝንብ
9. ደም ________ ይቀጥናል
   ሀ. ከውኃ ለ. ከዘይት ሐ. ከቤንዚን መ. ሁሉም መልስ ነው
10. ደረቴን ቢያመኝ ________ አገመኝ
    ሀ. ቁርጭምጭሚቴን   ለ. እግሬን
    ሐ. እጄን   መ. ሁሉም መልስ ነው
11. ድሃ ________ ይዳራ
    ሀ. ከሚስቱ   ለ. ከጋለሞታ
    ሐ. ከንቡ   መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
12. ድሃ ያመልክት ________ ያሟግት
    ሀ. ጉረቤት   ለ. ዳኛ
    ሐ. ሽማግሌ   መ. ሁሉም መልስ ነው
13. ድንጋይ ላይ ተቀማጭ ________ ተለጣጭ
    ሀ. የባሉጌ ለ. የሀብታም ሐ. የድሃ መ. የስነፍ

14. ዶሮ ________ትጫወታለች
ሀ. በልጇ ለ. በትሎች
ሐ. በልጇ አንጀት መ. መልሱ የለም

15. ዶሮ ________
ሀ. በጋን ለ. በሸክላ ድስት
ሐ. በብረት ድስት መ. ሁሉም መልስ ነው

16. ደገኛ ሲያርስ ________ ያነፍስ
ሀ. ወሬኛ ለ. ባላገር ሐ. ቆለኛ መ. ገበሬ

17. ደግ ሳይበላ ________ ይመራ
ሀ. ቆንጆ ለ. ባለጌ ሐ. ክፉ መ. ሞኝ

18. ደግና ማለፊያ ________ ልፊያ
ሀ. ጥፊና ለ. ቦክስና ሐ. ትግልና መ. ሁሉም መልስ ነው

19. ደግ ጉረቤት ________ እያስገዛም
ሀ. ክር ለ. ገመድ ሐ. ዕቃ መ. መልሱ የለም

20. ደግ ጉረቤት ________ ያሳድጋል
ሀ. ውሻና ድመት ለ. ፍየልና ዶሮ
ሐ. በግና ላም መ. ሁሉም መልስ ነው

21. ደፋር ________ ያውቃል
ሀ. ሸክላ ለ. ልብ ሐ. ወጥ መ. ገበያ

22. ዱላ ለባለጌ ________ ለአሮጌ
ሀ. ክራንች ለ. ምርኩዝ ሐ. ዳቦ መ. እንጀራ

23. ዶሮ ________ ታፈስ
ሀ. ከትሪ ለ. ከእንቅብ ሐ. ሳትበላው መ. መልሱ የለም

24. ዶሮ ከቆጥ ________ ከጋጥ
ሀ. በሬ ለ. ቆቅ ሐ. ጅግራ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

25. ዶማ ለመማሻ ________ ለመፈለሻ
ሀ. ማረሻ ለ. ዲጅኖ ሐ. ዶማ መ. መልሱ የለም

26. ዶሮ ብትታመም ________ አረዱላት
ሀ. ጫጩት ለ. በግ ሐ. አህያ መ. ሁሉም መልስ ነው

27. ዶሮ ቢጠፋ ከቤቱ ________ እናቱ
ሀ. አለቀለች ለ. ተናደደች
ሐ. መነከለች መ. አታለለችው

28. ዶሮ በማለሮ________ ለዝንጀሮ
ሀ. ሜዳ ለ. ሥጋ ሐ. ጥሬ መ. ገደል



29. ዶሮና ቀበሮ ________
ሀ. ተገናኝተው ጓሮ ለ. ተያይዘው ጫካ
ሐ. ተያይዘው ገደል መ. መልሱ የለም

30. ደግ ጉረቤት ________
ሀ. ያስገዛል ዕቃ ለ. ያወጣል ከመአት
ሐ. አያስገዛም መ. መልሱ የለም

31. ዱባ ባገሩ ________ ያህላል አሉ
ሀ. ጋን ለ. ዳቦ ሐ. እንስራ መ. ሁሉም መልስ ነው

32. ዲያቆን ከዘፈነ ________ ከቀዘነ
ሀ. ልጅ ለ. ከብት ሐ. ፍየል መ. ጅብ

33. ዳሩ ሲፈታ ________ ዳር ይሆናል
ሀ. መሀሉ ለ. ዘመድ ሐ. ባዳ መ. መልሱ የለም

34. ዳቦ በገና ________
ሀ. ሻይ በጀበና ለ. ቡና በፔርሙስ
ሐ. ቡና በጀበና መ. ሁሉም መልስ ነው

35. ዳቦ ያለቅርፊት ________ ያለምርጊት
ሀ. ጠላ ለ. ጭቃ ሐ. አሸዋ መ. መልሱ የለም

36. ዳተኛ በሬ ________
ሀ. ድሃ ነው ለ. ሀብታም ነው
ሐ. ጉልበታም ነው መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

37. ዳኛ ምን ያደላ ________
ሀ. ከረታው ሊበላ ለ. ከጠበቃ ሊበላ
ሐ. ከተረታው ሲበላ መ. መልሱ የለም

38. ዳኛ ሁን ________
ሀ. እንደኛ ለ. ለመፍረድ ሐ. ክመሳቀቅ መ. መልሱ የለም

39. ዳኛ ቢንቁ ________
ሀ. እሳቶ ላይ ይወድቁ ለ. ከገደል ይወድቁ
ሐ. ከመከራ ይወድቁ መ. ሁሉም መልስ ነው

40. ዳኛ ቢያጉድል ________
ሀ. በዳኛ ለ. በንጉሥ ሐ. በሽማግሌ መ. ሁሉም መልስ ነው

41. ዳክዬ ከውኃው ________
ሀ. ጥጃ ከጋጥ ለ. ዶሮ ከጋጥ
ሐ. ፈረስ ከገለባው መ. ጅብ ከዋሻው

42. ዳኛ ያደላበት ________
ሀ. ሆዳም የበላበት ለ. ሞኝ የበላበት
ሐ. እሳት የበላበት መ. ሁሉም መልስ ነው

43. ድሃ ሲቆጣ ________
ሀ. ሚስቱን ይደበልባል ለ. እግሩ ይፈናጠራል
ሐ. እግሩ ያነክሳል መ. መልሱ የለም

44. ድሃ ሲንቀባረር _____ ይመስላል
ሀ. ያለቀለ ለ. የተከሳተረ ሐ. ያበደ መ. ያረጀ

45. ድሃ ባይ __________
ሀ. አዘንኩኝ ለ. ድህነቴን ረሳሁ
ሐ. ዐይኔን እመመኝ መ. መልሱ የለም

46. ድርጕ ራቱ ________ ቢቀር ሞቱ
ሀ. ዱላ ለ. ውኃ ሐ. ድርጕ መ. ዳቦ

47. ድንቢጥ እንደእቅሟ _______ ትታገማለች
ሀ. በብር ለ. በወኜሻ ሐ. በወርቅ መ. በነሐስ

48. ድምፅና ቁንጫ ______ ይወዳል
ሀ. ቪላ ቤት ለ. ባዶ ቤት
ሐ. ክርካሳ ቤት መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

49. ድሮ ካያታችን ______ ትውልዳችን
ሀ. ወሳሞ ነው ለ. ቅይጥ ነው
ሐ. ካጤ ነው መ. ከአባት ነው

50. ድንገተኛ ስሕተት ________ ውድቀት
ሀ. እጉል ለ. የቁልቁለት ሐ. የዳገት መ. ሁሉም መልስ ነው

ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ
ሀ. ሌባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል
ለ. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
ሐ. የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ
መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

2. ድንጋይ ቢያጕኑት ተመልሶ ባናት
ሀ. የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ በራሴ
ለ. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሰው ባፉ
ሐ. ባጕረስኩ እጄን ተነከስኩ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

3. ደባ ራሱን ስለት ድግሱን
ሀ. እሥር ያባረረ አንድ አይዝም
ለ. እጅግም ስለት ይቀዳል እፎት
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም



4. ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ አይድንም
ሀ. የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ
ለ. ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ
ሐ. የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አያርፍም
መ. ሁሉም መልስ ነው

5. ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ
ሀ. በግ ባልበላሽ ትበይኝ
ለ. አህያ ወደ ጅብ ለቅሶ ሄደች
ሐ. እሳት ቢተኛ ገለባን ለደድ ጕበኘው
መ. ሁሉም መልስ ነው

6. ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን
ሀ. በቅሎ ለኮዋን በጠለች በራሷ አሳጠረች
ለ. ራስ ሳይጠና ጉተና
ሐ. ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው
መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

7. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
ሀ. ጥርስና ከነፈር ተደጋግፎ ያምር
ለ. የሳጭን ልጅ ቅማል በላው
ሐ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
መ. መልሱ የለም

8. ደመና ለዝናብ ድግስ ለሆዳም
ሀ. ሆዳም ድግስ አይቶ አይመለስም
ለ. ከደመነ ይዘንባል
ሐ. በግ ባልበላሽ ትበይኝ
መ. መልሱ የለም

9. ደስታና መከራ ቀኝና ግራ
ሀ. መከራ ቀኝና ግራ ይሆናል
ለ. ተፈራራቂ ናቸው
ሐ. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
መ. መልሱ የለም

10. ደግ ሰው ከእንጀራው ቆርሶ ከወጡ እጥቅሶ
ሀ. ደግ ሰው ለደግነቱ ወደር አይገኝለትም
ለ. ደግ ጕረቤት ዕቃ አያስገዛም
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

## ሐ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. ድንጋይ ወደ ሰማይ ቢወረወር ተመልሶ ወደምድር | ሀ. ዓመለኛ ዓመሉን አይተውም |
| 2. ድንጋይ ሲያረጅ መጭ ያበቅላል | ለ. ከባለቀትር አትቀታተር |
| 3. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር | ሐ. ያባይን ልጅ ውኃ ጠማው |
| 4. ድመት መንኩሳ ዓመሏን አትረሳ | መ. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል |
| 5. ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት | ሠ. ቢያጥቡት ይነጣል ቢመረምሩት ይወጣል |
| 6. ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጁ | ረ. አጉል ቅንጦት ለከፋ ችግር ይዳርጋል |
| 7. ዳኛ ገንዘቡን ተቀማ | ሰ. አሞራ ውሎዋ ሰማይ አዳሯ ምድር |
| 8. ድሃ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል | ሸ. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ |
| 9. ድሃና ጌታ ተሟግቶ ቅልና ድንጋይ ተማቶ የማይሆን ነው ከቶ | ቀ. ያለው ማማሩ |
| 10. ድሪያ የዝሙት ዋዜማ | በ. መተባበር ኃይል ነው |
| 11. ድሃ ሲናገር ሬት ኮሶ ሀብታም ሲናገር የማር በሶ | ተ. ባለመሬት በበደለ ጭሰኛ ይከሳል |
| 12. ዳኛ ይመረምራል ጣዝማ ይሰረሰራል | ቸ. አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች |
| 13. ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ | ኀ. ካንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ |
| 14. ድሃ ሲያገኝ ያጣ አይመስለውም | ነ. የዘፈን ዳር ዳሩ አስክስታነው |
| 15. ዳኛ ሲኖር ተናገር ውኃ ሲጠራ ተሻገር | ኘ. ምኝ የለቱን ብልሀ ያመቱን |
| 16. ዱቄት በአመድ ይሥቃል | አ. አዬ ሌላ ወዬ ሌላ |
| 17. ዱባና ቅል አበቃቀሉ አንድ ይመስላል አበላሉ ለየቅል | ከ. ዳኛሲኖር ተናገር ውኃ ሲጉድል ተሻገር |
| 18. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር | ኸ. አንዱ በአንዱ ሲሥቅ ጀንበር ጥልቅ አለ |
| 19. ድሃ ባይ ዐይኔን አመመኝ | ወ. አጉል መመጻደቅ |
| 20. ዶሮ እኔ ባልበላው ጭሬ አላፈስም ወይ አለች | ዘ. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ |



## ጀ

ጀማሪ ይጥፋ ስካራም ይትፋ
- ራስን ዐውቆና በአቅም ያልተደረገ ነገር ጉዳት አለው

ጀምሮ የማይፈጽም ፈጭቶ የማያልም
- ጀምሮ ይጨርሳል አልሞ ይተኩሳል

ጀምሮ ይጨርሳል ለጉም ይተኩሳል
- ጀምሮ ይጨርሳል አልሞ ይተኩሳል

ጀምበር ሳለ ሩጥ አባት ሳለ አጊጥ
- ጊዜ ሳያልፍብህ ሥራበት

ጀርባ ለባለቤቱ ባዕድ ነው
- ከኋላ የሚባለውን ባለቤት አይሰማም

ጀርባው ከብዶታል
- ብዙ ቤተሰብና ንብረት አለው

ጀርባዬን አሳከከኝ ተንጠራርቼ ማከክ ተሳነኝ
- ልተወው የማልችለው ችግር ገጠመኝ

ጀርባዬን አከከኝ ለእኔ እራቀኝ
- በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዲደርስ በሌላ ሰው ማስፈጸም

ጀግናን ከደረቱ አበባን ከእናቱ
- ልበሙሉን ሰው ከአኳኋኑ ያውቁታል

ጀግና የሚታወሰው ወይም ከሞተ ወይም ከተለየ በኋላ ነው
- ሰው ካልሞተና ካልተለየ አይመስገንም ጥሩ ጐኑ አይታየንም

ጃርት ያስደነገጠው ዱባ ይመስላል
- አኳኋኑ ሁሉ የሚያስጠላ እዚህም እዚያም የተቦተራረፈ

ጆምርን ለነገ አያሳዩም
- የዛሬን ለዛሬ የነገን ነገ ያውቃል

ጆምር ይጨረሳል ልጉም ይተከሳል
- ሥራን ለነገ ብሎ ማስቀመጥ ጥሩ አይደለም ሥራን ከሥር ከሥሩ መሥራት ነው

ጆራትና ጉድ ወደ ኋላ ነው
- ጆራትና ሐሜት ከበስተኋላ ነው

ጆራቷን ታደርሳለች ካናቷ
- ችግሯን ለሌሎች አሷን ለመስሉት ታደርሳለች

ጆራፍ መቶ ያለቅሳል ባለጸጋ በድሎ ተመልሶ ይወቅሳል
- የባለጸጋ አዕምሮ በገንዘብ ሰክሯል አጥፍቶ ያጠፋ አይመስለውም

ጆራፍ እሱው ይገርፍ እሱው ይለፍ
- እራሱ በድሎ ተበዳይ ይመስላል

ጆብ ምን ይመስላል? እግሩ ያነከሳል አፉ ይነከሳል
- ጆብ የ "ምን" ቅርጽ ይይዛል ለማለት

ጆብ ሲበላህ በልተኸው ተቀደስ
- ከመቀደም መቅደም

ጅብ ባጥንት የተገደገደ በጅማት የተማገረ ቤት አለ ቢሉት ወዴት ነው ሳይል ገደል ገብቶ ሞተ
- የጅብን ሆዳምነት ያመለክታል

ጅብና ሽማኔ ከጉድጓድ አይወጡም
- ከጉድጓድ የሚውሉበት ሁለቱም ምክንያት አሏቸው

ጅብና እህል ሳይተዋወቁ ይኖራሉ
- ጅብ የእህልን ጣፋጭነት ባለማወቁ እህልን አልፎ ምግብ ፍለጋ ይዞራል

ጅብን ለመግደል ከአህያ ተጠለል
- ጠላትን ለመግደል በዘዴ ተጠቀም

ጅብን ከምን መታኸው ከአፉ አለፋሁለት
- ባልቻገረው መቻገር

ጅብን ፈርቼ ከዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ
- ከአንደኛው ሳመልጥ ሌላ ችግር ደግሞ ገጠመኝ

ጅብ አጥንት ባየበት ይመላለሳል
- የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

ጅብ አማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል
- ስደት ለወሬ ያመቻል

ጅብ አለኪነክሰ ያነክስ
- የፈለከውን ነገር እስከታገኝ መታገስ አስፈላጊው ነው

ጅብ እንኳን ጓደኛውን ይጣራል
- የተገኘውን ነገር ከጓደኛ ተካፍሎ መብላት ጥሩ ነው

ጅብ እንደቁመቱ ልብ የለውም
- ድፍረት በሰውነት ውፍረት አይለካም

ጅብ እንደአባቱ ይዘርጥጥ
- ልጁ የአባቱን ባሕርይ ወረሰ

ጅብ እንደአባቱ ይዘርጥጥ አህያ እንደአባቱ ይፈርጥጥ
- ልጁ የአባቱን ባሕርይ ወረሰ

ጅብ እንደአገሩ ይጮሃል የደላው ሙቅ ያኝካል
- ሁሉም ነገር የሚከናወነው እንደአካባቢው ነው

ጅብ እንደጉልበቱ ልብ የለውም
- ድፍረት በጉልበት አይለካም

ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ
- ላለፈው ነገር መቆጨት አያስፈልግም

ጅብ ከላይ ውኃ ሲጠጣ ከታች ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ አለ
- አለቃነቱን ሲያሳውቅ

ጅብ ከሚበላህ ጅብ በልተህ ተቀደስ
- ከመቀደም መቅደም

ጅብ ካኮተኮተ ሰው ከተከተ
- ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ

ጅብ የኔ ነው ስለው ወናፌን ቀማኝ
- የተማመንኩበት ሰው እራሱ በደለኝ



ጅብ ጥጃቹን ጠብቅ ቢባል ይጠፉብኛል አለ
- ስደት ለወሬ ያመቻል

ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው
- ሰው ለለእሱ የሚወራበትን ነገር ፈጽሞ አያውቀውም

ጆሮ በላ ሆድ ጦሙን አደረ
- የሰሙት መልካም ነገር ምግብ አይሆን

ጆሮ ባይጠም ይመስላል ሆዳም
- ጆሮ ያገኘውን ሁሉ አያግበለብስም

ጆሮ አይጠምም ዓይን አይጠግብም
- ዓይን የሚያየው ጆሮ የማይሰማው የለ

ጆሮ ዕዳውን አይሰማም
- ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው

ጆሮ ካያቱ ያረጃል
- ጆሮ የጥንት ታሪክን ሁሉ ይሰማል

ጆሮውን ቢቆርጡት መስሚያው ይቀራል
- ዋናው ነገር ከተነሳ ዋናነቱ ይቀራል

ጆሮውን አለው
- በጥፊ መታው፣ ሸጠው

ጆሮ የሰማውን ለማየት ዓይን ይንከራተት
- ፍላጐት ሲቀሰቀስ ፍላጐትን ለማሟላት ጥረት ይደረጋል

ጆሮ የሰማውን ልብ ያውቃል
- የማስተዋልና የመገንዘብ ሁኔታዎች

ጆሮ የቀድሞዎቹ እኩያ ነው
- አብረውት ከተፈጠሩት ጋር በዕድሜ እኩያ ነው

ጆሮ ዳባ ልበስ አለ
- ጉዳዩን አልሰማሁም አለ

## ገ

ገለፈንት የሌት ጋለሞታ
- ጋለሞታ በሆነው ባልሆነው የምትሥቅ ናት

ገላጋይ አጥቼ ግልገሌን በላኋት
- መካሪ አጥቼ ማጥፋት የሌለብኝን ነገር አጠፋሁ

ገልቱ ቢመከር አይዘክር
- ገልቱ ሰው ቢመከርም ምክሩን አያስታውስም አይጠቀምበትም

ገልፋጣ የሴት ጋለሞታ
- ጋለሞታ በሆነው ባልሆን ትገለፍጣለች

ገመድ ሲበጠስ መቀጠል አባይ መስካሪ ገደል
- ዋሾን ሰው መቅጣት ያስፈልጋል

ገረመኝ የማላውቀው ሰው ቢስመኝ
- የት አውቅሽ ብሎ አጥብቆ ሳመኝ

ገረድ የቤት ሞረድ
- ገረድ የቤቱን ዕቃ ትፈጀዋለች

ገራገሩን ተጫውቶ ይኖራል ተስማምቶ
- ላይ ላዩን እየተጫወቱ መኖር ያስማማል

ገርነት የእግዜር ቸርነት
- ገርነትን እግዚአብሔር የሚወደው ባሕርይ ነው

ገርነት ያገባል ገነት
- ገርነት መንግሥተሰማያት ያስወርሳል

ገርና ልል ሙዳይና አገልግል
- በሁለቱ መካከል ብዙ ልዩነት የለም

ገርን ልጅ እናቱም አትወደው
- ማንም ቢሆን ለመብቱ መታገል አለበት

ገርገሩን ተጫውቶ ይበሏል ተስማምቶ
- ወደውስጥ ሳይገቡ ላይ ላዩን በመጨዋወት በስምምነት መኖር ይቻላል

ገበሬና ወላድ አንድ አያጣም
- ወላድ ከብዙ ልጆች አንድ ሁነኛ ልጅ አታጣም

ገበሬ አቆጣጥረኝ ወታደር አወራውረኝ
- ገበሬ ቤተዘመዱን ሲሸኝ ከየአህል ዓይነቱ ቆጣጥሮ በመስጠት ነው

ገበሬ አክባሪውን ባለጌ መካሪውን ይጠላል
- ገበሬ የሚያከብረውን ይጠላል

ገበያ ቢመቻት ልጇን ሸጠቻት
- መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል

ገበያ ነሽ ብለው ይሻሻጡብሻል
- አንድ ፍሬ ነሽ ግን እንደትልቅ ተቆጠርሽ /ንቀትን ለመግለጽ/

ገበያ እንደሰጠህ እንጂ እናትህ እንደላከችህ አይሆንም
- ገበያ ሲሰጥ በርካሽ ይሸመታል

ገበያ እንዴት ዋለ? ቢለው እንዱ ባንዱ ሢሥቅ
- ሸማች በሻጭ ላይ ሻጭ ደግሞ በሸማች

ገበያ ከደራ ነጋዴም አይፈራ
- ገበያው ሞቅ ካለ ነጋዴ ዋጋውን ለቀቅ ያደርጋል

ገበያ የሚሰጥህን እናት አትሰጥም
- ከንግድ ብዙ ጥቅም ይገኛል

ገበጣ ላዋቂ ወሬ ለጠያቂ
- ካልጠየክ ልታውቅ አትችልም

ገበጣ ላዋቂ ወሬ ለጠያቂ ዋዛ ፈዛዛ ከሣቂ
- ዋዛ ፈዛዛ የሚያበዛ ሰው ከችግር ላይ ይወድቃል

ገቢ በእናት ልጅ ትገቢ
- ነገረኛ ሰው እናትና ልጅን ከማጋደል አይመለስም

ገቢውን ባለቤት ያውቃል
- ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው



ገቢ ያፈርሳል ቀዳዳ ያፈሳል
- ነገረኛ ሰው ለውና ለው ያጣላል

ገባር ያህያ ግንባር
- ገባር ለባለመሬቱ እንደአህያ ግልጋሎት ይሰጣል

ገባ ወጣ ነገር ያመጣ
- ገባ ወጣ ማለት አንዳች ጣጣ ያመጣል

ገብርኤል ያየው ሚስጥር
- በታቦት ስም የተደረገ ነገር ምስጢርነቱ ከባድ ነው

ገብስ ሲበስል አባቱን ይመስል
- ያልዘሩት አይበቅል

ገብስና ሸንኩርት ቂጡ ሲለብስ ነው
- የተፈለገው ነገር በተፈለገው መጠንና ሁኔታ ካልተገኘ አያስደስትም

ገብስና ገብስ አብሮ ይነፍስ
- ብጤ ከቢጤው ነው

ገናም በሙከቱ ሑዳዴ በእልበቱ ይታወቃል
- ሁሉም እንደጊዜውና እንደወቅቱ ይከናወናል

ገናና ጥምቀት እኩል ዓውደ ዓመት
- ገናና ጥምቀትም ያው ዓመት በዓል ናቸው

ገና ዘንቦ ባርቶ
- ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ

ገንዘቡ የሰው ቢሆን አዳዩ የኔ ይሁን
- አዳዩ የኔ ወገን ከሆነ ማግኘቱ አይቀርም

ገንዘቤ አትውጪ ከቤት ታጣይኛለሽ ከጉረቤት
- ገንዘብ ለማይመልስ ተው አታበድር ያቀያይማል

ገንዘብ ለዕዳ ሙግት ለባዳ
- ሙግት አለብኝ ከማለት ሥራ አለኝ ማለት ይበልጣል

ገንዘብ ማግኘቱ ይቀላል ከማከማቸቱ
- ገንዘብን በአግባቡ ማውጣትና የተረፈውን በአግባቡ መቆጠብ ይከብዳል

ገንዘብ በልጅነት ማን ለብስቦሽ በእርጅና ማን አግኝቶሽ
- ገንዘብ የሚገኝ በሃያ ዓመት ልብ የሚገኘው በአርባ ዓመት

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ያመጣል ጣጣ
- ገንዘብን ቢያበድሩት ያለአንዳች ችግር አይመለስም

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ይመጣል ይዞ ጣጣ
- አንዴ ከእጅ ከወጣ ለማስመለስ አስቸጋሪ ይሆናል

ገንዘብ ከጅ ዘመድ ከደጅ
- ገንዘብ ካለህ ዘመድህ ብዙ ነው

ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ
- ሀብት ያለው የፈለገውን ማድረግ ይችላል

ገንዘብ የልብ ሥር ነው አጥፊውም ሰው ነው
- ገንዘብ በሕይወት ውስጥ ወሳኝ ስፍራ አለው

ገንዘብ የሚገኝ በሃያ ዓመት ልብ የሚገኝ በአርባ ዓመት
- ድሃና ገበያ ሳይገናኙ ይኖራሉ
ገንዘብ የጠፋበት ብዙ ኃጢያት አለበት
- እገሌ አገሊት ወስዳብኝ ይሆናል በሚል
ገንዘብ ያልያዘ መንገደኛ አይፈራም ቀማኛ
- የበለበለ ዝናብ አይፈራም
ገንፎ ለጉንፋን ይበጃል እግረመንገዱንም ለሆድ ይበጃል
- ገንፎ ለጉንፋን ደግ ነው እግረመንገዱ ሰመብልም ጥሩ ነው
ገንፎ ማላመጥ በእግዜር ማልመጥ
- የደላው ሙቅ ያኝካል
ገንፎ ሠርታ ለራት ቢያጉርሳት ተኮሳት
- እንቺው ታመጪው እንቺው ታሮጪው
ገንፎ ሲበሉ ልጅ አስወግዶ ጠላ ሲጠጡ እሳት አንድዶ
- ለራስ ያሰቡት ነገር አፍጣጭ ገላማጭ በሌለበት ይከውኗል
ገንፎ በድስት ጐመን በምንቸት
- ለእያንዳንዱ ተግባር የሚያመቹ የተለያዩ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ይኖራሉ
ገንፎ እፍ እፍ ቢሉሽ ሲውጡሽ ነው እውነት አይምሰልሽ
- የሚያባብሉሽ ሊጠግቡሽ ነው
ገዘቶ የማይቆጣ አጥቦ የማያነጣ
- ሕዝብን በማስተዳደር ሒደት ውስጥ የሚያበሳጩ አጋጣሚዎች አይታጡም
ገደል ለዝንጀሮ ጉድጓድ ለቀበሮ
- ሰሁሉም እንደተፈጥሮው ባሕርይውና ልማዱ መሠረት
ገዳም የገባ አይወጣ ከል የገባ አይነጣ
- አንዱ ቆርጦ ለነፍሱ ያደረ ወደ ዓለማዊ ተግባር አይመለሰም
ገዳዩ ከጥይቱ ሥጋ ከብልቱ
- ማንኛውም ሥራ ሲከናወን በሥርዓት በሥርዓት መሆን አለበት
ገዳይ ሳይገኝ ጉሮ ወሸባዬ
- ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ
ገዳይ ቢያረፍድ ሟች ይገሠግሣል
- ሁን ያለው መች ይቀርና
ገዴ ገድሽ ለኔ ሥጋሽ ላረመኔ
- ለእኔ ሁኚልኝ እንጂ ከዚያ ወዲያ አንቺ እንደፍጥርጥርሽ
ገድለው ካላመለጡ ምንድነው ጌጡ
- ዓላማው ግብ ካልመታ ድካሙ ሰምንድነው
ገድሎ ነበር ሞተ
- የእጁን አገኘ
ገድሎ ካለቃዬ ከሶ ከጠበቃዬ
- አጥፍቶ ጥፋቱን ለመሸፋፈን መሞከር



ገጣባ አህያ ትለለቻለች ጭና ታበላለች
- አልፎ አልፎ ጠልተኸው የነበረ ሰው ያገለግልሃል
ገጣጣ ሲሞት የሣቀ ይመስላል
- በአንዳንድ ሁኔታዎች አሰመሞኘት
ጉልበት አለኝ የበላ ምላስ አለኝ የለላ
- በጉልበቴ ብቻ ሳይሆን በምላሴም ሰውን የማሳመን ችሎታ አለኝ
ጉልበት አለኝ የዝሆን አፍ አለኝ ላንተ የሚሆን
- በጉልበት ብቻ ሳይሆን ነገሮኝ የማሳመን ችሎታ አለኝ
ጉልበት አለኝ የዝሆን አፍ አለኝ የመኮንን
- በጉልበት ብቻ ሳይሆን ነገሮኝ የማሳመን ችሎታ አለኝ
ጉልበት የሌለው ወንበዴ ትርፍ የሌለው ነጋዴ
- ሥራ ለመሥራት ጉልበት አስፈላጊ ነው
ጉልበት የሌላት ወይዘሮ ገደል የሌለው ዝንጀሮ
- ጉልበት ከሌላት ሥራ መሥራት አትችልም
ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም
- የሰዎች መለዋወጥ ሥራውን አይለውጠውም ስለዚህ ጠንክረን እንሥራ
ጉልቻ የሳቀው አመድ ያጠለቀው
- ድሃ ሰው የደኸየ
ጉልቻ የሳቀኝ አመድ ያጠለቀኝ አለአማኑኤል ማን ጠየቀኝ
- የደኸየሁ ጊዜ አለእግዚአብሔር ማን ደረሰልኝ
ጉም መግመጥ ውኃ መግመጥ
- የአንድን ነገር ውስጣዊ ሁኔታ ወይም ዝምድናን ማወቅ
ጉም ሲለቅ የታባትህ ትገባ አንተ ሌባ
- በአንዱ ተመክተህ ስትኖር የተመካህበት ሰው ከዚያ ቦታ ሲነሳ ምን ይውጥሃል
ጉም ተራራን ያለብሳል ሹም ለሹም ያወርሳል
- ሹም ሹመቱን ለሹም ቢያወርስ ተራራውን እንዳለበሰው ጉምነው ዘላቂነት የለውም
ጉሬዛ ቢውል ከጠጣ ጥፋት ለምዶ መጣ
- ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ መጣች
ጉሮሮ የሚውጠውን እጅ ይመጥነዋል
- በልክ የሆነ ነገር ጥሩ ነው
ጉቦና ሌባ በር አይወድም
- ጉቦ የሚሰጠው በስውር ነው
ጉቦኛ የባለ መጋኛ
- የሰው ገንዘብ ፈላጊ እንደክፉ በሽታ ይታያል
ጉቦ የለመደ ዳኛ አህያ የለመደ ጅብ አንድ ነው
- ጉቦኛ ሰው ሆዳም ነው አያመዛዝንም
ጉትቻ ለጆሮ ትንሽ ትመስላለች ዛፍ ጐበዝ ትቆጥራለች
- ምንም ቢሆን ጐበዛዝት እንጂ ለነፍ ዛፍ አይቆርጥም

ጉትቻ ለጆሮ እልፍኝ ለወይዘሮ
- ሴት ቤትን ታሳምራለች

ጉትቻ ለጆሮ ጥሬ ለዶሮ
- ሁሉም ነገር እንደተፈላጊነቱ ይሠራል

ጉንዳን ባልንጀራው ሲሞት ብቻውን ተሸክሞ ይዞራል
- ለገቢህ ተንገብገብ

ጉንዳን ቤቱን ይመራል
- ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

ጉንዳን እስኪወጣብኝ ተኛሁ
- ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ

ጉንዳን የባልንጀራው ሬሳ ብቻውን ያነሳ
- ጠንካራና ቆራጥን ከሆንክ ከባድ የሆነን ሥራ ለብቻህ ትሠራዋለህ

ጉንዳን ያየህ እመድ
- ችግርን ለመቅረፍ መረባረብ

ጉንፋን የተያዘና ፍየል ይዞ የተደበቀ ሳይጋለጥ አይቀርም
- ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት

ጉንፋን ሲያንድዱት በሽታ ይሆናል
- ቀለል ያለ በሽታ ካካበዱት ጥሩ አይሆንም

ጉደኛ ውሻ ሥጋ ተቀምጦ ቆሎ ትሻ
- ጥሩ ነገር እያለ ሌላ ትንሽ ነገር መመኘት አይገባም

ጉዳት ከመጣ መካር አይታጣ
- ይሁንም አይሁንም ሰው የሚለው አያጣም

ጉዳት የደረሰበት እረኛ አረጭ አያባርርም
- የተጐዳ ሰው ቀላል ሥራ እንኳን መሥራት ይቸገራል

ጉዳይ ሳይኖርህ ገበያ አትውረድ ያንዱን ነገር ሰምተህ አትፍረድ
- የአንድ ሰው ነገር አዳምጠህ ውሳኔ መስጠት ስሕተት ላይ ይጥላል

ጉዳይ አሳልፍ እንድትታማ እሮጌ ሁን ልትፎክር ሙት ልትመሰገን
- የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር

ጉዳይ የሌለህ ገበያ አትውረድ ያንዱን ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ
- ያለጉዳይ ወዲያ ወዲህ አትበል

ጉድ ለባለቤቱ ልግም በገላ ነው
- ሰው እራሱ የሚሠራው ነገር ጥሩ ይመስለዋል ነውሩ አይታየውም

ጉድ ለባለቤቱ የአንገት ልብስ ነው
- ሰው ነውሩ አይታየውም

ጉድሽ ድንቅሽ ናብለሽ ወዴት ሔድሽ
- ትገርሚያለሽ

ጉድነሽ ያንኮበር ቅጠል እያደረ ትለበልቢያለሽ
- ታስገርሚያለሽ

ጉድ ነገር አበድሮ መቸገር
- ሳይሞላህ ማበደር ችግር ላይ ይጥላል



ጉድና ብርቅ እስከ ሦስት ቀን ያስጨንቅ
- ጉድ አንድ ሰሞን ነው

ጉድና ድንቅ አለ አንድ ጊዜም አይደምቅ
- ጉድ አንድ ሰሞን ነው

ጉድና ድንቅ አንድ ሰሞን ነው
- ለጊዜው ነው ካለፈ በኋላ ይረሳል

ጉድና ጅራት በስተኋላ ነው
- ቆይቶ ቆይቶ ነው ጉዱ የሚወጣው

ጉድ እንግዳ ነገር አሳድሮ መቸገር
- አስቸጋሪ ነገር ምንጊዜም አስቸጋሪ ነው

ጉድ ይገርማል ጅብ ካህያ ጋር እንዴት ይከርማል
- አጥፊና ጠፊ አብረው የሚኖሩት ጊዜ ቢኖር ያስደንቃል

ጉድ ጉድ ምን ያንተ ጉድ እየው የእኔንም ጉድ
- የኔም የባሰ ነገር አለ

ጉድጓድ በራሱ ዐፈር አይሞላም
- በአንድ እጅ አይጨበጨብም

ጉጉት ብትጠቃ እርከሟ ሆነች ጠበቃ
- የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ

ጉፋያ ሲበሉ ስብ ይቀላቅሉ
- አብሮ የሚያካሔድ ነገር ማፈላለግ

ጉፋያ ሲነዱ ይሽከሙ
- ሁኔታን ግልጽ ሳለማውጣት የሚደረግ ጥረት

ጉፋያን ሲበሉ ሰብ ይቀላውጡ
- ጥሩ ነገር ተመልክቶ ጥሩ ያልሆነውን መብላት

ጉፋያ ከመብላት ስብ መሸከም ይሻላል
- የማይረባ ነገር ከመብላት ጥሩ ነገር ማየቱ ይሻላል

ጉፋያ ከሚያርዱ ሰብ ይቀላውጡ
- የተበላሸ ነገር ከሚሠሩ ጥሩ ነገር መቀላወጥ ይሻላል

ጊዜ ሲከዳ መሬቱ ያድጣል
- የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል

ጊዜ እስኪያልፍ ያባቴ ባሪያ ይግዛኝ
- እስኪያልፍ ያለፋል

ጊዜ ወርቅ ነው ግን ኃላፊ ነው
- በጊዜህ ተጠቀምበት

ጊዜ የሌለው የለም ግን ከዕድሉ የሚያልፍ የለም
- ሁሉም በጊዜው ያገኛል ቢባልም ዕድል ደግሞ ከፍና ዝቅ ያደርጋል

ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል
- ባለጊዜ የሆነ ሰው የፈለገውን ማድረግ ይችላል

ጊዜ የሰጣት እይጥ ከፈረሰኛ እኩል ትሮጣለች
- ባለጊዜ የሆነ ሰው የፈለገውን ማድረግ ይችላል

ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅ
- ያለው ሰው ጊዜን አይናፍቅም

ጋለሞታና ጌታ ደጅ የጠኑ ለታ
- ችግሩ እየጠና ለመምጣቱ ምልክት ነው

ጋራና ገባ ቅልና ዱባ
- ቀልቀሎ ስልቻ ስልቻ ቀልቀሎ

ጋሽ ለግንባር ጫማ ለጠጠር
- ለቦታውና ለሁኔታው በሚያመች መንገድ

ጋሽና ውጊያ እንዴት ነው ቢለው ጋሽ ወርውሮ ጦር መመከት ነው አለው
- የማያውቀውን ነገር ዘባረቀ

ጋሽና ግምባር አይሸሽግም
- ፊትለፊት የሚታይ ነገር አይደበቅም

ጋሽ እሰጥ ጋሽ እሰጥ ሲሉ ጦር ገባ
- ወታደሩ ሳይደራጅ ጠላት ገባ

ጋሽ ዱሮ ቀረሽ
- የጥንቱ የተሻለ ነበር

ጋን ሠሪ ምጣድ አይወጣለትም
- የማያውቁትን ነገር መሥራት ያስቸግራል

ጋን ሲለቀለቅ ማድጋን ይሞላል
- ከትልቁ ፊት የሚነሳው የበታቹን ያጠግበዋል

ጋን ሲያሟጥጡት ምንቸት ይሞላል
- የግመል መጫኛ ቢበጠስ ለአህያ ይበቃል

ጋን በጠጠር ይደገፋል
- ትናንሽ ነገሮች አይናቁም ይጠቅማሉና

ጋን ቢያንጫልጡት ማሰሮ ይሞላል
- የግመል መጫኛ ቢበጠስ ለአህያ ይበቃል

ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
- የበላይ ወደታች የበታቾች ደግሞ የበላይ ሆኑ

ጋይ የለ እሸት ስጡኝ አለ
- በቅሎ ሳይገዙ ኮርቻ

ጋጋሪ ያስበላል ተናጋሪ ያስመበላል
- ከብዙ ወሬ ትንሽ ተግባር ይበልጣል

ጌታ ሁን እንዳሻህ ሁን
- እንደፈቀድክ ሁን ሀብታም ሁን

ጌታ ለሎሌው ነጋዴ ላሞሌው
- ሁሉም ለሚያገኝበት ነገር ይጠነቀቃል

ጌታ ሲሰጥ ማን ይከለክላል
- ጌታ ካዘዘ ማንም አይከለክልም

ጌታ ሲወድ ማን ይጠላል ጌታ ሲሰጥ ማን ይከለክላል
- ያለው ቢሰጥ ማን አለበት



ጌታ ቢጫወት ያልኮራ ይመስላል
- ሰው ምንም ቢሆን ክብሩን መጠበቁ አይቀርም

ጌታ ባወቀው ይፈርዳል ሰው ባላወቀው ይጐዳል
- በመጥፎ አጋጣሚ ሰው ባላሰበው ሊጐዳ ይችላል

ጌታና ሎሌ ተጣልተው ዱባና ቅል ተማተው ኸረ አይመስልም ተው
- የማይመስል ነገር

ጌታና ሎሌ ተጣልቶ ቅልና ድንጋይ ተማቶ
- ማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ

ጌታና ገበታ አቅራቢ ነው ሰጭው እግዜር ነው
- ለሁሉም የእለት እንጀራ ሰጪ እግዚአብሔር ሲሆን ሰው ምክንያት ነው

ጌታና ጋለሞታ ደጅ የጠኑ ለታ
- ማንኛውም ነገር ለማግኘት ማክበር አለብህ

ጌታዋን የምታምን ውሻ ፍሪዳ ሲታረድ እወንዝ ወረደች
- ጌታዋን ያመነች በግ ላትዋን እውጭ ታሳድራለች

ጌታዋን የምትወድ ላም በመስከረም ትወልዳለች
- በመስከረም በቂ ሣር ስላለ እሷም ተጠቅማ ባለቤቷንም ትጠቅማለች

ጌታዋን ያመነች በግ ላትዋን እውጭ ታሳድራለች
- አስተማማኝ ክሆነ ያለስጋት ማከናወን ይቻላል

ጌታውን ያየ አሽከር ይጥላል በትግል
- ሞራሉ መንፈሱ ስለሚነቃቃ ሊያሸንፍ ይችላል

ጌታ ያዛል ውኃ ያንጻል
- የሥራ ስልትና ዕቅድ በማውጣት ኃላፊ ሥራ ይመራል

ጌታ ያዛል ውኃ ይለዛል
- በውኃ ውስጥ የገባ ጥሬ ይለዛል ከደህና ሰው ጋር የዋለ ጠባዩ ይገራል

ጌታዬ ምን አልኩህ? ጠጅ አጠጥተህ ውኃ
- አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ ለምን ታደርገኛለህ

ጌታዬ ካሉበት እግሙኝ
- አለቃዬ በሚሉት በሚሰጡት መመሪያ መሠረት መፈጸም አለብኝ

ጌቶች ወደውኛል ጨርቃቸው ነክቶኛል
- አጉል ምኞት የቀን ሕልም

ግልግልና ገንፎ ትኩሱን እያስገባም
- የችኮላ ነገር እያስተማምንም

ግመል ምን ተጭነሃል? ሽመል ምን ያወዛውዝሃል? ዐመል
- ሌባ ላመል ዳቦ ይልሳል

ግመል ሰርቆ አጐንብሶ
- የጐላ ስሕተት ፈጽሞ ለመሸሸግ አይቻልም

ግማሹን ተላጭታ ግማሹን ተቀብታ
- በሥርዓት ያልተሠራ ሥራ

ግማሽ ልጩ ግማሽ ጐፈሬ
- በሥርዓት ያልተሠራ ሥራ

ግም ለግም አብረህ አዝግም
- ባለጌ ከባለጌ ጋር ይውላል

ግረፍ ከባት አትለፍ
- በሥነ ሥርዓቱ ቅጣ

ግራ መብል ቀን ገንፎ ሌሊት ድፎ
- ማንኛውም ነገር ሥርዓት ከሌለው አይጥምም

ግራ መብል ቀን ገንፎ ሌሊት ዶሮ
- ማንኛውም ነገር ሥርዓት ከሌለው አይጥምም

ግራ ነገር ከወንዝ ማዶ ፍቅር ከጐረቤት ጥል
- ሁሉም ነገር አለቦታው ሲሆን አይጥምም

ግርግርታ የሌባ ደስታ
- ለሌባ ግርግር ያመቸዋል

ግባ ያለው ገንዘብ አጥር ቀዶ ይመጣል
- ሳንተ ያለው እንጀራ ይሻግታል እንጂ ማንም አይበላውም

ግብር እስከመቃብር
- የሰው ጠባይ እስከመቃብር አይለይም

ግብር ይውጣ የማይቀር ዕዳ
- መጥፎ ጠባይ ቢደብቁት የማይደብቅ ነው

ግብዝና መቼ እንደድቁና
- እንዲህ ቀላል አይምስልህ

ግብዝን ሁለት ጊዜ እባብ ነክሰው
- ሲመክሩት የማይሰማ አደጋ ይገጥመዋል

ግንብና ድንጋይ ጌታና አባይ
- አባይ ሎሌ በጌታው ዘንድ የተናቀ ነው

ግንቦት ቢዳምን የሚዘንብ ይመስላል አሮጌ ቢፎክር የሚዋጋ ይመስላል
- ሁሉም ያለጊዜው የሚሆን አይደለም

ግንቦት ቢዳምን ይዘንብ ይመስላል ሐምሌ ቢያባራ በጋ ይመስል
- ወቅቱንና ጊዜውን ሁኔታዎችን እያዩ አይዘነጉም

ግንድ ለሺ አይከብድ
- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አስበኝ
- ጥሩ ባስብለት መጥፎ ነገር አስበብኝ

ግዳይ ለክንፈሬ ጥምጣም ለመምሬ
- ሁሉም መለያ የሚሆነው ምልክት ይኖረዋል

ግዳይ እምሯቸው ዘመቱ እሳቸውም ሞቱ
- የሚያምር ነገር መመኘት ለአደጋ ያጋልጣል

ግፈኛ የሰይጣን መልዕክተኛ
- ግፈኛ ሰው ሰይጣን የተጠጋው ነው



ግፍ ሲቆም ጸሎት አያሻም
- ሁኔታዎች ሲለወጡ የነበረው ጭንቀት ይዘነጋል

ግፍስ በባሕር ይሞላል ዓሣ ዓሣውን ይበላል
- በደል ሲበረክት ሰው በሰው ላይ ይነሳሳል

ግፍ ባገር ሲናኝ ኩበት ጠልቆ ድንጋይ ይዋኝ
- የሁኔታዎች መለዋወጥ

ግፍ አይፈሬ መሬት እንክርዳድ ያበቅላል
- ሚስትህ ወሰደች ወይ ቢለው ማንን ወንድ ብላ አለው አሉ

ግፍ የተሠራብን በኛ ካሱ ይሉናል በዳኛ
- ገበሬ እሱው ተበድሎ እሱው ይከሳል

ጐልማሳ በሚሥቱ ንጉሥ በሠራዊቱ
- ምንም ቢሆን ጐልማሳ በሚስቱ መቅናቱ አይቀሬ ነው

ጐልማሳ ሲታጠቅ ከደረቱ ሲሮጥ ከጉልበቱ
- ጐልማሳ ጉልበት ብቻ ሳይሆን ልብም አለው

ጐልማሳ እበቀለበት ሳም አይማረክም ሽማግሌ እበቀለበት ነገር ሊይሳሳትም
- ጐልማሳ ካለበት ስፈር ላይ ምንም አይስረቅም

ጐልማሳ ካለበት ከብት አይነጠቅ ሽማግሌ ከዋለበት ነገር አይወድቅ
- ሽማግሌ በሰፈሩ ካለ ነገር አይገንም ቶሎ ስለሚያስታርቅ

ጐመን በጤና
- ነገር አልፈልግም ቶሎ ልሒድ

ጐመን ባወጣው ነፍስ አትኩራ ገብስ
- እንዱ በሠራው እንተ አትኩራ

ጐረምሳ እንደበላህ አንሳ
- በጉልበትህ ሥራበት

ጐረቤት አያውቅ ነገር ወንጠፍት አያጠራው እሳር
- ጐረቤት የማያውቀው ምስጢር የለም

ጐረቤት ይሆናል ጠላት ያቺን ሴት አትዝጊ በሏት
- የሚሆነው አይታወቅምና ተጠንቅቀህ ተራመድ

ጐረቤት ጤና ይደር አንተ ጤና እንድታድር
- የጐረቤት ሰላም ሳንተ ሰላም ጥሩ ነው

ጐራዴህ ጐመዳም ሚስትህ አመዳም
- ትዳርህ ጥሩ አይደለም

ጐራዴ ለወንበዴ ሱቅ ለነጋዴ
- ሁሉም ነገር እንደጠቃሚነቱ ተጠቀምበት

ጐራዴና ምስጥ ውስጥ ለውስጥ
- ተንኮለኛ ሰው ውስጥ ውስጡን ነው

ጐርፍ ሲወስድ እያሣሣቀ ተንኮለኛ ሲጐዳ እየተራቀቀ
- ተንኮለኛ ሰው ሲጐዳ እያስመሰለ ነው

ጐሽ ለልጇ ብላ ትወጋ
- እናት ለልጇ ስትል ራሷን ታስጨንቃለች

ጉሽ ጠመድኩ ይሆነኛል ብዬ ፈትቼ ስደድኩ አይሆንም ብዬ
- የሚሆን መስሎኝ አደረኩ ሳይሆን ሲቀር አባረርኩ

ጉበዝ ፊት ሰማይ ሰማይ ያያል ኋላ ምድር ምድር ያያል
- ያስመሳዮች ባሕርይ መሆኑ ነው

ጉባጣን ሲቀብሩ እንደ ምግባሩ
- ሰውን እንደ ዐመሉ መያዝ ይገባል

ጉባጣን ቀንና ቅዝምዝምን አጉንብሰህ እለፈው
- የችግርን ጊዜ በትዕግስት አሳልፈው

ጉኑ ቀኜ ቀኑ ለኔ
- ደካማ ሰው ስለሆንኩ ችግሩን ልቋቋም አልቻልኩም

ጉንደሬ ሲናገር እንኳን ሸዋ ጉጃሜም አይሰማው
- የጉንደሬን ንግግርን ጉረቤቱም አያውቀውም

ጉንደር ወጣ ምን ይዞ መጣ
- ጉንደር ሔደህ ምን ይዘህ ተመለስክ

ጉዳናና መንገድ ጉንጉንና ገመድ
- ብዙ ባለመራራቅ ይመሳሰላሉ

ጉዳ ከብት ከቀንዳም ይብሳል
- አንዳንድ ጭምት ሰው ከተናደደ አያድርስ ነው

ጉዳው ፍየል ቀንዳሙን ወጋው
- ይሆናል ተብሎ ያልተጠረጠረው ተፈጸመ

ጉድሎ ነበር ሞላ ሞልቶ ነበር ፈላ
- አጥቼ ነበር አሁን ከልክ በላይ አገኘሁ

ጉጃም ሲያምጥ በጌምድርን በፍልጥ
- እህያውን ፈርተው ዳውላውን

ጉጃም በዘነበ ሳይንት እህል ሆነ
- የማይመስል ነገር

ጉጆ ወጪ ሙሽራ በገፍ ወጥ ትሠራ
- ልምድ የሌለው ሰው መመጠን አይችልም

ጓያና ድንግል ያላንድ ጊዜ አይበቅል
- ዕድል አንድ ነች አንዴ ካለፈች ተመልሳ አትገኝም



## መልመጃ 15 /ገ/

**ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ**

1. ግም ለግም ________
   ሀ. አብረህ አዝግም ለ. አይከፋው ዘላለም
   ሐ. አያስቀምጥ አያስቆም መ. በሥራ ይለግም

2. ግዛኝ ብለው ________
   ሀ. ለመሸጥ አሰበኝ ለ. ሸጠኝ
   ሐ. ወረቴን ቀማኝ መ. ለመንጠቅ አሰበኝ

3. ______ ድንጋይ ይሰብራል
   ሀ. ጊዜ የሰጠው ጥጥ ለ. ጊዜ የሰጠው እንቁላል
   ሐ. ጊዜ የሰጠው ሙዝ መ. ጊዜ የሰጠው ቅል

4. ጌታና ____ ደጅ የጠኑለት
   ሀ. ሎሌ ለ. ጋለሞታ ሐ. ሚስት መ. ጉረቤት

5. ጌታ ያዛል _____ ይሰዛል
   ሀ. ቆሎ ለ. ቡና ሐ. ውኃ መ. አሻሮ

6. ግልገልና ገንፎ _____ አያስገባም
   ሀ. ትኩሉን ለ. ቀዝቃዛውን
   ሐ. ለብ ያለ መ. መልሱ የሰም

7. ጉመን ______
   ሀ. በአገር ለ. በጤና ሐ. ለመጉረስ መ. መልሱ የለም

8. ጉመን ባወጣው ነፍስ _____
   ሀ. አትኩራ ለሳጣ ለ. አትኩራ ሥንዴ
   ሐ. አትኩራ ድንች መ. አትኩራ ገብስ

9. ጉራዴህ ጉመዳም _________ አመዳም
   ሀ. ልጅህ ለ. ሚስትህ ሐ. እህትህ መ. መልሱ የለም

10. ጉራዴና ምስጥ __________
    ሀ. አብሮ ያዝግም ለ. ጉን ለጉን
    ሐ. ውስጥ ለውስጥ መ. ፊትፊት

11. ጉጃም ሲያምጥ __________
    ሀ. በጌምድር በፍልጥ ለ. ጋሞጉፋ በጠመንጃ
    ሐ. ባሌ በሽጉጥ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

12. ጉዳው ፍየል ______
    ሀ. በጉን ወጋው ለ. ላሟን ወጋት
    ሐ. ቀንዳሙን ወጋው መ. መልሱ የለም

13. ጉሽም በዘነበ ______
ሀ. ሐረር ጫት በጫት ሆነ ለ. ሳይንት እህል ሆነ
ሐ. ጋሞ ጉፋ እህል በቀለ መ. ሁሉም መልስ ነው

14. ገጣጣ ሲሞት ______ ይመስላል
ሀ. ያለቀሰ ለ. የሣቀ
ሐ. ያረገደ መ. መልስ የለም

15. ጉልበት እለኝ የበላ ______ እለኝ የሰላ
ሀ. ቢላ ለ. ጉራዴ
ሐ. ምላስ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

16. ገጣባ እህያ ትለለቻለች ______ ታበላለች
ሀ. ጤፍ ለ. ጭና ሐ. ዳቦ መ. እርሳ

17. ጉልቻ ቢለዋወጥ ______
ሀ. እርፎ አይቀመጥም ለ. ወጥ አያጣፍጥም
ሐ. ደስ አይልም መ. መልስ የለም

18. ጉም መግመጥ ______
ሀ. ዳቦ መግመጥ ለ. ቂጣ መግመጥ
ሐ. ውኃ መግመጥ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

19. ጉበኛ ______ መጋኛ
ሀ. የባለ ለ. መታው
ሐ. አጣፋው መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

20. ጉበና ሌባ ______ አይወድም
ሀ. በር ለ. መስኮት ሐ. ኪስ መ. ዘመድ

21. ጉትቻ ለጆሮ ______
ሀ. ኩሽና ለወይዘሮ ለ. ምግብ ለወይዘሮ
ሐ. እልፍኝ ለወይዘሮ መ. መልስ የለም

22. ገልቱ ቢመከር ______
ሀ. አይዘክር ለ. አይስማማ ሐ. ይፎክር መ. ያቅራራ

23. ገርነት ______ ቸርነት
ሀ. የሰይጣን ለ. የጠንቋይ ሐ. የእግዜር መ. የተፈጥሮ

24. ገረድ ______ ሞረድ
ሀ. የኩሽና ለ. የቤት ሐ. የብረት መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

25. ______ የሴት ጋለሞታ
ሀ. ደደብ ለ. ባላገር ሐ. ገልፋጣ መ. ገጣጣ

26. ገርነት ______
ሀ. የእግዜር ቸርነት ለ. ያገባል ገነት
ሐ. ቸርነት መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ



27. ገርና ልል ______ አገልግል
ሀ. ሙዳይና ለ. እንጀራና
ሐ. ፍትፍትና መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

28. ገበሬና ወላድ ______ አያጣም
ሀ. ጤፍ ለ. ዘር
ሐ. እንድ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

29. ገርን ልጅ ______
ሀ. ሚስቱም አትወደውም ለ. እህቱም አትወደውም
ሐ. ጓደኛው አትወደውም መ. እናቱም አትወደውም

30. ገብያ ቢመቻት ______
ሀ. ልጇን ሸጠቻት ለ. እህቷን ሸጠቻት
ሐ. ከብቷን ሸጠቻት መ. ሁሉም መልስ ነው

31. ገበያ ከደራ ______
ሀ. ሌባም አይፈራ ለ. ነጋዴም አይፈራ
ሐ. ባለቤት አይፈራ መ. መልስ የለም

32. ገበጣ ላዋቂ ______
ሀ. ወሬ ላሳባቂ ለ. ወሬ ለጠያቂ
ሐ. በሽተኛ ለጠያቂ መ. ወሬ ለደራ

33. ጉም ሲለቅ ______ ትገባ
ሀ. ፀሐይ ለ. የታባሀ ሐ. አገርሀ መ. ጓደኛ ቤት

34. ጉንዳን ______
ሀ. ቤቱን ይመራል ለ. ከቤት ያባርራል
ሐ. እጥንት ይሰብራል መ. መልሱ የለም

35. ጉንዳን የባልንጀራውን ______
ሀ. እጥንት ያነሳ ለ. ሬሳ ብቻውን ያነሳ
ሐ. ምግብ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

36. ጉደኛ ውሻ ሥጋ ተቀምጦ ______
ሀ. ዳቦ ትሻ ለ. እጥንት ትሻ
ሐ. ቆሎ ትሻ መ. መልስ የለም

37. ጉዳት ከመጣ ______
ሀ. ሞት አይታጣ ለ. መካር አይታጣ
ሐ. ደፋሪ አይታጣ መ. በሽታ አይታጣ

38. ጉጀ ወጪ ሙሽራ ______ ትሠራ
ሀ. ዶሮ ወጥ ለ. ሥጋ ወጥ ሐ. ሽሮ ወጥ መ.በገፍ ወጥ

39. ጌታውን ያየ ______ ይጥላል በትግል
ሀ. ውሻ ለ. በግ ሐ. አሽከር መ. ፈረስ

40. ጌቶች ወደውኛል ________
ሀ. ይንከባከቡኛል ለ. ይሰድቡኛል
ሐ. ያበሻቅጡኛል መ. ጨርቃቸው ነክቶኛል

41. ግርግርታ ________ደስታ
ሀ. ለሌባ ለ. ለሙሽራ ሐ. ለልጅ መ. ለጉረቤት

42. ግማሽ ልጨ ______
ሀ. ግማሽ ሽሩባ ለ. ግማሽ ጉፈሬ
ሐ. ሙሉ ሽሩባ መ. መልሱ የለም

43. ግባ ያለው ገንዘብ ________ ይመጣል
ሀ. አጥር ቀዶ ለ. ባዶ እጁን ሐ. ተገፍቶ መ. እየሮጠ

44. ግራ መብል ________ ሌሊት ዶሮ
ሀ. ቀን ሽሮ ለ. ቀን ቆሎ ሐ. ቀን ገንፎ መ. ቀን ዳቦ

45. ግረፍ ______
ሀ. ከባት አትለፍ ለ. ከጀርባ አትለፍ
ሐ. ከጭንቅላት አትለፍ መ. መልሱ የለም

46. ግብር ______
ሀ. እስከ ዕቁብ ቤት ለ. እስከ መቃብር
ሐ. እስከ ዳር ድንበር መ. መልሱ የለም

47. ግብዝን _____ ነከሰው
ሀ. አንድ ጊዜ እባብ ለ. ሁለት ጊዜ እባብ
ሐ. ሁለት ጊዜ ጉንዳን መ. ሁለት ጊዜ ንብ

48. ግንብና ድንጋይ _____
ሀ. ጌታና አባይ ለ. ጌታና ሎሌ
ሐ. ድሃና ገንዘብ መ. ተማሪና ደብተራ

49. ______ ጥምጣም ለመምሬ
ሀ. ግንድ ለቆራጭ ለ. ግብዝ ለከንፈሬ
ሐ. ግዳይ ለከንፈሬ መ. መልሱ የለም

50. ግዳይ አምሯቸው ዘመቱ ________
ሀ. እሳቸውም ተማረኩ ለ. እባቸውም ማረኩ
ሐ. እሳቸውም ተመቱ መ. እሳቸውም ሞቱ



ለ. <u>ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. ግመል ሰርቆ አጎንብሶ
   - ሀ. ግመል ከሰረቁ በኋላ አጎንብሶ መሔድ
   - ለ. ግመል ሲሰርቅ ያጎነብሳል
   - ሐ. ትልቅ ጥፋት ሠርቶ መሸሸግ አዳጋች ነው
   - መ. ትልቅ ሌባ አጎንብሶ ይሰርቃል

2. ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
   - ሀ. ወርካ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል
   - ለ. ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል
   - ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   - መ. መልሱ የለም

3. ገረድ የቤት ሞረድ
   - ሀ. ሌባን ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው
   - ለ. ገረድ የቤቱን ዕቃ ትፈጀዋለች
   - ሐ. ገረድ ለቤቷ ታበባለች
   - መ. መልሱ የለም

4. ገበያ የሚሰጥህን እናት አትሰጥም
   - ሀ. ከንግድ ብዙ ጥቅም ይገኛል
   - ለ. አንዳንድ እናት ቆንቋና ናት
   - ሐ. ገበያ ከእናት ይበልጣል
   - መ. መልሱ የለም

5. ጊዜ ሲከዳ መሬቱ ያድጣል
   - ሀ. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል
   - ለ. ሾላ በድፍን
   - ሐ. የጭቃ እሾህ
   - መ. ለአህያ ማር አይጥማትም

6. ጋን ቢያንጫልጡት ማሰሮ ይሞላል
   - ሀ. ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች
   - ለ. የግመል መጫኛ ቢበጠስ ለአህያ ይበቃል
   - ሐ. ያልተገላበጠ ያራል
   - መ. ሁሉም መልስ ነው

7. ጋይ የለ እሸት ለጡኝ አለ
   - ሀ. በቅሎ ሳይገዙ ኮርቻ
   - ለ. ሲሰሟት ቀርቶ ሲሰቧት
   - ሐ. የወገብ ቅማል
   - መ. ልጅቷ ንብ ናት

8. ግንድ ለሺ አይከብድ
   - ሀ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
   - ለ. መተባበር ኃይል ነው
   - ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   - መ. መልሱ የለም

9. ግራ ነገር ከወንዝ ማዶ ፍቅር ከጐረቤት ጥል
   - ሀ. ግራ መብል ቀን ገንፎ ሌሊት ዶሮ
   - ለ. ግራ መብል ቀን ገንፎ ሌሊት ድፎ
   - ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   - መ. መልሱ የለም

10. ግንቦት ቢዳምን የሚዘንብ ይመስላል እርጉዝ ቢፎክር የሚዋጋ ይመስላል
   - ሀ. ግንድ ለሺ አይከብድ
   - ለ. ግብር እስከ መቃብር
   - ሐ. ግንቦት ቢዳምን ይዘንባ ይመስላል ሐምሌ ቢያባራ በጋ ይመስላል
   - መ. መልሱ የለም



## ሐ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል | ሀ. ጌታዋን ያመነች በግ ላትዋን አውጥታ ታሳድራለች |
| 2. ጐጃም ሲያምጥ በጌምድር በፋልጥ | ለ. ጉድ አንድ ሰሞን ነው |
| 3. ጉንፋን የተያዘና ፍየል ይዞ የተደበቀ ሳይጋለጥ አይቀርም | ሐ. የማይሰመል ነገር ለሚስትህ አትንገር |
| 4. ጌታዋን የምታምን ውሻ ፍሪዳ ሲታረድ አወንዛ ወረደች | መ. የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል |
| 5. ግንድ ለሺ አይከብድ | ሠ. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን |
| 6. ጉዳይ አሳልፍ እንዳትታማ፣ እርጉዝ ሆን ልትፎክር፣ ሙት ልትመሰገን | ረ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር |
| 7. ጉድና ብርቅ እስከ ሦስት ቀን ያስጨንቅ | ሰ. ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት |
| 8. ጊዜ ሲከዳ መሬቱ ያድጣል | ሸ. ጊዜ ደካማውን ብርቱ ብርቱውን ደካማ ያደርጋል |
| 9. ጋን ሲያሚጥሉት ምንቸት ይሞላል | ቀ. እስኪያልፍ ያለፋል |
| 10. ጊዜ እስኪያልፍ ያባቱ ባሪያ ይግዛኝ | በ. የገመል መጫኛ ቢበጠስ ለአህያ ይበቃል |
| 11. ጋዩ የለ እሸት ስጡኝ አለ | ተ. በቅሎ ሳይገዙ ኮርቻ |
| 12. ጉሬዛ ቢውል ከጦጣ ጥፋት ለምዶ መጣ | ቸ. ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች |
| 13. ግባ ያለው ገንዘብ አጥር ቀዶ ይመጣል | ኀ. መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል |
| 14. ገበያ ቢመቻች ልጁን ሸጠቻት | ነ. ላንተ ያለው እንጀራ ይሻግታል እንጂ ማንም አይበላውም |
| 15. ገቢውን ባለቤት ያውቃል | ኘ. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው |

ጠላው ሳይገባ ማቶቱ፣ ቀንዱ ሳይገባ ጅራቱ
- የማይመስል ነገር ሥርዓቱን ያልጠበቀ ነገር

ጠላው የባዕድ አሳላፊው ዘመድ
- የራስ ባልሆነ ነገር ሽርጉድ አላስፈላጊ ነው

ጠላ ያለ አተላ ጠጅ ያለ አምቡላ
- ከሁሉም ነገር መጨረሻው ላይ ጥቂት መጥፎ ነገር አይጠፋም

ጠልቶ ለጠላት አስሮ ለእስራት
- ለከባድ ችግር አሳልፎ ሰጠኝ

ጠመንጃ ራሱ ገድሎ ራሱ ይጮሃል
- ራሱ ጉድቶ እንደተጉዳ ያስመስላል

ጠመንጃ ያለጥይት ዱላ ወንድ ያለ ሴት ቀውላላ
- ሁሉ ነገር አስፈላጊው ነገር ካልተሰተካከለለት ውጤት የለውም

ጠመንጃ ያለጥይት ዱላ ወንድ ያለ ሴት ድሃ
- ሁሉ ነገር አስፈላጊው ነገር ካልተስተካከለት ውጤት የለውም

ጠመደ ናበሬ ናዝሆን መቼም እንዳይሆን
- የማይመስል ነገር

ጠማማ ዛፍ በጊዜው ካልቀና አይስተካከልም
- ማንኛውም ሥራ በጊዜው ካልተሠራ ውጤት የለውም

ጠረፍ ያለ ባላንጣ ቤት ያለ ጣጣ
- አገር ያለ ዘብ አትቆምም

ጠርቦ ለደጁ ፈርዶ ለልጁ
- ሁሉም እንደአስፈላጊነቱ ይደረግለታል

ጠርጥር ከምግቡ ውስጥ አለ ስንጥር
- መጠራጠር አስፈላጊ ነው ጥንቃቄ ካላደረጉ ለአደጋ ይጋለጣሉ

ጠቃሚ ከእሪያ ይመጣል አጥፊ ከጉልበት ይወጣል
- ተጠቀም ካለህ ምክንያት ይፈልግልሃል

ጠቋሚ ጠቃሚ
- አንዳንዴ ለመጉዳት ብሎ የተደረገ ነገር ሲጠቅም ይችላል

ጠበቃ ታፈጀ በርበሬ ታረጀ
- አሮጌ ነገር እንደአዲስነቱ አያገለግልም

ጠበቃና ቅል ባጠገብ ይውላል
- ተከራካሪህ አጋርህ ስለሆነ ካጠገብህ አይጠፋም

ጠባ ለኪዳን መሸ ለቁርባን
- እለልቺ ኑሮ ለውጥ የሌለበት

ጠባቂ ያላት በግ ላቷን እደጅ ታሳድራለች
- መመኪያ ያለው ሁሉንም ነገር ያለፍርሃት ያከናውናል

ጠባብ አልጋ የግድ ያስተቃቅፋል
- በክፉ ጊዜ ሰዎች ይቀራረባሉ

ጠባይ ሲያረጅ ባሕርይ ይሆናል
- ማንኛውም ነገር አብሮ ሲቆይ ይላመዳል



## ጠ

ጠላ ሲሉት ሽምጥጥ ከሉ ሲሉት ስቅጥጥ
- ለሥራ ይሸሻል ለመብል ጊዜ ይሰጣል

ጠላ በማቶቱ እንጀራ በሌማቱ
- ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ነገር አለው

ጠላትህን ውኃ ሲወስደው እንትፍ ብለህ ጨምርበት
- ጠላትህ እየደከመ በሚሔድበት ጊዜ በይበልጥ እንዲደከመው አድርገው

ጠላትህን የምትጠነቀቀው አንድ ጊዜ ወዳጅህን የምትጠነቀቀው ሁልጊዜ
- ወዳጅ መስሎ ጠላት ለላለ ጥንቃቄ አስፈላጊ ነው

ጠላት ሲነሳብህ የወዳጆችህን ቁጥር አበርክት
- ብዙ ወዳጅ ካለህ ጠላት ይፈራሃል

ጠላት በጥርስ ሲገኝ እባክህ አታስጉምጀኝ
- ጠላት በእጅህ ላይ ሲወድቅ አትልቀቀው

ጠላት ቢያባብሉት ወዳጅ አይሆንም
- ጠላትን ምን ብትለማመጠው መልሶ ወዳጅ አይሆንም

ጠላት ባጭር ታጥቆ ዘገር ነጥቆ
- ከተደራጀህ የፈለከውን ነገር ማድረግ ትችላለህ

ጠላትን ለማግኘት ሲጉረጉሩ በወዳጅ ይጀምሩ
- አልፎ አልፎ ወዳጅ ጠላት ሲሆን ይችላል

ጠላትን በጦር አባትን መጦር
- ጠላትህን ማጥፋት አባትህን ደግሞ በስተርጅና መጦር ያስፈልጋል

ጠላት የሌለው ወዳጅ አያሻውም
- የሚያጠቃው ሰው የለም

ጠላት ይቀባል ጥላት
- ጠላትህ ስምህን ከማጥፋት ወደኋላ አይልም

ጠላና ወጥ ያነለው ደረቀ
- ጠላና ወጥ ቅመማ ቅመሞቹ ካልተሟሉ ጠላም ወጥም ሲሆኑ አይችሉም

ጠላና ዝና እለቱን አይደርስም
- የሚያኮራ ሥራ የሚሠራ ሰው ቀስ በቀስ ነው

ጠላና ጉተና እለቱን አይደርስም
- የሚያኮራ ሥራ የሚሠራ ሰው ቀስ በቀስ ነው

ጠላኝ ማለት ያስጠላል ልግደል ማለት ያስገድላል
- ክልብ አውጥቶ መናገር አያስፈልግም

ጠላ ሥር ነገር ካገር
- ጠላትን እስመጨረሻው ካላጠፉት እረፍት ይነሳል

ጠላ ካስከረው ወተት ያስከረው
- ጥጋብ ያስከረው መመለሻ የለውም

ጠብ ባለበት ቤት ዶሮ ትሞት
- ግርግር ለሌላ ሰው ዳፋ ነው

ጠብ ተጀመረ አንበሳ ላምን ሰበረ
- ጉበዝን ካናደዱት ጥሩ አይመጣም

ጠብ ተጀመረ ያ ልጅሽ አለ? ልጄ ሲል የነበረ
- ልጅን በሥነ ሥርዓት ማሳደግ ኋላ ከመጸጸት

ጠብ ካለበት ቤት ዶሮ ከቆጥ ትሞት
- ባንዱ ዳፋ አንዱ ተደፋ

ጠብ ያሻ መኮንን የዶሮ ሻኛ አምጡ ይላል
- ሊጣላ የፈለገ ሰው ሰበብ አያጣም

ጠንቋይ ለራሱ አያጠቅ መድኀኒቱ ላዋይ
- ለሌላው እየረዳ እራሱን መርዳት ግን አይችልም

ጠንቋይ ባያሳምን ያጠራጥር
- ጠንቋይ ትንሽም ቢሆን ያውቃል

ጠንቋይ አባይ ቤት ያስፈታል
- ውሸታም የሰውን ቤት ያበጣብጣል

ጠያቂ ባይኖር ሁሉ መምህር
- ዝናብ ባይኖር ሁሉም ቤት

ጠያቂ የለም እንጂ ከድሃ ምክር ይገኛል
- በድሃነቱ ይነቀታል እንጂ ደሃም ጋር ዕውቀት አለ
- ከመከራ ከችግር ትምህርት ያገኛል

ጠይብ በገል ይበላል
- ምጥ ለእናቷ አስተማረች

ጠጅ ለወረት ወዳጅ ለችግር አለት
- እውነተኛ ወዳጅ ለችግርህ ጊዜ ይደርስልሃል

ጠጅ ለጨዋ ልጅ መጫወቻ ለባለጌ ልጅ መማቻው
- መጠጥ ለጨዋ ሰው ቁም ነገር የሚወራበት ነው ለባለጌ ግን መደባደቢያው ነው

ጠጅ በብርሌ ነገር በምሳሌ
- ነገርን በምሳሌ ሲነገር አዳማጭ ይኖርሃል

ጠጅና መኮንን ድሃና ጉመን
- ቢጤ ከብጤው

ጠጅ የሌለበት አበጋዝነት
- ምንም ሳይሟላ የኋላውን እፊት

ጠጅ የወረት ወዳጅ
- በመጠጠ የተዋወቁት ወዳጅ የወረት ነው

ጠጅ ይሻላል በመጠኑ የጨዋ ልጅ ይበልጣል በቀጭኑ
- መጠጥን መጥነው ከጠጡት ለውርደት አሳልፎ አይሰጥም

ጠገብሁ ያለውን ብላ አትበለው ፈራሁ ያለውን ድፈር አትበለው
- ሰውን ያለፍላጉቱ አትገፋፋው



ጠጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል
- ወፍራም ሰው ሕመሙ ሳይታወቅ ይሞታል

ጠፍር መጫኛ ቁርበት መጋኛ
- ጠፍር ለመጫኛነት ያገለግላል

ጠፍር በሲታ ብትሔድ ልጓም በሲታ መጣች
- ከእናቲቱ ልጅቱ የባሰች ዓመለኛ ነች

ጡት መጥባት የናት
- የእናት ጡት ለልጅ አስፈላጊ ነው

ጢምህን እጠላለሁ መሳምህን እወዳለሁ
- ሁለት ነገር ወዶ አይሆንም

ጢም የሌለው መምህር አጸድ የሌለው ደብር እምሮ እያምር
- አስፈላጊ ነገር ካልተሟላ አያስደስትም

ጢሰኛ ሲቆይ ባለርስት ይሆናል
- የቆየ ከሚስቱ ይወልዳል

ጣል በደጅ እሰር በፍንጅ
- ሁሉንም ነገር በሥርዓት አከናውን

ጣመኝ ድገመኝ
- ይጣፍጣል ይደገመኝ

ጣት ገማ ተብሎ ተቆርጦ አይጣልም
- የእራስ የሆነ ነገር መጥፎም ቢሆን አይጠሉትም

ጣዝማ ሰርሳሪ ዳኛ መርማሪ
- ዳኛ እውነትን ለማጣራት ይመረምራል

ጣይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም
- ከሕዝብ የሚደበቅ ነገር የለም

ጣጣ ፈንጣጣ ድንጋይ ፈለጣ
- ችግር የበዛበት ነገር

ጣፊያ ቢነሷት ታናሽ ታላቅ ላኩልኝ አለች
- ምኑንም ሳታገኝ ትልቁን ተመኘች

ጣፋጭ ፍቅር ሲያረጅ ፍቅረኞችን ያፋጅ
- ፍቅር ሲቀዘቅዝ ጭቅጭቅ ንዝንዝ ይፈጥራል

ጤና ከሀብት ወፍጮ ከከብት አይቆጠርም
- ጤና ካለህ ሠርተህ ሀብትን ታገኛለህ

ጤፍ መፍለስሽን ቢያይ ገበሬ ባልዘራሽ
- ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው

ጤፍ ቢለኩ ለማይን ቢያኩ አይገኝም ልኩ
- ሚስጥሩ አልተገኘም

ጤፍ አይቀላ የጨዋ ልጅ አይጠላ
- የጨዋን ልጅ ማንም አይጠላውም

ጤፍ አጉደለ ቢለው ገብስ እንዳይሰማ አለው
- የሆነው ሆነ ያልሆነውን ካልተደረገው ነገር ጠንቀቅ በል

ጤፍ ከዘመዷ ጉታ ትሞላለች
- ሁሉም በየለፍራው

ጤፍ ካላረጡ አይለማ ሥጋ ካልሰነበተ አይገማ
- ሥራን በወቅቱ ካላከናወኑት ውጤት የለውም

ጥለውት የመጡትን ጓደኛ ዞረው አያዩትም
- መጥፎ ሥራ ሠርተው ተመልሰው ማየት ያሳፍራል

ጥላና ሸኚ ቤት አይገቡም
- ሸኚ ቤት አያደርስም

ጥልቅ ብዬን ውኃ ወሰዳት
- የእርጉ ዝንብ

ጥል ያለሽ በዳቦ
- ያለምክንያት ጠብ መፈለግ

ጥል ያጠላላ ከሶ ዛፍ ይጠላ
- ግጭት ያጨካክናል

ጥምባሆ ለምን ይበጃል ያስተዋውቃል
- ሲጋራ ለምንም ነገር አይጠቅምም

ጥምብ ባለበት ቁራ ይዞራል
- ጥሩ ነገር በሚገኝበት ቦታ ሁሉም ይሯሯጣል

ጥምድ እንደበሬ ቅንት እንደገበሬ
- ሁሉም እንደየአስፈላጊነቱ

ጥምጥም የሌለው መምህር አጸድ የሌለው ደብር
- አይኳኳኑም

ጥሩ መስሎ አተላ ፍሬ መስሎ ገለባ
- ሲያዩት ደህና ይመስላል ውስጡ ግን አይረባም

ጥሩ እንደብርሌ ቀይ እንደበርበሬ
- ከሆነ አይቀር ጥሩ ዕቃ መሆን አለበት

ጥሩ ወዳጅ ጥሩ ጠላት ይሆናል
- ወዳጅ አንድ ቀን ጠላት ሲሆን ይችላል

ጥሩ ድህነት ጥሩ ነፃነት ጥሩ ሀብት መልካም እርስት
- ከሆነ አይቀረ እንዲህ መመሳሰል አለበት

ጥሬ ለዶሮ ግልገል ለቀበሮ
- ተስማሚ ነገር ነው

ጥሬና ክፉ ንግግር ሆድ ያሻክራል
- መጥፎ ንግግር ሆድን ያሻክራል

ጥርስና ከናፍር ቢደጋገፍ ያምር
- ተባብረው የሠሩት ነገር ያረካል

ጥርስና ከናፍር አብሮ ይደማል
- እውነተኛ ወዳጅ አብሮ ይሞታል

ጥቂት ሕመም ታመህ ወደጅ ጠላትህን እየው
- ወዳጅ ዘመድህን በክፉ ጊዜ ፈትነው



ጥቂት ሥጋ እንደመርፌ ትወጋ
- የሥጋ ዘመድ ሲጠቃ ያበሳጫል

ጥቂት ያላት አረፍት የላት
- ትንሽ ሀብት ያለው ሰው ካሁን አሁን ተዘረፍኩ ብሎ በሐሳብ ሲጨነቅ ያድራል

ጥቂት ጥቂት ኤሊም ትሔዳለች ካሰበችበት ትደርሳለች
- በጥቂት በጥቂት ይሞላል ልቃቂት

ጥቃት ከጥንብ ይገማል
- መጠቃት ያዋርዳል

ጥቅልል ያለን ጠጉር ዘርዘር ያለ ሚዶ ያስነሳዋል
- ለሁሉም ነገር ጌታ አለው

ጥበብ ያስከብራል ሀብት ያስጨፍራል
- ዕውቀት ያስከብራል

ጥሩ ወዳጅ ጥሩ ጠላት ጥሩ ጠላት ጥሩ ወዳጅ ይሆናል
- ወዳጅህ አንድ ቀን ጠላትህ ሲሆን ይችላል

ጥንብ ባለበት ቁራ ይዞራል
- ሁሉም ምግቡን ያውቀዋል

ጥንቱንም ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ
- ቀድሞውንም አሳፋሪ ሥራ ባልሠራሽ

ጥንቱንም የተውሶ ጠፋ ተመልሶ
- የራስ ያልሆነ ነገር አያስተማምንም

ጥንቱን ሲሉህ ቡዳ ቆዳ ይዘህ ሜዳ
- በነገሩ እየታማህ የምትታማበትን በአደባባይ ይዘህ ትዞራለህ

ጥንቸልም ለሆዷ ዝሆንም ለሆዱ አብረው ውኃ ወረዱ
- ሁሉም ለሆዱ ይሯሯጣል ይለፋል

ጥንቸል እንደ ዝሆን እጮሃለሁ ብላ ተለንጥቃ ሞተች
- ከአቅም በላይ የሆነ ነገር አትሞክር

ጥንቸል እንዳቅሟ ታግታለች
- ሁሉም የአቅሙን ያህል ይሠራል

ጥዋት ሽሮ ማታ ዶሮ
- የማታ እንጀራ ይሰጠኝ

ጥዋት ከበላተኛ ማታ ከጸመኛ
- አስመሳይ ሰው

ጥዋፍ ያበራል ከሳሽ ይመራል
- ቀደምትነት ያለው አብዛኛውን ጊዜ ይሳካለታል

ጥይት እይር ፈትል ድውር
- ማንኛውም ነገር ግጣሙን አያጣም

ጥይት የፈራትን ትወጋለች
- የፈራኸው ነገር አይቀርልህም ካልተጠነቀቁ

ጥጃ ሣር ይበላል ቤቱ ዕዳ ይሞላል
- በትክክል ይሠራል

ጥጃ ቢሳሳት ከናቱ ነገር ቢሳሳት ከጧት
- ነገርን በጊዜው ካላስተካከሉት ለአደጋ ያጋልጣል

ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ውኃ ቢሔድ በጉድጓዳ
- ሁሉም በአካባቢው ይዝናናል

ጥጃ ጠባ ከሆድ ገባ
- የራስ ወገን አገኘ ማለት አንተ እንዳገኘህ ትቆጥረዋለህ

ጥጋበኛና ውኃ ሙላትን ቀመህ አሳልፈው
- ትዕግስት ጥሩ ነው

ጥጋብ ቢሻህ ባቁላ ቢሻህ ችላ
- ኑሮን ሳይጨነቁ መኖር መልካም ነው

ጥጋብ ቢያምርህ ጠላ መግዛት ቢያምርህ ችላ
- ከሌለህ የለህም

ጥጋብ ወደኛ በል ጥጋበኛን ወዲያ በል
- ጥጋበኛን ሰው አታቅርበው

ጥጋብ የማይችል አህያ ነው
- ጥጋብ የማይችል ሰው ለአደጋ የተጋለጠ ነው

ጥጥ ለፈታይ ሸልማት ላገልጋይ
- ለሚሠራ ሰው ሽልማት ያስፈልገዋል

ጥጥና ሹም አያደር ይከዳል
- ሰው ሲሾም ይኮራል

ጦም ከማደር ዳቦ ቀርቅር
- ለወደፊቱ አስበህ ማስቀመጥ ይበጃል

ጦም የሚያድሬ ሆድ በጠዋት ይራባል
- ሳይኖርህ ብዙ ነገር ያምርሃል

ጦር ለወረወረ መሬት ለገበረ
- መሣሪያን ካልተጠቀሙበት ዋጋ የለውም

ጦር ለወረወረ ጉራዴ ለሰነዘረ
- መሣሪያን ካልተጠቀሙበት ዋጋ የለውም

ጦር መጣ ሲባል ሰማያ ቆረጣ
- ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ
- ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

ጦር እንደወረወሩት ጉራዴ እንደሰነዘሩበት
- መሣሪያን ካልተጠቀሙበት እንደመሣሪያ አይቆጠርም

ጦር ከወጋው ምላስ የወጋው
- ነገር የገባው ሰው ያበላሼል ከሚናገሩህ ቢመቱህ ይሻላል

ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው
- በወሬ የተሸበረ በወሬ ተበተነ

ጦርና ጭሬ አራሽና ገበሬ
- ለሁሉም ነገር እግዚአብሔር ያመቻችልናል



ጦጣ ምን ትወጂያለሽ ቢሏት ከዛፍ ላይ ትግል
- ሁሉም የሚወደውን ነገር ያስቀድማል

ጦጣ በልታ በዝንጀሮ አፍ አበሰች
- የራሷን ስሕተት በሌላ ሰው አላከከች

ጦጣ ባለቤቷን ታስወጣ
- ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ

ጦጣ ተይዛ ትዘፍን
- እጠላት እጅ ከገቡ የሚያደርጉት ያጣሉ

ጦጣና ዝንጀሮ ተከላና ቀበሮ
- ቢጤ ከቢጤው

ጧሪ በፈጣሪ
- ዓምላክ ካለ ምንም አላስብም

ጧት ከበላተኛ ማታ ከዕድምተኛ
- ሁሉንም በሥርዓት አከናውን

ጧት ከበላተኛ ማታ ከጦመኛው እንደ ሽመላ በሁለት ይበላ
- ካንዱ ያልሆነ

ጧት ከጀንበር ማታ ከጨንገር
- ማታ ተደብቆ እጠንቋይ ቤት መሔድ

## ጬ

ጨለማ ልብሱ
- ሁሉንም ነገር ተደብቆ በጨለማ ነው የሚያከናውነው

ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል
- መሪው ሲጠፋ ደካማው ተነስቶ እኔ ነኝ የበላይ ይላል

ጨረቃ ብትደምቅ አትሞቅ
- አንድ ነገር ቢመሳሰልም እንደዛኛው አይሆንም

ጨረቃና ሴት ዛሬ ብርሃን ነገ ጽልመት
- ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ አንድ ነው

ጨቅጫቃ ሚስትና የሚያፈስ ቤት አንድ ናቸው
- ጨቅጫቃ ሚስት ያለው ሰው ሁሌ ሰላም የለውም

ጨብጦ የቀረ ተጨብጦ ቀረ
- ሀብቱን በሥራ ላይ የማያውል ሰው አይከበርም

ጨካኝ ለይጣን መሰይ
- ጭካኔ ከጋኔን ያስቆጥራል

ጨካኝና ጢስ መውጫ አያጣም
- ደፋር ማምለጫውን አያጣም

ጨካኝ አልሞተ ፈሪም አልሞተ አጓጉልኛ ሞተ
- ፈሪም ይጠነቀቃል ቸልተኛ ሰው ግን ለአደጋ የተጋለጠ ነው

ጨዋታ ለዐዋቂ ወሬ ለጠያቂ
- ነገር የሚያውቅ ሰው ጨዋታው ይማርካል

ጨዋታን አዳምጦ እህልን አላምጦ
- ጨዋታ ካልተደማመጡ ቁም ነገር የለውም

ጨዋ አይነቀፍ እሳት አይታቀፍ
- ጨዋ ሰው ይከበራል

ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል
- ጸባይህን አሳምር ጸባይህን ካላስተካከልክ ራስህን ትጎዳለህ

ጨው ሲበዛ ያቅራል በርበሬ ሲበዛ ይመራል
- ከልክ በላይ የሆነ ነገር ጥሩ አይደለም

ጨው ሻጭ በገበያ ጦር በሶማያ
- ማንኛውም ነገር በአካባቢው ያምራል

ጨው ቢያልጥ በምን ይጣፍጣል ዳኛ ቢያደላ በምን ይሟገቷል
- ዳኛ አንዴ ከፈረደ ልትሟገተው አትችልም

ጨውና በርበሬ ጆሮና ወሬ
- ወሬ ካላጣፈጡት ለሚ አያገኝም

ጨው የሌለው ምግብና ሰው የሌለው ሰው አንድ ነው
- አጋር የሌለው ሰው ብድር የሚመልስለት ሰው አያገኝም

ጩኸት ለቁራ መብል ላሞራ
- የሠራው ሳይበላ ያልሠራው ይበላ

ጫማ ምንም ወርቅ ቢሆን ከእግር በታች ነው
- ምንም ቢያምር ከመረገጡ አይድንም

ጫማ የለንም ብለው የሚያጉረመርሙ እግር የሌላቸውን አይተው ይጽናኑ
- ካንተ የባሱ እያሉ ኑሮን ማማረር አይገባም

ጫንቃዬን ተገርፌ ጨርቁን ተገፍፌ
- ቀማኛ ዘረፈኝ

ጫን ካለ ጫን ይፈጃል
- ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም

ጫን ያለው ኮርቻውን ለምን ያለው ስልቻውን አያጣም
- ሁሉም እንደፍላጎቱ ይሟላለታል እግዜር ጥሎ አይጥልም

ጫጩትን አትቁጠር አይሆኑም እጥር
- ጥቅም በማይጠቅምህ ነገር እምነት አትጣል

ጭልፊትና ሲላ ተጋብተው ጉጉት ወለዱ
- የእላት ልጅ አመድ

ጭልፊትን የወደደ መንጠቅን የለመደ
- መንጠቅ የለመደ ሰው ዓመል ይሆንበታል

ጭምት ያበደ እንደሆን የጤፍ ቆረን ደኑ
- ደህና ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም

ጭምጭምታ ክፉኛ ያስመታ
- ያልተረጋገጠ ወሬ ማውራት ለአደጋ ይሰጣል



ጭራሮ የምጣድ ጉሮሮ
- ጭራሮ ለምጣድ መለኮሻ ናት

ጭሰኛ ካለበት እሳት አይጠፋም
- ሥራውን የሚሠራበት ነገር ከሠራተኛው ሥር አይጠፋም

ጭስ አጨሰበት እሳት አይጠፋም
- ሥራ ከተሠራ ውጤት ይገኛል

ጭብጥ ቆሎ ይዘህ ከአሻሮ ተጠጋ
- ትንሽ ገንዘብ ይዘህ ከሀብታም ተጠጋ

ጭንቅ አልጋ ያስተቃቅፋል
- ጭንቅ ከሰው ያቀራርባል

ጭንቅ ያለመቃብር የለም
- መጨነቅ መፍትሔ ስለማያስገኝ ትዕግስት ያስፈልጋል

ጭድና ጭቃ ቡሃና ቦቃ
- ሁሉም እንደአስፈላጊነቱ ይከናወናል

ጭጭ ጭልፊት እንደዘረው ጫጩት
- መደንገጥ ዝም ያስብላል

ጮሌ ሲያረጅ መጋዣ ይሆናል
- ሁሉ ሰው ሲያረጅ ጠቃሚነቱ ያከትማል

ጮኻ የማታውቅ ወፍ አንድ ቀን ብትጮህ እለቁ እለቁ አለች
- ሠርቶ የማያውቅ ሰው አንድ ቀን ቢሠራ አላስቀምጥ አለ

## ጰ

ጳጉሜን ሲወልስ ገበሬ ጉተራህን አብስ
- ጳጉሜ ከዘነበ እጥጋቢ ተስፋ ስላለ ያለህን ተጠቀምበት

ጳጉሜ ቢለግስ ጉተራህን አብስ
- ጳጉሜ ከዘነበ እጥጋቢ ተስፋ ስላለ ያለህን ተጠቀምበት

## መልመጃ 16 /ጠ፣ ጨ፣ጸ/

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. ________ ልጓም በሊታ መጣች
   ሀ. ጥሬ በሊታ ብትሔድ ለ. ጠፍር በሊታ ብትሔድ
   ሐ. ጥገት በሊታ ብትሔድ መ. ልጅ በሊታ ብትሔድ

2. ጥምብ ባለበት ________
   ሀ. ቁራ ይዞራል ለ. አትሩጥ ሐ. አትለፍ መ. ወፍ ይዞራል

3. ጣት ገማ ብሎ ________
   ሀ. ቆርጦ አይጣልም ለ. ይቆረጣል ሐኪም ቤት
   ሐ. ይታከማል መ. መልሱ የለም

4. ጥላና ሸኝ ________ አይገባም
   ሀ. ኩሽና ለ. ቤት ሐ. ጉድጓድ መ. ገደል

5. ጣፋጭ ፍቅር ሲያረጅ ________ ያፋጅ
   ሀ. ጉረቤት ለ. ጉረምሳ
   ሐ. ፍቅረኞችን መ. ሁሉም መልስ ነው

6. ጨኸት ለቁራ ________
   ሀ. ፋከራ ለጀግና ለ. ዳቦ ለልጅ
   ሐ. አጥንት ለውሻ መ. መብል ላሞራ

7. ጨው ሻጭ በገበያ ________ በሰማያ
   ሀ. ዶማ ለ. ጦር
   ሐ. ጋሻ መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

8. ጨውና በርበሬ ________
   ሀ. ዓይንና ግንባሬ ለ. ወሬ ለጠያቂ
   ሐ. አካልና ጉበት መ. ጆሮና ወሬ

9. ጭልፊትን ________ መንጠቅን የለመደ
   ሀ. የመታ ለ. ያባረረ ሐ. የወደደ መ. የጠላ

10. ጫንቃዬን ተገርፌ ________
    ሀ. ጨርቄን አራግፌ ለ. ጨርቄን አንጨፍጭፌ
    ሐ. ጨርቄን ተገፍፌ መ. ልብሴን አጣጥቤ

11. ______ የምጣድ ጉሮሮ
    ሀ. ጭራሮ ለ. እንገቴ ሐ. አከንባሎዬ መ. አካሌ

12. ______ ክፉኛ ያስመታ
    ሀ. ጨዋታ ለ. ልፍለፋ ሐ. ጭምጭምታ መ. ፉገራ



13. ጭድና ጭቃ ______ በቃ
    ሀ. ፍሬና ለ. በሣና ሐ. ጠላና መ. ጭድና

14. ጳጉሜ ________ ጉተራህን አብስ
    ሀ. ሲደርስ ለ. ቢለግስ ሐ. ካለፌ መ. መልሱ የለም

15. ጥሬ ለዶሮ ________ ለቀበሮ
    ሀ. ሥጋ ለ. እንጀራ ሐ. ጥንብ መ. ግልገል

16. ጢሰኛ ሲቆይ ______ ይሆናል
    ሀ. ባለቤት ለ. ድሃ ሐ. ሀብታም መ. ባለርስት

17. ጡት ______ የናት
    ሀ. ያለ ለ. መጥባት ሐ. የሌላት መ. መልስ የለም

18. ጣጣ ፈንጣጣ ________
    ሀ. ድንጋይ ፈለጣ ለ. ከባድ ፈለጣ
    ሐ. ዳኛ መርማሪ መ. መልስ የለም

19. ጥል ያጠላላ ______ ላፍ ይጠላ
    ሀ. ሬት ለ. ዐረቄ ሐ. ጠላ መ. ኮሶ

20. ጥል ያለሽ________
    ሀ. በዳቦ ለ. ባካፋ ሐ. ባበሳ መ. በሌላ

21. ጥሩ ወዳጅ________ ይሆናል
    ሀ. ደጋፊ ለ. ጥሩ ጠላት
    ሐ. አሳቢ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

22. ጥቂት ______ እንደመርፌ ትወጋ
    ሀ. እሳት ለ. ውኃ
    ሐ. ሥጋ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

23. ጥቂት ያላት ______
    ሀ. ሐሳብ የላት ለ. ሐሳብ የለባት
    ሐ. ድፍረት አላት መ. እረፍት የላት

24. ጥቃት ________
    ሀ. ከጥንብ ይገማል ለ. ያበሳጫል
    ሐ. ያስገድላል መ. ያጋድላል

25. ጥይት ________
    ሀ. አይር ለ. የፈራትን ትወጋለች
    ሐ. ሰው ታበላሻለች መ. መልሱ የለም

26. ጥንቸል እንደአቅሟ ______
    ሀ. ታግታለች ለ. ትማታለች
    ሐ. ታስታርቃለች መ. ትኮራለች

27. ጥዋት ከበላተኛ __________
ሀ. ማታ ከጠጪ ለ. በምሳ ሰዓት ከረኃብተኛ
ሐ. ማታ ከጸመኛ መ. ማታ ከከዳተኛ

28. ጥጥና ሹም _______
ሀ. እያደር ይሠራል ለ. እያደር ይቀላል
ሐ. እያደር ያስባል መ. እያደር ይከዳል

29. ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ _______ በጕድጓዳ
ሀ. ምግብ ቢበላ ለ. ገበጣ ጨዋታ
ሐ. ዝንጀሮ ቢሔድ መ. ውኃ ቢሔድ

30. ጦር ለወረወረ ______ ለለነዘረ
ሀ. ሥጋ ለ. ቦከስ ሐ. ድንጋይ መ. ጉራጌ

31. ጦር መጣ ሲባል _________
ሀ. ሰማያ ቀረጣ ለ. ዛቢያ ቀረጣ
ሐ. ፋከራ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

32. ጦር ለወረወረ______ ለገበረ
ሀ. ነጋዴ ለ. ገበሬ ሐ. መሬት መ. መልሱ የለም

33. ጦር ከፈታው ______
ሀ. ገበሬ የፈታው ለ. ዳኛ የፈታው
ሐ. ወሬ የፈታው መ. ሽማግሌ የፈታው

34. ጧሪ _______
ሀ. በእለኝታ ለ. በፈጣሪ ሐ. በእከባሪ መ. በእባሪ

35. ጨረቃ _____አትሞቅ
ሀ. ብትወጣ ለ. ከፀሐይ ሐ. ከኮከብ መ. ብትደምቅ

36. ጨካኝ ______ መሳይ
ሀ. ጨዋ ለ. ጥሩ ሐ.ሰይጣን መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

37. ጨብጦ የቀረ _______
ሀ. ያለሐሳብ ቀረ ለ. እፍርቶ ቀረ
ሐ. እድቦ ተቀመጠ መ. ተጨብጦ ቀረ

38. ጭልፊትና ሲሳ ተጋብተው ________
ሀ. እርግብ ወለዱ ለ. ዶሮ ወለዱ
ሐ. ጫጩት ወለዱ መ. ጉጉት ወለዱ

39. ጭስ እጨስበት ____________
ሀ. እሳት አይጠፋም ለ. ዕንጨት አይጠፋም
ሐ. ጭራሮ አይጠፋም መ. ሁሉም መልስ ነው



40. ጭምት ያደበ እንደሆነ __________ ደኑ
ሀ. ሥንዴ ለ. ጫካ ሐ. የጤፍ ቆረን መ. ጭራሮ

ለ. <u>ሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው</u>

1. ጠላ ሲሉት ሽምጥ ኮሶ ሲሉት ስቅጥጥ
ሀ. መብል ሲሉት ይሮጣል ሥራ ሲሉት ይሸሻል
ለ. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

2. ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ
ሀ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
ለ. ሉሚን ካልመጠጡት እንቧይ ነው
ሐ. ሙሽራ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
መ. መልሱ የለም

3. ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ እባወራ ይሆናል
ሀ. ወርካ በሌለበት እንቧጮ እድባር ይሆናል
ለ. ጋኖች እለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
ሐ. ዓይን መሪ ልብ መካሪ
መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

4. ጥርኝ ቆሎ ይዘህ ከእሻሮ ተጠጋ
ሀ. ጅብን ሲወጉ ከእህያ ይጠጉ
ለ. መንፈራገጥ ለመሳሳጥ
ሐ. ሁለት ነዶ ይዞ ወደክምር ጠጋ
መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

5. ጠጣ ባለቤቷን ታስወጣ
ሀ. ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ
ለ. ቢጤ ከቢጤው
ሐ. መንፈራገጥ ለመሳሳጥ
መ. መልሱ የለም

6. ጥጥና ሹም እያደር ይከዳል
ሀ. ዓይን መሪ ልብ መካሪ
ለ. ሰው ሲሾም እያደር ይከራል
ሐ. ጥጥና ሹም አንድ ናቸው
መ. መልሱ የለም

7. ጨረቃና ሴት ዛሬ ብርሃን ነገ ጽልመት
    ሀ. ሙሽራ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
    ለ. ሁለት ነዶ ይዞ ወደከምር ጠጋ
    ሐ. ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ አንድ ነው
    መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

8. ጭልፊትና ሲሳ ተጋብተው ጉጉት ወለዱ
    ሀ. የእሳት ልጅ አመድ
    ለ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ
    ሐ. በጨዉ ደንደስ በርበሬ ተወደስ
    መ. መልሱ የለም

ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1.ጠጣ ባለቤቱን ያስወጣ | ሀ. እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ |
| 2.ሙሌ ሲያረጅ መጋጃ ይሆናል | ለ. ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ አንድ ነው |
| 3.ጥርስና ከንፈር ተደጋግፎ ያምር | ሐ. በኋላ የመጣ ዓይን አወጣ |
| 4.ጠባቂ ያሳት በግ ላትዋ አደጅ ያድራል | መ. የእሳት ልጅ አመድ |
| 5.ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ | ሠ. ጌታውን የተማመነ ውሻ ሰንጋ ሲታረድ ወንዝ ይወረድ |
| 6.ጨረቃና ሴት ዛሬ ብርሃን ነገ ጽልመት | ረ. ይታደሱታል እንጂ አይታገሱትም |
| 7.ጫን ካለ ጫን ይፈጃል | ሰ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር |
| 8.ጭልፊትና ሲሳ ተጋብተው ጉጉት ወለዱ | ሸ. ደህና ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የሰውም |
| 9.ጭምት ያደበ እንደሆን የጤፍ ቆረን ደነ | ቀ. ጳጉሜ ቢለግስ ጕተራህን አብስ |
| 10. ጳጉሜ ሲወልስ ገበሬ ጕተራህን አብስ | በ. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል |
| 11. ጠያቂ ባይኖር ሁሉ መምህር | ተ. ዝናብ ባይኖር ሁሉም ቤት |
| 12. ጠይብ በገል ይበላል | ቸ. ምጥ ለእናቷ አስተማረች |
| 13. ጢበኛ ሲቆይ ባለርስት ይሆናል | ኀ. የቆየ ከሚስቱ ይወልዳል |
| 14. ጥዋት ሽሮ ማታ ዶሮ | ነ. የእርጕ ዝንብ |
| 15. ጥልቅ ብዬን ውኃ ወሰዳት | ኘ. የማታ እንጀራ ይስጠኝ |



## ፀ

ፀሐይ ሳለ ሩጥ አባት ካለ አጊጥ
- በጊዜህ ተጠቀምበት

ፀሐይ ብልጭ ወፍ ጭጭ ሲል
- በማለዳ

ፀሐይና ንጉሥ ሳለ ሁሉም አለ
- ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ

ፀሐይ ካልወጣ ከሰፈረበት አይነሣ አንበጣ ሴት ምክንያት አታጣ
- ሴት መላ አታጣም

ፀሐይ የጠዋት አዱኛ የሽበተ
- የኋላ እንጀራ ይስጠኝ

ፀሐይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም
- ከሰው የተደበቀ ነገር አይኖርም

## ጸ

ጸሎት በጥሞና ነገር በደመና
- እምነት ከልብ መሆን አለበት

ጸሎት በፍቅር ኃይማኖት በምግባር
- መጸለይ ልብን ንጹህ አድርጕ ነው

ጸሎት ከፍቅር ኃይማኖት ከግብር ይበጃል
- እምነት ከልብ መሆን አለበት

ጸሎት ያለ ፍቅር ኃይማኖት ያለግብር አይረባም
- ከልብ ያልሆነ እምነት አያጸድቅም

ጸጸት እያደር ይመሠረት
- ነገር እያደር ሲገባህ የረሳኸው ነገር እንደገና ይቀሰቅሰብሃል

ጻድቃን ካልተቃጠሩበት ስፍራ ይገናኛሉ ኃጠአን ግን ከታቃጠሩበት ይተጣጣሉ
- ጻድቃን ሰው ምኞቱ ይሳካለታል

ጽሕፈት በብራና ዘፈን በገበና
- ሁሉም ተስማሚ ነገር ይመቻችለታል

ጽዋ በተርታ ሥጋ በገበታ
- ማንኛውም ነገር በሥርዓት ሲከናወን ያስደስታል

ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ
- ዋናው ቀርቶብኝ ትንሹንም ባገኘሁ

ጽድቅ ለመንኲሽ ቀን ለከሳሽ
- ከመነኮስክ ትጸድቃለህ

ጾማ ጾማ ለጸሎት ሐሙስ እርጕ ትልስ
- ለፍቶ መና

ጾም ገዳፊና ሰው ጠባቂ ለጥቂት ይሳሳታል
- ለፍቶ መና

# ፈ

ፈላ ገነፈለ ተሞላ ጐደለ
- ከተጠቀሙበት የማያልቅ ነገር የለም

ፈረሰኛ ሲሮጥ እግረኛ ምን አቆመው
- በማይመስከተው ነገር ምን አገባው

ፈረሰኛ የወሰደው እግረኛ አይመልሰውም
- ሁሉም ነገር ያለቦታው ተፈጻሚነት አይኖረውም

ፈረሱም ይኸው ሜዳውም ይኸው
- ከቻልክ አድርገው ተፈቅዶልሃል

ፈረስ ሲያጠብቅ ልጓም አይለቅ
- አደገኛ ሁኔታ እንኳን ቢያጋጥምህ ከቁም ነገር ላይ እንዳታፈነግጥ

ፈረስ በራሪ በቅሎ ሰጋሪ
- ሁሉም እንደየፍጥረቱ ነው የሚያገለግለው

ፈረስ ቢያነክስ አህያ ታጉዝ
- ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም

ፈረስ ቢጠፋው ኮርቻ ገልቦ አየ
- የማይደረግ ነገር አረገ

ፈረስ ዐውቃለሁ ስገታ እወድቃለሁ
- ሳታውቅ ዐውቃለሁ ማለት ጥሩ አይደለም

ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም
- ለሚፈለገው ነገር እርዳታ ይሰጣል እንጂ ሙሉ በሙሉ አይረዳም

ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል በቅሎ ጥሎ ይግጣል
- የጨዋ ልጅ ሳደረገው ስሕተተ ይጸጸታል የባለጌ ልጅ የባለ ነገር ይፈጽማል

ፈረንጆች እንደመረሬ ይገቡ እንደዋርካ ይሰፉ
- ለላ ብሎ ገብቶ እቤቴ ቀረ ተንሰራፍቶ

ፈሩ ፈሩ ማጀት እሩ
- እስከመቼ ተፈርቶ ይኖራል

ፈሪ ለእናቱ ይገባል
- ፈሪ ከአደጋ እራሱን ይጠብቃል

ፈሪ ለእናቱ ጀግና ለጀግንነቱ
- ፈሪ ከአደጋ እራሱን ይጠብቃል

ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል
- ከተጣላ አደጋ ላይ ስለሚወድቅ ራሱን ያረጋጋል

ፈሪና ንፉግ እያደረ ይቆጨዋል
- ማንኛውም ሰው ኋላ ላይ ሲያውቀው ይጸጸታል

ፈሪን በውኃ ውስጥ ያልበዋል
- ከመጠን በላይ ስለሚፈራ



ፈሪ እንዳይሉኝ አንድ ገደልሁ ጀግናም እንዳይሉኝ አልደገምሁ
- የማይችሉትን ነገር ለመሞከር አያድርጉ አለመቻል እያዋርድም

ፈሪ ካልጋ ላይ ይወድቃል
- ፈሪ በሆነው ባልሆነው ነገር እንደባነነ ነው የሚኖረው

ፈሪ የናቱ ልጅ ነው
- ፈሪ ለእናቱ ይገባል

ፈሪ ፈራና ከጉድባ ቢተኛ ጆሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ
- አጉል ፍራቻ ለባሰ አደጋ ያጋልጣል

ፈርተው ድንጋይ ቢወረውሩ ጅብ ወጣ ከዱሩ
- ፈርተው የሚሠሩት ነገር ለአደጋ ያጋልጣል

ፈስ በወረንጦ እየተለቀመ ነው
- በጣም እየተጨነቁ ነው

ፈስቶ ቂጥ መያዝ
- ስሕተት ሠርቶ ያልሠሩ መምሰል

ፈስ ያለበት ቂጥ ዝላይ አይችልም
- ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም

ፈትል ሲረዳዳ አንበሳ ያስራል
- ከተባበሩ ከባድ ሥራ መሥራት ይቻላል

ፈዛዛ እያንቀላፋ ይገባ ፈፋ
- መፍዘዝ ለአደጋ ያጋልጣል

ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ እስቲበርድ ይራበኝ
- ከፍትፍቱ ፊቱ

ፈገግታ የልብ አለኝታ
- ከፍትፍቱ ፊቱ

ፈጣሪን ያህል ጌታ ርስትን ያህል ቦታ
- ፈጣሪን የሚያህለው የለም

ፈጥነው የገመዱት ፈጥኖ ይበጠሳል
- የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

ፈጥኖ መስጠት ኋላ ለመጸጸት
- የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

ፈጭታ የነበረች ላመልማሎ ኮራች
- ከባዱን ሥራ ሠርታ ለቀላሉ ኮራች ለፍቶ መና

ፉት ቢሉት ጭልጥ
- ለቅምሻ እንኳን የማይሆን

ፊተኛው ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ ምነው? ኋለኛው እንዳይሸሽ
- ሁሉን ነገር በዘዴ ማከናወን ጥሩ ነው

ፊት ከወጣ ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠ
- ከበፊቱ የኋለኛው ተሻለ

ፊት የተናገረን ሰው ይጠላዋል ፊት የደረሰን ወፍ ይብላው
- ቀደም ቀደም ማለት ጥሩ አይደለም

ፊት ያሞጠሙጧል ኋላ ያፏጯል
- ስሜትህ ያስታውቅብሃል

ፊት ያሞጠሙጣል ኋላ ያስሟል
- ስሜትህ ያስታውቅብሃል

ፊት ጆሮ ይበቅላል ኋላ ቀንድ ይበቅላል
- ቅደም ተከተሉን መከናወን ይኖርበታል

ፊደል ያወቀ ሁሉን አስለቀቀ
- መማር መልካም ነገር ነው

ፋሲል ሲፈርስ ጎንደር ይታረስ
- የፋሲል ግንብ ቅርስ ስለሆነ መቼም አይፈርስ ከፈረሰ ግን ጎንደር መታረስ አለበት ነው የሚሰው

ፋሲካን ሊያገኙ ሁዳዴን ይመኙ
- ችግርን አልፈህ ነው ደስታን የምታገኘው

ፋሲካ የሌለው ጦም ደስታ የሌለው ዓሰም
- የሁዳዴን ጾም ያልጾመ ክርስቲያን ሊባል አይችልም

ፋቂ ቁርበቱን አናጢ ዕንጨቱን
- ሁሉም የሚስማማውን የሚሠራበትን ነገር ያዘጋጃል

ፋኖ ቢሰማራ ከጠላት ሊበላ
- የጫካ ወንበዴ ሕዝብን እያስገደደ ይበላል

ፌቆ ስትዘል አትፈራ ገደል
- በራሱ የሚተማመን ሰው ሥራውን በድፍረት ይሠራል

ፌንጣ ብትቆጣ አንድ እግሯን ታጣ
- ሁሉን ነገር በትዕግስት ማሳለፍ ደግ ነው ያለበለዚያ አደጋ ሊደርስ ስለሚችል መጠንቀቅ

ፌንጣ ብትቆጣ እግሯን ጥላ ሔደች
- ታግሶ አለማለፍ ለችግር ይዳርጋል

ፌንጣ አቅሟን ዐታውቅ ትንጣጣ
- አቅምን ዐለማወቅ ለአደጋ ያጋልጣል

ፍላጎት አይረግፍም ካልከሰሙ እንደፍም
- ሰው ከሆንክ መመኘትህ አይቀርም

ፍልፈል ሳትጠረጥር አጥር አትመንጥር
- እራስህን ሳታጠናክር ትልቅ ነገር ለመሥራት አታቅድ

ፍረድ ለነፍስህ ብላ ለክርስህ
- ለጽድቅ ብለህ ፍርድ አታዛባ

ፍሬ ለመብል ስንቅ ባገልግል
- ማንኛውም ነገር መገልገያ ተፈጥሮለታል

ፍርድ ለልጅ ጥራጊ ለደጅ
- ፍርድ ማዛባት ጥሩ አይደለም

ፍርድ ለተቀማጭ ወጥ ለቀላዋጭ
- ወጥን የሚያውቀው ቀላዋጭ ሰው ነው



ፍርድና ፍትፍት በየፊት
- ፍርድ የሚፈረደው በግልጽ ነው

ፍርድና ፍትፍት ወደፊት
- ፍርድ የሚፈረደው በግልጽ ነው

ፍርድ አያውቅ ዳኛ ተገን አያውቅ እረኛ
- ብልሃት የሌለው ሰው ሥራውን በትክክል ሊሠራ አይችልም

ፍርድ እንደ አሉላ ጽድቅ እንደ ላሊበላ
- ከጸደቁ አይቀር እንደ ቅዱስ ላሊበላ ነው

ፍርድ ገምዳይ እውነት አጉዳይ
- በትክክል የማይፈርድ እምነት አጉዳይ ነው

ፍርድ ጐደሰ ደሃ ተበደለ የሚል ንጉሥ አይታጣ
- ለእውነትና ለድሃ የሚያስብ ሰው አይጥፋ

ፍቅርህን የፈለገ ልጅህን ጥልህን የፈለገ የላም ልጅህን
- ልጅህን እየጠሉ አንተን ቢወዱህ ትክክል አይመጣም

ፍቅር ሊጠና ቆሎ ያጓርሳል
- ፍቅር ዕውር ያደርጋል ይሉኝታን ያሳጣል

ፍቅር ያስከረው ነግቶም ያገረሻል
- በፍቅር ያበደ የሚያደርገውን ነው የሚያሳጣው

ፍቅር ያስራል ዕውቀት ያስከብራል ጥበብ ያኮራል
- መማርና ዕውቀትን መገብየት ያስከብራል

ፍቅር ይታወቃል በእግር
- ፍቅር የያዘው ሰው ሲመላለስ ያስታውቅበታል

ፍቅርና ጦር ይጥላል ካጥር
- ፍቅር ያገጣጥማል

ፍትፍት ለልጅ ጥራጊ ለደጅ
- የራስን ልጅ በጣም ስለሚወዱት ይንከባከቡታል

ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ
- አቋሜ አቋሜ ነው ፍንክች የለም

ፍንጥር ፍንጥር እንደሽንብራ ያባ ምንትዋብ ቆከራ
- እንጣጥ እንጣጥና ቆከራ እግባብ አይደለም

ፍየል ላምስት ዶሮ ለባልና ሚስት
- መስለት ሆዳም መሆን

ፍየል መንታ ትወልድና አንዱን ለመጽሐፍ አንዱን ለወናፍ
- ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም

ፍየል በልታ በበግ አሳበበች
- ብልጥ ሰው አድርጎ ባላደረገው ያሳብባል

ፍየል በግርግር እናቷን ይሰርር
- ግርግር ለሌባ ያመቸዋል

ፍየልና ቀበሮ ምጥማጥና ዶሮ
- ሁሉም ነገር የሚመገበውን ነገር አዘጋጅቶለታል

ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
- የቸኮለች እፍሳ ለቀመች

ፍየል ወዲሀ ቅዝምዝም ወዲያ
- አራንባና ቆቦ የማይገናኝ ነገር ፈጸመ

ፍየል የለኝ ከነብር ምን አጣላኝ
- በማያገባኝ ነገር ውስጥ ምን አስገባኝ

ፍየሏን እንደበግ
- የማይመስልን ነገር ማታለል

ፍዳ ለንጥሃን እሴት ለጻድቃን
- ሁሉም እንደየሥራው ነው የሚለጠው

ፍጥም አያናግር የጉርፍ ሙላት አያሻግር
- ቃል መለወጥ ያስጸይፋል

ፍጥም ያቆማል ዕርቅ ይጠቀልላል
- ቃል ያስከብራል ዕርቅ ያፋቅራል

ፍጥም ያውላል አቧራ ያስላል
- ቃል ያስከብራል

ፍጥምጥም አፍራሽ ቤተክርስቲያን ተኳሽ
- ቃልን ያፈረሰ ሰው በሰማይ ቤት ይጠየቃል

ፎከሮ መሸሽ ታሪክ ያበላሽ
- እንጉል ፋከራ መፎከር በኋላ ላይ ደብቁኝ ደብቁኝ ያመጣል



## መልመጃ 17 /ፀ፣ ጸ፣ፈ/

ሀ. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ

1. ጸሎት በጥሞና __________ በደመና
   ሀ. ነገር ለ. ሥጋ ሐ. ክብት መ. መልሱ የለም
2. ጽሕፈት በብራና __________
   ሀ. ዘፈን በጭፈራ ለ. ዘፈን በብራና
   ሐ. ዳንኪራ በጭፈራ መ. ዘፈን በበገና
3. ፈሪ __________
   ሀ. በገዛ ጠበ ገላጋይ ይሆናል
   ለ. የእናቱ ልጅ ነው
   ሐ. በውኃ ውስጥ ያልበዋል
   መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ
4. ፀሐይ ብልጭ __________
   ሀ. ውኃ ምጥጥ ለ. ወፍ ጭጭ ሲል
   ሐ. ዝናብ ሲርከፈከፍ መ. መልሱ የለም
5. ፈንጣ ብትቆጣ __________
   ሀ. እግሯን ጥላ ሔደች ለ. እንድ እግሯን ታጣ
   ሐ. ምን ሊመጣ መ. ትንጣጣ
6. ፍቅር ሲጠና __________
   ሀ. ቆሎ ያጓርሳል ለ. ያጣላል
   ሐ. ያደባድባል መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ
7. ፈገግታ __________
   ሀ. ዕድሜ ይሰጣል ለ. የልብ አለኝታ
   ሐ. ያበሳጫል መ. መልሱ የለም
8. ፈቶ ስትዘል __________
   ሀ. እትከለስ ለ. ትንከባለል
   ሐ. አትፈራ ገደል መ. ትሰበር
9. ጽድቅ ለመንኳሽ __________ ለከሳሽ
   ሀ. ገንዘብ ለ. ቀኝ ሐ. ግራ መ. ሐሳብ
10. ጸጸት እያደር __________
    ሀ. ይመሠረት ለ. ይከሰም
    ሐ. ይደረጅ መ. ሀ እና ሐ መልስ ይሆናሉ
11. ጸሎት በፍቅር __________ በምግባር
    ሀ. ጸባይ ለ. ትምህርት ሐ. ኃይማኖት መ. መልሱ የለም

12. ጽዋ በተርታ ______ በገበታ
ሀ. እህል ለ. ዳቦ ሐ. ሥጋ መ. ሁሉም መልስ ነው

13. ፀሐይ ያየውን ______ አይቀርም
ሀ. ሳይደርቅ ለ. ሰው ሳያየው
ሐ. ከሌለ መ. መልሱ የለም

14. ፀሐይና ንጉሥ ካለ ______
ሀ. ሁሉም አለ ለ. ዳኝነት አለ
ሐ. ክብት አለ መ. ግብር አለ

15. ፀሐይ ላለ ሩጥ ______ አጊጥ
ሀ. እናት ካለ ለ. አባት ካለ
ሐ. ወዳጅ ካለ መ. ሁሉም መልስ ነው

16. ፈረሰኛ ሲሮጥ አግረኛ ______
ሀ. ምን አባረረው ለ. ምን አስቀመጠው
ሐ. ማን መታው መ. ምን አቆመው

17. ፈረስ ______ በቅሎ ሰጋሪ
ሀ. ተቀማጭ ለ. በራሪ ሐ. አጋጅ መ. ጫኝ

18. ፈረስ ቢያነክስ ______
ሀ. አህያ ይጋልብ ለ. ውርንጭላ ታገዝ
ሐ. በሬ ታገዝ መ. አህያ ታገዝ

19. ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል ______
ሀ. በቅሎ ጥሎ ይፈረጥጣል ለ. በቅሎ ጥሎ ይረግጣል
ሐ. አህያ ጥሎ ይግጣል መ. ለ እና ሐ መልስ ይሆናሉ

20. ፈረሱም ይኸው ______
ሀ. አህያውም ይኸው ለ. በቅሎውም ይኸው
ሐ. ሜዳውም ይኸው መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

21. ፈሪ በገዛ ጠቡ ______
ሀ. ይለማመጣል ለ. ገላጋይ ይሆናል
ሐ. ይጮሃል መ. ያንባርቃል

22. ፍረድ ለነፍስህ ______ ለከርስህ
ሀ. ዳቦ ለ. ሥጋ ሐ. ብላ መ. ሁሉም መልስ ነው

23. ፍሬ ለመብል ስንቅ ______
ሀ. በፌስታል ለ. በሣህን
ሐ. በድስት መ. በአገልግል

24. ፈረሰኛ የወሰደውን ______
ሀ. ሕዝብ አይመልሰውም ለ. ፈረስ አይመልሰውም
ሐ. እግረኛ አይመልሰውም መ. መልሱ የለም



25. ፈሩ ፈሩ ______
ሀ. እሜዳ አሩ ለ. ማጀት አሩ
ሐ. ጉረቤት አሩ መ. ሸንት ቤት አሩ

26. ፈረንጆች ______ እንደዋርካ ይሰፉ
ሀ. እንደመርፌ ይገቡ ለ. እንደምሰጥ ይገቡ
ሐ. እንደአይጥ ይገቡ መ. መልሱ የለም

27. ፈሪ ______ ይገባል
ሀ. ገደል ለ. ኩሽና
ሐ. ለእናቱ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

28. ጾም ገዳፊና ______ ለጥቂት ይላሳታል
ሀ. እረኛ ለ. ቄስ ሐ. ደብተራ መ. ሰው ጠባቂ

29. ፈረስ ቢጠፋው ______ አየ
ሀ. ኩሽና ለ. ወደላይ
ሐ. ኮርቻ ገልቦ መ. መልሱ የለም

30. ፈሪና ንፋግ ______ ይቆጨዋል
ሀ. ሐሙስ ለ. እያደር ሐ. ነገ መ. በሳምንት

31. ፈረስ ሲያጠብቅ ______ አይለቅ
ሀ. ጋማ ለ. ኮርቻ ሐ. ልጓም መ. ሁሉም መልስ ነው

32. ______ እየተለቀመ ነው
ሀ. ፈሪ ለ. ፍራፍሬ ሐ. ፍርኃት መ. ፈስ በወረንጦ

33. ፈርተው ድንጋይ ቢወረውሩ ______ ከዱሩ
ሀ. አንበሳ ወጣ ለ. ጅብ ወጣ
ሐ. ቀበሮ ወጣ መ. ሁሉም መልስ ነው

34. ፈበቶ ______
ሀ. አፍ መያዝ ለ. ማፈር ሐ. መሮጥ መ. ቂጥ መያዝ

35. ፈዛዛ ______ ይገባ ፈፋ
ሀ. ሲሮጥ ለ. ሲንጠለጠል
ሐ. እያንቀላፋ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

36. ፈሪ ______ ላይ ይወድቃል
ሀ. ከዛፍ ለ. ከገደል ሐ. ከአልጋ መ. ሁሉም መልስ ነው

37. ፈትል ሲረዳዳ ______
ሀ. ማገዶ ያስራል ለ. ውሻ ያስራል
ሐ. አንበሳ ያስራል መ. መልሱ የለም

38. ፊት ያሞጠሙጧል ______
ሀ. ኋላ ያፏጯል   ለ. ኋላ ይደብሯል
ሐ. ኋላ ይኮሳተሯል   መ. መልሱ የለም

39. ፈጥኖ የገመዱት ______
ሀ. ፈጥኖ ይበጠሳል   ለ. ፈጥኖ ሥራ ላይ ይውላል
ሐ. ፈጥኖ አይሠራበትም   መ. መልሱ የለም

40. ፈጭታ የነበረች ______
ሀ. ለመተኛት ኮራች   ለ. ላመልማሎ ኮራች
ሐ. ለቡና መጠጣት ኮራች   መ. ለምግብ ኮራች

41. ፋቂ ቁርበቱን ______
ሀ. ሞራጅ ወናፉን   ለ. ግንበኛ ድንጋዩን
ሐ. አናጢ ዕንጨቱን   መ. ሁሉም መልስ ነው

42. ፈደል ያወቀ ______ አስለቀቀ
ሀ. ሁሉን ለ. እስረኛን ሐ. ጭቃውን መ. ውሻውን

43. ፍልፈል ሳትጠረጠር ______
ሀ. አትግባ መንደር   ለ. ግባ እመንደር
ሐ. አጥር አትመንጥር   መ. አጥሩን መንጥር

44. ፍርድ _____ ጥራጊ ለደጅ
ሀ. በዳኛ ለ. ለልጅ ሐ. በሽማግሌ መ. በንጉሥ

45. ፍርድ ለተቀማጭ ______ ለቀላዋጭ
ሀ. ወጥ ለ. ፍርፋሪ ሐ. ካልቾ መ. ሁሉም መልስ ነው

46. ፍርድና ፍትፍት ______
ሀ. ወደፊት   ለ. በየፊት
ሐ. ከኛ ፊት   መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

47. ፍርድ ዐያውቅ ዳኛ ______ ዐያውቅ አረኛ
ሀ. ወግ ለ. ጥበቃ ሐ. ተገን መ. መልሱ የለም

48. ፍቅርና ጥል ______
ሀ. ይጥላል ከመንደር   ለ. ይጥላል ካጥር
ሐ. ይጥላል ከገደል   መ. ሁሉም መልስ ነው

49. ፍንክች ______
ሀ. የባለጌ ልጅ   ለ. የባለሥልጣን ልጅ
ሐ. ያባ ቢላዋ ልጅ   መ. የጨዋ ልጅ

50. ፍቅር ______ በእግር
ሀ. ይጓዛል   ለ. ያሯሩጣል
ሐ. ይታወቃል   መ. ሁሉም መልስ ነው



ለ. ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍቺ ምረጡላቸው

1. ፉት ቢሉት ጭልጥ
ሀ. በርቦ የነሷት በገበቴ አማራት
ለ. ለቅምሻ ያህል እንኳን የማይሆን
ሐ. ዋቢ ያለው ባጤ በቅሎ ይቀመጣል
መ. የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ አንጂ ሲወረወር አይታይም

2. ፈጥኖ መስጠት ኋላ ለመጸጸት
ሀ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
ለ. የቸኮለ አፍሶ ለቀመ
ሐ. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
መ. ሁሉም መልስ ነው

3. ፈረስ ቢያነክስ አህያ ታገዝ
ሀ. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ
ለ. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን
ሐ. ውሻን ምናገባው እርሻ
መ. ሁሉም መልስ ነው

4. ፊት የተናገረውን ሰው ይጠላው
ሀ. ፊት የደረሰውን ወፍ ይበላው
ለ. ተናካሽ ውሻ የዝንብ መቋደሻ
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

5. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
ሀ. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች
ለ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
ሐ. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
መ. ሁሉም መልስ ነው

6. ፎክሮ መሸሽ ታሪክ ያበላሽ
ሀ. ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
ለ. ጦር እንደወረወሩት ጉራዴ እንደሰነዘሩት
ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
መ. መልሱ የለም

7. ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም
   ሀ. ኃላፊነት የተጣለበትን ጉዳይ ከፈጸመ የተቀረው የሌላው ባለጉዳይ ፋንታ ነው
   ለ. ለአህያ ማር አይጥማትም
   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ
   መ. መልሱ የለም

8. ጾም ገዳፊና ሰው ጠባቂ ሰጥቂት ይሳሳታል
   ሀ. ለፍቶ መና
   ለ. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
   ሐ. ውሻን ምናገባው አርሻ
   መ. መልሱ የለም

## ሐ. <u>የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አዛምዱ</u>

| | |
|---|---|
| 1.ፍየል በልታ በበግ አበሰች | ሀ. መች መጣሽ ሙሽራ መች ቆረጠምሽ ሽንብራ |
| 2.ፀሐይ ብልጭ ወፍ ጭጭ ሲል | ለ. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም |
| 3.ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ | ሐ. ለፍቶ መና |
| 4.ፈጅቶ ከማያጠግበኝ አስቲበርድ ይራብኝ | መ. ያብዬን እከክ ወደእምዬ ልክክ |
| 5.ፈረስ ቢያነክስ አህያ ታጉዝ | ሠ. የኋላ እንጀራ ይሰጠኝ |
| 6.ጾማ ጾማ ሰጸሎት ሐሙስ አርጕ ትልስ | ረ. ዓሰም ከተፈጠረች አንስቶ |
| 7.ፀሐይ የጠዋት አዱኛ የሽበት | ሰ. የቸኮሰች አፍሳ ሰቀመች |
| 8.ፈጥነው የገመዱት ፈጥኖ ይበጠሳል | ሸ. ሰላ ብሎ ገብቶ እቤት ቀረ ተንሰራፍቶ |
| 9.ፈረንጆች እንደመርፌ ይገቡ እንደዋርካ ይሰፉ | ቀ. ፈሪ ሰእናቱ ይገባል |
| 10. ፈሪ የናቱ ልጅ ነው | በ. ከፍትፍቱ ፊቱ |
| 11. ፈስ ያሰበት ቂጥ ዝላይ አይችልም | ተ. ቁስል ያሰበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም |
| 12. ፍየል መንታ ትወልድ አንዱን ለመጽሐፍ አንዱን ሰወናፍ | ቸ. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም |
| 13. ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲያ | ኅ. አራንባና ቆቦ |
| 14. ፍጥም ያቆማል ዕርቅ ይጠቀልላል | ነ. ቃል ያስከብራል ዕርቅ ያፋቅራል |
| 15. ፀሐይ ካልወጣ ከሰፈረበት አያነሳ አንበጣ ሴት ምክንያት አታጣ | ኘ. ሴት መላ አታጣም |



## <u>አንድና ከአንድ በላይ ፍቺ ምሳሌያዊ አነጋገር ያላቸው</u>

- ተረትና ምሳሌ በመቆየቱ ተረት፣ በግብር ግን ምሳሌ ይባላል። እርስ በእርሳቸው የሚተረጐሙ ምሳሌዎች

1. ሁለት ባላ ትክል አንዱ ቢነቀል ባንዱ ተንጠልጠል
   ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም
   አንቺ ምንቸገረሽ ሁለት አባት አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባን
   ትምያለሽ

2. ሰሃምሣ ጋን አንድ አሎሎ
   ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም
   ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ
   የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
   የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ድረስ ነው

3. ሰልጅ ጥርስህን ሰዝንብ ቁስልህን አታሳይ
   ሰልጅ ከሣቁለት ሰውሻ ከሮጡለት

4. ሰመከራ ያለው መነኩሴ ዳዊቱን ሸጦ አህያ ይገዛል
   ሰመከራ የጣፊው ቢነግድ አይተርፈው

5. ሰሰው ብሎ ሲያማ ሰእኔ ብለህ ሰማ
   ሰመሰክርልህ ዋልክ ቢለው ሰታዘብህ ዋልኩ አለው

6. ሰእሳት ውኃ ሰፀጉር ቡሃ
   ሰአበጥ ፍላት ሰዕንጨት እሳት

7. ሰቀባሪው አረዱት
   ምጥ ሰእናትዋ አስተማረች
   ሰአንበሳ አይመትሩ ሰብልህ አይነግሩ

8. ሰተማሪ ቆሎ ሰወታደር በቅሎ
   ሰተራብ ቂጣ ሰተጠማ ዋንጫ

9. ሰተሾመ ይመሰክሩለታል ሰተሻረ ይመሰክሩበታል
   እርሱ ሲሞት ቀባሪው ሃምሣ ልጁ ሲሞት መቶ ሃምሣ

10. ሰኃጣን የወረደ ሰጻድቃን ይተርፋል
    እርጥብ ከደረቅ ይነዳል

11. ሰውሻ ገለባ ሰበራ ወለባ
    ካለበት ዶሮ በአጓት

12. ሲበሏት ያሰቧትን አሞራ ሰሚን ይሏታል ዥግራ
    አሞራን ሲበሉ ስሙን ዥግራ ይሉ
    አያጅበ ሳታመካኝ ብላኝ

13. ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም
ላለፈ አይጸጸቱም ለሚመጣው አይበለጡም
ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ ማቀፍ
የሞተ አይከለስ የፈለሰ አይታፈስ

14. ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ እህል የሚደርስ በፍልሰታ

15. ልብ ሲፈቅድ መግደርደር ራስን መግደል
ተግደርዳሪ ጾም አዳሪ

16. ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል
ክስር ያለው ቢነግድ አያተርፍም

17. ሎሌ ሲከበር ጌታውን ይከሳል
ሙክት ሲለባ ሾተል ይልሳል

18. መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ
ከእንጀራው የለሽ ከወጡ የለሽ ከጠላው የለሽ እንዲያው በላይነሽ
በጦሩ ቅብጥ በጠላው ቁጭ

19. መሬት ሲያረጅ መጅ ያበቅላል
አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል

20. መርፌ የምትሾልክበትን እንጂ የሚከተላትን ክር አታይም
አሚሉሽን በለማሽ ገበያም ባልወጣሽ

21. መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳትለፋ የሰው ትጠቅማለች
የራስ ጉድ ጨለማ ነው
የላጭን ልጅ ቅማል በላው
የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው

22. መታፈር በከንፈር
ዝምታ ወርቅ ነው
ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም

23. መች መጣሽ ሙሽራ መች ቆረጠምሽ ሽንብራ
ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

24. መናገር ብር ነው ዝምታ ወርቅ ነው
ዝም አይነቅዝም

25. መንፈራገጥ ለመላላጥ
ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሠበሩ



26. መጥፎ ሣር ይለመልማል እንጂ አይጠፋም
የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል

27. ሙሽራ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
አርሻ ቢሉ ሞፈር ቆረጣ
ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ

28. ሙክት ሲለባ ሾተል ይልሳል
አይጥ ሞትዋን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ ሔዳ ታሽታለች የድመት አፍንጫ

29. ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር
ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት

30. ማን ያውቃል አገር ምን ይጠብቃል ማገር
የምትከነን ነፍስ ጉረቤት ያውቃታል

31. ምላጭ ምላጭን አይቆርጠውም
ብልጥ ለብልጥ ዓይን ብልጥጥ

32. ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ
ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ

33. ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል
እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል

34. ሞኝ ቢመክሩት ከልማዱ አህያ ቢያጥቡት ካመዱ
የለመደ ልማድ ያስርቃል ከማዕድ

35. ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው
ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው
በቅሎ ለኮዋን በጠለች ለራሷ አላጠረች
እጅግም ስለት ይቀዳል አፎት
ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር
ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን

36. ሥራ ከመፍታት ልጄን ላፉታት
ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
ሥራ ያጣ ሚስት ያወጣ
ሥራ ያጣ አፍሶ ይለቅማል
ሥራ ያጣ ጭስ ይሞቃል
ሥራ ያጣ ገንፎ ያላምጣል
ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይገባል

37. ረዥም ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩበት
ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው

38. ራስ ሳይጠና ጉተና
ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

39. ራስዋን ሹሩባ ልትሰራ ሔዳ ፀጉሯን ተላጭታ መጣች
በገዛ እራሱ እባብ ጠመጠመ
ተኩላ እንደ አንበሳ እጮሃለሁ ብላ ተተረተረች
አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
እተርፍ ባይ አጉዳይ
ዓሣ ጉርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የለው ፈላጊ የራሱን ያጣል
የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
ጅብ ከሚበላኝ ጅብ በልቼ ልቀደስ

40. ራት የለህ ቢሉት ከወጡ አውጡልኝ አለ
ቀለብ የሌለው ውሻ ጣዲቅ አምጡልኝ አለ

41. ራት የሌለው ቄስ እንደልቡ አይቀድስ
ከሆዱ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም

42. ርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ
እውነትና ንጋት እያደር ይታያል

43. ሰው በካሕን በላተኛው ማይም
በልጅ አመካኝቶ ይበሏል አንጉቶ
በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

44. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
የቸኮለች አፍላ ለቀመች
የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
ፈጥኖ መስጠት ኋላ ለመጸጸት

45. ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት
ሳይጠሩት ይመጣል ሳይዘሩት ይበቅላል

46. ሴት በዛ ጉመን ጠነዛ
ወንሻ ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል

47. ሹሩባ ልትሰራ ሔዳ ተላጭታ መጣች
ሲያጌጡ ይመላለጡ

48. ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሔዳል
የውኃ ጠብታ እያደር ድንጋይ ይበሳል

49. በሞኝ ከምር ዝንጀሮ ልጇን ትድር
በሞኝ ክንድ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበታል

50. በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ
ያልጠረጠረ ተመነጠረ



51. በሬ ካራጁ ይውላል
ይገርማል አህያና ጅብ አብሮ ይከርማል

52. በርበሬ በገዛ እጅ ገዝቶ ይፋጃል
ለፍቅር ብተኛት ለጸብ አረገዘች
ባጉረስኩ እጄን ተነከስኩ
እህል ሳበደረ ዐፈር ወርቅ ሳበደረ ጠጠር
አጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ

53. በቅሎ አጐቴ አጐቴ ይላል ፈረስ ግን ግድ የለውም
ግዛኝ ግዛኝ ብለው ሲሸጠኝ አለበ

54. በቡሃ ላይ ቆረቆር
እምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

55. በወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል
ለሒያጅ የለውም ወዳጅ

56. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
በጣይ ቅቤ አያበሩበት
አያ ጅቦ እንኳን ድጓ በልተህ ድሮውን ጯሂ ነህ
እንኳን ዘንበብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

57. በግ ባልበላሽ ትበይኝ
አህያ ወደ ጅብ ለቅሶ ሔደች
አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሽታለች
እሳት ቢተኛ ገለባን ሰደድ ጉበኘው
እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጉበኘው
ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ

58. ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ
ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይመቱ

59. ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም
በሽታውን የደበቀ መድኀኒት አይገኝለትም

60. ባሰጌ ቀቅ በራሱ ያወራል
አላዋቂ ተራች የራሱን አመልካች

61. ባልንጀራ ቢያጠቃው ወደሚስቱ ሮጠ
አህያውን ፈርቶ ዳውላውን
አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ
ውሻው ምን አገባው እርሻ
ፈረስ ቢያነከስ አህያ ተኩስ

62. ባንድ ወናፍ ሁለት አፍ
በአንድ ራስ ሁለት ምላስ

63. ብልጥ ለብልጥ ይተያያሉ ውስጥ ለውስጥ
አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ

64. ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ
የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አያርፍም
የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ
ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ አይድንም

65. ተናካሽ ውሻ የዝንብ መቋደሻ
ፊት የተናገረውን ሰው ይጠላው ፊት የደረሰውን ወፍ ይበላው

66. ተናዳጅ እንጂ አናዳጅ አይሞትም
የተከፋ ተደፋ

67. ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ
ሆድን በጐመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይሰግማል
አሰባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ
የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ በራሴ
ድንጋይ ቢያጐኑት ተመልሶ ባናት

68. ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም
ተመክሮ ልብ ተሸምቶ ድልብ

69. ነብር ባየሰበት ድመት ይኮርታል
ንብ ሢነግሥ ዝንብ ይነግሥ

70. አህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሰበርም
የዘመድ ጥል የሥጋ ትል

71. አህያ በሞተች ባመቱ ኩርኩር
አምና የሞተውን ጥጃ ሰደዱ

72. አሰባሰቤቱ አይነድም እሳቱ
ባለቤቱ ካልጮኸ ጐረቤት አይረዳም

73. አሥር ያባረረ አንድም አይዝ
ሁለት የተመኘ አንዱንም አላገኘ

74. ዐረምን መንቀል ሥር ሳይሰድ ነው
ልጅን መቅጣት በጡት
ሳይቃጠል በቅጠል
ይህች ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቆረጠምም



75. ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል
በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው

76. አብ ሲነካ ወልድ ይነካ
አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል

77. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
ጮሌ ሲያረጅ መጋኛ ይሆናል

78. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይጸጸቱ
አንድ ቀን ስትሰርቅ ካይዋት ብትቆርብም አያምኗት
ያንድ ቀን መዘዝ ያለ አንድ ዓመት አይመዘዝ

79. አንድ ግንድ ለሺህ አይከብድ
ሃምሣ ሎሚ ለሃምሣ ሰው ጌጡ ነው ለአንድ ሰው ግን ሸክሙ ነው

80. ዐወቅሽ ዐወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች
ያመኑት ፈረስ ይጥላል በደንደስ
ይበጃል ያሉት መድኀኒት ዓይን አጠፋ

81. አዞ አንድም ተናዞ አንድም ስንቅ ይዞ
ወዴት ትሔዳለህ ወደበለሳ ለሴን የሰህምላ

82. አያገባው ገብቶ አያወዛው ተቀብቶ
ሳይገድሉ ጐፈሬ ሳያጣሩ ወሬ
አንበሳ ሳይገድሉ ቆዳውን ያስማማሉ

83. አይጠቅም ጠላ ባልና ሚስት አጣላ
የማያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ያሰጣል

84. አገባሻለሁ ያለሽ ላያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
ከእጅ አይሻል ዶማ
የማያድን ጋሻ ጐን ይሰብራል
የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም

85. እህል ሲገኝ ወፍጮ ይደንዛል
ደሃና ገበያ ሳይገናኙ ይኖራሉ

86. እርስ በርሱ ሥጋን በኩበት ጠበሱ
እሾህን በሾህ

87. እርሻው ቢያምር ዳቦው ያምር
ቅርንጫፍ እንደዛፉ
የማሽላ ዘር ከነአገዳው ቸር

88. እጅና አፍ አይተጣጡም
ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
ዘር ከልጓም ይስባል

89. እግር የላት ክንፍ አማራት
እንጀራ የሰም እንጂ በወተት አምገህ ትበላ ነበር

90. ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ድንጋይ መንከስ
ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ
ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ

91. ከሞቱ በኋላ መድኀኒት ካረጁ በኋላ እቤት እቤት
ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም

92. ከሰቀሰ ወደ ጥላ
ከርሞ ጥጃ

93. ከቆረሰ የጐረሰ
ካጨደ የሰበሰበ

94. ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ
ከዳቦ የተገኘ ወጥ አብረህ ግመጥ

95. ከእሾህ ወጥቶ ወደ ጋሬጣ
ከጅብ ጉሬ ወጥቶ ወደ ጅብ ዋሻ

96. ከከፉ ባለዕዳ የጉመን ዘር ተቀበል
ከነገሩ ጦም እደሩ

97. ካላዩ አይነድ ካልሰሙ አይቆጭ
ያላዩት አገር አይናፍቅም

98. ወጥ ቤቶች ሲበዙ ወጥ ያበላሹ
ሴት በዛ ጉመን ጠነዛ

99. ዋርካ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል
ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ

100. ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል
ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጉረቤት

101. ዓይን-ካላዩበት ግንባር ነው
ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ነው
አህያ ካልተጫኑ አሳማ ነው

102. ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
ዓይን መሪ ልብ መካሪ

103. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
ግም ለግም አብረህ አዝግም



104. ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም
ዝም አይነቅዝም
ዝምታ ያስከብራል

105. የሆድ ብልሃት የጋን መብራት
ካልታረደ አይታይ ስባቱ ካልተናገረ አይታወቅ ብልሃቱ

106. የሰመደ መደመደ
የለመደች ጠጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ

107. የላጭን ልጅ ቅማል በላው
የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው

108. የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል
ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

109. የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦ ያስታውቃል
የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ

110. የበው ወርቅ አያደምቅ
ከሰው ሰስላሳ የራስ ክርካሳ

111. የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ
ያብዬን እከክ ወደእምዬ ልከክ

112. የራሷ ጊዜ አለቀሰች የሰው ጊዜ ሣቀች
በበው ቁስል ዕንጨት ሰደድበት

113. የቸገረው እርጉዝ ያገባል
የተቸገረ ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

114. የነገር ወጡ ማዳመጡ
ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ
የቡና ሰባቱ መፋጀቱ

115. የፉከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
የጋራ ወንጋራ

116. ያላበበ ተመነበደ
ያላወቀ አለቀ
ያልጠረጠረ ተመነጠረ

117. ያልተገላበጠ ያራል
ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል

118. ያይጥ እንግዳ ከስልቻ ውስጥ ጉዝጉዙልኝ አለች
ጅብ የማያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ

119. ያገሩን ለርዶ ባገሩ በሬ
ያስባለቤቱ አይነድም እሳቱ

120. ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽንብራ
እኔም ሌባ አንተም ሌባ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ

121. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም
ክሰር ያለው ቢነግድ አያተርፈው

122. ጀርባ ሰባለቤቱ ባዳ ነው
የሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

123. ጅብ እንዳባቱ ይዘረጥጥ አህያ እንደእባቱ ይፈረጥጥ
ዘር ከልጓም ይስባል
የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

124. ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ
ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ

125. ጌታውን የተማመነ ውሻ ለንጋ ሲታረድ ወንዝ ይወርዳል
ጠባቂ ያሳት በግ ሳትዋ እደጅ ያድራል

126. ጦጣ ባለቤቱን ያሰወጣ
ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ

127. ጥርስና ከንፈር ተደጋግፎ ያምር
ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

128. ጥርኝ ቆሎ ይዘህ ከአሻሮ ተጠጋ
ሁለት ነዶ ይዞ ወደ ክምር ጠጋ
ጅብን ሲወጉ ከአህያ ይጠጉ

129. ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል
ዋርካ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል
ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆነ



## የቃላት መፍቻ

- ሁዳድ .......................... ለፊ የእርሻ መሬት
- ለከ .......................... የበቅሎ እና የፈረስ የፊት ገጽታ ላይ
- ላዋት .......................... በቤት ውስጥ የምትመለክ መንፈስ
- ለዳን .......................... ክቁና የሚበልጥ የእህል መስፈሪያ
- ልቅ .......................... ልቃቂት
- ልበሳንባ .......................... በደረቱ አካባቢ ቀይ የሆነ
- ልባልባ/ማ/ .......................... በበቅሎ ወይም በፈረስ የፊት ገጽታ ላይ የሚደረግ ለመሳቢያ የሚያገለግል
- ልግም በገላ .......................... ጥሩ ጌጥ ያለው ልብስ
- መልክኛ .......................... ባላባት የመሬት ክበርቴ
- መቀናጆ .......................... በወንፈል የመጣ በሬ
- መቋደሻ .......................... ቁርስ
- መበለት .......................... ባል የሌላት መነኩሲት
- መባ .......................... ለቤተክርስቲያን የሚለጥ ስጦታ
- መናጆ .......................... ተከታይ
- መናፍቅ .......................... ተቃዋሚ፣ ተጠራጣሪ /ለኃይማኖት/
- መን .......................... የሸማ መሥሪያ ዕቃ
- መንኋላ .......................... የማይረባ፣ ንፍጣም
- መዘለፍያ .......................... ጥልቀ እነስተኛ መጥረቢያ
- መዳሮ .......................... ድር ማድሪያ
- መጋዞ .......................... እራሽና እሳራሽ የሚያደርጉት ስምምነት
- መግሳሲት .......................... የማበሮ መክደኛ
- መጭ .......................... ኑግ የሚመስል ዐረም
- ሙር .......................... በዕውቀት ብዛት እንደዕብድ የተቆጠረ
- ሙተራ .......................... በጉጃም ያለ ተራራ ስም
- ሙሴ .......................... የማኅበር አለቃ
- ማህሌት .......................... በክበሮና በጽናጽል እየታጀበ የሚቀርብ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት
- ማርያም ውኃ .......................... በጉንደር ያለ ቀበሌ
- ማቅ .......................... ክበግ ፀጉር የሚሠራ ብርድ ልብስ
- ማዘንት .......................... ከእሳት የሚወጣ ድስት ለማስቀመጫ ምድጃ አካባቢ ከድንጋይና ከጭቃ የሚሠራ
- ሜሮን .......................... ቅዱስ ቅባት ቅባ ቅዱስ
- ምርቅ .......................... እንደ ገብስና ሥንዴ ባሉ እህሎች ላይ ያለ ሽካራ ቀጫጭን እሾህ
- ምስለኔ .......................... በመሬት ከበርቴው ረዳት የነበረ ሹም
- ምንደኛ .......................... በሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሠራ እረኛ ደሞዝተኛ
- ምዝግዝግ .......................... የተወረወረ የተምዘገዘገ ዱላ
- ረሻት .......................... ከዘር ለልጅ ያለፈ ገንዘብ ወይም ቅርስ
- ረዓይት .......................... ጠንካራና ረጃጅም ሰዎች

- ሬጋ .............................. ባሰአጅ ቀጥቃጭ ሸክላ ሠሪ
- ርቦ .............................. እሩብ፣ አንድ አራተኛ፣ ትንሽ መስፈሪያ
- ሮቃ .............................. የብርብራ ዓይነት ዛፍ ፍሬውን ሲበሉት የሚከመጥጥ
- ሰለባ .............................. ምርኮ
- ሰርተት .............................. ከረፈፍ፣ ጐተት፣ ቀረፈፍ
- ሰናድር .............................. የጠመንጃ ስም
- ሰናፌል .............................. ተንፋነፍ ሰ·ሪ
- ስግዳዳ .............................. ስዋራ ድብቅ ስፍራ
- ሱፋጭ .............................. ስሰት ያሰው ድንጋይ
- ሲቀጣጥብዋት .............................. ሲያታልሏት፣ ሲያላግጡባት
- ሲወበሩ .............................. ሲቀናጣ፣ የማይፈቀድሰትን ሲያደርግ
- ሳታት .............................. የሌሊት ጸሎት
- ስሉስ .............................. ሦስት ምስክር
- ስማርድ .............................. የአውሬ ወጥመድ
- ስንቆ .............................. የጕመን ዓይነት
- ስብቆ .............................. የአጃ አጥሚት /ሙቅ/
- ሶማያ .............................. የጦር እጀታ
- ሶኩና .............................. በከብት እግር ጫፍ የሚበቅል ጥፍር
- ሾተል .............................. ቀጥ ያሰ ስሰት ያሰው ሰይፍ
- ሾጤ .............................. በአቋቋም በመልክ የተዋበ ያማረ ሰው
- ቀርቃሪ .............................. የጐደጐደ ቦታ በጣም ቆላነት ያሰው
- ቀርበበ .............................. ከቆዳ የተሠራ ሚዛን ቁና
- ቀብቅቦ .............................. የእርሻ መሬቱን አሰስልሶ
- ቀነቀነ .............................. በጥሩ ዜማ ዘፈነ
- ቀንጠፋ .............................. የሾለ እሾህ ያሰው ቁጥቋጦ ዕንጨት
- ቀየዷት .............................. የበቅሎ ፊት እግርና የኋላ እግር ወይም ፊት እግርና አንገት ማሰር
- ቀጠነኝ .............................. ፍርድ ተዛባብኝ
- ቀጠና .............................. ረኃብ ችግር
- ቁልቢጥ .............................. ትንሽ ቁና
- ቁረንጮ .............................. በሰበሰ ብዛት የተበጣጠሰ የቆዳ ብጫቂ
- ቀረፍራፌ .............................. የተሰነጣጠቀ
- ቁግ .............................. ከጅማትና ከቃጫ የሚሠራ የጅራፍ ጫፍ
- ቃጢ .............................. ትንሽ ቁና
- ቅሃ .............................. በጕንደር ያሰ ወንዝ ስም
- ቅንብቻ .............................. ከቆዳ የተሰፋ ከሮጃ
- ቆረን .............................. አዝመራ የታጨደበት ማሳ
- ቆርቶ .............................. ሰውነት በጥቶ ስንጥቦ
- ቋያ .............................. የበረሃ ሣር ሳይታጨድ ቆይቶ የደረቀ
- በሰጠብ .............................. ትንሽ መስፈሪያ /የቅቤ ቅል መክደኛ/



- በመርገድ .............................. በማህሌት
- በቀልት .............................. የተምር፣ የስሌን ዛፍ
- ቡሃ .............................. እንደ ቆረቆር ያሰ በሽታ
- ቡላድ .............................. ሲፋጭ እሳት የሚወጣው ብርጭቆ መሳይ ድንጋይ
- ቡሌ .............................. ዳለቻ መልክ ያሰው
- ቢስ .............................. ንፉግ፣ ገብጋባ
- ቢዛቁን .............................. ድቁና ቢቀበል፣ ቢሰፋ፣ ቢደክም
- ቢያረምም .............................. ዝም ቢል ድምፅ ባያሰማ
- ባጥ .............................. የጣሪያ መደገፊያ
- ብርእ .............................. የሥንዴ ወይም የገብስ አገዳ
- ብርብራ .............................. የሚያስክር የዛፍ ዓይነት
- ብየኛ .............................. በካሳ የሌላውን ገንዘብ የበላ
- ቦራ .............................. ቢጫነት ያሰው በሬ
- ቦቃ .............................. ግንባረ ነጭ በሬ
- ቦና .............................. ድርቅ
- ቦዝ .............................. ተላላ፣ ዝንጉ፣ ቸልተኛ
- ቧጓች .............................. ውድማ ሰውድማ እየዞረ የሚሰምን
- ተሟረ .............................. ሲያውቅ ዐበድ
- ተታታ .............................. ተወሳሰበ፣ ተጐነጐነ
- ተጋደደ .............................. ተሰማጠጠ
- ተጣማኝ .............................. ተቀጣሪ የሰው መሬት አራሽ

- ታርጣጣ .............................. ሰነፍ፣ ከተቀመጠችበት የማትነሳ፣ ውዝፍ ሴት
- ትርሽማ .............................. ሾጣጣ ድንኳን
- ቶፋ .............................. ወኪል፣ ገባሪ
- ነቁ /ነቅእ/ .............................. የውኃ ጉድጓድ /ምንጭ/
- ነዳይ .............................. ድሃ፣ ለማኝ
- ነጠር .............................. ነፍስወከፍ
- ንዳማ .............................. እልህ፣ ቁጭት
- አሰሌ .............................. አውደልዳይ፣ ዘዋሪ
- አላል .............................. የተጫነውን ጭነት ሰማስተካከል ተጨማሪ ትንሽ ጭነት
- እማጭ .............................. ሚስት ሰሌሰው ሚስት የሚያጋባ
- አሜከላ .............................. የእሾህ ዓይነት
- አምበራስ .............................. የአምባ ሹም፣ የአካባቢው ሕዝብ ተጠሪ፣ ተወካይ
- አምዛ .............................. ወፍራም የጤፍ እንጀራ
- አራድማ .............................. በመንዝ ውስጥ ያሰ አገር
- አስድ .............................. የአንበሳ ዘር፣ የኮከብ ስም በእሳት የሚመሰል
- አሳጅ .............................. የጕን ሥጋ

- አሸን ........................... ክረምት አግቢ
- አሽክት ........................... ሽካራ፣ ቁርንድድ፣ በወረቀት ላይ ተጽፎ በቆዳ ተሰፍቶ አንገት ላይ የሚታሰር
- አቃቢት ........................... በቤተክርስቲያን የምታገለግል መነኩሲት
- አቃቤ ........................... ዘበኛ /ጠባቂ/
- አቢላማ ........................... አረኛ፣ ላም ጠባቂ
- አባሎ ........................... ለጠላና ለወተት ዕቃ ማጠኛ የሚሆን የዛፍ ዓይነት
- አብርጣም ........................... ሹሩባ
- አብያ ........................... ልግመኛ ለነፍ
- አቦሬ ........................... ክቅል የተሠራ አፌ ሰፊ የሆነ ትልቅ የጠላ መጠጫ
- አትቀታተር ........................... አትሯከክር
- አንቃ ........................... የቆላ ዕንጨት፣ ሙጫው እንደ ዕጣን የሚሸት የዛፍ ዓይነት
- አንጋዳ ........................... ጠመዝማዛ፣ አዘቅት
- አንጣሪያ ........................... መሬት ለመሬት እያደገ የሚራባ ቅጠል
- አጉራ ........................... የበረት መዝጊያ
- አግሬ ........................... ትልቅ ጋሻ
- አጐዶ ........................... የከሰል ጉድጓድ
- አጣሪ ........................... ቸርቻሪ ነጋዴ
- አጽቅ ........................... አንጓ፣ የዛፍ መብቀያ
- አፈላማ ........................... ከብት አዝመራ ሲበላ የሚከፈል ዕዳ
- አፍላላ ........................... ክሽክላ የሚሠራ ድስት
- አፎት ........................... ሰገባ፣ የለይፍ የጐራዴ መክተቻ ቤት
- አመ ........................... አማሆይ
- አርክፍካፎ ........................... ካፊያ
- አርኮት ........................... ከቆዳ የተሠራ የውኃ መያዣ
- አርያ ........................... የአሳማ ዓይነት የዱር አውሬ
- አቡይ ........................... ትዕቢተኛ፣ አብሪተኛ
- አናርያ ........................... በወላይታና በሲዳሞ የሚኖር ነገድ
- እንበለ /ግዕዝ/ ........................... ያለ
- እክት ........................... ቅራቅንቦ ዕቃ
- እይር ........................... ድብልቅ፣ ቅልቅል
- ከርከሬሻ ........................... ብጥብጥ፣ ጠብ፣ ፍጅት
- ከፈር ........................... እንቅብ
- ኩርዲዳ ........................... ብርቱ አራዊት ገሪ
- ኩተት ........................... ቁንጮ፣ ሕፃንነት
- ካይላ ........................... በጐንደር የሚገኝ ነገድ
- ካድሬ ........................... ሹም፣ አስተዳዳሪ
- ወለባ ........................... የሚሰካ የሴት የፀጉር ጌጥ
- ወለፌንድ ........................... ወልጋዳ፣ ጠማማ



- ወረት ........................... ገንዘብ
- ወሶ ........................... ጐሽ፣ ጥሩ፣ አሰየው
- ወቁራ ........................... በልዩ ልዩ ዓይነት የተሠራ ቢለዋ
- ወበራ ........................... ቅንጡ፣ ቀበጠ
- ወታቦ ........................... ከአበትና ከአመድ የተሠራ የጐድጓዳ ዕቃ
- ወንጋራ ........................... ወልጋዳ
- ወንጠፍት ........................... የቅቤ፣ የዘይት ማጥለያ ወንፊት
- ወንጭት ........................... በመርሃቤቴና በደራ መሃከል ያለ ጅረት
- ወዘት ........................... እሳት አጠገብ መቀመጥ
- ወይኖ ........................... የወይንማ በሬ ስም
- ወዳጅ ........................... ዙሪያው የታጠረ የአትክልት ስፍራ
- ወጋሪ ........................... ዓሣን ወርውሮ በድንጋይ ላይ የሚከሰክስ
- ወጭት ........................... ጣባ
- ዋቢ ........................... ዋስ፣ ሰጪ፣ አቀባይ
- ዋግ ........................... የሰብል በሽታ
- ውኸርምኸርም ........................... ረኸርም፣ ጐታታ
- ውኸርም ........................... መቃ ለጋያ መጠጫ የሚሆን
- ዘለላ ........................... ቁጥቋጦ ምልመላ
- ዘማ ........................... አመንዝራ
- ዘቆነ ........................... ዲያቆን ሆነ
- ዘባን ........................... ጀርባ፣ ኋላ
- ዘባጣ ........................... ዝቅተኛ ቦታ
- ዘፈር ........................... የልብሰ ዘርፍ
- ዛብ ........................... ለበቅሎ ፈረስ እንደልጓም የሚገታ
- ዝማሜ ........................... በመቋሚያ እየተወዛወዙ የሚዘምር መንፈሳዊ መዝሙር
- ዝባድ ........................... ከጥርኝ የሚገኝ የሽቶ ቅባት
- ዘላ ........................... ሰነፍ
- ያራኝ ........................... ዕቃ ጫኝ
- ይብራ ........................... አግረ ቀይ መልከ ብዙ የውኃ ዶሮ
- ይቶት ........................... መነኩሲት
- ይኮርታል ........................... ያኮርፋል፣ ይነፋነፋል
- ይዋጁ ........................... ይገዙ
- ይጋጃል ........................... ከጥምት ውጪ ይሆናል፣ ይበላሻል
- ደለማ ........................... ጨለማ፣ ሰዋራ
- ዶልሶ ........................... ሀብት፣ ብልጽግና
- ደረባ ........................... የጐተራ ሽፍን
- ደረጣ ........................... ሁከት
- ደራል ........................... የዕንጨት ዓይነት
- ደባይ ........................... ሰፊ ነጋሪት
- ደንቃራ ........................... ደካማ፣ አላዋቂ
- ደንገጡር ........................... የንግሥት አጃቢ
- ዳምትራ ........................... የሚናደፍ ጥቁር መርዘኛ ሽረሪት

- ዳንዴ .............................. ዘራፊ፣ ቀማኛ
- ዳኮ .............................. ቆዳ፣ ሽርጥ፣ ያለቀ ልብስ
- ድርጕ .............................. ጉርሻ
- ድበላ .............................. ከምስር፣ ከባቄላ፣ ከአተር፣ ከሥንዴና ከገብስ ቅልቅል የሚጋገር እንጀራ
- ድቡሽት .............................. የአሸዋ ክምር
- ድጉስ .............................. ማጎደር
- ዶስኛ .............................. ኃይለኛ፣ ጉልበታም
- ዶባ .............................. ቀንዳም በሬ
- ዶጮ .............................. ከገንቦ የሚያንስ የሸክላ ዕቃ፣ የጠላ የጠጅ የውኃ ማኖሪያ
- ጀላፋ .............................. ሰነፍ
- ጀንፎ .............................. በሽመል ጫፍ ላይ የሚሰካ ጥምጥም ብረት
- ጀጀባ .............................. በወንዝ ዳር የሚበቅል ፍሬው የሚበላ ዛፍ
- ገለንፊት .............................. በሆነው ባልሆነው የምትሥቅ ሴት
- ጉልማ .............................. ለእሽከር፣ ለዘመድ፣ ለወዳጅ ተከፍሎ የተሰጠ ማሳ
- ጉጣ .............................. ያለቀ የማረሻ መሣሪያ
- ጊጉይ .............................. ወንጀለኛ አመጸኛ
- ጋሬዳ .............................. የመዋጮ ገንዘብ ክፍፍል
- ጋት .............................. መዳፍ፣ የውስጥ እጅ
- ጋይ .............................. ዐፈሩን በማቃጠል የእርሻ ማዳበሪያ
- ጋፍ .............................. ጅል፣ ሞኝ፣ መጥፎ
- ጌኛ .............................. መጋዣ፣ ፈረስ
- ግልንቢጥ .............................. የተገላቢጦሽ
- ግጫ .............................. የሣር ዓይነት
- ጕመድ .............................. አጭር
- ጕታ .............................. የአህል ማስቀመጫ ጕተራ
- ጕዳ .............................. ቀንድ የሌለው በሬ፣ ላም የተጕዳ ኮሳሳ ከብት
- ጕፍላ .............................. ጌጥ
- ጠራቂ .............................. ቢያጅ
- ጠገራ .............................. ትንሽ መጥረቢያ
- ጣቁሣ .............................. ሰውን በነገር መነካካት
- ጥረሽ .............................. ሳይቦካ የተጋገረ ዳቦ
- ጥቅንጥቅ .............................. ውስብስብ
- ጥንቅል .............................. ቁንጣሪ፣ በጣም ጥቂት
- ጨንቋራ .............................. ሽውራራ
- ጨንገር .............................. የዛር ስም
- ጭራንፎ .............................. የጭራሮ ጫፍ
- ጭሬ .............................. ቅጠለ ጠባብ ጦር



- ጭቃ ሹም .............................. ቀደም ሲል የነበረ የሹም ዓይነት የቀበሌ ሹም
- ጽላሎት .............................. ጥላ
- ፈርዛዛ .............................. ደስተኛ
- ፈገጡት .............................. ተውት፣ አሽቀነጠሩት
- ፈጠም .............................. ማላ፣ የነገርመግቻ
- ፈፋ .............................. የውኃ መውረጃ
- ፉቅራ .............................. ቃልቻ
- ፌራ .............................. ተላላፊ በሽታ፣ ተስቦ፣ ወረርሽኝ
- ፌቆ .............................. የሚዳቋ ዓይነት /የዱር ፍየል/
- ፍንጅ .............................. ከብረት የተሠራ የእጅ ማሰሪያ

## ሀ/ የመልመጃ 1 /ሀ፣ ለ፣ ሐ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሀ | 2.መ | 3.ለ | 4.ለ | 5.ሀ | 6.ለ | 7.መ | 8.ለ | 9.ሐ | 10.ሀ |
| 11.ለ | 12.ሐ | 13.ለ | 14.ሀ | 15.ሐ | 16.ለ | 17.መ | 18.ሐ | 19.ለ | 20.ሐ |
| 21.ለ | 22.ሐ | 23.ሀ | 24.ለ | 25.ሐ | 26.መ | 27.ሐ | 28.መ | 29.ሀ | 30.ለ |
| 31.ሀ | 32.ለ | 33.መ | 34.ሐ | 35.ለ | 36.ሀ | 37.ሐ | 38.ሀ | 39.ሐ | 40.መ |
| 41.ለ | 42.ሐ | 43.ሀ | 44.ለ | 45.መ | 46.ለ | 47.ሀ | | | |

## ለ/ የመልመጃ 1 /ሀ፣ ለ፣ ሐ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ለ | 2.ሀ | 3.ለ | 4.ሐ | 5.ለ | 6.ሀ | 7.ሐ | 8.መ | 9.ሀ | 10.ለ |

## ሐ/ የመልመጃ 1 /ሀ፣ ለ፣ ሐ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ረ | 2.ለ | 3.በ | 4.ሽ | 5.ሀ | 6.መ | 7.ቀ | 8.ለ | 9.ሠ | 10.ሐ |
| 11.ተ | 12.ቸ | 13.ነ | 14.ኀ | 15.እ | 16.ፐ | 17.ከ | 18.ዠ | 19. | 20.ዘ |
| 21.ደ | 22.የ | 23.ገ | 24.ጀ | | | | | | |

## ሀ/ የመልመጃ 2 /መ፣ ሠ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሀ | 2.ለ | 3.ሐ | 4.ሐ | 5.ለ | 6.ሀ | 7.መ | 8.ሐ | 9.ለ | 10.ለ |
| 11.ሀ | 12.ሐ | 13.መ | 14.ለ | 15.ሐ | 16.መ | 17.ሐ | 18.ሀ | 19.ለ | 20.ሐ |
| 21.መ | 22.ሀ | 23.ሐ | 24.መ | 25.ሀ | 26.ሐ | 27.ሐ | 28.ሐ | 29.መ | 30.ለ |
| 31.ሐ | 32.መ | 33.ለ | 34.ሀ | 35.ሐ | 36.መ | 37.ሀ | 38.ለ | 39.ሐ | 40.ለ |
| 41.ሐ | 42.መ | 43.መ | 44.ሐ | 45.ሀ | 46.ሐ | 47.መ | 48.ሐ | 49.መ | 50.ሀ |

## ለ/ የመልመጃ 2 /መ፣ ሠ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሀ | 2.ሐ | 3.ሐ | 4.ለ | 5.ሀ | 6.ሀ | 7.ለ | 8.ሐ | 9.ለ | 10.ለ |

## ሐ/ የመልመጃ 2 /መ፣ ሠ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሰ | 2.ሠ | 3.በ | 4.ቀ | 5.ሀ | 6.ሽ | 7.ሐ | 8.ተ | 9.ለ | 10.ረ |
| 11.መ | 12.ነ | 13.ኀ | 14.ቸ | 15.ኘ | 16.ደ | 17.ጀ | 18.አ | 19.ዠ | 20.ገ |
| 21.ከ | 22.ዘ | 23.ወ | 24.የ | 25.ጠ | | | | | |

## ሀ/ የመልመጃ 3 /ረ፣ ሰ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሀ | 2.ለ | 3.ሐ | 4.መ | 5.ለ | 6.ሐ | 7.ሐ | 8.ሀ | 9.ሀ | 10.ለ |
| 11.ሐ | 12.መ | 13.ሀ | 14.ሀ | 15.ሐ | 16.ሐ | 17.መ | 18.ሀ | 19.ለ | 20.መ |
| 21.መ | 22.መ | 23.ሀ | 24.ለ | 25.ሐ | 26.ሐ | 27.ሐ | 28.ሐ | 29.ለ | 30.ሐ |
| 31.መ | 32.መ | 33.ሐ | 34.ሀ | 35.መ | 36.ሐ | 37.ሐ | 38.መ | 39.ሐ | 40.ሐ |
| 41.ለ | 42.ሐ | 43.ሀ | 44.ሐ | 45.መ | 46.ሐ | 47.ሀ | 48.ለ | 49.ሐ | 50.መ |



## ለ/ የመልመጃ 3 /ረ፣ ሰ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.መ | 2.ሐ | 3.ለ | 4.ሐ | 5.መ | 6.ሐ | 7.መ | 8.ሐ | 9.ለ | 10.ለ |

## ሐ/ የመልመጃ 3 /ረ፣ ሰ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.በ | 2.ተ | 3.ገ | 4.ሀ | 5.ዠ | 6.ለ | 7.ጠ | 8.ጀ | 9.አ | 10.መ |
| 11.ደ | 12.ወ | 13.ሐ | 14.ዘ | 15.የ | 16.ቀ | 17.ረ | 18.ከ | | |

## ሀ/ የመልመጃ 4 /ሸ፣ ቀ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሀ | 2.ሐ | 3.ሀ | 4.ለ | 5.ሐ | 6.መ | 7.ለ | 8.ሐ | 9.መ | 10.ሀ |
| 11.ሐ | 12.ለ | 13.ሐ | 14.ሀ | 15.ሐ | 16.ለ | 17.ሐ | 18.ሐ | 19.ሐ | 20.ሀ |
| 21.መ | 22.ለ | 23.መ | 24.ለ | 25.ሐ | 26.ሀ | 27.ሀ | 28.ሐ | 29.ሀ | 30.ሐ |
| 31.መ | 32.ሀ | 33.መ | 34.ሐ | 35.መ | 36.መ | 37.መ | 38.ሐ | 39.ሐ | 40.ለ |

## ለ/ የመልመጃ 4 /ሸ፣ ቀ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሐ | 2.ሀ | 3.ሐ | 4.መ | 5.ሐ | 6.ሐ | 7.መ | 8.መ | 9.ለ | 10.ሐ |

## ሐ/ የመልመጃ 4 /ሸ፣ ቀ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሠ | 2.መ | 3.ሀ | 4.ሽ | 5.ሐ | 6.ቀ | 7.ለ | 8.ሰ | 9. | 10.ረ |
| 11.ተ | 12.ነ | 13.ቸ | 14.ኘ | 15. | 16.ነ | 17.ዘ | 18.አ | 19.ኸ | 20.ወ |
| 21.ደ | 22.የ | 23.ዠ | 24.ጀ | 25.ገ | | | | | |

## ሀ/ የመልመጃ 5 /በ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.መ | 2.መ | 3.ለ | 4.መ | 5.ለ | 6.ሀ | 7.ሐ | 8.ሐ | 9.ሐ | 10.ለ |
| 11.ለ | 12.ሀ | 13.ለ | 14.ሀ | 15.ሀ | 16.ለ | 17.ሐ | 18.ሀ | 19.ሀ | 20.ሀ |
| 21.ለ | 22.ሀ | 23.ለ | 24.ለ | 25.ሀ | 26.ሀ | 27.ለ | 28.ሐ | 29.ሐ | 30.መ |
| 31.ሐ | 32.መ | 33.ለ | 34.ለ | 35.ሀ | 36.ሐ | 37.ለ | 38.ሐ | 39.መ | 40.ለ |

## ለ/ የመልመጃ 5 /በ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ሐ | 2.ሐ | 3.ሀ | 4.መ | 5.ሐ | 6.መ | 7.መ | 8.ሐ | 9.ሐ | 10.መ |
| 11.ሐ | 12.ለ | 13.ሐ | 14.ሐ | 15.መ | | | | | |

## ሐ/ የመልመጃ 5 /በ/ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.ረ | 2.ቀ | 3.ሽ | 4.ለ | 5. | 6.ሀ | 7.መ | 8.ለ | 9.ሠ | 10.ኘ |
| 11.ሰ | 12.ዠ | 13.ነ | 14.በ | 15.ቸ | 16.ተ | 17.ዐ | 18.ከ | 19.ኀ | |

### ሀ/ የመልመጃ 6 /ተ፣ ቸ፣ ኀ/ መልስ

1.ለ 2.ለ 3.መ 4.ሐ 5.መ 6.ሐ 7.ሐ 8.ለ 9.ለ 10.ሀ
11.ሀ 12.ሀ 13.ለ 14.ሐ 15.ለ 16.ለ 17.ለ 18.ሐ 19.መ 20.ሐ
21.ለ 22.ሐ 23.ሀ 24.ለ 25.ለ 26.ሀ 27.ሐ 28.ሐ 29.ሀ 30.ለ
31.ለ 32.ሐ 33.ሐ 34.ለ 35.ሀ 36.ሐ 37.ሀ 38.መ 39.ሀ 40.ሐ
41.መ 42.ሐ 43.ለ 44.ሐ 45.ሐ 46.ሐ 47.መ 48.መ 49.ለ 50.ሀ
51.ሐ 52.መ 53.መ 54.ለ 55.መ 56.ሀ 57.መ 58.ለ 59.መ 60.ሐ

### ለ/ የመልመጃ 6 /ተ፣ ቸ፣ ኀ/ መልስ

1.ሀ 2.መ 3.ለ 4.ሐ 5.ሐ 6.ሐ 7.ሀ 8.መ 9.ለ 10.ሐ

### ሐ/ የመልመጃ 6 /ተ፣ ቸ፣ ኀ/ መልስ

1.ሠ 2.ሐ 3.ሀ 4.ለ 5.ሸ 6.መ 7.ረ 8.ተ 9.ቀ 10.ሰ
11.ኀ 12.በ 13.ቸ 14.ነ 15.ኘ 16.አ 17.ከ 18.ኸ 19.ዠ 20.ወ
21.ዘ 22.ገ 23.ደ 24.የ 25.ጀ

### ሀ/ የመልመጃ 7 /ነ/ መልስ

1.ሐ 2.ሐ 3.ለ 4.ሀ 5.ሀ 6.ለ 7.መ 8.ለ 9.ሀ 10.ሐ
11.ሀ 12.ሐ 13.ሐ 14.ለ 15.መ 16.ለ 17.ሐ 18.ለ 19.ሀ 20.ሐ
21.ለ 22.መ 23.መ 24.ሐ 25.ሀ 26.መ 27.ሐ 28.ሐ 29.መ 30.ሐ

### ለ/ የመልመጃ 7 /ነ/ መልስ

1.ሐ 2.መ 3.ሐ 4.ሐ 5.መ 6.ሐ 7.ሀ 8.ለ 9.መ 10.ለ

### ሐ/ የመልመጃ 7 /ነ/ መልስ

1.መ 2.ሸ 3.ረ 4.በ 5.ሀ 6.ቀ 7.ሠ 8.ለ 9.ሰ 10.ሐ

### ሀ/ የመልመጃ 8 /አ/ መልስ

1.መ 2.ለ 3.መ 4.ለ 5.ሀ 6.ለ 7.ለ 8.ሀ 9.ለ 10.ሐ
11.ለ 12.ሐ 13.ሐ 14.ሀ 15.ሐ 16.ሐ 17.ሐ 18.ሀ 19.ሐ 20.ለ
21.ሀ 22.ሀ 23.ለ 24.ሀ 25.ሐ 26.ሀ 27.ለ 28.ሀ 29.ሐ 30.መ
31.መ 32.መ 33.ለ 34.መ 35.ለ 36.ሀ 37.መ 38.ሐ 39.ሀ 40.ሐ
41.መ 42.ሀ 43.ሐ 44.መ 45.ሐ 46.መ 47.መ 48.መ 49.ለ 50.ሐ



### ለ/ የመልመጃ 8 /አ/ መልስ

1.መ 2.ሐ 3.መ 4.ሐ 5.መ 6.መ 7.መ 8.ሐ 9.መ

### ሐ/ የመልመጃ 8 /አ/ መልስ

1.ረ 2.ሸ 3.ሀ 4.ሰ 5.ለ 6.ቀ 7.ሐ 8.ሰ 9.መ 10.ኘ
11.ነ 12.አ 13.ኀ 14.ቸ 15.በ 16.ተ 17.ዠ 18.ደ 19.የ 20.ዘ
21.ከ 22.ሠ 23.ኸ 24.ገ 25.ጀ

### ሀ/ የመልመጃ 9 /ከ/ መልስ

1.ሀ 2.ለ 3.ሀ 4.መ 5.ሐ 6.ሐ 7.ሀ 8.ለ 9.ሀ 10.ሐ
11.ሐ 12.ሀ 13.ሐ 14.ሐ 15.መ 16.መ 17.ሀ 18.ለ 19.ሐ 20.ሀ
21.ሀ 22.ለ 23.ሐ 24.ለ 25.ሐ 26.ለ 27.ለ 28.ሀ 29.መ 30.ሐ
31.መ 32.ለ 33.ሐ 34.ሀ 35.ለ 36.ሀ 37.ሐ 38.ሐ 39.መ 40.ሐ
41.ሀ 42.መ 43.መ 44.ሐ 45.መ 46.መ 47.ለ 48.መ 49.ሀ 50.ሐ

### ለ/ የመልመጃ 9 /ከ/ መልስ

1.መ 2.መ 3.ሐ 4.መ 5.መ 6.ሐ 7.ሐ 8.ሐ

### ሐ/ የመልመጃ 9 /ከ/ መልስ

1.ረ 2.ሸ 3.ሀ 4.ሐ 5.ሰ 6.መ 7.ሠ 8.ሰ 9.በ 10.ቀ
11.ተ 12.ኀ 13.ቸ 14.ነ 15.ኘ 16.አ 17.ከ 18.ኸ 19.ወ 20.ዘ
21.የ 22.ዠ 23.ደ 24.ገ 25.ጀ

### ሀ/ የመልመጃ 10 /ኸ/ መልስ

1.መ 2. 3.ሀ 4.ለ 5.ሐ 6.ሐ 7.ለ 8.ለ 9.ሀ 10.ለ
11.ሀ 12.ሀ 13.ሀ 14.ለ 15.ሐ 16.ሐ 17.ለ 18.ሀ 19.መ 20.ለ
21.ሐ 22.ሀ 23.ለ 24.ሀ 25.ሐ 26.ሀ 27.መ 28.ሐ 29.ሀ 30.ሐ
31.መ 32.ለ 33.ሀ 34.ሐ 35.ለ 36.መ 37.ሀ 38.ለ 39.ሐ 40.መ
41.ሀ 42.ሐ 43.ሐ 44.መ 45.ሐ 46.መ 47.ሐ 48.መ 49.መ 50.ሐ

### ለ/ የመልመጃ 10 /ኸ/ መልስ

1.ለ 2.ለ 3.ለ 4.ሐ 5.ለ 6.መ 7.ሀ 8.መ 9.ሐ 10.ሀ

### ሐ/ የመልመጃ 10 /ኸ/ መልስ

1.ሠ 2.ሐ 3.ሰ 4.ሀ 5. 6.መ 7.ሰ 8.ሸ 9.በ 10.ቀ
11.ቸ 12.ተ 13.ኀ 14.ነ 15.ኘ

## ሀ/ የመልመጃ 11 /ወ፣ ዐ/ መልስ

1.መ 2.ሀ 3.ለ 4.ለ 5.ሀ 6.ለ 7.ሀ 8.ሀ 9.ሀ 10.ሐ
11.ሀ 12.ሀ 13.ሐ 14.ለ 15.ሀ 16.ሐ 17.ሐ 18.ሀ 19.መ 20.ሀ
21.ለ 22.ሀ 23.ሐ 24.ሀ 25.ለ 26.መ 27.መ 28.ለ 29.ለ 30.መ
31.ለ 32.ሐ 33.ሀ 34.ሀ 35.መ 36.ለ 37.ሐ 38.ለ 39.ሐ 40.ለ
41.ሀ 42.መ 43.ሐ 44.ሀ 45.ለ 46.ሀ 47.ሐ 48.ሐ 49.ሀ 50.መ

## ለ/ የመልመጃ 11 /ወ፣ ዐ/ መልስ

1.ሐ 2.ለ 3.መ 4.ሀ 5.ለ 6.መ 7.መ 8.ሀ 9.ሀ 10.መ

## ሐ/ የመልመጃ 11 /ወ፣ ዐ/ መልስ

1.ረ 2.ሀ 3.ሠ 4.ሐ 5.ሸ 6.ለ 7.መ 8.ሰ 9.ቀ 10.ጎ
11.ኘ 12.እ 13.ነ 14.ተ 15.በ 16.ቸ 17.ኸ 18.ከ 19.ዠ 20.ዘ
21.ወ 22.ገ 23.ጀ 24.ደ 25.የ

## ሀ/ የመልመጃ 12 /ዘ፣ ጀ/ መልስ

1.ሐ 2.መ 3.መ 4.ለ 5.ሐ 6.መ 7.ሐ 8.መ 9.ሐ 10.ለ
11.መ 12.መ 13.ሀ 14.መ 15.መ 16.ሐ 17.ሐ 18.መ 19.ሐ 20.ሐ
21.ሀ 22.ለ 23.መ 24.ሐ 25.መ 26.ሀ 27.ሐ 28.መ 29.ሀ 30.መ
31.ሀ 32.ለ 33.ሐ 34.ለ 35.ሐ

## ለ/ የመልመጃ 12 /ዘ፣ ጀ/ መልስ

1.መ 2.ሀ 3.ሐ 4.ሐ 5.መ 6.መ 7.ለ 8.ሀ 9.ሐ 10.ሀ

## ሀ/ የመልመጃ 13 /የ/ መልስ

1.ሀ 2.ሐ 3.ለ 4.ሀ 5.ሀ 6.ሀ 7.ሐ 8.ሀ 9.ሀ 10.ሀ
11.ለ 12.ለ 13.ሀ 14.ሐ 15.ለ 16.ሐ 17.ሐ 18.ለ 19.ሐ 20.ሐ
21.ሀ 22.ለ 23.ለ 24.ሐ 25.መ 26.ሀ 27.ሀ 28.ሀ 29.ሐ 30.መ
31.ሀ 32.ለ 33.ለ 34.ለ 35.ሀ 36.ሐ 37.መ 38.ለ 39.ሐ 40.ለ
41.ሀ 42.ለ 43.ለ 44.ሐ 45.ሀ 46.ሐ 47.ሀ 48.ሀ 49.መ

## ለ/ የመልመጃ 13 /የ/ መልስ

1.ሐ 2.መ 3.ሐ 4.ሀ 5.ሐ 6.ሀ 7.መ 8.መ 9.መ 10.ሀ

## ሐ/ የመልመጃ 13 /የ/ መልስ

1.ተ 2.መ 3.ቀ 4.ነ 5.ለ 6.ቸ 7.ሸ 8.ከ 9.ሰ 10.እ
11.ኀ 12.ገ 13.ጀ 14.ኘ 15.የ 16.ደ 17.ኸ 18 .ዘ 19.ዠ 20.ወ



## ሀ/ የመልመጃ 14 /ደ/ መልስ

1.ሀ 2.ሀ 3.ለ 4.ሀ 5.መ 6.ሐ 7.ሐ 8.መ 9.ሀ 10.ለ
11.ሐ 12.ለ 13.ሀ 14.ሐ 15.ሀ 16.ሐ 17.ሐ 18.ሐ 19.ሐ 20.ሀ
21.ሐ 22.ለ 23.ሐ 24.ሀ 25.ሀ 26.ለ 27.መ 28.መ 29.ሀ 30.ለ
31.ሀ 32.ሐ 33.ሀ 34.ሐ 35.ሀ 36.ለ 37.ሐ 38.ሀ 39.ሐ 40.ሀ
41.ሐ 42.ሐ 43.ሐ 44.ሀ 45.ሐ 46.ሐ 47.ሀ 48.ለ 49.ሐ 50.ለ

## ለ/ የመልመጃ 14 /ደ/ መልስ

1.መ 2.መ 3.ለ 4.መ 5.መ 6.መ 7.ሀ 8.ሀ 9.ለ 10.ሀ

## ሐ/ የመልመጃ 14 /ደ/ መልስ

1.ሰ 2.መ 3.በ 4.ሀ 5.ሸ 6.ለ 7.ሐ 8.ረ 9.ቸ 10.ነ
11.ቀ 12.ሠ 13.ተ 14.ኘ 15. ከ 16.ኸ 17.እ 18.ጎ 19.ወ 20.ዘ

## ሀ/ የመልመጃ 15 /ገ/ መልስ

1.ሀ 2.ሀ 3.መ 4.ለ 5.ሐ 6.ሀ 7.ለ 8.መ 9.ለ 10.ሐ
11.ሐ 12.ሐ 13.ለ 14.ለ 15.ሐ 16.ለ 17.ለ 18.ሐ 19.ሀ 20.ሀ
21.ሐ 22.ሀ 23.ሐ 24.ለ 25.ሐ 26.መ 27.ሀ 28.ሐ 29.መ 30.ሀ
31.ለ 32.ለ 33.ለ 34.ሀ 35.ለ 36.ሐ 37.ለ 38.መ 39.ሐ 40.መ
41.ሀ 42.ለ 43.ሀ 44.ሐ 45.ሀ 46.ለ 47.ለ 48.ሀ 49.ሐ 50.መ

## ለ/ የመልመጃ 15 /ገ/ መልስ

1.ሐ 2.ሐ 3.ለ 4.ሀ 5.ሀ 6.ለ 7.ሀ 8.ሐ 9.ሐ 10.ሐ

## ሐ/ የመልመጃ 15 /ገ/ መልስ

1.ሸ 2.ሠ 3.ሰ 4.ሀ 5.ረ 6.ሐ 7.ለ 8.መ 9.በ 10.ቀ
11.ተ 12.ቸ 13.ነ 14.ጎ 15.ኘ

## ሀ/ የመልመጃ 16 /ጠ፣ ጨ፣ ጸ/ መልስ

1.ለ 2.ሀ 3.ሀ 4.ለ 5.ሐ 6.መ 7.ለ 8.መ 9.ሐ 10.ሐ
11.ሀ 12.ሐ 13.ለ 14.ለ 15.መ 16.መ 17.ለ 18.ሀ 19.መ 20.ሀ
21.ለ 22.ሐ 23.መ 24.ሀ 25.ለ 26.ሀ 27.ሐ 28.መ 29.መ 30.መ
31.መ 32.ሐ 33.ሐ 34.ለ 35.መ 36.ሐ 37.መ 38.መ 39.ሀ 40.ሐ

## ለ/ የመልመጃ 16 /ጠ፣ ጨ፣ ጸ/ መልስ

1.ሀ 2.ሐ 3.መ 4.መ 5.ሀ 6.ለ 7.ሐ 8.ሀ

### ሐ/ የመልመጃ 16 /ጠ፣ ጨ፣ ጰ/ መልስ

1.ሐ 2.በ 3.ሰ 4.ሠ 5.ሀ 6.ለ 7.ረ 8.መ 9.ሸ 10.ቀ
11.ተ 12.ቸ 13.ኀ 14.ኘ 15.ነ

### ሀ/ የመልመጃ 17 /ጸ፣ ፀ፣ ፈ/ መልስ

1.ሀ 2.መ 3.መ 4.ለ 5.ሀ 6.ሀ 7.ለ 8.ሐ 9.ለ 10.ሀ
11.ሐ 12.ሐ 13.ለ 14.ሀ 15.ለ 16.መ 17.ለ 18.ሐ 19.ለ 20.ሐ
21.ለ 22.ሐ 23.መ 24.ሐ 25.ለ 26.ሀ 27.ሐ 28.መ 29.ሐ 30.ለ
31.ሐ 32.መ 33.ለ 34.መ 35.ሐ 36.ሐ 37.ሐ 38.ሀ 39.ሀ 40.ለ
41.ሐ 42.ሀ 43.ሐ 44.ለ 45.ሀ 46.መ 47.ሐ 48.ለ 49.ሐ 50.ሐ

### ለ/ የመልመጃ 17 /ጸ፣ ፀ፣ ፈ/ መልስ

1.ለ 2.መ 3.መ 4.ሐ 5.መ 6.ሐ 7.ሀ 8.ሀ

### ሐ/ የመልመጃ 17 /ጸ፣ ፀ፣ ፈ/ መልስ

1.መ 2.ረ 3.ሀ 4.በ 5.ሐ 6.ለ 7.ረ 8.መ 9.ሸ 10.ቀ
11.ተ 12.ቸ 13.ኀ 14.ነ 15.ኘ